# ብዙ ዐየሁ

## የሕይወቴ ታሪክና ትዝታ

ታደሰ ገብረኪዳን

ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ

ሻማ ቡክስ
የመ.ሳ.ቁ. 8153
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በጽሑፍ ፈቃድ ወይም በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 የስነ ጽሑፍና ኪነጥበብ ሥራዎች ባለቤትነትን በተመለከተ ከአንቀጽ 1647 እስከ አንቀጽ 1674 በተደነገገው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ከመጽሐፉ አንድ አንቀጽ እንኳን መልሶ ማሳተም መቅዳት ወይም በሌላ መልክ ማሳተምና ማሰራጨት አይፈቀድም።

የመጀመሪያ ኅትመት 1998 (2006)

ISBN 99944-0-002-9

Printed in India

# ም ስ ጋ ና

የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ አንብበው የማሻሻያ አስተያየቶችን ለሰጡኝ ለአቶ ካሳዬ ወልደቂርቆስ፣ ለአቶ ተስፋዬ ቀለታ፣ ለዶክተር ኃይሉ ማሞ፣ ለአቶ ሰይፉ ደመቀ፣ ለአቶ እስጢፋኖስ ስሜና ለዶክተር ኃይለሚካኤል ኪዳነማርያም የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። አስተያየትና ምክር በመስጠት የረዱኝንና በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን የሌሎች ሰዎችን ስም መዘርዘር ስለእነሱ የጻፍኩት በወዳጅነት ስሜት የተበረዘ ወይም የተከለሰ እንዳይመስልብኝ ብሎም በተቺዎች በራዥ ከላሽ እንዳልባል በመፍራት ስማቸውን ከመጥቀስ ተቆጥቤአለሁ። ተሳስቼ ከሆነም ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ።

መጽሐፉ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ግድፈት የተለገሱኝን አስተያየቶች ወይም ምክሮች ካለመቀበል ጭምር የመነጨ ሊሆን ስለሚችል ኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የራሴ የደራሲው ነው።

*ታደሰ ገብረኪዳን*

# ማውጫ


**መንደርደሪያ** .......... 8

**ምዕራፍ አንድ** — **የልጅነት ዘመን** .......... 13

**ሙሀር፣ 1938-1945** .......... 13

**ዳያ፣ 1942-45** .......... 16

**የሙሀር ሰፈር ሕይወት** .......... 19

**ምዕራፍ ሁለት** — **የትምህርት ዘመን** .......... 56

**ፊደል ቆጠራ** .......... 56

**አንደኛ ደረጃ ትምህርት** .......... 58

**ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት** .......... 72

**አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ** .......... 78

**ድህረ ምረቃ** .......... 88

**ሥልጠና** .......... 94

**ምዕራፍ ሦስት** — **አዲስ አበባ ባንክ** .......... 98

**ምዕራፍ አራት** — **ብሔራዊ ባንክ** .......... 125

**ብሔራዊ ባንክ ቦርድ** .......... 156

**የብር ለውጥ** .......... 165

**የባንኮች ኮምፕዩተር ማእከል** .......... 193

| | | |
|---|---|---|
| | የሞቃዲሾ ጉዞ | 197 |
| | የቻይና ጉብኝት | 210 |
| | የአፍሪቃ ልማት ባንክ ውዘግብ | 217 |
| | የኑሮ ውድነት አስወጋጅ ኮሚቴ | 226 |
| | የሊብያ ጉዞ | 232 |
| | ፕሬዚዳንት ባንዳ | 224 |
| | ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የነበረው ግንኙነት | 252 |
| | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት | 288 |
| | የመንግሥት እርሻዎችና ጣጣቸው | 301 |
| | የፓርቲ አባልነት | 309 |
| ምዕራፍ አምስት | የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር | 317 |
| ምዕራፍ ስድስት | የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ባለሙያዎች ማኅበር | 337 |
| ምዕራፍ ሰባት | ውጭ ንግድ ሚኒስቴር | 343 |
| | ጫት | 349 |
| | ቆዳ | 358 |
| | ገጠመኞች በያይነቱ | 367 |
| ምዕራፍ ስምንት | አምባሳደርነት | 387 |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ዘጠኝ | የስደት ኑሮ | 409 |
| | ኬፕ ታውን፣ ደቡብ አፍሪቃ | 420 |
| | ላይቤርያ | 435 |
| መደምደሚያ | | 470 |
| ግጥሞች | | 475 |
| | ገሀነም ወይ ገነት | 475 |
| | የኢትዮጵያ አብዮት | 484 |
| | ባለጸጋን መለማመጥ | 510 |
| | ነጭና ጥቁር | 537 |
| | ዲያሎ | 543 |

# ብ ዙ ዐ የ ሁ

# የሕይወት ታሪክና ትዝታ

## መንደርደሪያ

በደርግ ዘመነ መንግሥት፣ ይኸውም የዘውድ አገዛዝ በተገረሰሰ ማግስት፣ ከየካቲት 1967 እስከ ሰኔ 1983 የብሔራዊ ባንክ ምክትል አዛዥና ዋና አዛዥ፣ የውጭ ንግድ ሚኒስትር፣ እንዲሁም በካናዳ አምባሳደር ነበርኩ። የደርግ መንግሥት ከፈረሰ ጀምሮ ነዋሪነቴ ከቤተሰቤ ጋር በካናዳ ሆኗል። በሁለት አፍሪቃ አገሮች በአማካሪነት አገልግያለሁ። በሥራ ላይ ያጋጠሙኝና የተመለከትኳቸው አንዳንድ ሁኔታዎችና ክስተቶች ምናልባት ትምህርት የመስጠት ኃይል እንዳላቸው በሚል በጽሑፍ ቀርጬ ላስቀራቸው ፈለግሁ። የጽሑፉ ይዘት እንዳይንዛዛ ወይም ፈር እንዳይስት ትረካዬን ከሕይወቴ ታሪክ ጋር አቆራኝቼዋለሁ። ይህ ዘይቤ በውል ስላላጤንኳቸው ውስብስብ ጉዳዮች ከመዘባረቅ አድኖኛል ብዬ አምናለሁ።

መጽሐፉን ለመጻፍ ያነሳሱኝን ሌሎች ምክንያቶች ከዚህ በታች ገልጫቸዋለሁ። ከሃያ ሦስት አመታት በፊት፣ እአአ በ1982[1]፣ የዓለም ባንክና የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት IMF ዓመታዊ ጉባኤ በካናዳ ቶሮንቶ ከተማ ተደርጎ በነበረበት ወቅት የባንኩ ፕሬዚዳንት ሚስተር ሮበርት

---

[1] በመጽሐፉ ውስጥ እ.አ.አ ከተመለከተ ዘመኑ በአውሮጳውያን አቆጣጠር ነው። እአአ ካልተመለከተ ዘመኑ በኢትዮጵያውያን አቆጣጠር ነው።

ማክናማራና የ IMF ሥራ አስኪያጅ ዲሬክተር ሚስተር ደላሮዚዬር የጥቁር አፍሪቃ የገንዘብ ሚኒስትሮችንና የማእከላዊ ባንኮች አዛዦችን አንድ ላይ ሰብስበው ባነጋገሩበት ወቅት ሚስተር ማክናማራ፡-

“ሌላው አለም ወደፊት እየተራመደ ነው፣ ለሚገጥመው ችግር ከሞላ ጎደል መፍትሔ ማግኘት ችሏል፣ ጥቁር አፍሪቃ ግን ወደኋላ እየተንሸራተተ ነው፤ ምን ነካችሁ? ችግራችሁ ምንድነው?”

ብሎ በተቆርቋሪነት በግልጽ የጠየቀን ጥያቄ ነጋም ጠባም ዘወትር ሲከነክነኝና ኅሊናዬን እረፍት ነስቶት ይኖራል።

ሚስተር ማክናማራ ኢትዮጵያውያንን ብቻ አንድ ላይ ተሰብስበን ቢያገኘን ኖሮ በአገራችሁ ለምንድነው ረኀብ፣ ድንቁርና፣ መታረዝ፣ በሽታ የነገሡት? ለምንድነው ወደፊት መራመድ ያልቻላችሁት? ችግራችሁ ምንድነው? ብሎ መጠየቁ የማይቀር ነበር። በተዋረድ ኢትዮጵያን ለማስቀደም የምናደርገው ጥረት የመከነው ከጥረት ማነስ ነው? ወይስ ጥረታችንን የሚያቀናጅና የሚያስተባብር በመጥፋቱ? ወይስ እራሳችን ለራሳችን ፍቱን መርዝ ስለሆንን? ብለን መጠያየቅ ይኖርብናል። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምን ሠራሁ? መሥራት ስችል ሳልሠራ የቀረሁት ምንድነው? መሥራት ሳይገባኝ የሠራሁትስ ምንድነው? ብሎ እራሱን መጠየቅና መመርመር ይጠበቅበታል።

በጎ ተግባራትን ማበራከትና ድክመቶቻችንን ማስወገድ ከቻልን ሰው የደረሰበት መድረስ የማንችልበት አንድም ምክንያት አይኖርም። ድክመቶቻችንን ለማስወገድ መተራረም አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ሒስን ስለምንጠላ ሒስ ደርዳሪን እንደጦር እንፈራለን። ወቀሳን በጸጋ መቀበል አናውቅበትም። ሰውን ላለማስቀየም እየተባለ ችግሮችን ሸፋፍነን ማለፍ ይቀናናል። የሐሳብ ልዩነት ካለን ጋር ተቻችሎ እንደመኖር ወይም ችላ እንደማለት ድራሹን ለማጥፋት እንፈልጋለን። ማስተዳደር ማለት ረግጦ ወይም አዋርዶ መግዛት ይመስለናል። በመሆኑም የበቀል ልጆችን

መፈልፈል ብሔራዊ መለያችን ሆኗል፡፡ ለችግሮቻችን መፍትሔ ሳናገኝላቸው እየቀረን በችግር ላይ ችግር እየደራረብን በልማት ወደፊት መግፋት አቅቶናል፡፡ ለኋላቀርነታችን እያንዳንዳችን ጥፋተኞች መሆናችን አምነን መቀበል አልቻልንም፡፡ አንዳችን በሌላችን ማሳበብና እራሳችንን ነጻ ለማውጣት መቀበጣጠር እንጂ ለውድቀታችን ኃላፊነትን መውሰድ አልተማርንም፡፡ የሚጠበቅብንን ተግባር ሳናከናውን እየቀረን ሰኞና ማክሰኞ አልገጣጠም ሲሉን እግዚአብሔርን ማስቸገር እንወዳለን፤ እንዳሰብነው ሳይሆን ሲቀር ፈጣሪያችንንም ከማማት አንመለስም፡፡

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የምንል ሰዎች ግለኝነትን፣ ተጠራጣሪነትን፣ እራሳችን አንሰን ሌላውን ወገናችንን አሳንሰን በማየት ያልሆንነውን ነን ማለቱን ለምንድነው የሙጥኝ ብለን የያዝነው? የኤኮኖሚ ልማት ከሌለና ከሌላው በተለይም ከባላጋራዎቻችን ወይም ባላንጣዎቻችን አንሰን ከተገኘን ያገርና የሕዝብ አንድነት ሊኖር እንደማይችል መገንዘብ እንዴት ተሳነን?

ቅድመ አያቶቼ እነማን ነበሩ? ከየት መጡ? ወዴት ሄዱ? ምን አደረጉ? ለሰው ልጅ ደኅንነት ታጋዮች ነበሩ? ወይስ አቆርቋዦች? ለሚሉት መልሶች የሉኝም፡፡ ስለሆነም፤ ውስጠ ቀፎነት ወይም ግንጥልነት ይሰማኛል፡፡ ዘር ማንዘሬ ተመሳሳይ ስሜት እንዲጸናወተው ስለማልሻ፣ ከሌላው ልምድ አለመማር የሚያስከትለውን ኪሳራ ወይም ትርፍ ወደጎን ትቼ፣ የልጅ ልጆቼና ወዳጆቼ ስለእኔ ወይም ስለአመለካከቴ ለማወቅ ያላቸውን ፍላጎት ለማርካት ስል ታሪኬን ለመጻፍ ተነሳሳሁ፡፡

ልጆቼ በቅርብ ያለውን አባታቸው ማንነት ጠንቅቀው ሳያውቁ ስለሰው ዘር አመጣጥና ስለታሪክ ሂደት እንዲመራመሩ መወትወት አግባብ እንዳልሆነ ስለተረዳሁ ታሪኬን ቀርጬ ላስቀርላቸው ወሰንኩ፡፡ እንደኔው ታሪክ ማንበብን እንዲወዱና አመለካከታቸውና የአስተሳሰባቸው አድማስ እንዲሰፋላቸው እፈልጋለሁ፡፡ የዓለማቸው ስፋትና ምጥቀት በረገጡት መሬትና አንጋጠው በሚያዩት ሰማይ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር አልፈልግም፡፡ ቢቻል የዓለም ዜጋ፣ ቢያንስ ቢያንስ ኢትዮጵያዊ ነን ብለው እንዲያድጉ

እፈልጋለሁ:: የኢትዮጵያ አምላክ ጠባቂያችን ብቻ ሳይሆን የሚፈታተኑትን የማይወድ፣ ቀናተኛና ድል አድራጊም እንደሆነ እነግራቸውና እንዲማጸኑት እመክራቸዋለሁ::

ልጆቼና ዝርያቸው ብቻ ሳይሆኑ ይህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሁሉ ሕይወት የውጣ ውረድ ጎዳና መሆኑን አውቀው ለሚገጥማቸው ሁሉ ተዘጋጅተው እንዲገኙ፣ በራሳቸው እንዲተማመኑ፣ ሕይወት ክቡር መሆኑን አውቀው ዕድሜያቸውን በዋዛ ፈዛዛ እንዳያሳልፉ፣ ለሐቅ በሐቅ እንዲታገሉ ለማበረታታትና ጥሩ ሰዎች ለመሆን ከመጣር ምንጊዜም እንዳያቋርጡ አደራ ለማለት ፈልጌ የንጉሥ ዘር ወይም የገዥው መደብ ከፍተኛ ባለሥልጣን ባለመሆኔ ታሪክ ጸሓፊዎቻችን እንደማያንቆላጽላጥሱኝ አውቃለሁና የአንጎሌን በማንጎሌ[2]፣ እራሴን በራሴ ለማንቆላጳላጠስ ተነሳሁ::

የአንድ ሕዝብ ታሪክ በግለሰቦች እንቅስቃሴና ገጠመኞች፣ እንዲሁም በሰዎች መካከል የሚደረጉ ግንኙነቶች በሚያስከትሏቸው ተጽዕኖዎች ጥርቅም ይወሰናል:: ይህ ሁላችንንም ታሪክ ሠሪዎች ወይም የታሪክ ባለቤቶች ያደርገናል ማለት ነው:: የሰው ዘር ሁሉ የታደልነው የሕይወት ፍሬ ወይም ዲ ኤን ኤ ከሞላ ጎደል አንድ አይነት ቢሆንም በሰዎች መካከል ልዩነት የሚፈጠረው እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገው እንቅስቃሴ በዓይነቱ፣ በብዛቱና በጥራቱ የተለያየ በመሆኑ ነው:: ይህም ማለት፣ ለሆነውም ሆነ ላልሆነው፣ እንዲሁም ለተሆነውም ሆነ ላልተሆነው ተጠያቂው፣ ከሞላ ጎደል፣ እያንዳንዱ ግለሰብ እንዲሁም አቅፎ ደግፎ የያዘው ወይም እግር ተወርች አስሮ ወይም አፍኖ ወደኋላ ያስቀረው የኛ ነህ የሚለው ማኅበረሰብ ወይም ኅብረተሰብ ነው:: አንድ ሰው የተጓዘበት የሕይወት ጎዳና ቢታይ፣ ማንነቱንና አስተዋጽኦዎቹን ስለወሰኑት ነቁጦች ወይም ክስተቶች መረዳት ይቻላል:: እኔም፣ ይኸው በዚህ መጽሐፍ

[2] በብዕሬ

አማካይነት ልቤንና አእምሮዬን ከፍቼ ቀርቤአለሁና ጊዜ ያለው ሁሉ ገልጦ ይየኝ::

የእኔን ማንነት ከወሰኑት ነቁጦች መካከል ዋነኛው ከኔ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበራቸው ሰዎች በሥነልቦናዬ ላይ የቀረጹት ማኅተም ወይም የተዉት ጠባሳ ነው ብዬ አምናለሁ:: አንድ ሰው ካልመነነ በቀር ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዳሻው መወሰን ወይም መቆጣጠር አይቻለውም:: በመሆኑም፣ የተጓዝኩበትን የሕይወት ጎዳና በዐይነ ኅሊናዬ ወደኋላ ተመልሼ ስቃኝ፣ ስለግለሰቦች ማውሳት የግድ ነው:: በዚህ የሚከፋብኝ ካለ ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: እውቀት የሚያስፋፋው አንዱ ሌላውን ሲያርመው ወይም አንዱ የሠራውን ሌላው ሲያዳብረው ስለሆነ ያላጤንኩት ወይም የተሳሳትኩት ነጥብ ካለም አርሙኝ እላለሁ::

ታሪካቸው የተጻፈላቸው ሲታወሱ፣ ምንም ታላቅ ሥራ ቢሠሩ ታሪካቸው ያልተጻፈ ሰዎች ሲረሱ አያለሁ ወይም እንደሚረሱ እገነዘባለሁ:: ስለሆነም፣ ታሪኬን ጽፌ ለማስቀረት ያነሳሳኝ አንድም እራስ ወዳድነት መሆኑን አልክድም::

ዛሬ ተራ የሚመስለን ነገር በነገ መነጽር ሲታይ ግን አስገራሚ ወይም ዕፁብ ድንቅ ሊሆን ይችላል:: የቀድሞ ሰዎች እንዴት ያስቡ ነበር? ምን ያደርጉ ነበር? በተወሰነ አቅጣጫ ለምን ወደፊት መራመድ ቻልን? በሌላው ለምን ወደኋላ ቀረን? ብለው ተከታይ ትውልዶቻችን መጠየቃቸው የማይቀር ስለሆነ ማንነታችንን፣ ማለትም ድክመቶቻችንንና ጥንካሬዎቻችንን መዝግበን የማስቀረት ኃላፊነት አለብን ብዬ ስለማምን የዜግነት ግዴታዬን በመጠኑም ቢሆን በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ተወጥቼዋለሁ::

# ምዕራፍ አንድ

# የልጅነት ዘመን

## ሙህር፣ 1938 - 1945

የተወለድኩት ህዳር 5 ቀን 1938፣ ታችኛው የሳንቃ፣ ሙህር፣ ጉራጌ ነው። አባቴ ስራጋ የክርስትና ስማቸው ገብረኪዳን፣ አባታቸው አትጋቦ፣ እናቴ ደግሞ ያቤሽወት ቡታ ሲሆኑ ሰባተኛው ልጃቸው ነኝ። እናቴ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየችው ሶስት አመት ሳይሞላኝ ቢሆንም ያረፈች ሌሊት የነበረውን የልቅሶ ውካታ እንዲሁም እንድትነቃልኝ ስቀሰቅሳት እንደነበር አስታውሳለሁ። በጣም ትወደኝ ስለነበር ታምሜ ሳለ ጦሴን ለመውሰድ ስትዞረኝ በሽታዬ እንደተጋባባት ዘመዶቼ ነገሩኝ። እኔም ለሷ የነበረኝ ፍቅር ያላነሰ እንደነበር እገምታለሁ። አንድ ቀን አዝላኝ ወንዝ ስትሻገር "እማዬ ቀስ በይ፣ ወንዙ ይወስድሻል" እንዳልኳት ተነግሮኛል።

አባቴ እናታችንን በቀላሉ እንዳላገኟት ተረድቻለሁ። ታሪኩ እንደሚከተለው ነው።

በሀብታቸው ብዛት ተማምነው ያቤሽወት ለልጃቸው እንድትዳርላቸው ጠይቀው በመከልከላቸውና ለምስኪኑ አባቴ በመሰጠቷ የተበሳጩት የገንዞ ጎሳ አባላት የማንገፍር ጎሳውን አባቴን በማጥላላት የሚከተለውን መልእክት ለፋሊሉ ጎሳ አያቴ ለቡታ ላኩ።

| ጉራጌኛ | አማርኛ |
|---|---|
| ያቤሾ አባኽ ተዳናም | ያቤሾ፣ አባትሽ ተላላ፣ |
| በኩወር ቸም በሌጣ ቾናም | ሌጣ ጋላቢ፣ ኮርቻ ጠላ፣ |
| በምስል ቸም ቦቃራ በናም | በዩ በካራ፣ እያለ ቢላ:: |
| ጊቤ ቸም ቧቶ ተገናም | ጊቤን ናቂ፣ ጨሬ አፍቃሪ፣ |
| ገረድ ኤወጂዬናም አወጀናም | ልጅ እማትዳርበት ዳሪ:: |

## የቡታ መልስ

| | |
|---|---|
| ገረድ ያወጄሜ አወጀህናም | አዎን፣ ለጀግና ልጄን ዳርኳት፣ |
| በገሽ ኳና ሰቀርህናም | ሰቀልኳት በጎሽ አናት፣ |
| ያብም ተርች በቅር ተመና | ልጅም አባት፣ መቶ ግዳይ ከጣሉበት<br>ወንድ ነኝ ያለ እስቲ ያውርዳት |

ግጥሙ የተገጠመው 1910 ገደማ ነው:: ግጥሙን የወረደልኝ አጎቴ ገብረሚካኤል ቡታ ነው:: ወንድሜ ዶክተር ብርሃኑም በቃሉ ያውቀው ኖሮ ብላክስበርግ፣ ቨርጂንያ በ1987 ልጠይቀው ሄጄ ጉራጌኛውን ጽፎ ሰጠኝና ወደ አማርኛ ተረጎምኩት::

የቡታ መልስ ባጭሩ የሚለው ልጄን ለጎበዝ ወገን ሰጥቻታለሁ፣ አርፋችሁ ተቀመጡ ነው፡፡ በወቅቱ በአባታችን ጎሳ በማንገፍር ውስጥ፣ ልጅ፣ አባትና አያት አበጋዝ ወይም በጉራጌኛው አብጋዝ የነበሩት አንድ ቤተሰብ ነበር፡፡ ገንዞዎች ግን አንድም አብጋዝ አልነበራቸውም፡፡ አንድ ሰው አብጋዝ የሚባለው ቢያንስ መቶ ጠላት ወይም እንደ ጎሽ የመሳሰሉ ኃይለኛ የዱር አራዊት ሲገድል ነበር፡፡

አሽሚጣጮቹ ወይም ተራቢዎቹ የቡታ መልስ አንገታቸውን አስደፍቷቸው ኮምሽሽው አርፈው ተቀመጡ ይባላል፡፡

ያቤሽወት ቡታና ስራጋ (ገብረኪዳን) አትጋቦ ስምንት ልጆች ወለዱ፡፡ ከእነርሱም አራታችን አዳነች፣ ብርሃኔ፣ ደንባርጋና ታደሰ በሕይወት ስንኖር አራቱ በጨቅላነታቸው ተቀጭተዋል፡፡ የመጨረሻው ልጅ መኩሪያ እናታችን እንዳረፈች ወድያው በስድስት ወሩ ተቀጨ፡፡ እናታችን በ1941 ዋዜማ ጳጉሜ 5 በድንገተኛ ሕመም ሳቢያ አረፈች፡፡

እማማ በሕይወት እያለች ደንባርጋን ልጆች እንደደበደቡትና ጭንቅላቱን እንደፈነከቱት አስታውሳለሁ ብዬ ስናገር የሰሙ ዘመዶቼ ከዕድሜህ ማነስ የተነሳ በምንም ዓይነት ልታስታውስ አትችልም ብለውኝ ነበር፡፡ ደንባርጋን ስጠይቀው እውነት መሆኑን ነግሮኝ ጠባሳውን አሳይቶኛል፡፡ የተደባደበው ከሁለት ወንድማማቾች ጋር ነበር፡፡ የተጣላው ከአንዱ ጋር ሲሆን ሌላኛው ጥፋተኛው ማን መሆኑን ሳያጣራ በዐይን ጭፍን ለወንድሙ አግዞ ደንባርጋን መደብደቡ በአእምሮዬ ላይ ዘለአለማዊ ጠባሳ ትቶ አልፏል፡፡ ድርጊቱን አስመልክቶ በ1985 የጻፍኩት ግጥም "ገሀነም ወይ ገነት" በሚል ርዕስ በገጽ 452 ሰፍሯል፡፡

የሳንቃ የሚገኘው በአክሱም ዘመነ መንግሥት ስለመቋቋሙ በታሪክ ዐዋቂዎች በሚነገርለት በገዳመ ኢየሱስ አጠገብ ነው፡፡ የሙህር ሰዎች አክራሪ ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች ናቸው፡፡ እንደሌሎች የክርስቲያን አካባቢዎች ሁሉ፣ የኦሪት ሕግጋትም ጎን ለጎን ወይም በቁርኝት ይከበራሉ፡፡

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ፣ ዓርብ የተፈታ መቀነት በዕለተ ቅዳሜ መታጠቅ፣ ቡና መውቀጥ የተወገዘ ነበር። እንደተቀረው ሰባት ቤት ጉራጌ ሳይሆን ሙህሮች በአካባቢ አማልክት አያመልኩም። አምላካቸው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ከአባቴ እንደሰማሁት የሙህር ክርስትያኖች ቡና መጠጣትን እንደኀጢአት ይቆጥሩት ስለነበር፣ መጠጣት የተጀመረው ከዘጠኝ አመታት አይበልጥም። መጀመሪያ ቡና ስትጠጣ የተገኘችውን ሴት ማኅበረሰቡ እንዳገለላት ነግረውናል። ሲጋራ ማጨስም እንደዚሁ የተወገዘ ልምድ ነበር። ሙህር ለጉብኝት ሄጄ ስመለስ "ሕዝቡ በካቲካላ የተለከፈ ይመስላል፤ ሊጠይቁኝ የመጡ ዘመዶቻችን ገና ከማለዳው ጠርሙስ በብብታቸው እየሸጎጡ መጡና ሞኝ አንግሥን ስንጎነጨው አረፈድን፣ የሕዝቡ ባሕል ምን ያህል እንደተበላሸ ዓይቼ መጣሁ" ብላቸው ነው እንግዲያስ ስለቡና ልንገራችሁ ብለው የነገሩን። ወደ ካናዳ ከመጣሁ በኋላ በአገራችን ጫትም ተመሳሳይ ደረጃ ላይ እንደደረሰ እየሰማሁ የባሰ አታምጣ እያልኩ እቆዝማለሁ።

የካቶሊክ ሚሲዮናውያን መጀመሪያ የመጡትና ሊቆናጠጡ ፈልገው የነበረው ሙህርን ነበር። ሕዝቡ ስላልተቀበላቸው ወደ ቸሀ ወርደው ከሃይማኖቱ ትምህርት ጎን ለጎን የትምህርት ዕድል አስፋፉ። የሙህር ሕዝብ በሃይማኖቱ ጽናትና በዘመናዊ ትምህርት ኋላቀርነቱ እስከቅርብ ጊዜ የታወቀ ነበር።

# ዳያ፣ 1942-45

እናቴ ካረፈች በኋላ እዣና ሙህር ድንበር ወደሚገኘው ዳያ የሚባል አካባቢ ተወሰድኩ። ይህ የተደረገው የቤት ሠራተኞችን ጡርወት አዲስ አበባ በንግድ ሥራ ላይ ለነበሩት አባታችን ባስተላለፈችው መልእክት ይህ የሙት

ልጅ በእጄ ቢሞት ተጠያቂ አልሆንም በማለትዋ ነበር፡፡ ታደሰን አዲስ አበባ ወስዶ በኃይለኛዋ እንጀራ እናታችን በዘርጊ ፈይሳ ከማሰቃየት ይልቅ ዳያ ሄዶ ከሴት አያቱ ከጉርጉር ሲፈኖና ከአጎቶቹ ከወልደሰንበትና ከወልደትንሣኤ ጋር ቢቀመጥ ይሻለዋል ስለተባለ ነበር ወደ ዳያ የተወሰድኩት፡፡

ዳያ በነበርኩበት ወቅት ጎልተው ከማስታውሳቸው፣ ደበሎ ወይም የበግ ቆዳ ለብሼ በጎችና ጥጃዎች አግድ እንደነበረ ነው፡፡ ዳያ ግርጌ በጣም ትልቅ የቀርከሃ ዱር ነበር፡፡ ቀርከሃ ለጉራጌ ቤት ሥራ በጣም ተፈላጊ ስለሆነ ዱሩ ከቅርብና ከሩቅ የሚመጣውን ቤተሠሪ ያስተናግድ ነበር፡፡ እውስጡ ከጥጃዎቼና በጎቼ ጋር መራወጥና ከዛፎቹ ላይ የሚያንጸባርቀውን ብርሃን ማድነቅ በጣም ያስደስተኝ ነበር፡፡ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆኜ ዘመዶቼን ለመጠየቅ ዳያ በተመለስኩበት ወቅት ትዝታው በልቤ ይመላለስ ወደነበረው ዱር እንሂድ ብላቸው የምን ዱር? ዱሩ ከሄደ ውሎ አድሮአል እኮ አሉኝ፡፡ የለም፣ ሄጄ በዐይኔ ካላየሁ አላምንም ስላልኩ ወሰዱኝ፡፡ አካባቢውን ቀደም ብሎ ለማያውቀው ሙሉ በሙሉ በተራቆተው ስፍራ እዚህ ዱር ነበር ቢሉት በፍጹም ሊያምን አይችልም፡፡ ምን ተፈጠረ? ብላቸው፣ ደጋ የነበሩትን የቀርከሃ ጫካዎች በሙሉ በሽታ ገብቶ ጠራረጋቸው ብለው አረዱኝ፡፡ ሐዘኑ እስካሁን አልለቀቀኝም ብል የማጋንን አይምሰላችሁ፡፡ በቀላሉ የማልገላገለው አስደንጋጭ ገጠመኝ ሆኖ አእምሮዬ ውስጥና በስነልቦናዬ ተቀርጾ ቀርቷል፡፡ ስለደን ጭፍጨፋና መሬት መራቆት በተነሳ ቁጥር በሐሳብ ወደ ዳያ እነጉዳለሁ፡፡ የ1966ቱ አብዮቱ ሲፈነዳ የመንግስት ቅድሚያ ትኩረት ምን ይሁን? ሲባል ደን ተከላና መሬትን መንከባከብ ነበር ያልኩት፡፡

ዳያ ሦስት ዓመት ያህል ከኖርኩ በኋላ ወንድሞቼ ብርሃኔና ደንባርጋ አንድ ቀን በድንገት ከተፍ ይላሉ፡፡ ዕድሜው ከዐሥራ ሦስት ዓመት የማይበልጠው ደንባርጋ ያባት መሬት ጠባቂ ሲሆን ብርሃኔ ደግሞ አዲስ አበባ በበየነ መርዕድ ትምህርት ቤት የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ነበር፡፡ ከአያቴ

ስንለያይ ለስንብት ብላ እናቴ ላይ የጠፈጠፈችውንና ፊቴ ላይ የመረገችውን ቅቤ ዳያ ግርጌ ካለው ትንሽ ወንዝ እንደደረስን ብርሃኔ ሙልጭ አድርጎ ጠርጎ እንዳጠበኝ ትዝ ይለኛል።

የሳንቃ ተመልሼ ከደንባርጋ ጋር ጥቂት ከቆየሁ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተወሰድኩኝ። ከየሳንቃ ወሊሶ ለመድረስ በእግር አንድ ቀን ፈጀብን። ወሊሶ አድረን ወደ አዲስ አበባ የተጓዝነው፣ የተንቀረፈፍነው ማለት ይሻላል፣ በፎርድ አውቶቡስ ሲሆን 115 ኪሎሜትሩን ርቀት ለማጠናቀቅ የወሰደብን አንድ ቀን ተኩል ነበር። አውቶቡሱ ውስጥ ያስቀመጡኝ ወለሉ ላይ ሲሆን አንገቴን ቀና ባደረግሁ ቁጥር የማየው የሚጓዙ ዛፎችን ስለነበር ይህን ትልቅ ታምር እየመሰከርኩና ጉድ፣ አበስኩ ገበርኩ እያልኩ አዲስ አበባ ገባን።

አዲስ አበባ ደርሰን ከተክለሃይማኖት ቤተክርስትያን ደቡብ ምዕራብ፣ የንጉሥ ወልደጊዮርጊስ ግቢ ከነበረው ዝቅ ብሎ፣ የሙህር ሰፈር ከሚገኘው ያባቴ ቤት ደርሼ አዲሷን እንጀራ እናቴ ባዬቹን ገና ከመተዋወቄ አጎቴ ኬርጋ በርበሬ በረንዳ የሚባል አካባቢ ይዞኝ ይሄድና ሻይና ዳቦ ይጋብዘኛል። የዳቦም ሆነ የሻይ ወይም ስኳር ጣእም ከዚያን በፊት ጭራሽ ስለማላውቅ ዳቦውን ጎርሼ፣ ሻዩን ፉት ከማለቴ ይተናነቀኝና ያስመልሰኛል። ጣፋጭም ነገር ቢሆን ካላወቁት ወይም ካልለመዱት ወይም መንፈስ ካልፈቀደው ሰውነት እንደማይቀበለው እንዲሁም የማያውቁትን ነገር መውደድ እንደማይቻል የመጀመሪያው ትምህርት ሆነኝ። በነገራችን ላይ ወደደ ለሚለው የአማርኛው ቃል ተመሳሳዩ በጉራጌኛው ረመደ ነው። ይህ ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጎም ለመደ ይሆናል። በሻይ ቤቲቱ አጠገብ ባለፍኩ ቁጥር ፈገግ ብዬ ዐያትና በሐሳቤ ታስታውሺኛለሽ? እላታለሁ። ካናዳ ከታዘብኳቸው ነገሮች መካከል አንዱ እዚህ ግባ የማይባለውን ሕንጻ ሁሉ የታሪክ ቅርስ ነው እያሉ እንዳይፈርስ መከላከል ስለሆነ ሻይ ቤቲቱ በተአምር ወደዚህ ለመምጣት ብትችል የካናዳ የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲመዘግባትና እንዲንከባከባት ማመልከቻ አስገባ ነበር።

# የሙህር ሰፈር ሕይወት

በ1945 አዲስ አበባ ስገባ የሙህር ሰፈር የሚባለው አምስት የሳር ቤቶች ብቻ የነበሩት መንደር ነበር፡፡ የእነአባባ አሶሬ ቤት ከሌሎቹ ይተልቃል፡፡ የኛ ቤት የነበረው አንድ ዋና ክፍልና ጓዳ ብቻ ነው፡፡ የዋናው ክፍል ስፋት ከዐሥራ ስድስት ካሬ ሜትር የማይበልጥ ሆኖ፣ መዋያ፣ ማደርያ፣ መመገብያ፣ እንግዳ መቀበያ፣ መደሰቻና ሲያመጣው ማልቀሻም ነበር፡፡ የእነአባ አልጋ የጓዳውን ግድግዳ ተጠግቶ በመጋረጃ የተከለለ ነበር፡፡ ወለሉ አፈር ሆኖ ከዘንባባ የተሠራ ሰሌን ይለብሳል፤ ለዓመት በዓል በጊቻ መጥረጊያ በሚገባ ከተጠረገ በኋላ አዛባ ይለቀለቃል፡፡ ግድግዳው ከውጭ አልፎ አልፎ በኖራና ቀይ አፈር ይጌጣል፡፡ ቤቱ ያለው አንድ መስኮት ሲሆን ማለዳ ይከፈትና ሲመሽ ይዘጋል፡፡ ጓዳው ጭስ ቤትና የቅራቅንቦ ማጠራቀሚያ ነው፡፡

አባታችን በዘመዶቻችን የተሰጣቸው ቅጽል ስም ገጎ ነው፡፡ ትርጉሙ ገላዬ፣ ወይም አይኮሰኩሴ ማለት ነው፡፡ ዘመዶቻችን ስለአባባ የሚከተለውን ይሉ ነበር፡፡

የእንጣርየ ያበሌ ይቡይት የዘገደ

የአትጋቦ ስራጋ ተደንም ሰተተ

ትርጉሙ በአጭሩ "የአትጋቦ ስራጋ ክፋት ወይም ተንኮል በሆዱ የማይዝ ሰው ነው" ማለት ነው፡፡ አባታችን ያዩትን በሆዳቸው የመያዝ ችሎታቸውና ትዕግስታቸው በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ "አማራ ስም ማውጣት ይችላል፤ ጫካን ደን አለው" ይሉ ነበር፡፡ ደን በጉራጌኛ ሆድ ማለት ነው፡፡ ሆድ እንደጫካ ነው፤ ሁሉንም መደበቅ ይችላል ማለታቸው ነው፡፡ የሆድን ሁሉ አውጥተው ከተናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል ይሉም ነበር፡፡ ይህም ሲባል ስለጉዳዮች አስተያየት አይሰጡም ነበር ማለት አይደለም፡፡ የተመለከቱትንና

የሰሙትን ከሆድ ወደ ጭንቅላት አዛውረው ስለጉዳዮች በጽሞና ከተመራመሩ በኋላ በጣም ጥልቅ ትርጉም ያላቸውን ወይም ብልኅ አስተያየቶችን የመስጠት ችሎታቸው ከፍተኛ ነበር:: የሚናገረው መሬት ጠብ አይልም ከሚባልላቸው ሰዎች መካከል ነበሩ:: በፋሲካ ዋዜማ፣ የአክፍለት ዕለት፣ ጠጅ የተጋተ ቄስ አይቼ "አባባ፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?" ብላቸው፣ "ልጄ፣ እግዚአብሔር የሚለውን እንጂ ቄስ የሚያደርገውን አትከተል" ያሉኝ ዘወትር ትዝ ይለኛል::

ልጆቼ ሕይወታቸውንና የድርጊት እንቅስቃሴዎቻቸውን ሁሉ በግብረገብነት ላይ የተመሠረተና የታጠረ እንዲሆን የምለግሳቸው ምክር አንዳንዴ ሲያቅለሸልሻቸው ምነው እነገሌ እዚህ የደረሱት እንዲህ ስላደረጉ አይደለም እንዴ? ሰው ሁሉ እንዲህ እንዲያ እያደረገ እኛ ብቻ አንተ የምትለውን ፈለግ ብንከተል ከጓደኞቻችን በታች እንውል አይደል እንዴ? ሲሉኝ ጽናቱን ሰጥቶት ትክክለኛውን ጎዳና የተከተለ ያሸንፋል እላቸዋለሁ:: ካባቴ የተማርኩት ንጹሕ ሕይወት መኖር የደስታ ምንጭ እንደሆነ ነው:: ስም ከመቃብር በላይ ይውላል፤ ሕይወት ለዘላለም ትኖራለች የሚለው እውነት መሆኑን አሁን በትክክል ተገንዝቤአለሁ:: መጀመሪያ ነገር ዕድሜ ለቪዲዮ የሞተን ማየት የምንችልበት መስኮት ተሠርቶልናል:: ሁለተኛ፣ ሰው በሠራው ሥራ ለዘላለም ሲታወስ ይኖራል:: መልካም ሥራ የሠራ በዚሁ ሲታወቅ ክፉ የሠራ በክፋነቱ ሲታወስ ይኖራል:: ኅሊና ያለው ሰው እርጉምነትን ለዘር ማንዘሩ አውርሶ መሄድ አይፈልግም:: ምንም ያልሠራ ግን አልተፈጠረ ይመስል ተረስቶ ይቀራል::

ቤታችን ከአገር ቤት የሚመጣ ዘመድ ብቻ ሳይሆን ያባታችንን እንግዳ ተቀባይነት ዝና የሰማ ወይም ዘመድ ፊት የነሳው ወይም ያዞረበት ሁሉ የሚያመራው ወደ ስራጋ ቤት ነበር:: ከሦስተኛዋ እንጀራ እናቴ ከእልፍነሽ ጽጌ፣ አብርሃም፣ ብሩክ ተወልደዋል:: ሠራተኛ አለች:: በተጨማሪ፣ በደባልነት የተጠጋ ዘመድ ምንጊዜም አይጠፋም:: ባጭሩ፣ በሰው ብዛት የስራጋ ቤት ብዙ ተወዳዳሪ አልነበረውም::

ከአገር ቤት እንደመጣሁ ቤታችን የሰፈሩ ላውንድሪ ነበር:: እቤታችን የሚኖረው አጎቴ ኬርጋ ሥራው ልብስ አጣቢነት ነበር:: መንደረተኛው ያደፈ ልብሱን አምጥቶ ያስረክበዋል:: ልብሶቹ እስኪጠራቀሙለት ይጠብቅና በሳምንት አንድ ጊዜ አቃቂ ወይም ቀበና ወንዝ ተሸክሞ ሄዶ አጥቦና አድርቆ ይዞ ይመለሳል:: ቀኑ ፀሐያማ ካልሆነ ያጠበውን ልብስ እርጥቡን ተሸክሞ ይመለስና እንጨት አጥር ላይ ሰቅሎ ያደርቃል:: ሌባ ሰርቆበት እንዳይሄድ ይጠባበቃል:: ተኩስ የማያስፈልጋቸው ጋቢ፣ ነጠላ፣ ቡልኮ፣ የሴት አገር ልብሶች በውል ታጥፈው ይቀመጣሉ:: የቤቱ ሰው አስተጣጠፍ ላይ ይረዳዋል:: ተኩስ የሚፈልገው በከሰል ካውያ ይተኮሳል:: ከልብሶች ሁሉ የጆርጆርቲ ቀሚስ አተኳኮስ ከበድ ይል ነበር:: ጆርጆርቲ ብጫ ቀለም ያለው ከሐር የሚሠራ ወፍራም ጨርቅ ነው:: ከጆርጆርቲ የሚሠሩ ቀሚሶች ብዙውን ጊዜ ባለሽንሽን ነበሩ:: ቀሚሱ ሲተኮስ ሽንሽኖቹ ሳይዛነፉ ከወገብ እስከ ቀሚሱ ግርጌ ቀጥ ብለው እንዲዘልቁ ማድረግና የእያንዳንዱ ሽንሽን ሰምበሩ ግትር እንዲል ማድረግ ያስፈልጋል:: ያማረ ጆርጆርቲ ቀሚስ የለበሰች ሴት ሽንጥና ዳሌዋ እየተውረገረገ፣ መቀመጫዋ እየጠቀሰ፣ የቀሚስዋ ሽንሽኖች ግራና ቀኝ እየረገጡ ከምቧ፣ ከልቻ ስትል ማየት ትልቅ ያይን ተስፋ ነበር:: ለበርካታ ጎልማሶች አጉል ምኞት ዓለም ውስጥ መዋኘትና ብሎም ገሀነም መስመጥ የአጎቴ ኬርጋ እጅ አለበትና ምንም የማይሳነው አምላክ የሱንም የነሱንም ነፍስ ይማር::

ኬርጋ እኛ ቤት እስኪወጣ ድረስ ልብሴን በነጻ እያጠበ ተኩሶ ይሰጠኝ ነበር:: አልፎ አልፎ አቃቂ፣ አሮጌው አየር ማረፊያ ግርጌ እና ቀበና፣ ፈረንሳይ ኤምባሲ ግርጌ፣ ተከትዬው እየሄድኩ ልብሶቼን እራሴ ለማጠብ መሞከሬ አልቀረም::

ኬርጋ ሱፍ ልብስም ጠርጎና ተኩሶ ያስረክብ ነበር:: ሱፉ የሚጠረገው በቤንዚን ነው:: ቤንዚን በጠርሙስ ይገዛል:: የሱፍ ጨርቅ ቁራጭ ጥብቅ ተደርጎ በቁመቱ ይጠቀለልና እንዳይበተን ሦስት ቦታ፣ ወገቡ ላይና ከላይና ከታች፣ በጠንካራ ክር ይታሰራል:: የጨርቁ ራስጌ ጠርሙሱ አፍ ላይ

ጥብቅ ተደርጎ ተይዞ በደንብ እንዲርስ ይደረጋል፡፡ ሱፉ በጠረጴዛ ላይ ተዘርግቶ በራሰው ጨርቅ ነፍሱ እስኪጠፋ ይጠረጋል፡፡ ጠረጋው ወይም ፍተጋው ሲያልቅ የተጠረገው ልብስ እንዲናፈስ ይሰቀላል፡፡ ጥቂት ቆየት ብሎ በልብሱ ላይ ሳሳ ያለ ጨርቅ ጣል ተደርጎበት ይተኮሳል፡፡

ልብስ አስረካቢና ተረካቢ፣ የመንደራችን ወዶ ገቡን ውሻ ቹሎን በመፍራት፣ ከአጥር ውጭ ቆሞ "ኬርጋ!" እያለ ሲጣራ ይውላል፣ ያመሻል፡፡ ለብዙ የኬርጋ ደንበኞች ስራጋ የቤተሰቡ ደባል፣ ኬርጋ ደግሞ ባለቤት ቢመስላቸው አያስደንቅም ነበር፡፡ እንደ ኬርጋ በስራጋ ቤት በነጻ ተጠግተው ለኑሮአቸው መሠረት የጣሉ በርካታ ናቸው፡፡ አባባ ስለበጎ አድራጎታቸው ውለታዬ ይመዝገብ ሲሉ ሰምቼ አላውቅም፡፡

ቤታችን ላውንድሪ ብቻ ሳይሆን ክሊኒክም ነበር፡፡ አባባ የተሰበረ አጥንት የመጠገን፣ ብጉንጅ የማፍረጥና ቆሻሻ ደም በዋግምት መጥጦ የማስወገድ ችሎታ ስለነበራቸው እሁድ እሁድ ከቤተክርስትያን መልስ አጥንቱ የተሰበረ፣ ራስ ምታት ናላውን ያዞረው ወይም ብጉንጅ አላፈናፍን ያለው ከቤታችን አይጠፋም ነበር፡፡ በነጻ የሚታከመው ሕመምተኛ ከሕመሙ ተፈውሶ እፎይ ሲልና የስራጋ ዘርማንዘር ይባረክ እያለ ሲመርቅ ሁላችንም ደስ ይለን ነበር፡፡ ከስራጋ ተወላጆች ብርሃኔ የእጽዋት ሊቅ፣ ጽጌና የደንባርጋ ልጅ ይፋትወርቅ የሰውና የከብት ሐኪሞች፣ እንዲሁም ልጄ ጎሊና የማይዳሰሱ ነፍሳት ተመራማሪ ስለሆኑ አባባን እንኳን ሰው ቀርቶ ሳር ቅጠሉና ሕዋሳት ሁሉ ሃሌ ሉያ እያሉ በሰማይ ቤት ያለማቋረጥ እንደሚያዜሙላቸው ባልጠራጠርም የምስክርነት ቃል መስጠት የምችለው ግን ያቺ ቀን ደርሳ እላይኛው ቤት ስንገናኝ ብቻ ነው፡፡

ካገር ቤት የሚመጣው እንግዳ መጫሚያ ስላልነበረው ማታ ማታ እግሩን ማጠብ የተለመደ ነበር፡፡ ሽምገል ወይም ከበድ ያሉትን ሠራተኛዋ ወይም በደባልነት የሚኖር ልጅግር ዘመድ ያጥባል፡፡ አጣቢው ያጠበውን እግር ይስማል፣ በምላሹ ምርቃቱን ይከናነባል፡፡ እንደ ጠባያቸውና እንደ

አንደበታቸው የለሰለሰውን ያባባን እግር ማጠብ እወድ ነበር። በዕድሜ አነስ ያለው እራሱ ይታጠባል። ጠዋት ጠዋት የእግዚአብሔርን ብርሃን ተገን አድርጎ በመርፌ ቁልፍ ሙጃሌ ወይም ሞያሌ ከእግር ቆፍሮ ማውጣት የተለመደ ነበር። ሙያሌ እግር ውስጥ ሰርስራ ገብታ ቤት ከሠራች በኋላ ምን ያህል እንደምታሳክክ የሚያውቀው የደረሰበት ብቻ ነው።

ቤታችን ከሚያርፉት እንግዶች በተለይ ትዝ የሚሉኝ አዝማች ገለቶና አጎቴ ሽምብር ጡራግባ ናቸው። አዝማች የማንገፍር ጎሳ ንጉሥ ነበሩ።

አንድ ንጉሥ የጎሳው የበላይ ዳኛ፣ አስታራቂ፣ አስተባባሪና ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ለሚደረጉ ግንኙነቶች ዋና ተወካይና ሲያስፈልግም የጦር መሪ ነበር። መገመት እንደሚቻለው የማእከላዊው መንግሥት ሥልጣንና ኀይል በጉራጌ መሬቶች ላይ እየተጠናከረ ሲመጣ የጎሳ ንጉሦች ሥልጣን እየቀነሰ ሄደ። በአሁኑ ወቅት የማንገፍር ንጉሥ ዙፋን ክፍት ነው፤ በቅርቡ ይሞላል ተብሎ አይታሰብም። ነገር ግን ሕዝብን በጎሳ የመሸንሸኑ ተግባር ከተገፋበትና ሥር እየሰደደ ከሄደ የጎሳ ንጉሥነት በአንድ ቅርጽ ወይም በሌላ ተመልሶ ሊመጣ ይችላል። ማእከላዊው መንግሥት ከመጠናከሩ በፊት የነበረው ዓይነት በጎጥ ተከፋፍሎ መጋጨትና መዋጋት የነገው ዕጣችን ሊሆን ይችላል።

አዝማች ገለቶ የንጉሥነት የብር አምባር በጨርቅ ተሸፍኖ በክንዳቸው ታስሮላቸው አይቻለሁ። ለአንድ ንጉሥ ሥራ መሥራት ክልክል ስለሆነ መሬታቸውንና ቤታቸውን የሚንከባከቡላቸው የጎሳው አባላት ነበሩ፣ በተለይም በመኖሪያቸው አካባቢ የሚገኙት። በነገራችን ላይ የንጉሡ የአገር ቤት መኖሪያቸው የሳንቃ ሳይሆን ችሮማን አጠገብ ደብር በሚባለው ሥፍራ ነበር። የማንገፍር ጎሳ አባላት ጥንት የሰፈሩት እዚህ ችሮማን ነው ይባላል። ጥቂቶች አሁንም እዚያው ይኖራሉ።

ችሮማን በተራራ የተከበበች ጥልቅ ወጨት መሰል ጎድጎዳ ስፍራ ናት። የክልሏ ስፋት ግፋ ቢል ከሦስት ኪሎሜትር አይበልጥም። ችሮማን ተወልዳ

ያደገች አንዲት ልጅ ዐሥር አመት ሲሞላት ዳገቱን ወጥታ አፋፉ ላይ ትቆምና ዙርያዋን ትቃኛለች:: ያየችውን ማመት ያቅታታል:: አፍዋን ይዛ፣ ቋንቋዋ ወይ ጉድ! ወይ ጉድ! ብቻ ይሆናል:: ምነው? ብትባል፣ ሰዎች በጣም ይገርማል፣ ለካስ ከዥማንም ሌላ አገርና ሰማይ አለ አለች ይባላል:: የጠባብ ብሔረተኞች አይነጥላ ሲገፈፍ እንደዥማንዋ ዘመዴ ሁሉም ነገር ወለል ብሎ ይታያቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

አዝማች አንደበተ ርቱዕ፣ ተናጋሪና አናጋሪ ስለነበሩ እሳቸው በነበሩበት ስፍራ ነገሮች በዙሪያቸው ይሽከረከሩ ነበር ማለት ይቻላል:: ከተማ ውስጥ ብዙ ትላልቅ ወይም በተለምዶ አባባል አሉ የሚባሉትን ሰዎች ያውቁ ስለነበር ከማን ጋር እንደዋሉ ሲዘረዝሩ ምስኪኑ ሁሉ በመደነቅ ጸጥ ብሎ ያዳምጣቸዋል እንጂ የሚያቋርጥበት ወይም ደፍሮ የሚከራከርበት አፍ አልነበረውም:: ማታ ማታ ፉት ብለው ይመጣሉ፤ ወይም ጠጅ ተገዝቶ ይመጣላቸውና ሲኮሞኩሙ ያመሻሉ:: ሞቅ ሲላቸው ግንባራቸው ይወዛል፤ ዐይናቸው ይበራል፣ አንደበታቸው ይከፈታል፤ ከዚያ ጨዋታው ይዥጎደጎዳል:: በጣም ሞቅ ያላቸው ቀን ግን መረን ይለቁና ሌላውን ከማብጠልጠልና ከማንቋሸሽ አይመለሱም ነበርና ከልክ እንዳያልፉ እንሰጋ ነበር:: ያልጠጡ ቀን ጭር ያለች ዶሮ ይመስሉና ቤቱንም ጭር ያደርጉት ነበር:: ያኔ፣ ምነው ያ ነገር በቀረበላቸው እያለ ሁሉም በልቡ ያስባል፤ ነገር ግን ሐሳቡን በተግባር የሚደግፍበት ወይም የሚተረጉምበት ዐቅም ያለው ስለማይኖር ሐሳቡ ሐሳብ ሆኖ ይቀራል:: ሁሉም የሚጠብቀው ያው አባባን ነበር:: አዝማችን ሌላ የማስታውስበት ምክንያት፣ በፊታቸው ገጽታና በጣም በሚያምረው የጸጉራቸው ሽበት የተነሳ ነው:: አፍንጫቸውና የፊታቸው ገጽታ በዕውቅ ሰዓሊ ተስሎ በመሮ የተቀረጸ ይመስል ነበር::

ጋሼ ሽምብር መለስተኛ ነጋዴ ነበር:: በየክፍለ ሀገሩ ወይም በዚያን ዘመን አጠራር በየጠቅላይ ግዛቱ እየዞረ ጌጣጌጥ ይቸረችር ነበር:: ሽምብር አዲስ አበባ መጣ ማለት ፋሲካ መጣ ነው:: ቀልዱና ጭዋታው በፍጹም አይጠገብም:: በዓለም ላይ ብርሃንን ለመፈንጠቅ፣ ደስታን ለመርጨት

የተፈጠረ ይመስላል። ስለገጠመው ያልተሳካ ሕይወት አምላኩን ሲያማርር ባይውልም የነበሩትን አማራጮች አይመረምርም ነበር ማለት አይደለም። አንዴ አገር ቤት ለመስቀል በገባበት ወቅት፣ የዕድሉን ቋት ለማስፈተሽ ጠንቋይ ዘንድ ይሄዳል። ጠንቋዩዋ፤ አገርህን ጥለህ ከሄድክና በዚያው ከቀረህ ሐብታም ትሆናለህ ትለዋለች። ሽምብርዬ ውድ ልጆቹን አለምሸዋን፣ ደምሻሽን፣ ምርካሼንና ግዛውን ከኩርማን መሬት ጋር ለእናታቸው አስታቅፎ ጭልጥ ብሎ ጠፋ። ድህነትንና ያጎቱን የመመርየ ማያሞን እጅ ደጋግሞ ማየት ምን ያህል አንገሽግሾት እንደነበር ከዚህ የበለጠ ማስረጃ የለም። ለቤተሰቡና ለኛ አጎደለብን እንጂ ጋሼ ሽምብር ገሙጎፋ ገብቶ ሕይወቱን ገንብቶ፣ ሌሎች ልጆች አፍርቶ የሕይወቱን ሁለተኛ ምናልባትም መጨረሻ ምዕራፍ እንደተያያዘው ደረስንበት። አባባ መመርየ ሲያርፉ የሞት ሞቱን አዲስ አበባ ደርሶ ተመለሰ እንጂ የሳንቃ ለመሄድ አልደፈረም።

ምድራዊ ሕይወቱን በተመለከተ ጋሼ ሽምብርን የአባቶቹ ሃይማኖት ሳይሆን አጉል እምነቱ አድኖታል። እምነት በራሱ መነሻና መድረሻ ሳይሆን እግባችን ለመድረስ የምንጠቀምበት መሣርያ ነው ለሚል ሰው ጋሼ ሽምብርን እምነቱ ከተጸናወተው የድህነት በሽታ አድኖታልና ክርስቶስ እምነትህ ያድንሃል ሲል የጋሼ ሽምብር ዓይነቱን እምነት አይጨምርም ብሎ ማንም ደፍሮ መናገር አይቻለውም።

ግዛው ሙህር ሰፈር እኛ ቤት ተቀምጦ ተማረ። ባለቤቴና ልጆቼ የሰው መልአክ ይሉታል። በጣም እንወደዋለን። እንደ አባቱ አንድ ጋሬጣ የሆነበት ነገር አለ። የግዕዝ ወይም የአማርኛ ፊደላትን በትክክል አይጽፋቸውም። ስለሆነም፣ የትምህርት ዕድሉን አሰናክሎበታል። በስምንተኛው ክፍል መልቀቂያ ፈተና በአማርኛ ፈተና ያገኘው ውጤት፣ ካልተሳሳትኩ ስምንት ከመቶ ብቻ ነበር። ዩኒቨርስቲ ለዲግሪ ኮርስ እንዳይገባ አያ አማርኛ መንገድ ላይ ጠብቆ ተመለስ እንዳለው አስታውሳለሁ። ጋሼ ሽምብር ከድህነት ለመገላገል አገር ለቆ እንደተሰደደ ሁሉ፣ ምናልባት ግዛውም አማርኛ

ወደሌለበት ወደቲምቡክቱ ቢሄድ ኖሮ በበለጠ ይሳካለት ነበር:: አልሸሹም ዞር አሉ ቢመስልም፣ ሲዳሞ፣ ሻኪሶ ገብቶ ሕይወቱን መመሥረቱ ያባቱን ፈለግ ተከትሎ ሳይሆን አይቀርም::

የሙህር ሰፈር ቤታችን መብራት ወይም ብርሃን የሚያገኘው በአሽከር ቢያጡ ላይ ቁጢጥ ብሎ እቤት ውስጥ የሚሆነውንና የሚደረገውን ሁሉ ከሚታዘብ፣ ላምባ ግብሩ፣ ሥሪቱ ከቆርቆሮ የሆነ ቡጢ ከሚያክል ኩራዝ ነበር:: ከመጨለሙ በፊት ኩራዙ ላምባ ይሞላል፤ የኩራዙ ብርሃን ጨለምለም እንዳይል ወይም በሚገባ እንዲያበራ የክሩ ጫፍ ወደላይ ሳብ ይደረጋል:: ክሩ በጣም ወደ ላይ ከተሳበ ብዙ ላምባ እየመጠጠ ስለሚያቃጥል፣ ብሎም ውዱን ላምባ በቶሎ ስለሚጨርስ፣ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ክሩ ሲያልቅ ተገዝቶ ይተካል::

እንግዳ በመጣ ቁጥር ጠላ መጋበዝ የተለመደ ስለነበር ማንቆርቆርያ አንጠልጥለን "ጠላ ያለሽ!" እያልን መንደር ዞረን እንገዛለን:: ቅዳሜ ቅዳሜ ከልኪንዳ ሥጋ ይገዛል፤ ተቆራርጦ በትልቅ ብረት ምጣድ የደቀቀ ጨው ተነስንሶበት እየተንጨረጨረ ይጠበስና ትልቅ፣ ትንሽ፣ ሠራተኛ፣ ባለቤት ሳይባል ለሁሉም እኩል ይታደላል::

የመኝታ ሰዐት ሲደርስ ከሰበዝና ቀጫጭን ሲባጎ የተሠራ ከአገር ቤት የሚመጣ ጅባ ይነጠፍና ሰው በየተመደበለት ስንዝር መሬት ከተጋደመ በኋላ እንቅልፍ እስኪወስደውና የቅዥት አምላክ በክንፉ ይዞት እስኪነጉድ ድረስ ገፋኸኝ፣ ገፋሽኝ፣ ፈቀቅ በል፣ ጉልበትህን ዘርጋ፣ አትግፈፊኝ፣ ሲባባልና ሲቀላለድ፣ ሲተራረብ ከቆየ በኋላ ቀጥሎ የሚሰማው ድምጽ ቡም፣ ቱስ፣ ጡጥ፣ ተረረም ብቻ ይሆናል:: አልፎ አልፎ ደግሞ የወናፍ አይነት ድምጽ ይሰማል:: አንዳንዴ እንግዳ የበዛ ዕለት የመኝታ ስፍራ ይጠብና አግዳሚ ወንበር ላይ ጎኔን አሳርፌ ያደርኩባቸው ሌሊቶች ጥቂት አልነበሩም::

በ1954 ብርሃኔ ከአለማያ እርሻ ኮሌጅ እንደተመረቀ የሳሩን ቤት አስፈርሶ የተሻለ አሠራልንና ገላገለን፡፡ አባቴም የወለዱት ይወልዳል ሲሉ ሰማኋቸው፡፡

አባባ አሶሬ የሰፈሩ ብቻ ሳይሆን በአዲስ አበባ የሙህር ተወላጆች ሰብሳቢ ወይም ማእከል ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡ የዋናው የሙህር እድርና የትልቁ እቁብ ሰብሳቢ ናቸው፡፡ ተወዳዳሪ ያልነበረው ቁጡነታቸው ብቻ ሳይሆን ሐቀኛነታቸውና ደግነታቸውም ነበር፡፡ ሽምግልና ተቀምጠው ካስታረቁዋቸው ሰዎች በተዋጣ ገንዘብ የተገዛ ጠላ ወይም ምግብ በጭራሽ አይቀምሱም፡፡ ካለማወቅ ወይም በስሕተት ፍርድ አዛብቼ ከሆነ፣ ከተበዳዩ ገንዘብ ወስዶ መደሰት እግዚአብሔር አይወደውም፣ ኀጢአት ነው ይሉ ነበር፡፡ በታማኝነታቸው ስለማይጠረጠሩ ብዙ ሰው ገንዘብ እርሳቸው ዘንድ ያስቀምጥ ነበር፡፡ መጻፍና ማንበብ ስለማይችሉ በአደራ የተሰጣቸውን ገንዘብ በጨርቅ ይጠቀልሉና መኝታ ክፍላቸው ካለው ካዝናቸው ኪሶች አንዱ ውስጥ ወሽቅ አድርገው ያስቀምጡታል፡፡ የሰው ገንዘብ እናዳይደበላለቅባቸው ልዩ ልዩ ቋጠሮ ያደርጋሉ ወይም የመጠቅለያውን ጨርቅ ጫፍ በመቅደድ ምልክት ያደርጋሉ፡፡ እኔ እስከማውቀው በአደራ የሚቀበሉት ገንዘብ አይቆጠርም፡፡ ይቀበላሉ፤ ይቀመጣል፤ ይመለሳል፡፡

ወደኋላ ትምህርት መጣና ጣጣ አመጣ፡፡ የበኩር ወንድ ልጃቸው እንዳለ ማንበብና መጻፍ እንደቻለ የግምጃ ቤት ጸሓፊነት ይሾማል፡፡ የገንዘብ አጠቃለሉና ምልክት አደራረጉ ተቀየረ፡፡ ወረቀት የጨርቅን ስፍራ ይወስዳል፤ እንዳለ የገንዘቡን ባለቤት ስም በእሽጉ ላይ ይጽፍበታል፡፡ ቀስ በቀስም የካዝናው ቁልፍ እጁ ይገባል፡፡ ያንን አምጣ፤ ይህን ውሰድ ይባላል፡፡ የሚከተለውን መገመት ከባድ አይደለም፡፡ እንድሽ አንዱን የወረቀት እሽግ ይከፍትና አንድ ቅጠል፤ ቆየት ሲል ሁለት ሳብ ያደርጋል፡፡ ከየት አመጣህ? ስለው አባቴ ሰጡኝ፣ እገሌ ሰጠኝ እያለ ይነግረኛል፡፡ የአባባ አሶሬ ወዳጅ ለመሆን የሚጥረው ብዙ መሆኑን አይ ነበርና እንዳለ የሚነግረኝን የምጠራጠርበት ብዙ ምክንያት አልነበረኝም፡፡ ውሎ አድሮ

እውነተኛ ምንጩን ነግሮኝ ከሆነም፣ መቼ እንደነገረኝ በውል አላስታውስም።

እራሴም ብሆን መልአክ ነበርኩ ለማለት አይደለም። አንድ ቀን አባባ ለእንጀራ እናቴ ለእልፍነሽ ገንዘብ እንድሰጥ ያስረክቡኛል። ከውስጡ ትንሽ ቆንጥሬ አስቀራለሁ። ይደረስበትና ለምን ወሰድክ? ብባል የሆነውን ያልሆነው ቀበጣጠርኩ። ደብተርም እንደገዛሁ ገለጽኩ። ገንዘብ ሲያስፈልግህ ጠይቅ እንጂ በአደራ የተሰጠኽን በምንም ዓይነት አትብላ ወይም አታስቀር ተብዬ ተነገረኝ። ሌላ ጊዜ ደግሞ ለጸጉር መስተካከያ ሃያ አምስት ሳንቲም ቢሰጠኝ በዐሥር ሳንቲም ጣሳ ቁርጥ ተቆርጬ እመጣለሁ። ይታወቅብኝና ሌላ ግሳጼ ይደርስብኛል። አሁንም፣ ፍራንክ ስትፈልግ ጠይቅ እንጂ የቅጥፈቱ ጎዳና ይቅርብህ ተብዬ ግሳጼ ከምክር ጋር ይለገሰኛል። ልጆቼን ሳሳድግ አንድ ስከተለው የነበረ ፖሊሲ ትርፍ ገንዘብ እጃቸው እንዲገባ አለማድረግ ነበር። በአንጻሩ ግን ለዚህ ጉዳይ ገንዘብ ያስፈልገናል ይሰጠን ካሉ ብዙም አልጫናቸውም ነበር። ፖሊሲው ለኔ ሠርቷል። በተጨማሪም እግረመንገዳቸው የተማሩልኝ ገንዘብ ፍላጎት ማሟያ መሣርያ እንጂ በራሱ የሚመለክ ወይም የሚሰገድለት ነገር እንዳልሆነ ነው። ደጎችና ለሰው አዛኞች ስለሆኑ የደጉ አባታችን ስራጋ አምላክ ይጠብቃችሁ እያልኩ እመርቃቸዋለሁ።

እኔና እንዳለ ከፍቅራችን ብዛት የተነሳ መንገድ ስንሄድ እንኳ አንገት ለአንገት እየተቃቀፍን ነበር። ከቤታችን ያመጣነውን ቆሎ አንደኛችን ኪስ ውስጥ አጋብተን ነበር ከዚያ እያወጣን የምንቆረጣጥመው። አብዛኛው ሰው ይህን ስለሚያውቅ ከረሜላ መግዣ የሚሰጠን ለሁለታችሁም እያለ ነበር። እኔና እንዳለ አብረን መሆናችንን ዕያየች ለእንዳለ ለብቻህ ይሁንህ ብላ ሳንቲም የሰጠችውን ሴት እስከዛሬም ልቤ እንደሸፈተባት ነው።

እንዳለ ከየትም ያምጣው ከየት ገንዘቡ ሁሉ የጋራ ንብረታችን ነበር። ፓስቴ እንበላበታልን፤ ከረሜላ እንገዛለን፤ ሻይ እንጠጣለን፤ ሲኒማ እንገባለን። ከዕለታት አንድ ቀን ሲኒማ ዐይተን ስንመለስ ትራፊ ቅንስናሽ ገንዘብ እኪሱ

ውስጥ እየተንቻቻ ያስቸግረዋል፡፡ ቤት ከተገኘብኝና ከየት አመጣኸው ከተባልኩ መልስ ስለሌለኝ ምን ላድርገው? ይለኛል፡፡ ያሉንን አማራጮች ጠልቀንም ሳንመረምር ሳንቲሞቹን ከኪሱ አፍሶ አወጣና ጥቅጥቅ ካለው ዘውዴ ግቢ ባሕር ዛፎች ውስጥ ጭንቀት ለምኔ ብሎ በተናቸው፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን እኔ ትምህርቴን ከመከታተል ወደኋላ አላልኩም፡፡ በትምህርት ጎበዝ የነበረው እንዳለ እየደከመ ሄደ፡፡ የአባባ አሶሬም ብራቅነት ድንጉጥ አደረገው፡፡ አንድ ቀን፣ አንደኛ ክፍል ሆነን፣ ትምህርት ቤት በራፍ እንደደረስን እንዳለ የቀኝ ኋላ ዞሮ በእሩጫ ነጎደ፡፡ ተከተልኩት፤ ግን መድረስ አቃተኝ፡፡ ትምህርት ቤት ውዬ ስመለስ ቅድም ምን ሁነህ ነው የከነፍከው? ብዬ ብጠይቀው “አላየህም እንዴ? ጎፈር እኮ በጉማሬው ሊገርፈኝ ሲል በሩጫ አመለጥኩት” አለኝ፡፡ አስፈሪው ጎፈር፣ የትምህርት ቤታችን ዘበኛ፣ በእውን ብቻ ሳይሆን በሐሳቡም እንደሚያስበረግገው ተረዳሁለት፡፡

አባባ አሶሬን ከልጆቻቸው በመጠኑም ቢሆን ሊቋቋማቸው የሚሞክር ይልማ ነበር፡፡ በእግራቸው ተተክቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ቤቱን የሚያስተዳድረው እሱ ነበር፡፡ አንድ ቀን ቤታቸው ጉንዳን ይገባና ቤተሰቡን ያስጨንቃል፡፡ ጉንዳን ጎማ ሲጨስበት ጠልቶት ይሸሻል ስለሚባል አባባ አሶሬ ይልማን ይጠሩትና ሂድና ጉማ አምጣ ይሉታል፡፡ ትእዛዙ ያልገባው አስመስሎ ወፍራም ዱላ ፈልጎ ያመጣላቸዋል፡፡ ትእዛዜን በትክክል አትሰማም ማለት ነው? እኔ ያልኩህ ጉማ ነው ብለው ያንባርቁበታል፡፡ “አባዬ፣ ይሄ እኮ ጉማ ነው” ካላቸው በኋላ፣ መለስ አድርጎ፣ “አሁን ገና ገባኝ፤ ለካስ የፈለጉት ጎማ ነበር” ይላቸዋል፡፡ ጉማ በጉራጌኛ ዱላ ማለት ነው፡፡ “አንተ፣ የትናንት ውልድ ትሞከሙከኛለኽ እንዴ?» ይሉታል፣ “ትኮምከኛለህ እንዴ?” ሊሉ ፈልገው፡፡

ስለ እንዳለ ለማጠቃለል፣ ዋለ አደረ እንጂ የገንዘብ ጉድለት ጥያቄ አፍጦ መምጣቱ አልቀረም፡፡ የትምህርት ደረጃችን ሲለያይ የጓደኞቻችንም ዓይነትና የሕይወታችን አቅጣጫ እንደዚሁ እየተለያየ ሄደ፡፡

አካባቢያችን የነበሩት የጉድጓድ ውሃዎች ለመጠጥነትም ሆነ ለልብስ ማጠቢያ አይሆኑም ነበርና መንደረተኛው ውሃ የሚያገኘው ውሃ ካስገባ ሰው እየገዛ ነበር፡፡ ቧንቧ ውሃ አካባቢው ከመድረሱ በፊት ደግሞ፣ ጥሩ ነው የተባለ ጉድጓድ እየተፈለገ ይገዛ ነበር፡፡ ሰፈራችን የቧንቧ ውሃ መጀመሪያ የገባው እነአባባ አሶሬ ቤት ይሁን እንጂ ውሃ ይሸጡ እንደነበር አላስታውስም፡፡

እራሴን በተመለከተ ትምህርት ቤት ስሄድ የምቀያይረው ልብስ ስላልነበረኝ ቅዳሜ በመጣ ቁጥር ያለችኝን ማጠብ የግድ ነበር፡፡ ውሃ ለመግዛት እንደማንኛውም መንደረተኛ ራቅ ብዬ መሄድ ነበረብኝ፡፡ በውሃ የተሞላውንና የቁመቴ አጋማሽ የሚሆነውን ባልዲ አንጠልጥዬ ስግተረተር ከእግሬ ጋር እየተጋጨብኝ አሽመድምዶ የሚፈታተነኝ ይመስል ነበር፡፡ አንድ ቀን፣ እንደተለመደው ውሃ ሳመላልስ አባባ አሶሬ በራፋቸው ተቀምጠው ያስተውሉ ኖሮ የእንዳለን እንጀራ እናት ወይዘሮ አፀደን ይጠሩና ከዛሬ ጀምሮ ታደሰ ልብሱን ለማጠብ የሚያስፈልገው ውሃ በነጻ ይውሰድ ብለው አዘዙልኝ፡፡ ባልሳሳት እኛ ቤት ውሃ ያስገባነውን ከእነአባባ አሶሬ ጥቂት ዓመታት ዘግይተን ስለነበር ያቃለሉልኝ ሸክም ቀላል አልነበረም፡፡

አንድ ቅዳሜ ቀን ልብሴን በብረት ምጣድ ላይ አድርጌ ሳጥብ የመንደሩ ሕፃናት አጠገቤ ተኮልኩለው ይጫወታሉ፡፡ ከመካከላቸው በኩረ ይገኝበታል፡፡ በኩረ የአባባ አሶሬ የልጅ ልጅ፣ የአብሮ አደጌ የአበበች የበኩር ልጅ ነው፡፡ አባቱ ጋሼ ወልደየስ ከመንደሩ ነዋሪዎች ሠልጠን ያለ ነው፤ አማርኛ ማንበብና መጻፍ ይችላል፤ ክራቫትና አንገቱ ላይለያዩ ተማምለዋል፡፡ የመንደሩ ሕፃናት ከበኩረ ጋራ ሲነጻጸሩ በዕድሜ እንጂ በአለባበስና በምቾት አጠገቡ አይደርሱም፡፡ በኩረን መጫሚያ አይለየውም፣ ሌሎች ግን በጫማ ስለመሄድ በሐሳባቸው ወይም በሕልማቸው እንጂ በእውናቸው አያውቁትም፡፡

በተጠቀሰው ዕለት በኩረ እንደሌሎቹ ሕፃናት መሆን ፈለገና ጫማውን አወለቀው:: ጓደኞቹ እግሩን አፈር ሲነካው ሲያዩ ከመደንገጣቸው የተነሳ በአንድ ላይ ግር ብለው "እትዬ አበቡ! እትዬ አበቡ!" እያሉ በኩረን ጥለው ወደ እሱ ቤት ነጎዱና እያለከለኩ ደረሱ:: ምን ሆናችሁ ነው? ተብለው ሲጠየቁ መልሳቸው "በኩረ ጫማውን አውልቆ በባዶ እግሩ እየሄደ ነው" የሚል ነበር:: ዕድሜ ልካቸውን በባዶ እግራቸው የሚሄዱት ሕፃናት በጫማ መሄድ ሰልችቶት እነሱን መምሰል ለፈለገው ለዕድሜ ጓደኛቸው አዝነው፣ እግሩን አፈር ስለነካው ተቆርቁረው ወላጅ እናቱ ከዚህ አዘቅት ጎትታ እንድታወጣው ለመማጸን የልጅነት ጨዋታን ያህል ነገር መስዋዕት አድርገው ሲሽቀዳደሙ ሳይ በጣም ተገረምኩ:: በኑሮ ደረጃ መውጣት እንጂ መውረድ አስከፊ መሆኑ የልጅነት አእምሮዋቸው ደርሶበት ይሆን? ወይስ ድህነት ብሎም በባዶ እግር መሄድ ለእነሱ አስቀድሞ የተበየነ? በኩረ ግን ከእርግማኑ የተከለለ ነው ብለው አምነው ኖሯል? ያም ተባለ ይህ ድርጊታቸው ዘወትር ሲገርመኝ ይኖራል::

ሌኒን በጭቆና ቀምበር የተጠመዱትን ነጻ ላወጣ ነው ብሎ አድማጭ ሰብስቦ በሚያስተምርበት ወይም በሚያነቃበት ወቅት ዘወትር ሸክ ያለ ልብስ ይለብስ ነበር ይባላል፤ ሰደርያና የደረት ኪስ መሐረብ አይለዩት እንደነበረ ይነገራል:: አንድ ቀን እንደተለመደው የኑሮ ሸክም ክብደቱ ያሽመደመዳቸውንና የታረዙ ደንበኞቹን ሰብስቦ ሲቀሰቅስ ከመካከላቸው አንዱ በሌኒንና በተሰብሳቢዎቹ መካከል የነበረውን የአለባበስና የወዝ ልዩነት ከተመለከተ በኋላ "የኛ መምህር ሌኒን፤ አንተ አታላይ ሳትሆን አትቀርም፤ እኛን አትመስልም፤ ለእኛ የቆምክ ልትሆን አትችልም፤ አለባበስህና ገጽታህ ይመሰክራሉ፤ ለኛ የቆምክ ብትሆን ኖሮ እኛን መስለህ በቀረብከን ነበር" ይለዋል:: ሌኒን ለቀረበለት አፍራሽ ትችት አጥጋቢ መልስ መስጠት ከተሳነው በሩስያ አብዮት ለማምጣት የነበረው ዕቅድ ሊዳፈን እንደሚችል ተረዳ:: "ስማ፣ ወድንሜ" አለ ሌኒን፣ "የኔ ዓላማና ትግል እናንተን እኔ ወዳለሁበት ደረጃ ጎትቼ ለማውጣትና ለማደላደል ነው እንጂ እራሴን

እናንተ ወደ ተዘፈቃችሁበት አዘቅት ለማውረድ አለመሆኑን ተረዱልኝ" አላቸውና የአብዮቱን እንቅስቃሴ ማፋፋም ቻለ ይባላል፡፡

በኩረ እንጂ እኛ ጫማ ለማጥለቅና የተሻለ ኑሮ ለመኖር ያልታደልን ነን ብለው እራሳቸውን በራሳቸው የኮነኑትን እነዚያን ጮርቃ ሕፃናት እናንተም እንደበኩረ ጫማና ሌላም ነገር ከማግኘት የሚያግዳችሁ ምንም ኀይል ሊኖር አይችልምና አይዞዋችሁ፣ በርቱ ብሎ እንደ ሌኒን ሰብስቦ የነገራቸው ወይም የመከራቸው አልነበረም፡፡ ችግርና ስቃይ በሚንሰራፋበት አካባቢ የሚፍተለተለው ሕይወትን ስለማቆየትና ቀንን ስለመግፋት እንጂ ስለወደፊት ተስፋና የተሻለ ኑሮ ስለመኖር አይደለም፡፡ ለዚህም ሊሆን ይችላል በኩረ በትጋት ተምሮ የማስትሬት ዲግሪ ለማግኘትና የተዋጣለት መሀንዲስ ለመሆን ሲበቃ እነዚያ አብረውት አፈር ሲፈጩና ጭቃ ሲያቦኩ ያደጉት ጓደኞቹ ግን አብዛኞዎቹ ወይ ከመሬት አልተነሱም አለበለዚያ ያ ለበኩረ ከተጸየፋለት አፈር ጋር ተደባልቀዋል፡፡ መጽሐፉ “ላለው ይጨመርለታል፣ ከሌለው ግን ይወሰድበታል” ያለው የበኩረንና የጓደኞቹን ታሪክ የሚሸፍን ይመስለኛል፡፡ እነሌኒን በትግላችን ሁሉንም እኩል እናደርጋለን፤ የሰው ልጅ ሕይወት የተሟላ እንዲሆን መንገድ እንቀይሳለን ያሉት ከንቱ ሆኖ መቅረቱን በሂደቱ ወላፈን ተጠብሰን ያለፍን ሕያው ምስክሮች ነን፡፡ ቢሆንም፣  እነሌኒን ለሰው ልጅ በጎ በማሰባቸው ብቻ ታሪክ ነጻ እንደሚያወጣቸው አምናለሁ፡፡

የአባቴና የአባባ አሶሬ የንግድ መደብር ጐን ለጐን ነበር፡፡ የሚነግዱት ጌጣጌጥ፣ የቤተክርስትያንና የባሕል እቃዎች ነበር፡፡ የንግዱ አካባቢ ጉትቻ ተራ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ጌጦቹ ከብር፣ ከንኬል፣ ከመዳብ፣ ከነሐስ፣ ከቆርቆሮ፣ ከአሉሚንየም የተሠሩ ናቸው፡፡ የጆሮ ጉትቻ፣ የአንገት አሸንክታብና ድሪ፣ በያይነቱ የአንገት መስቀል፣ የእግር አልቦ፣ የጣት ቀለበት፣ የአንገት ቀለበት፣ የእጅ አንባር፣ በጸጉር ላይ የሚሰካ ወለባ ይይዛሉ፡፡ እንዲሁም ከብረት የተሠራ ወስፌ፣ ሾህ መንቀያ ወረንጦ፣ ከአሉሚንየም የተሠራ የጆሮ ኩክ ማውጫ ይሸጣሉ፡፡ ቁሳቁሶቹ የሚሠሩት

በተለያየ ስፍራ በሚገኙ አንጥረኞች ወይም የእጅ ዕውቀት ሙያተኞች ነው:: ለምሳሌ አቶ ኃይሌ ሲደልል ዕውቅ የአንገት መስቀል ሠራተኛ ናቸው:: አቶ ውቤ ደግሞ በአንገትና ጣት ቀለበት ሠሪነታቸው የታወቁ ናቸው::

ጉትቻ ተራ ከሚነገዱ የቤተክርስትያን እቃዎች፣ ጸናጽል፣ መስቀሎች በያይነቱ፣ መቋሚያ፣ ጭራ፣ ከበሮ፣ ደወልና ጉልላት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ከሚነገዱት የባሕል እቃዎች መካከል ከጎሽ ወይም ከበሬ ቆዳ የተሠራ ልሙጥ ወይም የተለበጠ ወይም የተለበደ ጋሻ፣ ጦር፣ ጎራዴ፣ ጨቤ፣ ወደ ጦር ሜዳ ሲኬድ በትከሻ የሚንጠለጠል የድቁስ በርበሬ መያዣ ቀንድ፣ ከቀንድ የተሠራ ዋንጫ፣ መለኪያና ማንኪያ ይገኙበታል:: በጉሬዛና በሜዳ አህያ ቆዳም ይነገድ ነበር::

ነጋዴው ሸቀጥ ወደ እቃ አንጥረኛው ወይም ጥበበኛው ዘንድ በመሄድ አለበለዚያም መደብሩ ድረስ መጥቶለት ይገዛል:: ቅዳሜ ጠዋት በየአንጥረኛው ቤት እየዞርኩ ከአባቴ ጋር የተዋዋሉትን እቃ እየተረከብኩ ወደ መደብር እወስድ ነበር::

አቶ ውቤ ዘንድ ስላክ፣ ጌጥ ሲሠራ ብዙ ጊዜ ያጋጥመኝ ነበር:: ሠላሳ ሳንቲሜትር ያህል ከመሬት በታች የተቆፈረ ጉድጓድ ከሰል ይሞላና በመሬት ውስጥ በተቀበረ ወናፍ ኃይል በሚነድ እሳት ከጭቃ የተሠራ አነስተኛ ሾጣጣ ኩባያ ፍም እስኪመስል ድረስ ይግላል ወይም ይጠበሳል:: ጌጡ የሚሠራው ከነሐስ ከሆነ፣ ቁርጥራጭ የነሐስ ብረት ኩባያው ውስጥ በረጅም የብረት ወረንጦ እየተለቀመ ይጣልና ሙሉ በሙሉ እስኪቀልጥ ድረስ የእሳቱ መናፋት ይቀጥላል:: ከዚህ ሥራ ጎን ለጎን ደግሞ፣ መጠኑ የሙሉ ሰው እጅ የሚያክል፣ አራት ማእዘን ቅርጽ ኖሮት ጎኑ ጠባብና ቁመቱ ረዘም ያለ፣ ለሁለት ተከፋች ሆኖ እመጋጠሚያው ላይ ፈሳሽ የማንቆርቆርያ ቀዳዳ ያለው የብረት መያዣ ይዘጋጅለታል:: የመያዣው

የላይኛው ክዳን ይነሳና በታችኛው አቃፊ የከሰል ዱቄትና የእንጨት ፍቅፋቂ ድብልቅ ይሞላል:: የድብልቁ አቀማመጥ ወጣ ገባ ሳይኖረው አንድ ወጥ ወይም ጠፍጣፋ እንዲሆን ከተስተካከለ በኋላ ለመሥራት በተፈለገው ጌጥ አይነት ሙሌቱ ላይ፣ የመሀሉን ግራና ቀኝ ይዞ፣ ጫን እየተደረገ ቦታው የፈቀደ ያህል ቅርጾች ይታተማሉ:: የሚሠራው እያንዳንዱ ቅርጽ ጥልቀቱ የማተሚያውን ጌጥ ውፍረት እንዲይዝ ይደረጋል:: ይህ ማለት፣ የቅርጽ ማውጫው ጌጥ አናቱ ከጠፍጣፋው መደብ እኩል፣ ከፍ ወይም ዝቅ ሳይል፣ ቀበር ይደረጋል:: ከዚያም በቀዳዳው ትይዩ መሀል ለመሀል የሚወርድ አንድ ዋና ቦይና እያንዳንዱን ቅርጽ ከዋናው ቦይ ጋር የሚያገናኙ ቅርንጫፍ ቦዮች ይተለማሉ:: ከዚያም መያዣው ይከደንና የኩባንያው ከንፈር በጉጠቱ ተይዞ የቀለጠው ነሐስ በቀዳዳው ውስጥ እስኪሞላ ድረስ ይፈሳል:: ፈሳሹ ነሐስ የተተለመለትን ጎዳና ወይም ቅያስ ተከትሎ ይሄድና ይረጋል:: ከዚያም፣ የመያዣው ሆድ እቃው መሬት ላይ ይዘረገፍና የከሰልና ፍቅፋቂ ድብልቁ ከፊት ከፊት ተደርጎ ተያይዘው የወጡት ጌጦች ጆሮዋቸው በብረቱ ወረንጦ እየተያዘ ተቀርፈው እንዲለያዩ ይደረጋል:: በቦዮቹ ውስጥ የረጋው ነሐስ ደግሞ እንደገና ይቀልጣል:: በዚህ ዓይነት፣ መያዣው ደጋግሞ እየተሞላና እየተዘረገፈ፣ ነሐስ እየቀለጠ የሚፈለገው የጌጥ ቁጥር እስኪገኝ ድረስ ሥራው ይቀጥላል:: ጌጦቹ በሞረድ ከተስተካከሉና ከለዘቡ በኋላ በጎድጓዳ ብረት ሳሕን ውስጥ ይኮላሉ፣ ማለትም ተነክረው ይታጠባሉ:: በብር ውሃ የተኮላው የብር መልክ ይዞ ይወጣል፤ በወርቅ ውሃ የተኮላው እንዲሁ ወርቅ መስሎ ቁጭ ይላል::

ጌጡ ተሽጦ በተጠቃሚ እጅ ከገባ ከወራት በኋላ ኩሌቱ ቀስ በቀስ ይገፍና ወይም የተቀባው ቀለም ይለቅና የተሠራበት ብረት እውነተኛ ማንነት አግጦ ብቅ ሲል፣ ያለው እድል መጣል ወይም ሸክም ተብሎ እየተናቀ መኖር ነው:: ብረት፣ ቆርቆሮና አሉሚንየም ስለማይኮሉ ማንነታቸው ከስር መሠረቱ ስለሚታወቅ፣ ከጊዜ ጋር ስለማይለዋወጡ፣ ጊዜ ስለማይሸራቸው ተከብረው፣ ዋጋቸውን ጠብቀው ይኖራሉ:: ችግር የሚገጥማቸው በኩሌት ኃይል ያልሆኑትን ሆናችኋል የሚባሉት ናቸው:: ይህ ሐቅ ለብረታብረት

ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅንም የሚመለከት ስለመሆኑ የሕይወት ልምድ አስተምሮኛል፡፡

ማታ ማታ አንድ መደበኛ የቤት ሥራችን የንኬልና ብር ጌጦችን ማስረጀት ነበር፡፡ ከአንጥረኛ የተገዛ የንኬልና የብር ጌጥ የኩራዝ ጭስ እንዲጠግብ ይደረግና ዘይት በጠገበ ጨርቅ ማሩኝ እስኪል ድረስ ተደጋግሞ ይታሻል፡፡ በመጨረሻ አሮጌ መስሎ ቁጭ ይላል፡፡ አዲስ አበባን የጎበኘ ቱሪስት ጉትቻ ተራን ሳይረግጥ አይሄድም ነበርና አሮጌ ጌጥ ውለዱ ሲል ጭስና ዘይት የጠገበ ንኬል ወይም ብር ይቀርብለታል፡፡

አንጥረኛና ነጋዴ ሲጨቃጨቁ ማየት የተለመደ ነበር፡፡ አንጥረኛው የቅድሚያ ክፍያ ወስዶ እቃ አያቀርብም ወይም ከናካቴው ይሰወራል፡፡ ነጋዴው ደግሞ በዱቤ ለገዛው እቃ ሒሳቡን ወቅት ጠብቆ አይከፍልም፡፡ እቃው ስላልተሸጠ ገንዘብ አላገኘሁምና ምን ላድርግ? እያለ ምክንያት ይሰጣል፡፡ እኔ ቅዳሜ አንጥረኛ ዘንድ እመላለስ የነበረው አንድም ቀብድ የተከፈለበትን እቃ እጅ ለማስገባት ነበር፡፡ ዐዋቂዎች በተዋዋሉት መሠረት ቃላቸውን እንዴት አያከብሩም? እያልኩ ዘወትር እገረም ነበር፡፡ ቢሆን ኖሮ ለተማሪ ጣፋጭ የሆነውን የቅዳሜ ጠዋት እንቅልፍ አልቀማም ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን መደብር ከእንዳለ ጋር ተቀምጠን ሳለ የምናውቀው ልጅ ሲያልፍ ሰላም ስንባባል አባባ አሶሬ ያያሉ፡፡ እንዳለን፣ ሳያመልጥህ ተከተለውና ጋብዘው ብለው ገንዘብ አስይዘው ሰደዱት፡፡

የዕድል ነገር ሆኖ አባባ አሶሬ የሚታወቁት ከደግነታቸው ይበልጥ በቁጡነታቸው ነበር፡፡ ከገበያተኛ ጋር በዋጋ መጨቃጨጭ ስለማይወዱ፣ ዋጋቸውም ብዙም ውጣ ውረድ ስለሌለው ቋንቋቸው ካልተስማማህ ጥለህ ሂድ ነው፡፡ ባንድ ሰው ከተናደዱበት “ይሄ የተለከፈ” ብለውት ነጠላቸውን አንዘርፍፈው መሬት ለመሬት እየጎተቱ ጥለውት መሄድ ነው፡፡ ኃይለኛ ትክ ትክ ያጠቃቸው ስለነበር በጣም በተናደዱ ቁጥር ስለሚነሳባቸው ነገሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ይሆንባቸዋል፡፡

ወጣቱ ክፍል ሌላ እድርና እቁብ እያቋቋመ ከልብ የሚያውቋቸው ሽማግሌዎች ሲቀሩ፣ አባባ አሶሬን ቀስ በቀስ እየጣላቸው ገለል ማለት ጀመረ:: አሮጌው በአዲስ ሲሻር ዐየሁ:: ቀጥተኛነት ብቻውን በቂ እንዳልሆነ ተመለከትኩ:: ልጅ ብሆንም አድናቂያቸው ነበርኩ:: በውሃው ምክንያት ብቻ ሳይሆን ከአብዛኛው ሰው የበለጠ ያወቅኋቸው ወይም የተረዳኋቸው ይመስለኝ ስለነበር ነው፤ ሁለት ቋንቋ፣ ቅጥፈት፣ ነገር ወዲያ ወዲህ ማሳከር ወይም ማምታታት፣ ንዝህላልነት በጭራሽ አይወዱም ነበር:: አባቴ የዋሁ ስራጋ ቢሆኑም እንደማንኛውም የኢትዮጵያ መንደር አሳዳጊዬ መንደርተኛው በሙሉ ስለነበር አባባ አሶሬ ጥለውብኝ የሄዱት ትዝታ ዘላለማዊ ነው::

አባባ አሶሬ አብዛኛውን ጊዜ ቁጡ ይሁኑ እንጂ ቀልድ ሲያልፍ አይነካቸውም ነበር ማለት አይደለም:: መልካቸው ጠይም፣ ዐሣ መሳይ፣ ስልክክ ያለ ፊትና ፈገግ ሲሉ የሚያማምሩ ጥርሶችና የደስታ ስሜት የሚያንጸባርቅ ግንባር ነበራቸው:: የሣቁ ቀን ሁሉም ይሥቃል:: በእርግጥ ይህ ክስተት የሚታየው እንደመስቀል ወፍ አልፎ አልፎ ነበር::

አንድ ቀን አባቴ ያመቱን ገብርኤል ለመሳም ወይም ደጅ ለመጥናት ሐረርጌ ቁልቢ ይሄዱና የእቁብ ገንዘብ ለመክፈል መዋያዬ፣ መጫወቻዬ ወደሆነው ቤታቸው በልበ ሙሉነት እሄዳለሁ:: ከየአካባቢው የመጣ የሙህር ተወላጅ ቤቱን ሞልቶታል:: ቆሎ ይቆረጠማል፣ ጠላ ይጠጣል:: የእማማ አጸደ ዋነኛ ተግባር ለእሁድ እቁብ መዘጋጀት ነበር ማለት ይቻላል:: እጣ ሲወጣ ለአባቴ ይደርሳል:: እቁብተኛው "ዕዩት የገብርኤልን ሥራ" እያለ አማተበ:: እኔም በልቤ ለካስ አምላክም እንደሰው የእጅ መንሻ ወይም ጉቦ የሚወድ መንፈስ ነው ብዬ ተገረምኩ:: አባባ አሶሬ ምንም ፈገግታ ሳያሳዩ "ታደሰ፣ በል፣ ዋስ ጥራና ገንዘቡን ውሰድ" ይሉኛል:: እውነት መስሎኝ ብድግ እልና፣ እዚህ ጋ ያሉት አባባ እገሌ፣ እዚያ የተቀመጡት አባባ እገሌ እባካችሁን ዋስ ሁኑኝ እላለሁ:: ቤቱ በሣቅ ፈነዳ:: አባባ አሶሬም ለሣቅ ከዳረጉኝ በኋላ አሳዘንኳቸውና ግድየለም ተቀመጥ አሉኝ:: ኀፍረቴን

ተከናንቤ ገና ቁጭ ከማለቴ አጠገቤ የነበረው ሰው፣ አርፈህ ተቀመጥ፣ የልጅ አዋቂ አንፈልግም ያለኝ በጣም አንገበገበኝ። ስሙንና መልኩን አሁንም አስታውሰዋለሁ።

ከመንደራችን ነዋሪዎች ሌላው ጎልተው ትዝ የሚሉኝ እማማ ሲጃት ናቸው። አዲስ አበባ የገቡት ከጣልያን ወረራ በፊት ቢሆንም አማርኛና እሳቸው ሳይስማሙ እስከመጨረሻው ዘለቋት። ነገሩ ለሁላችንም አስገራሚና ግራ አጋቢ ነበር። ከአገር ቤት አዲስ አበባ ገና እንደገባሁ ስምህ ማነው? ይሉኛል። ታደሰ ነው እላቸዋለሁ። ሌላ ማን ብዬ ልጥራህ? ይሉኛል። እንዴት እንደመጣልኝ ባላውቅም ቀኛዝማች እላቸዋለሁ። እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ቀኛዝማች እንጂ ታደሰ ብለውኝ አያውቁም። ታድያ ነገሩን የማያውቅና ከሌላ አካባቢ የመጣ ሰው ቀኛዝማች እያሉ ሲጠሩኝ ግራ ሲገባው አይ ነበር። የጃንሆይ ጆሮጠቢዎች ደርሰውበት ቢሆን ኖሮ "እኛ ያላጸደቅንልህ፣ ሽፍታ" ተብዬ ወኅኒ መውረዴ የማይቀር ነበር።

እማማ ሲጃት የሴት ልጃቸው የለዘብን ልጆች ካገር ቤት አዲስ አበባ አስመጥተው አሳድገዋል። እኔ በደንብ የማውቃቸው ክንፉንና አበራሽን ነው። ቀድሞ የመጣው ክንፉ ነው። ክንፉ የሚጠይቀውን ብቻ ሳይሆን ከዚም በላይ ከአያቱ ያገኛል። በምግብ፣ በልብስ ይህ ነው የማይባል ክብካቤ ይደርግለታል። እማማ ሲጃት ገበያ ከመውጣታቸው በፊት መግበውት ካልሄዱ የሞት ሞት ስለሚመስላቸው ዘወትር በጠዋት ይቀሰቀሳል። የክብካቤው መጠን ጉሮሮው ደረሰና ቋቅ ሊለው ሆነ። በወቅቱ እኔ የ0ሥረኛ ወይም የ0ሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ነኝ። እኔም እንደሱ በጠዋት መነሳት አለብኝ። ለመመገብ ሳይሆን ሰማንያ ደቂቃ የሚፈጀውን የእንጦጦ መንገድ በጊዜ ለመያያዝ ነው። ሳንቲም ካለኝ ሳይጠግብ ያደረውን ሆዴን አንድ ወይም ሁለት ፓስቴ አስተኛበትና ረጅሙን ጉዞ እያያዘዋለሁ።

ከዕለታት አንድ ቀን እንደተለመደው በጠዋት ተነስቼ ትምህርት ቤት ለመሄድ ስዘጋጅ ድምፅ  እሰማለሁ። መጀመሪያ የውሻ ወይም የድመት

ድምፅ መሰለኝ:: አላቋርጥ ሲል ጊዜ ድምፁ ወደ መጣበት አቅጣጫ ፊቴን ሳዞር ሰው ያየሁ መሰለኝና ጠጋ ብዬ ስመለከት ለካስ እንቅልፌን ተነፈግሁ ባዩ ክንፋ ኖሮዋል:: ምን ሆንክ? አልኩት:: ግጥም አድርጎ፣ ምንም ሳያወላውል "እባክህ እዚህ ቤት ቢበሉላቸው ቢበሉላቸው ምስጋና የላቸውም" ይለኛል:: ጆሮዬን ማመን አቃተኝና ትክ ብዬ ዐየሁት:: እዚሁ አፍንጫዬ ሥር እንደዚህ ዓይነት ዓለም አለ እንዴ? አልኩኝ:: በጣም በጣም ገረመኝ:: የክንፋ አባባል እስከዛሬም በጆሮዬ ያቃጭላል:: አባቴ ቤት እንደማይመቸኝ ስለሚያውቁ በሳንቲሞች ይደግፉኛል:: ብርሃኔም ከሩቅ አይዞህ ይለኛል::

አንድ ቀን ይልማና ክንፋ ተደብቀው ሲጋራ ሲያጨሱ የይልማ እናት ያዩዋቸውና እማማ ሲጃት ዘንድ ሄደው ክንፋ ሲያጨስ ዐየሁት ይሏቸዋል:: ይልማ እንደነበረበት ግን ይደብቃሉ:: እማማ ሲጃት ሲንደረደሩ ቤት ይገባሉ:: ክንፋ የቤት ሥራ ይሠራል:: "አንተ ክንፋ፣ ሲጃራ መጠጣት ጀመርክ እንዴ?" ብለው ያፋጥጡታል:: እንደተደረሰበት ሲያውቅ፣ ያያቱን ድክመት ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ለመሸጋገር ፈለገና "እማዬ፣ እኔ ሲጋራ ባጨስ እንደዚህ ማስመርያ ይስበረኝ" ይልና ይሰብረዋል፤ "እንደዚህ ወረቀት ይቅደደኝ" ይልና ይቀደዋል:: በዚህ ጊዜ እማማ ሲጃት አንጀታቸው ይንቦጫቦጭና፣ አዎን፣ ልክ ነህ፣ እኔን ካንተ ሊያጣሉ ፈልገው ነው እንጂ አንተ እንደዚህ ዓይነት ነገር እንደማታደርግ ዐውቃለሁ ብለውት ያርፋታል:: በካሳ መልክ ማስመሪያ እንዲገዛና በሄደበትም ያማረው ምግብ ገዝቶ እንዲበላና ለስላሳ መጠጥም እንዲጠጣ በቂ ገንዘብ ያስታቅፉታል::

እህቱ አበራሽ የታናሽ እህቴ ጽጌ የልጅነት ጓደኛ ናት:: ሁለቱ አንድ ቀን ተደብቀው ፓስቴ ሲበሉ ይታይና፣ ፓስቴ መብላት ለሴት ልጅ አስነዋሪ ነው ተብሎ ይታመን ስለነበር፣ ለእንጀራ እናቴ ለእልፍነሽ ይነገርባቸዋል:: የእንጀራ እናቴ ጽጌን ሙሽልቅ አድርጋ ከገረፈቻት በኋላ እማማ ሲጃት ዘንድ ሄዳ ጉዳቸውን ታረዳቸዋለች:: የጽጌን መገረፍ ትነግራቸዋለች::

እማማ ሲጃት አበራሽን ባስቸኳይ ያስፈልጓትና ቤት አስገብተው በሩን ይቀረቅሩታል:: ጋቢ አልብሰው ያስተኟታል፤ ምግብም ይመግቧታል:: ከቤት ውጭ ያለ ሰው እንዲሰማላቸው ዱላ ይዘው ባዶ አልጋ ድው ድው ያደርጋሉ:: ተሳስተው አካለ ጎደሎ እንዳያደርጓት የሰጋ ዘመድ ከውጭ ተኮልኩሎ እማማ እባክዎን ይበቃታል፣ ለዛሬ ይተዋት እያለ ይወተውታል:: አበራሽ ሣቅ አፍኗት አፏን በጨርቅ ሳትጠቀጥቀው አልቀረችም::

የኔና የክንፋ ችግር ሲመዛዘን እኔ ዕድለኛ ነበርኩ እላለሁ:: ክንፋ ከፈተና ጣጣ ተከለለ፤ እኔ ተፈትኜ ወጣልኝ:: ወንጌሉም የሚለው መቼ እንደምመጣ አታውቁምና ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ ነው:: እኔ ለፈተና ተዘጋጀሁ፤ ተፈተንኩ፤ አለፍኩ:: ክንፋን ይህ ዕድል ሳይገጥመው ቀረ:: ስለሆነም፣ የዛሬ አርባ አምስት ዓመት ከነበረበት ቦታ ፈቀቅ አላለም:: እማማ ሲጃት ካረፉ ከሃያ አምስት አመት በላይ ነው:: በክንፋ ሕይወት ያኔ ከነበረው አሁን ያለው ልዩነት፣ ጠዋት እየቀሰቀሰ ብላልኝ ብሎ የሚያስቸግረው ሰው ስለሌለ የጠዋት እንቅልፍ በማናለብኝነት ያለተቀናቃኝ ይለጥጠዋል:: ልጆቹም በዕድላቸው እያደጉ ናቸው::

የክንፋን እህት አበራሽን እንደ አባት ሆኜ ለአለማየሁ የሰጧት ወይም የዳርኳት እኔ ነኝ:: አበራሽና አለማየሁ በየጊዜው የባልና የሚስት ጥል ይጣላሉ፣ አበራሽ ዘላ እኔ ዘንድ ትመጣለች፤ እናስታርቃለን:: ችግራችሁ ምንድነው? ስንላት ቅናት ትለናለች:: አለማየሁ በበኩሉ ችግሩ ምላስ ነው ይላል:: ትዳራቸው እንዲፈርስ ስለማልፈልግ ማስታረቁ ሰልችቶኝ አያውቅም:: የአለማየሁ የነገር አባት ሆኖ አበራሽን የጠየቀለት ሽማግሌ ግን ሰልችቶት ኖሮ አንድ ቀን እኔ ዘንድ ይመጣና እናፋታቸው ይለኛል:: የወንድ ወገን ለሴት ወገን እንደዚህ ዓይነት ሐሳብ ማቅረብ ያልተለመደ ብቻ ሳይሆን አስገራሚ ሆኖ አገኘሁት:: ሰውዬው እኔ ዘንድ የመጣው አለማየሁ ጠይቆት አይመስለኝም:: ሰውዬውን አይሆንም ብዬ እመልሰዋለሁ:: ስለአበራሽ እሱ የማያውቀው እኔ የደረስኩበት አንድ

እውነታ ነበር፡፡ አበራሽ ታርቃ ቤትዋ ከመግባትዋ ለአሌ ምንም ሳታስቀር ሁሉንም ትዘረግፍለታለች፡፡ ስለሆነም፣ በመካከላቸው ገብቶ ላንዱ ማድላት ወይም ላንዱ ተቆርቋሪ መሆን ለግንኙነት ጤና አደገኛ መሆኑን አስተምራናለች፡፡

ይህን በተመለከተ ሙህር ሰፈር ሆኜ ከአጎቴ ከወልደሰንበት ጎራጋ ሚስት፣ ከእትዬ ወጉ፣ ትልቅ ትምህርት ቀስሜአለሁ፡፡ ወልደሰንበትና ወጉ ሁሌ ይጣላሉ፡፡ አሁንም ችግሩ ቅናትና ምላስ ነው ይባላል፡፡ አንድ ቀን ብርጭቆ ወርውሮ አናትዋን ክፉኛ ይተረክካታል፤ ደም እንደ ጎረፍ ይፈሳል፡፡ በቃ አሁንስ ተፋቱ ተባለ፡፡ የመንደር አዛውንት ለሽምግልና ተቀመጡ፡፡ ወጉ አልታረቅም፣ አሻፈረኝ ትላለች፡፡ በጥሞና ትለመናለች፡፡ ከእህትዋ ከእንጀራ እናቴ ከእልፍነሽ ጋር ሊመካከሩ ደጅ ይወጡና እልፍነሽ እንዳትታረቂ፣ ሞት ካልሽተተሽ በቀር፣ ብላ ትመክራታለች፡፡ ተመልሰው ሽማግሌዎቹ ዘንድ ሲቀርቡ ሊበስል መስሎ የነበረው ጉዳይ እንደገና ይገነትራል፡፡ ሽማግሎቹ እንደምንም ሃይ ሃይ ይሉና ወልዴ የተጣለበትን ካሳ ከፍሎ ያስታርቃሉ፡፡ ወጉ ተመልሳ ቤትዋ ከመግባትዋ እልፍነሽ አትታረቂ ብላት እንደነበር የወልደሰንበትን ክንድ ስትንተራስ ዘክዝካ ትነግረዋለች፡፡ ወልደሰንበት ከዚያን ቀን ጀምሮ እልፍነሽን እንደ ጠላቱ ነበር የሚያያት፤ እስከመጨረሻው ይቅርታ ያደረገላት አይመስለኝም፡፡ ያኔ ገና አንድ ፍሬ ልጅ ብሆንም ትምህርቱ ከልቤ ጠፍቶ አያውቅም፡፡ ባልና ሚስት ሲጣሉ ታረቁ እንጂ ተፋቱ ብዬ አላውቅም፣ ብሞት፡፡ ምኔ ሞኝ፡፡

ስለሙህር ሰፈር ሌላ የማስታውሰው ባንድ ወቅት የአባባ አሶሬ ሱቅ ጠባቂ የነበረውን ተክሉን አስመልክቶ ነው፡፡ ሱቁን በተለያዩ ጊዜያት ከጠበቁት በርካታ ሰዎች መካከል ተጠቃሹ በዕድሜ ከሁሉም አነስተኛ ነበር፡፡ ዱቤ ሲለምኑት ትንሽ ያንገራግርና የአዛኝነቱ ሚዛን እየደፋበት እሺ ይላል፡፡ ብዙዎች አልከፍል እያሉት ሲጨቃጨቅ ሲጣላ ዕናያለን፡፡ እንቢተኛውን ወደላይ በማንጋጠጥ ለፈጣሪው ዳርጎ ይተወዋል፡፡ ይህን ድክመቱን ያወቁ አንዳንድ ደንበኞቹ እንደምንም አባብለውና አግባብተው እቃ በዱቤ

ከወሰዱበት በኋላ ከጀርባው ስድባችንን ያቅምሰንና እንዲድበት እያሉ ሲሳለቁበት እንሰማ ነበር። በዚህና በሌላም ምክንያት ችግሮች ተደራረቡበትና ጭንቀት ውስጥ ይዋኛል። አንድ ቀን ሱቅ ብቅ ስል መስኮቱን ሊዘጋ ሲዘጋጅ ዐየሁትና "ተክሉ፣ እቃ ልታመጣ መሄድህ ነው እንዴ?" ብዬ እጠይቀዋለሁ። "አይደለም፣ ሱቁን ዘግቼ ሕይወቴን ላጠፋ ነው" ይለኛል። ሐሳቡን እንዲለውጥ ብዙ ለመንኩት፤ ተማጸንኩት፣ ተለማመጥኩት፤ የቆጡን የባጡን ቀበጣጠረኩ። አሻፈረኝ ብሎ መስኮቱን ለመዝጋት መቁረጡን ሳይ አካባቢውን ለቅቄ ሄድኩ። ከአንድ ሃያ ደቂቃ በኋላ ስመለስ ተክሉ የሱቁን መስኮት ከፍቶ፣ እጆቹን በደረቱ ላይ አቆላልፎ ሲቆዝም አገኘሁት። ስለተፋፈርን ቃላት የተለዋወጥን አይመስለኝም። በልቤ፣ አለህ እንዴ? አልኩት፣ እሱም እንደዚሁ በልቡ አዎን፣ ሐሳቤን ለውጫለሁ፣ ለማንኛውም ግን የማትረባ ነህ፣ እንዴት ለአንዱ ሳትናገር ዝም ብለህ ጥለኸኝ ትሄዳለህ? ሳይለኝ እንዳልቀረ እገምታለሁ። ነገሩን የሰማ ሁሉ ፈረደብኝ፣ ተገረመብኝ። እኔም የዚያን ዕለት ምን እንደነካኝ አላውቅም። ተክሉ ያኔ ቢሞት ኖሮ፣ ማን ያውቃል፣ የሱ ሕይወት አደብ መግዛት ተሳነሽ ተብላ ለመቀመቅ ስትዳረግ የኔም የወንድምሽ ጠባቂ መሆን አቃተሽ ተብላ ወደ አዘቅት ትወረወር ነበር። ተክሉ ለኔም ሲል ስለሰነበተልኝ ነፍሱ ጊዜዋ ደርሶ ሰማይ ቤት ስትሄድ አንቺ ቅብጥብጥ ተመለሺ ብሎ ቅዱስ ሚካኤል በር እንዳይዘጋባት እማጸንላታለሁ።

የሙህር ሰፈር ድንበርተኞች በስተምሥራቅ የደርጉ አባል የአለማየሁ ኃይሌ አያት የፊታውራሪ ገብረማርያም ግቢ፣ በምእራብና ደቡብ የሶዶ ጉራጌዎች መንደርና በሰሜን ደግሞ የንጉሥ ወልደጊዮርጊስ ግቢ ናቸው። ከሶዶ ሰፈር ደቡብና ምእራብ በጣልያን ወረራ ወቅት ዐይነስውሮችንና አካለስንኩሎችን ለማስፈርያ የተሠራ የጡረታ ሰፈር የሚባለው ትልቅ መንደር ይገኛል። ከጡረታ ሰፈር በስተሰሜን ደግሞ ከሐረር ከተማ ቀጥሎ ትልቁ የአደሬዎች መኖሪያ ሰፈር ነው።

የጡረታ መንደር ነዋሪዎች ከመንግሥት ቀለብ የሚሰፈርላቸው ቢሆንም አብዛኛዎቹ ለልመና እየተሰማሩ ገቢያቸውን ይደጉማሉ:: በዚያን ዘመን በተለምዶ ለለማኝ የሚሰጥ የገንዘብ መጠን አንድ ሳንቲም ነበር:: ጓደኛሞች ከትምህርት ቤት ወይም ከኳስ ጨዋታ መልስ ወጪ ወራጁን ለማየት ወይም ወሬ ለመከካትና ለመሰለቅ የጡረታ ሰፈርን ከኛ አካባቢ በሚለየው ሰፊ የአፈር ጎዳና አፋፍ ላይ በሚገኘው ቂጥ አርጥብ ብለን በሰየምነው ትልቅ ድቡልቡል ድንጋይ ላይና ዙሪያ ተኮልኩለን ዐይነስውር፣ አንካሳ፣ በእንፉቅቅ ወይም በምርኩዝ የሚሄድ ሽባ ዘወትር እናያለን:: ለልመና ተግባር ራቅ ብሎ መሄድ የተሳናቸው የኔቢጤዎች በጎዳናው አጠገብ ተኮልኩለው ይቀመጡና "ስለእመአምላክ፣ ስለበንተእግዚትነማርያም፣ ስለወላዲቷ" ሲሉ ማየትና መስማት ልምዳችን ነበር:: ልመናው አልሳካ ካለ ቋንቋቸው "በእግዚትነማርያም፣ በወላዲትዋ፣ ሞቶ በተነሳው" በሚለው ይተካል:: ገቢ በደንብ አልገባም ማለት ነው፣ ወደውግዘት ተሸጋገሩ እንባባላለን::

ከተማ ውለው የሚመለሱት ለማኞች አቅመ ደካማ በመሆን ራቅ ብሎ መሄድ ለተሳናቸውና በዋናው ጎዳና ተኮልኩለው ለሚቀመጡት የዕጣ ጓደኞቻቸው ከሰበሰቡት ምጽዋት እያካፈሏቸው ወይም እየሰጧቸው ሲያልፉ እናይ ነበር:: ለማኝ ለለማኝ ሲመጸውት ማየት ለኛ በጣም አስገራሚ ነገር ነበር:: የሌለው ለሌለው ሲያዝን ብንመሰክርም፣ በተገላቢጦሹ ዐይን ያለው በሌለው ሲጨክንም እናይ ነበር:: አንዳንድ ተንኮለኞች ልጆች ጎዳናውን ውሃ ረጭተው ካዳለጡት በኋላ ዳር ቁጭ ብለው ዐይነስውር እስኪመጣ ይጠብቃሉ:: የፈረደበት ዐይነስውር ሰማይ ደርሶ ሲፈርጥ እየተሣሣቁና እየቧረቁ ሲሸሹ እናይ ነበር:: ጥፋቱ የነሱ ብቻ ሳይሆን የኛም ጭምር ነበር:: አንደኛ፣ ክፉ ድርጊታቸውን ዝም ብለን እናይ ነበር፤ ሁለተኛ፣ ዐይነስውሮቹን አናስጠነቅቃቸውም ነበር፤ ሦስተኛ፣ ያላየን መስለን፣ ድምፅ አጥፍተን ትርዒቱን ለመቋደስ በአርምሞ እንጠባበቅ ነበር:: ጥፋቱ ከደረሰ በኋላ ግን ለይስሙላ "እነዚህ ባለጌዎች፣ አሳዳጊ የበደላቸው" እንል ነበር::

ጡረታ ሰፈር ግርጌ፣ የጎርፍ ውሃ ለሁለት የነደለው ረዥም ተረተር ነበር፡፡ የሰፈር ልጆች ተያይዘን እዚያ እንወርድና ሽርተቴ ስንጫወትበት እንውል ነበር፡፡ አጠገቡ ካለው ትንሽ ወንዝ ውሃ እንቀዳና እስኪጠግብ ድረስ እናፈስበታለን፡፡ በደንብ ከራሰ በኋላ አፈሩ ጠበቅ እንዲል እንደመድመዋለን፡፡ ፊትዋን ለጋ ቅቤ የተቀባች ሴት ወይዘሮ አስመስለን እስኪወዛ እናሚሸዋለን፡፡ ከዚያ የሸንተረሩን ቅርጽ ተከትለን የተረከዝ ስፋት ያለው ቦይ መሀል ለመሀሉ በጣታችን እንበጣለን፡፡ የመጫወቻው ስፍራ በዚህ መልክ እንደተዘጋጀ ለመብረር እንዳኮበኮበች አሞራ ክንዶቻችንን ወደጎን ዘርግተን የቀኝ ተረከዛችንን ቦዩ ላይ ተክለን መሬት አደራሽን፣ እፈለግሽው ድረስ ተሽክመሽ ውሰጅን፣ ብለን እየተከታተልን መንጎድ ነው፡፡ ከመካከላችን ሚዛኑን በደንብ መጠበቅ የሚችልና ደፋር የሆነው ራቅ ብሎ ይሄዳል፡፡ ከመርበትበት ይሁን በራስ ካለመተማመን የተነሳ ብዙም ሳይርቅ ወርዶ የሚከሰከሰው ከኋላ ተከትለውት የሚከንፉትን መንገድ ይዘጋባቸውና ይዟቸው ይወድቃል፡፡ ደጋግመን ከተንሸራተትን በኋላ ጨዋታው ሲያበቃ በጭቃ የተጨማለቀውን ልብሳችን ወንዙ ውስጥ አጥበን፣ በፀሐይ አድርቀን፣ ለብሰን ወደ መንደራችን እንመለሳለን፡፡ ቀኑ ፀሓያማ ካልሆነም በሰውነታችን ሙቀት ስለሚደርቅ እርጥቡን አንዳለ እንለብሰዋለን፡፡ ሽርተቴ የመቀመጫችን ጠላት በመሆኑ ቁምጣችን መሳሳት፣ ከዚያም መቀደድ የሚጀምረው ከኋላው ነበር፡፡ ስለሆነም፣ የሰፈራችን መርፌዎችና ክሮች ውሎአችሁ የት ነበር? ቢባሉ የኋላ ስናርስ ማለታቸው የማይቀር ነበር፡፡

የዩኒቨርስቲ ተማሪ ሆኜ የጂኦግራፊ አስተማሪያችን መስፍን ወልደማርያም የአፈር መሸርሸር መንስኤዎች ምንድናቸው? ብሎ ይጠይቀናል፡፡ ከታወቁት ከውሃ፣ ነፋስ ወዘተ ውጭ ሌላ አናውቅም ብንለው መንገድ እሠራለሁ እያለ ከመንገድ ግራና ቀኝ አፈር የሚሸረሽረውን የንጉሠ ነገሥቱን የመንገድ ሥራ ባለሥልጣንን እንዴት ረሳችሁት? ብሎናል፡፡ ጡረታ ሰፈር ግርጌ መጥቶ ሽርተቴ ስንጫወት ዐይቶን ቢሆን ኖሮ እኛንም በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ኅሊና ውስጥ ቀርጾ ያስቀረን ነበር፡፡

ሌላው ጨዋታችን የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ማንበብ ነበር፡፡ ጨዋታው ቁጥር በመከፋፈል ይጀምራል፡፡ ለምሳሌ 2፣ 6፣ ለአንዱ፣ 1፣ 4 ለሌላው ተጫዋች ይታደላሉ፡፡ መኪና መንገድ ዳር እንቀመጥና መኪና ባለፈ ቁጥር ያገኘነውን ቁጥር እንቆጥራለን፡፡ ከፍተኛ ድምር ያገኘው አሸናፊ ይባላል፡፡ ያየሁትን የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ለረጅም ግዜ የማስታወስ ልምድ ነበረኝ፡፡ አንደኛ አመት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ሆነን ፓትሪሺያ ሺሉንግ የምትባል የክፍል ጓደኛችን ነበረች፡፡ አባቷ አንድ ባለነጭና ሰማያዊ ቀለም አውቶሞቢል ነበረው፡፡ ከብዙ ዓመት በኋላ ያች አውቶሞቢል ቀለሟ ተቀይሮ አያታለሁ፡፡ አብረውኝ ለነበሩ ጓደኞቼ ያውላችሁ የፓትሪሺያ ሺሉንግ አባት መኪና እላቸዋለሁ፡፡ እንዴት አወቅህ? ቢሉኝ ታርጋው 1258 መሆኑን ነገርኳቸው፡፡ ይህ የትናንት ታሪክ ነው፤ ዛሬ ግን ትናንት ያየሁትንም ማስታወስ ትግል ነው፡፡ ሁሉም ነገር በጊዜው ነው፡፡

እንዳሁን አያድርገውና በዚያን ዘመን በርካታ የኳስ መጫወቻ ስፍራዎች ስለነበሩ በንጉሥ ወልደጊዮርጊስ ግቢና በየመንደሩ እየዞርን የእግር ኳስ ግጥሚያ እናደርግ ነበር፡፡ አንበላችን ክንፋ ተድላ እስካለ ድረስ የልብ ልብ ስለሚሰማን የምንሸነፍባቸው ወቅቶች በጣም ጥቂት ነበሩ፡፡ ወደ ላስቲክና ሽራ ከመሸጋገራችን በፊት የጨርቅ ኳስ የሚሰፋልን ክንፋ ነበር፡፡ የክንፋ አባት አባባ ተድላ ልብስ ሰፊ ነበሩ፡፡ የሚሰፉት እመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ነበር፡፡ እንደሳቸው አስተሳሰብ ዘመናዊ ትምህርት ቤት መሄድ ማለት ካቶሊክ መሆን ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ ክንፋና ታላቅ ወንድሙ ሳህሌ በዘመኑ አጠራር እንግሊዝኛ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ ተከለከሉ፡፡ ያባባ ተድላ ስፌት መኪና ገረገው ገረገጭ ትርርር ስትል የክንፋ ሥራ ደግሞ እሥራቸው ተቀምጦ ዳዊት ማነብነብ ነበር፡፡ የተሳሳተ ወይም የገደፈ እንደሆነ ኩርኩም ይቀምሳል፡፡ የቀኑን ንባብ ሲጨርስ ሥራው ከኛ ጋር የሚጫወትበትን ጨርቅ ኳስ ለማዘጋጀት ያመራል፡፡ ነገሩን ወደ ኋላ ሄጄ ስመለከተው ተማሪ ቤት ውለን የምንመለሰው ልጆች ኳስ ብቻ ሳይሆን በክንፋ ጊዜና ዕድልም እንደተጫወትን ይሰማኛል፡፡

ክንፉ የቡሄ አስተባባሪያችንና መሪያችንም ነበር፡፡ ለቡሄ ጨዋታ መጀመሪያ ያስገቡኝ በቀላሉ አልነበረም፡፡ ለቡሄ ጭፈራ አናስገባም ያሉኝ የልጆች ቁጥር በዛ ብለው ወይም በዕድሜዬ ማነስ ይሁን አላስታውስም፡፡ ደጋግሜ ብለምናቸው እምቢ ይሉኛል፡፡ ጓደኛዬ እንዳለ ገብቶ እኔ ልቀር አልፈለግሁም፡፡ ዘዴ አውጠነጠንኩ፡፡ እማማ ሲጃት ለቡሄ ልጆች ደኅና ገንዘብ እንደሚሰጡ፣ እኔንም እንደሚወዱኝ ዐውቃለሁ፡፡ እቤታቸው ድረስ እሄድና እነክንፉ ቡሄ ጭፈራ አላስገባም ስላሉኝ ገንዘብ አይስጡዋቸው እላቸዋለሁ፡፡ እሺ አሉኝ፡፡ ቀጥዬም መንደራችንን ፊት ለፊት ያሉትም ቤቶች እንደዚሁ እንዲተባበሩኝ ለመንኳቸው፡፡ እነሱም እሺ አሉኝ፡፡ እነክንፉ እንደለመዱት ሆያ ሆዬ፣ አስዮው ቤሌማ፣ የቤሌማ ጥጃ፣ አብረን እንጫጫ እያሉ በር ቆርቁረው እማማ ሲጃት ቤት ቢገቡ የምንሰጠው የለንም ተመለሱ ይባላሉ፡፡ ያልለመዱት ስለሆነ ግራ ይጋባሉ፡፡ ጨፋሪዎቹ ሲመጡ እኔን እዚያ ቆሜ አይተውኝ ስለነበር ሳይጠራጠሩ የቀሩ አይመስለኝም፡፡ የሚቀጥለው ቤት ቢሄዱ ተመሳሳይ መልስ ይሰጧቸዋል፡፡ ይሄኔ ጠጋ እልና ብታስገቡኝ ኖሮ ይሰጣችሁ ነበር እላቸዋለሁ፡፡ ና ግባ ተባልኩ፡፡

የቡሄ ጭፈራ ወይም ጨዋታ ነሐሴ ዐሥራ አንድ ማታ ይጀመርና ነሐሴ 13 ከረፋዱ ያበቃል፡፡ የተሰበሰበውን ዳቦና ሳንቲም እነሙሉጌታ ጉዲሳ ቤት እንከፋፈለዋለን፡፡ ገንዘቡ ተቆጥሮ ለተጨዋቾቹ እኩል ሲከፋፈል ዳቦው ግን ለሽሚያ ይዳረግ ነበር፡፡ እኔ ብዙውን ጊዜ መሻማቱን ስለማልወድ ፈንጠር ብዬ እመለከት ነበር፡፡ የሙሉጌታ እናት አንተም ተሻማ እንጂ እያሉ ሲያደፋፍሩኝ ትዝ ይለኛል፡፡

እኔና እንዳለ ባገኘነው ፍራንክ የሥዕል መሥሪያ ወረቀትና ዱቄት ቀለም እንገዛና ሥዕሎችን እንሠራለን፡፡ የሠራናቸውን ሥዕሎች አብዛኛዎቹን ስንሸጥ፣ የተቀሩትን ገንዘብ ይሰጡናል ብለን ለምናምንባቸው ሰዎች የእንቁጣጣሽ ዕለት አዙረን እንሰጣለን፡፡ በኔ በኩል እማማ ሲጃት፣ አክስቴ አስካለ መመርየና አባባ አሶሬ በመጀመሪያ ደረጃ ከማስቀምጣቸው ውስጥ ነበሩ፡፡ የሚሰጠን ገንዘብ ካሥር ሳንቲም እስከ አምሳ ሳንቲም ይደርሳል፡፡

የተሰበሰበውን ገንዘብ ጥቂቱን የፓስቴና የሳምቡሳ አምሮታችንን መወጫ ካደረግነው በኋላ አብዛኛውን መስከረም 18 ትምህርት ቤት ሲከፈት ደብተርና እርሳስ እንገዛበታለን።

ኳስ አዘውትረን የምንጫወትባቸው ስፍራዎች አንዱ ልዑል መኮንን ሆስፒታል፣ በደርግ ዘመን ጥቁር አንበሳ ተብሎ የተሰየመው፣ የተሠራበት ስኳር ሜዳ ነበር። ይህን ስም ያገኘው ከአፈሩ ኖራማነት የተነሳ ነበር። እግር ኳስ የምንጫወተው በባዶ እግር ስለነበር የምንጫወትበት ላስቲክ ኳስ ከመርገጫችን በላይ ያለውን የእግራችን ክፍል እየሰነጣጠቀ ኖራው እስንጠቁ ውስጥ ሲገባ ይውልና ሌሊት የሚያስከትለው የመለብለብ ስሜት በጣም ኃይለኛ እንደነበር አስታውሳለሁ። ሲነጋ ሕመሙ ስለሚረሳ ከስኳር ሜዳ ሊያስቀረን የቻለ የስዊድን ቡልዶዘር ብቻ ነበር። በስዊድን እርዳታ በተገነባው ሆስፒታል ከራስ እስከ እግር የታከመበት ሁሉ እድሜ ለስዊድን መንግሥትና ጽድቅ ለልዑል መኮንን ብሎ መርቋል። ቢሆንም፣ ስለሕፃናት መጫወቻ ስፍራ በሚገባ የሚታሰብበት ጉዳይ ባለመሆኑ አሳሳቢነቱ እየጨመረ መምጣቱን ሳይ አዝናለሁ። ልጅነት ያለጨዋታ የማይታሰብ ነው። በዚህ ረገድ ሕፃናት ያላቸውን መብት አሳንሶ ማየት ትልቅ ስሕተት ነው። ልጅነቱን የተቀማ ታዳጊ ወጣት ቂመኛ ሆኖ ስለሚያድግ ይህ ለማንም የሚበጅ አይደለም።

ስኳር ሜዳ አጠገብ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት መስበኪያ ግቢ ወይም ሚሲዮን አለ። ስሙም ሱዳን ኢንቲርየር ሚሽን ይባላል። ሰባኪዎቹ ከግቢያቸው ወጥተው መስበክ አይፈቀድላቸውም ነበር መሰለኝ ከውስጥ ሆነው አጥሩን ተደግፈው መጽሐፋቸውን ይይዙና በደንብ እንዲታዩ ድንጋይ ላይ ቆመው ኮማሪት ይመስል ወጪ ወራጁን በዐይን ያባብላሉ። ፕሮቴስታንቶች በማርያም ማማለድ ስለማያምኑ በዘመኑ ቋንቋ ፀረማርያም ስለሚባሉ ኦርቶዶክስ ክርስትያኖች ለፀረማርያሞች የነበራቸው ጥላቻ በጣም ከፍተኛ ነበር። አንድ ቀን፣ ረቡዕ ወይም ዓርብ ይመስለኛል፣ ስኳር ሜዳ ኳሳችን ተጫውተን ወደሰፈራችን ስንመለስ ሁለት ሰባኪዎች

እንደተለመደው አጥሩን ተደግፈው ቆመው ስናይ ሄደን እናድርቃቸው ተባባልን:: ወዳንዱ ጠጋ አልንና፣ መጽሐፍህ ምን ይላል? ብለን ጠየቅነው:: በምላሹ፣ ስለምን? ብሎ ጠየቀን:: ለምሳሌ፣ ስለጾም አልነው:: መጽሐፉ፣ የጾመ ባልጾመ አይሣቅ፣ ያልጾመ በጾመ አይሣቅ ይላል አለን:: እኛ እስከምናውቀው ድረስ ያልጾመ በቀጥታ ወደ ገሀነም ወርዶ ዘላለማዊ እሳት እንደሚንቦገቦግበት እንጂ አንድ ሰው ካልፈለገ ላይጾም ይችላል የሚለው ከፀረማርያምነት የበለጠ ኀጢአት ነው ብለን አሰብን:: የያዙትም መጽሐፍ ሰይጣን የጻፈው መሆን አለበት ብለን ገመትን:: መጽሐፉን አሳየን አልነውና ሰጥቶን አገላብጠን ብናየው እውነትም መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ዐየን:: ሁላችንም ወንጌል በግዕዝ አንብበናል፤ ግን ትርጉሙን አናውቅም:: ቀጥለን፣ ቅድም የነገርከንን ጥቅስ ዐሳየን አልነው:: ፈልጎ ዐሳየን:: በጣም ተገረምን፣ ተደነቅን::

እንደዘመዶቼ እኔም በጣም አክራሪ ኦርቶዶክስ ክርስትያን ስለነበርኩ በፋሲካ ዋዜማ ማክፈል የጀመርኩት ገና በልጅነት ነበር:: ማክፈል የጀመርኩበት ዘመን አባቴ ላክፍል ነው ስል ይሰሙና ዕድሜህ ለዚህ ገና ስላልደረሰ ቆይ ቢሉኝም አሻፈረኝ እላለሁ:: ዓርብ የስቅለት ዕለት ምግብ አዘጋጅታችሁ አሳድሩ፣ ነገ ጠዋት ሥራ ከመሄዴ በፊት አብልቼው እሄዳለሁ ሲሉ ሰማሁ:: እኔ ምኔ ሞኝ፣ ሳይነጋ ቀስ ብዬ በር ከፍቼ ወጣሁና ንጉሥ ወልደጊዮርጊስ ግቢ ባሕርዛፍ ውስጥ ተደበቅሁ:: ቢፈልጉኝ አጡኝ፤ አባቴም ወደሥራቸው አርፍደው ይሄዳሉ:: ማታ ሲመጡ ደከምከም ብያለሁ:: ምግብ አምጡ አሉና አፌን ከፍተው ሊያጎርሱኝ ቢሞክሩ እሞታታለሁ እንጂ እዚህ ደርሼ አልበላም አልኩ:: አባቴም፣ በሉ ተዉት፣ እንደፈለገው ይሙት አሉና ተዉኝ:: ዶሮ ጮሆ ከቤተክርስትያን መልስ ሲፈስክ ፈሳሽ በአፌ ተንቆርቁሮ ነው በእርግጥም ከሞት የዳንኩት:: በሚቀጥለው ዓመት ይመስለኛል አባባን ተከትዬ ፋሲካን በጸሎት ለመቀበል ተክለሃይማኖት ቤተክርስትያን ሄደን ሳለን ባጠገባችን ቄሶች ሲያልፉ ጋን ጋን ይሸተኝና "አባባ፣ ከትናንትና ጀምሮ ሊጠጡ ስለማይችሉ አፋቸው አሁን እንዴት ሊሸት ይችላል?» ብዬ ጠየቅኋቸው:: ልጄ፣ እግዚአብሔር እንደሚለው

እንጂ ቄሶች የሚያደርጉትን መከታተል አይጠቅምም አሉኝ:: አልተዋጠልኝም:: እኔ ትንሹ ልጅ እንኳ ሳከፍል እንዴት ያውም በቄስ ጉሮሮ ውስጥ ጠጅ ተንቆረቆረ? ለሚለው ጥያቄዬ መልስ ሳላገኝ ነው ጥያቄው እንደገና ተክልዬ ግርጌ በፀረማርያሞች አምባ እንደገና ብቅ ብሎ ለክህደት የዳረገኝ::

ቤት እንደደረስኩ ሠራተኛችን ታመቼን ከትናንትና የተረፈ ሥጋ ወጥ ካለ ስጭኝ አልኳት:: ለምን? ብትለኝ፣ ልበላ እላታለሁ:: ቀልድ መስሏት አቀረበችልኝ:: አክራሪነቴን ስለምታውቅ በጾም ሥጋ ይበላል ብላ በጭራሽ አልጠረጠረችም:: እንክት አድርጌ በላሁ:: የታመምኩ መስሏት ደነገጠችና ፈዛ ቀረች:: መንደረተኛው ሰማ:: አባቴ ሲመጡ ሲፈሩ ሲቸሩ ነገሯቸው:: እሳቸውም ጥቂት ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ በነፍሱ ከፈረደ እኔ ምን ማድረግ እችላለሁ? አሉና ለነፍሴ ያለባቸውን ኃላፊነት ከራሳቸው አወረዱት::

ካደሬ ሰፈር ልጆች ጋር ኳስ ሜዳ ስንገናኝ አልፎ አልፎ የድንጋይ ውርወራ ጦርነት እንገጥም ነበር:: አብዛኛውን ጊዜ መነሻው የሚጫወቱበት ኳስ ከመጫወቻው ሜዳ ርቃ ስትሄድ እየተጠባበቁ ኳሳቸውን ይዘው የሚሸሹ የሰፈራችን ልጆች ነበሩ:: አደሬዎቹ ከብስጭት የተነሳ እዚያ ያገኙትን ሁሉ ዐይንህን ላፈር ለማለት ይፈልጋሉ:: ጭቅጭቅ ይጀመራል:: ስድብ ይከተላል:: አደሬ፣ ቂጡ በርበሬ፣ ስንላቸው በምላሹ፣ አበሽነታቸውን ዘንግተው ወይም ክደው ይሁን አናውቅም፣ አበሻ፣ እራሱ መዶሻ ይሉናል:: ከዚያም የጦርነቱ ዋናው ክፍል ይከፈታል:: በተለይ ጀግናው ካሱ ካለልን ከሙሉ ልብ ጋር ስለምንዋጋ ጦርነቱ አብዛኛውን ጊዜ በኛ አሸናፊነት ይደመደም ነበር::

ከኳሱ ጨዋታም ሆነ ከድንጋዩ ጦርነት የልጅነት አእምሮዬ የተገነዘበው፣ መሪ ሆኖ ለመውጣት ችሎታ ወሳኝ ሲሆን አሸናፊ መሆን የሚቻለው ግን ተመሪው በመሪው ላይ እምነት ሲኖረው ብቻ ነው::

በዚያ ዘመን በግሉ ራድዮ ያለው ሰው በጣም ጥቂት ስለነበር መሸት ሲል ጓደኞሞች ተሰባስበን መርካቶ፣ ከአራተኛ ፖሊስ ጣቢያ ዝቅ ብሎ ወደሚገኘ ው የካፖርት ተራ የአደባባይ ራድዮ እንሄድና ከሥሩ ተኮልኩለን ዜናና ሙዚቃ አድምጠን እንመለሳለን:: በተለይ በሳምንት አንድ ቀን ይተላለፍ የነበረውን የዘፈን ምርጫ ለማዳመጥ ቀጠሮአችን እዚያ ነበር:: የራድዮ ሰዓት ከመድረሱ በፊት ተሰባስበን፣ በእግር ተጉዘን፣ አደባባዩ ደርሰን፣ ጠፍጣፋ መቀመጫ ድንጋይ ፈልገን፣ ቦታችንን ይዘን ፕሮግራሙን ማዳመጥ ስንጀምር የፈለግነውን በጥረታችን በማግኘታችን ሂደቱ የራሱ የሆነ የደስታ ስሜት የመፍጠር ኃይል ነበረው::

አንድ ሰው የፈለገውን ነገር ሁሉ ስላገኘ ብቻ ደስታን ተጎናጸፈ ማለት አይደለም:: ሁሉም በጄ ሁሉም በደጄ ሲሆን የማግኘት ትርጉሙ ስለሚጠፋ የደስታ ምንጭነቱ ይቀራል:: አንድ ያጣ ሰው የተመኘውን በጥረቱ ሲያገኝ ደስ ይለዋል:: ደስታ ያጎናጸፈው የፈለገው ነገር መገኘቱ ይምሰል እንጂ የደስታው እውነተኛው ምንጭ ጥረቱ በመሳካቱ ነው:: የደስታን መጠን የሚወስነው አንድ ሰው የፈለገውን ለማግኘት ያደረገው ጥረት መጠንና የሄደበት መንገድ ነው:: በቀላሉ ወይም በሽፍጥ የተገኘ ነገር የደስታ ምንጭ ለመሆን አይችልም:: አንድ ፍላጎት እንደተሟላ ወይም አንድ የተፈለገ ነገር እንደተገኘ የደስታ ምንጭ መሆኑ ያበቃለታል:: ፍላጎቱ ወደሌላ አቅጣጫ ይሰማራል:: ራድዮ ያለው ቲቪ ይፈልጋል፤ ጫማ ያለው ቢስክሌት ወይም መኪና ይፈልጋል፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ያጠናቀቀ ሁለተኛ ደረጃን መጨረስ ይፈልጋል፤ ወዘተ:: ስለሆነም፣ የሰው ልጅ ፍላጎት ማብቂያ ወይም ማቆሚያ የለውም:: የሰው ልጅ ከመጣር እንዳያቋርጥና ዘሩ እንዳይጠፋ ተፈጥሮ የሸረበው ዘዴ ሳይሆን አይቀርም::

ብሔራዊ ባንክ ሆኜ ልብሴን ላውንድሪ እሰጥ የነበረው ብዙውን ጊዜ በድሉ ሕንጻ ፊትለፊት ለነበረው ለአቶሚክ ላውንድሪ ነበር:: አንድ ቀን ከባለቤቱ ከአቶ ጥላሁን ጋር ላውንድሪው በራፍ ቆመን ወጭ ወራጅ ዕያየን ስንቀላምድ ሥራ እንዴት ነው? ብዬ ጠየቅሁት:: ጥሩ ነው፤ ኑሮአችንን

ማሸነፍ ችለናል አለኝ:: ይህ ከሆነ ደስተኛ ነህ ማለት ነዋ አልኩት:: የምታስበውን ያህል አይደለም አለኝ:: ለምን? ብለው፣ ገንዘብን ብዙ ሰው የሚያየው የኑሮ ፍላጎትን ማሟያ መሣሪያ ብቻ አድርጎ ነው፤ እኔና መሰሎቼ እሱን ደረጃ አልፈነዋል፤ የሚያስጨንቀን በሀብት ውድድር ወደኋላ እቀር ይሆን? የሚለው ነው፤ እኔና መሰሎቼ የምንከታተለው እገሌ ምን ደረጃ ላይ ነው ያለው? በኔ ደረጃ ካሉት ማን አልፎኝ ሄዶ ይሆን? የሚለው ስለሆነ ዋናው ተግባራችን ላለመበለጥ ወይም ኋላ ላለመቅረት መታገል ነው አለኝ:: ስለካፒታሊዝም በጽሑፍ ካነበብኩትና ክፍል ውስጥ ከተማርኩት ይልቅ ጥላሁን የነገረኝ ቁምነገር በአእምሮዬ ተቀርጾ ቀርቷል::

የሙህር ሰፈር ትዝታዎቼን ከመጨረሴ በፊት አሮጌው ጨርቅ ተራ የሆነውን ልተርክ:: ጨርቅ ተራ የሚገኘው ያደሬ ሰፈር ግርጌና የጡረታ ሰፈር ራሴን መገናኛ ላይ ነው:: ጋሼ ተሰማ ብዛ እዚያ መደብር አለው:: የሚሸጡት ልብሶች በምስማር ይንጠለጠላሉ:: ገዥ ይህን አውርድ፣ ያንን አውርድ እያለ ይሞክራል::

ጋሼ ተሰማ የእንዳለ ቅርብ ዘመድና የሙህር ተወላጆች እቁብ ጸሓፊ ነው:: በዚያ ዘመን ከሱ የበለጠ የሚዘንጥ ሰው አናውቅም:: ሲኒማ መግባት ከመጀመራችን በፊት ማለቴ ነው:: በጣም ቆንጆ ነው:: ጸጉሩ በጣም ሉጫ ሆኖ ዘወትር እንደአበጠረውና ወደጎን እንዳስተኛው ነው፤ በውርርድ ከኪሱ ማበጠሪያ አይጠፋም::

ከእንዳለ ጋር አልፎ አልፎ መደብሩ እየሄድን የሻይና የፓስቴ ፍራንክ እንዲሰጠን አጠገቡ ቆመን ዐይናችንን እናቁለጨልጫለን:: የፊደል ተማሪዎች ሆነን፣ አንድ ቀን እዚያ ቆመን ዐይን ዐይኑን እያየን ሳለ ሁለት ባላገር ኦሮሞዎች ይመጡና ይህን አውርድ፣ መልስ፣ ያንን አውርድ፣ መልሰህ ስቀል እያሉት ብዙ ልብሶችን ለረጅም ጊዜ ከሞከሩ በኋላ የሚስማማን አጣን ብለው ለመሄድ ሲዘጋጁ ተሰማ ይናደድና ሊደባደብ ፈልጎ ረብሻ ያስነሳል:: ሰዎቹ በሁኔታው ይደናገጡና ዱላቸውን ይመዛሉ::

ተሰማ ይዘልና አንደኛውን አንቀ ሲይዘው የሰውዬው ፍራንኮች ከኪሱ አፈትልከው ይበተናሉ፡፡ ይህን ጊዜ ተሰማ ከሰውዬው ጋር መተናነቁን ይተውና ከሰዎቹ ጋር በመሻማት ወደተበተነው ፍራንክ ለቀማ ይሰማራል፡፡ የሰበሰበውን ለሰዎቹ እያሳየ፣ ወንድ ከሆናችሁ እስኪ ኑና ከእጄ ፈልቅቃችሁ ውሰዱ ይላቸዋል፡፡ ረብሻው እልባት ሳያገኝ የሰበሰበውን ፍራንክ እንዳለ ለኛ ይሰጠንና፣ ካካባቢው ሂዱ ጥፉ፣ ገንዘቡን ሻይ ጠጡበት፣ ፓስቴ ብሉበት ብሎ ያባርረናል፡፡ እኛም ጨርቅ ተራ ግርጌ፣ ዶቢ ሰፈር መሻገርያ ላይ፣ ወደነበረ አንድ ወደምናውቀው ፓስቴ ቤት እናመራለን፡፡ ደጃፉ እንደደረስንም ቆም አልንና፣ ግን እኮ ይሄ የያዝነው ፍራንክ የጭቦ ገንዘብ ነው፤ የበላንበት እንደሆነ እግዚአብሔር አይወደውም፣ ኀጢአት ነው፣ እንኮነናለን ተባባልን፡፡ ምን ማድረግ እንደሚሻል ጥቂት ከተመካከርን በኋላ፣ ግድየለም መብላቱና መጠጣቱ ይቅርብንና ገንዘቡን ለድሃ እንስጠው ብለን ተስማማን፡፡ ፍራንኩን ለኔቢጤዎች እየሰጠን ጨረስነው፡፡ አንዱንም ሳንቲም ቢሆን ለራሳችን ጥቅም አላዋልነውም፡፡

የጋሼ ተሰማ የመጨረሻው ታናሽ ወንድም ቀድሩ ከአገር ቤት መጥቶ ሙህር ሰፈር ይኖር ነበር፡፡ የቀድሩ ሥራ ማሣቅና መሣቅ ነበር፡፡ መንደሩን ሲያስስ፣ ወሬ ሲከሰክስና ሲነሰንስ ይውላል፡፡ አባታቸው ብዛ ጎና ሊሞቱ አቅራቢያ ልጆቻችውን አንድ በአንድ ይጠሩና፣ ያሰብከው ይሙላልህ ብለው ሊመርቁ ፈልገው፣ እያንዳንዳቸውን ስታድግ ምን መሆን ትፈልጋለህ? ብለው ይጠይቋቸዋል፡፡ ሁሉም በልቡ የያዘውን ይናገራል፡፡ ቀድሩ በበኩሉ፣ አባዬ፣ እኔ የሴቶች እረኛ መሆን እፈልጋለሁ ብሏቸው ቁጭ፡፡ ሰውዬው ይደነግጣሉ፤ ይገረማሉ፡፡ በልባቸው፣ ምንድነው የወለድኩት? ሳይሉም አይቀሩም፡፡ ቆይቶ የሆነውን ካየን በኋላ ቀድሩን አባቱ የልብህ ይሙላልህ ሳይሉት እንዳልቀሩ ገምተናል፡፡

ጋሼ ተሰማ አባቱን ምን እንዳላቸውና ምን ብለው እንደመረቁት አልሰማሁም፡፡ ከዩኒቨርስቲ ከተመረቅሁ በኋላ፣ አንድ ማታ ከአብሮ አደግ ጓደኛዬ ከታከለ ደበላ ጋር መርካቶ ምዕራብ ሆቴል ቢራ ስንጎነጭ ተሰማ

ይመጣል:: ባንኮኒው አጠገብ ሄዶ ይሰቀልና የሚጠጣውን ይጠጣል:: ትንሽ ቆየት ብሎ ካንዱ ጋር ይጣላል:: ተሴ ሽጉጡን ይመዝና ያዙኝ ልቀቁኝ ይላል:: ሃይ ሃይ ይባላል፤ ነገሩ በዚሁ ያልቃል:: ካናዳ በስደት ላይ ሆኜ እንደሰማሁት፣ ተሰማ ከአንድ ጠብደል ጎረምሳ ጋር ይጣላል:: ሱቃቸው አጠገብ ለአጠገብ ነው:: ተሰማ መውጫ መግቢያ ያጣል:: ስድብና ውርደት ቁርስና ምሳው ይሆናል:: ሲበዛበት ሽጉጡን ላጥ አድርጎ ባላጋራውን በጠራራ ፀሐይ ይደፋዋል:: ይህን ስጽፍ ተሰማ ወኅኒ ወርዶ ፍርዱን እየተጠባበቀ ነው:: የደም ካሳ ከፍሎ ጉዳዩ በሽምግልና እንዲያልቅ ሙከራ እየተደረገ ነው አሉ:: እዚህ ቁጭ ብዬ ስለተሰማ ሕይወት ሳሰላስል፣ ነፍሱን ምን እንደሚጠብቃት ባላውቅም፣ አንቺ ሆዳም የከርቸሌ ምላጭ፣ የተሴንም ጸጉር ተውጦልሽ በላሽ? እያልኩ መገረሜ አልቀረም::

ከልጅነት ትዝታዎቼ በፍጹም ከአእምሮዬ ሊጠፉ የማይችለው የጃንሆይን ሃያ አምስተኛ ንግሥ በዓል ምክንያት በማድረግ በ1948 በአሮጌው አየር ማረፊያ የተደረገው ታላቅ ኤግዚቢሽን ነው:: የመንደር ልጆች ተሰባስበን ትርዒቱን ለማየት እንሄዳለን:: እንደኛ ዓይነቱ ኩታራ ቦታ ስላልነበረው ቀኑን ሙሉ የእግረኛና ፈረሰኛ ፖሊስ ላይ ታች ሲያራውጠንና ድብብቆሽ ሲያጫውተን ዋልንና ወደቀኑ በስተመጨረሻ እኛ አሸንፈን ወይም ፖሊሶቹ ተሰላችተው ይሁን አላውቅም እንደምንም ብለን ኤግዚቢሽኑ መንደር መግባት ቻልን:: ዋና ሥራ አድርገን ይዘን የነበረው ለኛ ብርቅዬ በመሆናቸው በነጻ ይታደሉ የነበሩትን የመግለጫ ወይም የማስታወቂያ ወረቀቶችን መሰብሰብ ነበር:: አንድ አካባቢ ስንደርስ ዙሪያው ባማረ ድንጋይ የተከበበ ውሃ ተንጣሎ ዐየሁና ለማድነቅ ጫፍ ላይ እንደቆምኩ ያዳልጠኝና እወድቃለሁ:: እውስጡ ጠልቄ ልዘፈቅ ስል እንደምንም ብዬ የድንጋዩን ጠርዝ ይዤ ተንጠልጥዬ ቀረሁ:: ወረቀቶቹን ከድንጋዩ ጋር ጨፍልቄ ያዝኳቸው:: ከዚህም ጎትቶ የሚያወጣኝ ሰው እጠባበቅ ጀመር:: ከጥቂት ደቂቃዎች ጥበቃ በኋላ አንድ በዕድሜው አባቴ ሊሆን የሚችል ጠረንገሎ ወደኔ ሲመጣ ዐየሁና ከሞት አፋፍ ተስቤ ልወጣ ነው ብዬ በጣም ደስ አለኝ:: ሰውዬው ጎንበስ ሲል እጅህን ስጠኝ የሚለኝ መስሎኝ ባዶውን እጄን

ዘረጋሁለት፡፡ የተዘረጋውን እጄን ትቶ ወረቀቶቹን ወደ ያዘው እጄ ጠጋ አለና ወረቀቶቹን ነጥቆኝ እየሣቀና ተገላምጦ እያየኝ መንገዱን ቀጠለ፡፡ ፍጹም ማመን አቃተኝ፡፡ በምድር ላይ እንደዚህ ዓይነት አረመኔነት አለ ብዬ እስከዚያን ጊዜ ድረስ አላውቅም ወይም አላምንም ነበር፡፡ ደግነቱ ወድያው አንዱ ይመጣና ጎትቶ ያወጣኛል፡፡ የዘነበባት ሶለግ ቡችላ መስዬ በቅርብ ያየሁትን ፖሊስ አረመኔውን በጣቴ እየጠቆምኩና የንዴት ሲቃ እየተናነቀኝ ስለበደሌና ስለሰውዬው ጨካኝነት ላስረዳ ብሞክርም ፋዳ ሳይለኝ እንዳልሰማ ሆኖ እሱም መንገዱን ቀጠለ፡፡

ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ እስክሄድ ድረስ ሙህር ሰፈር ተመልሼ ከ1961 እስከ 1962 በወላጅ አባቴ ቤት ኖሬአለሁ፡፡ ከሥራ ስወጣ በታክሲ ተክለሃይማኖት አደባባይ እወርድና ወደ ቤት ከማምራቴ በፊት ብዙ ጊዜ አሰብ ሆቴል ጎራ እልና አንድ ሁለት ቢራ እጎነጫለሁ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ወደዚያ ጎራ ሳልል በቀጥታ ወደ ቤት ሄድኩ፡፡ የተለመደውን ጠበል ሰውነቴ ባለማግኘቱ ቅር ተሰኝና አስታወሰኝ፡፡ ወይኔ ሰውዬው፣ ከሲጋራ ለመገላገል ያን ያህል ትግል አድርጌ አሁን ደግሞ የከፋ ባላንጣ ሊያንበረክከኝ ነው አልኩና ፈራሁ፡፡ ቆራጥ እርምጃ ለመውሰድ ወሰንኩ፡፡ ለዘጠኝ ወር ምንም አይነት ከአልኮል የተሠራ መጠጥ አፌ ውስጥ እንዳይገባ ወሰንኩ፡፡ ተግባራዊም አደረግሁት፡፡

አንድ ቀን ደግሞ ከሥራ ወደቤት ስመለስ ዘራፊዎች አሳቻ መንገድ ላይ ጠብቀው ሰዓቴን ሊቀሙኝና ኪሴ ውስጥ የነበረውን ገንዘብ አራግፈው ሊወስዱ ሲሞክሩ ታግዬ አስጥያቸዋለሁ፡፡ ሰዓቱን ከእጄ አውልቀው ሊያመልጡ ሲሉ አልለቅ ብዬ ስንታገል የማሠሪያው ብረት መዳፌን ስለተረተረው ጠባሳው እስካሁን ድረስ አለ፡፡ ዘረፊዎቹ አምስት ያህል ነበሩ፡፡ በውል አልለየኋቸውም እንጂ ኳስ ሜዳ የምንገናኝ የአካባቢው ልጆች ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ ከልጅነት እስከ ዕውቀት መሬት አዳልጬ፣ ኳስ ተጫውቼ፣ ቡሄ ጨፍሬ ባደግሁብት ሰፈር እንዴት ተደፈርኩ? ብዬ

ተናደድኩ። የሰፈሩና ያካባቢው ሰው ሁሉ ወዳጄ ይመስለኝ የነበረው ስሜቴ በመጠኑም ቢሆን ውሃ ተቸለሰበትና አዘንኩ።

በሙህር ሰፈርና አካባቢው የመጀመሪያውን ቴሌቪዥን ገዝቼ አባቴ ቤት ያስገባሁት እኔ ሳልሆን አልቀርም። ዘመኑ 1961 ነው። ቴሌቪዥኑ ቤት የገባ ዕለት ያካባቢው ሰው ቤታችንን እጥለቀለቀው። እበረንዳው ለተኮለኮለው መስኮት ተከፈተለት። ሁለት ሰዓት ላይ የወሬ ፕሮግራም ተጀመረና የዛምቢያው ፕሬዚዳንት ኬነት ካውንዳ ምሥል ስክሪኑን ሞላው። ቤቱ በአንድ ጊዜ በሣቅ ተናጋ፣ አንዳንዱ ልጅ ወለሉ ላይ ይንፈራፈራል። ምን ሆናችሁ? ቢባሉ አሁን ያየነው ሰው ነው ወይስ ዝንጀሮ? ብለው ጠየቁ። ዩኒቨርስቲው ውስጥ ብዙ አፍሪቃውያን ተማሪዎች ነበሩ። ኢትዮጵያውያን አፍሪቃዊነታቸውን አልተቀበሉም የሚል ቅሬታ ስለነበራቸው እነሱን ለማስታመምና ስሜታቸውን ለመጠበቅ ጥረት ይደረግ እንደነበር ዐውቃለሁ። ተራው ሰው ስለአፍሪቃዊ ምንነት ያለውና የተሳሳተ አስተያየት ለማረምና እራሱም አፍሪቃዊ መሆኑን ለማስረዳትና ለማስገንዘብ ረጅም ጊዜ እንደሚፈጅ ግልጽ ሆነልኝ። ስለዘረኝነት አፋችንን ሞልተን መከራከር የማንችልበት ሁኔታ ውስጥ እንዳለንም ተረዳሁ።

እቤት ስኖር ቁርሴን እራሴ ሰርቼ እንድበላ አስቤ አንድ ትንሽ ምድጃና የቡታ ጋዝ ሲሊንደር ገዛሁና እክፍሌ ውስጥ አስቀመጥኩት። ሠራተኞችንን ጋዙ ቢያመልጥ አደገኛ ስለሆነ እንዳትጠቀሙበት ብዬ አስጠንቅቄአለሁ። ለካስ ቀን ቀን እየተደበቁ ወይም እየደበቁ ይጠቀሙበታል። አንድ ሌሊት በሰመመን እነቃለሁ፣ ነገር ግን ለመላወስ አቅም አጣለሁ፣ መተንፈስ እማልችልበት ደረጃ ደርሻለሁ፣ ሰው መጣራት አልቻልኩም። ሰው ጢም ብሎ የጎን ማሳረፊያ ይጠፋ በነበረበት በስራጋ ቤት የተሻለ ተሠራ ተብሎ፣ ሰው ከሰው በክፍል ተለይቶ፣ ያመለጠ ጋዝ መውጫ ቀዳዳ አጥቶ፣ አናፋሽ ሰው ለመድኃኒትነት በሚፈለግበት ቀውጢ ወቅት ሰው ራቀኝ። ዐይኔ ዕያየ፣ ኅሊናዬ ዕያወቀ ሕይወቴ ለአደጋ ተጋለጠ። በመኝታ ክፍሌና በዋናው መግቢያ በር የነበረው መጋረጃ ብቻ ስለነበር እንደምንም ብዬ በሩ

ዘንድ ብደርስ ሕይወቴን ለማዳን ዕድል እንዳለኝ ተገነዘብኩ:: በአልሞት ባይ ተጋዳይነት እንደምንም ብዬ ከአልጋ ተንከባልዬ ወረድኩና በደረቴ እየተሳብኩ ወደ በሩ አመራሁ:: ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ መዝጊያው ዘንድ ደረስኩና መቀርቀርያውን ታግዬ ከፈትኩት:: በረንዳ ላይ ወጥቼ ተዘረርኩ:: ያንኑ ሌሊት ሲሊንደሩን አውጥቼ ጣልኩት:: የቁርሱን ነገር ጉሮሮዬን ለከፈተው ጠባቂዬ ተውኩት::

# ምዕራፍ ሁለት

# የትምህርት ዘመን

## ፊደል ቆጠራ

ሀ ሁ ብዬ ትምህርት የጀመርኩት አዲስ አበባ ተክለሃይማኖት ቤተክርስትያን አጠገብ፣ ከበርበሬ በረንዳ ዝቅ ብሎ ይገኝ በነበረው በየኔታ ኃይሌ የቄስ ትምህርት ቤት ነው። አቡጊዳ ወይም መልእክተ ላይ ሳለሁ ይመስለኛል ከሞክሼዬ ከታደሰ ገብረኪዳን ኩፍኝ ይጋባብኝና ትምህርቴ ይሰናከላል።

በወቅቱ የእንጀራ እናቴ እማማ ባዴቼ ሿጌ ነበረች። በዕድሜ ትንሽ የሚበልጠኝ ኪዳኔ የሚባል ልጅ ነበራት። ኩፍኙ ወደሱ እንዳይጋባ ሰጋችና ሳልገለጥ በብርድ ልብስ ተሸፍኜ እንድውልና እንዳድር ታደርግ ነበር። ከጊዜ በኋላ ኩፍኙ ዐይኖቼ ውስጥ ስለገባ ሁለቱም ዐይኖቼ አደጋ ላይ መውደቃቸው ይደረስበታል። ዛጎል ይፈጭና እጆቼ ተጠፍረው ተይዘው ዐይኖቼ ውስጥ ይጨመራል። በጣም እንዳቃጠለኝ አስታውሳለሁ። ምንም ሳይሻለኝ ሲቀር አባቴ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል በጋሪ ይዘውኝ ይሄዳሉ። እኛ አንችልም፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ውሰዱት ተባለና እዚያ ስንሄድ የግራ ዐይኑ አልቆለታል፣ ቀኙ ትንሽ ተስፋ ያለው ስለሚመስል ገንዘብ ከከፈላችሁ ተኝቶ ሊታከም ይችላል ተባለ። አባባ የተጠየቀው ገንዘብ ስላልነበራቸው አጎታችን አባባ መመርየ ዘንድ ሄደው እንዲያበድሩዋቸው ጠየቋቸውና እሺ ብለው ስለተባበሩ ተኝቼ መታከም ቻልኩ። አንድ ዐይኔ ሊድን ቻለ። ሕክምናው ሦስት ወር የፈጀ ይመስለኛል። ከሆስፒታል ከወጣሁም በኋላ እየተመላለስኩ ለረጅም ጊዜ ታከምኩ። ወንድሜ ብርሃኔ

ገንዘብ ሲገኝ በአውቶቡስ፣ ሲጠፋም በእግር ይዞ እንዳመላለሰኝ አስታውሳለሁ።

አባባና ባዴቺ የሳንቃ ገብተው ሳለ የአባባ ወቢሳ አሎ ልጅ፣ እልፍነሽ፣ ውሃ ለመቅዳት በቤታችን ደጃፍ ስታልፍ ባዴቺ ታይና ታያታለህ? ገጎ፣ ይህች ልጅ እንዴት ታምራለች? ትላቸዋለች። አባባ ያኔ ቢያንስ አምሳ ዓመት አያጡም። እልፍነሽ ግፋ ቢል ዐሥራ ስምንት ቢሆናት ነው። አባባ ልጅ መውለድ ይፈልጋሉ። ባዴቺ አልቋጥር ትላለች። ባዴቺ ሳታውቅ አባባ በምስጢር ሽማግሌ አባባ ወቢሳ ዘንድ ይልኩና እልፍነሽን ያስጠይቃሉ። ይሰጣሉ። ባዴቺ ብትፈርጥ፣ ብትቀጠቀጥ ያለቀለት ጉዳይ ሆነ፤ እያለቀሰች ቤቱን ጥላ ወጣች።

አባባና እልፍነሽ በተጋቡበት ዘመን አገር ቤት ገብቼ በሚቀጥለው ዓመት ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ጎላ ሰፈር፣ ሚካኤል ቤተክርስትያን አጠገብ በሚገኘው ትምህርት ቤት ፊደል ቆጠራ እንደገና ተያያዝኩት። ጎላ ሚካኤል የሄድኩት እነእንዳለን ተከትዬ ነው ለማለት ይቻላል። በዐይኔ ሕመም ምክንያት በትምህርት ወደ ኋላ ቀርቼ ስለነበር እንዲረዱኝ ታስቦ የተደረገ ነበር።

ወደ ትምህርት ቤት ስንሄድ የምንጠጣውን ውሃ በጠርሙስ ይዞ መሄድ የተለመደ ነበር። ሁለት ፍራንክ (በዘመኑ ቋንቋ) ወይም አምስት ሳንቲም ካለን በመንገዳችን ዐሥራ ሁለት ኮሾ ከረሜላ እንገዛና ውሃው እንዲጣፍጥልን እውስጡ እንጨምረዋለን። ከረሜላ አዘውትረን የምንገዛው ተሰማ አባቀማው መንገድ ሃጂ ፈይሳ ደጋጋ ሕንጻ ጀርባ ከሚገኘው ከጋሼ አያሌው ሱቅ ነበር። አንድ ቀን እንደተለመደው ከረሜላውን ገዝተን በጠርሙሱ ውስጥ ከተነው ትምህርት ቤታችን ልንደርስ ጥቂት ሲቀረን ለከረሜላው መክፈል ወይም ሳንቲሙን መስጠት እንደረሳን አወቅን። ወደኋላ እንዳንመለስ የትምህርት ቤት ሰዓት ሊረፍድብን ሆነ፤ ዝም ብለን እንዳንሄድ እግዚአብሔር የማይወደው ነው አልንና ምን ብናደርግ ይሻላል?

ተባባልን። ምርጫችን ውስን ስለነበር ከትምህርት ቤት መልስ በመስጠቱ ላይ ተስማማን። በቀኑ መጨረሻ ሁሩ በሰላም ደወል እንደተደወለ ወደ ጋሼ አያሌው ዘንድ በሩጫ ሄደን የተከሰተውን ነገርነውና ፍራንክህን እንካ ብለን ሰጠነው። በመገረም መልክ ትኩር ብሎ ካየን በኋላ ፍራንኩን ተቀበለን። ወዲያውኑ፣ እንካችሁ የፈቀዳችሁትን አድርጉበት ብሎ ስሙኒ ወይም ሃያ አምስት ሳንቲም ከካዝናው አውጥቶ ሰጠን።

# አንደኛ ደረጃ ትምህርት

ወንጌል ማንበብ እንደጀመርኩ እንግሊዝ ትምህርት ቤት መግባት ፈለግሁና ለ1947 ትምህርት ቤቶች መክፈቻ ላይ አባቴን ወንድሜ ብርሃኔ እተማረበት በየነ መርዕድ ትምህርት ቤት ወስደው እንዲያስገቡኝ ብጠይቃቸው ጎረቤታችን የነበረው አቶ ወልደየስ ቤቶሳ ዘመዱን ሊያስገባ ወደዚያው ስለሚሄድ እሱ ይውሰድህ ተባልኩና ይዞኝ ሄደ። ጋሼ ወልደየሰ ዘመዱን ታግሎ እንደምንም ብሎ አስገባው፤ ለኔ ቦታ አልተገኘም ተባልኩና አንድ ተጨማሪ አመት መጠበቅ ተገደድኩ። በወቅቱ ጅማ ሁለተኛ ደረጃ እርሻ ትምህርት ቤት ይማር የነበረው ወንድሜ ብርሃኔ በዓመቱ መጨረሻ ለእረፍት አዲስ አበባ እንደመጣ እኔንና እንዳለን አማኑኤል ቤተክርስትያን መሳለሚያ አጠገብ ወደሚገኘው ወደ ልዑል መኮንን፣ ኋላ ወሰን ሰገድ ከዚያም የካቲት 23 ተብሎ ወደ ተሰየመው፣ ትምህርት ቤት ወስዶ አስመዘገበኝ።

የአንደኛ ደረጃ ትምህርቴን በመስከረም 1948 ጀምሬ በሐምሌ 1952 አጠናቀቅሁ። በዘመኑ ትምህርት ቤቱ በነበረው ልምድ መሠረት በአንደኛ ተርም ፈተና ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የሚወጣ ተማሪ ከሁለተኛው ተርም ጀምሮ ወደሚቀጥለው ክፍል እንዲዛወር ወይም እንዲዘል ይደረግ ነበረ። እኔም የዕድሉ ተጠቃሚ ስለነበርኩ የስምንት አመቱን ትምህርት በአምስት ዓመት መጨረስ ቻልኩ።

የዐይን ሕመም ከገጠመኝ ከ1945 ጀምሮ ማየት የተሳነው ግራ ዐይኔ በ1981 በኦፕራሲዮን እስከተወገደበት ጊዜ ድረስ ለሠላሳ አምስት ዓመታት ሕመሙ ተለይቶኝ አያውቅም። ብዙ ሰው ሳያውቅልኝ ወይም ሳያውቅብኝ ለረጅም ጊዜ ጦርነት አካሂጃለሁ። ጦርነቱ ሥጋዊ ብቻ ሳይሆን ሥነልቦናዊም ነበር። ሕመሙ እየቀጠቀጠ ቤት ሊያውለኝ፣ ከተሰለፍኩበት መስክ ሊያስተጓጉለኝ፣ ወደኋላ ሊያስቀረኝ ሲከጅል ሞኝህን ፈልግ እያልኩ ታግዬዋለሁ። እንዲያውም፣ ቆይ ማንነቴን አሳይሃለሁ እያልኩ የውስጥ ሕመሜን በውስጤ አምቄ የተያያዝኩትን ተግባር ወይም እንቅስቃሴ አጠናክሬ እገፋበታለሁ። በመሆኑም፣ ከዓላማዬ ዝንፍ ብዬ ወይም ከጓደኞቼ በታች ውዬ አላውቅም።

መለስ ብዬ የነገሮችን አመጣጥ ሳጤን ከሕመሙ ጋር ያደረግሁት ትግል የጠባዬን ይዘት ወስኖታል ብዬ አምናለሁ። እጅ መስጠት፣ መሸነፍ፣ መጠቃት፣ ተስፋ መቁረጥ አልወድም። ችግር ሲገጥመኝ ወይም ሲያጋጥመኝ መአት እንደመጣ ሳይሆን ፕሮብሌም ለመቋቋም ወይም ለመፍታት ዕድል እንደገጠመኝ የመቁጠር ወይም የማየት ዝንባሌ አለኝ። እርግጥ ትምህርትና የሕይወት ልምድ የሚያሳድሯቸው ሥነልቦናዊ ተጽዕኖዎች ድንበራቸውን ለመለየት ቀላል ባይሆንም ከዐይኔ ሕመም ጋር ያደረግሁት ከፍተኛ ትግል ኑሮዬንና መለስተኛ ጠላቶቼን ብቻ ሳይሆን ደካማ ጎኔንም ለማሸነፍ እንደረዳኝ አምናለሁ። ይህ አባባል ግራ የሚያጋባ ቢመስልም ስለእውነትነቱ ምስክሩ በተመሳሳይ መንገድ ተፈትነን የወጣልን ወይም የወጣን ብቻ ነን።

አንደኛ ክፍልን የማስታውስበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ሒሳብ በግጥም ተምሬበታለሁ። መምህር ይሄይስ፣ ለምሳሌ፣ ስለዜሮ ምንነት ያስተምሩን እንዲህ ብለው ነው፣

ቁጥር ሳያስቀድም ቢደረደር ዜሮ፣

ዋጋቢስ መሆኑን ያውቀዋል አእምሮ።

እንዲሁም ሦስተኛ ክፍል ሆነን የአማርኛ መምህራችን ኃይለማርያም ሰዋሰው ያስተማሩን በግጥም ነበር:: ለምሳሌ፣ ስለንዑስ ሐረግ የተማርነው እንደሚከተለው ነበር፣

ንዑስ ሐረግ አሉት እውነትም ያነሰ

ስሜት የሌለው ጉድ የተልከሰከሰ::

ግጥሞቼን ለወዳጄ ለደራሲ ጸጋዬ ገብረመድህን ሲያቀብጠኝ ወርጄለት፣ ግጥሞቹ ያንተ ባይሆኑም የግጥም ዝንባሌ አለህና አዳብረው እያለ ዘወትር ይወተውተኝ ነበር:: በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ የሰፈሩትንና መደበኛ የግጥም ሕግጋትን ያልተከተሉትን ግጥሞቼን ምናልባት በላይኛው ቤቱ ካነበበ አሁንም በውትወታው ይቀጥል እንደሆነ አላውቅም::

እንዳለና እኔ ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት ከመግባታችን በፊት የእንግሊዝኛ ፊደላትን በራሳችን ጥረት ለይተን አውቀናል:: ሌሎች የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች ግን እንደማያውቁ ተረዳን:: ተመካከርንና ማወቃችንን የአማርኛ መምህራችን መልካሜ ቢያውቁልን ያለ ምንም ጥርጥር ወደ ሁለተኛ ክፍል ወዲያው ያሸጋግሩናል ብለን አመንን:: የእምነታችን መሠረቱ ምን እንደነበረ ግን በውል አላስታውስም:: መልካሜ እንዲያውቁልን ለማድረግ የቤት ሥራ ደብተር ስናስረክብ እላዩ ላይ ስማችንን በእንግሊዝኛ እንድንጽፍ ተስማማን:: በተግባርም ተረጎምነው:: ሥራችን ታርሞ ደብተሮቹ የሚመለሱበትን ቀን በጉጉት ስንጠባበቅ ቆየን፤ ቀኑም ደረሰልን:: መልካሜ ገና ክፍል ከመግባታቸው፣ ማነው ገብረሰንበት? አሉ:: ይህ ስም የእንዳለ የትምህርት ቤት መጠርያ ወይም ኦፊሴል ስሙ ነው:: እንዳለ ከመቀመጫው ዘሎ፣ እጁን ወደሰማይ በመቀሰር «ቲቸር፣ እኔ ነኝ» አለ:: ና ውጣ ተባለ:: እኔም ቁና ቁና መተንፈስ ጀመርኩ:: ቀጥለውም፣ ማነው? ታደሰ ሲሉ ልቤ ከደረቴ አፈትልኮ ሊወጣ ምንም አልቀረውም ነበር:: በቃ፣ ሁለተኛ ክፍል ሄድኳት ብዬ በደስታ ወከክ አልኩ:: ና ውጣ ተባልኩ:: ሁለታችንም በክፍል ጓደኞቻችን ፊት

እንደቆምን፣ መምህር መልካሜ ወደኔ አቅንተው ዕያዩ፣ ደግሞ አንተ ብሎ ታደሰ፣ አሮጌ ነህ እንዴ፣ በአማርኛ ደብተር ላይ በእንግሊዝኛ የምትጽፍ አሉኝና አረፉት፡፡ ወሽመጣችንን ቆረጡት፡፡ ተገርፈን ተቀመጥን፡፡ ክንፍ አውጥቶ በሰማይ ላይ ለመብረር በመንደርደር ላይ የነበረው የልጅነት ተስፋችንም፣ ደራሲ ጸጋዬ እንደሚለው፣ ጎማው ቱስ አለና ባፍጢሙ ተደፋ፡፡ ልጅ ለማሳደግ ወይም ለማስተማር ኃላፊነት የተሰጠው ሁሉ የስንቱን ተስፋ እንዳለመለመና የስንቱን ደግሞ እንዳጠወለገ በዚህ አጋጣሚ እራሱን ይጠይቅ፡፡

ቢሆንም፣ ወደ ሁለተኛ ክፍል ለመሸጋገር የነበረን ፍላጎት ስላልተገታ በርትተን ማጥናት ቀጠልን፡፡ በአንደኛ ተርም መጨረሻ፣ በግብረገብ ፈተና እለት ፈተናው የሚሰጠው ከቀትር በኋላ መስሎን ብንሄድ፣ የት ነበራችሁ? ጠዋት ነበር እኮ፣ አመለጣችሁ ተባልንና ከፍተኛ ሐዘን ዋጠን፡፡ በግብረገብ ስም በጉሮሮአችን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ስብከት የሚያንቆረቁሩት አስተማሪ ገብረሰንበት የሚለው የክርስትና ስም አንጀታችውን በልቶት ይሁን ወይም ኅሊናቸውን አዳሽቶት እንደሆን ባይታወቅም ለእንዳለ 50 ሲቸሩት አረመኔ ወይም ክርስትያን መሆኑ ላልታወቀው ታደሰ ዋጋቢሱን ዜሮ አስታቅፈውት ቁጭ አሉ፡፡ ውጤት ሲቀመር እንዳለ ከክፍል አንደኛ ይወጣና በሁለተኛ ተርም ወደ ሁለተኛ ክፍል ይዛወራል፡፡ እኔ ደግሞ በነበርኩበት ታግቼ ዴስኬ ላይ አንገቴን ደፍቼ መንፈቅፈቅ የእለት ተእለት ተግባሬ ሆነ፡፡ አስተማሪዎቼ የሚያደርጉትን እስኪያጡ ድረስ አስቸገርኩ፡፡ ቢያባብሉኝ፣ ምን ቢሉኝ፣ የተጸናወተኝ ሐዘንና ንዴት በቀላሉ አልለቅህ አለኝ፡፡ ክፍል አለመዛወሩ ብቻ ሳይሆን ከእንዳለ መለየቱ አንገበገበኝ፡፡ የግብረገብ አስተማሪያችን በነካ እጃቸው ለእኔስ ምነው 50 አልሰጡኝም አልኩና ከልብ ረገምኳቸው፡፡ ከጊዜ ብዛት እንደምንም ተረጋጋሁና ሁለተኛውን ተርም ከዚያም ሦስተኛውን ተያያዝኩት፡፡ በዓመቱ መጨረሻም ከክፍል አንደኛ ወጣሁና ከአባባ ጃንሆይ እጅ የመጽሐፍ ሽልማት ለመቀበል በቃሁ፡፡

የሽልማቱ ስርአት የተካሄደው በታችኛው ግቢ በታላቁ የምኒልክ አዳራሽ ነበር። ለሽልማት የቀረብን ተማሪዎችን ውጭ ተሰልፈን እንደቆምን ጃንሆይ በአጃቢ ይመጣሉ። እንዳጋጣሚ እሳቸው የተሳፈሩበት አውቶሞቢል ያወረዳቸው እኛ በተሰለፍንበት ቦታ አጠገብ ነበር። ወደ አዳራሹ ለመግባት ራመድ ራመድ እያሉ ፊታቸውን ወደኛ ሲያዞሩ እይታቸው አንድ ተማሪ ላይ ያርፋል። ጠጋ ይሉና፣ አንተ፣ የማን ልጅ ነህ? ይሉታል። መልሱ ዝም ይሆናል። ደጋግመው ቢጠይቁት ልጁ ከመደንገጡ የተነሳና አምላክ ከሰማይ ወረዶ የሚያነጋግረው ስለመሰለው የሚለው ሁሉ ይጠፋውና አንደበቱ ይተሳሰርበታል። በዚህን ጊዜ ጃንሆይ ተስፋ ይቆርጡና «ይህስ አባቱንም የማያውቅ ነው» ብለውት ወደ አዳራሹ አመሩ። ምናባክ፣ የታባቱ የሚለው ስድብ ትርጉሙን መረዳት የጀመርኩት ከዚያን እለት ጀምሮ ነው። ቀጥሎም፣ ለንደን እኖር በነበረበት ወቅት ነው። በዚህኛው ላይ ወደኋላ እመለስበታለሁ።

ወደ አዳራሹ ስንገባ ያየሁትን ሁሉ ማመን አቃተኝ። የተኮለኮለውና አዳራሹን የሞላው ሰው አለባበሱና ሁኔታው እኔ ከማውቀው ውጭ ነው። እኔ የማውቃቸው ትልልቅ ወይም ከባድ ሰዎች እነአባባ አሶሬና አዝማች ገለቶ ናቸው። አዝማች ገለቶ የሚሄዱት በባዶ እግራቸው ሲሆን እዚህ ያየሁዋቸው ሰዎች ሁሉም የተዋበ ጫማ አላቸው። እኔ እንደማውቀው ቤት ውስጥ የሚነጠፈው የሰሌን ኬሻ ነው። አዳራሹ ውስጥ ግን እጅግ የተዋበ ምንጣፍ ተነጥፎ ሲረገጥ አየሁ። የኸማንዋ ዘመዳችን እንዳለችው ሁሉ እኔም ለካስ ሌላም ዓለም አለ? ብዬ ተገረምኩ።

ያንን አዳራሽ እንደገና ያየሁት ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ነው። ያየሁት ልዩነት ጃንሆይ ተቀምጠውበት የነበረው ወንበር ጨርቅ ተከናንቦ አዳራሹ ውስጥ ይደረግ የነበረውን ይታዘብ እንደነበር ብቻ ሳይሆን ያኔ ያየሁዋቸው ትልልቅ ሰዎች ምንጣፉን ለተረኛ ረጋጭ ትተው ከወለሉ በታች ውለው የወቅቱን አሸናፊ ፍርድ አንጋጠው ይጠባበቁ እንደነበር ነው።

ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት ለመርካቶ ወይም አዲስ ከተማ አካባቢ ትልቁና ዋነኛው ትምህርት ቤት ነበር፡፡ አዲስ አበባ ከነበሩት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከማንናቸውም ጋር የሚስተካከል ነበር፡፡

የትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ስብጥር ሚዛናዊ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ጓደኛሞች የምንመራረጠው ብሔረሰብን መሠረት አድርገን ሳይሆን የአስተሳሰብና የዝንባሌ መሰሎቻችንን እየፈለግን ነበር፡፡ የኔ የቅርብ ጓደኞች ያኔም እንዳሁኑ ከልዩ ልዩ ብሔረሰቦች የሚመጡ ናቸው፡፡ ሰውን በሰውነቱ እንጂ በጎሳው ምክንያት መጥላት ወይም መውደድ፣ ማንሳት ወይም መጣል እኔን የተጸናወተኝ በሽታ አይደለም፡፡ በዚህ ታምቼ ከሆነም፣ ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነውና ምንም ማድረግ አልችልም፡፡ አንዳንድ ጉራጌ ጓደኞቼ ሲቀልዱብኝ፣ አንተ እኮ የአዲስ አበባ ጉራጌ እንጂ እውነተኛ ጉራጌ አይደለህም ይሉኛል፡፡ እውነተኛነቴ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል እንዲሆን ከጠባቂ አምላኬ ጋር ቃል ኪዳን እንዳለብኝ አሳውቂያቸው ትተውኛል፡፡ እንዲያውም፣ ትልቅ ሜዳ እያለላቸው እራሳቸውን በትንሽ ስፍራ እንዳያስሩ መክሬአቸዋለሁ፡፡ ስለዥማኗ ዘመዴም ነግሬአቸዋለሁ፡፡

የአንደኛ ደረጃ አስተማሪዎቻችን የተከበሩና የተፈሩ ነበሩ፡፡ በዚያን ዘመን ልዑል መኮንን የተማርን ሰዎች ስንገናኝ የሳይንስ አስተማሪያችን ጀምበሬ ተሰማን ሳናነሳ አናልፍም፡፡ ጀምበሬን ልጆች አግኝተውት፣ ጋሼ፣ ደህና ነህ? ቢሉት፣ ይመስገነው ጤናዬ የተሟላ ነው፤ ታደለ ጀምበሬ ሕክምና ትምህርት ቤት መግባቱን ስለሰማሁ ቢያመኝ ትምህርቱን ጨርሶ እስኪወጣ ድረስ በሽታዬን እንደምንም አስታምመዋለሁ ያለና ተማሪዎቹ ባስተማሪነቱ ብቻ ሳይሆን በጨዋነቱና አርአያነቱ በጣም የምንኮራበት ሰው ነበር፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ኑሮ ያልተሟላላቸው አንዳንድ አስተማሪዎች ካስተማርናቸው ተማሪዎች በታች ሆነን እያሉ ያማርሩ እንደነበር ሰምተናል፡፡

ስለጀምበሬ ከተወሳ አንድ ገጠመኝ ላጫውታችሁ፡፡ ሦስተኛ ወይም አራተኛ ክፍል ሆነን የቀኑ ትምህርት ስለፍራፍሬ ነበር፡፡ የምታውቁትን ፍራፍሬ

ዓይነት ተናገሩ ይለናል:: እነብርቱካን፣ ሎሚና ትርንጎ ከሰሌዳው ጋር ከተዋወቁ በኋላ የሚቀሰረው ጣት ቀስ በቀስ እያነሰ መጣና በመጨረሻም ከናካቴው ቆመ:: ቲቸር ጀምበሬ፣ ጨምሩ እንጂ እያለ ያበረታታል፣ ያደፋፍራል:: አጠገቤ የነበረው አያሌው በጆሮዬ ሹክ ይለኛል:: አያሌው የሀብታም ፊታውራሪ ልጅ ስለሆነ በእርግጥ እኔ የማላውቃቸው ብዙ ዓይነት ፍራፍሬዎች በልቶ ሊሆን ይችላል አልኩና እጄን አወጣሁ:: ጀምበሬ ደስ አለውና፣ ታደሰ፣ እሺ፣ ይሄ ነው የኔ ጎበዝ ተማሪ ከማለቱ «ሙጀልጀል» እላለሁ:: የተማሪዎቹን እንተወውና ጀምበሬ እንደዚያን እለት በሣቅ ሲፈነዳ አላየሁም:: ሁሉም ሢሥቅ ግራ ገባኝና አይኔ ፈጠጠ:: የሣቁ ሁከት በረድ እንዳለ ከየት አመጣኸው ቢለኝ እውነቱን ነገርኩት:: የራሴን መገረፍ እንጂ ስለአያሌው አላስታውስም::

ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ሦስተኛ ክፍል ሆነን፣ ጀምበሬ በጥቁር ሰሌዳው ላይ የምንገለብጠውን ሲጽፍ አንድ የሚጠላው ነገር ይፈጸማል:: ማን እንዳደረገው ሁላችንም አይተናል:: ጀንበሬ ፊቱን ያዞርና ማነው ያደረገው? ብሎ ቢጠይቅ ሁሉም ዝም ይላል:: ሳላስበው እይታውን እኔ ላይ ያነጣጥርና ታደሰ፣ ማነው ያደረገው? ይለኛል:: እኔም አማረ ይልማ ነው እላለሁ:: በኔ ቤት እግዚአብሔር በሚያዘው መሠረት ሳልዋሽ ያየሁትን መናገሬ ነበር:: የሚፈለገውና የሚጠበቀው ይኸው መስሎኝ ነበር:: አማረ ቅጣቱን ይከናነባል:: ለእረፍት ስንወጣ ልጆቹ ሊበሉኝ ደረሱ:: በተለየ ኃይለማርያም አኒቼ የፎከረብኝና በዐይኑ አፈር ድሜ ያስጋጠኝ ምንም አልረሳውም:: በልጆቹ አመለካከት አሳባቂ መሆኔን ተረዳሁ:: እውነት ጥሬዋን የምትዘረገፍ ሳይሆን ተጠርዛ፣ ተቀባብታ፣ ወቅት ጠብቃ፣ እንደሸማቹ ፍላጎት ተሸሞንሙና የምትቀርብ መሆኑን አስተማሩኝ:: ያስተማሩኝ አድማ ስለመምታትም ነበር:: ያስተማሩኝ እውነትን መናገር ሥጋ በለበሱ ፍጡሮች ዐይን እንደጎጥያት ሊታይ እንደሚችል ነበር:: እውነቱን ለመናገር፣ እስካሁንም ልካንበት ያቃተኝ ከሰው ጋር በሰላም ለመኖር ከተፈለገ እውነት እንዴት መያዝ ወይም መስተናገድ እንዳለባት ነው:: ለራሱ ሰላም ብቻ ያደረ ሰው ማለት ያለበት ሁሉንም አላየሁም፣

አልሰማሁም፣ አልናገርም ነው:: ሆኖም፣ እውነት በመነገሩ ብዙ ሰው የሚጠቀም ከሆነ ግን እውነትን ተናግሮ በመሸበት ማደር እንደሚሻል አምኛለሁ::

ከትምህርት ቤት ዲሬክተሮች ምትኬ ደስታና ስምንተኛ ክፍል ሆነን የመጣውን ሙሉጌታን በተለይ አስታውሳቸዋለሁ:: አራተኛ ወይም አምስተኛ ክፍል ሆኜ ወንድሜ ብርሃኔ ከአሮጌው መጻሕፍት ተራ ክላራ ባርተን የሚል ባለሮዝ ቀለም መጽሐፍ ገዝቶ ይሰጠኛል፡፡ የአንደኛው ተርም ፈተና እንዳለቀ ይመስለኛል ከጥቂት የክፍል ጓደኞቼ ጋር ፒያሳ ዳርማር ጫማ ሱቅ ፊትለፊት ወደነበረው አሜሪካ ቤተመጻሕፍት እንሄዳለን:: መጽሐፉን ይዤዋለሁ:: የምናነበውን ወይም የምናገላብጠውን ጨርሰን ስንወጣ የቤተመጻሕፍቱ ኀላፊ ያስቆመኝና ይህ መጽሐፍ ከኛ የተሰረቀ ስለሆነ ይዘህ መሄድ አትችልም ብሎ ወሰደብኝ:: አልፎም፣ ትምህር ቤት ደውሎ ሁኔታውን ለምትኬ ነገረው:: ትምህርት ቤት ስሄድ ምትኬ ቢሮ ያስጠራኝና የትምህርት ቤታችንን ስም በክፉ አስነስተሃል ብሎ ገረፈኝ:: እኔም በጣም ተበሳጭቼ ሄጄ ለአባቴ፣ ሌባ አለመሆኔን ሄዳችሁ አስረዱልኝ፣ ያለጥፋቴ ስለመታኝም የተፈጸመብኝ ልክ አለመሆኑን ንገሩልኝ ብዬ ጠየቅኋቸው:: እሳቸውም አጎቴ ገብረሚካኤል ቡታን ይዘው ምትኬ ዘንድ ተያይዘን እንሄድና በምን ምክንያት እንደመታኝ ጠየቁት:: እጠየቅበታለሁ ብሎ አስቦ ስላልነበር የሆነውን ያልሆነውን ቀበጣጠረ:: እነሱ ግን አልተቀበሉትም:: ለማንኛውም፣ መብቴን በመጠኑም ቢሆን አስጠበቅሁ ብዬ ደስ አለኝ:: ከሁሉ አንገብግቦኝ የነበረው ሌባ መባሌ ስለነበር ስሜን ማንጻት ቻልኩ:: ስለመጽሐፍ ስርቆትና የአሮጌው መጻሕፍት ተራ ሚና የማይታወቅ ጉዳይ ስላልነበረ ወንድሜ ገዝቶ የሰጠኝ መጽሐፍ በእርግጥም የተሰረቀ ሊሆን ስለሚችል ሙግት ሳንገጥም ለቤተ መጻሕፍቱ ተውንለት::

ስምንተኛ ክፍል ሳለን የትምህርት ቤታችን ዲሬክተር ሆኖ የመጣው አቶ ሙሉጌታ በጣም የሚያስገርም ሰው ነበር:: እብዱ የሚል የቅጽል ስም አወጣንለት:: ሥራው ትምህርት ሚኒስቴር እየሄደ ልዩ ልዩ ማልያዎችን

በገፍ ማምጣትና ተማሪዎች ኳስ እንዲጫወቱ መገፋፋት ነበር:: ለሱ፣ ኳስ ቀዳሚ፣ ትምህርት ተከታይ ነበር:: ለኳስ ጨዋታ ስምሪት ማስገደዱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችንም ይጨምር ስለነበር ለስምንተኛ መልቀቂያ ፈተና ለማጥናት ከክፍል ሸሽተን ትምህርት ቤቱ ግርጌ የባሕር ዛፍ ጥቅጥቅ ውስጥ እንደበቃለን:: የክፍል ጓደኞችን ወልዱ ወልደገብርኤልን ካጠገቤ እንዳትለይ እያለ ያስቸግረው ስለነበር የጥናት ጊዜ እያጣ ሲጨነቅ እያየን እናዝንለት ነበር::

ስለትምህርት ቤቱ ግርጌ ሲነሳ ሃደሼ ወይም ሃጠሼ ትዝ ትለኛለች:: ልዑል መኮንን ወይም ወሰን ሰገድ ተምሮ የሃጠሼን በቆሎ ቂጣ ያልበላ ቢኖር በጣም ጥቂት ነው:: በነበረው ባሕላዊ ተጽእኖ ዳቦውን የበሉ ሴቶች ቁጥር ከወንዶቹ ቢያንስ አያስገርምም:: እህቴ ጽጌ ፓስቴ በላሽ ተብላ ድብን ተደርጋ እንደተገረፈች ቀደም ብዬ ገልጫለሁ::

የሙሉጌታ የምሽት ዋና ተግባር ደግሞ በየዳንስ ቤት መዞር ነበር:: ዳንስ ቤት ሲሄዱ በጓደኝነት የመለመላቸው ተማሪዎች ያጅቡታል:: ረብሻ ቢነሳና ተደባዳቢ ቡጢ ቢሰነዝርበት ተጋፍጦ የሚዘርር ጠባቂ አዘጋጅቷል:: ስለሆነም፣ ያለሐሳብ ሲጠጣ፣ ሲዳራ፣ ሲጫወትና ከተማውን ሲያስስ ያመሻል:: ሊነጋጋ ሲል ወደ ትምህርት ቤት ያመራል፤ ቀን ገርበብ አድርጎት የሄደውን የቢሮው መስኮት ገፋ ያደርግና ከጓደኞቹ ጋር ዘሎ ገብቶ በወለሉ ላይ ይነጠፋል:: ጠዋት ጠዋት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ዲሬክተሩ ቢሮ ፊትለፊት ካለው ትንሽ አደባባይ እንሰለፍና፣ ብሔራዊ መዝሙር ኢትዮጵያ ሆይ ላንቃችን እስኪሰነጠቅ ዘምረን፣ በሦስቱ ቀለማት ያሸበረቀችውን ባንዲራ ሰቅለን ኢትዮጵያን በእውቀት ብርሃን ጮራ ለመምራት ወደየክፍላችን ስንሽቀዳደም፣ አያ ሙሉጌታ ደግሞ ውድ ኢትዮጵያችን፣ ለሺህ አመታት ተኝተሻል፣ እኔ ውድ ልጅሽ ዛሬም እንደትናንትና መጥቼ ላቅፍሽ ተዘጋጅቻለሁ ብሎ የቢሮውን በር ይዘጋና፣ የለሁም ያሰኝና በጠራራ ፀሐይ ጨለማ ለብሶ እናት አገሩን ጨለማ ለማከናነብ ይጣደፋል::

ስለጥበቃ ሲወሳ በተለይ ትዝ የሚሉኝ የአንደኛ ደረጃ ጓደኞቻችን “ቂሱ” ስዩም ተሰማና ታምሩ ተስፋዬ ናቸው፡፡ ስዩም አንድ ቀን ደጃች ውቤ ሰፈር ሄዶ በማታ ሲንደፋደፍ የጠገቡ ጎረምሶች ያንፈራፍሩታል፡፡ በደሉን በወቅቱ በጉልበቱና በተጠቂ ጠባቂነቱ ለሚታወቀው ለታምሩ አስተዛዝኖ ይነግራል፡፡ በሚቀጥለው ማታ ታሜ ወንጀሉ የፈጸሙትን አንድ በአንድ አድኖ፣ እራሱን ፖሊስ፣ ዳኛና ወጋሪ ሾሞ በጓደኛው ስም አጋድሟቸው ተመልሷል፡፡

ከስድስተኛ እስከ ስምንተኛ ከክፍላችን ትንንሾቹ ታደለ ጀምበሬ፣ ናርዶስ ውብሸትና እኔ ነበርን፡፡ በትምህርት ውጤትም ከአብዛኛው ተማሪ የተሻልን ስለነበርን አንዳንድ አሳጡን የሚሉ ትልልቅ ልጆች ሊተናኮሉን ሲፈልጉ ጠባቂያችን ታምሩ ስለነበር እንወደዋለን፡፡ ጉልበተኛ ነኝ፤ እስቲ የሚደፍረኝ ይምጣ የሚለውን እንጂ ታምሩ ደካማ ወይም አቅመቢስ ሲተናኮል ወይም ሲያጠቃ አይቼው አላውቅም፡፡ የሕይወት ተልእኮውና ተግባራዊ እንቅስቃሴው ደካሞችን መጠበቅ ስለሚያካትት አድናቂው ነበርኩ፡፡ ይህም ሲባል መልአክ አይቻለሁ ብዬ ለመመስከር አይደለም፡፡ አንድ ጊዜ ከአንዲት ሴት ጋር ተጣልቶ እንደደበደባት ሰምቻለሁ፡፡ ምን ያህል ቢከፋባት ወይም ቢማረርባት ነው አልኩ እንጂ የታምሩ እምነትና ድርጊት ከረፋዱ የቀኝ ኋላ ዞረው ነበር ብዬ አላምንም፡፡

በዓመቱ መጨረሻ የትምህርት ውጤት መግለጫ የሚሰጠን ከትምህርት ቤቱ በውሰት የወሰድናቸውን መጻሕፍት ስናስረክብ ነበር፡፡ መጽሐፍ የጠፋባቸው ልጆች አሮጌው መጻሕፍት ተራ እየሄዱ መግዛት ይገደዳሉ፡፡ ገንዘብ የሌለው ይጠበባል፤ ይጨነቃል፡፡ የእንዳለ የክፍል ጓደኛው አስፋው ዋቂ ችግሩን የተወጣው በዘዴ ነበር፡፡ መጻሕፍት ተራ ይሄድና ማርች ኦፍ ታይምስን አሳዩኝ ይላል፡፡ አገላብጦ ዐይቶ በጠፋበት ምትክ ትምህርት ቤቱ የሚቀበለው ዓይነት መሆኑን ሲያረጋግጥ፣ መጽሐፉን ከደረቱ ጋር በሁለት እጆቹ ጥብቅ አድርጎ፣ ኡ ኡ ብሎ ጩኸቱን ያቀልጠዋል፡፡ አካባቢው የነበረ ሰውና ወሬ ቃራሚ ይሰበሰባል፡፡ ምን ሆንክ? ቢባል፣ ይኸው የተሰረቀብኝ

መጽሐፌን አግኝቻለሁና ይገቼ እሄዳለሁ ይላል። ነጋዴው አንጡራ ንብረቴን ላጭበርባሪ አሳልፌ አልሰጥም ይላል። አስፋው መጽሐፉን አንቆ ሙጭጭ ይላል። የአሮጌ መጻሕፍት ነጋዴዎቹ የተሰረቀ መጻሕፍት አደባልቀው እንደሚይዙ ያደባባይ ምስጢር ቢሆንም የሌባ ተቀባይ ተብለው እንዲታወቁ አይፈልጉም። ስለሆነም፣ የነጋዴው የሥራ ጓደኞች ነጋዴውን ወደ ጎን ወስደው፣ ይህ ሁሉ ሰው ተሰብስቦ ምንም ማድረግ ስለማይቻል ልቀቅለት ይሉትና ያግባቡታል። ጀብደኛው አስፍሽ ጨኸትንና የወሬ ተመልካችን ተገን አድርጎ፣ ስውር ሌብነትን በግልጽ ሌብነት ድል መትቶ ነጻ ያወጣውን የጊዜ ግስጋሴ የተሰኘውን መጽሐፍ እጉያው ሸጉጦ ጮቤ እየረገጠ ወደ ትምህርት ቤት ገሰገሰ።

ከአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የማይረሳ ትዝታ ከጣሉብኝ መካከል ጸጋዬ ኃይለማርያም ይገኝበታል። ያወጣልን የቅጽል ስሞች አንዳንዶቻችን ላይ አሁንም ተለጥፈውብን እንደቀሩ ናቸው። ጓደኞችን ስዩም ተሰማ አሁንም ስዩም ቁሱ ነው። እኔ ታደሰ ጫካ ነበርኩ፡ ጸጋዬ አሁን ቢያየኝ ታደሰ ሰሀራ ሳይለኝ አይቀርም። ኳስ ስንጫወት እርግጫዬ አስቸግሮት ነበር መሰለኝ ታደሰ አይረገም (ብረቱ) ይለኝ ነበር። አሁን ሽክላው መሆኔን ማን በነገረው።

ከ1953ቱ የመንግሥቱ ንዋይ ግርግር በኋላ ጸጋዬ ነው ከፍተኛውን የፖለቲካ ትምህርት ያኮመኮመኝ። እሱ የጉምሩክ ሠራተኛ ሆኖ፣ እኔ የ0ሥረኛ ወይም የ0ሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ መንገድ ላይ እንገናኛለን። ከየት እንደምመጣ ይጠይቀኛል። የኢትዮጵያ ጦር ሶማልያን ድል ስለመታ ጃንሆይን እንኳን ደስ ያለዎት ለማለት ቤተመንግሥት ደርሰን መመለሳችን ነው እለዋለሁ። ምስኪኑ የኢትዮጵያ ሰራዊት የእነራስ መስፍንን መሬት ለመጠበቅ ሲዋጋ በመሞቱ ደስ ብሎሃል እንዴ? ይለኛል። ጉዳዩን በዚህ መልክ አይቼው ስላልነበር ጸጋዬን እንደከሃዲም ላየው ፈለግሁ። ነገር ግን ስለማውቀው አባባሉን በቅጡ መረዳት አለብኝ አልኩና

ስለነገሩ ማሰላሰል ጀመርኩ፡፡ አባባሉ ድንበር የዘለለ ይሁን እንጂ ፍጹም ከእውነት የራቀ እንዳልሆነ ተረዳሁ፡፡

በሌላ ወቅት ስንገናኝ ልጋብዝህ ብሎ በዘመኑ ከታወቁት ያገር ምግብ ቤቶች ሜክሲኮ አደባባይ አጠገብ ወደ ነበረው አልማዝ ምግብ ቤት ይዞኝ ይሄዳል፡፡ ጣፍጦኝ በላሁ፡፡ በማግስቱ እንገናኝና የትናንቱ ምግብ ተስማማኽ ወይ? ይለኛል፡፡ ትንሽ ነዳኝ እለዋለሁ፡፡ "ድሮስ ቢሆን፣ አሹቅ ከለመደ ሆድ ምን ይጠበቃል?" ብሎ በታወቀበት በወርጅናሌ ቋንቋው ልኬን ነገረኝ፡፡

ኦኤዩ ሲቋቋም የማላዊ ፕሬዚዳንት ካሙዙ ባንዳ በመክፈቻው ሥነሥርዓት ላይ አልተገኙም፡፡ ከዚያም በኋላ በመሪዎች ስብሰባዎች ላይ ተገኝተው አያውቁም፡፡ ሰውዬው በነጻነት ትግል ወቅት የእነንክሩማህ የትግል ጓደኛ የነበሩና እሳት የሚተፉ፣ የለየላቸው ጸረ ነጭ አገዛዝ አቋም የነበራቸው፣ የአፍሪቃዊ ስብእና ተደፍሯልና ከወደቀበት ለማንሳት ባንድነት ቆመን ክንዳችንን ማፈርጠም አለብን የሚሉ ታጋይ አፍሪቃዊ ነበሩ፡፡ ገና ሥልጣን ላይ ከመውጣታቸው ዘረኛው የደቡብ አፍሪቃ አገዛዝ ባለሥልጣኖች አፋቸውን በብር ጠቅጥቀው ዝም አሰኙዋቸው፡፡ ይባስ ብሎ፣ አፍሪቃ ፣ አፍሪቃ ይሉት የነበሩት ሰው የስድብ ቃላት እየፈበረኩ የአፍሪቃ መሪዎችን ኢላማቸው አደረጉ፡፡ ሕዝባቸውን ስለአፍሪቃውያን ቋንቋና ታሪክ እንደማስተማር ቅድሚያ ለላቲን ሰጡ፡፡ ባጭሩ፣ ነጭ አምላኩ ሆነው ቁጭ ይላሉ፡፡ የእልፍኝ አስከልካያቸውና የጓዳ አማካሪያቸው ነጭ ሴት መሆኗ ከመታወቁ በቀር፣ ዘረኞች ከገንዘብ ሌላ አፍዝ አደንግዝ አቅምሰዋቸው እንደሆነ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡

ባንዳ የአፍሪቃ አንድነትን በማጥላላት ስላደረጉት ንግግር ጸጋዬ ኃይለማርያም የነገረኝ ዐይናችንን በደንብ ባልከፈትንበት፣ በፖለቲካ ድንጋይ ዳቦ ዘመን፣ ከአርባ አመት በፊት ነበር፡፡ የነገረኝን ቃል በቃል አስታውሰዋለሁ፡፡ አፍሪቃን ሊደርስ አር ኔሮስ ኖት ሂሮስ፤ ዘይ አር ፕሌዩንግ ዘ ፓን አፍሪካኒዝም ኦርኬስትራ ሁዌን ዜር ሆምስ አር በርኒንግ

(African leaders are Neros, not heroes; they are playing the Pan Africanism orchestra when their homes are burning)፡፡ *ትርጉሙ፣ የአፍሪቃ መሪዎች ጀግኖች ሳይሆኑ እንደሮማው ቄሳር ኔሮ ቤቶቻቸው ሲቃጠሉ እያዩ እንደሚጨፍሩ ሰዎች ናቸው፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ አፍሪቃን ሊደርስ አር ላይክ ሃይናስ፣ ዘይ ሃውል ኤንድ ግራውል፣ በት ዘይ ዱ ኖት ባይት* (African leaders are like hyenas; they howl and growl but they do not bite) ብለዋል፡፡ *የአፍሪቃ መሪዎች በጅብ ይመስላሉ፤ ማላዘንና ማጉረምረም እንጂ ጠላታቸውን መጋፈጥ ይፈራሉ እንደማለት ነው፡፡*

*እንደኔ ታጋይ የለም ይሉት የነበሩት ባንዳ መርዘኛ በታኝ ለመሆን ታጥቀው መነሳታቸው ሁሉንም አስገረመ፡፡ የፖለቲካ ሰዎች ምርጫን ለማሸነፍ ወይም በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠው ለመቆናጠጥ ሲሉ የሚለፍፉትን ብቻ ሳይሆን ድርጊታቸውንም በውል መከታተል እንደሚያስፈልግ ባንዳ ጥሩ ማስረጃ ናቸው፡፡ ባንዳን የሰቀላቸው ሕዝብ በቀላሉ ሊያወርዳቸው ባለመቻሉ የማላዊ ሕዝብ የከፈለው መስዋዕትነት ከፍተኛ ቢሆንም ውሎ አደረ እንጂ ማንነታቸው ተጋልጦ፣ ማቅ ተከናንበው ወደሚወርዱበት ወርደዋል፡፡ ባንዳን በአገራቸው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ታሪኩን አንባቢ ወደኋላ ያገኘዋል፡፡*

*ቀደም ብሎ አገር ለቆ ሂዶ የነበረ የጸጋዬ ጓደኛ የ1966ቱ አብዮት እንደፈነዳ ይመለስና ለአብዮቱ መሳካት አስተዋጽኦ ለማድረግ አንደተዘጋጀ የሚመለከታቸው እንዲያውቁለት ያደርጋል፡፡ ጸጋዬ ስለሰውዬው መመለስ አስተያየቱን ሲገልጽ፣ እገሌ እበላለሁ ብሎ አ ብሎ አፉን ከፍቶ መጥቷል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክፉ ነው፡፡ እንካ ብሎ ድንጋይ ያጎርሰዋል ብሏል፡፡ ሰውየው የሚያጠግብ ነገር ስላላገኘ ለሁለተኛ ጊዜ አገር ጥሎ ወጣና በዚያው ለዘለአለም ሲቀር የኢትዮጵያ አብዮት በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ምርጥ ልጆቹን፣ ውድ ወንድሜ አብርሃምን ጨምሮ፣ ቅርጥፍ አድርጎ በላ፡፡*

ጸጋዬ የእግዚአብሔርን ልጅ አግኝቶ፣ ሙሉ ጊዜውን እሱን ለማገልገል ወስኖ፣ የዓለምን ነገር ለዓለማውያን ትቶ የጎልማሳ ኑሮውን ከተያያዘው ውሎ አድሩዋል፡፡ የሰማዩን ትቶ ወደ ምድራዊ ዝባዝንኬ እንዲመለስ ጓደኞቹ ባንመኝለትም የፖለቲካ ትረባው፣ ሽሙጡ፣ ጸጉር ሰንጣቂነቱ፣ የነገር ብልት አውጭነቱ ስለሚናፍቀን ትርፍ ጊዜ ፈልጎ ቢያጫውተን የሰማዩ አባታችንም የሚወደው ነገር ሳይሆን አይቀርም፡፡

ባለሥልጣኖች መስመር ሲስቱ፣ በሥልጣን ሲባልጉ፣ ከሕዝብ አገልጋይነት ወደ ተገልጋይነት እራሳቸውን ሲያሸጋግሩ እንደጸጋዬ ዓይነቶቹ ቆቅ ተመልካቾችና አንደበተ ርቱኦች በለብላቢው ምላሳቸውና ተናዳፊው ብዕራቸው ሰቅጠጥ እንዲሉና ቆም ብለው እንዲያስቡ ስለሚያደርጓቸው እነዚህን ሕዝብ አቅፎና ደግፎ ሊይዛቸው ይገባል፡፡

ለአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና እየተዘጋጀን እያለ አንድ ቀን የትምህርት ቤታችን ምክትል ዲሬክተር አቶ ደስታ ወልደትንሣኤ ክፍላችን ድረስ ይመጣና ወደፊት ምን መሆን እንደምትፈልጉ ግለጹ ይለናል፡፡ ትዕዛዙ ወይም መመሪያው የመጣው ከትምህርት ሚኒስቴር ነው ያለን ይመስለኛል፡፡ የነገርነውን በየስማችን አኪያ አስፍሮ ሄደ፡፡ እኔ ከገንዘብ ነክ ሥራ በስተቀር በማናቸውም ዓይነት ሙያ ላይ ለመሰማራት ዝግጁ እንደሆንኩ ተናገርኩ፡፡ ታደለ ጀምበሬ ዶክተር መሆን እንደሚፈልግ ተናገረ፡፡ ታደለ የተመኘውን አግኝቷል፤ እኔ ደግሞ የልጅነት መንፈሴ የጠላውን ታቅፌ ቀርቻለሁ፡፡ ገንዘብ ነክ ሥራ አልፈልግም ያልኩበት ምክንያት አባቴ የእቁብ ዋስ እየሆኑ ዋስ የጠሯቸው ሰዎች የእቁብ ክፍያ እያቆሙ ሲቸገሩ ዐይ ስለነበር ነው፡፡ ገንዘብና ችግር የተቆራኙ አድርጌ ወስጃቸው ነበር ማለት ነው፡፡ በእቁብ ዋስትና ችግር የተነሳ በአንድ ወቅት መኖሪያ ቤታችን ሊሸጥ ነበር፡፡ ገንዘብ የደስታ ሳይሆን የችግር ምንጭ ነው የሚለው አመለካከቴ ስለሚያይል ነው መሰለኝ ሕይወቴ ወይም የቤተሰቤ ሕይወት በገንዘብ አስተዳደር ምክንያት እንዳይቃወስ ወይም እንዳይዛባ የማደርገው ጥንቃቄ አብዛኛው ሰው ከሚያደርገው በላይ ይመስለኛል፡፡

ብድርና ዱቤ አልደፍርም፣ የነገን እግዚአብሔር ያውቃል በሚል በደመነፍስ አልገዝም፤ እንደኪሴ እንጂ እንደጎረቤቴ አልኖርም፤ ዘመን አመጣሽ ነገሮች ግልጽ ጠቀሜታ ከሌላቸው በቀር በዘመናዊነት ስም ተሽንግዬ አላግበሰብሳቸውም:: በመሆኑም በገንዘብ አስተዳደር ምክንያት ተዋርጄ ወይም ሕይወቴ ተውሰብስቦ አያወቅም:: በዚሁ እንዲያዘልቅልኝ የገንዘብ አምላክን አደራ ብዬዋለሁ::

# ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

ስምንተኛ ክፍል ስንገባ የትምህርት ቤታችን ስም ተቀይሮ ወሰን ሰገድ ተባለ:: በ1949 ለሞተው ለልዑል መኮንን ማስታወሻ ከተሠሩት ሕንጻዎች አንዱ መርካቶ እራስጌ ያለው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው:: የቀድሞው ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት በሚቹ የበኩር ልጅ በወሰን ሰገድ ተሰየመና አዲሱ ትምህርት ቤት የሚቹን ስም እንዲይዝ ተደረገ::

በ1952 አንደኛ ደረጃ ስንጨርስ እኔ የተመደብኩት ልዑል መኮንን ትምህርት ቤት ነበር:: ትምህርት ቤቱ አዲስ በመሆኑ ጥራቱ ያልተረጋገጠ ስለነበርና በወቅቱ የአለማያ እርሻ ኮሌጅ ተማሪ የነበረው ወንድሜ ብርሃኔ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እንድገባ ስላደፋፈረኝ ምድቤ እንዲቀየር ጠየቅሁ:: እንግሊዛዊው የልዑል መኮንን ዲሬክተር የአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ውጤቴ ጥሩ መሆኑንና በስምንተኛ ክፍል ውጤትም አንደኛ መውጣቴን አይቶ ሊለቀኝ አልፈለገም ነበር:: ለምን ወደ ተፈሪ መኮንን መቀየር እንደምፈልግ አጥብቆ ቢጠይቀኝ፣ ወላጆቼ መኖሪያቸውን ወደ ስድስት ኪሎ አካባቢ ስላዛወሩና የአውቶቡስ ገንዘብ ከፍዬ መርካቶ መመላለስ አቅም ስለሌለኝ ነው ብዬ ዋሸሁት::

ከጥቂት ውጣ ውረድና የትምህርት ዓመቱ ከጀመረ ከዐሥራ አምስት ቀናት በኋላ፣ ጥቅምት 1953 መጀመሪያ ላይ፣ ወደ ተፈሪ መኮንን መቀየር ቻልኩ:: በተፈሪ መኮንን ትምህርት የጀመርኩበት የመጀመሪያው ቀን

ትዝታ ከአእምሮዬ የማይጠፋ ነው፡፡ ዲሬክተሩ ሪሼ ቢሮ ሄጄ መምጣቴን ከማመልከቴ ወዲያውኑ በቁራጭ ወረቀት ማስታወሻ ጽፎ ሰጥቶ ምክትል ዲሬክተሩ ጋኞ ቢሮ ሂድ አለኝ፡፡ ሲነግረኝ አማርኛ ደባልቆ ስለነበር ምክትል ሲል መከተ ያለ መስሎኝ የመከተ ዲሬክተሩ ቢሮ የትኛው ነው? እያልኩ ሳጠያይቅ ስሕተቴ የገባው አንድ ተማሪ ጋኞ ቢሮ ድረስ ወሰደኝ፡፡ ጋኞም 9ኛሲ ማስታወሻ አስይዞ ላከኝ፡፡ 9ሲ ሄጄ ሳንኳኳ የታወቀው ስካውት ማስተር ሚስተር ቦድሪ እንግሊዝኛ እያስተማረ ነበር፡፡ ማስተማሩን ያቆምና በራፍ ድረስ መጥቶ እንኳን ደህና መጣህ ብሎ ጨበጠኝና ተማሪዎቹን ተነስታችሁ ቁሙ አላቸው፡፡ በጣም ተገረምኩ፤ ተደነቅሁ፡፡ ልዑል መኮንን ለጥቂት ቀናትም ቢሆን በቆየሁበት ወቅት አንድ ሬኖልድስ የሚባል አሜሪካዊ አስተማሪ ተማሪን በእርግጫ ሲመታ አይቼ ስለነበር እዚህ ከተደረገልኝ አቀባበል ጋር ሳነጻጽረው ልዩነቱ እንደሰማይና መሬት አከለብኝ፡፡ ልዩ እርካታም አሳደረብኝ፡፡ የሰው ስብእናው ሲከበር በጣም በጣም ስለሚያስደስተኝ ልቤና መንፈሴ የሚፈልጉትን እንዳገኙ ተሰማኝና ከልብ ደስ አለኝ፡፡

ተነስተው የቆሙትን ልጆች በዐይኔ ስቃኝ እይታዬን የሳበው ጸጉሩ ወደኋላ የተበጠረው፣ አረንጓዴ ጃኬት፣ ሰማያዊ ጂንስ ሱሪና ቀይ ሸሚዝ የለበሰው፣ በሁለት እጆቹ ዴስኩን የተደገፈው ገዛኸኝ ታደሰ ነበር፡፡ ሚስተር ቦድሪ ከምሳሌ ሰለሞን ጎን በነበረው ባዶ ስፍራ ሄጄ እንድቀመጥ ነገረኝ፡፡ እንደተቀመጥኩ ተማሪዎች ቁጭ እንዲሉ ተፈቀደላቸው፡፡ ከገዛኸኝ ጋር በዐይን ብቻ ሳይሆን ልብ ለልብም ተገናኝተን የምስጢር ጓደኛሞች ሆነን ቀርተናል፡፡ የጓደኝነታችን ጥንካሬ የታወቀ ነበር፡፡ አስራ አንደኛ ክፍል ሆነን አንድ ሰዋራ ስፍራ ላይ ግንብ ተደግፈን ተቀምጠን ስንጨዋወት የክፍል ባልደረባችን ከበደ ያየናል፡፡ ከበደ መልኩ በጣም ጠይም ስለነበር ስለጠይምነቱ እኛ ብቻ ሳንሆን እራሱም ይቀልድ ነበር፡፡ ሲያየን፣ "ገዛኸኝንና ታደሰን የሚለያይ ይጥፋ? ቀይ ጠብቁ፣ ሌሊት ሰይጣን ሆኜ መጥቼ ባልለያያችሁ" ብሎ አስቆናል፡፡

በጊዜው ትምህርት ቤቱን በኃላፊነት የሚያስተዳድሩት ከካናዳ፣ ክዊቤክ፣ የመጡ ኢየሱሳውያን የተሰኙት ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ነበሩ። ከመንግሥት ጋር በነበራቸው ስምምነት መሠረት ይመስላል የሃይማኖት ትምህርት አያስተምንሩም ነበር። እንዲውያም፣ በግብረገብ ስም ስለኦርቶዶክስ ሃይማኖት እንማር ነበር። ከአማርኛ ትምህርት በቀር አስተማሪዎቻችን ካናዳውያንና ከኬሬላ፣ ህንድ፣ በካናዳውያኑ ተመልምለው የሚቀጠሩ ክርስትያኖች ነበሩ።

የተፈሪ መኮንን ሚሲዮናውን ለምን የሃይማኖት ትምህርት አይሰጡን እንደነበር ለመረዳት የኢትዮጵያን ታሪክ ወደኋላ መለስ ብሎ መዳሰስ ያስፈልጋል። የግራኝ ጦር ተመትቶ ወደመጣበት ወደ ሐረርጌ ከተሻገረ በኋላ የካቶሊክ ሃይማኖት ሰባኪያን በብዛት አገራችን መግባት ጀመሩ። ቀስ በቀስም የሕዝቡን ሥነልቦና ሰልበው ለአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ሁኔታዎችን ለማመቻቸት አስበው ሳይሆን አይቀርም የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚከተለው የክርስትና ሃይማኖት የተሳሳተ ወይም ያልተስተካከለ ስለሆነ ካቶሊካዊነትን መቀበል አለባችሁ ብለው ወጥረው ይይዛሉ። 1600ኛው መቶ አመት መባቻ ላይ አጼ ሱስንዮስን እንደምንም ብለው ያሳምናሉ። ንጉሡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተለውጦ በካቶሊካዊነት ተተክቷል ብለው ያውጃሉ። ቄሱም ሕዝቡም አልቀበል ይላል። ያወጁትን ኃይል ተጠቅመው ተግባራዊ ለማድረግ ይሞክራሉ። ሕዝብ ከሸፈተ የሚያቆመው ወይም የሚቋቋመው ስለሌለ ሳይሳካላቸው ይቀራል። ኢትዮጵያ እንደገና የጦርነት አውድማ ሆነች። ከዐሥራ አምስት አመት ፍዳ በኋላ ንጉሡ ተስፋ ቆርጠው፣ አልጋቸውን ለልጃቸው ለፋሲለደስ አውርሰው ገዳም ገብተው አረፉት። አጼ ፋሲልም ያባታቸውን አዋጅ ሽረው ሕዝቡ በአባቶቹ ሃይማኖት እንዲጸና ፈቀዱለት። የዕለት ተዕለት ሥራውንም ተረጋግቶ እንዲያከናውን አበረታቱት።

አንድ ፈረንጅ እንዳላይ ብለው አውሮጳውያኖቹን ከአገራችን ሙልጭ አድርገው ማስወጣት ብቻ ሳይሆን ተመልሰው እንዳይመጡም አወጁ።

ፈረንጆች ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የጀመሩት ረጅም ጊዜ ካለፈ በኋላ አንድ ሁለት እያሉ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፈረንጂና ለክርስትና ሃይማኖት ሰባኪዎች ልቡን ላለመስጠት የወሰነው ካቶሊኮች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሃይማኖትን ለማጥፋት በነበራቸው ገሀድ አላማ የተነሳ ነው:: በዚህ አንጻር፣ የፋሺስት ጦር ኢትዮጵያን ለመውረር በ1928 ሲነሳ የባረከው የሮማው ካቶሊክ ቤተክርስትያን ስለመሆኑና ለዚህም አረመኔያዊ ድርጊት የኢትዮጵያ ሕዝብ እስካሁን ይቅርታ እንዳልተጠየቀ በፍጹም መረሳት የሌለበት ጉዳይ ነው:: ኢየሱሳውያኑም ይህችን ስለሚያውቁ ብዙ ነገር መነካካትና የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያንን ቁጣ በላያቸው ላይ ማዝነብ አይፈልጉም ነበር::

አሁን ግን እነሱም እንደሌሎች ሰባኪያን ሁሉ በነጻነት ስምና የሕዝቡን ድህነት እንቀርፋለን እያሉ የሚፈልጉትን ሲያደርጉ እየታየ ነው:: ይህ አዲስ ክስተት በኢትዮጵያዊነት ሥነልቦናና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ወይም ተጽእኖ የሚታወቀው ወደፊት ነው:: ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከኦርቶዶክስ ሃይማኖት ጋር የተቆራኘ ስለመሆኑ ማንም የሚክደው ስላልሆነ ገንቢ ውጤት ይኖረዋል ብሎ መጠበቅ የዋህነት ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም፣ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በሃይማኖትነቱ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ አንድነት መሠረት መሆኑ ታውቆ መጠበቅ ያለበት ነው::

በሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ፈረንጆች ያፍሪቃውያንን ሥነልቦና በልዩ ልዩ መንገድ ይፈታተኑ እንደነበር ከብዙ አቅጣጫ የሰማነው ነው:: እኔ እንደተመለከትኩት የተፈሪ መኮንን አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸው ብቃት ኖሯቸው የአገር አመራር ኃላፊነት ለመረከብ ዝግጁ እንዲሆኑና ሕዝብ የጣለባቸውን አደራ እንዳይበሉ በየአጋጣሚው ከማሳሰብ ቦዝነው አያውቁም:: በትምህርት ቤቱ ያስተማሩ ኢየሱሳውያን የኢትዮጵያን ሳይሆን የውጭ ኃይሎችን ጥቅም ለማስጠበቅ የመጡ ነበሩ ብሎ የሚጠረጥራቸው

የተፈሪ መኮንን ተማሪ ነበር ብዬ አላምንም። እንዲያውም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለእነሱ ባለውለታ ነው እላለሁ።

በ1953 ዘጠነኛ ክፍል በአራት ሴክሽን ተከፍለን የጀመርነው ተማሪዎች ቁጥራችን 135 ሲሆን ዐሥራ ሁለተኛ ደርሰን ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የተቀመጥነው 17 ብቻ ነበርን። ዐሥራ አንዳችንን ዩኒቨርስቲው ለዲግሪ ፕሮግራም ተቀበለን።

ጓደኛዬ ገዛኸኝ ለዲግሪ ፕሮግራም የሚያበቃውን መለኪያ ለጥቂት ሳያሟላ ቀረና ከእንዳለ በኋላ ከሌላው ከምወደው ጓደኛዬ ለመለያየት ተገደድኩ። ደግነቱ ገዛኸኝ በሚቀጥለው አመት የሚፈለገውን አሟልቶ ለዲግሪ ፕሮግራም መግባት ቻለና እንደገና ተገናኘን።

በ1956 መጨረሻ እኔ ዩኒቨርስቲ ለመግባት ስዘጋጅ፣ ገዛኸኝ ደግሞ ቋሚ ሥራ እየዞረ ሲፈልግ ቆይቶ ወወክማ ፊት ለፊት ከሚገኘው የጡረታ ኮሚሽን የክረምት ሥራ ያገኛል። ለሥራው ለመመረጥ የበቃው በእጅ ጽሑፍ ፈተና አጥጋቢ ውጤት ስላስመዘገበ ነበር። ቋሚ ሥራ ለመፈለግ እንደገና ብሰማራ ይሻለኛል አለና  የተገኘውን የክረምት ሥራ እድል እኔ በሱ እግር ተተክቼ የምጠቀምበትን ዘዴ አውጠነጠንን። ገዛኸኝ ታደሰ ነኝ ብዬ እንድቀርብ ተስማማን።

ሥራው በሚጀመርበት ቀን ፈተናውን ያለፉት ተማሪዎች ተሰብስበው በሠራተኛ አስተዳደር ኃላፊው ቢሮ ተገኙ። እኔም ተደባልቄ ቀረብኩ። ሌሎቹን ማመልከቻ ለማስገባት ሲመላለሱ፣ የእጅ ጽሑፍ ፈተና ሲወስዱ አስተዳዳሪው ዐይቷቸዋል። እኔን ዐይቶኝ ስለማያውቅ አንተ ደግሞ ማነህ? ይለኛል። ታደሰ እለዋለሁ። አከታትዬ፣ ይቅርታ ገዛኸኝ ታደሰ ማለቴ ነው እለዋለሁ። ስምህን የማታውቅ ነህ እንዴ? ቢለኝ፣ የለም፣ ያባቴን ስም አስቀድሜ መጥራት ስለሚቀናኝ ነው እለዋለሁ። እኔም ያራዳ ልጅ ነኝ፣ ሞኝህን ፈልግ፣ በል ናና ገዛኸኝ የጻፈውን ጽሑፍ ገልብጠኽ አሳየኝ ብሎ የገዛኸኝን የፈተና ወረቀት አውጥቶ ይሰጠኛል። እንዳጋጣሚ ሆኖ የኔና

የገዛኸኝ የእጅ ጽሑፍ ከመመሳሰልም አልፎ አንድ ይመስላል:: በመሆኑም የገዛኸኝን የእጅ ጽሑፍ አስመስዬ በቀላሉ ገለበጥኩት:: የቁጥር አጣጣላችንም አንድ አይነት ሆኖ በ9 ቁጥር ላይ ልዩነት እንዳለን ፊት ለፊቴ ካለው የገዛኸኝ ጽሑፍ ዐየሁ:: እሱ እግሩን ቀልበስ ሲያደርገው እኔ ቀጥ አድርጌ እለቀዋለሁ:: በዕለቱ ግን እኔም እንደሱ ወደላይ ቀለበስኩት:: አስተዳዳሪው ገዛኸኝ መሆኔን ይመንም አይመን ጽሑፌን ስላልጠላው ምን አደርጋለሁ የሚልም ይመስላል ተቀበለኝ:: ሦስት ወር ጡረተኞች የሞሉትን ቅጽ ኮሚሽኑ ባዘጋጃቸው ፎርሞች ከዐሥር ከማያንሱ ሌሎች ተማሪዎች ጋር በወር ሰባ ብር እየተከፈልን ሳወራርስ ከረምኩ::

ሥራውን ከጀመርኩና እንደማልባረር ሳውቅ ለክረምት ሥራ ለተቀጠሩት ተማሪዎችና ለክፍሌ ሠራተኞች ገዛኸኝ ሳልሆን ታደሰ መሆኔን ነገርኳቸውና በትክክለኛው ስሜ ይጠሩኝ ጀመር:: ከክፍሉ ሠራተኞች አንደኛው አሻፈረኝ ብሎ ግንኙነታችን እስኪቋረጥ ድረስ ገዛኸኝ ይለኝ ነበር::

እኔ የተመደብኩበት ክፍል ኃላፊ አቶ አምዴ ይባላል:: በጣም ትጉህ፣ ሠርቶ የሚያሠራ አለቃ ነበር:: የሥራ ሰዓት ያከብራል፣ ጨዋ ነው፣ አጓጉል አመሎች የሉትም:: ባጭሩ፣ የተዋጣለት የሥራ መሪ ነው:: ከዕለታት አንድ ቀን፣ ከምሳ በኋላ፣ ቅጾችን በካርድ ለማወራረስ የሥራ እቅድ ተይዞ የነበረበው የግቢ ሚኒስቴር ሠራተኞች ለሞሉዋቸው ቅጾች ነበር:: ክፍሉ የተመደብነው ተማሪዎችና ቋሚ የክፍሉ ሠራተኞች በዚያን ዕለት ያለወትሮ ቀደም ብለን ገብተናል:: ቅጾቹ ከካዝና ወጥተው አምዴ ጠረጴዛ ላይ ተከመሩ:: እንደተለመደው እያንዳንዱን ቅጽ ከፊት ለፊቱ ቅጹን የሞላው ወይም የሞላችው የመንግሥት ሠራተኛ ፎቶግራፍ ተለጥፏል:: ሥራ ለመጀመር ጥቂት ደቂቃዎች ይቀሩ ስለነበር ቅጾቹን ከመከፋፈላችን በፊት ገልበጥ ገልበጥ እያደረግን ስናይ ፎቶግራፎቹ ሌላ ጊዜ ከምናውቃቸው ዓይነት ለየት ያሉ ሆነው አናገኛቸዋለን:: አብዛኛዎቹ ሠራተኞች ሴቶች ሆነው የብዙዎቹ አንገታቸውና ጆሮዋቸው በጌጣ ጌጥ

ያሸበረቀ ነበር። ፎቶግራፎቹን እያየን አስተያየት መስጠትና አቃቂር ማውጣት ተጀመረ። ይህቺ የእቴጌን ወገብ፣ ይህች ደግሞ ጭናቸውን የምታሽ ናት፣ ወዘተ እንባባላለን። እንሳሳቃለን። በዚያ ሲያልፉ የነበሩት የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ፣ አቶ ለገሰ በዙ፣ ስብሰባው ምን እንደሆነ ለማየት የኛን ቢሮ ውስጥ ለውስጥ ከሚቀጥለው ቢሮ ጋር ከሚገናኘው በር በኩል ቀስ ብለው ይገቡና የሚደረገውን ያያሉ፣ የሚባለውን ያዳምጣሉ። የሁሉም ትኩረት ፎቶግራፎቹ ላይ ነበርና እሳቸውን አላየናቸውም። አንዱ ድንገት ቀና ሲል ያያቸዋል። በተለይ ቋሚዎቹ ሠራተኞች ሰማይ የተደፋባቸው፣ መሬት የከዳቻቸው መስሎዋቸው በጣም ደነገጡ። አቶ ለገሰም "አምዴ፣ ሥራህ ለካስ ይኼ ኖሯል? አየሁልህ" ብለውት ወደ ቢሮአቸው አመሩ።

አምዴ እጅግ አዘነ፣ ሁላችንም አዘንለት። ቀን ከድቶት፣ ያለሥራው፣ በእድሉ ላይ ምስማር እንደተቸነከረበት አወቀና ቅስሙ ተሰበረ። ከጊዜ ብዛት አገግሞ እንደሆነ አላውቅም።

በ1966ቱ አብዮት ወቅት አቶ ለገሰ የወሎ አስተዳዳሪ ሆነው የክፍለሀገሩ ሕዝብ በረሃብ ምክንያት መሰደዱን አስመልክቶ የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ፣ ይህ እስኪሆን ድረስ ምን ታደርጉ ኖርዋል? ብሎ ቢጠይቃቸው «የወሎ ሕዝብ መሰደድ ድሮም ልማዱ ነው» በማለታቸው ሲብጠለጠሉና ለአብዮታዊ ፍርድ ሲዳረጉ፣ አቶ አምዴ በቂም ተነሳስቶ እሰዬው አለ? ወይስ ቀን ወይም ምላስ ስለከዳቸው አዝኖ፣ ነግ በኔ መሆኑን ሁልሽም እወቂበት ብሎ ጓደኞቹን አስጠነቀቀ? የኋለኛውን አድርጎ ከሆነ አምዴ ትልቁ ሰው እለዋለሁ።

# አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

በመስከረም 1957 በንግድ አስተዳደር ኮሌጅ የሒሳብ አያያዝና የንግድ ሥራ አመራር ትምህርት መከታተል ጀመርኩ።

ሁለተኛ አመት እንደጨረስኩ ለክረምት ሥራ ትምባሆ ሞኖፖል ቀጠረኝ:: በወቅቱ የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ትንሣኤ ነበሩ:: የተቀጠርኩት የድርጅቱ አስተዳደር የሚሻሻልበትን መንገዶች አጥንቼ ሐሳብ እንዳቀርብ ነበር:: ስለ ድርጅቱ ደኅና ግንዛቤ እንድጨብጥ ታስቦ ከመዝገብ ቤት እንድጀምር ተደረገ:: ሥራውን የጀመርኩ ዕለት ስልክ ይደወላል:: የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ ከስልኩ ራቅ ብሎ ፋይል ይፈልግ ስለነበር ስልኩን አነሳሁት:: ሃሎ የሚል ድምጽ መጣ:: መልሼ ሃሎ አልኩ:: እንደገና ሃሎ አለ:: እኔም መልሼ ሃሎ አልኩ:: ይሄኔ በቁጣ፣ የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ የለም እንዴ? ይለኛል:: አለ ስል አሁንም በቁጣ ቶሎ አቅርበው ብሎ አዘዘኝ:: አቀረብኩ:: ሠራተኛው የሰውዬውን ድምፅ እንደሰማ ፈንጠር ብሎ ከመቀመጫው ተነስቶ እጅ እየነሳ ቋንቋው አቤት ጌታዬ፣ እሺ ጌታዬ ብቻ ሆነ:: ደጋግሞ ደጋግሞ እጅ ይነሳል:: ጌታዬ፣ ለክረምት የተቀጠረ ተማሪ ነው ሲል ሰማሁ:: ስልኩን እንደዘጋ ወንበሩ ላይ ዝልፍልፍ ብሎ ዘጭ ይልና፣ እግዚአብሔር ይይልህ፤ ከሃያ ዓመት በላይ ከሠራሁበት መሥሪያ ቤት ልታፈናቅለኝ፤ ዐይን ያልከፈቱ ልጆቼን በምን ላሳድጋቸው ነው? እያለ እሮሮውን አዥጎደጎደው:: ወይኔ፣ ወይኔ ይላል:: ምን ተፈጠረ? ብለው፣ አንተ ነሃ፣ የቦርዱ ሊቀመንበር አቶ ታደሰ ያዕቆብ ናቸው እኮ፣ እሺ ጌታዬ እንዴት አትልም? ብሎ አምቧረቀብኝ::

አቶ ታደሰ ያዕቆብ ስማቸውን በዜና ማሰራጫዎች ከመስማቴ በቀር ድምፃቸውን በስልክ የምለይበት ዘዴ አልነበረኝም:: ለይቼ ባውቀውም ኖሮ እሺ ጌታዬ ማለት ትምህርት ቤት አላስተማሩኝም፣ ቤቴ ስልክ ስለሌለ አልለመደብኝም:: አንድ ሰው በግድ አክብረኝ ስላለኝ ሳይሆን ከልብ የማከብረው ከሆነና በእድሜ ብዙ የሚበልጠኝ ከሆነ "ጌታዬ" ማለት አሁንም ልምዴ ነው::

በሰዎች መካከል መኖር ስላለበት ጤናማ ግንኙነት ተማሪ ቤት የተማርኩት፣ በማናቸውም መስክ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ከተፈለገ ሰው በሰውነቱ ስብእናውን ማክበርና ማበረታታት እንጂ ወልደማርያም

ገብረማርያምን እንዴት አድርጎ ሥነልቦናውን ገፎ በቁጥጥሩ ሥር እንደሚያደርገው አልነበረም። እኛ የተማርነው ሰው ከአጓጉል ተጽዕኖዎች ቢላቀቅ ወይም አእምሮው ነጻ ቢደረግ የእድገትንና የብልጽግና መሠረት መጣል እንደሚቻል ነው። ኢትዮጵያን ወደኋላ ያስቀራት በየመስኩ የእውቀትና የጥበብ ማነስ ሲሆን የችግሩ ዋና መሠረት ግን ፊውዳላዊው ሥርዓት እንደሆነ ተማሪው አካባቢ ሙሉ ግንዛቤ ስለነበር ነው የተጠቀሰው ሥርዓት መገርሰስ አለበት ብሎ ተሜ ሽንጡን ገትሮ የተነሳው። ስለሆነም፣ የአቶ ታደሰ ቁጣና የመዝገብ ቤቱ ሠራተኛ ፍርሃት በነገው ኢትዮጵያ ቦታ አይኖራቸውም ብዬ አሰብኩ እንጂ እራሴን እንደጥፋተኛ በፍጹም አልቆጠርኩም።

የሦስተኛ አመት ተማሪ ሆኜ የኮሌጃችን ጋዜጣ አዘጋጅ ነበርኩ። ጋዜጣውን "ቢዝነስ አውትሉክ" ብዬ ሰይሜ ኅትመቱን የጀመርኩት እኔ ልሁን እንጂ ብዙ ተባባሪ ነበረኝ።

በአዳሪነት ዩኒቨርስቲው ቅጥር ግቢ የሚኖሩ ሴቶችን ከዩኒቨርስቲው ውጭ የሚመጡ ሰዎች ፎርም እየሞሉ እንደሚያወጡዋቸው ደርሼበታለሁ ብሎ አንዱ የጋዜጣችን ተባባሪ ይነግረኛል። ለጋዜጣችን ከዚህ የበለጠ ትኩስ ዜና ሊኖር አይችልምና ፎርሙን እንደምንም ፈልገህ አግኝልኝ እለዋለሁ። ጥቂት ካደከመው በኋላ ሰንበት ብሎ አግኝቶ አመጣልኝ።

የተረዳሁት፣ የተማሪዎቹ ሞግዚት ወይም የሆስቴሉ ኃላፊ አንዲት አሜሪካዊት እንደሆነች፣ የፎርሙ አላማዎች ሴቶች ተማሪዎች የኑሮ ጓደኛ ለመፈለግ ያላቸውን እድል ለማስፋትና በተለይም ከአዲስ አበባ ውጭ ለመጡት በሳምንቱ መጨረሻ የመዝናናት እድል ለመክፈት ታስቦ እንደነበር ነው። አሰራሩም፣ አንዲት ተማሪን ለማውጣት የሚፈልግ ሰው ፎርሙን ይሞላና ለሞግዚትዋ ያቀርባል። ሞግዚትዋ የምትከለክልበት ጥሩ ምክንያት ከሌላት በስተቀር፣ ለምሳሌ ጠያቂው ሥራ ፈት ወይም ማንነቱ የማይታወቅ ካልሆነ በቀር፣ ተማሪዋ ከአመልካቹ ጋር እንድትሄድ

ይፈቀድላታል፡፡ ወጭዋ ልጅ ከሄደችበት ስትመለስ ለመመለስዋ በገቢ መዝገብ ይወራረስና የአውጭው ተጠያቂነት ከመዝገብ ይፋቃል፡፡

ፎርሙን እንዳለ በጋዜጣችን አወጣሁት፡፡ የስድስት ኪሎ ግቢ ጨሰ፣ ተጫጫሰ፡፡ ጋዜጣውን ያነበበ፣ ወሬውን የሰማ የስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ተማሪ አስተያየት ከምናለበት እስከ ዩኒቨርስቲው የርካሽ ባሕል ማስፋፊያ ማእከል ሆነ ከዚያም አልፎ የውጭ አገር ሰዎች እህቶቻችንን ደፈሩ፣ አስደፈሩ የሚል ነበር፡፡ የጋዜጣችን አማካሪ የነበረው፣ አሜሪካዊው ክራውሊ፣ ሞግዚትዋ በዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት ላይ እንደከሰሰችኝና፣ ከኮሌጅ እንድባረር እንደጠየቀች ነገረኝ፡፡ የክሱ መሠረት፣ ምስጢር በማውጣትና ሆስቴሉን መሳለቂያ በማድረግ የሚል ነበር፡፡ ይሄኔ ትንሽ ተረበሽኩ፣ ልቤም ፈራ፡፡ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት "ምንም ያጠፋሁት ነገር የለም፣ ለመብቴ እከራከራለሁ፣ ዩኒቨርስቲው ሐሳብ ያለፍርሃት መለዋወጫ መድረክ ነው እየተባለ እንዲህ ዓይነቱን ማስፈራርያ ቦታ ሊሰጠው አይገባም" አልኩት፡፡ "የኔም አቋም የተለየ አይደለም" ሲለኝ በጣም ደስ አለኝ፤ የልብ ልብ ተሰማኝ፡፡ አጋር እንደሚኖረኝም ተረዳሁ፡፡

ነገሩ የትም ሳይደርስ ያንድ ሰሞን ወሬ ሆኖ ከሰመ፡፡ ሆኖም፣ ሴቶቹን እየፈረሙ ማውጣት ወዲያው ስለተሰረዘ ጉዳዩ በቀጥታ ይመለከታቸው የነበሩት ወጭና አውጭ በልባቸው ቢረግሙኝ እንጂ የሚመርቁበት ምክንያት አይኖራቸውም፡፡ ያስጣልኩት ወይም እንጀራ የዘጋሁበት የውጭ ዜጋ ካለ ይቅርታ የምጠይቅበት ምክንያት አይኖረኝም፡፡ እንዲያውም እራሴን ከነጻ አውጭዎች ጎራ አሰልፋለሁ!

ሦስተኛ አመት ስንጨርስ በ1960 ለብሔራዊ አገልግሎት የተመደብኩት ሲዳሞ፣ ይርጋለም ከተማ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው ትምህርት ቤት በአስተማሪነት ነበር፡፡ ያስተማርኩት ታሪክና ቢዝነስ ነክ ሒሳብ ለሰባተኛ ክፍል ተማሪዎች ነበር፡፡ እድሜዬ ሃያ አንድ ብቻ ስለነበርና አንዳንዶቹ ተማሪዎች እድሜያቸው የኔን እንደሚስተካከል ወይም እንደሚበልጥ እሰማ ስለነበር ትልቁ ፍራቻዬ በዚህ እድሜዬ እንዴት የተማሪዎቼን አመኔታ

ማግኘት እችላለሁ? የሚል ነበር። ግዴታን በሚገባ ከተወጡ፣ ተማሪዎቹ እውቀት እንዲገበዩ ያልተቆጠበ ጥረት ከተደረገና እውነተኛ ፍቅር ካሳዩዋቸው የእድሜው ጉዳይ እንደሚረሳ ብዙም ሳይቆይ በውል ተረዳሁ። እንዲያውም፣ የልጅ አዋቂ ሆኖ መገኘት አስከባሪ እንደሆነም አወቅሁ።

ተማሪዎቼ ብዙ እንዲያውቁና እንዲመጥቁ ብሎም ከፍተኛ ደረጃ እንዲደርሱ ከፍተኛ ጉጉት ነበረኝ። ሆኖም፣ ይህ ስሜት ወህኒ ሊያወርደኝ ነበር። የሰባተኛ ዲ ተማሪዎች አጥኑ ያልኳቸውን በሚገባ ሳያጠኑ ይመጣሉ። እበሳጭና ጥያቄዬን መመለስ ያልቻሉትን እየዞርኩ እጃቸውን እመታለሁ። አንድ ተማሪ ከምቱ ለማምለጥ እጁን ዞር ሲያደርግ በድንገት አጥንቱ ላይ አገኘሁትና እጁ አበጠ። ሄዶ ለወላጆቹ ነገረ። በሚቀጥለው ቀን ይመስለኛል፣ እዚያው ክፍል ሳስተምር በሩ ይንኳኳል። ብወጣ ፖሊስ ነው፣ ምን ትፈልጋለህ? ስለው፣ አንተን ይለኛል። ከሳሾቼ ከጀርባው ተኮልኩለው ስላየሁዋቸው ለምን? አላልኩትም። አንተም ሆንክ እኔ የተማሪዎቹን ጊዜ የማባከን መብት ስለሌለን እስክጨርስ ጠብቀኝ አልኩት። እሺ አለ። ክፍለ ጊዜው አልቆ ወጥቼ ባይ ፖሊሱም ሆነ ከሳሾቼ የሉም። ዲሬክተሩ ቢሮ ይሆናሉ ብዬ ብሄድ እዚያም የሉም። መፍራቴ አልቀረም ነበርና ነገሩን ትተው መሄዳቸው ደስ አለኝ። እንደዚያ ተሰባስበው የመጡት ሰዎች በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ምን ተፈጥሮ ጥለው እንደሄዱ እስከዛሬም አላውቅም።

ተማሪዎቼ ከሳሼን፣ እንዴት ጋሼ ታደሰን ትከሳለህ? እኛንም ሆነ አንተን የመታን ሊጎዳን ፈልጎ ሳይሆን ጥሩ ተማሪዎች እንድንሆን ካለው ጉጉት የተነሳ ነው፣ ብለው እንደተቆጡት ወዲያው ሰማሁ። ተማሪዎቼ እንዲያውቁ፣ እንዲተጉ ያለኝ ፍላጎትና ጉጉት ባይቀንስም ከዚያን ቀን በኋላ የተማታሁ አይመስለኝም። የሰባተኛ ዲ ተማሪዎች ከሳሼን ለአፋቸው ቢቆጡትም በልባቸው ግን ለከፈለው መሥዋዕትነት ምስጋና ሳያቀርቡለት አልቀሩም ብዬ እገምታለሁ።

ሲውል ሲያድር የተመለከትኩት ነዋሪነታቸው ከተማው ውስጥ የሆነ ተማሪዎች ራቅ ብለው ከገጠር ከሚመጡት በትምህርት ይዞታቸውና በንቃታቸው በአመዛኙ ይሻሉ እንደነበር ነው:: ከሩቅ የሚመጡት በቂ ምሳ ስለማያገኙ ይርባቸዋል:: ጠዋት የተመገቡትም ቢሆን በመንገድ ተቃጥሎ ያልቃል:: ስለሆነም፣ ብዙውን ጊዜ ረኀብ እንደጠናባቸው ይውላሉ:: ሆዳቸው ባዶ ሲሆን ትምህርት የመቅሰምም ሆነ የቀሰሙትን የመያዝ ችሎታቸው እንደሚዳከም ተረዳሁ:: በችግራቸው ላይ ዱላ ሲታከልበት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ስለመሆኑ ብዙም አያጠያይቅም:: ከሳሼ ጓደኞቹን ከሚያሳምም ዱላ፣ እኔን ደግሞ ከኀሊና ወቀሳ አድኖኛልና እኔም ላመሰግነው ይገባል::

ይርጋለምን የማስታውስበት ሌሎችም ምክንያቶች አሉኝ:: በዋዛ ፈዛዛ በልጅነት የጀመርኩትን ሲጋራ የማጨስ አመል ልላቀቀው ብዙ ጊዜ ሞክሬ ሳይሳካልኝ ቀርቶ ነበር:: የብሔራዊ አገልግሎት፣ አሜሪካን ፒስኮርና ህንድ አስተማሪዎች ህዳር 1960 አንድ ቡና ቤት ውስጥ በሳምንቱ መጨረሻ ተሰባስበን ቢራ ስንጠጣ አብዛኞዎቻችን ሲጋራ እንደምናጨስ ተገነዘብንና ሰለ ሲጋራ መጥፎነት ማውራት ጀመርን:: በመጨረሻም ማቆም እንደሚሻል ተስማማን:: ከመቼ ጀምሮ? ቢባል፣ መልሱ ከነገ ጠዋት ነበር:: የመጀመሪያው ቃሉን ሰባሪ በማግስቱ ከአልጋ ከመነሳቱ አጨሰ:: እስከማውቀው ድረስ እስከመጨረሻው በቃሌ ጸንቼ የተገኘሁት እኔ ብቻ ነኝ:: ዓመቱ አልቆ አዲስ አበባ ስንመለስ ለጓደኛዬ ለአስፋው አገኘሁ ማቆሜን ብነግረው አላምን አለኝ:: ይባስ ብሎ ይሄኔ ሽንት ቤት ተደብቀህ ታጨስ ይሆናል አለኝ:: በእርግጥም አለማጨሴን ሲረዳ እኔም አላጨስም ብሎ ወሰነና አቆመ::

የራስ ደስታ ትምህርት ቤት ስካውቶችን ለማደራጀትና ለማጠናከር ኃላፊነቱን ወስጄ ነበር:: ከምናደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አንዱ ሽርሽር መሄድ ወይም የእግር ጉዞ ማድረግ ነበር:: አንድ ቀን ከጉዞ ተመልሰን ገና ቤት ከመድረሴ ታምሜ እወድቃለሁ:: ባስቸኳይ አቦስቶ ሆስፒታል ወስደው

ያስተኙኛል። የሚያየኝ ሐኪም ከእስካንድኔቪያ ለልምምድ የመጣ ተማሪ ሐኪም ወይም ኢንተርን ነበር። ውጋት ቅስፍ አድርጎ ይዞኛል፤ ትኩሳቱ ሰማይ ደርሷል፤ ያንቀጠቅጠኛል። ሕመሜ ምን እንደሆነ ግን አላወቁልኝም። ሐኪሙ ወባ ይመስለኛል ሲል አንድ ቀን ሰማሁ። የወባ መድኃኒት በገፍ ስውጥ ሰነበትኩ። ነገር ግን አሁንም ሳይሻለኝ ይቀራል። በፍጻሜው ሰዓት ነፍሴ ከሥጋዬ ስትሰናበት ተማሪዎቼ አልጋዬ ዙርያ ተሰብስበው ሲላቀሱ አየሁዋቸው። ከዚያም እንቅልፍ አሸለበኝ። ቀጥሎም የነበረውን ልዩ የደስታ ወይም የእርካታ ስሜት መግለጽ አልችልም። ባሸበረቀ መንገድ በደስታ ተውጬ ስነጉድ ዐየሁ። ብዙም ሳይቆይ ዐይኔ ተገለጠ። ተማሪዎቼ አሁንም ሲያለቅሱ ዐየሁ። ያ ልዩ የደስታ ስሜት ወድያው በሕመም ተለወጠና የደስታው ጉዞ ተቋርጦ ወደ ስቃዩ ዓለም በመመለሴ ከፋኝ። በዚህ ዓይነት ከሞት አፋፍ በተአምር ካመለጥኩ በኋላ ሕመሜ የሳንባ ምች ወይም ኒሞንያ መሆኑ ታወቀ። ተለማማጁ ዶክተርም ከህሊና ጸጸት ዳነ።

የይርጋለም አቧራ ለዐይኔ ጠር ሆኖ ሕመሙ ካቅሜ በላይ ስለሆነብኝ ዓመቱ ሊያልቅ አንድ ወር ያህል ሲቀረው፣ ወደ አዲስ አበባ ተመልሼ የዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታሉ ዶክተር ፓውሎስ ቀነአ ኦፕራስዮን አደረገኝና ፋታ አገኘሁ።

ለተማሪዎቼ የነበረኝ ፍቅር በጣም ከፍተኛ ነበር። ይርጋለም ልዩ ትዝታ የጣለብኝ ቦታ ነው። ከተማሪዎቼ መካከል ጓደኞቼ፣ ጠያቂዎቼ ሆነው የቀሩ ብዙ ናቸው።

ከትምህርት ገበታ የመባረር እጣ የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ሆኜም እንደገና ገጠመኝ። ዘመኑ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የተማሪ ተቃውሞ የደራበት ነበር። የኛ ዋና አጀንዳ መሬት ላራሹና ፊውዳሊዝም ይውደም ነበር። የትምህርት ማቆም አድማ ተጧጡፏል። ተማሪ ክፍል ወጣ ገባ ይላል።

መጨረሻ አመት ላይ የነበርነው የቢዝነስ ኮሌጅ ተማሪዎች ምን ማድረግ እንዳለብን ለመወሰን ስብሰባ አደረግን:: ለመጨረስ የቀረን ጊዜ በጣም አጭር ስለሆነ ትምህርታችንን ጨርሰን ከዩኒቨርስቲው ብንሰናበት ይሻላል የሚለው ሐሳብ በድምጽ ብልጫ አለፈና ቀሪውን የትምህርት ዓመት ተያያዝነው:: በሐሳቡ ያልተስማሙት ትምህርታቸውን አቋርጠው ግቢውን ለቀው ወጡ::

በዚያው ሰሞን ዩኒቨርስቲው አንድ ደንብ ያወጣል:: ከተወሰኑ ቀናት በላይ ከትምህርት ገበታው የተለየ ተማሪ ከዩኒቨርስቲው ይታገዳል ተባለ:: እታመምና ከተደነገገው የጊዜ ገደብ በላይ ቤት እውላለሁ:: ሲሻለኝ ትምህርት ቤት ብሄድ ደንቡ ተጠቅሶ ወጥተሃል ተባልኩኝ:: ደንቡ እኮ የወጣው የታመመ ተማሪን ለማባረር አይደለም ብል ማን ይስማኝ?

የኮሌጃችን ዲን ጀምስ ሊ ዘንድ ብሄድ ደንቡን እኔ አላወጣሁት፤ ምንም ማድረግ አልችልም ካለኝ በኋላ፣ በጠረጴዛው መሀል ወደ ተቀመጠ አንድ ትልቅ ድንጋይ በጣቱ እያመለከተ፣ ይሄ ምን እንደሆነ ታውቃለህ? ይለኛል:: አላውቅም እለዋለሁ:: ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲን የሚያህል ታላቅ የትምህርት ማእከል ትቼ የመጣሁት ኢትዮጵያውያንን ለመርዳት ነበር:: የተረፈኝ አንድ ዐይኔን ማጣት ነው፤ ይህን ያደረሱብኝ ያገርህ ሰዎች ናቸው፤ ከአሁን በኋላ ለአንተም ሆነ ለሌላ ኢትዮጵያዊ የምራራበት አንጀት አይኖረኝም አለኝ:: ሕጉን ያወጣው እሱ አለመሆኑን ለሁለተኛ ጊዜ አስታወሰኝና በዩኒቨርስቲው ደንብ መሠረት ወደ ትምህርት ገበታ መመለስ እንደማልችል ነገረኝ:: ቢሮውንና ኮሌጁን ለቅቄ ወጣሁ::

ጀምስ ሊ የጀብደኝነት ጠባይ የሚጸናወተውና ሁሉን ነገር አውቃለሁ የሚል ሰው ነበር:: አስተማሪያችን በነበረበት ወቅት ክፍል ውስጥ ከሱ ጋር መከራከር እወድ ነበር:: እንደሚመስለኝ በአንድ በኩል በጥሩ ተማሪነቴ ሲያደንቀኝ በሌላ በኩል ስለምከራከረው አይወደኝም ነበር::

ፕሮፌሰር ሊ ዐይኑን ያጣው የተማሪ ሰላማዊ ሰልፍ ለማየት መርካቶ ሃብተጊዮርጊስ ድልድይ አካባቢ ድረስ ይሄድና ከመኪናው ወጥቶ ፎቶግራፍ ሲያነሳ ያየው ተማሪ ድንጋይ ወርውሮ መትቶት ነው፡፡ ባስቸኳይ ለሕክምና ውጭ አገር ሄዶ ቢታከምም የዐይኑን ብርሃን ሊያተርፉለት አልቻሉም፡፡ ሕክምናው እንዳለቀ ወድያው ተመልሶ መጣ፡፡ የኮሌጃችን ዲን ሆኖ የተሾመው ዐይኑን ከመመታቱ በፊት ይሁን ወይስ ከዚያ በኋላ አላስታውስም፡፡

ደንቡ ተጠቅሶብን ከልዩ ልዩ ፋከልቲዎች ከትምህርት ገበታችን የተባረርነው ዐሥራ አምስት ያህል ተማሪዎች ነበርን፡፡ በኔ አስተባባሪነት ወደ ዩኒቨርስቲው ፕሬዚዳንት አክሊሉ ሃብቴ ቢሮ ሄደን አቤት አልን፡፡ እሱም ሕግ ሕግ ነው፤ምንም ማድረግ አልችልም ይለናል፡፡ የለም፣ የሕጉ መንፈስ በትክክል ቢተረጎም የሚያስወጣ ጥፋት የለብንም ብለን ተከራከርን፡፡ ሊሰማን ሳይፈልግ ቀረ፡፡ ፕሬዚዳንቱ አይሆንም ያለውን አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ዶክተር መኮንን ክብረት ያቃናዋል ብለን ባናምንም የነበረን የመጨረሻ አማራጭ ወደ እሱ ዘንድ ሄደን እድላችን መሞከር ስለነበር ተሰባስበን ሄድን፡፡ ዶክተር መኮንን በጥሞና ካዳመጠን በኋላ ጉዳዩ ብያኔ እስኪያገኝ ድረስ ወደየክፍላችሁ ተመልሳችሁ ተጠባበቁ፡ ውጡ ከተባላችሁ ትወጣላችሁ ብሎ አሰናበተን፡፡ ደስ ብሎን ወደየክፍላችን ተመለስን፡፡ ውጡ የሚለን ሳይመጣ ቀረ፡፡ አራተኛ ዓመት የነበርነውም ትምህርታችንን መጨረስ ቻልን፡፡

የምረቃ ስነሥርዓት ለማዘጋጀት ለጃንሆይ የሚያመች ቀን ሲጠበቅ ብዙ ቀኖች አለፉ፡፡ ጥቂት የክፍል ጓደኞቻችን የምረቃ በዓል እስኪደርስ ለክፍል ጓደኞችን ለተከተል ሀብተጊዮርጊስ ሰርግ ሆሳእና ከተማ ደርሰን እንምጣ ብለው ይሄዳሉ፡፡ ገና ከመሄዳቸው ለምረቃው እንድንዘጋጅ ይነገረናል፡፡ ከአዲስ አበባ ሆሳእና የነበረው የአውሮፕላን በረራ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ስለነበር የሄዱት ጓደኞቻችን በስነሥርዓቱ ላይ ሳይገኙ ቀሩ፡፡ ከመካከላቸው አየለ አበጋዝ በሕይወቱ በጣም ከሚመኛቸው ነገሮች አንዱ ከጃንሆይ እጅ

ዲግሪውን መቀበል ነበርና በወሳኙ ወይም በቀውጢው ወቅት ከአጠገባችን ተለይቶ መሄዱ ዘወትር የሚያስገርመን ነገር ነበር። የምረቃው ስነሥርዓት በሐምሌ 1961 ተከናወነ።

የዩኒቨርስቲ ትምህርት አሰጣጡ አስተማሪ የሚለውን ብቻ ሰምቶ መለያየት ሳይሆን የሐሳብ ለሐሳብ ልውውጥ፣ አስተያየት መስጠትና ሲያስፈልግም መከራከር ስለሚያካትት ከመጀመርያ እስከ መጨረሻ እንደወደድኩት አለቀ። ለዚህም ሊሆን ይችላል በከፍተኛ ማእረግ ለመመረቅ የበቃሁት። ከጃንሆይ እጅም የወርቅ መዳልያ ተሸለምኩ።

እአአ በሴፕቴምበር 1964 አንደኛ አመት አብረን ከጀመርነው መካከል የሚከተሉትን አስታውሳለሁ፣ ሁለት አጥናፋዎች፣ አብርሃም ተስፋዬ፣ አየለ ደምሴ፣ አየለ አበጋዝ፣ አበበ ከበደ፣ አበራ ፈለቀ፣ አበራ ወልደሚካኤል፣ አሰፋ ወልደኪዳን፣ አስፋው አገኝሁ፣ አብደላ ከማል፣ አየነው ቢተውልኝ፣ አባይ አብርሃ፣ አፎሚያ፣ አስመላሽ፣ አወቀ፣ አስቴር ወዬሳ፣ በሻህ አዝምቴ፣ ብሩክ፣ ብርሃኔ ኃይሌ፣ ደምመላሽ አለሙ፣ ደሳለኝ በንቲ፣ ደምሴ ተፈራ፣ ፋንታሁን ሳልልህ፣ ፍቅሬ ንጉሴ፣ ፍሬወይኒ፣ ፍስሃዬ፣ ጌታቸው አየሁ፣ ሃይሌ ቶላ፣ ከበደ አድነው፣ ኪሮስ ወልደስላሴ፣ ካሳሁን ባርዴ፣ ካሳሁን መስቀሌ፣ መኮንን ተሰማ፣ መሃሪ፣ ማርዬ ተፈሪ፣ ማሞ ወልደጊዮርጊስ፣ ማርቆስ ላቀ፣ ሙሉጌታ ፈረደ፣ ሙሉብርሃን፣ ነገደ ብስራት፣ ነግዳር ፓሩኪያን፣ ነጋሳ ቱምሳ፣ ርእሶም ሃይሌ፣ ፓትሪሽያ ሺሎንግ፣ ሰለሞን ሉሉ፣ ሳሙኤል በቀለ፣ ሳራ ጆሴፍ፣ ስዩም ረታ፣ ስንሻው፣ ተከስተብርሃን ገብረሚካኤል፣ ተስፋዬ ያዕቆብ፣ ተከተል ሃብተጊዮርጊስ፣ ተኮላ ገብረኪዳን፣ ተክሉ ሃይሌ፣ ታደሰ ወልደሚካኤል፣ ታዬ ተፈሪ፣ ታዬ በቀለ፣ ቶቶ መልካ፣ ጥግነህ መርሻ፣ ፀሃዬ ወልደሚካኤል፣ ወልደጊዮርጊስ አቢይ፣ ወርቁ ጌታሁን፣ ወልደስላሴ፣ የማነ እማኙ፣ የኑስ ጌታሁን፣ ዮሃንስ ገብረስላሴ፣ ዮሐንስ ፓውሎስ፣ ይልማ ከበደ፣ ቫህራም፣ ዘውዲቱ ላቀው።

አንድ ላይ የተመረቅነው ቁጥራችን አብረን ከጀመርነው ጋር ሲነጻጸር ከእሩብ የማይበልጥ ሲሆን ከትምህርት ቤት እንደወጣንም የመሠረትነው ማኅበራዊ ግንኙነት አሁንም አቅፎ ደግፎ እንደያዘን ወይም እንደ ሙጫ ሆኖ እንዳጣበቀን ነው፡፡ ማኅበራችን ክፉ ጊዜ ሲመጣ አብረን እንድንቆም፣ በደጉ ጊዜ ደግሞ ደስታችንን እንድንጋራ አስችሎናል፡፡ በመሆኑም፣ ቤተሰባችን ወደ አገሩ ሲመለስ ብዙ የተዘረጉ እጆች እንደሚጠብቁት ስለማውቅ ደስ ይለኛል፡፡

# ድህረ ምረቃ

ከመስከረም 1964 እስከ ታህሳስ 1965 በኮለምቢያ ዩኒቨርስቲ፣ ኒው ዮርክ፣ የባንኪንግና ፋይናንስ ትምህርት ተከታትዬ የማስተር ኦፍ ቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ዲግሪ አግኝቻለሁ፡፡

ለአፍግራድ ስኮላርሺፕ ውድድር ስቀርብ የአዲስ አበባ ባንክ ሠራተኛ ነበርኩ፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር አዳራሽ ውስጥ የተሰበሰበው መራጩ ኮሚቴ ያልጠበቅሁት ጥያቄ አቀረበልኝ፡፡ የኮሚቴው ሊቀመንበር፣ መንግሥትን ወክሎ፣ ዶክተር ኃይሌ ወልደሚካኤል ሲሆን በርከት ያሉ የአሜሪካ መንግሥት ተወካዮችም ነበሩ፡፡ "ስኮላርሺፑ ፋይናንስ የሚደረገው የአሜሪካን መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት በሚሰጠው እርዳታ ነው፤ የስኮላርሺፕ እድል የመጣው ለመንግሥት ሠራተኞች ነው፤ ከዚህ ቀደም ለግል ሠራተኛ የመንግሥት ስኮላርሺፕ ተሰጥቶ አያውቅም፤ አንተ ግን የግል ድርጅት ሠራተኛ ነህ፤ ስለዚህ የመወዳደር መብት የለህም፤ በቂ መልስ ከሌለህ በቀር የአንተ ማመልከቻ በዚሁ ያልቅለታል" ተባልኩ፡፡ ከፍተኛ ትምህርት ተምሮ ዲግሪ ማግኘት ከቢዝነስ ኮሌጅ ከመመረቄ ቀደም ብሎ ያሰብኩበትና ከልብ የምመኘው ነገር ስለነበር ይህ ያልጠበቅሁት ጥያቄ እውነተኛ ፈተና ውስጥ እንደጣለኝ ተረዳሁ፡፡

ከባድ ፈተና ውስጥ ስገባ አእምሮዬን በሙሉ ኃይሉ እየተንቀሳቀሰ ከጉድ ያወጣኝ ጥቂት ጊዜ አልነበረምና ዛሬም ነገሩን ላንተ ትቼዋለሁ ብዬ አእምሮን ተማጸንኩ። ለኮሚቴው የሰጠሁት መልስ እንደሚከተለው ነበር። እርግጥ የምሠራው ለግል ባንክ ነው። ቢሆንም፣ ባንኩ የሚያስተዳድረው የግል ሳይሆን የሕዝብ ገንዘብ ነው። ከሥራው ጠባይ የተነሳ በግል ባንክና በመንግስት ባንክ መካከል ልዩነት የለም። አንድ ባንክ በተቀማጭ መልክ ከሕዝብ በአደራ የሰበሰበውን ገንዘብ በሚገባ መያዝና ብድር ለሚያስፈልገውና መመዘኛ ለሚያሟላ ተበዳሪ በጥንቃቄ አከፋፍሎ ሳይባክን መሰብሰብ ይጠበቅበታል። ይህ አሠራር ከሰመረ ሕዝብ በባንክ ላይ የሚኖረው አመኔታ ይጨምራል፣ ብሎም የኤኮኖሚ ልማትና ማህበራዊ እድገቶችን ማፋጠን ይችላል። ታደሰ ስለባንክ አሠራር ያለውን ችሎታ ለማዳበር የስኮላርሺፕ እድል ቢሰጠው የግል ባንክ ሠራተኛ በመሆኑ ብቻ ማንም ሊቀናቀነው ወይም ኮሚቴውን ወቃሽ ሊነሳበት አይገባም ብዬ መለስኩ። ኮሚቴው በመልሴ ስለረካ ይመስለኛል ሌላ ጥያቄ ሳልጠየቅ ተሰናበትኩ።

የነጻው ትምህርት እድል ተሰጠኝ፤ በጣምም ደስ አለኝ። ኮለምብያ ዩኒቨርስቲ ወዳለበት ወደ ኒውዮርክ ከተማ ሳመራ እግረመንገዴን አስመራ፣ ሮምና ፓሪስ እያንዳንዳቸው ውስጥ ሶስት ቀን ቆይቻለሁ። አስመራን ከዚያን በፊት አላውቀውም ነበር። ከአንዳንድ የአዲስ አበባ ባንክ ቅርንጫፍ ሠራተኞች በስተቀር አማርኛ የሚናገር ሰው ያጋጠመኝ እጅግ ጥቂት ስለነበር እውነቱን ለመናገር ከአገሬ እንደወጣሁ የተሰማኝ አስመራ ሆኜ ነበር። ሆቴል ክፍሌ ሆኜ እንባ ሳያመልጠኝም አልቀረም።

ሮም እንደገባሁ ምግብ የት ማግኘት እንደምችል እተከራየሁት ማረፊያ ቤት ሥር የነበር አንድ የጋዜጣ ቸርቻሪ ብጠይቀው መግባባት ሳንችል እንቀራለን። ስንደናቆር አንዲት ጠና ያለች ሴት ቆማ ታይ ኖሮ ክንዴን ጎተት አድርጋ ወደ ጎን ወስዳ በጣትዋ እያመለከተች፣ ዜር ፒዛ፣ ፒዛ ጉድ፣ ፒዛ ቺፕ ብላኝ መንገድዋን ቀጠለች። እናት ያገኘሁ መሰለኝና በጣም ደስ

አለኝ:: አስመራ ሆኜ የተሰማኝ የባእድነት ስሜት በፈረንጂ አገር፣ ያውም በታሪካዊው ጠላታችን ጣልያን፣ ለዘበልኝ:: በዚህ ያልታሰበ ክስተት መገረሜ አልቀረም::

የፓሪስ ከተማን በእግሬ ሳዳርስ መንገድ እየሳትሁ አቅጣጫ ስጠይቅ ሰው በተቻለ መጠን ይረዳኝ ነበርና በውጭ አገር ቆይታዬ ችግር አይገጥመኝም ብዬ ተማመንኩ:: ሰውን በሰውነቱ እንጂ በቆዳው ቀለም መፍረድ የለብኝም አልኩ::

በሮምና ፓሪስ ቆይታዬ የዘረኝነት ችግር ስላላጋጠመኝ ሰውን በሰውነቱ እንጂ የቆዳን ቀለም አይቶ ስለማንነቱ ለመናገር መሞከር ስሕተት ነው ያልኩት ሰውዬ አሜሪካ ስገባ ግን የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤታቸው ከጠየቀኝ ጥያቄዎች አንዱ የቆዳህን ቀለም ግለጽ የሚል ነበር:: የቆዳ ቀለም ቦታ የለውም የምትለውን ፈሊጥ ብትረሳው ይሻላል የሚል ማሳሰቢያ ነበር:: በእርግጥም በሰሜን አሜሪካ ነጮች የበላይ፣ ጥቁሮች የበታች የሆኑበት አገር መሆኑን አየሁ:: ጥቁር በየምክንያቱ በወህኒ ይታጎርና ይገደል እንደነበር ተመለከትኩና አሜሪካን የክርስትና ካባ ያጠለቁ አረመኔዎች የሚገዟት አገር ናት አልኩ:: ኒውዮርክን ለቅቄ በወጣሁ በሃያ ስድስተኛው አመት አንድ መሣሪያ አልባ የነበረን የጊኒ ተወላጅ ነጭ ፖሊሶች በአርባ አንድ ጥይት ደብድበው ገደሉት መባሉን ስሰማ ብዙም አልተገረምኩም:: አፍሪቃውያን በሆነ ባልሆነው እየተጣላን ወይም አገሮቻችንን ወደ ሥልጣኔ ጎዳና ማምራት እያቃተን ወደ ሰሜን አሜሪካ እየተሰደድን ችግር ቢደርስብን ጥፋቱ የኛም ጭምር መሆኑን አምናለሁ::

እውነትን ስለማፍረጥረጥ የመጀመርያው ፈተና በአሜሪካ የገጠመኝ ገና መኖሪያዬ ሳልደርስ በመንገድ ነበር:: ታክሲ ከኒውዮርክ አውሮፕላን ማረፊያ ወደ መኖሪያዬ የወሰደኝ በቀጥታ ሳይሆን የጫናቸውን ሌሎች ተሳፋሪዎች እየዞረ ካራገፈ በኋላ ስለነበር እግረመንገዴን ከተማዋን በከፊል የማየት ዕድል አጋጠመኝ:: ሁለታችን ስንቀር ስለኒውዮርክ ምን አስተያየት አለህ? ይለኛል:: ብዙ ሕንጻዎች ከጀርባቸው ወይም ከኋላቸው ከእሳት

አደጋ ማምለጫ መሰላል ተሸክመው አይቻለሁ፤ ብዙ ያየሁዋቸው ሕንጻዎች ጠቋቁሮችና አሮጌ መሳዮች ነበሩ:: ለሰውዬው በሰጠሁት መልስ፤ አሁን የምመጣው ከፓሪስ ነው፤ ፓሪስ ውስጥ ቆንጆና ንጹሕ ሕንጻዎች በብዛት አይቻለሁ፤ እዚህ ካየሁት እዚያ ያየሁት ይሻላል እለዋለሁ:: ሰውዬው ክልስ ነው:: መልሴን እንደሰማ አቅጣጫውን ቀየረና ወደ መሀል ከተማ ይዞኝ ነጎደ:: ደህና ደህና ሕንጻዎች ያሉበት ስፍራ አዙሮ አሳየኝ:: አሁን ያየሁዋቸው ሕንጻዎች የተዋቡ፤ መሰላል በጀርባቸው ያላዘሉ፣ በጭስ ያልተበከሉ ነበሩ:: ማሳየቱን እንዳበቃ አቅጣጫውን ወደ መኖሪያዬ ተያያዝነው:: ጥቂት እንደሄድን፣ አሁንስ ስለከተማው አስተያየትህ እንዴት ነው? ብሎ ይጠይቀኛል:: አሁን ያሳየኸኝ አካባቢ በጣም ቆንጆና አስደናቂ ነው አልኩት:: ይሄኔ ፊቱ ፈካ አለና ፈገግ ብሎ፣ “ናው ዩ ሃብ ካም ቱ ዘ ፖይንት” (Now you have come to the point) አለኝ፣ ትርጉሙ አሁን የሚፈለገውን ነጥብ መታህ ማለት ነው:: ውሎ አድሮ የተረዳሁት የኒውዮርክ ሰዎች በዓለም የነሱን ከተማ የሚስተካከል የለም ብለው እንደሚያምኑ ነው::

ኒውዮርክ መኖሪያዬ ሃርለም አጠገብ ኢንተርናሽናል ሃውስ ውስጥ ነበር:: ከተማው በገባሁ በሁለተኛ ቀን ጋዜጣ ልገዛ መኖርያዬ አጠገብ ወደነበረው ኪዮስክ ብገባ የጋዜጣው ዓይነት ብዙ ስለነበር አንብቤ ተብዬ የተነገረኝን አመስተርዳም ኒውስን በቀላሉ ላገኘው አልቻልኩም:: ተቀምጣ ጋዜጣ የምታነብ አንዲት ጥቁር ሴት፣ በኔ ቤት እህቴን፣ አየሁና ደስ አለኝ:: በቃ፣ እስዋን ብጠይቃት ደስ ብሏት ትነግረኛለች፣ እኔን ለመርዳት እድል በማግኘትዋ እርግጠኛ ነኝ ደስ ይላታልና ለምን እድሉን ልንፈጋት? ብዬ አሰብኩና ሄጄ ጠየቅኋት:: መጀመሪያ ነገር አነጋገሬ ወይም አክሰንቴ እንግዳ ስለሆነባት ጥያቄዬ የገባት አይመስለኝም:: ቀና ብላ ካየችኝ በኋላ፣ የንባብ መነጽርዋን ቦርሳ ውስጥ አደረገችው፤ ጋዜጣውን በስነሥርዓት አጣጠፈችና፤ ተነስታ ቆመችና ቀሚስዋን አስተካከለች:: ከዚያም፣ ወደኔ ፍጥጥ ብላ እያየች፣ “ኋይ ዶንት ዩ ዱ ዩር ኦውን ቲንግ?” (Why don't you do your own thing?) አለችኝና አረፈችው:: ባጭሩ፣ ለምን ታስቸግረኛለህ? ማለት

ነው። ብራቅ የመታኝ እንጂ ሰው የተናገረኝ አልመሰለኝም። በልቤ፣ የሮማዋ ፈረንጅ እንኳ ሳልጠይቃት እንዲያ ረድታኝ እህቴ አረመኔ ትሁንብኝ? አልኩና በጣም አዘንኩ። ጋዜጣና የኒውዮርክ ሰዎች ድራሻችሁን ያጥፋው ብዬ ክፍሌ ገብቼ ተከረቸምኩ። ቢያንስ አንድ ሙሉ ቀንና ሌሊት አልጋዬ ውስጥ ተሸፋፍኜ ንዴቴን ልወጣው ሞከረኩ። ሌሊት ሙሉ የእሳት አደጋ መኪናና አምቡላንስ ጩኸቱን ሲያቀልጠው ያድራል። ከምድር በታች የሚሄደው ባቡር እንደ አይጥ ከጉድጓዱ የሚወጣው መኖሪያዬ ትይዩ ስለሆነ ብረት ከብረት ጋር ሲጋጭ የሚፈጠረው ከፍተኛ ድምፅ አያምጣው ነው። ጩኸቱ ከሴትዮዋ ድምጽ ጋር ተዳምሮ በጆሮዬ ውስጥ እያቃጨለብኝ ለብዙ ቀናት በጣም ተቸገርኩ። አምላኬ ምኑ አገር ነው ያመጣኸኝ? ብዬ አማረርኩት።

ጥቂት ኢትዮጵያውያን፣ እነእንግዳ ደስታ፣ ግርማ ኃይለ ልዑል፣ አለማየሁ ሰይፉ፣ እኔ የምኖርበት ሕንጻ ውስጥ ይኖሩ ነበርና ተዋውቅን ልምዳችንን ስንለዋወጥና አይዞህ ስንባባል ቀስ በቀስ እየተሻለኝ መጣ። በተለይም፣ የሁላችንም እንግዳ ተቀባይ፣ አስተናጋጅና ችግር ደራሽ ወልደየሱስ ገብረማርያምን ካገኘሁት በኋላ ተረጋጋሁ።

ብዙ ወራት ከቆየሁ በኋላ በውል የተረዳሁት የኒውዮርክ ሰው እራሱን በራሱ ለራሱ ሲያሽከረክር፣ ሲያጦዝ ስለሚውል ለሌላ ሰው ጊዜ ወይም ግድ እንደሌለው ነው። ሰው ሥራው መክነፍ፣ ጊዜን ተከትሎ ጨርቁን ጥሎ መሮጥ ነው። ጋዜጣ ሻጩ ሱቅ ያገኘኋት ጥቁር ሴት ከሌላው ኒውዮርከር የተለየች እንዳልሆነች ቀስ በቀስ ገባኝ። ሴትዮዋ ያለችኝ በመሠረቱ ጊዜዬን አታባክን ወይም አትስረቅ ነው። ሰው ከመቸኮሉ የተነሳ አንዱ በከፈተው በር ሌላው ዘው ብሎ ይገባል፣ ቱር ብሎ ይወጣል። በዚህ በጣም እናደድ ነበር፤ እንዴት እኔ በከፈትኩት በር ቀድሞኝ ይገባል ይወጣል? እያልኩ እንጨረጨር ነበር። እንደኔ ዓይነቱ ቆሞ ይውላል እንጂ ማንም ፋይዳ ስለማይለው ትርፉ ጊዜ ማጥፋት ብቻ ነው። እውነቱን ለመናገር፣ ሲውል ሲያድር እኔም እንደሌላው ሆንኩ። ለአንድ የኒው ዮርክ

ነዋሪ ቀስ ማለትና ቀሰስተኛ መሆን አንድ ናቸው፡፡ የኒውዮርክ ሰዎች በቂ እንቅልፍ አይተኙም፤ ብዙ እንቅልፍ መተኛት ነውር ይመስላቸዋል፡፡ ኒው ዮርክ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ ወይም የኖረ ሰው በአገራችን ቋንቋ ንክ ይመስላል፡፡ በግልባጩ ደግሞ ረጋ ካለ አካባቢ የመጣ ሰው ለኒው ዮርክ ነዋሪ በቁሙ የሚሄድ በድን ወይም ዞምቢ ይመስላል፡፡

ትምህርቴን ልጨርስ አካባቢ የሲቲ ባንክ ሊቀመንበር ንግግር ሊያደርግልን ትምህርት ቤታችን ይመጣል፡፡ በወቅቱ የአዲስ አበባ ባንክ 40 በመቶ ባለቤትነቱ ለንደን የሚገኘው ናሽናል ኤንድ ግሪንድሌይስ ባንክ ሲሆን ሲቲ ባንክ በፈንታው 40 ከመቶ የግሪንድሌይስ ባንክ ባለቤት ነበር፡፡ በዚህ መሠረት አዲስ አበባ ባንክ 16 በመቶ ባለቤትነቱ የሲቲ ባንክ ነበር ማለት ነው፡፡ ትምህርቴን ስጨርስ የሥራ ልምምድ እንዳደርግ ሲቲ ባንክ እንዲቀጥረኝ ለሊቀመንበሩ ጻፍኩ፡፡ ባንኩ በመሠረቱ ሊቀጥረኝ ቢወስንም በእርግጥ የአዲስ አበባ ባንክ ሠራተኛ መሆኔን ለማረጋገጥ ፈልጎ ለአዲስ አበባ ባንክ ጻፈ፡፡ አዲስ አበባ ባንክ ሲመልስ ሠራተኛችን አይደለም አለና ቁጭ አለ፡፡ እኔንም አታላይ አስደረገኝ፡፡ የባንኩ ድርጊት በፍጹም አልገባህ አለኝ፡፡ ባንክ ነክ ኮርሶችን ስወስድ የከረምኩት አዲስ አበባ ባንክ መመለሴ ጥያቄ ውስጥ ገብቶ ስለማያውቅ ነበር፡፡ በእርግጥ ከባንኩ ስሰናበት ስሜ ከፔይሮል ተሰርዟል፡፡ ይህ የተደረገው በትምህርት ላይ ሳለሁ የደመወዝ ጥያቄ እንዳላነሳ በባንኩ በኩል ታስቦ ስለነበር ነው፡፡ በስኮላርሺፕ ኮሚቴውም ሆነ በአዲስ አበባ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ በአቶ ደበበ ሀብተዮሐንስ አስተሳሰብ ትምህርቴን ጨርሼ ስመለስ ባንኩ መልሶ እንደሚቀጥረኝ ነበር፡፡ ይህ መሆኑ እየታወቀ ለምን እድሉ እንደተዘጋብኝ አልገባህ አለኝ፡፡ ተንኮል እንዳለበትም ጠረጠርኩ፡፡ እድሉ ተጨናግፎ አዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላ የተነገረኝ ደብዳቤው የተጻፈው አቶ ደበበ ሳያውቁ በአስተዳደር ሥራ አስኪያጁ በመሐመድ ሸሪፍ እንደነበር ነው፡፡

# ሥልጠና

እንደማካካሻ ተደርጎ ሥራ ሳልጀምር ወዲያውኑ ለንደን ሄጄ ግሪንድንሌይስ ባንክ ለስምንት ወር የሥራ ልምምድ እንዳደርግ አቶ ደበበ አስፈላጊውን ሁሉ አደረጉና በመጋቢት 1964 መጨረሻ ወደ ለንደን ሄድኩ:: በባንኩ ኢንስቲትዩት ስለብድር ትንተና የሚሰጠውን ኮርስ ወስጄ አጠናቀቅሁ:: ከዚያም፣ በባንኩ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተዘዋውሬ ልምምድ አደረግሁ:: ብዙ የቆየሁት ዓለም አቀፍ መምሪያ ነበር:: መምሪያው ቋሚ አድርገን እናስቀርህ፤ የሥራ ፈቃድህንም እናሳድስልሃለን አለኝ:: አይሆንም፣ አገሬ ተመልሼ መሥራት ነው የምፈልገው አልኳቸው:: ይህን ስላቸው ተገርመው አዲስ አበባ ባንክ ምን ቢያዘጋጅልህ ነው የኛን አይሆንም ያልከው? ብለው ተገረሙ:: "ባይገርማችሁ ምን እንደሚጠብቀኝ አላውቅም፤ የማውቀው አገሬ ለመመለስ ያለኝ ፍላጎት አጠራጣሪ እንዳልሆነ ነው" አልኳቸውና ጉዳዩ ዳግመኛ አልተነሳም:: ቀደም ብሎ ምን ላይ ባተኩር ይሻላል? ብዬ ለአዲስ አበባ ባንክ ጽፌላቸው ነበር:: መሐመድ ሸሪፍ ሲመልስልኝ፣ እኛ ታደሰ ለሚባል ሰው በተለይ ያዘጋጀነው ቦታ የለም፣ ስትመለስ በምትመደብበት ቦታ ትሠራለህ አለኝ:: የደብዳቤው ዓላማ ቅስም ለመስበር የተጻፈ ለመሆኑ ምንም አጠያያቂ አልነበረም:: በዚህ ተስፋ ሳልቆርጥና ሳልበሳጭ በህዳር 1965 አዲስ አበባ ተመለስኩና የባንኩ ፕላን ክፍል ኀላፊ ተብዬ ተመደብኩ::

ለንደን ከአገራችን ሰዎች ጋር የነበረኝ ግንኙነት በጣም ውስን ነበር:: ከተማው እንደገባሁ የማውቀው ሰው ያገኘሁት ከሼል ኢትዮጵያ ለሥልጠና መጥቶ የነበረውን ማዕከለ ተወልደን ብቻ ነበር:: ቢዝነስ ኮሌጅ ሳለን አንድ ዓመት ይቀድመኝ ነበር:: አገሩን ለቅቄ ለመሄድ አንድ ሳምንት ያህል ሲቀረኝ የአፍሪቃ ተማሪዎች ባዘጋጁት አንድ የምሽት በዓል ላይ ተገኝቻለሁ:: ካገኘኋቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን መካከል የታወቀው የታሪክ ምሁር ዶክተር ባህሩ ዘውዴ ነበረበት:: የበዓሉ አስተባባሪ ኢትዮጵያዊነቱን

ከዶ ሱማሌነቱን የመረጠው አብዱል መጂድ ሁሴን ነበር:: ወያኔ ሥልጣን ሲይዝ የኢትዮጵያዊነት ካባውን መልሶ ደረበ መባሉን ስሰማ ነገ ደግሞ ሌላው ሲተካ የሚደርተውን ለማየት ያብቃን ብያለሁ::

ለንደንን ያለማመደኝ በሕክምና ትምህርት ላይ የነበረው የትምህር ቤት ጓደኛዬ የአየለ ደምሴ ታናሽ ወንድም ዶክተር አክሊሉ ነበር:: የአገሬንና የአገሬን ሰው ናፍቆት ለማርካት እንድችል ኤምባሲያችን እንዲወስደኝ ጠየቅሁትና አብረን ሄድን:: አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ ኤምባሲ ስፋቱ በጣም ትልቅ ስለሆነ ለንደን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲም የእንግሊዞቹን ባያክልም የራሱ ግቢ ያለው ትልቅ ሕንጻ ይሆናል ብዬ ገምቼ ነበር:: ኤምባሲው ስንደርስ በአንድ መንገድ ዳር ተያይዘው ከተሠሩ ቤቶች ውስጥ አንደኛው ደጃፍ መሆኑን ሳይ ቅር ተሰኘሁ:: በሩን አንኳኩተን ስንገባ ፊት ለፊት የተቀመጠችው የኤምባሲው አስተናጋጅ ፈረንጅ ናት:: ደነገጥኩ:: እኔ የጠበቅሁት ያገሬ ሰው አያለሁ ብዬ ነበር:: አስተናጋጅዋ እንደምን ዋላችሁ? ሳትል ምን ትፈልጋላችሁ? ብላ ጠየቀችን:: አካሄዳችን አበሻ ለማየትና ቢቻልም ጋዜጣ ካለ ተቀምጠን ለማንበብ በአጠቃላይ ደግሞ “ቤታችንን” ረግጠን ለመመለስ ስለነበር ፈረንጅዋ ምን ትፈልጋላችሁ? ስትል እዚህ ጉዳይ ከሌላችሁ በቀር ቀኝ ኋላ ዞራችሁ መሄድ ትችላላችሁ ማለቷ እንደሆነ ከአነጋገርዋና ከሁኔታዋ በቀላሉ ተረዳን:: ለጠየቀችን ጥያቄ ስንመልስ፣ አይ ምንም አይደለም፣ እንዲያው ብቻ፣ እንዲያው ዝም ብለን ነው፣ ጋዜጣ ካላችሁ ብለን ነው እያልን ግልጽ ባልሆነ መንገድ የመጣንበትን ምክንያት ስናድበሰብስ ከጀርባዋ የነበረው በር ይከፈትና ሁለት ጎምቱ ሰዎች ብቅ ይላሉ:: ሁለቱም ፎቅ የሚያክል ባርኔጣ ደፍተዋል፤ ባለሰደርያ ሱፍ ልብስ ለብሰዋል፤ ጥቁር ሱፍ ካፖርት ደርበዋል፤ ከዘራ ይዘዋል:: አክሊሉ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ፣ አጭሩ አምባሳደሩ ናቸው፣ ሌላኛው ደግሞ የፓሪስ አምባሳደር ናቸው ይለኛል:: ጄኔራል ኢያሱ መንገሻና አቶ መስፍን የበጋሸት መሆናቸው ነው:: ጄኔራሉ ከጸሓፊያቸው ጋር መነጋገር ያዙ:: ንግግራቸውን እንደጨረሱ ወደኛ ተጠግተው እንደሚስሙን፣ ቢያንስ እንደሚጨብጡን፣ ቆም ብለው እንደሚያነጋግሩን፣

ከዚያውም የፈለግነውን ያህል ቆይተን ጋዜጣ አንብበን ባሰኘን ጊዜ መሄድ እንድንችል እንደሚያረጋግጡልንና ለጸሓፊያቸውም አደራ ሰጥተውን ይሄዳሉ ብዬ ገምቻለሁ:: ሌላ ጊዜ ተመልሰን ቢሮአቸው ውስጥ ቡና እንድንጋበዝ እንደሚጠይቁንና ከኤምባሲው ሠራተኞች ጋር ሊያስተዋውቁን ቃል እንደሚገቡልን ሙሉ ተስፋ አድርጌአለሁ::

ሰውዬው ከጸሓፊያቸው ጋር የሚያደርጉትን ንግግር እንደጨረሱ ክቡራን አምባሳደሮቹ ደረታቸውን ነፍተው በአጠገባችን እየተራመዱ ወደበሩ አመሩ:: በፍጹም የማይታመን:: አላዩንም እንዳንል ከውስጥ በር ሲከፍቱ ፊት ለፊት ስለነበርን በደንብ ተያይተናል:: ጸሓፊያቸውን ማነጋገር ሲጀምሩ ወደ ጎን ዞር ስንል አይተዋል:: አራት ያህል እርምጃዎች ወደ ፊት እንደተራመዱ ጄኔራሉ ወደኋላ ይመለሳሉ:: እይታቸውን አክሊሉ ላይ ይተክሉና "አንተ፣ የደጃዝማች እገሌ ልጅ ነህ?" ይሉታል:: አክሊሉም "አይ አይደለሁም፣ ጌታዬ፣ የቄስ ደምሴ ልጅ ነኝ" ብሎ ይመልስላቸዋል:: (እኔ ብሔራዊ አገልግሎት ይርጋለም ሰባተኛ ክፍል ሳስተምር የኔታ ደምሴ አንደኛ ክፍል የአማርኛ መምህር ነበሩ::) "አባትህ የሚታወቅ ካልሆነ ምናባክ ታደርገኛለህ? ወይም ምን ታደረግልኛለህ?» የሚል ይመስል ጄኔራሉ ተፈናጥረው ወደበሩ አመሩ:: እኔና አክሊሉ በቤታችን ከእንግዳም እንግዳ ሆነን የምንለውና የምናደርገው ጠፍቶን ለጥቂት ሰኮንዶች ፈዘን ከቆምን በኋላ በሩን ከፍተን ሹክክ ብለን ወጥተን ሄድን::

ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ ውጭ ከነበርነው አምባሳደሮች መካከል ዘጠና በመቶውን ከሥራ ገበታችን አፈናቅሎ በባዕዳን አገሮች በትኖ አስቀርቶናል:: በሌላ በኩል ግን ጄኔራል እያሱን በሰማንያ አመታቸው ከጡረታ ጠርቶ የፓሪስ አምባሳደር አድርጎ ሾማቸው::

የዘመኑ አሜሪካኖች አሜሪካን ጀስቲስ ወይም የአሜሪካውያን ፍትህ ሲሉ እንሰማለን:: አሜሪካኖቹ ፍትሕ ነው የሚሉት ሁሉ ፍትሕ ነው፤ ሌላ የሚለው ግን ምንም ፋይዳ የለውም ማለታቸው ነው:: የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በየአገሩ የተሰማሩ ዲፕሎማቶች ሲባረሩ ጄኔራሉ የትግራይ

ወይም ኤርትራ ተወላጅ በመሆናቸው ብቻ በመብራት ተፈልገው ቦታ እንዲይዙ ሲደረግ ሳይ በኢትዮጵያ ፍትሐዊ አሰራር ተቀብሮ በቦታው የጎጠኞች "ፍትሕ" ተተክሏል ብያለሁ። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ ይህ አድሏዊ ወይም ኢፍትሐዊ አሠራር በደቦ መነቀሉ የማይቀር ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# አዲስ አበባ ባንክ

አዲስ አበባ ባንክ ሥራ የጀመርኩት ባጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል:: ከብሔራዊ አገልግሎት ተመልሼ ዐይኔን ኦፕራስዮን ከሆንኩ በኋላ ባለፈው ዓመት ለክረምት የሠራሁበት የትምባሆ ሞኖፖል ለሁለተኛ ጊዜ ሲቀጥረኝ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ ትንሣኤ ትምህርቴን ስጨርስ በቋሚነት እንደሚቀጥሩኝ ያላቸውን ሐሳብ ገልጸውልኝ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ ደግሞ ቀን ቀን የትርፍ ጊዜ ሥራ እንደሚሰጡኝ ተስማምተን ነበር:: የክረምቱ ሥራ ሊያልቅ አንድ ሳምንት ያህል ሲቀር ይመስለኛል ቢሮዋቸው ሄድኩና መቼ ልጀምር? እላቸዋለሁ:: ምኑን? ይሉኛል:: የትርፍ ጊዜውን ሥራ እላቸዋለሁ:: ለሠራተኛ ደመወዝ በመጨመሬ የበጀት እጥረት ስለገጠመኝ ልቀጥርህ አልችልም ይሉኛል:: እውነቱን ለመናገር ድርጅቱ ሁለት ጊዜ የክረምት ሥራ እድል ስለሰጠኝ ውለታውን ላለመብላት ብዬ ነው እንጂ ሥራ አጣለሁ በሚል አልነበረም አቀራረቤ:: ነገሩ እንትን አለቀ ቢሉ እንትን ቀለለ ሆነና ተሰናብቼ ሄድኩ::

ትምህርት ቤት ሲከፈት የክፍላችን ተማሪዎች የትርፍ ሰዓት ሥራ ማባረር ጀመርን:: በርከት ያሉትን ንግድ ባንክ ወሰዳቸው:: ከበደ አድነውን፣ ታዬ ተፈሪን፣ አስፋው አገኘሁንና እኔን አዲስ አበባ ባንክ ቀጠረን:: ከተመረቅን በኋላ አስፋው ሲቀር ሦስታችንን ባንኩ በቋሚነት ቀጠረን:: አስፋው ከመሐመድ ሸሪፍ ጋር ተጣላና ባንኩን ጥሎ ሄዶ ሌላ መሥሪያ ቤት ገባ::

የትርፍ ሰዓት ሠራተኛ ሆኜ ምድቤ ዋናው መሥሪያ ቤት ሥር በሚገኘው ቅርንጫፍ ውስጥ ሒሳብ ማስታረቂያ ወይም አካውንትስ ሪኮንሲልዩሽን ሴክሽን ነበር:: ቅርንጫፉ ከሌሎቹ የባንኩ ቅርንጫፎች ጋር የነበረውን

ሒሳብ መከታተልና ልዩነት ሲገኝ ምክንያቱን ፈልጎ እንዲስተካከል ማድረግ ነበር። ለኔ የተመደበ ዴስክ ስላልነበረ ግርማ ገብረሄና ዴስክ ጎን ተለጥፌ፣ ቀኝ ክንዴን እሱ ዴስክ ላይ አስደግፌ የታዘዝኩትን እሠራ ነበር። በሳምንት የምሠራው በጠቅላላው ከዐሥር ሰዓት የሚበልጥ አይመስለኝም። ግርማ የሥራ ችሎታውና ጠባዩ እንከን የማይገኝበት፤ የሁሉንም አመኔታ ማግኘት የቻለ ተወዳጅ ሠራተኛ ነበር። የሚያሳዝነው ግን የተሰጠውን አመኔታ ተገን በማድረግ ባንኩን ለረጅም ጊዜ ሙሽልቅ አድርጎ ከበላ በኋላ እኔ ለትምህርት አሜሪካ በነበርኩበት ወቅት ወንጀሉ ተደርሶበት ወደ ወኅኒ ቤት ተጋዘ። ግርግር ለሌባ ያመቻል ነውና መንግሥት ሲለወጥ ከወህኒ አምልጦ እንደወጣ ሰማሁ። አመኔታ ጥሩ፣ ቁጥጥር ግን በጣም ጥሩ ስለመሆኑ የገንዘብ ድርጅቶች ዘወትር ማስታወስ እንዳለባቸው ከግርማ ድርጊት የተሻለ ማስረጃ የለም።

ግርማን አንዳንድ ጥያቄዎች ስጠይቀው የክፍል ኃላፊያችን ሀብቴ ኪዳኔን ጠይቀው ይለኝ ነበርና ሀብቴን ይህ ለምን እንደዚህ ይደረጋል? ያስ ለምን እንደዚህ ይሆናል? እያልኩ ልቡን ውልቅ አደርገው ነበር። ጥያቄዬ ሲበዛበት አንድ ቀን እንዲህ አለኝ፣ ስማ ታደሰ፣ አንተ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ለማወቅ ወይም ልትደርስበት ትፈልጋለህ፣ ለምትጠይቃቸው ጥያቄዎች እኔም መልሶቹን የደረስኩባቸው ብዙ አመታት ከሠራሁ በኋላ ነው፤ አንተም ቀስ ብለህ ትደርስበታለህ፤ አሁን ማተኮር ያለብህ ሥራው እንዴት እንደሚሠራ እማወቁ ላይ ነው እንጂ ለምን? የሚለውን ወደፊት ስለምትደርስበት አሁን እሱ አያስጨንቅህ፣ ሥራህን አርፈህ ሥራ አለኝ።

በ1962 ወይም 1963 የኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባር ብሎ እራሱን የሰየመው ድርጅት አስመራን ልይዝ ስለሆነ የኤርትራ ተወላጆች አገራችሁ ግቡ ብሎ ውስጥ ውስጡን ጥሪ አስተላልፎ ኖሮ ሀብቴ ኪዳኔም እቃውን ሸጦ ሄዶ ነበር። ምኞታቸው እውን ሳይሆን ሲቀር ሀብቴ አዲስ አበባ ተመልሶ መደበኛ ሥራው ላይ ተሰማራ። በዚያው ዘመን የባንኩ የሕግ አማካሪ የነበረው አብዱልቃድር ደመወዝ አነሰኝ፤ የወጪ ቀዳዳዎቼ ብዙ ናቸው

ብሎ ሲዘረዝርልን ለኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባርም እንደሚከፍል እየሣቀ በገሀድ ነበር የነገረን:: እኛም ስቀን ዝም አልን እንጂ እንዴት ሊሆን ይችላል? ብለን፣ ነገሩ አሳስቦን የወሰድነው እርምጃ አልነበረም:: እንዲሁም፣ ደመወዝ ክፍያ ሰሞን አንድ ምስኪን መሳይ ሰው ቢሮአችን ድረስ እየመጣ እነ ተክስተ መአሾን ወደ ኮሪደር እየጠራቸው ገንዘብ ሲሰበስብ እናይ ነበር:: ነገር ግን ሌሎቻችን ምንም አናደርግም ነበር:: ታዲያ እነዚህ ሰዎች አህዮች ናቸው ቢሉን ምን ያስገርማል?

ከዋናው መሥሪያ ቦት ሪኮንሲልዬሽን ክፍል ሠራተኞች ሌላ ትዝ የሚለኝ መከተ በጋሻው ነው:: በቁመቱና መልኩ ሰማይ ጠቀስ፣ የሥራ ውጤቱ ግን ድንክዬ የሆነ ሠራተኛ ነበር:: እኔ የትርፍ ሰዓት ሠራተኛ ሆኜ በአንድ ወይም በሁለት ሰዓት የማከናውነውን እሱ ቀን ሙሉ ውሎበትም ፈቀቅ አያደርገውም:: መከተ፣ ብናግዝህስ እያልን ሥራውን ከጁ ፈልቅቀን የምንሠራባቸው ጊዜያት ጥቂት አልነበሩም:: መከተ ችግሩ የችሎታ መጉደል ሳይሆን የፍላጎት ማነስና የሐሞት መፍሰስ ነበር:: ሥራው እግሩን አንፈራጦ ዐይኑን አፍጥጦ ጣራውን እያየ የቀን ሕልም ማለም ነበር:: መከተ፣ ምነው? ደህና? ስንለው፣ እዚህ ቤት መሥራት ምን ዋጋ አለው? ደመወዝ አይከፍሉም ይለናል:: ለሚከፈለው እንኳ እንደማይሠራ እዚያው ቅርብ ያለነው ምስክሮች ነበርን:: ጠላትህ ስንፍናህ እንጂ መሥሪያ ቤቱ አይደለም ብለን በተዘዋዋሪ ስንወርፈው፣ ተግተህ ሠርተህ ማንነትህን ዐሳያቸውና አሳፍራቸው እንለዋለን:: አይሰማም:: በመጨረሻ ሥራውን ጥሎ ይወጣል:: እንደተረዳነው የተሻለ አገኛለሁ ብሎ ነበር:: ሥራ የውሃ ሽታ ሆነበት:: የሚላስ የሚቀመስ ሲጠፋ ያገባች ታናሽ እህቱ አስጠጋችውና ከጉድ አወጣችው:: በሌላ ተመልካች ዐይን ባማቱ እጅ መውደቁ እንዲያውም ገበናው ተጋለጠ እንጂ አልተሸፈነም ሊል ይችላል:: መከተ ቢያንስ ለሁለት ዓመት በችግር ጭቃ ጅራፍ ከተገረፈ በኋላ የ1966ቱ አብዮት ሲፈነዳ በአድኃሪው መንግሥት አገዛዝ ዘመን ያለአግባብ ከሥራ ገበታቸው የተባረሩ ሠራተኞች እንዲመለሱ ሲታዘዝ መከተም የትዕዛዙ ተጠቃሚ ሆኖ ባንኮ ዲ ሮማ ተቀጠረ:: በወቅቱ በባንክ ውስጥ ይሠሩ

የነበሩት ጓደኞቼ እነታዬ እንደ መከተ ጠንካራ ሠራተኛ በውርርድ አይገኝም እያሉ ሲነግሩኝ እደነቅ ነበር፡፡ በሰው ከተመከረ በችግር ውስጥ የተነከረ እንደሚሻል መከተ አስመሰከረ፡፡

ገና ሥራ ዓለም ከመግባቴ ግልጽ የሆነልኝ ሁለት ዓይነት ሠራተኞች እንዳሉ ነበር፤ እነሱም፣ ሥራን ለማሻሻል የሚጥሩና የተሰጣቸውን ሥራ ለመሥራት የተሰለፉ ናቸው፡፡ የዩኒቨርስቲ ትምህርት የቀሰምን ሠራተኞች አብዛኛዎቻችን በተተለመው ጎዳና መንገድ ብቻ ሳይሆን አንድ ሥራ ለምን እንደሚሠራ አውቆ ሥራው እንዲሻሻል እንጥራለን፡፡ ያወቅነውንም ለማሳወቅ ኃላፊነት እንዳለብን እንገነዘባለን፡፡ ትምህርት ቤት ሄዶ የመማር ጥቅሙ የተሻሻሉ ቴክኒኮችን አውቆ ለመውጣት ብቻ ሳይሆን እራስን ለለውጥ ማዘጋጀትና ብሎም የለውጥ ሐዋርያ ለመሆን እንደሆነ፣ የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ሠራተኞች ሎጂክን ተከትለው ይህ ቢደረግ ይህ ይከተላል፣ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ እታሰበው ግብ መድረስ ይቻላል ብለው መንገድ የሚያሳዩና ፊር ቀዳጆች እንደሆኑ አውቃለሁ፡፡ የሰላ አእምሮ አንዴ አፎቱ ከተመዘዘ፣ እንደሀብቱ ዓይነቱ አርፈህ ተቀመጥ ቢለውም፣ እሰገባው ውስጥ እንደማይመለስ ሀብቴና መሰሎቼ እንደማይረዱ ተገነዘብኩ፡፡ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅ ያለውና አሠራር ከልምድ የቀሰሙ ሠራተኞች አብዛኛዎቹ ዋናው ትኩረታቸው ሌላው የሚሠራውን ዐይቶ አሠራሩን ተከትሎ መሥራት ወይም በጥንቃቄ መገልበጥ እንደሆነና የተረከቡትን የአሠራር ሥርዓትና ዘይቤ በታማኝነት መጠበቅና እንዳይፈርስ መከላከል እንደሆነ ተገነዘብኩ፡፡ ባንኩ ውስጥ የአሠራር ብቻ ሳይሆን የአስተሳሰብ ለውጥ የማምጣት እድል እንዳለኝና ኃላፊነትም እንዳለብኝ ተረዳሁ፡፡

በቋሚነት በመስከረም 1962 ተቀጥሬ በዋናው መሥሪያ ቤት ሒሳብ ማስታረቂያ ክፍል ተመደብኩ፡፡ አንድ ቀን የክፍላችን ሠራተኛ ተከስተ መአሾ አቶ ደበበ ቢሮ ተጠርቶ ስለሥራ ሲወያዩ ትጉህ ሠራተኛ ስለመሆኔ ለአቶ ደበበ ይናገራል፡፡ ወድያው በባንኩ ልዩ ልዩ ክፍሎች ተዘዋውሬ

እንድሠራ ፕሮግራም ይወጣል:: በውጭ ምንዛሪ ክፍል ለጥቂት ሳምንታት እንደሠራሁ ፕሮግራሙ ይቋረጥና ይልማ ካሳዬ ለቆ የሄደውን የብድር ክፍል ኃላፊነት እንድረከብ ይደረጋል:: እድሜዬም ሃያ አራት አመት ነበር:: የጸሓፊዬ የመሠረት ኃይሌ ጓደኞች እየመጡ ሰርቀው ሲያዩኝ አስታውሳለሁ::

ከጓደኞቼ ከታዬና ከከበደ ጋር ምሳ የምንበላው ብዙውን ጊዜ አሁን ሼራተን ሆቴል በተሰራበት ቦታ ላይ በነበረ በአንድ የጣልያን ምግብ ቤት ነበር:: ምግቡን እያጣጠብን ወደታች የምንሸኘው ብዙውን ጊዜ በአምቦ ውሃ ሲሆን አልፎ አልፎም የጣልያን ምግብ እንዴት መድኃኒታችን የፈቀደውን ቪኖ ይከለከላል? እየተባባልን ና ግባ ወዳፉኪ እንለዋለን:: ከምሳ መልስ እየተንከተከትን ስንሥቅ ያየ አንድ ሠራተኛ ለኛ ሳይሆን ለባንኩ ጤንነት ተቆርቁሮ፣ እነዚህን ልጆች መጠጥ አሳስቆ ወደ ገደል ይዞ ከመውረዱ በፊት በቶሎ ይመልሷቸው ብሎ አቶ ደበበን ያሳስባቸዋል:: አንድ ቀን ከምሳ መልስ፣ ገና ቢሮ ከመግባታችን፣ አቶ ደበበ ይፈልጉሀል ተብዬ ቢሮአቸው እሄዳለሁ:: ስለዚህ ጉዳይ እንድታስረዳኝ ነው የጠራሁህ ይሉኛል:: እኔም ገለጻ ከመጀመሬ፣ የለም፣ ናና እዚህ አጠገቤ ቆመህ አስረዳኝ ይሉኝና አጠገባቸው ሄጄ ቆሜ ሐሳቤን መግለጽ እጀምራለሁ:: የለም በደንብ እንዲሰማኝ ጆሮዬ ጋ ጠጋ ብለህ አስረዳኝ ይሉኛል:: ስጠጋ ስጠጋ የቀረኝ ከንፈራቸውን መሳም ብቻ ነበር:: በመጨረሻም ግድየለም ተወው፣ ቢሮህ ሂድ ብለው አሰናበቱኝ:: የፈለጉት ትንፋሼ ቪኖ ወይም አልኮል ይሸት እንደሆን ለማወቅ መሆኑን ወዲያው ገባኝ:: ደግነቱ ያን እለት ምድቡ ለቪኖ ሳይሆን ለአምቦ ውሃ ስለነበር ፈተናውን አለፍን:: ከዚያን ቀን በኋላ፣ ቪኖ የሚባል ነገር በምሳ ሰዓት ነክተን አናውቅም:: ይኸውም፣ እራሳችንን ከተፈታኝነት ወደ ፈታኝነት እስክናሸጋግር ድረስ ነበር:: በደርግ ዘመን ቀን ቀን አልኮል መጠጣት ተከልክሏል ሲባል እድሜ ለአቶ ደበበና ለአቶ ተቆርቋሪ፣ እኛ እራሳችንን በራሳችን ከከለከልን ውሎ አድሮ ነበርና ጭንቅን ቤትሽን ፈልጊ አልናት::

እኔ የብድር ክፍል ሆኜ፣ ታዬ በዋናው መሥሪያ ቤት ቅርንጫፍ የተቀማጭ ገንዘብ ክፍል ኃላፊ፣ ከበደ ደግሞ በዋናው መሥሪያ ቤት የሒሳብ ክፍል ምክትል ሹም ነበር።

ለታዬ የሚታዩት ከቀለማት ነጭና ጥቁር፣ ከጠባይ ጥሩና መጥፎ፣ ከአመኔታ ወስላታና ታማኝ፣ ከግል ስሜት መውደድና መጥላት፣ ከአገር ስሜት መውደድና መካድ፣ ከግንኙነት መቅረብ ወይም መራቅ፣ ወዘተ ብቻ ነበር። ለታዬ በሁለቱ መካከል የሚወድቅ ነገር የለም። ስለሆነም፣ ለታዬ ዓለም የምትታየው በሁለት ጎራ ተከፍላ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ለታዬ ዓለም ሁለት ፈርጆች ወይም፣ በእንግሊዝኛው፣ ዳይሜንሽንስ ብቻ ነው ያላት። ከዚህ ውጪ በግን፣ በቢሆንም፣ በዚህ ቢሆን፣ በዚያ ቢሆን፣ በእንዲህ ቢሆን፣ በእንዲያ ቢሆን፣ እያሉ ሌሎች ፈርጆች ለማውጣት መሞከር፣ እንደታዬ አስተሳሰብ፣ ለቅጥፈት መንገድ ማመቻቸት ነው። ለታዬ ቀጥ ብሎ መሄድ የማይችል ሁሉ ጠማማ ነው። ታዬን አንድ ሰው ከጣመው ወዳጁ ነው፣ ካልጣመው ፊቱን እንኳን ማየት አይፈልግም።

እናቱ ስትፈጥረውም ባይሆን የሕይወት ልምድና ከባቢ ኃይሎች ጨፍልቀው የጠፈጠፉትን ታዬ ማን ይግጠመው ቢባል፣ አቶ ደበበ የሪልፖሎቲክ ጳጳስ፣ አስመሳዮቹ ኃይሉ ቢላትና መሐመድ ሽሪፍ። በታዬ መለኪያ ሁሉም ጠማሞች ወይም ወልጋዶች ናቸው።

ታዬ የተቀማጭ ገንዘብ ክፍል ኃላፊ ሆኖ የአቶ ደበበ ቀኝ እጅ የነበሩት ኃይሉ ቢላትና መሐመድ ሽሪፍ ለዕቃ ወይም ለአገልግሎት ግዢ የሰጡዋቸው ቼኮች በቂ ገንዘብ ሒሳባቸው ውስጥ ባለመኖሩ ሲመለሱ ያያል። እንዲህ ዓይነት ቼክ የተሰጣቸው ሰዎች መሐመድ ቢሮ ሲሄዱ የሉም እንደሚያሰኝ ይሰማል። ገንዘብ ሳይኖር ቼክ መጻፍ እንኳን ከባንኩ ኃላፊዎች ቀርቶ ከማንም የሚጠበቅ አይደለም፤ ወንጀልም ነው። ወራዳ ድርጊታችሁን አቁሙ ብሎ ታዬ የኀበጡትን ሊያቀና ይሞክራል። ያተረፈው የእነ መሐመድን ጠላትነት ብቻ ይሆናል። ተደፈርን ይሉና ቂም ይይዙበታል።

አንድ ጊዜ ከባንኩ ገንዘብ ይጭበረበርና ይሰረቃል፡፡ የተጭበረበረው ቼክ የተመነዘረው ንግድ ባንክ መርካቶ ቁጥራ ቅርንጫፍ ነበር፡፡ ቼኩን የመነዘረው ምን ዓይነት ሰው ነው? ቢባል ታዬን የሚመስል ነው ተባለ፡፡ እንዳጋጣሚ ቼኩ የተመነዘረ ዕለት ታዬ ሥራ አልገባም ነበር፡፡ ታዬን ሊያገኙት የፈለጉት ጠላቶቹ ኃይላቸውን አስተባበሩና አንድና አንድ ሁለት ነው ብለው ታዬን ከሥራ አባረሩት፤ ከሥራ ከመባረሩ ሌባ መባሉ!

ታደሰ ወልደሚካኤል የሚባል የትምህርት ቤት ጓደኛችን ቀደም ብሎ ከታዬ በርከት ያለ ገንዘብ ይበደርና የለብኝም፣ አልከፍልህም ብሎት ነበር፡፡ ታዬ ቢሞክር ቢሞክር ማግኘት ስላቃተው ምን ማድረግ እችላለሁ? ብሎ ነገሩን ተወት አድርጎት ነበር፡፡ የሚገርመው ግን ታደሰ ታዬ ከሥራ መባረሩን ሲሰማ ፈልጎት ገንዘቡን ሰጠው፡፡ በዚህ አድራጎቱ የተነሳ ለታደሰ ያለኝ አድናቆትና ከበሬታ በልቤ ላይ ለዘለአለም ተጽፎአል፡፡ ይህን ስለሚያውቅ ሊሆን ይችላል፣ ታደሰ ለሽፍጥ አመቻችቶኝ ልቤ እያወቀ ተረትቼለታለሁ፡፡ ታደሰ የካደውን ገንዘብ ለጊዜውም ቢሆን ጊዜና ሰው ለከዳው ታዬ አምጥቶ መስጠቱ በኔ መለኪያ ታደሰን ትልቅ ሰው አድርጎ ስላስቀመጠው፣ እኔን ያታለለኝ ቢቸግረው ነው አልኩ እንጂ አልፈረድኩበትም፡፡

ታዬ ጉዳዩን ለመከታተል ባንክ ይመላለስ ነበር፡፡ አንድ ቀን ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጁ አቶ ገብረመድህን ሽንቁጤ ቢሮ ተቀምጦ ባላጋራው ኃይሉ ቢላት ይገባል፡፡ አመጣጡ ድንገት ይሁን ወይስ ተጠርቶ አላውቅም፡፡ ኃይሉ ታዬ ፊት ለፊት ይቀመጥና ሽጉጡን ላጥ አድርጎ ታዬ ላይ ያነጣጥርበታል፡፡ ከዚያም እስኪ ምን ልትሆን ነው? እያለ ታዬን ያስፈራራዋል፣ ይዝትበታል፣ ይሰድበዋል፡፡ አቶ ገብረመድህን በጣም ይደነግጣል፤ የሚይዘው የሚጨብጠው ይጠፋበታል፡፡ ታዬ ድምጽ አጥፍቶ አቀርቅሮ መሬት መሬት ብቻ ያያል፡፡ እንደዚያ ማቀርቀሩ የሚጠላውን ሰው ዐይኑን ማየት እንደማይፈልግ ለማስመስከር ብቻ ሳይሆን ለብልኀትም ነበር፡፡ ኃይሉ መሣሪያውን እንዳነጣጠረ ነው፤ ድንፋታው አላቆመም፤ ታዬ ሽጉጥ ያነጣጠረውን የኃይሉን እጅ ድንገት ሳይታሰብ ይመታል፤ ሽጉጥ

ተሽቀንጥሮ ይወረወራል። ከዚያም ኃይሉን የኋሊት የፊጥኝ ይዞ በጉልበቱ ጀርባውን እየጎሰመ ኮሪደር አቶ ደበበ ቢሮ ፊት ለፊት ይዞ አውጥቶ ወለል ላይ ካነጠፈው በኋላ ሊደቁሰው ሲል ገላጋይ ያስጥለዋል። ወንጀል የተሠራበትን ሽጉጥ የባንኩ ባለሥልጣኖች ተባብረው አሸሹት። ለኃይሉ አደላችሁ የሚለው ድምጽ ሲበዛ፣ ኃይሉ ያስፈራራበት ሽጉጥ የውሸት ነው አስባሉለት።

ታዬም ከተከሰሰበት ወንጀል ስሙን ለማንጻት ትግሉን ቀጠለ። በመጨረሻም አሸነፈና ወደ ሥራ ገበታው ተመለሰ። ቼኩን ያጭበረበረው ዮሐንስ የሚባል ሠራተኛ ሆኖ ተገኘ። በእርግጥም መልኩ ታዬን ይመስላል።

ስለታዬ መልክ ከተነሳ አንድ ታሪክ ላጫውታችሁ። በቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክበብ ፊት ለፊት፣ ከባቡር ጣብያ ወደ አብዮት አደባባይ በሚወስደው መንገድ በስተግራ ገባ ብሎ ሐረር መሶብ፣ እንዳገሩ ምግብ ቤት የሚባል ነበር። ጣልያኑ ምግብ ቤት ካልሄድን ቅርብ በመሆኑ በእግራችን እየሄድን ምሳ የምንበላው እንዳገሩ ነበር። ታድያ ምግብ ለማቅረብ ጊዜ ይፈጃሉ። የተራበ አይምጣብን የሚሉ ይመስላል። መጀመሪያ ምግብ ቤቱን የረገጥኩት 1957 ገደማ ተማሪ ሆኜ ከወንድሜ ከብርሃኔና ከጓደኛው ከበቀለ ወርቁ ጋር ነው። ያኔም ለምሳ ነበር የሄድነው። ሆድ ቢንጓጓ፣ ሐሞት ቢፈስ ምግብ ከጓዳ አልወጣ ይላል። በቀለ ትእግስቱ ያልቅና፣ ይሄ ምግብ ቤት እውነትም እንዳገሩ ነው፤ ተኝቷል፣ አይነቃነቅም፣ ቀስቃሽ ይፈልጋል አለ።

የእንዳገሩን ጽናት የዘመን ብዛት ሳይነቀንቀው እንደነበር አገኘሁት። ያኔም እንደድሮ የራበህ ባለህበት እርጋ የሚል ይመስላል። አንድ ቀን አቶ ረሃብን ለማታለል የቆጡን የባጡን ስንቀበጣጥር ቆየንና ግድግዳ ላይ ወደተሰቀሉት የአገር ባሕል እቃዎች ትኩረታችንን አዞርን። ታዬ፣ ያ ምንድን ነው? ቀጥሎ ያለውስ? ከዚያስ በታች? በላይ? በጎን? እያለ ከበደንና እኔን ያፋጥጠናል። ሲያቅተን እናንት ቀሽሞች ብሎ የግሰጻ ኩርኩም እያቀመሰን መልሱን ይነግረናል። አሳላፊዋ ጓዳ ገብታ ወጥ ቤቶችን እንደማትጋት ለካስ

የጎረምሳ ዐይን ዐይን ዕያየች ከታዬ አፍ የሚፈልቀውን ለዛ እያጣጣመች ትምግ ኖሯልና ድንገት ሳናስበው ሣቋን ትለቀዋለች:: ዐይኖቻችን ከግርግዳው ወደ ዳሌና ባቷ ከመቅጽበት ዞረው አነጣጠሩ:: ምን ተፈጠረ? ብለን ብንጠይቃት፣ በአገጭዋ ወደ ታዬ እያመለከተች፣ ዐይኖችዋን እያስለመለመች "እሳቸው እንኳ ሲያውቁ እናንተ ሁለታችሁ እንዴት አቃታችሁ ብዬ ነዋ" ብላ አንገትዋን አቅለሰለሰች::

እስከዚያ ቀን ለታዬ የሰጠነው የቅጽል ስሙ ፈረንጁ ነበር:: እኛም በተራችን ከት ብለን ሣቅን:: ታዬ ክልስነትህ ታወቀብህ አልነው:: አንድ ጊዜ ቦንጋ ለሥራ ሄዶ የከተማው ሕፃናት እየተከተሉ ፈረንጅ እያሉ ያበሽቁት እንደነበር እራሱ ነግሮናል:: ታዲያ ልጅ ይታየዋል ተብሎአልና ታዬ አዋቂ ዘንድ ሄዶ እጣን ቢያስጨስ እውነቱ ይገለጽለት ይሆናል:: እሱ ግን እስከሚያውቀው ድረስ የፈረንጅ ደም አንድም ጠብታ አልተደባለቀበትም:: እናቱ ወደ ሰማዩ አባታችን ዘንድ ለመሄድ እየተዘጋጁ ሳለ ያደረጉት ኑዛዜ ካለ አላውቅም::

እድሜ ለእንዳገሩ፣ የታዬ ሁለተኛ ቅጽል ስም እሳቸውእንኳሲያውቁ ሆኖ ቀርቷል:: ከበደና እኔ ካገር ውጭ ስለሆንን ታዬ ሲከፋው፣ ተራቢ ሲያጣ፣ ሕይወት እጅ እጅ ሲለው ወይም ቅመም ሲያንሰው፣ ማን እሳቸውንእንኳንሲያውቁ ብሎ ይጥራኝ? ሳይል አይቀርም ብዬ እገምታለሁ::

የእንዳገሩ መስተንግዶ ዳተኛነት ስናወግዝ ሁሉም ነገር ይለወጥ ማለታችን እንዳልሆነ መታወቅ አለበት:: አንዳንድ የሚያውቁት ነገር ሳይለወጥ በቦታው እንደነበር ሲያገኙት ያስደስታል:: ይህ በተለይ የሚመለከተው ግብረገብ ነክ ሥርዓቶችን ነው:: የሕብረተሰብ ማንነት አቅጣጫውን ሳይስት ህልውናውን ጠብቆ ማቆየት የሚቻለው የማኅበረሰቡ አባላት ሕግጋትን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴአቸው መመሪያ ሲያደርጉና ሲከተሏቸው ብቻ ነው:: ኮምፓሱ ከተሰበረ ወይም ሁሉም በመሰለው አቅጣጫ ከነጎደ ያ ኅብረተሰብ እራሱን በራሱ እንደሚያጠፋ ወይም በባዕዳን ኃይሎች እንደሚዋጥ መታወቅ አለበት::

ታዬ ከሥራ ታግዶ በነበረበት ወቅት አንድ ታሪካዊ ሥራ ሠራ፡፡ የባንኩን ሠራተኞች በምስጢር በማኅበር አደራጅቶ፣ ማኅበሩ የሕግ ሰውነት እንዲያገኝ አደረገ፡፡ አደራጆቹ ስብሰባ ሲያደርጉ ብዙ ጊዜ ሰዋራ ቦታ እየፈለጉና ጫካ ውስጥ እየተደበቁ ነበር፡፡

ሠራተኛውን በማኅበር እንዲደራጅ የገፋፋው የባንኩ ኃላፊዎች ታዬን ማንገላታታቸው ብቻ ሳይሆን ሠራተኛው ለሰጠው ነጻ አገልግሎት የኃላፊዎቹ ውለታቢስነትም ነበር፡፡ በዲሴምበር ሠላሳ አንድ ሠራተኛ ያመቱን ሒሳብ ሲዘጋ አምሽቶ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ ለሠራው ሥራ የትርፍ ሰዓት ክፍያ አይጠይቅም፡፡ በጃንዋሪ አንድ አንዳንድ ሠራተኞች በእንቅልፍ ተሸንፈው ጠዋት ልክ በሁለት ሰዓት ተኩል ሳይገቡ ይቀሩና ጥቂት ደቂቃዎች ያረፍዳሉ፡፡ የባንኩ የሠራተኛ አስተዳደር ክፍል ለአርፋጆቹ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡ ሠራተኛው በጣም ተቆጣ፡፡ አስተዳዳሪዎቹ የማመዛዘን ችሎታ የጎደላቸው ኀሊናቢሶች ናቸው ብሎ ደመደመ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሠራተኛና አሠሪ አይጥና ድመት ሆኑ ማለት ይቻላል፡፡ ሠራተኛው መብቱና ጥቅሙን ስለሚያስከብርበት መንገድ በጥሞና ማሰብ ጀመረ፡፡

አቶ ደበበ የማኅበሩን መቋቋም ሲሰሙ እንደ እብደትም ቃጣቸው፡፡ ያናደዳቸው የማኅበሩ መቋቋም ብቻ ሳይሆን የማቋቋሙ ሂደት ሲጠነሰስና ሲካሄድ ስላልደረሱበትም ነበር፡፡

አቶ ደበበ የባንኩ ኃላፊ ብቻ ሳይሆኑ እራሳቸውን እንደሠራተኛው አባትም ይቆጥሩ ስለነበር ልጅ አባቱን ተጋፍቶ እንዴት እንዲህ አይነት ሥራ ይሠራል? አሉ፡፡ ሠራተኛው ሥራ ስለፈጠርኩለት ሊያመሰግነኝ ይገባል እንጂ እንዴት የማልወደውን ነገር ከጀርባዬ ሄዶ ይሠራል? የሚገባውን መቼ ነፍጌው አውቃለሁ? አባት ለልጁ እንደሚያስብ እኔስ ያባትነት ግዴታዬን ተወጥቼ አይደለም እንዴ? አሉ፡፡

እውነቱ ተገልጦ ሲታይ ግን በአቶ ደበበም ሆነ በባንኩ ኃላፊዎች ዐይን ታዬና ኃይሉ ቢላት ወይም መሐመድ ሽሪፍና ታዬ እኩል አልነበሩም። ጥቅማ ጥቅምንም በተመለከተ የአቶ ደበበ ኃላፊነት በመሠረቱ ለባንኩ ባለቤቶች እንጂ የሠራተኛውን መብት ማስጠበቅ አልነበረም። የባንኩ ባለቤቶችና ሠራተኛው በጥቅም ቢጋጩ የሚያደሉት ለባለ አክስዮኖች ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ባለቤቶቹ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ተደራጅተዋል፣ ቦርድ አቋቁመዋል፣ ፍላጎታቸውን የሚያስፈጽሙ ወይም የሚያሳኩ ሥራ አስኪያጆች መርጠው ሾመዋል። ባንጻሩ፣ ሠራተኛው መብቱንና ክብሩን ለማስጠበቅ፣ በደል ለመቋቋም፣ ጥቅሙን ለመደራደር በማኅበር ቢደራጅ አያስደንቅም። ሠራተኛው በማኅበር መደራጀቱ የበላበትን ወጭት እንደሰበረ መታየት አልነበረበትም። አቶ ደበበ የማኅበሩን መቋቋም እስከመጨረሻው ባይዋጥላቸውም ሳይወዱ ከማኅበሩ ጋር እንዲደራደሩ ተገደዋል። የባንኩ ባለቤትነት በ1967 ወደ መንግሥት ይዞታ ሲዛወርና እሳቸውም የባንኩ ኃላፊ መሆናቸው ሲቀር በእሳቸው አስተዳደርና በሠራተኛው መካከል የነበረው ትግል አከተመ።

ባንኩ ሲወረስ እኔ ወደ ብሔራዊ ባንክ ተዛውሬ ምክትል ኃላፊ ነበርኩ። ለርክክብ አቶ ደበበ ብሔራዊ ባንክ መጥተው በነበረበት ወቅት «እኔ የምጠይቀው አንድ ነገር ብቻ ነው፣ አዲስ አበባ ባንክ የሚለውን ስም እንዳትሰርዙብኝ» አሉ። ጥቂት ቆይቶ አዲስ አበባ ባንክና ባንኮ ዲ ሮማ ሲዋሃዱ አበባው ተቀነጠሰና ውህዱ አዲስ ባንክ ሆነ። በመጨረሻም አዲስ ባንክና ንግድ ባንክ ሲዋሀዱ የባንኩ ስም አዲስ ንግድ ባንክ እንዲባል ለቦርዱ ሐሳብ አቀረብኩ። ሐሳቡን ሳቀርብ አቶ ደበበ የባንኬን ስም እንዳትፍቁት ያሉት ትዝ ሳይለኝ አልቀረም። ቦርዱ ሐሳቡን ሳይቀበል ቀረና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጸና።

አቶ ደበበ ያቋቋሙት ባንክ ተወርሶ በመጨረሻ ስሙ ከመዝገብ ቢፋቅም ሁለት የባንክ አዛገሮችን፣ ማለትም ለይኩን ብርሃኑንና ታደሰ ገብረኪዳንን፣ እና አንድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ጥላሁን አባይን፣

ስላፈራሁ እኮራለሁ ይሉ ነበር። እኔን በተመለከተ እንደ አስተማሪና አባት ሆነው፣ አበረታትተው የባንክን ሥራ ሞያዬ እንዳደርግ ስለረዱኝ ከፍተኛ ውለታ አለብኝ። ብዙዎች ሌሎችም እንደዚሁ እንደሚሉ አልጠራጠርም።

ብድር ክፍል ሆኜ በተለይ ከማስታውሳቸው፣ ጠንካራውና ትጉሁ የናዝሬት ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ በቀለ ታደለ ይገኝበታል። በብድር ክፍል ዋናው ተግባሬ ከባንኩ ቅርንጫፎች የሚመጡ የብድር ማመልከቻዎችን እንዲሟሉ አድርጌ በባንኩ ሁለተኛ ሰው፣ እንግሊዛዊ የግሪንድሌይስ ባንክ ተወካይ፣ ለሚመራው ለዋናው የብድር ኮሚቴ ማቅረብና የኮሚቴውን ውሳኔ ለቅርንጫፎች ማስተላለፍ ነበር። ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ እንጠየቃለን፤ ስለብድር አመልካቾች ማንነት ዋናው መሥሪያ ቤት ጥሩ ግንዛቤ የለውም፤ መፈቀድ ያለባቸው የብድር ማመልከቻዎች ውድቅ ይደረጉብናል እያሉ ቅርንጫፎች ያማርራሉ። አንዳንዶቹ በወረቀቱ ሥራ ብዙም ስለማይተጉበት ምልልስ ይበዛል።

በቀለ ታደለ የኮሚቴውን አባላት ናዝሬት ድረስ ይጋብዝና አንዳንዶቹ የብድር አመልካቾችን አዙሮ ያሳየናል። እነዚያን የጠየቃችኋቸውን ጥያቄዎች እነዚህ ሰዎች አሁንም ይመልሱዋቸዋል ብላችሁ ታምናላችሁ? ብሎ ይጠይቀናል። ዘመናዊ የሒሳብ አያያዝ ዘዴ አይጠቀሙም፤ ስለሥራ እቅዳቸው በጽሑፍ የማስቀመጥ ችሎታ፣ ልምድም ሆነ ዝንባሌ የላቸውም፣ እኛ ዋና የምናተኩረው ማንነታቸውን አውቀን፣ ሥራቸውን ተከታትለን የወሰዱትን ገንዘብ መመለስ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለውን በአእምሮአችን ካወጣን ካወረድን በኋላ ብድር እንዲሰጣቸው ስንደግፍ እናንተ በቂ ምክንያት ከሌላችሁ በቀር የኛን የድጋፍ ድምፅ ውድቅ ባታደርጉት ይመረጣል ይል ነበር።

የናዝሬት ቅርንጫፍ ከሚሰጠው ብድር ሳይመለስ የሚቀረው መጠኑ እዚህ ግባ የማይባል በጣም ትንሽ ስለነበር በቀለ የባንኩ የበኩር ልጅ ተደርጎም ይታይ ነበር። ለሱ የነበረን አድናቆት ከናዝሬት ጉብኝታችን በኋላ በይበልጥ ከፍ አለ። ታዲያ ቀይቶ እንደሰማነው አንድ ተበዳሪ አልከፍልም ብሎ

ቢያስቸግረው በቀለ ያለውን ኃይል ሁሉ ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይመለስ ነበር፡፡ በአንድ ተበዳሪ ላይ መሣሪያ መዞ፣ እጅ ፊልቅቆ የባንኩን ገንዘብ ነጻ አውጥቶ ጉሮ ወሽባዬ እያለ መመለሱን ሰምተናል፡፡

አንድ ቀን የዋናው ብድር ኮሚቴ አባላት አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙትን የኮታሪና የበለጠ ሺበሺ የቡና ላኪ ድርጅቶችን፣ የተስፋዬ አትሬሶን የጫማ ስፌት ፋብሪካ ተዘዋውረን ጎበኘን፡፡ ኮታሪ ከፍተኛ የብድር ተጠቃሚ ነው፡፡ እናንተ ባንኮች የምታውቁት ብድር መስጠት ብቻ ነው፤ የተበዳሪዎቻችሁን ሥራ ተዘዋውራችሁ አታዩም እያለ ለባንኩ ያለውን ታማኝነት ለመግለጽና በምላሹም ባንኩ በሱ ላይ እምነት እንዲኖረው የማይፈነቅለው ድንጋይ አልነበረም፡፡ የጉብኝቱ ዕለት የቡናው መጋዘን ጢቅ ብሎ ሞልቷል፡፡ እዚህ ምን ያህል ቡና አለህ? ብለን ጠየቅነው፡፡ መልሱን ነገረን፡፡ ጥቂት ጆንያዎች መዝነው አሳዩን፡፡ ቁጥሮች አባዝተን ከደማመርን በኋላ ዓለም ጤና ናት፣ እንዳስቀመጥናት አገኘናት፣ የሰጠነው ብድር አልባከነም፣ ባለአክሲዮንና ገንዘብ አስቀማጭ በያለህበት ደስ ይበልህ ብለን እንቢልታ ነፍተን ተነስተን ልንወጣ ስንል ከቁመቱ ማጠር የተነሳ መኪና ሲነዳ የኋላ ማርሽ አይሆነኝም እያለ በራሱ ላይ የሚቀልደው የባንኩ ሦስተኛ ሰው አቶ ገብረመድህን እስቲ ክብደቴ ስንት እንደሆነ ልወቅ ይልና በቡናው ሚዛን ላይ ተነስቶ ይቆማል፡፡ ቁጥሩን ትክ ብሎ ያየዋል፡፡ አቶ ሚዛን ገብሬን፣ ትናንት ከነበርክበት የክብደት ደረጃ በአንድ ቀን በ30 ኪሎ ጨምረሃል እንኳን ደስ ያለህ ይለዋል፡፡ በጭራሽ የማይታመን! እኛም ከተል በማድረግ የዚህ ቤት ሚዛን አማልክት ተአምራቸው እንዴት እንደሚሠራ ይገለጽልን እንላለን፡፡ ኮታሪ እዚያው ቆሟል፡፡ እህስ? ታዲያስ? ቢባል ያ አንደበተ ርቱዕ አቶ ሐቀኛው ልሳኑ ተዘጋ፡፡ ዐይን ፍጥጥ ብቻ ሆነ፡፡ የሌለ ቡና አለ እየተባለ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር የባንኩ ገንዘብ እንደተጭበረበረ ግልጽ ሆነ፡፡ ባንኩ ለብዙ አመታት ገንዘቡን ለማስመለስ ያልተቆጠበ ጥረት ቢያደርግም አብዛኛውን መሰብሰብ ሳይቻል ቀረ፡፡

የኢትዮጵያ ባንኮችና ነጋዴዎች ስለውጭ ሰዎች አንድ በውል መገንዘብ ያለባቸው ነገር አለ:: እነሱን ማመን፣ ቀብሮ ነው የሚለውን እንተወውና፣ ዋስትና ይዞ ነው:: አንዳንዶቹ ወደ አገራችን የሚመጡት ሞኞች አገር ሄደን ቦጥቡጠን እንመለስ በሚል መንፈስ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል::

በለጠ ሺበሺ መጋዘኑ ብንሄድ የሚገኘው በመኖሪያ ቤቱ ነው ተባለና ወደዚያው አመራን:: ትንሽ ተጫጭኖት ኖሮ ጋቢውን ተከናንቦ ተቀምጧል:: ሕፃን ልጁ ጥብቆ ለብሳ ባዶ እግሩዋን ናት:: አኗኗሩ ድህነት የተቆራኘው እንጂ ከባድ የቡና ነጋዴ አይመስልም:: ጉብኝቱን ጨርሰን መንገድ እንደጀመርን የኮሚቴው ሊቀመንበር ሚስተር ማክዶናልድ፣ አንድ ተበዳሪ ገንዘቡን ሳያባክን በሥራ ላይ ሲያውለውና ሲያዋልደው እኛ የባንክ ሰዎች ደስ ይለናል፤ ታዲያ የአቶ በለጠም በዛ፤ ሕይወቱንም መርሳት የለበትም ብሎ ተናገረ::

በመጨረሻም፣ የተስፋዬ አትሬሶን ጫማ ፋብሪካ ጎበኘን:: አያያዙ ጥሩ ይመስላልና ድጋፍ ሊሰጠው የሚገባው ሰው ነው ተባብለን ከመጨረሳችን ተስፋዬ ተሰናብቶን በቢ ኤም ደብልዩ ገባና ተሽቀንጥሮ ሲሄድ አየነው:: ወዲያው ሚስተር ማክዶናልድ፣ ይህ ሰው ካሁኑ የቅንጦት ኑሮ የለመደ ይመስላልና የባንኩን ገንዘብ በአደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል አለ::

የብድር ክፍል ቀይታዬን ሳስታውስ ምንም የማይረሱኝ ወይዘሮ ሉሊት፣ የደጃዝማች አስፋው ከበደ ባለቤት ናቸው:: ደጃዝማች ይታመሙና እንግሊዝ አገር ለሕክምና መሄድ ያስፈልግዎታል ይባላሉ:: ሰውዬው አዲስ አበባ ውስጥ ካሉት ሀብታሞች አንዱ ይሁኑ እንጂ በባንክ ተቀማጭ ወይም በእጃቸው ጥሬ ገንዘብ የላቸውም:: አገር ፍቅር ማኅበር ጎን ያለውን ሕንጻቸውን የተከራየው አዲስ አበባ ባንክን ብድር ይጠይቁና ይፈቀድላቸዋል:: የአልጋ ቁራኛ ስለሆኑ ሄጄ እንዳስፈርማቸው እታዘዝና ውሉን አዘጋጅቼ ለማስፈረም ሄድኩ:: ሰውዬው በእርግጥም ታመዋል:: ገበናቸውን በጋቢያቸው ሸፍነው እንደምንም ከአልጋቸው ተነትተው

ወረዱ:: ልጄ፣ ተቸግሬ አስቸገርኳችሁ አይደል? አሉኝ:: በሀብት ሳይሆን በአልጋ መቆራኘታቸውን እናቱ አባቴን እሳቸው ቦታ አስቀመጥኩና ሰውዬው አንጀቴን በሉት:: ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ፊት ለፊት ያለው ቤተመንግሥት መሰል ሕንጻ የደጃዝማች አስፋው እንደነበረ እንሰማ ነበር እንጂ ሰውዬው ቀይ ይሁኑ ጥቁር ወፍራም ይሁኑ ቀጭን አላውቅም ነበርና ያን ዕለት እድል ገጥሞኝ ሳያቸው ደስ አለኝ:: ለካስ ቀኑ ሲደርስ የማይያዝ የለም ብዬም ተገረምኩ:: ማየትን፣ ማወቅን፣ መተዋወቅን፣ መነካካትን፣ አንድ ከባቢ አየር በጋራ መተንፈስን የመሰለ ነገር የለም መሰለኝ፣ ምስኪን የሀብታም ድሃ ብዬ አዘንኩላቸው:: ደጃዝማች ረጅሙ ፊርማቸውን በመጨረሻው ገጽ፣ አጭሩን ምልክታቸው በሌሎች አምስት ገጾች አሰፈሩ:: ውሉ የተዘጋጀው በስድስት ግልባጮች ስለነበርና ደጃዝማች ሲጽፉ በጣም ቀስ እያሉ ስለሆነ እሳቸውን የሚመለከተው የፊርማ ስነሥርዓት ረጅም ጊዜ ፈጀ:: ቢሆንም፣ ቅሬታ የነበረው አልነበረም:: ምክንያቱም፣ በጋራ መፈረም የነበረባቸው ባለቤታቸው እቤት ስላልነበሩ እስኪመለሱ ይጠበቁ ስለነበር ነው::

ወይዘሮ ሉሊት ቢፈለጉ ቢፈለጉ ይጠፋሉ:: እንደምንም ይገኙና ያንን ሰልካካ የሰጎን አንገታቸውን፣ ዳቪንቺ ሲቀርጸው የዋለ ያደረ የሚመስለውን ፊታቸውንና ልዩ ብርሃን የሚያንጸባርቀውን ገላቸው ይዘው ብቅ አሉ:: እውነቱን ለመናገር ያችን ዓይነት ቆንጆ ሴት ከዚያን በፊት፣ ምናልባትም በኋላም ዐይቼ አላውቅም፣ ከባለቤቱ በቀር ማለቴ ነው፣ ምኔ ሞኝ! ጸጉር ሠሪው፣ ጂኒ ጃንካው አስቆይቶኝ፣ በዚህ ወጥቶ፣ በዚህ ወርዶ አሉና የቆጡን የባጡን ቀበጣጠሩ:: እኔ የምጠረጥረው አንዱ አርቲስት ፊት ለፊት እስቀምጦ ዐይን ዐይናቸውን ወይም ሌላ አካላቸውን አገላብጦ ሲመረምር እንዳዋላቸው ነው::

ወይዘሮ ሉሊት በተዘጋጀላቸው ስፍራ ፊርማቸውንና ምልክታቸውን እንዲያስቀምጡ አሳየኋቸው:: ምንም እንኳ በእድሜ እናቴ ለመሆን ትንሽ የሚቀራቸው ቢመስልም ተጠጋግተን ጠረናቸውን ሳሸት የቆይታዬ ካሳ ነው

አልኩና ድምፅ አጥፍቼ ማግሁት። ሴትዮዋ ሁለት ኮፒዎች ሰርተው እንደጨረሱ ስክሪፕቶው ጣታቸውን የጨቆነበትን ቦታ ወደ ዐይናቸው አስጠግተው ያዩና አስቸጋሪውን መጻፊያ ጣል አድርገው፣ አላለቀም እንዴ? ይሉኛል። አራት ኮፒዎች ይቀራሉ ስላቸው፣ ይሄ ሁሉ ፊርማ ለዐሥራ አምስት ሺህ ብር ብቻ ነው? አሉኝና አረፉት።

ከመቅጽበት የማየው ተለውጦ፣ ፊቴ ተደቅና የታየችኝ ቆንጆ፣ ካፍዋ ማር የሚዘንብ፣ ጠረንዋ የሚያውድ ሴት ሳትሆን ስለክላካ የደሃ ጠላት፣ የጨቋኙ መደብ ተወካይ ነበር። ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን በወረቀት ላይ ምልክት አድርጎ ብዙ ሺህ ብር የማግኘት እድል ደጃፉ ሊያንኳኳ ይቅርና እድሜ ልኩን አፈር እየገፋ ላቡን ቢያንጠፈጥፍም ሰኞና ማክሰኞ አልገጣጠም እያሉት በቀን አንድ ጊዜ እንኳ ጠግቦ የሚበላው የሌለው መሆኑን እያወቅሁ ስክሪፕቶ ጣቴን ጎዳ ለምትል ቅንጡ ቅምጥል የብር አቅራቢ መሆኔ አንገበገበኝ። ለደጃዝማች የነበረኝ ሐዘኔታ በሴትዮዋ ድርጊት ተበረዘ፣ ተመረዘ። የኢትዮጵያ አብዮት ለምን ፈነዳ? ተብሎ ውይይት ሲከፈት ወይዘሮ ሉሊትን ከማስታወሻ ማኅደሬ ጎትቼ ሳላወጣ ቀርቼ አላውቅም።

በመጀመሪያ በአውሮፕላን የተጓዝኩት ከብድር ሥራ ጋር በተያያዘ ነው። አዋሽ ዳርቻ ጥጥ ያመርቱ የነበሩ የአለማያ ኮሌጅ ምሩቆች የብድር ጥያቄ አስገብተው ስለነበር እርሻቸውን እንይላቸው ተብሎ አምስት ሰው በምታስቀምጥ አውሮፕላን ከአቶ ደበበ ጋር አውሮፕላኑን ሞልተን ሄድን። አቶ ደበበ በአየር ስንዝ የመጀመሪያዬ መሆኑን ሲያውቁ አንተን መጀመሪያ ማሳፈር በትልቁ አውሮፕላን ነበር ይሉኛል። አይደለም ጌታዬ፣ በትንሽ ጀምሮ ከፍ እያሉ መሄድ ይሻላል ብያቸው ለረጅም ጊዜ ታደሰ እንዲህ አለ እያሉ ያሥቁብኝ ነበር።

ሌላ ጊዜ ደግሞ በ1962 ከአቶ ገብረመድህን ጋር አሳይታ ለጥጥ ለቀማ ብድር ለመስጠት ሄደናል። ብድሩ የሚሰጠው ሡልጣን አሊ ሚራህ ለፈቀዱላቸው ተበዳሪዎች ብቻ ነበር። በሄድንበት ወቅት ገንዘቡ በጣም

ይፈለግ ስለነበር ሥልጣኑ ዘብ አሰልፈው፣ መሣሪያ አስይዘው፣ ቆመው ነው የተቀበሉን:: እጃችንን ጨብጠዋል፤ መስተንግዶም ተደርጎልናል:: ብድሩ ከተሰጠ ከጥቂት ወራት በኋላ ገንዘቡ በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ለመከታተልና የመመለስ እድሉን ለመገምገም ከገብሬ ጋር እንደገና ሄድን:: የሱልጣኑ ዘብ አሁንም አለ፣ እንዲያውም ተጠናክሮ፤ ነገር ግን የሱልጣኑ እግሮች ከተቀመጡበት ፍንክች ሳይሉ ቀሩ:: ጉብ ብለው የተከመሩት ትልቁ ሰውዬ እጃቸውን ወደ ላይ ሲዘረጉት ገብሬ አፈፍ አድርጎ ያዘው:: እኔ ተከታይ ነበርኩና ገና እጄን ከመሰንዘሬ የሡልጣኑ እጅ በአስማት እንደተሰወረ ዓይነት ከመቅጽበት ታጥፎ ጉያቸው ሥር ሲገባ የተዘረጉት እጆቼ አየርና ጡር አፍሰው ተመለሱ:: ለጊዜው የኀፍረት ስሜት ነካኝ እንጂ አልበከለኝም:: ይልቁኑ በሰውዬው ከንቱነትና አዙሮ የማየት ችሎታቸው አነስተኛነት አዘንኩላቸው:: ትልቅ ነኝ የሚል ሰው ትንሽነቱ የሚጋለጠው ትንሽ ነው የሚለውን ሰው ፈልጎ ሲያገኝና ካንተ በላይ ነኝ ብሎ ሲያውጅ መሆኑን ወዲያው ተገነዘብኩ:: አምላኬንም፣ ትልቅ ሳይሆን ትልቅ ነኝ ከሚለው ጋር የመታገያ ኃይል፤ ከኔ በታች ለሆኑት ደግሞ ጋሻና ከለላ ሆኜ አክብሬ እንድጠብቃቸውና በማናቸውም ዓይነት መንገድ እንዳልጎዳቸው ልብና አእምሮ ስጠኝ፣ ስሳሳትም በጥበብህ መልሰኝ ብዬ ተማጸንኩት::

በ1967 አሊ ሚራህ አገር ጥለው ከፈረጠጡ በኋላ የብሔራዊ ባንክ ምክትል ኃላፊ ሆኜ አዲስ አበባ ባንክ በሰጠው ብድር ተመርቶ ያልተነሳ የጥጥ ክምር ለማየትና የሚነሳበትን መንገድ ለመፈለግ የአዲስ አበባ ባንክ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ከነበረው ከጥላሁን አባይና ከባንኩ የደሴ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ከሻምበል ሰይፉ ተሰማ ጋር አሳይታ ሄደናል:: ጊዜ እናድናለን ብለን ሲያቀብጠን በአጉል መንገድ በመሄዳችን መኪናችን አሸዋ በርሀ ውስጥ ተቀርቅሮ ቀልጠን ልንቀር ነበር:: ተስፋ ቆርጠን፣ ለላይኛው ቤት ሰውዬ፣ መጣን ተቀበለን ብለን ካማተብን በኋላ ሾፌራችን የነበረው ሻምበል ሰይፉ የመጨረሻ ሙከራ ላድርግ ብሎ ሲሞክር ተሽከርካሪው ቆፍሮ ከገባበት አሸዋ ተፈትልኮ ወጣ::

ብድር ክፍል ሆኜ መስፍን ሳህሌ አስተዳደርን ለቆ የሥላሴ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ነበር፡፡ እንደማናቸውም ቅርንጫፍ ዋናው መሥሪያ ቤት ውድቅ ስለሚያደርጋቸው የብድር ማመልከቻዎች እሱም ቅሬታዎች ነበሩት፡፡ አንድ ሰኞ ቀን በጠዋት ይደውልልኝና፣ ስማ ታደሰ፣ ባለፈው ዊኬንድ የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጆች ተገናኝተን አግባብ ያልሆኑ ጥያቄዎች እያነሳህ ስላስቸገርከን አንተን አቶ ደበበ ከቦታው እንዲያነሱልን እንድንጠይቅ ተስማምተናል ይለኛል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ግልጽና ቀጥተኛ አነጋገር ከዚህ በፊት በተለይም ከኢትዮጵያዊ ሰምቼ አላውቅ ስለነበር ቀልድ መሆን አለበት፣ እውነቱን ከሆነ ደግሞ ምን ዓይነቱ ጀዝባ ነው በቀጥታ ደውሎ የሚነግረኝ? ምን እንዳደርግስ ፈልጎ ነው? ብዬ ከት ብዬ ሣቅሁኝ፡፡ መስፍን የገመተው፣ ደንገጥ ብዬ፣ ምን አጥፍቼ ነው? ማሩኝ፣ አይለምደኝም እንድለው ነበር መሰለኝ፡፡ የቀጠርኩት እኔ ነኝና እኔ አምጸረጽረዋለሁ፣ ለኔ ተዉልኝ ብሏቸውም ይሆናል፡፡ እንዲህ አስቦ ከሆነ ታደሰ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ አያውቅም ማለት ነው አልኩኝ፡፡ ሲያጠብቁበት የሚጠብቅ መሆኑን እስከዚያን ወቅት አያውቅም ነበር፡፡

መስፍን ቁም ነገር ያለውን በሣቅ ሳፈርስበት ተገርሞ፣ ቀልዴን መሰለህ እንዴ? ሙት እውነቴን እኮ! ነው ይለኛል፡፡ ታዲያ መንገር ያለብህ ለእኔ ሳይሆን ለአቶ ደበበ ነው እለዋለሁ፡፡ ለትምህርት ወደ ውጭ እስክሄድ በቦታው ላይ ስለቆየሁ በስልክ ተወቅቶ በስብሰባ የተመረተውን አድማ በቀጭኑ ሽቦ እንዳቃጠልኩት ገመትኩ፡፡ ወይም አቶ ደበበ የቀረበላቸውን አቤቱታ ሳይቀበሉት ቀርተዋል ማለት ነው፡፡

የእንጀራ ገመዴ ቀጣይ መስፍን ባንድ ወቅት የሱን የማሳጥር ሆኜ ታየሁት፡፡ አንድ ሰው ነገ የት ይሆናል? ለሚለው ዛሬ መልስ ስለማይገኝለት ታማኝነት ለሥራ እንጂ ለሰዎች መሆን እንደሌለበት የመጀመሪያው ትምህርት የቀሰምኩት ገና ከጠዋቱ ነው፡፡ መስፍንና የሒሳብ ባልንጀሮቹ አስቸገርከን ሲሉኝ፣ እኔ በበኩሌ ሥራዬን በትክክል በመሥራቴ ቁጥጥር ጠሊታዎች አደሙብኝ አልኩ፡፡ እውነተኛው እውነት ያለው

በሁለቱ እውነቶች መካከል ሳይሆን አይቀርም። መስፍን ከባንክ ወጥቶ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ፣ እኔ የብሔራዊ ባንክ ኃላፊ ሆኜ ስንገናኝ ባንክ እንድገባ በር የከፈተልኝ እሱ መሆኑን ያስገነዝበኝ ነበር። እንደሱ ግልጽ የመሆን ችሎታ ስለሌለኝ ከብድር ክፍል ኃላፊነት እንድነሳ አሳድሞብኝ እንደነበር ግን አንስቼበት አላውቅም። መስፍንና እኔ ቀሪው እድሜያችን የተመደበው ስላለፈው እያነሳን በራሳችን ጭምር ለመሣቂያ ስለሆነ አገር ቤት ስመለስ ስለአድማው አውጣጣዋለሁ ብዬ አስቤአለሁ።

ብድር ክፍል ሆኜ አንድ ቀን አንድ ሰው ቢሮዬ ይገባል። ዐይኔን ማመን ያቅተዋል። አስማት መሆን አለበት አልኩና አሸሁት፣ በለጠጥኩት። ሰውዬው እየቀረበ ሲመጣ የልጅነት ጓደኛዬ የጸጋዬ ሃይለማርያም አምሳያ እንጂ እሱ ሊሆን አይችልም ብዬ ሕዋሳቶቼ የሚነግሩኝን፣ የሚያዩልኝን ካድኩ። ጸጋዬ ሥራ አጥቶ ለረጅም ጊዜ ከተንገላታ በኋላ በ1961 የሶቭየት መንግስት ስኮላርሺፕ ይሰጠዋል። እስከሚሄድ ቸኩሏል። ተሰናብቶን ሲሄድ “አውሮፕላኑ ልክ ሱዳን ድንበር እንደገባ ፊቴን ወደ ኋላ አዞርና እንጀራ በከለከለችኝ ኢትዮጵያ ላይ እንትፍ ብዬ እተፋባታለሁ” ብሎ የሄደውን ሰውዬ ነበር የማየው። ወይ ጉድ፣ የኢትዮጵያ አምላክ ማንነቱን ሊያሳየው ከሰማይ ወደ መሬት ጎትቶ አውርዶ መልሶ አመጣው? አልኩና ተገርምኩ። ጸጋዬ አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለምን እንደተመለሰ በውል የማውቀው ነገር የለም። ጓደኞችን ስዩም ቄሱ ሲናገር እንደሰማሁት ያ ነገር ሞልቶ ፈልቶ ባናቱ ሊወጣ ሲል አላስችል ስላለኝ ተመለስኩ እንዳለ ነው።

ከብድር ክፍል ወደ ኒውዮርክ ለትምህርት፣ ከዚያም ለሥልጠና ወደ እንግሊዝ አገር መሄዴን ገልጫለሁ። ከእንግሊዝ አገር በኅዳር 1965 ተመልሼ የባንኩ የፕላን ክፍል ኃላፊ ሆኜ ተመደብኩ። እቅድ ስለማውጣትና ማስፈጸም እንዲሁም ስለባንኩ የወደፊት የሥራ እቅዶች መጽሔት አዘጋጀሁና ለኅትመት አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ወስጄ ሰጠሁ። የነበረው ሐሳብ መጽሔቱን ለባንክ ሠራተኞች በሰፊው ለማሰራጨት ነበር። መጽሔቶቹን ተረክቤ ከማሰራጨቴ በፊት አንዴ ልውጣው ብዬ ሳነበው

ብዙ የፊደል ግድፈቶች አገኘሁበት:: ጥፋቱ የማተሚያ ቤቱ ሳይሆን የራሴ ነበር:: ስሕተቱ የተፈጸመው እኔው እራሴ ለኅትመት ፈርሜ የሰጠሁት ቅጂ ስሕተቶቹን ያዘለ ስለነበር ነው:: ከዚያ ልምድ ያገኘሁት የማይረሳ ትምህርት አንድ ሰው የራሱን ጽሑፍ አርሞ ከስሕተት የነጻ ማድረግ እንደማይችል ነው:: ሌላ ሰው ሊያይለት ይገባል::

ወዳጄንና ሐቀኛው ኃይሉ ሻውልን መጀመሪያ ያየሁት በመጽሔቱ ሳቢያ ነው:: መጽሔቱ ታርሞ ከተበተነ በኋላ አቶ ደበበ ባንኩን ሊያስተዋውቁበት ስለፈለጉና እግረመንገዳቸውን እኔንም ከቢዝነስ ኮምዩኒቲው ጋር ሊያስተዋውቁኝ ፈልገው የላየንስ ክለብ ወርሀዊ ስብሰባ ላይ ይዘውኝ ይሄዳሉ:: ስብሰባው የተደረገው ሒልተን ሆቴል ሲሆን የእለቱ ዋና ንግግር አድራጊ አቶ ኃይሉ ነበር:: በወቅቱ የሼል ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነበር:: ንግግሩን አደነቅሁ:: እንደሱ ዓይነት ችሎታና በራስ መተማመን ስላላቸው ኢትዮጵያውያን ብዙም አላውቅም ነበርና መድረኩን ወስዶ አስረግጦ ሲጫወትበት ሳይ ልቤን አሞቀው፤ ኮራሁበት:: ከዚያ በኋላ የተገናኘነው የመንግሥት ሹሞች ሆነን ነው:: በሥራ ላይ ሆኖ ዐይኑ ላይ አደጋ ይደርስበታል:: ሕክምና ሳያገኝ እንዲታወር የፈለጉ አንዳንድ ባለሥልጣኖች ግራና ቀኝ እንደኳስ ሲወራወሩት ዐይኔ ሕክምናው እንዳይተጓጎልበት ከረዱት ውስጥ አንዱ በመሆኔ ደስ ይለኛል:: ያንን አስከፊ እጣ የደገሱለት ሰዎች የጃቸውን እያገኙ ስለሆነ የሰው ፍርድ ቢዛባም ጠባቂያችን ሥራውን ምን ጊዜም እንደማይዘነጋ አምኛለሁ::

ሌላ በዚያን እለት ያየሁት የአቶ ደበበና የንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ የአቶ ተፈራ ደገፌን መሽነቋቆር ወይም መጎነታተል ነበር:: ይህ ድራማ የደርግ መንግሥት እስረኞች በነበሩበት የአምስት ዓመት ዘመንም እንደቀጠለ ያይን ምስክሮች ነግረውኛል:: አቶ ደበበ መጽሔቱን በምሳ ላይ ለተገኙት የላየንስ ክበብ አባላት በሙሉ እንዳድል አዘዙኝ:: እራሳቸው ተነስተው አራት ተጨማሪ ኮፒዎች ይዘው ይሄዱና ለአቶ ተፈራ ይህ በብዛት የሚያስፈልግ ላንተ ነው ብለው ይሰጧቸዋል:: አቶ ተፈራ

ሲመልሱ፣ እኔም እንደ ሌላው አንድ ይበቃኛል፤ የተረፈህ ከሆነ ቆሻሻ መጣያ ውስጥ ዱለው ይሏቸዋል። እኔም በልጅነት አቅሜ ለፍቼ የሕይወት እስትንፋስ የሰጠሁትና እንደ በኩር ልጄ የማየው መጽሔት ለቆሻሻ መጣያ ይዳረግ ተብሎ አፍ ሞልቶ ሲነገር ከፋኝ፤ ቆሽቴ በገነ። ዋናው ቅሬታዬ አንቋሻሺው አቶ ተፈራ ላይ ቢሆንም በልቤ አቶ ደበበንም ምነው ክቡሩን አጀንዳዎን በመንዜ ፌዝ አስረከሱት? ብዬ አዘንኩ።

የሁለቱን ተቀናቃኞች ልውውጥ የዚያን እለት የሰማና የግንኙነታቸውን ታሪክ ለማያውቅ ለዋዛ ፈዛዛ የተቀላለዱ ይመስል ነበር። ነገር ግን፣ በአዲስ አበባ ባንክና በንግድ ባንክ መካከል በነበረው ትግል ጎልማሳው ንግድ ባንክ ጨቅላውን አዲስ አበባ ባንክን ቢያመቸው ለመጨፍለቅ፣ ባይሆንለት ለማቁሰል አይመለስም ነበር። አዲስ አበባ ባንክ በ1956 ከተቋቋመ ጀምሮ ንግድ ባንክን ያስቸገሩ ተበዳሪዎች በብልጎት ወደ አዲስ አበባ ባንክ ተገፍተው ይጣሉ ነበር። ከንግድ ባንክ እንዳይሄዱ የሚፈለጉት ደንበኞች ደግሞ አዲስ አበባ ባንክ ፍላጎታችሁን የማስተናገድ አቅም ስለሌለውና ከሳሚ ድርጅት ስለሆነ ከኛው ጋር አርፋችሁ ብትቀመጡ ይሻላችኋል እየተባሉ ማስፈራሪያ በምክር እየተሸፈነ ይታደላቸው ነበር። አቶ ደበበ አቶ ተፈራን በሰው ፊት ሊጋተሩዋቸው የተዘጋጁ ቢመስልም፣ እውነቱ ግን እውነተኛ ፍልሚያ ቢነሳ የአንበሳና ቀበሮ ጦርነት ይሆን ስለነበር በማን አሸናፊነት እንደሚደመደም አጠያያቂ አልነበረም። በተጨማሪም ብሔራዊ ባንክ ለንግድ ባንክ ያደላል እያለ የአዲስ አበባ ባንክ ሠራተኛ ያማ ነበር።

ቢሆንም፣ አንዳንዴ ከባላጋራ አንሶ መገኘት የሚያስገኘው ጠቀሜታ ሊኖር ይችላል። ትንሹ በትልቁ ያላግባብ የሚታሽ ወይም የሚጠቃ ከሆነ ትንሹ የተበዳይነት አርማ ይዞ ለመነሳት እድል ያገኝና፣ ባግባብና በወቅቱ እስከተቀመጠበት ድረስ፣ ተቆርቋሪና ወዶገብ ጦረኛ የማብዣ ወይም ማባዣ መሣሪያ ሊያደርገው ይችላል። እውነቱን ለመናገር አዲስ አበባ ባንክ የተቀጠርን አንዳንድ የቢዝነስ ኮሌጅ ተማሪዎች በዚሁ መንፈስ ተመርተን ሳይሆን አይቀርም ባንኩን ለማገልገል የወሰንነው። የሁለተኛ ዓመት

ተማሪዎች ሆነን አቶ ደበበ ትምህርት ቤታችን ድረስ መጥተው ለኮሌጁ ተማሪዎች ንግግር አድርገውልናል:: ከተናገሩት መካከል፣ በትግሌ የግል ባንክ አቋቁሜአለሁ፤ ገና እየዳኸ ነው፡ ብቻዬን ነኝ፤ ረዳቴ ጥቂት ነው፤ ተጋፊዬ ብዙና ኃይለኛ ነው፤ ኢትዮጵያችን የኤኮኖሚ አርበኞችም ያስፈልጉዋታል፤ ትምህርታችሁን ስትጨርሱ መጥታችሁ ብትረዱኝ ደስ ይለኛል ብለውን ነበር:: መልዕክታቸው በብዙዎቻችን አእምሮ ውስጥ ሲጉላላ ነበር:: የባንኩ ፐርሶኔል ክፍል ኃላፊ መስፍን ሳህሌ የትርፍ ጊዜ ሠራተኞችን ለመመልመል በ1961 ኮሌጃችን ድረስ መጥቶ በነበረበት ወቅት፣ ከበደ፤ ታዬ፤ አስፋውና እኔ እድላችን አሁን ነው፣ ለምን ሄደን አቶ ደበበን አንረዳም? ተባብለን ነው በወዶ ዘማችነት ለመመልመል የበቃነው::

ፕላን ክፍል ሆኜ የመጀመሪያዋ ጸሓፊዬ አብረኸት ተወልደ ነበረች:: ለትምህርት ወደ አሜሪካ ለመሄድ በአስመራ አድርጌ ሳልፍ ተዋውቀናል:: ከቅርንጫፉ ሠራተኞች ሁሉ የወዳጅነት ስሜት ያሳየችኝ እሷ ነበረች:: ከለንደን ስመለስ አዲስ አበባ ተዛውራ እንደገና ተገናኘን:: የባንኩ አስተዳደር ጸሓፊዬ አድርጎ መደባት:: ስለሙህር ሰፈር ሕይወቴ ሳወራ ቀድሩ ብዛ ምኞቱ የሴቶች እረኛ ለመሆን እንደነበር ተርኬአለሁ:: ወይዘሮ አብረኸት በእርግጥ የሴቶች እረኛ ነበረች:: የከተማው ቆነጃጅት፣ በተለይም የአየር መንገድ አስተናጋጆችን በመዳፏ ሥር የምትቆጣጠራቸው ወይም በክንፏ ሥር አድርጋ የምትጠብቃቸው ይመስል ነበር:: ቢሮዬ የነሱ መናኸርያ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ይመጣሉ፣ ይንሾካሾካሉ፣ ይሄዳሉ፣ ይመጣሉ:: ለአብረኸት የቢሮ ሥራ ትርፍ ሳይመስላት አይቀርም:: ይባስ ብሎ የጸሓፊነት ሥራ አለመቻል ብቻ ሳይሆን ዝንባሌውም የላትም:: ሥራ ከተባለ ማዛጋት ነው፣ መንጠራራት ነው፣ ወረቀት እየቀደዱ ቅርጫት ውስጥ መጣል ነው፤ አንድ ሁለት ሰዓት የሚፈጅ ሥራ አውሎ ማሳደር ነው:: እኔ ደግሞ ሥራ ቶሎ ተሰረቶ እንዲያልቅና ከእጃችን እንዲወጣ ነው የምፈልገው:: በሥራዬ በጣም ቀናተኛ ነኝ:: አንድ ሰው በሥራዬ ከሚመጣብኝ እራሴ ላይ ጉብ ቢል እመርጣለሁ:: ስለሆነም፣ ወይዘሮ አብረኸትን፣ በይ፣ ሁሪ በሰላም አላታለሁ:: በጣም ተከፋለች:: ባለቤትዋ

ካፕቴን አበበ ወርዶፋም እንደዚሁ:: ከእንግሊዝ አገር እንደተመለስኩ፣ ገና እኔ ዘንድ ሳትመደብ፣ ቤታቸው ጋብዘውኛል:: ሂጂ ስላት ምግባችንን በልተህ እንዴት ይሆናል? እንደሆነም አላውቅም፣ ተቀየሙኝ:: ካፕቴኑ ባሰ:: ጸሓፊዬ ከሆነች በኋላ የቴሌቪዥን አንቴና አውሳኝ ነበር:: ስለማንጠቀምበት አግኝተህ ስትገዛ ትመልሳለህ ተብያለሁ:: በእርግጥም የሚሸጥ ፈልጌ አጥቼ ነበር:: አብረኸት ከፕላን ክፍል ስትወጣ የመጀመሪያው እርምጃቸው አንቴናቸውን ማስመለስ ነበር:: ቆይቶ ኑሯቸውን ናይሮቢ መስርተው በነበረበት ወቅት እቤታቸው ምሳ ጋብዘውኛል:: የድሮን ባዲስ ተካነው፣ ወይም የተተካ አስመሰልነው:: ድሮውንም ያከረረው ካፕቴን ይመስለኛል:: ስለ አብረኸት የቢሮ ሥራ ችሎታ የሚያውቁት መሥሪያ ቤትዋ፣ ታደሰና አብረኸት እንጂ ካፕቴን አልነበረምና ሊያመር አይገባውም ነበር:: የቤት ሚስትነት ሌላ፣ የቢሮ ሠራተኛነት ሌላ:: ማን ያውቃል? አብረኸት ባልዋን ሳትታዘበው ትቀር ይሆን?

የአብረኸት ተቃራኒ መሠረት ኃይሌ ነበረች:: መሠረት ብድር ክፍል እንደተመደብኩ ጓደኞችዋን እየጠራች በእድሜ ሕፃኑ በሥራ ሽማግሌ የሆነውን አለቃዬን ኑ እዩ ትል የነበረችዋ ናት:: የተዋጣላት፣ በጣም ፈጣን ጸሓፊ ስለነበረች ሰምና ወርቅ ሆንን:: ከወንድ ጓደኞችዋ ስትጣላ መካሪ ወይም አማካሪ ነኝ፣ አስታራቂ የሆንኩበት ጊዜ አይጠፋም:: እንደ ታናሽ እህቴ ነው የማያት:: ከቤተሰብዋ ጋር ተዋውቄ ቤተኛ ሆኛለሁ:: አንዴ ትታመምና ሆስፒታል ትገባለች:: ጓደኞችዋ ስለጤናዋ ሊጠይቋት ሲሄዱ የታደሰ የቢሮ ሥራ እንዴት ነው? ብላ ትጠይቃቸዋለች:: በሚፈልገው ፍጥነትና ጥራት አልሄድለት እያለ ሲበሳጭ እናያለን ይሉዋታል:: መሠረት ሐኪሞቹን ተሽሎኛልና አሰናብቱኝ ብላ ከሆስፒታል ትወጣለች፤ ሳታገግም ወደ ሥራ ገበታዋ ትመለሳለች:: ሳይውል ሳያድር እንደገና ታመመችና ወደ ሆስፒታል አልጋዋ ተመለሰች:: ለትምህርት ኒውዮርክ ስሄድ ባንኩን ለቅቃ አየር መንገድ ገባች:: እንደተመለስኩ ቢሮዬ ድረስ መጥታ፣ ተመልሼ ካንተ ጋር መሥራት እፈልጋለሁና ምን ታስባለህ? አለችኝ:: ደስታውን

አልችለውም ነበር፤ ነገር ግን ላንቺ የወደፊት እድል መቃናት አየር መንገድ ይሻልሻል ብያት ወደ ባንክ ሳትመለስ ቀረች።

ለንደን ሥልጠና ላይ ሆኜ በ1965 አጋማሽ የድርቁን ፊልም ዐይቼ ስለነበር አዲስ አበባ እንደገባሁ የተረዳሁት አብዛኛው ሰው ስለ መዐቱና እልቂቱ እንደማያውቅ ነበር። ማመን አቃተኝ። ከዚህ የበለጠ ሊታወቅ የሚገባው ምን ሊኖር ይችላል? አልኩና በጣም ተገረምኩ። አስከሬን አስቀምጦ መብላት ነውር በሆነበት አገር ብዙ ሺህ ሕዝብ እያለቀ የነበረው አስረሽ ምቺው ሙታንን አለመቅበር ብቻ ሳይሆን ሥጋውን እንደመብላት የሚቆጠር ነበር። የቦሎቄ ገንዘብና የአኗኗር ውድድር የብዙ ሰውን ኅሊና ሸርሽሮ ዐየሁ። ወሎ ሄጄ ማገልገል እፈልጋለሁና እዚያ የተሰለፉት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች የትኞቹ ናቸው? ስል የሰሙ የቅርብ ጓደኞቼ፣ ወሬ አናፋሽ፣ ችግር ፈጣሪ ተብለህ እራስህን ችግር ውስጥ ትከታለህና አርፈህ ተቀመጥ ብለው መከሩኝ።

መኖሪያዬ ግዮን ሆቴል መግቢያ ላይ ካለው የጄኔራል መኮንን ደነቀ ሕንጻ ላይ ነበር። እራቴን ብዙ ጊዜ መስቀል አደባባይ በሚገኘው ራንዴቩ እበላለሁ። አንድ ቀን ወደ ሬስቶራንቱ ስገባ አንድ ጠብደል ጎረምሳ ለማስካካት የከጀለች ዶሮ መስሎ ሁለት ክንዶቹን ወጣ አድርጎ ከደረጃው ይወርዳል። መሄጃውን ሁሉ አስፍቶ የግሉ አድርጎታል። ሁለት ጠረንገሎዎች ተከትለውታል። እንደምንም ብዬ ተሹለክልኬ ለማለፍ ስሞክር በዘረጋው ክንዱ ሆን ብሎ ይነካኝና ልትመታኝ ነው እንዴ? ይለኛል። የአብዬን ለእምዬ ማለት ይህ ነው አልኩኝ፣ በልቤ። ጠባቂዎቹ ሊተናኮሉኝ ፈለጉ። ምንም መልስ ሳልሰጥ፣ ዞር ብዬ ሳላይ ደረጃውን ወጣሁና የምቀምሰውን ቀምሼ ወደ መኖሪያዬ ተመልሼ ተከረቸምኩ።

በማግስቱ የልጅነት ጓደኛዬ ታከለ ደበላን አገኘውና ማታ የደረሰብኝን እነግረዋለሁ። ኦ እሱን አታውቀውም እንዴ? አቶ ያለኔማንአለ የጄኔራል አቢይ አበበ ልጅ ነው እኮ፤ የማኪያቶ ሒሳብ ዐሥራ አምስት ሳንቲም ለመክፈል መቶ ብር ኖት ጨምድዶ የቦይ ግምባር የሚተረክክ ጀግና ነው

ይለኛል:: በነገራችን ላይ፣ በ1970 የሚከራይ ቤት ስፈልግ ከጄኔራሉ ወራሾች የተወረሰ ቤት አሮጌው አየር ማረፊያ ተከራይቼ ሁለት ዓመት ኖሬአለሁ::

ያየሁት፣ የምሰማው ሁሉ አልጥምህ ይለኛል:: በመሥሪያ ቤትም ቢሆን መሐመድ ሽሪፍና ተባባሪዎቹ በተለመደው አሽሙራቸው ይሸነቁጡኛል::

የራንዴቡ ፍልሚያ አንድ ሳምንት ሳይሞላው ዓለም ባንክ ተወካይ ቢሮ ሄጄ ሥራ ይኖራቸው እንደሆነ ጠየቅሁ:: ላንተ የሚሆን ሥራ እዚህ የለንም፣ ግን፣ ዓለም ባንክና አይ ኤም ኤፍ በጋራ የሚያካሄዱት ያንግ ፕሮፌሽናልስ ፕሮግራም Young Professionals Program የሚባል አለ፤ ለሱ መወዳደር ከፈለግህ ዋሺንግተን የሚገኘው ዋናው መሥሪያ ቤት የማመልከቻውን ፎርም እንዲልክልህ ማድረግ እንችላለን ይሉኛል:: ፕሮግራሙ ለውድድር ክፍት የሚሆነው የትምህርት ደረጃቸው ከማስተር ዲግሪ ላላነሰና እድሜያቸው ደግሞ ሰላሳ ላልሞላ የኢኮኖሚክስ ወይም የንግድ አስተዳደር ትምህርት ላላቸው ነበር:: ለመወዳደር እንደምፈልግ ገለጽኩላቸው፣ ሂደቱ ተጀመረ:: ከዋሺንግተን የመጣ የባንክ ተወካይ ሒልተን ሆቴል ኢንተርቪው አደረገኝ፤ አለፍኩ:: ለመጨረሻው ውድድር ፓሪስ፣ ፈረንሳይ፣ ሄድኩ:: ለ75 ክፍት ቦታዎች ከአምስቱም አህጉራት 3250 ተወዳዳሪዎች ቀርበው ስለነበር፣ ከአፍሪቃ አህጉር ከኔ በፊት ለፕሮግራሙ ተመርጦ የገባው አንድ ጋናዊ ብቻ ስለነበር፣ በጥር 1967 መመረጤ በቴሌግራም ሲገለጽልኝ በሕይወቴ እንደዚያን ቀን ደስ ብሎኝ አያውቅም ብል ትንሽ ማጋነን ይሆናል እንጂ እምብዛም ከእውነት የራቀ አልነበረም:: ዋሺንግተን እኤአ በጁላይ 1975 መጀመሪያ ላይ ተገኝቼ ሥራ እንድጀምር ተነገረኝ:: የደመወዜ ልክና የአበሎች ዝርዝር ተገለጸልኝ::

ይህ ሁሉ ሲሆን አብሮ አደጌና ጓደኛዬ የደርጉ አባል አለማየሁ ኃይሌ ያያል:: ለኔ ሳይነግረኝ ለደርግ አባላት ከአገር እንዳይወጣ ከልክለን እዚሁ እናስቀረው፣ አገልግሎቱን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፈልጋል ይላቸዋል፤

ስምምነት ያገኛል፡፡ ከዋሺንግተን የቅጥር ማረጋገጫ በመጣልኝ ዐሥር ቀን ባልሞላው ጊዜ ውስጥ አንድ ቀን ደርግ ቢሮ ትፈለጋለህ ተብዬ ከሰዓት በኋላ አጼ ምኒልክ ግቢ እሄዳለሁ፡፡ ግቢውን መጀመሪያ የረገጥኩት የአንደኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ በንጉሡ ልዩ ካቢኔ ውስጥ በሒሳብ ሠራተኛነትና በገንዘብ ያዥነት የሚያገለግለውን የልብ ወዳጄን ወልደሥላሴ ወልደትንሣኤን ለመጠየቅ ስሄድ ነው በድጋሚ የረገጥኩት፡፡

ተጠሪዎች የተሰበሰብንበትን ስፍራ ከዚያ ቀደም ብሎ ያየሁት ስለመሆኑ ትዝ አለኝ፡፡ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ዓመት ሆኜ፣ ማለትም ከዘጠኝ ዓመት በፊት፣ ተማሪ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጋል፡፡ ጃንሆይ ጉዳይ ካላችሁ ለኔ መጥታችሁ መንገር ነው እንጂ በየአደባባዩ እየዞራችሁ ብትጮሁ ምን ትፈይዳላችሁ? ይሉና እንሄዳለን፡፡ ያኔ የተሰበሰብነው ዛሬ የተጠራሁበት ቢሮ ፊት ለፊት ነበር፡፡ ትናንት የጃንሆይ ቢሮ ነበር፤ ዛሬ የደርግ ነው፤ የነገውን ማን ያውቃል? አልኩኝ፡፡ ፍርቱና ሹም ሽር ስታደርግ ግዑዙ ሕንጻ ምን ይል ይሆን? ብዬም አሰብኩ፡፡

ጃንሆይ ከቢሮአቸው ወጥተው በረንዳ ሆነው የተፈጠረውን አስረዱኝ ይሉናል፡፡ የመጀመሪያ ዕድል የተሰጠው ለፖሊሱ አዛዥ ነበር፡፡ ሰውዬው ባቀረቡት ዘገባ ተማሪ የወረወረው ድንጋይ ከመብዛቱና መንገድ ላይ ከመቆለሉ የተነሳ ተሽከርካሪ መተላለፍ አልቻለም ይላሉ፡፡ ተማሪ ይህን ወፍራም ውሸት ሲሰማ ሁሉም የተመካከረ ይመስል በአንድ ላይ ሆ ሆ ሆ ብሎ ጩኸቱን አቀለጠው፡፡ እንደ አምላክ መታየት የሚፈልጉት ንጉሥ ተማሪ አፍንጫቸው ሥር ቁሞ ጆሮአቸው እስኪደፈን ሲጮህባቸው በጣም ይበሳጫሉ፡፡ ምነው? ምነው? ምነው? የሚያስተምሯችሁ ሆ ብቻ ነው? ይላሉ፡፡ ተማሪም እርስበርሱ እየተሸካሸከ ሀ ሁም እናውቃለን ብሎ ስለእውቀቱ መግለጫ የሰጠበት ስፍራ መሆኑ ትዝ አለኝ፡፡

በእንግዳ ማረፊያው በርከት ያሉ ሰዎች ተቀምጠዋል፡፡ አንዱንም አላውቅም፡፡ መጨረሻ የመጣው ታደሰ ወልደ ገብርኤል ነበር፡፡ ለምንድነው የተጠራሁት? ምንም የሠራሁት ወንጀል የለም እያለ ቀበጣጠረ፡፡ ቀልዱን

ይሁን የምሩን አላውቅም፡፡ እኛም ለምን እንደተጠራን አናውቅም፣ እንደኛው ተቀምጠኽ ብትጠባበቅ ይሻላል አልነው፡፡ ጥቂት ቆይቶ ወደ ሚቀጥለው አዳራሽ ግቡ ተባልን፡፡ መቶ አለቃ አለማየሁ ነበር የተቀበለን፡፡ የደርጉ የአስተዳደር ጉዳይ ኃላፊ መሆኑን ስለማውቅ የተጠራነው ለሥራ ምደባ እንደሆነ ገመትኩ፡፡ አሁንም ወደ ሚቀጥለው አዳራሽ እንድንገባ ተነገረን፡፡ ሦስቱ የደርግ የበላይ ሹሞች፣ ማለትም ተፈሪ በንቲ፣ መንግስቱ ኃይለማርያምና አጥናፉ አባተ ቆመው ተቀበሉን፡፡ አለማየሁ አጭር ንግግር አደረገ፡፡ የሥራ ምደባችንን ዘረዘረ፡፡ የኔ ምድብ የብሔራዊ ባንክ ምክትል አዛዥነት ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ታደሰ ወልደገብርኤል ዋና ኦዲተር ሆኖ ተሾመ፡፡ ምክትሉ ሆኖ የተሾመው ወዳጄ የሆነው በቀለ ታምራት ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ እንደሚጠብቅብን ተነገረን፤ አደራ ተባልን፡፡ እጃችንን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጭነን የሕዝብ አደራ ብንበላ አብዮቱ ቅርጥፍ አድርጎ ይብላን ብለን ማልን፡፡

ዋሺንግተን ሄጄ ወፍራም ደመወዝ እንዳልበላና የተንደላቀቀ ኑሮ እንዳልኖር እነአለማየሁ መንገድ ዘጉብኝ አላልኩም፡፡ በተቃራኒው፣ ሕዝብን ለማገልገል በመታመኔና እድል በማግኘቴ በጣም ደስ አለኝ፡፡ አብዮቱ የመጣው ፊውዳላዊ አሠራርን ለማስቀረት ነው ሲባል የትምባሆ ሞኖፖሉ ታደሰ ያዕቆብ፣ በሰፊው ሕዝብ ላይ የሚፏልሉትን ለማስወገድ ነው ሲባል የራንዴቩው ትዕቢተኛ ጠብደል፣ ለድሆች አለኝታ ለመሆን ነው ሲባል ወይዘሮ ሉሊት ትዝ አሉኝ፡፡ የአብዮቱ ዓላማ በጥቅሉ የተረገጠውን ሰፊ ሕዝብ ከወደቀበት ለማንሳት ነው ሲባል ከዚህ የበለጠ ምን ቅዱስ ሥራ ሊኖር ይችላል? አልኩኝ፡፡ ከሕፃንነት ጀምሮ ስንጋት ያደግነው ትምህርት መገልገያነቱ ለራስ ሳይሆን ለሕዝብ እንደሆነ ስለነበር ሁኔታዎች ተመቻችተው ቀርበዋል ብዬ አመንኩ፡፡ ኢትዮጵያ ትቅደም ያለምንም ደም ሲባል አትራፊው ሁሉም፣ ከሳሪው ማንም አልኩኝ፡፡ ፈረሱ ይኸው፣ ሜዳውም ይኸው ስትባል ታዴ ምን ትጠብቃለህ? በል ግባበት አልኩት፣ እራሴን፡፡ ወዲያውኑ አገሬ ስለምትፈልገኝ እዚሁ ቀርቻለሁ ብዬ ለዓለም ባንክ ቴሌግራም አስተላለፍኩ፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ብሔራዊ ባንክ

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ኃላፊ ሆኜ የካቲት 10፣ 1967 ስመደብ እድሜዬ 29 ነበር:: መጀመሪያ የተዋወቅሁትና ወስዶ ከባንኩ አዛዥ ከአቶ ተፈራ ደገፌ ጋር ያስተዋወቀኝ የደርጉ የለውጥ ሐዋርያ መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ ሲሆን አቶ ተፈራን መጀመሪያ ያየኋቸው ያዘጋጀሁትን ፕላኒንግ ማኑዋል ቅርጫት ውስጥ ይጣል ብለው ከአቶ ደበበ ጋር ሒልተን ሆቴል ከሁለት ዓመት በፊት ሲቆሳሰሉ ነበር::

የአስተዳደር መምሪያ የቅጥር ቅጽ እንድሞላ ያቀርብልኝና ሞልቼ እመልሳለሁ:: የትውልድ ዘመን በኢትዮጵያና በአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር እንዲሞላ ቅጹ ይጠይቃል:: የሞላሁትን ቅጽ ከመረመሩ በኋላ የሞላኸው የልደት ዘመን ልክ አይደለም ይሉኛል:: ከባለቤቱ ያወቀ መጣ፤ ጉድ ፈላ አልኩና ስሕተቱ ምን ላይ ነው? ጌቶቼ፣ እላለሁ:: የተወለድከው ህዳር 5፣ 1938 ከሆነ ቀኑ በአውሮጳውያን ዘመን አቆጣጠር ኖቬምበር 14 እንጂ ኖቬምበር 12 ሊሆን አይችልም ይሉኛል:: እንዴት አወቃችሁ? እላቸዋለሁ:: ከ1938 በፊት ጀምሮ የሁለቱንም ዘመን አቆጣጠር የሚያሳዩ መቁጠሪያዎች ወይም ሰንጠረዦች ስላሉን የአንዱን ወደሌላ ለመተርጎም ወይም ለማመሳከር በቀላሉ እንችላለን ይሉኛል:: አሠራራቸውን አደነቅሁ:: ለካስ ለረጅም ጊዜ ሳላወቅ ስዋሽ ከረሜአለሁ አልኩ:: ከአገር ውጭ ጭምር ያሉት ሬኮርዶች በኖቬምበር 12 ተወልዷል ስለሚሉ ለውጩው ውዥንብር ከሚፈጠር እንዳለ ብንተወው ይሻላል አልኳቸው:: ነገሩ በዚሁ ይዘጋ ወይም ትክክለኛውን ቀን ያስፍሩ አላስታውስም::

ለምክትል አዛዡ የተመደበውን ማርቼዲስ አውቶሞቢል እንድገለገልበት ይነገረኛል፡፡ ለአዛዡ የተመደበው ትልቁ ማርቼዲስ ቆሞ በአዲስ ሬኖ 16 በሾፌር ሲመላለሱ አየሁ፡፡ ባንኩ ያለው ትንሽ አውቶሞቢል አንድ የሽማኔ ጉድጓድ ብቻ እንደሆነና እሱም ለለውጥ ሐዋርያው እንደተመደበ ተገለጸልኝ፡፡ በወቅቱ በአገሪቱ በነበረው ጠቅላላ መንፈስና አስተሳሰብ በማርቼዲስ መንፈላሰስ እራስን ከአድኅሪው ጎራ ማሰለፍ ስለነበር ሌላ መኪና ይፈለግ አልኩ፡፡ ባንኩ ትንሽ አውቶሞቢል እስኪገዛ እንዳልታገስ የግሌ ተሽከርካሪ የለኝ፡፡ በታክሲ እንዳልመላለስ የባንኩን ክብር ላስነካ ነው ወይም ተስፈንጣሪ፣ የለየለት አስመሳይ ልባል ነው፡፡ ምርጫ ስለጠፋ በአሮጌ ላንድሮቨር በሾፌር እንድመላለስ ሁኔታው አስገደደ፡፡ ፔዦ 304 ታዘዘና ከውጭ እስኪመጣ ለሳምንታት በላንድሮቨር ተመላልሼ የሰፊው ሕዝብ አጋርነቴን አረጋገጥኩ!

መለስ ብዬ አንዳንድ ሁኔታዎችንና ድርጊቶችን በዐይነ ኅሊናዬ ስቃኝ ግልጽ የሆነልኝ የሰው አእምሮ የማመዛዘን ኃይሉ ለእምነት ማዕበል ምን ያህል ተገዥ እንደሆነ ነው፡፡ አጉል እምነትና ሃይማኖት እዚህ ውስጥ እንደሚካተቱ መካድ አይቻልም፡፡ እምነቶች፣ ድርጊቶች፣ ክስተቶች በራሳቸው መጥፎ ወይም ጥሩ ላይሆኑ ይችላሉ፣ ወሳኙ የሚያስከትሉት ውጤት ነው፡፡ በዚህ አንጻር መጠየቅ ያለበት፣ አንድ ነገር ለምን ተደረገ? ወይም እንዲህ ተብሎ ለምን ታመነ? ብቻ ሳይሆን እምነቱ ወይም ድርጊቱ ምን ውጤት አስከተለ? ነው፡፡ አጉል እምነትም ሆነ ሃይማኖት ለሰው ልጅ ደኅንነት፣ ብልጽግናና ሰላም ተገቢ አስተዋጽኦ እስካላቸው ድረስ መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ካልሆነ ግን መወገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ሁሉንም በሰማይ ቤት አገኘዋለሁ ወይም እፋረደዋለሁ ብሎ የተቀመጠውን ግን እምነትህ ያድንህ ብለን ከእሱ ጋር ክርክርም ሆነ ግብግብ መግጠም ዋጋ ቢስ ነው እላለሁ፡፡ የኛ ትኩረት ምድር ላይ ስላለው እንጂ የሰማዩንማ ምኑን አውቀነው እንዘባርቃለን?

የማርቼዲሶቹ በባንኩ ግቢ መታየት አብዮቱን እንዳያሰናክል ሰግተን ትልቁን በ4000 ብር ትንሹን ደግሞ በ9000 ጣልናቸው፡፡ ድርጊታችን አብዮቱን ከነበረበት ፈቀቅ አለማድረግ ብቻ ሳይሆን ይባስ ብሎ የሰፊውን ሕዝብ ንብረት ግለሰቦች እጅ እንዲገባ አስደረገ፡፡ ስለሆነም፣ ወደፊት ሌላ የመርማሪ ኮሚሽን ሲቋቋም ውሳኔውን ያሳለፍነውን ኃላፊዎች የሚያስጠይቀን ጉዳይ ነው!

ባንኩ በሄድኩ ማግስት ይመስለኛል በሳምንታዊው የፖሊሲ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንድገኝ ጥሪ ደረሰኝ፡፡ የኮሚቴው ሰብሳቢ ዋናው አዛዥ ሲሆን ሌሎቹ አባላት ምክትል አዛዡና የመምሪያ ኃላፊዎች ናቸው፡፡ በወቅቱ የነበሩት ኃላፊዎች የሚከተሉት ናቸው፣

| | |
|---|---|
| አቶ ከበደ ሰረቀብርሃን | ቁጥጥር መምሪያ |
| አቶ መስፍን በለጠ | የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር መምሪያ |
| አቶ አጥናፉ መንግሥቱ | የውጭ ባንኪንግ መምሪያ |
| አቶ መላኩ ኃይሉ | ሒሳብ ዋና ክፍል |
| አቶ በላይ ብናልፈው | የወጭ ገንዘብ ወይም ኢሹ ዋና ክፍል |
| አቶ ተሰማ ደምሴ | የገቢ ገንዘብ ዋና ክፍል |
| አቶ ምስክር ወልደ ትንሣኤ | አስተዳደር መምሪያ |
| ኦቶ በቀለ ገለቱ | ኤኮኖሚ ምርምር መምሪያ |

ባንኩ በየጊዜው የሚያጋጥሙትን አዳዲስ ፕሮብሌሞች እየሰበሰበ በጠረጴዛ ዙሪያ በተኮለኮሉ የባንኩ ኃላፊዎች በነጻና በግልጽ ውይይት የሚፈታበት መድረክ እንዳለው ስረዳ መገረም ብቻ ሳይሆን በጣም ተደሰትኩ፡፡ እውነቱን

ለመናገር ስለባንኩ የነበረኝ አስተያየት፣ ትምህርት የሌላቸው ሰዎች የተሰባሰቡበትና ዘመናዊነት ሲያልፍ ያልነካው ድርጅት እንደሆነ ነበር። ለዚህ አስተያየት ዋናው መሠረት የባንኩ ሠራተኞች የትምህርት ደረጃቸው መለስተኛ ስለመሆኑ የባንክ ኢንዱስትሪ ሠራተኞች እያነሱ ባንኩን የሚያጥላሉበት ነጥብ ነበር። ብዙዎች ኃላፊዎች ሁለተኛ ደረጃ እንኳ ያልጨረሱ ናቸው ይባል ነበር። ሁለተኛ፣ አዲስ አበባ ባንክ ሆኜ በባንኮች የቁጠባ ገንዘብ እንዲበራከትና ብሎም የአገሪቱ ኤኮኖሚ እንዲያድግ ለማገዝ የአገሩ ማእከላዊ ባንክ፣ ማለትም ብሔራዊ ባንክ፣ ፖሊሲ ሊቀይስ ይገባዋል ብዬ በኢትዮጵያን ሄራልድ ለሰጠሁት አስተያየት በባንኩ ስም የተሰጠው ምላሽ፣ የቁጠባ ገንዘብ ማበራከት ኃላፊነቱ የብሔራዊ ባንክ ሳይሆን የንግድ ባንኮች ነው የሚል ስለነበር ባንኩ ለምን እንደተቋቋመ በኃላፊነት የተመደቡት ሰዎች በውል አልተረዱም ብዬ ደምድሜ ስለነበር ነው።

ባንኩ ተግባራዊ የፖሊሲ ኮሚቴ ካለው፣

በልዩ ልዩ ጉዳዮች በግልጽ ተወያይቶ ካመርቂ ግብ ላይ በወቅቱ መድረስ ስለሚቻል፣

ወቅታዊ ፕሮብሌሞች በጥሞና ስለሚተነተኑና በመፍትሔነት የቀረቡት ሐሳቦች በወደፊት ውጤት ወይም አሠራር ላይ የሚያስከትሉት ተጽእኖ ከወዲሁ ለማየት ወይም መዳሰስ ስለሚቻል፣

ከአንድ ራስ ሁለት ይሻላል በሚለው መርህ መሠረት አንድን ፕሮብሌም ለመፍታት ካሉት የመፍትሔ አማራጮች የተሻለውን ለማግኘት ስለሚቻል፣

መምሪያ ኃላፊዎችን በወሳኝ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ በሥራቸው ላይ እንዲተጉና ንቁ እንዲሆኑ ስለሚገፋፋቸው እንዲሁም ያላቸውን የኃላፊነት ስሜትና እያንዳንዳቸው ስለራሳቸው ያላቸውን ግምት በይበልጥ ከፍ ስለሚያደርገው፣

በጋራ መሥራት በመሰለኝ ወይም በጀብደኝነት መዳከርን ስለሚያስቀር፣

የተሳሳተ ውሳኔን ለማለፍ ያለው እድል ስለሚጣበብ፣

በባንኩ ኀላፊዎች መካከል ያለውን የሙያ አንድነት ስሜት ስለሚያዳብር፣

ባንኩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በይበልጥ ሊረዱ የሚችሉትን የሥራ ኃላፊዎች ለይቶ ለማወቅ ስለሚያስችል፣

ከባድ ወይም ውስብስብ ፕሮብሌሞች እንዳይሸፋፈኑና ብሎም እንዳያመረቅዙ በወቅቱ ስለሚታዩ፣

የባንኩ የበላይ ኀላፊ የሥራ ጓደኞቹ የሰጡትን አማራጭ የውሳኔ ሐሳቦች አመዛዝኖ ወቅታዊ ውሳኔ ለማድረግ ስለሚያደፋፈር የተቀየሰው ዘይቤ የእሺ ነገ በሽታ መከላከያ ሆኖ ስለሚያገለግል፣

ባንኩ የሚያደርጋቸው ውሳኔዎች አመርቂ፣ ወቅታዊና ከስሕተት የጸዱ ከሆኑ ሕዝብ፣ መንግሥትና ሠራተኛው በባንኩ ላይ የሚኖራቸው አመኔታ ከፍ ስለሚል፣

የባንኩ ተደማጭነት፣ ክብርና ሞገስ ስለሚያድግ፣

መንግሥት ውጤታማ የኤኮኖሚ ፖሊሲዎች እንዲቀይስ ባንኩ የሚያበረክታቸው ምክሮችና የሚሰነዝራቸው አስተያየቶች ዋጋ ስለሚሰጣቸው፣

ባንኩ ባንኮችን ለመምራት፣ ለመቆጣጠር፣ ለማስተካከል፣ ሲያስፈልግም ለመገሰጽ ያለው ኃይል ስለሚዳብር፣

ሕዝቡ በባንኮች ላይ ያለው አመኔታ ከፍ ስለሚል፣

ሕዝብ የቆጠበውን ገንዘብ ባንክ ወስዶ ለማስቀመጥ ስለሚደፋፈር፣

መንግሥት አስተዋጽኦ ላደርግ እምችልበት ቦታ እንደመደበኝ ተረዳሁ። እውቀቴንና ጉልበቴን ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ለማዋል ተዘጋጀሁ።

ኮለምቢያ ዩኒቨርስቲ ሆኜ ከትምህርት ዓይነቶች ሁሉ በጣም ወድጄው የነበረው ስለ ማዕከላዊ ባንክ የወሰድኩት ኮርስ ነበር። ትምህርቴን ለመጨረስ ስቃረብ የኮርሱ አስተማሪ ፕሮፌሰር ፖንትኮርቮ አንድ ቀን ቢሮው ጠርቶ ለዶክትሬት መቀጠል ከፈለግሁ እሱ እንደሚረዳኝ ነግሮኝ ትምህርቴን እንድቀጥል ሐሳብ አቅርቦልኝ ነበር። እኔ ግን ወደ አገር ለመመለስ ጓጉቼ ስለነበር፣ አገሬ ሄጄ ሠርቼ እመለሳለሁ አልኩት። አሁን ብሔራዊ ባንክ እንድሠራ ስመደብ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ ጎትቶ እንዳመጣኝ ሳላየው አልቀረሁም።

በፖሊሲ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ ተገኘሁ። የደርጉ የለውጥ ሐዋርያ፣ መቶ አለቃ ፈቃደ፣ ድምፅ አይኑረው እንጂ በስብሰባው ላይ ተገኝቶ በውይይቱ ላይ እንደሚሳተፍ ዐየሁ። በቀኑ አጀንዳ ተይዞላቸው ውይይት የተደረገባቸው ጉዳዮች ፖሊሲ ነክ ሳይሆኑ ጥቃቅን አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንደሆኑ ተመለከትኩ። ለምሳሌ፣ የጥበቃ ጓድ የጠየቀው የደመወዝ ቅድሚያ ክፍያ ይገኝበት ነበር። በሚቀጥለውም ስብሰባ ሁኔታው ተመሳሳይ መሆኑን ዐየሁ። ያለፉትን ስብሰባዎች አጀንዳ አገላብጬ መረመርኩ። የተለየ ነገር ሳላይ ቀረሁ። የፖሊሲ ኮሚቴው የሚያስተናግደው የፖሊሲ ጉዳዮችን አይደለም ብዬ ደመደምኩ።

ባንኩ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ በርከት ያሉ የፖሊሲ ጉዳዮችን መመርመር እንዳለበትና የፖሊሲ ኮሚቴ በተራ አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን የባንኩን ተደማጭነትና ውጤታማነት ከፍ በሚያደርጉ ከፍተኛ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ስላለበት ይህን ለማድረግ ከፍተኛ ሥራ እንደሚጠብቀኝ ተገነዘብኩ።

እላይ የተገለጸውን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግና ሠራተኛውን በሚመለከቱት ጉዳዮች ላይ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖረው ታስቦ የሠራተኛው ተወካዮች በአባልነት የሚሳተፉበት የአስተዳደር ኮሚቴ እንዲቋቋም ያቀረብኩት ሐሳብ ተቀባይነት አገኘና በሥራ ተተረጎመ:: አሠራሩ በሌሎቹም ባንኮች ተግባራዊ እንዲሆን አመራር ሰጠን:: በተግባርም ተተረጎመ:: የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ሠራተኞች ማኅበር ግን በተሰጠው ዕድል መካፈል አልፈለገም:: ይተዉት አልንና ተውናቸው:: ከጥቂት ወራት በኋላ የልማት ባንኩ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅና የቅርብ ወዳጄ በቀለ ወርቁ ቢሮዬ ይመጣና የኛ ሠራተኞች በአስተዳደር ኮሚቴው አንሳተፍም ብለው ለጻፉት ደብዳቤ መልስ ባለማግኘ ታቸው ብሔራዊ ባንክ ስለኛ ግድ የለውም ብለው ቅር ተሰኝተዋል ይለኛል:: አልገባኝም፣ ምን ማለት ነው? እለዋለሁ:: እርሱም ብሔራዊ ባንክ ዝም ማለት ሳይሆን መድረክ ሰጥቶ እንዲያነጋግራቸው ፈልገው ነበር ይለኛል:: እኔም የተሰጣቸውን መብት አንጠቀምበትም ካሉ ምን ልምምጥ ያስፈልጋል? ብዙ ሥራ ስላለብን እንደነዚህ ዓይነቶቹን ለማስታመም ጊዜ የለንም ያልኩት ይመስለኛል:: ለማናቸውም፣ የማኅበሩን ሊቀመንበር አበበ ሙሉነህን ያነጋገርኩት ይመስለኛል::

ውሎ አድሮ የተገነዘብኩት አንዳንድ ሰው ለመታወቅና ሥልጣን ላይ ለመንጠላጠል ካለው ፍላጎት የተነሳ አስቸጋሪና እምቢተኛ መሆንን ዓይነተኛ ዘይቤ አድርጎ ይይዘዋል:: የዚህ ባሕላዊ መሠረቱ አሻፈረኝ ማለትና መሸፈት የጉብዝና መለኪያዎች ተደርገው ስለሚወሰዱ ሳይሆን አይቀርም:: ለዚህም ይሆናል ሳናውቀው አምባገነን እንዲገዛን መንገድ የምንከፍትለት:: የዚህ ዓይነቱ ፈንቃይ ስልጣን ላይ ከወጣ በኋላ በተራው ጊዜ ላነሳው ሽፍታና ተጋፊ ቦታ እንዲለቅ ይገደዳል:: ስለሆነም፣ ባገራችን የልማት መሠረት ለመጣል ያልተቻለው አንድም በመገለባበጥ በሽታ በመለከፋችን መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል:: በሽታው ከሥሩ ተመንግሎ የሚወገደው ለሰው ሳይሆን ለሕግ ተገዢ ለመሆን ስንመርጥና ተግባራዊ ያደረግነው ዕለት ብቻ ነው::

በልማት ወደፊት በገፋው ዓለም መብትና ግዴታ በሕግ ስለሚደነገግ ሁሉም ለድርጊቱ ተጠያቂ መሆኑን ያውቃል፤ መብቱን ያስከብራል፤ የሰውን መብት አይደፍርም፣ የደፈረ እንደሆነ እንደሚቀጣ ያውቃል፤ በሕግ የተደነገገውን ተላልፎ ቢገኝ ቅጣት እንደሚጠብቀው ያውቃል፤ የፈረመውን ውል ቢያፈርስ ተከሶ ካሳ ጭምር እንደሚከፍል ያውቃል። በጥቅሉ አንድ ግለሰብ ለሕግ ተገዢ ካልሆነ የሚጠብቀው ቅጣትና ስቃይ ነው። አንዳንዱ የዋህ ነጻው ዓለም ሲባል ሰው እንዳሻው የሚቧርቅበት ስፍራ ይመስለዋል። በተቃራኒው ማናቸውም የሰው ሕይወትና እንቅስቃሴ በሕግ የታሰረ ስለሆነ ሁሉም ሰው የሚያስኬደውን፣ የተከለከለውን ለይቶ አውቆ ሳይረግጥ ሳይረገጥ በጥንቃቄ የሚራመድበት ዓለም ነው። አቶ እንደልቡና አቶ እንዳሻው እዚህ ቦታ የላቸውም። ለሕግ አልገዛም ያለው ሁሉ እድሉ ወኅኒ ቤት ወይም የገንዘብ ቅጣት ነው።

የምዕራቡ አለም ሥልጣኔ ምስጢሩ ሕግ ከሰው በላይ መሆኑና መከበሩ ነው። የሁሉም እሩጫ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ሕይወቱን መምራትና ማስተካከል ነው። ነገ አንዱ ተነስቶ በማንአለብኝነት ሕልሙንና ተስፋውን አያጨልምበትም። የረጅም ጊዜ እቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ ይችላል። ልማት የሚካሄደው የዚህ ዓይነት አሠራር በሰፈነበትና በሰከነበት አካባቢ ነው።

እኛም አስተማማኝ የልማት መሠረት ለመጣል እንድንችል ሕግ አክባሪነትን መማር ይኖርብናል። ይህም ሲባል ኢሰብአዊና ጸረልማት ሕግጋት አይሻሻሉ ማለት እንዳልሆነ ማንም የሚገነዘበው ጉዳይ ስለሆነ ብዙ ማብራሪያ አያስፈልገውም።

ብዙ አገሮች የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የገቢ ታክስ ለተወሰነ ዘመን አያስከፍሉም፤ በገቢ እቃ ላይ የሚያስከፍሉትን ቀረጥ እስከማስቀረት ይደርሳሉ፤ ኢንቬስተሩ ያተረፈውን ገንዘብ በቀላሉ እንዲያስወጣ ይፈቅዳሉ፣ ወዘተ። ነገር ግን ያገራቸው ሰው ባገሩ ሕግና ባለሥልጣኖች አሠራር

ወይም አመራር ተማምኖ የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ እንዲመቻች በቂ ትኩረት አይሰጡትም:: ስለሆነም፣ ያገሩ ባለሀብት እንደእንጀራ ልጅ ከውጭ የመጣው ደግሞ እንደ ወለዱት ልጅ የሚታይበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ነጻነቴን አላስደፍርም ለሚል ማናቸውም አገር እንደዚህ ዓይነቱ ክስተት ውስጥ እራሱን መዝፈቁ አሳፋሪ ብቻ ሳይሆን ክብረነክም ነው::

የብሔራዊ ባንክ ኀላፊ በነበርኩበት ወቅት መንግሥት የውጭ ባለሀብቶችን ለመሳብ ፖሊሲ ያወጣል:: ስለወጣው ፖሊሲ ለንደንና ኒውዮርክ የሚገኙ አንዳንድ ባንኮች አስተያየታቸውን ጠየቅኋቸው:: የሰጡት መልስ፣ የራሳችሁን ባለሀብት እየወረሳችሁት የውጭ ባለሀብት እንዲገባ መጋበዛችሁ አጠያያቂ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለግል ሀብት ክምችት ያላችሁ ልባዊ ጥላቻ ስለሚታወቅ የውጭ ኢንቬስተር እንዴት አምኖአችሁ ሊመጣ ይችላል? የሚል ነበር::

አሁን በተደረሰበት ደረጃ ደግሞ፣ አንድ የውጭ ኢንቬስተር ሕግ በየስርቻው ወደሚጣስበት፣ የሕግ አፈጻጸም ወደሚቸረቸርበት፣ የኮንትራት ውል ማስፈጸም ወደማይቻልበት፣ ሕግ አስከባሪው ሕግ ወደሚጥስበት፣ ሕግ አስፈጻሚው እጅ መንሻ ወደሚጠይቅበት፣ ባጠቃላይ ሕግና አፈጻጸሙ ወደተለያዩበት አገር መሄድ አይፈልግም:: አንድ ባለሀብት ዋና ፍላጎቱ ሥራ ሠርቶ ወይም ገንዘቡን አሠርቶ ትርፍ ማግኘት እንጂ ናላው እስኪዞር በየቢሮው መሽከርከር፣ ገንዘቡና ጊዜው ዐይኑ እያየ መቀመቅ ሲወርዱ ማየት አይደለም:: ካፒታል ፈላጊዋ ብዙ ስለሆነ ካፒታሊስቱ በሰላም ሰርቶ የሚያተርፍበትን ስፍራ አሽትቶ ይሄዳል እንጂ ንቅዘት ውስጥ ሊንፈራፈር አይመጣም:: ሕግን አክብረው የሚያስከብሩ ባለሥልጣኖች ወዳሉበት አገር ይሄዳል:: ካፒታሊስቱ የጋበዘውን አገር እንዳይጎዳ መከላከልና በውል መደራደር ያገሩ ባለሥልጣኖች ኀላፊነት ነው:: ኢንቬስተር የመሳቢያ ዘይቤ ተጠቅሞ የራሱን ጥቅም በማስቀደም አገሩን የሚያስበዘብዝ ባለሥልጣን ለማጋለጥ ሁሉም ነቅቶ መጠበቅ ይኖርበታል::

ብሔራዊ ባንክ እንደሄድኩ ለመጀመሪያው ሁለት ወይም ሦስት ወራት ያተኮርኩት ስለባንኩ አሠራርና ሠራተኞች ማንነት ማጥናቱ ላይ ስለነበር ዋናው ሥራዬ ወረቀትና ፋይሎች ማገላበጥ ነበር:: ብዙ ሠራተኞች እየመጡ የሚወዱት እንዲሾም፣ የሚጠሉት እንዲባረር፣ የሆነውን ያልሆነውን ተቆርቋሪ መስለው ይነግሩኝ ነበር:: ጠቃሚ ጥቆማዎችም ላገኝ ችያለሁ:: አንድ ቀን አንዱ ቢሮዬ ድረስ ይመጣና ሠራተኛው ስላንተ የሚለውን ልንገርህ ይለኛል:: እህ፣ እለዋለሁ:: የተሾመው ባንኩን እንዲገለባብጥ ሆኖ ሳለ ወፍራም ደመወዝ ካገኘ በኋላ ሁሉንም ነገር ችላ ብሎ፣ በሩን ዘግቶ ተቀምጧል ብለው ያሙሐል ብሎ ነገረኝ:: አመሰግናለሁ ብዬ አሰናበትኩት:: ሌላ ጊዜ ደግሞ ጌታሁን አብቻለ ይመጣና እገሌ እንዲህ ብሎ አማሐ ይለኛል:: አመሰግናለሁ ብዬው ከቢሮዬ ከመውጣቱ የአስተዳደር ሰዎችን እጠራና ከነበረበት ቦታ ዝቅ አድርገው እንዲመድቡት አደርጋለሁ:: ለራሱ ብዬ ሄጄ አንድ የሚታማበትን ነገር ብነግረው ወስዶ ወረወረኝ ብሎ መናገሩን ሠራተኞች ሰሙ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ባንኩ ውስጥ ወሬ ማቀባበል፣ በወሬ መነገድ፣ አሉባልታ መንዛት፣ በሥራ ውጤት ሳይሆን ወሬ በማናፈስ ለማደግ መሞከር ቀርቶ ነበር ለማለት እችላለሁ:: ብሔራዊ ባንክ የሰከነ፣ ሠራተኛው ሥራውን የሚያከብርበት፣ በሥራው የሚኮራበት ድርጅት እንደነበር አፌን ሞልቼ መናገር እችላለሁ:: አሁንም ሁኔታው ከዚህ የተለየ እንዳልሆነ ተስፋ አደርጋለሁ::

የባንኩ ኃላፊዎች ጠንቃቃ፣ ትጉህ፣ ጨዋ፣ በባንክ ሠራተኛነታቸው የሚኮሩ ሆነው አገኘኋቸው:: ያገኙትን ወይም የተረከቡትን የሥራ ኃላፊነት አክብረው የመያዝና እንዳይበላሽ የመጠበቅና የማስጠበቅ ችሎታቸው ከፍተኛ ሆኖ አገኘሁት:: ነገር ግን አዳዲስ ሐሳብ ለማፍለቅም ሆነ የተሻሻለ የአሠራር ዘዴ ለመተለም ችሎታውም ሆነ ዝንባሌው እንደሌላቸው ተገነዘብኩ:: ስለሆነም፣ ብዙ ሥራ እንደሚጠብቀኝ ተረዳሁ::

የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ያላግባብ ተሰጥቶአል የሚል ጥቆማ ለባንክ ባለሥልጣኖች ደርሶ ኖሮ ጉዳዩ እንዲጣራ ብሔራዊ ባንክ ከመምጣቴ በፊት

ይወሰናል:: እንደመጣሁ የኮሚቴው ሰብሳቢ ሁን ተባልኩ:: ሥራ እንደጀመርን ከኮሚቴው አባላት አንዱ፤ ሳሙኤል አስራት፣ የውጭ ባንኮች መምሪያ ምክትል ኀላፊ፣ ይህ የፖሊስ ሥራ ነው፤ እኛ ፖሊሶች አይደለንም፤ ማጣራት አይገባንም ይላል:: እንደሱ አቀራረብ ከሆነ በባንኩ ውስጥ ተፈጸሙ የተባሉትን ስሕተቶች ወይም ጥፋቶች ለመመርመርና አጥፊውን ለመቅጣት ባንኩ መብት የለውም እንደማለት ነበር:: ፖሊስ እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ለማጣራት ዝግጅቱም ሆነ ችሎታው ስለሌለው አስተያየቱ አቅጣጫ የሚያስትና የሚያዘናጋ ስለነበር ሳልቀበለው ቀረሁ:: ሳሙኤልንም ለረጅም ጊዜ የጎሪጥ ሳየው ኖርኩና ወደኋላ ማንነቱን ጠጋ ብዬ ስረዳ የነበረኝ አስተያየት ተለውጦ ነበር:: ወንደላጤ ነበርና ለምን አታገባም? እያልኩ እጨቀጭቀው ነበርና አንድ ቀን አምርሮ፣ ጊዜው አልፎብኛልና ተወኝ፤ ከአሁን በኋላ ደፍሬ አልገባበትም አለኝ:: ከዚያን ቀን ጀምሮ ጭቅጭቁን አነሳሁለት:: ሳሙኤል በመዝገብ የሰፈረው እድሜውና አቋሙ አልገናኝ ይሉኛል:: ሳሙኤል መልኩ ገና ጥሬ ሆኖ እድሜው ግን የሽማግሌ ነበርና፤ ነገሩ ምንድነው? አልኩት:: ባንክ ስገባ እድሜዬ አስራ ስድስት ነበር፤ ነገር ግን የመቀጠርያ አነስተኛው እድሜ አስራ ስምንት ስለነበር ዋሽቼ ገባሁ አለኝ:: የሱ እድሜ ታሪክ ተቃራኒው ደግሞ የገንዘብ መረጣ ክፍል ኃላፊ የነበሩት የአቶ ባርናባስ ነው:: ሰውዬው ከማርጀት አልፈው ወደ መጃጀቱ ላይ ናቸው:: ግን መዝገቡ ጡረታ ለመውጣት ረጅም ጊዜ ይቀራቸዋል ይላል:: አሁንም ይህ ነገር እንዴት ነው? እላለሁ:: ሌላ መሥሪያ ቤት ይሠሩ የነበሩ ታናሽ ወንድማቸው የጡረታ እድሜአቸው ሞልቶ ከሥራ ከተሰናበቱ ዓመታት አልፈዋል ብለው ውስጠ ምስጢሩን ነገሩኝ::

ብሔራዊ ባንክ ሥራ እንደጀመርኩ ሰሞን ካጋጠሙኝ ሁሉ የማልረሳውና ትልቅ ትምህርት የሰጠኝ የበታች ሠራተኞች ያቀረቡት አቤቱታ ነው:: ሠራተኞቹ በደል ደርሶብናልና ታደሰን ማነጋገር እንፈልጋለን ብለው ግልብጥ ብለው ቢሮዬ ድረስ ይመጣሉ:: ወቅቱ ባለሥልጣን ይውረድ፣ ይሰቀል የሚባልበት ስለነበር ገና ከመምጣቴ በአስተዳደር ነክ ጉዳዮች

መወጠሬ ባያስደስተኝም ቅሬታቸውን ማስተናገድ ኃላፊነት ስላለብኝ ይግቡ እላለሁ። ቁጥራቸው በጣም በርካታ ስለነበር ተወካዮች እንዲመርጡና ያላቸውን ቅሬታ እነሱ ያቅርቡልኝ እላቸዋለሁ። ይስማማሉ። በተወካዮቻቸው በኩል የቀረቡት ቅሬታዎች ከሃያ በላይ እንደነበሩ አስታውሳለሁ። ጉዳዮቹን ለማጣራት ጊዜ ስጡኝ፤ ፋይል መርምሬ፣ የአስተዳደር ሰዎች የሚሉኝን ሰምቼ አስተያየቴን አሳውቃችኋለሁ እላቸዋለሁ። የአስተዳደር መምሪያ መረጃ አቀረበልኝ፤ ማብራሪያ ሰጡኝ።

አቤቱታዎቹን ሳጣራ የባንኩ አሠራር በመሠረቱ በሐቅ የተመሠረተ፣ ውሳኔዎች ሕግና ደንብ ተከትለው እንደሚደረጉ፣ ትጉህ ሠራተኛ እንደሚሾም እንደሚሸለም፣ ደካማ ሠራተኛም የጁን እንደሚያገኝ፣ ፍርደገምድልነት ቦታ እንደሌለው እግረመንገዴን ተገነዘብኩ። በመሆኑም፣ የሠራተኞቹን ትብብር አግኝቶ፣ ለላቀ ዓላማ እስካሰለፋቸው ባንኩ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ግባቸውን እንዲመቱ ለማድረግ የተመቻቸ ሁኔታ እንዳለ ተገነዘብኩና ደስ አለኝ።

በሠራተኞቹ ከቀረቡት አቤቱታዎች ሦስት ወይም አራት ብቻ ሊታዩላቸው የሚችሉ ሆነው አገኘሁ። የተቀሩት ካለመነጋገር ወይም ካለመረዳት የመነጨ ናቸው ብዬ ደመደምኩ።

የአቤቱታ አቅራቢዎቹ ተወካዮች ካንድ ወይም ሁለት ሳምንት በኋላ ቢሮዬ ተመልሰው ይመጡና ላነሷቸው ጥያቄዎች መልሶቹን አንድ በአንድ ተንትኜ ገለጽኩላቸው። ሦስት ወይም አራቱ በቅጡ ታይተው፣ የባንኩን ስነሥርዓት ተከትሎ ውሳኔ እንደሚደረግባቸውና ውሳኔዎቹን በወቅቱ እንዲያውቁት እንደሚደረግ ነገርኳቸው። ገና ተናግሬ ሳልጨርስ የተወካዮቹ መሪ ተነስቶ ቆመ። በእኔ ግምት አንተም የማትረባ ነህ፤ ከሥልጣን ውረድ፤ እዚህ ምን አመጣህ? የሚለኝ መስሎኝ ሆዴ ፈራ ተባ እያለ ሰውዬው የሚለውን ለመስማት ቸኮልኩ። የሚከተለውን ተናገረ፣

"ጌታዬ፣ በእርግጥ ፀሐይ ለኛም መውጣትዋን ዛሬ አወቅን፤ የጠየቅናቸው ጥያቄዎች ሁሉም እንደተስተናገዱልንና አዎንታዊ መልሶች እንዳገኘን እንቆጥረዋለን፤ ከዚህ በላይ የምንፈልገው ወይም የምንጠይቀው ነገር አይኖርም:: ከዚህ በፊት እኮ እዚህ ቤት ማንም ሰው አድርጎ አቅርቦ የሚያነጋግረን ወይም የሚያስረዳን አልነበረም፤ ለምናቀርባቸው ጥያቄዎች አንድ ቃል ብቻ፣ ይሆናል ወይ አይሆንም ነው እንጂ ዛሬ እርስዎ እንዳደረጉት አቅርቦ የሚያስረዳን ወይም የሚያነጋግረን አልነበረም:: እዚህ መሥሪያ ቤት የሠራሁት ካሥራ አምስት ዓመታት በላይ ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፣ የአዛዦቹ ቢሮ ምን እንደሚመስል ገብቼ ያየሁት ገና ዛሬ ነው፤ ሌሎቹም እዚህ ያሉት የምስክርነት ቃላቸው ከዚህ እንደማይለይ አልጠራጠርም:: እኛ ለበላይ ኃላፊዎች ጸያፎችና የተናቅን፣ በሩቅ መጠበቅ ያለብን ፍጡሮች መስለን ነው የምንታያቸው፤ ጌታዬ ዛሬ ታላቅ የደስታችን ቀን ነው፤ እግዚአብሔር ይስጥልን"

ብለው ተሰናብተውኝ ሄዱ::

በዚያን ዕለት ስለተሰበሰብንበት ስለምክትል አዛዡ ቢሮም ሆነ ጎኑ ስላለው ስለዋናው አዛዥ ቢሮ እኔም ሆንኩ አቤቱታ አቅራቢዎቹ የማናውቀው ነገር ነበር:: አንድ ቀን ጸሓፊዬ ብርቱካን ግዛው አቶ ሞናሴ ለማ "ልግባና ላነጋግረው" ይላሉ ትለኛለች:: ስሜቴ ተደበላለቀብኝ፤ የልቤም አመታት ፍጥነቱን ጨመረ:: ከ1952 እስከ 1966 በመጀመርያ የስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ ከዚያም የብሔራዊ ባንክ ገዢ ወይም አዛዥ የነበሩት አቶ ምናሴ አምስት ዓመት ከታሰሩ በኋላ መለቀቃቸው ነበር:: እሳቸው በእስር ሲማቀቁ እኔ ከአዲስ አበባ ባንክ የፕላን ክፍል ኃላፊነት እሳቸው ወደአደራጁት ቤት ተዛውሬ በወንበራቸው ላይ ተደላድዬ ተሰይሜአለሁ:: አምስት ዓመታት ለእሳቸው የመከራ ዘመን ሲሆን ለኔ የትምህርት ዓመታት ነበሩ:: ስለአብዮቱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ታዝቤና ወላፈኑ ገርፎኝ ሙክክ ባልልም

በመጠኑም ቢሆን በስያለሁ፣ በረድም ብያለሁ:: ዲሞክራሲና ሶሻሊዝም እጅና ጓንት ናቸው ተብሎ በጉሮሯችን የተንቆረቆረው ውሸት መሆኑን ተረድቻለሁ:: ሀብታም ይጥፋ በተባለበት አገር የሀብት ክምችት ብሎም የኑሮ መሻሻል ሊኖር እንደማይችል ተገንዝቤአለሁ:: በጥቅሉ ስለሶሻሊዝም አብነት ተጠራጣሪ ሆኛለሁ::

እኔ አቶ ምናሴ ተቀምጠውበት የነበረውን ወንበር እሳቸው ሲታሰሩ ወንበሩን ከተረከቡትና በኋላም እንደእሳቸው የመታሰር ዕጣ ከደረሰባቸው ከአቶ ተፈራ ደገፌ የተረከብኩት በአብዮቱ ስም ስለሆነ የቀማኛነት ስሜት ሳይጸናወተኝ አልቀረም:: ብርቱካን አቶ ምናሴ ለመግባት ቆመው ይጠባበቃሉ ስትለኝ ከተቀመጥኩበት ወንበር ተነስቼ ቆምኩ:: የአቶ ምናሴ ለማን ስም ተማሪ ሆኜ በደንብ አውቀዋለሁ፣ በተለይም ዩኒቨርስቲ ከገባሁ በኋላ:: የMoney and Banking አስተማሪያችን ጂ ዲ ቮን ፒሽክ ስለ አቶ ምናሴ ይነግረን ነበር:: ምናሴ ለማ ሲባል አእምሮዬ የቀረጸው አንድ ግዙፍ፣ ረጅም፣ ከባድ፣ ሰው የማይቀርብና የማያቀርብ ኩፍስ ሰው ነበር:: ብርቱካን አስገቢያቸው አልኳትና ገቡ:: ከተዘረዘሩት የገጽታ መግለጫዎች አንዱም ለሳቸው ተስማሚ አለመሆኑን ለመመስከር ብዙም ጊዜ አልፈጀብኝም:: አጠር፣ ቀጠን ያሉ፣ ተጫዋች፣ ተግባቢና የሰላ አእምሮ ያላቸው ሰው መሆናቸውን ተረዳሁ:: ያደጉት በግብጽ ምድር በመሆኑ አማርኛቸው ይጣፍጣል:: ጊዜ እሳቸውን ጣለ፣ እኔን አነሳ፣ የነገውን ማን ያውቃል? ብዬ በልቤ አሰብኩ:: ቢሆንም፣ መጽናኛ የሆነልኝ ገና ከልጅነቴ ሥልጣን የሕዝብ ማገልገያ መሣሪያ እንጂ የራስ መገልገያ ነው ብዬ ስለማላውቅ ከተሰጠኝ ኀላፊነት እንደሳቸው ብገለልስ? ብዬ ሳስብ ሥራ መሥራት፣ ማንነቴን በሥራዬ ማስመስከርና ሕዝብን ማገልገል ተከለከልኩ እንጂ ጥቅም ይቀርብኝና ጉዱ ይፈላል ማለቴ አልነበረም::

ከአቶ ምናሴ ጋር ስንተዋወቅ እድሜያቸው ቢያንስ 65 ገደማ ሳይሆን ስለማይቀር የተነጠቁት ቦታቸው ለ32 አመት ጎልማሳ መሰጠቱን ሲያዩ ቆይ ግድየለም፣ እድሜ ይስጥህና ይህ ዓለም ውጥንቅጥና ውስብስብ

መሆኑን፣ መውጣትና መውረድ የተቆራኙ ስለመሆናቸው፣ የፖለቲከኞች ቃላቸው ከተግባራቸው እንደማይገጣጠም እድሜ እንደኔ ይስጥህና አንተም ታየዋለህ ብለው አንድም ሳይመርቁኝ አንድም ሳይረግሙኝ አንድም አይ የኛ ተራማጅ፣ የኢትዮጵያ አራማጅ ብለው በልባቸው ሳይሥቁብኝ የቀሩ አይመስለኝም፡፡ ይልማ ዴሬሳ ከገንዘብ ሚኒስትርነት ተነስተው በቦታቸው ማሞ ታደሰ ሲሾም፣ "እንኳን ማሞ ማሚቱም ብትመጣ የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ካለበት ፈቀቅ አታደርገውም" ብለው ተናገሩ የተባለው ትዝ አለኝና አሁን ጫና ያለው በታደሰና መሰሎቹ እንጂ በእነ አቶ ምናሴ አለመሆኑን ስገነዘብ በአንድ በኩል ምንኛ የታደሉ ናቸው? አልኩ፡፡

አዛዡ ወንበር ላይ መቀመጡን መንፈሴ እምቢ ስላለኝና የሌባ ተቀባይ ነህ ብለው እንደሚፈርጁኝ ስለተሰማኝ እኔም እንደሳቸው በእንግዳ ማረፊያው ወንበር ላይ ተቀመጥኩና ጭውውታችንን ቀጠልን፡፡

ቢሮውን በዐይናቸው ቃኝተት ቃኝተት አደረጉና ስለዚህ ቢሮ ታሪክ ልንገርህ ይሉኛል፡፡ በአዛዡ ቢሮ ውስጥ የሚገኙት አብዛኛዎቹ ቁሳቁሶች፣ የተቀመጥንባቸው የእንግዳ ወንበሮች ጭምር፣ ጣልያን ከምስራቅ አፍሪቃ ሲባረር ኤርትራን ያስተዳድር የነበረው የእንግሊዝ አገረ ገዢ የሚገለገልባቸው ነበሩ፤ እንግሊዞች ክፍለ ሀገሩን ለቀው ሲወጡ ባንኩ የገዛቸው ናቸው፡፡ የባንኩን ሕንጻ በተመለከተ፣ ፕላኑ የጸደቀውና የግንባታው ሥራ የተጀመረው የማዕከላዊ ባንክ ሥራና የንግድ ባንክ ሥራ አንድ ላይ ተጣምረው በስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ አማካይነት በሚካሄዱበትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሕግ ከመፈጠራቸው በፊት ነበር፡፡ ሕንጻው የስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ ንብረት ይሆን ነበር ማለት ነው፡፡ በመሀሉ አቶ ደበበ ሀብተዮሐንስ ስቴት ባንክን ለቀው የግል ባንክ ለማቋቋም መንቀሳቀስ እንደጀመሩ በተለይ የግል ባንኮችን ሥራ የሚደነግግና የሚቆጣጠር ማእከላዊ ባንክ ማቋቋም እንደሚያስፈልግ ግልጽ ሆነ፡፡ አቶ ደበበ ያስገቡትን ባንክ የማቋቋም ማመልከቻ ውድቅ ከማድረግ ይልቅ ከግል ባንኮች ጋር መወዳደር የሚችል

እራሱን የቻለ ጠንካራ የመንግሥት ንግድ ባንክ መፍጠር እንደሚሻል ታመነበት:: የስቴት ባንክ ኦፍ ኢትዮጵያ የንግድ ባንክ ሥራ እየሠራ የግል ባንኮችን እንዲቆጣጠር ቢደረግ ባንኮቹ ምስጢራችንን ለተወዳዳሪያችን መንገር ይሆናል፣ አድልዎ ይደረግብናል ማለታቸው እንደማይቀር ግንዛቤ ተወሰደ:: ስለሆነም፣ ስቴት ባንክ ለሁለት ተከፈለና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1956 ተፈጠሩ::

የተጀመረው ሕንጻ ፕላን እንደገና ታየና ለሁለቱም የገንዘብ ድርጅቶች እንደሚስማማ ሆኖ እንዲያልቅ ተደረገ:: የተቀመጥንበት የዋናው አዛዡና የምክትሉ ቢሮዎችና መዳረሻቸው የሕንጻው ፕላን መጀመሪያ ሲጸድቅ የታሰበው የአሮጌ ብር መረጣ ክፍል እንዲሆን ነበር:: እንደሚታየው የቢሮዎቹ ጣሪያ በጣም ከፍ ያለ ነው:: ይህ የሆነው ፕላኑ ሲከለስ በአዛዦቹ ቢሮ ላይ ይደረብ የነበረውና ለቢሮዎች ጣሪያ ይሆን የነበረው ወለል እንዲነሳና ቢሮዎቹ የሁለት ፎቅ ቦታ እንዲይዙ በመደረጉ ነው:: በተለይ የአዛዡ ቢሮ በጣም የተዋጣለት ስለሆነ ውስጠ ምስጢሩን የማያውቅ ተመልካች ሕንጻውን ለመሥራት ያነሳሳው ዋና ምክንያት የተዋበ ቢሮ ለአዛዦቹ ለመሥራት ተፈልጎ ነው ብሎ ቢያምን አይፈረድበትም::

የሕንጻውን ኮምፐሌክስ፣ ማለትም ረጅሙን ፎቅና ክቡን የአዲስ አበባ ቅርንጫፍን ለመሥራት የፈጀው አራት ሚሊዮን ብር ነበር:: ሕንጻው ባለቤትነቱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይሁን እንጂ ሁለቱም እንደሚገለገሉበትና የሁለቱም ዋና መሥሪያ ቤት እንዲሆን ስምምነት ነበር:: ብሔራዊ ባንክ እንደደባል ተቆጥሮ በዓመት አራት ብር ወይም በወር 33 ሳንቲም የይስሙላ ኪራይ ይከፍል ነበር:: ታዲያ ክፍያው የደርግ መንግሥት ከተመሠረተና የትርፍ ቤቶች አዋጅ ከታወጀ በኋላ ችግር አስከተለ:: በደርግ አዋጅ መሠረት ማንኛውም ከመቶ ብር በታች ኪራይ የሚከፈልበት ቤት ቀበሌ እንዲረከበውና እንዲያስተዳድረው በተወሰነው መሠረት ብሔራዊ ባንክ የሚገለገልባቸው፣ ነገር ግን ባለቤትነታቸው

የንግድ ባንክ የሆኑትን ቢሮዎች ንግድ ባንክ ለቀበሌ ማስረከብ ነበረበት ማለት ነው። ብሔራዊ ባንክም ከ33 ሳንቲም ላይ መንግሥት የደነገገው ቅናሽ ተነስቶለት 20 ወይም 25 ሳንቲም ወደሚመለከተው ቀበሌ በየወሩ ሄደን መክፈል ይኖርብን ነበር። የአገሪቱን ማእከላዊ ባንክ ቀበሌ ወረሰው፣ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ በዓመት ትርፍ የሚያስገኘው ባንክ የሚከፍለው ወርሃዊ ክፍያ በመንገድ ላይ ቆሞ ለሚለምን የኔ ቢጤ የሚሰጠው ቅንስናሽ ገንዘብ ያህል ነው ተብሎ ቢነገር ባንኩም ሆነ አዋጅ ያወጣው መንግሥት የሕዝብና የዓለም መሣለቂያ ስለሚሆኑ አዋጁን ጥሶ የመጣው ቢመጣ ይሻላል ስለተባለ የአገሪቱ ሁለቱ ታላላቅ ባንኮች በቀበሌ ላይ በገሀድ ሸፍተው ይኖራሉ። እንደ ፈረንጅ አገር አሠራር ቢሆን ኖሮ ጉዳዩ የሚመለከተው ቀበሌ ሊቀመንበር ወይም ቅጥረኛ ጠበቃ ስሙን ለመትከል ሲል ባንኮቹን ወደ ፍርድ ቤት ጎትቶ መውሰዱ የማይቀር ነበር።

መንግሥቱ ኃይለማርያም ባንኩን በ1979 ገደማ በጎበኘበት ወቅት መንግሥት የመንግሥታዊ ድርጅቶችን ንብረት መውረሱ እራሱን በራሱ እንደወረሰ ከመቆጠሩም በላይ በተለይ ባንኮችና የመድን ድርጅት ባላቸው የረጅም ጊዜ እቅድ መሠረት በንብረትነት የያዟቸውን ሕንጻዎች ለገቢ ምንጭነት መጠቀም አለመቻል ብቻ ሳይሆን ሥራቸውን ለማስፋፊያ ሊያውሏቸው አልቻሉምና ትርፍ ቤቶችን የሕዝብ ያደረገው አዋጅ ሊሻሻል ይገባል ብዬ ላደረግሁት ንግግር መንግሥቱ መልስ ሲሰጥ ታደሰ ያለው ትክክል ነው፤ አስፈላጊው እርምጃ ይወሰዳል ብሎ ቃል ገብቶ ነበር። ነጥቡ ከዚህም በፊት ብዙ ጊዜ ተነስቶ ውሳኔ ሳያገኝ ቀርቶ ስለነበር መንግሥቱ ዛሬ በቀኝ ጎኑ ተነስቷል ተባብለን ደስ ብሎን ነበር። ነገር ግን መመሪያው በተግባር እንዲተረጎም ለሚመለከታቸው ለእነፋሲካ ሲደልል ባሳስብም የትም ሳይደርስ ዳዋ በልቶት ቀረ።

በነገራችን ላይ መንግሥቱ ባንክን ሊጎበኝ ሲወስን ከሚከተለው ነገር ጋር የተገናኘ ነው ብዬ አምናለሁ። አንድ ቀን በቢሮው ባንኮችን አስመልክቶ ውይይት ይደረጋል። በቡና እረፍት ወቅት በፓርቲው የኤኮኖሚ መምሪያ

የሚሠራ አንድ ግራቀደም ተስፈንጣሪ፣ ኅብረተሰብ ለባንኮች መሠረታዊ ፍላጎት የለውም፤ የገንዘብ ድርጅቶች የደም መጣጮች መሣሪያዎች ናቸው ሲልና ከመምሪያው ኃላፊ ከፋሲካ ሲደልል ጋር ሲሣሣቁ ሰማኋቸው:: ከእረፍት መልስ ስብሰባው እንደተጀመረ ሥራ በሠራን ለምንድነው የምንሰደበው? ባንኮች አስፈላጊ አይደሉም አንዴት ይባላል? በዚህ ዓይነት የባንክና ኢንሹራንስ ሠራተኞችን ሞራል ጠብቀን ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ እንዴት ማድረግ ይቻላል? ብዬ ሳልፈራ አምርሬ ተናገርኩ:: ደፍሬ እንደዚያ በመናገሬ በስብሰባው ላይ የነበሩት ተደናገጡ፣ ተገረሙ:: ምን አስቦ እንደሆነ አላውቅም መንግሥቱን ሣቅ አፈን አደረገው:: ማነው እንደዚያ ያለው? በፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው አለ:: ሚናችሁንና አስተዋጽኦዎቻችሁን ስለምናውቅ ሥራችሁን ጠንክራችሁ ሥሩ አለ:: ከሁለት ሳምንታት በኋላ ይመስለኛል ከቢሮው ተደውሎ ለጉብኝቱ እንድንዘጋጅ ተነገረኝ::

ወደ አቤቱታ አቅራቢዎቹ ታሪክ ስንመለስ በባንኩ ውስጥ የሚጠብቀኝ ሥራ ቀላልና ልዩ ጥረትና ጥበብ የማይጠይቅ መሆኑን ተረዳሁ:: ጥያቄዎቹን አቅም በፈቀደ መጠን ለማስተናገድ እስከተቻለ ድረስ ሠራተኛው ከሰማይ ጨረቃ ይውረድልኝ እንደማይል ተረዳሁ:: ሠራተኛው በአንደኛ ደረጃ የሚፈልገው ስብእናው እንዲከበርለትና ክብሩ እንዲጠበቅለት እንደሆነም ተረዳሁ:: የትም ይሁን የት፣ ላይ ልውጣ ታች ልውረድ፣ የኔም ፍላጎት ያልተለየ ስለሆነ የመንፈስ ወንድሞቼን እንዳገኘሁ ተሰማኝ:: በኃላፊነት ላይ የተመደብኩት እድልና ሁኔታዎች ተገጣጥመው እዚህ ስላደረሱኝ ነው እንጂ ከሌላው ኢትዮጵያዊ የተለየሁ ስለሆንኩ ይህን ቦታ ለመያዝ ቻልኩ ብዬ አላውቅም:: እንዲያውም አንዱ የሕይወቴ ዓላማ አድርጌ የተነሳሁት እንደዚህ ዓይነቱ አጉል እምነት ያላቸውን ለመዋጋት ስለሆነ በእርግጥ ሠራተኞቹን የሚያንቋሽሹ ኃላፊዎች ካሉ እኔ ወገንነቴ ከሠራተኛው ጋር በመሆኑ በልቤ አጋር አግኝታችኋልና እንኳን ደስ ያላችሁ ሳልል አልቀረሁም::

ሠራተኛ ጥያቄ በጥያቄ ላይ ሲደራርብ፣ ሱሪ በአንገት ይውለቅ ሲል ባመቸው መንገድ የበላዮቹን ሲፈታተን ተፈጸመብኝ ለሚለው በደል አጸፋውን ለማስከፈል የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደሆነ ተገነዘብኩ፡፡ በሌላ ቋንቋ ኢሰብአዊ የአስተዳደር በደል ተፈጽሞብኛል የሚል ሠራተኛ የሚያቀርበው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ሳይሆን የበላይ ኃላፊዎች ተደላድለው የተቀመጡበት ወንበር እሾህ ሆኖ እንዲወጋቸው የታለመ ሊሆን እንደሚችል ተረዳሁ፡፡ ተማሪዎች ሆነን ሾርባው ቀጠነ፣ ወጡ ተምቦጫቦጨ ብለን ሰላማዊ ሰልፍ የምናደርገው በእርግጥ ለሆድ ታስቦ እንዳልሆነ ብዙዎቻችን የምናስታውሰው ነገር ነው፡፡ የሠራተኛንና የተማሪን ሥነልቦና የሚገዛው ሕግ አንድ መሆኑን አውቃለሁ፡፡

ለማጠቃለል፣ ሠራተኛውን የአእምሮ ሰላም የሚነሳው ነገር ካለ እሱም በምላሹ በእጁ ያለውን መሣሪያ ተጠቅሞ የመዋጋት ዝንባሌ እንዳለው መታወቅ አለበት፡፡ ለመገንባት የተቀጠረው ሠራተኛ ወደ አፍራሽ ኃይል ተቀይሮ ቁጭ ሊል ይችላል፡፡ ሠራተኛና አሠሪ ተሳስበው፣ ልብ ለልብ ተገናኝተው፣ ሰላም ሰፍኖ ድርጅቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ አሠሪዎች ወይም የበላይ ኀላፊዎች ሠራተኛን ማክበርና ማቅረብ እንዳለባቸው ምንጊዜም መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡

የብሔራዊ ባንክ ኃላፊነት በማእከላዊ ባንክነት ብቻ ሳይወሰን ባንኮችንና መድን ድርጅትን በቀጥታ የማስተዳደር ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡ የባንኮች ቦርዶች ፈርሰው የብሔራዊ ባንክ ቦርድ ሥራቸውን ከላይ ሆኖ እንዲመራና እንዲቆጣጠር ተደረገ፡፡ በተጨማሪም በ1967 ዐሥራ ሦስቱ የመድን ኩባንያዎች ሲወረሱ አምስት አባላት ያሉት አንድ ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ቦርድ ተቋቁሞ ስለነበር የብሔራዊ ባንክን ወክዬ የምሳተፈው እኔ ነበርኩ፡፡ ኩባንያዎቹ ተጠቃለው በአንድ ኩባንያነት እንዲዋቀሩ ከተደረገ በኋላ ድርጅቱን የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነት ለብሔራዊ ባንክ ተሰጠ፡፡ ስለመድን ድርጅት አመሠራረት ወደኋላ እመለስበታለሁ፡፡

የገንዘብ ድርጅቶችን በአዲስ መልክ ለማደራጀትና ሥራቸውን ለመምራት የጠየቀው ጊዜና መሥዋዕትነት ቀላል አልነበረም:: እርግጥ ወደ መጀመሪያው ገደማ የትብብር ችግር ስላልነበረ የሥራው ሂደት አመርቂ ነበር::

አልፎ አልፎ ግን ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም:: አብዮት እየተካሄደ ክስተቱ በፍጹም አስገራሚ አልነበረም:: ከገጠሙኝ ችግሮች ሁሉ እልህ አስጨራሹ በንግድ ባንክ ውስጥ የተፈጠረው ሁኔታ ነበር:: ንግድ ባንክን የበለጠ ዘመናዊ ለማድረግ ታስቦ ይልማ ከበደና ፍቅሩ ገብረሚካኤል የሚባሉ የባንኩ ወጣት ኦፊሰሮች በመምሪያ ኃላፊነት በብሔራዊ ባንክ ይሾማሉ:: ሁለቱም በዩኒቨርስቲው የንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ምሩቃን ናቸው:: ድርጊቱን በመቃወም ከፍተኛ ስም የማጥፋት ዘመቻ በእኔና በነሱ ላይ ተከፈተ:: አነጣጣሪዎቹ አንዳንድ የባንኩ አንጋፋ ሠራተኞች ሳይሆኑ አይቀሩም:: ይህ በእንዲህ እያለ የንግድ ባንክ አንድ ክፍት ቦታ ለመሙላት የባንኩ ፖሊሲ ኮሚቴ ማመልከቻዎችን ሲመረምር አንደኛዋ አመልካች የኤርትራ ተወላጅ መሆንዋን ይመለከታሉ:: ከተጠቀሱት ሁለት መምሪያ ኃላፊዎች አንደኛው አሁን ባለው ሁኔታ ሴትዮዋን ቀጥሮ ለታሰበው ቦታ መመደብ በአገሪቱ ደኅንነት አኳያ ሲታይ ተደጋፊነት የለውም ይላል:: እንድትቀጠር ይወስኑ ወይም አይወስኑ አላስታውስም:: ሳይውል ሳያድር ባለቤትዋ ከበደ ተመስገን ይደውልልኛል:: በገንዘብ ሚኒስቴር የአንድ መምሪያ ኃላፊ ነው:: በንግድ ባንክ ፖሊሲ ኮሚቴ ስለሴትዮዋ የተባለውን በዝርዝር ያነሳና ባለቤቴ እንዴት እንዲህ ትባላለች? አብዮት እየተካሄደ እንዴት እንዲህ ይደረጋል? የኤርትራ ችግር በሰላም ይፈታ እያልን በሌላ በኩል ወገን ከወገን የሚለያይ አባባል እንዴት ይሰነዘራል? ብሎ ምሬት በተሞላ መንፈስ በስልክ ያነጋገረኝ ቢያንስ ለአርባ አምስት ደቂቃ እንደነበር አስታውሳለሁ:: አቶ ከበደ ባለው ተስማማሁለት::

ዋና ያሳሰበኝ ግን በፖሊሲ ኮሚቴ የሚነጋገሩትን፣ ውጭ እያወጡ የሚዘረግፉት ከሆነ ወይም እርስ በርስ ያላቸውን አለመግባባት ገሀድ

የሚያወጡ ከሆነ የጋራ አሠራር መንፈስን ገድለው የአገሪቱን ትልቁን ባንክ አደጋ ላይ ሊጥሉ ነው አልኩና ከፍተኛ ስጋት አደረብኝ። የፖሊሲ ኮሚቴውን ለማነጋገርና የሚያደርጉት ውይይት ሁሉ ምስጢር አድርገው እንዲይዙና በምንም ዓይነት ውጭ እንዳያወጡ መመሪያ ለመስጠትና ለመምከር ፈልጌ ተሰብስበው እንዲጠብቁኝ መልዕክት አስተላለፍኩ። በተባለው ቀንና ሰዓት ብሄድ ዋናው ሥራ አስኪያጅ አሰፋ ጸጋዬ ሌላ ስብሰባ አለብኝ ብሎ ከመሥሪያ ቤቱ ውጭ መሄዱን ነገሩኝ። መገኘት እንደማይችል ቀድም ብሎ የተነገረኝ ነገር ስላልነበረ ሆን ብሎ እኔን ለማናደድና ለመፈታተን ያደረገው መሆን አለበት ብዬ አሰብኩ። እነይልማ እንዲሾሙ ያደረገው ታደሰ ስለሆነ የማልፈልጋቸው ሰዎች ወዳጅ ስለሆነ ከሱ ጋር የምተባበርበት ምክንያት የለም ብሎ አቋም የወሰደ መሰለኝ። ከዋናው አዛዥ ጋርም ሳይነጋገሩ እንዳልቀሩ ኋላ ደረስኩበት። ሰውዬው ባይኖርም መልዕክቴን ማስተላለፍ ስለነበረብኝ ተባብረው እንዲሠሩና ምስጢር እንዲጠብቁ አበክሬ መክሬአቸው ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ። ሰውዬው ሄደበት ከተባለው ስብሰባ ከተመለሰ በኋላ ደውሎ ወይም ቢሮዬ ብቅ ብሎ ይቅርታ ሊጠይቀኝ ቀርቶ ለምን በስበሰባው ላይ እንዳልተገኘ ሳይነግረኝ ቀረ። ስለኔ ያለው አመለካከትና አቋም ግልጽ ሆነልኝ። ድፍረቱና ማናለብኝነቱ እልህ ውስጥ ከተተኝ። ጦርነት እንዳወጀብኝ ተሰማኝ።

በዚያው ሰሞን የባንኩ አዛዥ በላኩልኝ ደብዳቤ በሥራህ ትጉህ ነህ፣ ነገር ግን ከባንክ ባለሥልጣኖች ጋር ተስማምተህ መሥራት አልቻልክም አሉኝና ቁጭ አሉ። አሁን ነገሩ በጣም ግልጽ ሆነልኝ። ተፈርሞ ስለተላከልኝ ግምገማ ከአዛዡ ጋር ስንነጋገር አንድ ያሉት የንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ በሌለበት ባንኩ ድረስ ሄጄ ተሳድቤ እንደመጣሁ ነው። አሁን የኃይል አሰላለፉ ግልጽ ሆኖ መጣ። ዋናው ሥራ አስኪያጅ ከኔ ጋር የነበረውን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አቋርጦ የሚሠራው ከዋናው አዛዥ ጋር ብቻ ሆነ።

የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከቦታው ካልተነሳ በቀር ባንኩን መምራትና መቆጣጠር አይቻልም፣ በባንኩ ውስጥ ሰላም ሊሰፍን አይችልም፣ ሰውዬው የባንኩን ኮሚቴ አስተባብሮ መምራትና ማሠራት አይችልም፣ የባንኩን አንድነት አናግቶአልና በተቻለ ፍጥነት ከቦታው መነሳት አለበት የሚል ጠንካራና ግልጽ አቋም ያዝኩ:: ጉዳዩ ደርግ ዘንድ ቀርቦ ጥፋቱ የታደሰ ወይስ የአሰፋ? የሚል ሕይወት ያገኝና መንቀሳቀስ ይጀምራል:: በስለሺ መንገሻ ሰብሳቢነት ደርጉ አጣሪ ኮሚቴ አቋቋመ:: ቃልህን ስጥ ተብዬ ብዙ መስቀለኛ ጥያቄዎችን አቀረቡልኝ:: በተደጋጋሚ በሰጠሁት አስተያየት የግል ጉዳይ ሳይሆን የንግድ ባንክ ደኅንነት ጉዳይ ስለሆነ እኔን እዚያ ትሠራለህ ብላችሁ እስካስቀመጣችሁኝ ድረስ ከሰውዬው ጋር መሥራት አልችልም የሚል ነበር::

ነገሩ በእንዲህ እያለ አቶ ተፈራን ደርግ ያስራቸዋል:: ለምን እንደታሰሩ የማውቀው ነገር የለም:: ደርግ የሰጠው ምክንያት አብዮቱን ሊፈታተኑ ያሰቡትን በቁጥጥር ሥር ለማቆየት እንደነበር ነው:: አቶ ደበበ ሀብተዮሐንስ ያኔ ነው የታሰሩት::

አንድ ቀን ወደ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ጸሓፊዬ ብርቱካን መጥታ አቶ ተፈራን ይዘዋቸው ሄዱ እኮ ትለኛለች:: መቼ? ብላት ከአንድ ሰዓት በፊት ትለኛለች:: ለምን ወዲያው መጥተሽ አልነገርሽኝም? ብላት ያየሁት ስላስደነገጠኝ ወንበሬ ላይ ደንዝዤ ቀርቼ ነው አለች:: ምን አየሽ? እላታለሁ:: ሁለት የታጠቁ ወታደሮች ይመጣሉ:: አንደኛው ቢሮአቸውን በርግዶ ይከፍትና መሣሪያውን አነጣጥሮ እጅ ወደላይ ይላቸዋል:: እጃቸውን ወደላይ ይሰቅላሉ:: ከዚያም ለአዛዦቹ ቢሮ የተመደበውን ተላላኪ መርአዊን ሂድና ኪሳቸውን ፈትሽ ብሎ አነጣጣሪው ያዘዋል:: ኪሳቸው በተላላኪያቸው ይበረበራል:: ከዚያም ይዘዋቸው ሄዱ አለችኝ:: እውነቱን ለመናገር ከሰውዬው ጋር የሐሳብ ልዩነቶች ይኑሩን እንጂ በግላቸው ጨዋ፣ ቆፍጣና፣ ሰውና ሥራቸውን አክባሪ ስለነበሩ ለእንዲህ ዓይነት ውርደት መዳረጋቸው ዘገነነኝ:: ለምን ዓይነት ሰዎች ነው

የምሠራው? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ አቶ ተፈራ ስልክ ተደውሎ እዚህ ቦታ ድረስ ይምጡ ቢባሉ የሚተባበሩ ዓይነት ሆነው ሳለ እንዴት ቢሮአቸው ተበርግዶ እጅ ወደላይ ይባላሉ? ብዬ በጣም አዘንኩ፡፡ ጸሓፊዬ ብርቱካን ደንዝዤ ነው እንዳለችው እኔም ተይዘው የሄዱበትን ኮሪደር የማይበትን ጊዜ በተቻለ መጠን ለማራዘም ከቢሮዬ የወጣሁት ካቀድኩት ቢያንስ ሁለት ሰዓት ዘግይቼ ነው፡፡ ምነው ከዚህ ሁሉ ጣጣና ፈንጣጣ እዚያው ዋሺንግተኔ በሄድኩ ኖሮ ማለቴም አልቀረም፡፡

አቶ ተፈራ ለምን እንደታሰሩ አላውቅም ብያለሁ፡፡ ከመታሰራቸው ጋር ግንኙነት ይኑረው አይኑረው ባላውቅም አንድ ያየሁትን ነገር መናገሩ አይጎዳም፡፡ የገንዘብ ለውጥ ፕሮግራም በምስጢር ስንሠራ የደርጉ የኤኮኖሚ መምሪያ ኃላፊ ሻምበል ሞገስ ቅዳሜ ቅዳሜ እየመጣ ስለስሥራው ሂደት ይከታተል ነበር፡፡ አንድ ቀን ሥራችንን ጨርሰን ወደ የቤታችን ለመሄድ በባንኩ መኪና ማቆሚያ ስፍራ ዳርቻ ላይ ሆነን ትርኪ ምርኪውን እናወራለን፡፡ መቶ አለቃ ፈቃደም አለ፡፡ አቶ ተፈራ ከሕንጻው ይወጡና ወደ መኪናቸው ባጠገባችን ያልፋሉ፡፡ ሻምበል ትክ ብሎ ያያቸውና እኝህ አቶ ተፈራ አይደሉም እንዴ? ይላል፡፡ አዎን፣ ናቸው እንለዋለን፡፡ እኔ ሞገስ፣ እንዴት ሰላም ሳይለኝ ዝም ብሎ ይሄዳል? ይላል፡፡ የለም፣ አላዩህም፣ የዐይናቸውን ሁኔታ ታውቅ የለም እንለዋለን፡፡ የለም የለም አውቆ ዝም ብሎኝ ነው የሄደው፤ ይሄ ሽማግሌ እንዴት ጠገበ? ቆይ እኔ ሞገስ አይደለሁም፣ ባላሳየው፣ ይላል፡፡ ሞገስ እያጉረመረመ እያለ ሾፌር በር ይከፍትላቸውና አቶ ተፈራ መኪናቸው ውስጥ ይገባሉ፤ ከተቀመጡበት ፊታቸውን ወደኛ ሳያዞሩ ነጭዋ ሬኖ16 ከግቢው ተንፈላሳ ወጥታ ትሄዳለች፡፡ ሻምበል ሞገስን፣ ያዩህ አይመስለንም ብለን አሁንም ልናበርደው ሞከርን፡፡ የሰማን አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም መኪናዋ ከሄደች በኋላ የባሰበት መሰለን፡፡ እኛም ጨዋታችን ተወለካከፈና ብዙም ሳንቆይ ሰላም ተባብለን በየፊናችን ወደምንሄድበት አመራን፡፡ ይህ በሆነ ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነው አቶ ተፈራ የታሰሩት፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን አዛዦቹ ቢሮ ፊት ለፊት ካለው የእንግዳ ማረፊያ ሶፋ ወንበር ላይ አንድ ሰው ተቀምጦ አያለሁ:: ሰውዬው ኮፍያ ደፍቶአል:: ኮፍያ አድርጎ መቀመጥ የተለመደ ስላልሆነ ይሄ ማነው? ብዬ አሻቅቤ ሳይ አቶ ተፈራ ሆነው አገኘቸዋለሁ:: ቁልፍ ሊያስረክቡ መጥተው ይመስለኛል:: ስሜቴ ሁሉ ተደበላለቀብኝና ምን እንደምላቸው ጠፍቶኝ ቆም ብዬ ሳሰላስል ሰውዬው እንዳያዩኝ ወይም እንዳያነጋግሩኝ ፊታቸውን አዞሩትና ገላገሉኝ:: ቢሆንም፣ የተወሰዱ ዕለት በአእምሮዬ የተጉላላው ስሜትና የወጣውና የወረደው ሐሳብ እንደገና አገረሸበትና ለአንድ ሁለት ቀን ሌላ ዓለም ውስጥ ነበርኩ ማለት ይቻላል::

በአቶ ተፈራ ቦታ አቶ ለገሰ ጥቀሄር ተሹሞ ይመጣል:: አሰፋ ጸጋዬ ይነሳና ለንግድ ባንክ ሌላ ሰው ይሾማል:: መነሳት አለበት ተብሎ ከብዙ ትግል በኋላ ቦታውን እንዲለቅ የተደረገውን ሰውዬ እነአቶ ለገሰ ብሔራዊ ባንክ አማካሪ አድርገው ያመጡታል:: ሰውዬው ስለማእከላዊ ባንክ የሚያውቀው ነገር ስለሌለ እንዴት የኛ አማካሪ ሊሆን ይችላል? በተጨማሪ፣ እኔና እሱ አብረን መስራት እንደማንችል እየታወቀ እዚህ እንዲመጣ መደረጉ ንግድ ባንክ እንደተበጠበጠ ብሔራዊ ባንክም ይበጥበጥ ለማለት ነው እንጂ ሌላ የሚሰጠው ትርጉም አይኖርም፤ ስለሆነም፣ በምደባው በጭራሽ አልስማማም ብዬ እንደገና ለትግል ታጥቄ ተነሳሁ:: ያሁኑ ትግሌ ከአዲሱ አዛዥ ጋር ብቻ ሳይሆን ከቦርዱ ሊቀመንበር ከገንዘብ ሚኒስትሩና ከተቀዳሚ ሚኒስትሩም ጋር ሆነ:: ለነዚህ ሰዎች በምንም ዓይነት አላጎበድድም፤ በአገር ልጅነት የተባበሩብኝ ይመስላል፤ በማምንበት ጉዳይ ወደፊት እገፋለሁ ብዬ ቁርጥ ሐሳብ አድርጌ ተነሳሁ:: ከግራና ቀኝ ሊያጠቁኝ ቢሞክሩም የበለጠ ጠንክሬ አገኙኝ:: በመጨረሻም፣ ሰውዬው ብሔራዊ ባንክን ለቆ እንዲሄድ ተደረገ::

እናሸንፈዋለን ብለው የተነሱብኝ ሰዎች አንድም እንደትልቅ ነጥብ የቆጠሩት የአለማየሁ ኃይሌን መገደል ነበር:: ዝተው ተነሱብኝ:: አሰፋ ጸጋዬ ንግድ ባንክ የሚሠራ ጓደኛዬ ዮሐንስ ገብረሥላሴን አለማየሁ በተገደለ ማግስት

ቢሮው ያስጠራዋል፡፡ ዮሐንስ ዋና ሥራ አስኪያጁ ቢሮ ሲጠራ ይህ የመጀመሪያው ስለነበር ምን ተፈጠረ? ብሎ ግር ሳይለው አልቀረም፡፡ ተቀመጥ ካለው በኋላ፣ ታዲያ አሁን አንድ በአንድ አላገኘናችሁም? ይለዋል፡፡ አልገባኝም፣ ጌታዬ ይለዋል፡፡ አሁንም ይደግምለታል፡፡ አሁንም አልገባኝም ይለዋል፡፡ በል፣ ካልገባህ ተወው ወደፊት ይገባሀል ብሎ አሰናበተው፡፡ ዮሐንስ ከሥራ አስኪያጁ ቢሮ ከወጣና ሰሞኑ የሆኑትን ነገሮች ካገናዘበ በኋላ ነበር ነገሩን የደረሰበት፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን አለማየሁ ኢትዮጵያ እንድቀር ያደረገው እኔን ለመጥቀም እንዳልሆነ እየታወቀ ሞቱን ተገን አድርገው ሊያጠቁኝ የፈለጉትን በጣም ታዘብኳቸው፣ ናቅኋቸው፡፡ በበለጠ ኃይል እንድጋተራቸው ቁርጥ ሐሳብ አድርጌ ተነሳሁ፡፡

አብዮቱ እንደፈነዳ፣ አራት ጓደኞሞች እኔ ቤት ተገናኝተን የምናመሽበት ቦታ መርጠን እንድንዝናና ፕሮግራም አድርገን ነበር፡፡ አንዱ አለማየሁ ሲሆን የተቀሩት እነማን እንደነበሩ አሁን በውል አላስታውስም፡፡ በተባባልነው ሰዓት ተገናኘን፡፡ አለማየሁ አንድ ሐሳብ አመጣ፡፡ ለምን ዛሬ ስለአገራችን የወደፊት አቅጣጫ አንነጋገርም? ቢራ መላፋንና መዳራቱን ነገም እንደርስበታለን ይላል፡፡ አለማየሁ ባመጣው ሐሳብ መሠረት የምንጽፈውን ሳናስተያይ እያንዳንዳችን ዐሥር ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባ ቁም ነገሮች እንዘርዝር ተባለ፡፡ በመጨረሻ ዝርዝሮቹን ስንናበብ ሁላችንም ከአንድ እስከ ሶስት ያስቀመጥነው የአፈርና የደን ጥበቃ ጉዳይ ነበር፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀመጠበትን ቅርንጫፍ ቆርጦ ለመጣል እየገዘገዘ ስለመሆኑ ትናንትም ዛሬም ግንዛቤው አለ እንላለን፣ ግን የምናደርገው አመርቂ ነገር የለም፡፡ በተቃራኒው ሁኔታው እየተባባሰ ነው፡፡ ዐይናችን ሳይታወር ጎሊናችንን ሳንስት ጉድጓዳችንን እየቆፈርን ነን፡፡ ይህ በዚህ ከቀጠለ ኢትዮጵያ ምድረ በዳ የመሆንዋና የተረፈው ሕዝብ ተሰዶ ማለቁ የጊዜ ጉዳይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ የበለጠ አሳዛኝ ነገር በታሪካችን ሊኖር አይችልም፡፡

በደርግ ዘመን ተገቢ ያልሆነ ወሳኝ ውሳኔ ወይም እርምጃ ሲወሰድ የምናናፍሰው አንድ ቀልድ ነበር:: ዳይኖሶር የሚባለው ግዙፍ እንስሳ ለምን ከምድረ ገጽ ጠፋ? ለሚለው አቢይ ጥያቄ በርከት ያሉ መላ ምቶች አሉ:: አንዱ እንዲህ ይላል፣ ዳይነሶር ጭንቅላቱ በጣም ትንሽ፣ ሰውነቱ ግን በጣም ግዙፍ ነበር:: አንድ ቀን ይርበውና ዞር ሲል ትልቅ የሥጋ ክምር ያያል:: የማያልቅበት ቸሩ የዳይነሶር አምላክ ዛሬስ ምግብ አምጥቶ እዚሁ አጠገቤ ቁጭ አደረገልኝ ይልና እስኪጠግብ ቦጭቆ ቦጫጭቆ ሆዱን ይሞላል:: የበላው የገዛ ሰውነቱን መሆኑን ከጭንቅላቱ ማነስ የተነሳ አላወቀም:: ቁስሉ አመረቀዘና ሞተ:: አለቀ ደቀቀ:: ካ ካ ካ :: ድሮስ ቢሆን፣ ጎርፍ እያሣሣቀ ነው የሚወስድ እንል የለ? አሁን ቀልዱን እናሻሽለውና እንዲህ እንበል፣ *<u>የሕይወታችን መሠረት አፈራችን ከገፋፊውና ገፊው ውሃ ጋር ተጠራርገው እየዘፈኑ ወደ ጎረቤት አገሮች ሲነጉዱ ዳር ቆመን እንስቃለን</u>*:: ካ ካ ካ ::

የደርግ አባላት ስለሚያካሄዱት የፖለቲካ ትግል ማናቸውም ሰው ከሚሰማው ውጭ የማውቀው ነገር አልነበረም:: የአለማየሁ የፖለቲካ አማካሪ አልነበርኩም:: ሁላችንም በየፊናችን በሥራ ደክመን ተወጥረን ስለምንውል ስንገናኝ ስለማኅበራዊ ሕይወታችን እንጂ ስለቢሮ ሥራ አንነጋገርም ነበር:: አልፎ አልፎ አንዳንድ ነገር አምልጦት ከወረወረም ሰምቼ አልፋለሁ እንጂ ምስጢራቸውን እንዲዘከዝክልኝ አልፈልግም ነበር:: እኔ የቢሮ ምስጢር ለማንም መንገር እንደማልፈልግ ሁሉ እሱም እንዲሁ ምስጢሩን እንዲያባክን አልጠብቅም ነበር:: የገንዘብ ለውጥ ፕሮግራምን ለዐሥራ ስምንት ወሮች በምስጢር ስናካሄድ አለማየሁ አያውቅም:: ፕሮግራሙ ይፋ ከወጣ በኋላ ለምን ቀደም ብለህ አልነገርከኝም? ብሎ አልተቀየመኝም:: በተቃራኒው ስለኔ የነበረውን አመለካከት አጠናክሮለት ነበር የሚል ግምት አለኝ::

አለማየሁ በተገደለበት ዋዜማ ቤቴ መጥቶ መንግሥቱ በነፍስ ስለሚፈልገኝ ቤቴ ማደር ስለማልፈልግ ካንተ ጋር ልደር ይለኝና አብረን አንድ አልጋ ላይ

ተኝተን ነው ያደርነው:: የመጣው መትረየሱን አንግቦ ነበር:: ጠዋት ከመንጋቱ ተነስቶ ሄደ:: የዚያኑ ዕለት መንግሥቱ ለምሳ ሲያስቡን ለቁርስ አረግናቸው ብሎ በአስከሬናቸው ላይ አቅራራ::

አለማየሁ ከተገደለ በኋላ የኢ ህ አ ፓ አባል ነበር፤ የሚያራምደው የተጠቀሰውን ድርጅት ዓላማ ነበር ሲባል ስሰማ የጠላቶቹ ወሬ ነው ብዬ ነበር ያለፍኩት:: ሶማልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት የኤርትራ ተገንጣዮች ዕድላችን አሁን ነው ብለው ተነስተው ስለነበር አብዮተኛ ነኝ የሚለው ክፍል ተከፋፍሎ እርስበርስ ከሚፋለጥ የውጭ ወራሪንና ተገንጣይን ተባብሮ መመለስ ቀዳሚ ተግባሩ ሊሆን ስለሚገባ በፖለቲካ አመለካከት ቢለያዩም በአገራችን አለመበታተን የሚያምኑት ኃይሎች ሁሉ በመካከላቸው እርቅ የሚወርድበትን መንገድ ከመፈለግ ሌላ አማራጭ ሊኖራቸው አይችልም በሚለው ነጥብ ላይ የአለማየሁ የቅርብ ጓደኞች ከሱ ጋር ሆነን ተነጋግረንበት መተማመን ላይ ደርሰናል:: አለማየሁ ደርግን ለማሳመን ጥረት እንዲያደርግ መክረነዋል:: ጥረት እንዳደረገ አውቃለሁ:: አለማየሁ የኢ ህ አ ፓ አባል ነው የሚለው አባባል የመነጨው ከዚህ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ:: የድርጅቱ አባል መሆን አለመሆኑን በውል የሚያውቁት ግን ሟቹ ጓደኛዬና ኢ ህ አ ፓ ብቻ ናቸው::

እነአለማየሁ እነመንግሥቱን አሸንፈው ስልጣን ቢይዙ ኖሮ የኢትዮጵያ ታሪክ ምን ይመስል ነበር? ለሚለው ጥያቄ መልሱን መናገር ባይቻልም በወታደር አገዛዝ ዴሞክራሲ ይሰፍን ነበረ ወይም የወታደሩ ክፍል ሥልጣኑን በፈቃደኝነት ለሲቪል ያስረክብ ነበር የሚል ካለ ተአማኒነት አይኖረውም::

ከወታደሩ ክፍል ጋር ተሳትፎ መሥራት ውሃ ወቀጣና የአምባገነን መሣሪያ መሆኑን ተገንዝቦ የተሻለ ቀን እንዲመጣ እየጸለየ በልቡ ሸፍቶ የተቀመጠው ባለሥልጣን ቁጥር ጥቂት አልነበረም:: ይህ እኔንም

ይጨምራል። በሌላ በኩል አሜሪካኖች፣ በተለይም የሬጋን መንግሥት፣ የሶሻሊስት ሥርዓትን ለማፈራረስ ከነበራቸው ዓላማ አኳያ ገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖችን በመደገፍ ደርግን ለማስወገድ ቁርጥ ሐሳብ አድርገው ስለነበር፣ እንዲሁም ተገንጣዮች ለ«ነጻነት» ቋምጠው ስለነበር በኢትዮጵያ የሶሻሊዝምን ሥርዓት ገርስሶ ዲሞክራሲን የሚያራምድ የሲቪል መንግሥት ተመሥርቶም ቢሆን ኖሮ አገሪቱን አንድ አድርጎ ለማቆየት እልህ አስጨራሽ ትግል መግጠሙ የማይቀር ነበር እላለሁ። የተጠቀሰው ችግር የመካከለኛውን ምስራቅ አካባቢ በገጠመው የፖለቲካ ችግር አኳያ ሲገመገም የኤርትራን መገንጠል አሜሪካኖች መደገፋቸው በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካ የዘለቄታ ጥቅም አኳያ ሲታይ ታላቅ ስሕተት ነው። ደርግን ወይም መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለመቅጣት ተብሎ የኢትዮጵያን አንድነት መፈታተን ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት ነው። አሜሪካኖች የኃይል ባለቤት ለመሆን ስለበቁ ኃይልን አምላኪዎች ሆነዋል። ኃይል ኃይልን ስለሚጠራ ዓለምን ፈጣሪ ይጠብቃት ከማለት ሌላ ምን ማድረግ ያቻላል? የኢትዮጵያ ችግር በፖለቲካ መድረክ እንዲፈታ አሜሪካኖች አስተዋፅኦ እንደማድረግ ወንበዴዎችን በመሳሪያ መደገፍ መረጡ። አንድ ነጻ አገር እንዲፈራርስ በተዛዋዋሪም ሆነ በቀጥታ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በመንግሥቱና በአለማየሁ መካከል የነበረው ግንኙነት መሻከሩን ፍንጮች ዐይቼ ነበር። አንዱን ያሳየኝ እራሱ አለማየሁ ነበር። አንድ ቀን መንግሥቱ አለማየሁን ቢሮው ድረስ ጠርቶ የደርግ አባላት ቁጥር በጣም ስለበዛ በተለያየ ዘዴ እንበታትናቸውና ደርግን ጥቂት ሆነን እንምራው ብሎ አለማየሁን ጠየቀው። አለማየሁ ሲመልስለት የደርግ አባላት ከየክፍላቸው ተወክለው የመጡ ስለሆነ ውክልናቸውን የመሰረዝ መብት ለማንም አልተሰጠም እንዳለው ነግሮኛል። ሌላ ጊዜ ደግሞ መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ መንግሥቱ ቢሮ ሄዶ ሲጨዋወቱ እነአለማየሁ ሥልጣኔን ቀምተው እጄን አጣጥፌ እንድቀመጥ አስገደዱኝ ብሎ በምሬት እንደነገረው እራሱ ፈቃደ ነግሮኛል።

የእነአለማየሁ መገደል የተገለጸው ወደ ውድቀት ሌሊት ገደማ ነበር:: አለማየሁ የልጅነት ጓደኛዬ ነው:: መኖሪያው አባቴ ቤት ፊት ለፊት አያቱ ፊታውራሪ ገብረ ማርያም ግቢ ነው:: በልጅነት የመንደር ልጆች ኳስ ስንጫወት አለማየሁ ከፊታውራሪ አጠገብ እንዳይለይ ይደረግ ነበርና ቀርበን መተዋወቅ የቻልነው ይበልጥ ነፍስ እያወቅን ስንሄድ ነው:: አለማየሁ ከንፈሩን ገልቦ፣ ያቺ የወርቅ ጥርሱን ገልጦ ተንከትክቶ ኪ ኪ ኪ እያለ ሲሥቅ የደስታ ስሜት ባካባቢው የመፈንጠቅ ኃይል ነበረው:: ሌላ ስለሱ ትዝ የሚለኝ ከሴት ጋር ሲላፉ ገደብ እያለፈ ሣቅን ወደ እንባ የመቀየር ችሎታው ነው:: አለማየሁ፣ በቃህ፣ ቢባልም ኪ ኪ ኪ እያለ ልፍያውን ይቀጥላል:: በቁም ነገር ሲፈለግም በጠበቁት ስፍራ የሚገኝ ፈጥኖ ደራሽ አስተማማኝ ጓደኛ ነበር:: በመሆኑም መሞቱን ስሰማ ምርር ብዬ አለቀስኩ:: እናቴ ከዚህ ዓለም የተለየችው ማንነትዋን ሳላውቅ ነው:: በቅርብ አውቄው የኔ ነው የምለው ሰው ሲሞት አለማየሁ የመጀመሪያው ነበርና ከሕይወቴ ተቀንሶ እንደተወሰደብኝ ተሰማኝ::

ሲነጋጋ ገብርኤል ቤተክርስትያን አጠገብ ወደነበረው የወንደላጤ ቤቱ ተነስቼ ሄድኩ:: የሚያሳድገው ትንሽ ወንድሙ አሰፋ ኩርምት ብሎ አንገቱን ጉልበቶቹ ላይ ደፍቶ ሲያለቅስ ደረስኩ:: ትንሽ ቆይቶ ሌላው የልጅነት ጓደኞችን ሐዲስ ጸምሩ ከባለቤቱ ጋር መጣ:: ሌላ የማውቀው ሰው ስለመኖሩ አላስታውስም:: ጓደኞቹ ሁሉ ተሰባስበን የምናለቅስ ነበር የመሰለኝ:: እስከ አራት ሰዓት ገደማ ከቆየሁ በኋላ ቤቴ ሄጄ ልብሴን ቀይሬ ቢሮ ሄድኩ:: ቢሮ ገባሁ እንጂ ሥራ ሠራሁ ለማለት አይቻልም:: አንድ የቅርብ የጋራ ጓደኞችን ዘንድ ደወልኩና ማታ ተገናኝኝተን ለቅሶው ቤት እንሂድ እለዋለሁ:: ትቀልዳለህ እንዴ? ይለኛል:: የምን ቀልድ? ብለው፣ እሱ ሞቷል፤ ሁላችንንም ያሰጋናል፤ ይልቅስ ሕይወትህን ለማዳን ብትሞክር ይሻልሃል ይለኛል:: ምን አድርጌ ነው ለሕይወቴ የምሰጋው? አለማየሁ ጓደኛዬ መሆኑን ስለሞተ ልክዳው አልችልም፤ አልክዳውም፤ ይህ የሚያስጠይቀኝ ከሆነ ጠያቂ ይምጣ እለዋለሁ:: ማታ አለማየሁ ቤት ብሄድ አሁንም ከጠዋቱ የተለየ ነገር አላየሁም::

ሕይወቴን ከለወጡት ዋና ዋና ክስተቶች የአለማየሁ ሞት አንዱ ነው። ጓደኞቹ ፈርተው በሐዘኑ ላይ ሳይገኙ መቅረታቸውን እንደ ክህደት ቆጠርኩት። ነግበኤኔ አልኩ። ከዚያን ቀን ጀምሮ በራሴ እንጂ በማንም ላልተማመን ወሰንኩ። ቀደሞም ፍልስፍናዬ ከዚህ የተለየ ባይሆንም የአለማየሁ ሞት እምነቴን አጠናከረልኝ። ነገ አንድ ነገር ብሆን ጓደኛ እንኳን ሊደርስልኝ፣ አላውቀውም ብሎ ሊክደኝ እንደሚችል ተረዳሁ። ልቤ ደንዳና ሆነ። ይህንም ስል ስሜቴ በጥላቻና በምሬት ተመረዘ ለማለት ሳይሆን ሰው ሕይወቱን ለማዳን ወይም ለመጠበቅ ጓደኛውን እስከመካድ ሊደርስ የሚችል ፍጡር መሆኑን ተገነዘብኩ ማለቴ ነው።

ለእኔ ኢትዮጵያ ትቅደም ማለት የገንዘብ ድርጅቶችና መድን ድርጅት ተደራጅተው የልማት አለኝታ የሚሆኑበትን መንገድ መፈለግና ማመቻቸት ነበር። በቀን በአማካይ ዐሥራ ሁለት ሰዓት እሰራለሁ። ሳይነጋ ወጥቼ ቤቴ ውድቅት ሌሊት የምመለስባቸው ቀኖች ጥቂት አልነበሩም። አንድ ቀን ከቢሮ ወደ አምስት ሰዓት ተኩል ገደማ ከሌሊቱ ወጣሁና የሚቀመስ ፍለጋ አንዱ ጋ ጎራ እንዳልኩ የሰዓት እላፊ ገደብ ባለህበት እርጋ ያሰኘኛል። እዚያው ጉልበቴን ታቅፌ አደርኩ። ኢትዮጵያችንን ለማስቀደም የሚከፈል ሒሳብ ብዬ እራሴን አጽናናሁ ወይም አታለልኩ።

ነገር መሸረብ ወይም መተብተብ፣ አተካራ መፍጠር፣ ያለበቂ ምክንያት ከመሬት ተነስቶ መጠራጠር፣ አቅምን መቆጠብ፣ ሠራተኛን ማጥላላት፣ ሌላውን ወደኋላ የፊጢኝ ማሰር፣ በተጓዥ መንገድ ላይ ደንቃራ ማስቀመጥ፣ እሺ ነገ ማለት፣ ውጤት እንዳይሰምር ውሃ መቸለስ ለእኔ ኢትዮጵያን በልማት ወደኋላ ማስቀረት ነው። እነዚህን አሉታዊ አሠራሮች መዋጋት የተግባር መመሪያዬ አድርጌ ተነስቻለሁ። በሥራዬ ላይ የሚመጣብኝን ወይም ያለአግባብ የሚነካኝን ላልተኛለት ቁርጥ ሐሳብ አድርጌአለሁ። ግራዬን ሲጠፈጥፉኝ ቀኜን ላለመስጠት ወስኛለሁ። ለዚህኛው እምነቴ የኢትዮጵያ አብዮት አምላክ ይቅር እንዲለኝ ተማጽኜዋለሁ።

አለማየሁ በተገደለ በአምስተኛው ዓመት አንድ ወዳጄ አንድ ነገር አውቅ እንደሆነ ጠየቀኝ:: ምንድነው? እለዋለሁ:: የሚከተለውን ነገረኝ:: እነአለማየሁ በተገደሉ ማግስት የደርጉ ጉባኤ በመንግሥቱ ኃይለማርያም ሰብሳቢነት ይሰየምና የአለማየሁ የቅርብ ጓደኞች ተባባሪዎቹ ስለሆኑ አብዮታዊ ፍርድ ይፋፋምባቸው ተብሎ ስማቸው በዝርዝር ይሰፍራል:: የመጀመሪያው የኔ ስም ነው:: አርእስቱ ተዘግቶ ወደ ሌላ ጉዳይ ሊያመሩ ሲሉ ለገሰ አስፋው እጁን ያወጣና ይሄ ነገር ደስ አላለኝም፤ ታደሰ የምትሉትን ሰውዬ ቀይ ይሁን ጥቁር አላውቀውም፤ ግን ስትሉ የምሰማው ባንክ አካባቢ ደኅና እንደያዘልን ነው:: እንደማስታውሰው ሚቹ አለማየሁ ታደሰ ይጠቅማልና ካገር እንዳይወጣ፣ እዚሁ እናስቀረው እንዳለና እንደተስማማን ነው:: አሁን የአለማየሁ ጓደኛ ስለሆነ ብቻ ይወገድ ማለት ለኔ ለኅሊና የሚከብድ ጉዳይ ነው:: አጥፍቷል  የሚባል ከሆነ ጭብጥ ያለው ነገር ይነገረን፤ ያለበለዚያ የንጹህ ሰው ደም እንዳናፈስ መጠንቀቅ ይኖርብናል፤ ጓደኝነት ማለት አብሮ መብላት መጠጣት ከሆነማ ሁላችንስ ከአለማየሁ ጋር በልተን ጠጥተን የለ? ይላል:: ቤቱ ጸጥ አለ:: ሊቀመንበሩ መንግሥቱ ለገሰ ስላነሳው ነጥብ ምን አስተያየት አላችሁ? ብሎ ይጠይቃል:: መልሳቸው ዝም ሆነ:: አስተያየት ከሌላችሁ ለገሰ ባለው ተስማምታችኋል ማለት ነውና ቅድም ያደረግነውን ውሳኔ ሽረናል ይላል::

ኢትዮጵያን ለማስቀደም ደፋ ቀና የምትለዋን ምስኪን ነፍሴን በሕይወት ባላንጣነቱ እንጂ ባዳኝነቱ ዝናው በማይታወቀው በለገሰ አስፋው አማላጅነት የኢትዮጵያ አምላክ አተረፋት::

የሞት ፍርድ እንደተፈረደብኝ፣ ከዚያም ሳላውቀው ማምለጤን አምስት ዓመት ሙሉ አለመስማቴ ክፉ እንዳልሰማ የኢትዮጵያ አምላክ  በጥበቡ ጆሮዬን ዳባ አለበሰው:: በሬ ካራጁ ጋር ይውላል እንዲሉ ከደርግ አባላት ጋር መሥራት፣ ግብር መግባት ቀጠልኩ:: ከመካከላቸው ለክፉ የሚያስቡኝ ከነበሩም ይህ ምንም የማያውቅ ሞኝ፣ ለእርድ የሚወፍር በሬ ብለውኝም ይሆናል:: የመከላከያ ሚኒስትር የነበረው ለማርቼዲስ መኪና መግዣ

የውጭ ምንዛሪ እንድፈቅድለት ጠይቆኝ ይበልጥ አጣዳፊ ጉዳዮች ስላሉ አይሆንም ብዬ ባስቸግረው "ወንድሜ ታደሰ፣ አልገኝ አልክ እኮ" ያለኝ ማን ያውቃል? ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ደርግ መሰዊያ ጠረጴዛ ጎትቶ ወስዶ ወይም አንድ አሳቻ ስፍራ አስጠግቶ ሕዝብን ለመጠበቅ በተረከበው መሣሪያ ሊያንፈራፍረኝ አስቦ ሊሆን ይችላል። በአምስቱ የጆሮ ዳባ ልበስ ዘመን ያሳየሁት አመርታ ከተወጠነልኝ አለመኖር ወደ መኖር ብቻ ሳይሆን ከብሔራዊ ባንክ ምክትልነት ወደ ዋና አዛዥነትም ነበር። ሞት የደገሱልኝ ሰዎች የሹመት ካባ እንዳለበሱኝ ስሰማ ሳላደንቃቸው አላለፍኩም። እነዚህ ሰዎች በተግባር ሞኞች ይሁኑ እንጂ በልብ ግን ቂመኞች ላይሆኑ ይችላሉ አልኩኝ።

ስለደርግ ዘመን የሥራ ሕይወቴና ስለአገራችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ልባዊ ስሜቴን ለመግለጽ የደረስኩት ግጥም "የኢትዮጵያ አብዮት" በገጽ 461 ላይ ይገኛል።

# የብሔራዊ ባንክ ቦርድ

ብሔራዊ ባንክ በ1967 እንደሄድኩ የባንኩ ቦርድ አባላት የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ ነጋሽ ደስታ፣የመገናኛና ትራንስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ተካልኝ ገዳሙ፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ልጅ ሚካኤል እምሩ፣ የባንኩ አዛዥ አቶ ተፈራ ደግፌ ነበሩ። ሊቀመንበሩ የገንዘብ ሚኒስትሩ ነበሩ። የንግድ ሚኒስትሩም አባል የነበሩ ይመስለኛል። የቦርድ ጸሓፊ የባንኩ ምክትል አዛዥ ስለሆነ ጸሓፊነቱን ተረከብኩ።

በአንድ ስብሰባ ላይ የተደረገውን ውይይት በጽሑፍ ለማስፈርና ውሳኔዎቹን ለመመዝገብ ጊዜ እወስንና ብዕሬን አሹዬ እቀመጣለሁ። ማስታወሻ የወሰድኩበትን ወረቀት ብፈልገው አጣዋለሁ። የማይፈለግ ወረቀት መስሎኝ ቀዳድጄ እንደጣልኩት ትዝ አለኝ። ብጥስጣሹ ከቁሻሻ ጋር ተጥሎ መቃጠሉን ሳስታውስ ዐይኔ ፈጠጠ፣ ጉዴ ፈላ። ባወጣ ባወርድ መላ ጠፋ።

ምንም ምርጫ ስለሌለኝ በስብሰባው ላይ የተባለውን ለማስታወስ ልሞክርና ልጻፍ ብዬ ጀመርኩ:: ቀስ በቀስ ሁሉም ነገር መጣልኝ:: ቃለጉባኤውን አርቅቄ ለአባላቱ አሰራጨሁት:: የጎደለውን እነሱ ይሞላሉ ብዬ አሰብኩ:: ረቂቁ ያለምንም ለውጥ ተመልሶ መጣልኝ:: ምን ያህል ደስ እንዳለኝ መገመት ቀላል ነው:: ዝርክርክ ነው ብለው ስሜን እንዳያጠፉት በመፍራት ጉዴን ለቦርድ አባላት መንገር አልፈለግሁም:: የፈጸምኩት ስሕተት ትልቅ ትምህርት አገኘሁበት፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወረቀት ከመጣሌ በፊት አንድ በአንድ አገላብጬ አየዋለሁ:: ለዚህም ሊሆን ይችላል ወረቀቶች አይጠፉብኝም:: አሬን በዳቦ::

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ከመጀመሬ በፊት ረዘም ላለ ጊዜ ወደ ኋላ ጎትቶኝ የነበረው የዛሬ ሐምሳ ዓመት፣ አርባ አምስት ዓመት፣ ሰላሳ እና ሃያ አምስት ዓመት የሆነውን ያለማስታወሻ ድጋፍ እንዴት ላስታውስ እችላለሁ? የሚለው ጥርጣሬ ነበር:: ስለሆነም ያዘነበለው ስሜቴ ባልጀምረው ይሻላል የሚለው ነበር:: በሌላ ረገድ ግን አእምሮን ውለድ ብለው ካስጨነቁት እንደማያሳፍረኝ ከቦርዱ ቃለጉባኤ ያገኘሁት ልምድ ሳያደፋፍረኝ አልቀረም:: መጻፉን ከጀመርኩት በኋላ ረስቻቸው መስለውኝ የነበሩ ጉዳዮች ቀስ በቀስ ስለመጡልኝ በመጻፉ እንድገፋበት ተደፋፈርኩ::

ከዚህ በታች በሚገለጹ ምክንያቶች የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች፣ በተለይም የገንዘብ ሚኒስትሩ፣ ቦርዱን እንዲቆጣጠሩ መደረጉ ከፍተኛ ስሕተት መሆኑን በማስረዳት ለውጥ እንዲደረግ ለረጅም ጊዜ ያላሰለሰ ጥረት አድርጌአለሁ::

ያልተጠበቀ የዋጋ ግሽበት ሳይኖር የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማደፋፈርና ኤኮኖሚው ሚዛኑን ጠብቆ እንዲራመድ ለመደገፍ በኤኮኖሚው የሚሰራጨው ገንዘብ መጠን እንዳያንስ ወይም እንዳይበዛ መቆጣጠርና ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ የብሔራዊ ባንክ መሠረታዊ ኃላፊነት ነው::

የባንኮች ብድር የሚውለው የኤኮኖሚ አውታሮችን ለማስፋፊያ፣ ምርት ለማሳደግና የፍጆት ፍላጎት ለማርካት ነው። የበጀት ጉድለት ለማሟላት መንግሥት ከባንኮች ይበደራል።

በአንድ የሒሳብ ዘመን በኤኮኖሚው ውስጥ የሚሰራጨው ተጨማሪ ገንዘብ መጠኑን የሚወስኑት ዋና ዋና ነቁጦች የባንኮች ብድር መጠን ዕድገትና የውጭ ምንዛሪ ክምችት መቀነስ ወይም መጨመር ናቸው። በሌላ አነጋገር፣ የገንዘብ ክምችት ዕድገት የሚለካው፣ ከሞላ ጎደል፣ የባንኮች ጠቅላላ ብድርና የውጭ ምንዛሪ ክምችት በሚያሳዩት ለውጥ መጠን ነው።

በኤኮኖሚው ውስጥ የሚሰራጨው ተጨማሪ ገንዘብ የሚውለው፣ በአብዛኛው፣ ከአገር ውስጥና ከውጭ ምርትና አገልግሎት ለመሸመት ነው። በመንግሥትና ሕዝብ እጅ ያለው ገንዘብ ከአገር ውስጥ ምርት ጋር ሲነጻጸር በጣም ልቆ ከተገኘ ወይም ካልተመጣጠነ የዋጋ ግሽበት ይከተላል። በተራ አነጋገር ገንዘብ ዋጋውን ያጣል ወይም ይረክሳል። ይህም የሚሆነው፣ በኤኮኖሚስቶች አነጋገር፣ ብዙ ብሮች ጥቂት እቃ እየተከተሉ ስለሚያነፈንፉ ነው። በተቃራኒው፣ ምርት ተትረፍርፎ የገንዘብ ክምችት ዕድገቱ ከታቀደው በታች ሆኖ ከተገኘ የእቃ ዋጋ ከነበረበት ያቆለቁላል። በዚህ ክስተት ሸማች ባጭሩ ጊዜ ሲጠቀም አምራች ትርፍ ይቀንስበታል። አምራች ትርፍ ካላገኘ ደግሞ ሥራውን አያስፋፋም፤ አዳዲስ ፕሮጄክት ለመጀመር አይደፋፈርም። ስለሆነም፣ ሥራ አጥነት ይስፋፋል፣ ውሎ አድሮ ደግሞ የሸቀጣሸቀጥ እጥረት ይከተልና የዋጋ ግሽበት እውን ይሆናል። እንደዚህ ዓይነቱ መዋዠቅ በተቻለ መጠን እንዲቀንስ፣ ማለትም የምርት አቅርቦትና ፍጆታ እንዲጣጣሙ ኤኮኖሚው ሚዛኑን ጠብቆ እንዲያድግና የሥራ እድል እንዲሰፋ ብሎም የሕዝብ፣ የድርጅቶች እንዲሁም የመንግሥት ገቢ እንዲያድግ ሁኔታዎች የተስተካከሉ ወይም የተመቻቹ እንዲሆኑ መጣር የብሔራዊ ባንክ ዋና ተግባሩ ነው።

ለዚህም ባንኩ የሚጠቀምባቸው ዋና ዋና መሣሪያዎች፣ የወለድ መጠን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መወሰን፣ መንግሥት የሚያወጣቸውን የገንዘብ

ሰነዶችን፣ ለምሳሌ ቦንድ፣ መግዛትና መሸጥ፣ የመንግሥት ዋና የኤኮኖሚ አማካሪ ሆኖ ማገልገል ናቸው:: ወለድ ከፍ ሲል ተበዳሪ ይቀንሳል ወይም ለገንዘብ ያለው ፍላጎት ይገታል:: ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ የሚደረገው ኤኮኖሚው ያለመጠን ወይም ሳይመጣጠን አድጎ የዋጋ ግሽበት ከታቀደው በላይ ይሆናል ተብሎ ሲገመት ነው:: የወለድ መጠን ሲቀንስ ደግሞ ተበዳሪ ይበዛል ወይም በርከት ያለ ብድር ለምርትና ፍጆታ ይወሰዳል:: ይህ ፖሊሲ ተግባራዊ የሚደረገው የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ሲደክም መልሶ እንዲያንሰራራ ሲፈለግ ነው::

የመንግሥት ብድር ፍላጎት በጨመረ ቁጥር ለሌሎቹ ጉዳዮች የሚውለው ገንዘብ ያጥራል:: ስለሆነም፣ የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚና ግለሰቦች ለውስኑ ገንዘብ ስውር ጨረታ ውስጥ ስለሚሳተፉ ለሚያገኙት ብድር ከፍ ያለ ወለድ ለመክፈል ይገደዳሉ:: በሌላ አገላለጽ ብሩ ሲመነምንና ፈላጊው ሲበዛ ከፍ ያለ ወለድ የከፈለው ወገን ቅድሚያ ይሰጠዋል ማለት ነው:: የባንክ ወለድ በየጊዜው ከፍ ዝቅ ሳይል በባለሥልጣኖች በሚወሰንበት ሁኔታ፣ በባለሥልጣኑ አመለካከት የብድር ገንዘብ ቅድሚያ ናቸው ለሚባሉ ጉዳዮች ብቻ ይመደብና አስፈላጊ አይደሉም ወይም ቅንጦት ናቸው የሚባሉት የብድር ጥያቄዎች በይደር ይታለፋሉ::

በሥልጣን ላይ ያለ አንድ መንግሥት የሕዝብን ርካሽ ተወዳጅነት ለማትረፍ ወይም ድጋፍ ለማግኘት አስቦ ግራና ቀኝ ገንዘብ የሚረጭ ከሆነ ወይም መጣል የሚገባውን ታክስ ለመጣል ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የጣለውን ታክስ ሆን ብሎ ወይም ከአፈጻጸም ድክመት ሳይሰበስብ ከቀረ መንግሥት ወጪው ከገቢው ይበልጥና ጉድለቱን ለመሸፈን ወደ ባንክ ለብድር መሄድ ይገደዳል:: በዚህ መንገድ የሚሰጥ የባንክ ብድር የመንግሥትን ጥፋት ወይም ድክመት መሸፈኛ ሆነ ማለት ነው:: ባንክም የጥፋት ተባባሪ ሆነ ማለት ነው::

መንግሥት ወጪውን ያለአግባብ አንሮ ወይም ገቢውን ማሳደግ ተስኖት የበጀት ጉድለት ቢከሰት፣ ጉድለቱን ለመሸፈን ወደ ባንኮች ማምራት ልማዱ

ከሆነ ለአምራች ድርጅቶች በብድር መልክ ሊሰጥ የሚችለው ገንዘብ ስለሚያንስ የወለድ መጠን ከፍ ይላል ብለናል። ውጤቱም የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ መገታትና የምርትና የአገልግሎት አቅርቦት መዳከም ይሆናል። በአንድ በኩል የምርትና አገልግሎት አቅርቦት ስለሚዳከም በሌላ በኩል መንግሥት ከገቢው በላይ ከባንክ ተበድሮ የሚያደርገው ወጪ ፍጆትን ስለሚያስፋፋ ጣምራ ውጤቱ የምርትና አገልግሎት ዋጋ ከታሰበው በላይ ከፍ ማለት ይሆናል። ዋጋ ሲጨምር የደመወዝተኛው፣ ጡረተኛው እንዲሁም ሌላ በቋሚ ገቢ ተዳዳሪ የኑሮው ደረጃ ዝቅ እያለ ይሄዳል።

ባንኮች ለተበዳሪ የሚሰጡት ብድር ከግለሰቦችና ድርጅቶች በአደራ የተረከቡትን ገንዘብ ነው። ከብሔራዊ ባንክ መሠረታዊ ኃላፊነቶች አንዱ ባንኮች በአደራ የተቀበሉት ገንዘብ ሳይባክን ለኤኮኖሚ እንቅስቃሴ ማስፋፊያ እንዲውል ማድረግና አስቀማጩ ገንዘቡን ሲጠይቅ ያለምንም ችግር ገንዘቡን መልሶ መውሰድ እንደሚችል ማረጋገጥ ነው። ይህ ተዘንግቶ ባንኮች እንደ መንግሥት ቋቶች የሚታዩ ከሆነ አደጋው ለአስቀማጩ ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚው በጠቅላላ ይሆናል። ቀጥሎም የፖለቲካ ችግር ያስከትላል። ከዚያም የጸጥታ ችግር ይሰለፋል። ችግሮቹ ይጠረቃቀሙና ለአገር አንድነት ጠንቅ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለሆነም፣ የኋላ ኋላ ነገሩ እናቴ እንቁላል ስሰርቅ ዝም ባላልሽኝ ኖሮ መሆኑ የማይቀር ነው።

ብልኅ ሕዝብና መንግሥት ችግር እስኪያመረቅዝ አይጠብቅም። ከስር ከስሩ መፍትሔ ይፈልግለታል። የኛ ሰው እንዳየሁት ግን ችግር ሲነጋ ተኖ ይጠፋለት ይመስል ተሸክሞት ያረፍዳል፣ ይውላል፣ ያመሻል፣ ያድራል። ከአቅም በላይ ሲሆንበት አፍርሶ እንደገና ሀ ብሎ መገንባት ይጀምራል። ዘወትር ውሃ ወቀጣ። ከወደቅንበት እንድንነሳ ከተፈለገ የሚያስፈልገን ገንዘብ ሳይሆን በይበልጥ የአስተሳሰብ ተሐድሶ ነው።

ቦርዱን በተመለከተ፣ ባንኩን ተበዳሪዎች ከተቆጣጠሩት አገሪቱ አደጋ ውስጥ ትወድቃለች እያልኩ አበክሬ እወተውት ነበር። የመንግሥት ባለሥልጣኖች በባንኮች ገንዘብ ይዘዙ ማለት የሕዝብ ገንዘብ እንዲባክንና

የኤኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲዳከም መንገድ ማመቻቸት ነው እል ነበር፡፡ አሠራሩም ባንኩ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ሙሉ በሙሉ የሚጻረር መሆኑን አሳስብ ነበር፡፡

በቦርዱ ውስጥ ተሰይመው ለመንግሥት እርሻዎች የባንክ ገንዘብ ይሰጥ እያሉ ትዕዛዝ ያስተላለፉት በየጊዜው የነበሩት የገንዘብ ሚኒስትሮችና የሥራ ጓደኞቻቸው ነበሩ፡፡ እርሻዎቹ አትራፊ አይደሉም፣ የባንክ ብድር መውሰድ የለባቸውም እያልን በባንኩ በኩል ተቃውሞ ብናነሳም ተዋቸው ለአመላቸው ይለፍልፉ እንባል ነበር እንጂ የባንክ ብድር መለኪያ ስለማያሟሉ ብድር እንዳይሰጣቸው ብለው አይደግፉንም ነበር፡፡ ባጭር አነጋገር ብድር ጠያቂና ፈቃጁ አንድ ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡

እንደመንግሥት እርሻዎች የመሳሰሉ ከሳሪ ድርጅቶች ገንዘባቸውን ማግኘት የነበረባቸው በጀት ተይዞላቸው ከገንዘብ ሚኒስቴር ነበር፡፡ የገንዘብ ሚኒስትሩ ባንክ ቦርድ ላይ ተቀምጦ ባንክን ማሳዘዝ እስከቻለ ድረስ ስለመንግሥት እርሻዎች መሠረታዊ ውሳኔ የሚያደርግበት ወይም እንዲደረግ የሚገፋበት በቂ ምክንያት አልነበረም፡፡ የባንክን ማንቁርት ይዞ የሚፈለገውን ገንዘብ ማስተፋት እስከቻለ ድረስ ከሱ የሚፈለገው ቦርዱ ላይ ቁጢጥ ብሎ መቀመጥ ብቻ ነበር፡፡ ተዉ ነገሩ እማይነጋ መስሏት ዓይነት ነው ቢባሉም በተለመደው የአገራችን የደመነፍስ አባባል መልሳቸው ዛሬን እንለፈው፣ የነገን እግዚአብሔር ያውቃል ነበር፡፡ ስለሆነም የመንግሥት እርሻዎች ዕዳ ክምር ከዓመት ዓመት እያደገ ሂዶ ማንከባለል እማይቻልበት ደረጃ ተደረሰ፡፡

ዋጋ በገበያ ኃይሎች በሚወሰንበት ሁኔታ፣ የውጭ ምንዛሪ ክምችት አነስተኛ ሆኖ ብድር ያለመጠን ካደገ የብር የምንዛሪ ዋጋ በጣም እንዲያቆለቁል መንገድ ይከፈታል፡፡ የብር ውጭ ምንዛሪ ዋጋ በባለሥልጣኖች በሚወሰንበት ሁኔታ ደግሞ፣ በአንድ በኩል የብድር እድገት እንደተገለጸው ከሆነ የውጭ ምንዛሪ ተሟጦ እንዲያልቅ መንገድ ማመቻቸት ይሆናል፡፡ በአሠራር ግን ባለሥልጣኖች አስፈላጊ ናቸው

ለሚሿቸው ጉዳዮች ብቻ የውጭ ምንዛሪ እየፈቀዱ ሌሎች ፍላጎቶች ሳይሟሉ እንዲቀሩ ስለሚያደርጉ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ከተወሰነ መጠን በታች እንዳይወርድ ሊከላከሉ ይችላሉ፡፡ እኔ በባንኩ ባገለገልኩባቸው ዘመናት ስንከተለው የነበረው ስልት ወይም አሠራር በመጨረሻ የተገለጸውን ዓይነት ነበር፡፡

የውጭ ምንዛሪ ክምችትና የብድር መጠን እድገት ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳላቸው በአንድ ወቅት ለመግለጽ ስሞክር የስብሰባው መሪ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ፣ "ታደሰ፣ የውጭ ምንዛሪ ጉዳይና ብድር ለየቅሉ ስለሆኑ ነገሮችን አታሳክርብን" ብሎኛል፡፡ መንግሥት እጅ እጅ እንዳለና አቅጣጫ እንደሳተ ይበልጥ ግልጽ የሆነልኝ ከዚያን ቀን ጀምሮ ነበር፡፡ ሰውዬው ጥሩ አድማጭና ብልህ ቢሆንም ስለሁሉም ነገር ተረድቶ ገብቶታል ለማለት ስለማይቻል ስለማያውቀው ነገር አዋቂ ሆኖ ለመታየት ሲሞክር ሰው አሁንስ አበዛው እያለ ያጉረመርም ነበር፡፡ አብዛኛው ሰው፣ አውቃለሁ ካለ እንተውለት፣ እንደሚያውቀው ያቡካው፣ ይጋግረው፣ ይፈትፍተው እያለ በመንፈስ እየራቀ ሄደ፡፡ በበኩሌ በተሰማራሁበት የሥራ መስክ ሁሉ ነገሮች ቢቻል መልክ እንዲይዙ፣ ካልተቻለም ይበልጥ እንዳይበላሹ ከመጣር ተቆጥቤ አላውቅም፡፡ የማከናውነው የመንግሥቱ ኃይለማርያምን የግል ሥራ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብን ነው በማለት እስከመጨረሻው አዝግሜአለሁ፡፡

መንግሥት የሚያወጣቸው የኤኮኖሚ ልማትና አስተዳደር ፖሊሲዎች፣ የታክስ መጠንና አሰባሰቡ ለበጀት ጉድለት መጠንና ዋጋ መረጋጋት እንዲሁም ኢንቬስተሮች በመንግሥት ላይ ስለሚኖራቸው እምነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላላቸው ብሔራዊ ባንክ ጉዳዩን እየተከታተለ ግድፈት ወይም ድክመት ያለ ሲመስለው ያለምንም ይሉኝታ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የማሳሰብ ኃላፊነት አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር ብሔራዊ ባንክ የሕዝብ ጠበቃ ወይም እንባ ጠባቂ ሆኖ የመንግሥት ገንዘብ አስተዳደርና አጠቃቀም በጥቅል መልኩ ጤናማ መሆኑን የመከታተል ግዴታ አለበት፡፡ መንግሥት

የተሳሳተ አቅጣጫ ሲከተል ያስጠነቅቃል፤ በተዘዋዋሪ ይገስጻል:: ስለሆነም፣ በገንዘብ ሚኒስቴርና በብሔራዊ ባንክ መካከል የማያቋርጥ የግንኙነት ውጥረት ይኖራል:: የግንኙነታቸው ይዘት በመሠረቱ ይህ ሆኖ ሳለ የገንዘብ ሚኒስትሩን የብሔራዊ ባንክ ሊቀ መንበር ማድረግ ታላቅ ስሕተት ነበር::

እላይ እንደተብራራው የብሔራዊ ባንክ የመንግሥትን ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም በተዘዋዋሪም ቢሆን መቆጣጠር ሲኖርበት ነገሩ ተገልብጦ ባንክን መንግሥት በቀጥታ እንዲቆጣጠረው መደረጉ በፍጹም አግባብ አይደለም ብዬ የቦርዱ አባሎች እንዲለወጡ ዘመቻ እንደጀመርኩ አንዳንዶች ሚኒስትሮች ተደፈርን ማለታቸው አልቀረም:: የተደፋሪዎች ማኅበር ያቋቋሙ የሚመስልበት ብዙ ሁኔታዎችን ታዝቤ አልፌአለሁ::

ከኔ በፊት የነበሩት የባንኩ አዛዥም ቢሆኑ ከሚኒስትሮች ጋር መቀያየም ስላልፈለጉ የፕሮጀክቱ ደጋፊ ነበሩ ለማለት አይቻልም:: በበኩሌ እውነትን ጨብጫለሁና በመጨረሻ ማሸነፋችን አይቀርም በሚል እምነት በጉዳዩ ገፋሁበት::

በሌሎች አገሮቸ የገንዘብ ሚኒስትሩ እንኳን የቦርድ ሊቀመንበር ሊሆን ቀርቶ በቦርዱ ውስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር ተወካይ የሚሳተፍ ከሆነ ሐሳብ እንጂ ድምፅ መስጠት አይችልም:: ይህም የሚደረገው የባንኩን ነጻ አሠራር ለመጠበቅና የመንግሥት ጫና እንዳያርፍበት ለመከላከል ነው::

በአገራችን የቦርድ አባላት እነማን ነበሩ? የሚለውን ለመመለስ፣ የዛሬ አርባ አምስት ዓመት ገደማ አቶ ምናሴ ለማ የባንኩ አዛዥ ሆነው ሲሾሙ የቦርዱ ሊቀመንበር እሳቸው ነበሩ:: ቆይቶ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርዱ አባል ይሁኑ የሚል ሐሳብ መጣና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በአባልነት የሚገኙ ከሆነ በሥልጣን ዝቅ ያሉት አቶ ምናሴ ሊቀመንበር መሆን የለባቸውም ተባለና የባንኩ አዋጅ ተሻሽሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቦርድ ሊቀመንበር ተደረጉ:: ዋና ታሳቢ የተደረገው ለውጡ በባንኩ ሥራ ላይ የሚያስከትለው ውጤት ሳይሆን የግለሰቦችን ክብር መጠበቅ ነበር:: በነበረው ፊውዳላዊ

ሥርዓት ለሰዎች የሚሰጠው አክብሮት ‹ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት› ዓይነቱ ክብር አስገራሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ይልቅስ አስገራሚ ይሆን የነበረው ለድርጅታዊ ዓላማ፣ ለሥራ፣ ለውጤታማነት ብሎም የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ቅድሚያ ቢሰጥ ነበር፡፡

የ1966ቱ አብዮት እንደፈነዳ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሌሎችም ባለሥልጣኖች ከሥራ ገበታቸው ላይ ሲገለሉ ቦርዱ መሥራት ከማይችልበት ደረጃ ይደርሳል፡፡ የባንኩ አዛዥ አቶ ምናሴ ታስረው አቶ ተፈራ ተሹመዋል፡፡ እንዳልካቸው መኮንን ጠቅላይ ሚኒስትር ተብሎ ተሹሟል፡፡ እንዳልካቸው ከማን ጋር እንደተመካከረ አይታወቅም፣ የገንዘብ ሚኒስትሩን የባንኩ ቦርድ ሊቀመንበር አድርጎ ሰየመው፡፡ እንዳልካቸው የቋጠረውን ለመፍታት ዐሥራ ሶስት ዓመት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ብታገልም ሳይሳካልኝ ቀረ፡፡

ባንኩን በመጋቢት 1979 ስለቅ ቦርዱ መጠነኛ ለውጥ እንዲታይበት ተደረገ፡፡ ተበዳሪ አበዳሪውን ተቆጣጠረ የሚለውን ቅሬታ ለማስታገስ የመንግሥት እርሻ ሚኒስትርና መንግሥታዊ ንግድ ድርጅቶችን የሚመሩ ሚኒስትሮች ከቦርድ እንዲወጡ ተደረገ፡፡ ጉዳዩ የአገር እንጂ የታደሰ አለመሆኑ እየታወቀ እኔ ባንኩን ለቅቄ እስክወጣ ለውጡ እንዲዘገይ የተደረገው ታደሰን ደስ እንዳይለው ሲባል የተሸረበ ደባ ይመስላል፡፡

ለማጠቃለል፣ መንግሥት ከባንክ ተበዳሪ ስለሆነ የባንኩ ሊቀመንበር የገንዘብ ሚኒስትሩ ወይም ሌላ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን መሆን አይገባውም፡፡ የባንክን የብድር መለኪያ ማሟላት የማይችሉ መንግሥታዊ ድርጅቶች ገንዘባቸውን ማግኘት የነበረባቸው ከመንግሥት እንጂ ከባንክ መሆን አልነበረበትም፡፡ ጉዳዩን ፊት ለፊት ተጋፍጦ መሠረታዊ መፍትሔ መሻት ወይም እንዲፈለግ ግንባር ቀደም ዘመቻ ማድረግ የነበረባቸው የገንዘብ ሚኒስትሮች ባንክ ቦርድ ላይ ተቀምጠው ማዘዝ በማይገባቸው በሕዝብ ገንዘብ ላይ ማዘዛቸው ከፍተኛ ስሕተት ነው፡፡ ስለሆነም አገራችን

መሠረታዊ ስሕተት ፈጽማለች። ስሕተቱ ሙሉ በሙሉ ታርሞ ወደፊት እንዳይደገም ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

# የብር ለውጥ

የአጼ ኃይለሥላሴ ምስል ያለበት የወረቀትና ቅንስናሽ ገንዘብ እንደሚለወጥ ሳይታለም የተፈታ የነበረ ቢሆንም ለውጡ መቼ እንደሚካሄድ የምናውቀው በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበርን። እነሱም ከደርግ ሻለቃ፣ ኋላ ኮሎኔል፣ መንግሥቱ ኃይለማርያምና የኤኮኖሚ መምሪያ ኃላፊ የነበረው ሻምበል ሞገስ፣ ከብሔራዊ ባንክ አዛዡ አቶ ተፈራ ደግፌ፣ ኋላም አቶ ለገሰ ጥቀሄር፣ የግምጃ ቤት መምሪያ ኀላፊ አቶ ምስክር ወልደትንሣኤ፣ የደርጉ የለውጥ ሐዋርያ የመቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ፣ የኮሚቴው ጸሓፊ አቶ መኮንን አበበና እኔ ነበርን። ፕሮግራሙ ለዐሥራ ስምንት ወራት በምስጢር ሲካሄድ የደርጉ ሊቀመንበር ተፈሪ በንቲ እንኳ እንዲያውቁ አልተደረገም ነበር። በደርግ በኩል ጉዳዩን ከላይ ሆኖ የሚመራው መንግሥቱ ነበር።

ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ ግንባር ለግንባር ተገናኝተን መወያየት የቻልነው በገንዘብ ለውጥ ሳቢያ ነበር። ስለሰውዬው ምን ታስታውሳለህ? ተብዬ ብጠይቅ በአእምሮዬ ተቀርጾ የቀረው ቀዳዳ ካኒቴራው ነው። አንድ ቀን ስለብር ለውጥ ሂደት ለማስረዳት ቢሮው እንደሄድኩ ከዩኒፎርሙ ሥር የለበሰው አንገተ ሙሉ ካኒቴራ አንገቱ ከሌላው ሰውነቱ በከፊል ተለያይቶ አየሁና ልቤ ተነካ። እነዚህ ሰዎች እውነትም የራሳቸውን ጥቅም ለማጋበስ ሳይሆን የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ የመጡ ናቸውና ጥረታቸውን የመደገፍ ኃላፊነት አለብኝ ብዬ ቁርጠኛ ውሳኔ አደረግሁ።

በመጀመሪያዎቹ ዓመታት ሻለቃ መንግሥቱን ብዙዎቻችን አንተ ነበር የምንለው። እነአለማየሁ ከተገደሉ በኋላ አንድ ቀን የባንኩ የለውጥ ሐዋርያ መቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ ቢሮዬ ድረስ ይመጣና አንድ መመሪያ ወጥቷል፣

እንድታውቀው ይለኛል፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ሻለቃ መንግሥቱን አንቱ እንድንል ታዘናልና ይህ ሁላችንንም ይመለከታል አለኝ፡፡ በመንፈስ መንግሥቱን እንድቀርብ አድርጋኝ የነበረችውን ያቺን ቀዳዳ ካኒቴራ ከአእምሮህ ንዳ አውጥተህ ጣላትና ሳትጠጋ እራቅ ብለህ ቁም ተብሎ እንደተነገረኝ አድርጌ ወሰድኩት፡፡

ገንዘቡን ለማተም ጨረታውን አሸንፎ ኮንትራት የወሰደው ቶማስ ደላሩ የሚባለው የእንግሊዝ ኩባንያ ነበር፡፡ ብሩ ሲታተም ለማየት ሻምበል ሞገስና እኔ ወደ እንግሊዝ አገር አብረን ሄደናል፡፡ በባንኮች ተጠራቅሞ የነበረ የውጭ አገር ጥሬ ገንዘብ ገቢ ለማድረግ በዙሪክ ስዊዘርላንድ በኩል አድርገን እግረመንገዳችንን አለፍን፡፡ በዘመኑ እያንዳንዱ የደርግ አባል እራሱን እንደ ርእሰ ብሔር ይቆጥር ነበርና ለዩኒየን ባንክ ኦፍ ስዊዘርላንድ ስለጉብኝታችን ስናስተላልፍ ርእሰ ብሔር ለመቀበል ተዘጋጁ ብለን እንደሆን ባላስታውስም የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆቴላችን ድረስ በመምጣት አንድ ሬስቶራንት ወስዶ ግብዣ አደረገልን፡፡ ሰውዬው ሾፌሩ ጎን ተቀምጧል፡፡ ሻምበልና እኔ ከኋላ ነን፡፡ ወደ ሬስቶራንት የሄድንበት መንገድ እንዲጋጣሚ ይሁን ወይም ሥራ አስኪያጁ ሆን ብሎ ለሹፌሩ አስጠንቅቆት እንደሆነ አላውቅም ባንኮች በብዛት በተሰባሰቡበት አካባቢ ነበር፡፡ ሥራ አስኪያጁ በጣቱ እየጠቆመ ይህ እንዲህ የሚባለው ባንክ ነው፣ ያ ደግሞ ምንትስ ባንክ ነው እያለ ያሳየናል፡፡ በእርግጥም በጣም ብዙ ባንኮች እንዳሉ አየን፡፡ ሻምበል ሞገስ ያየውን እንዲህ ብሎ አጠቃለለው፣ "ሁዌር ዜር አር ሜኒ ቲፍስ ዜር አር ሜኒ ባንክስ" ብዙ ሌቦች ባሉበት ስፍራ ብዙ ባንኮች ይኖራሉ አለና ባገሩ ባንኮች ጳጳስ ፊት ያልተጠበቀ ቦምብ አፈነዳ፡፡ ምነው መሬት በዋጠኝ ኖሮ የሚለው አባባል ትርጉም በውል የገባኝ የዚያን ዕለት ነው፡፡ ከዚያ ነገሩ ሁሉ ተበላሸ፡፡ ምሽቱ እንደምንም ብሎ ተገባደደና ወደ ማደሪያችን አመራን፡፡ ሥራ አስኪያጁ አፍሪቃዊ ባየ ቁጥር ሻምበል ሞገስን እያስታወሰ ይበረግግ እንደነበር መገመት ይቻላል፡፡ ሻምበል ሞገስ እራሱን ሳንሱር ባለማድረግ የታወቀ ስለነበር ለምክክር ደርግ ጽሕፈት ቤት ቢሮው

ስሄድ ድምጹን ዝቅ እንዲያደርግና ጉዳዩ በምስጢር የተያዘ መሆኑና ሌላ የደርግ አባል መስማት እንደሌለበት አልፎ አልፎ ማስታወስ ነበረብኝ።

የፕሮግራሙ መደምደሚያ ወይም የገንዘቡ መለወጥ ይፋ የሚሆንበት ቀን ሲቃረብ ጉዳዩን ሌሎችም ሰዎች እንዲያውቁት ማድረግ ግድ ሆነ። ለምሳሌ የገንዘቡን ለውጥ ሕጋዊ ለማድረግ የሚወጣውን አዋጅ እማርቀቁ ላይ የፍርድ ሚኒስትሩ አቶ አማኑኤል አምደሚካኤል ከኛ ጋር እንዲሠሩ አስፈለገ። ከዚያም ገንዘቡን ከለንደን አዲስ አበባ ለማጓጓዝ የአየር መንገዱ ኃላፊዎች ማወቅ ነበረባቸው። ስለሆነም፣ ካሥራ ሰባት ወራት በላይ በከፍተኛ ምስጢር የጠበቅነው ጉዳይ ያለወቅቱ ይፋ ሊወጣብን ነው ብለን በጣም ሰጋን። በበኩሌ ደኅና እንቅልፍ ከሸሸኝ ውሎ አድሮ ነበር። ለስሙ በባንኩ በኩል የፕሮግራሙ አስተባባሪ የባንኩ አዛዥ ይሁን እንጂ በኃላፊነት የማስተባብረውና ሥራውን የምመራው እኔ ስለነበርኩ ምስጢሩ ሳይባክን እስከመጨረሻው መድረስ ከተቻለ የሚያጎናጽፈን ደስታ ከፍተኛ እንደሆነ አውቅ ነበር።

የወረቀቱ ገንዘብ መለወጫ ጊዜ ሲቃረብ ቅንስናሽ ገንዘቦችን ለማሠራት ጨረታ አወጣን። በጨረታው እንዲሳተፉ የጨረታውን ሰነድ በምስጢር ልከን የጋበዝናቸው ስማቸው በዓለም የታወቀ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ የሚገኙ የቅንስናሽ ገንዘብ ቀራጮችን ወይም ሠሪዎችን ነበር። በቀጥታ ከኛ ጋር እንጂ አገር ውስጥ በሚገኙ ወኪሎቻቸው አማካይነት እንዳይቀርቡን ጥብቅ ትእዛዝ ሰጠናቸው።

አንድ ቀን አንድ ሰው ግምጃ ቤት መምሪያ ስልክ ይደውልና የጨረታውን ሰነድ እንዴት ነው የማገኘው? ብሎ ይጠይቃል። ስልኩን የተቀበለው ኃላፊ ስለጉዳዩ የሚያውቀው ነገር እንደሌለ ይነግረዋል። በእርግጥም ሊያውቅ የሚችልበት መንገድ አልነበረም። ደዋዩም መልሶ፣ ምን ትቀልዳለህ? ጀርመን ያለው ወካያችን የላከልንን ቴሌክስ ላሳይህ እችላለሁ ይለዋል። ኃላፊው ይደናገጥና ወደ አቶ ምስክር ቢሮ ወዲያውኑ ሄዶ ሁኔታውን ይነግራል። አቶ ምስክር ስለጉዳዩ እሱም ምንም የሚያውቀው እንደሌለ

አስምስሎ ሠራተኛውን ከሸኘ በኋላ ወዲያውኑ እኔና መቶ አለቃ ፈቃደ ቢሮ ድረስ መጥቶ ይነግረናል:: እጢአችን ዱብ አለ:: የሳንቲም ጨረታ ጉዳይ ከተደረሰበት አንድና አንድ ሁለት ተብሎ የወረቀቱ ገንዘብ መውጣትም ተደርሶበታል ማለት ነው አልንና በጣም ተረበሽን::

ነገሩን የደረሰበት አቶ ገብረየስ ቤኛ፣ የአማልጋሜትድ ኩባንያ ዋና ሥራ አስኪያጅ ነበር:: ሰውዬው ጥቅም የሚያገኝበትን ሥራ አሽትቶ በመድረስ በከተማው ተወዳዳሪ ያልነበረው ሰው እንደሆነ ስለሚታወቅ ብዙም አልገረመንም ነበር:: ቀደም ብሎ ገንዘብ እንደሚለወጥ በመገመት ጀርመን ያለው ሳንቲም ቀራጭ ኩባንያ ውክልና ለሱ እንዲሰጠው ጠይቆ አገኘ:: ከሌሎችም ገንዘብ ሠሪዎች ጋር ተመሳሳይ ውክልና አግኝቶ ከሆነም ምንም አያስደንቅም::

ስለተፈጠረው ሁኔታ ጥቂት ከተመካከርን በኋላ ለአቶ ገብረየስ መቶ አለቃ ስልክ እንዲደውልለትና ሳይውል ሳያድር እኔ ቢሮ እንዲመጣና እንድናሸብረው ወሰንን::

አቶ ገብረየስ ስለጉዳዩ የሰሙትን ሠራተኞችን ሁሉ ይዞ እኔ ቢሮ ድረስ እንዲመጣ ተነገረው:: ጸሓፊውን ብቻ ይዞ መጣ:: የውጭ አገር ሰው እንደነበረች ትዝ ይለኛል:: ሌላ ሰው እንደማያውቅ አረጋገጠልን:: ያልነው እንደሚከተለው ነበር:: በል እንግዲህ የጠራንህ ለከፍተኛ ጉዳይ ነው፣ የሳንቲም ጨረታ መውጣቱን ከዚች ደቂቃ ጀምሮ አልሰማህም፣ ጸሓፊህም አልሰማችም፣ የተቀበልካቸውን መልዕክቶች ሁሉ ልክ ቢሮ እንደተመለስክ እንድታስወግድ፣ ጀርመን ለሚገኘው ወካይህ መልዕክት ልከህ ውክልናህ እንዲሰረዝ እንድትነግር፣ ምናልባት የሳንቲም ጨረታ ወጥቷል ተብሎ ከተማ ውስጥ ቢወራ ወይ ቢናፈስ ምንጩ አንተ እንደሆንክ ታውቆ መንግሥት በክፉ እንደሚፈልግህ እንድታውቅ አልንና አስፈራራነው:: ሰውዬው በልበ ደንዳናነት የታወቀ እንደሆነ እናውቅ ስለነበር ምን እንደሚል በጉጉት ተጠባበቅን:: መልሱን ወድያው አገኘነው:: ላቡ በግንባሩ

ላይ ችፍ አለ፤ ነጭ መሐረብ አውጥቶ እየደጋገመ ሲጠርግ ስናይ እንደተሳካልን አወቅን:: እየደጋገመ ወይ ጉድ ማለትና መቀመጫው ላይ መንቆራጠጥ ብቻ ሆነ:: ያልነውን ሁሉ እንደሚፈጽም ቃል ገብቶ ሄደ:: በማግስቱ ለጀርመኑ ኩባንያ የላከውን መልዕክት አምጥቶ አሳየን:: ከዚያም ሽው የሚል ነገር ካለ ብለን ጆሯችንን ቀስረን ለብዙ ቀናት ተጠባበቅን:: ምንም የተለየ ነገር ሳይመጣ ቀረ:: እፎይ አልንና ተረጋጋን::

የብር መለወጥ ምስጢር ቢወጣ ኖሮ ገንዘብ ያለው ሰው እቃና የውጭ ምንዛሪ ለመግዛት በብዛት ስለሚሰማራ ሰው ሰራሽ የእቃ እጥረት ደርሶ፣ ዋጋ ያለመጠን ጋሽቦ፣ የብር ዋጋ ወይም ተቀባይነት መሬት ላይ ወድቆ ኤኮኖሚው አፈር ይግጥ እንደነበር ግልጽ ነው:: የተያያዝነው ትግል ይህ ክስተት እውን እንዳይሆን መከላከል ነበር:: አቶ ገብረየስ ላቡን ያንጠፈጠፈው ለኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ደኅንነት ሲል ስለነበር ብዙም እንዳልተቀየመን ተስፋ እናደርጋለን::

የብር ለውጥ ፕሮግራም በንድፍ ደረጃ ለማጠናቀቅ አንድ በቀላሉ ያልፈታነው ወጭው እንዴት ይሸፈን? የሚለው ጉዳይ ነበር:: ዋናው ወጪ ብሩን የማሳተሚያ ሲሆን ጭነቱን ከለንደን ወደ አዲስ አበባ በአውሮፕላን ለማጓጓዝ የሚጠይቀው ወጪም ቀላል አልነበረም:: ጭነቱ ብዙ የአውሮፕላን ምልልስ የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል:: አገር ውስጥ ደግሞ በመላው ኢትዮጵያ የብር የመለወጫ ጣቢያዎችን አቋቁሞ ለሦስት ወር ሙሉ ሥራውን ለማካሄድ ወጪው በቀላል የሚገመት አልነበረም:: ጠቅላላው ወጪ ከ38 ሚሊዮን ብር በላይ እንደነበር ትዝ ይለኛል:: ሥራው በዘመቻ መልክ እንዲሠራ ባይደረግ ኖሮ ሒሳቡ ከዚህ በላይ እንደሚሆን ግልጽ ነበር::

ወጪው ስለሚሸፈንበት መንገድ አንድ ሐሳብ አቀረብኩ:: አብዮቱ ያስበረገገው ብዙ ሰው ገንዘቡን ከባንክ አውጥቶ በየቤቱ አስቀምጦ ነበር:: በየጊዜው ወደባንክ አስገብቶ እንዲያስቀምጥ ባለገንዘቡን ብንመክርም ብዙም እንዳልሰማን እናውቃለን:: እኔ ያቀረብኩት ሐሳብ ሁለት ወሮችን ባንድ

ድንጋይ መግደል እንዲሉ በባለ አምሳና መቶ ብር ኖቶች ላይ 8 በመቶ የገንዘብ መለወጫ ወጭ መሸፈኛ ሒሳብ ብናስከፍል ወጪያችንን ሁሉ ከመሸፈን ባሻገር ከባንክ ውጭ ገንዘብ ማስቀመጥ ጥሩ አለመሆኑን መልዕክት ለማስተላለፍ ያስችለናል አልኩኝ፡፡ ኮሚቴያችን በሐሳቡ መስማማት ሳይችል ቀረ፡፡ የሐሳቡ ዋና ተቃዋሚ የባንኩ አዛዥ አቶ ለገሰ ነበር፡፡ የፕሮግራሙ የበላይ አስተባባሪ ሻላቃ መንግሥቱ ዘንድ ሄደን ሁለታችንም ወገኖች በየበኩላችን ያለንን አስተያየት አስረዳን፡፡ ታክሱ ይጣል የሚለው ሐሳብ ተቀባይነት አገኘና በሥራም ላይ ዋለ፡፡

ባወጣነው ፕሮግራም መሠረት ስለለውጡ ለሕዝብ በይፋ ከመታወጁ ጥቂት ሰዐታት ቀደም ብሎ መጀመሪያ የሚነገረው ለደርግ አመራር አባላትና ሚኒስትሮች ነበር፡፡ ጉዳዩ ይፋ ሊደረግ አንድ ቀን ሲቀር ጊዜው የተመደበው ለሕዝብ የሚነገሩ መግለጫዎችን ለማጠናቀቅ ነበር ፡፡ ታዲያ ምን ይሆናል፣ ሻምበል ሞገስ ኮሚቴውን ሳያማክር ወይም አስቀድሞ ሳያስጠነቅቅ ከሻለቃ መንግሥቱ ጋር ተመካክሮ የደርግ ኀላፊዎችንና ሚኒስትሮችን በስሕተት ከታሰበው አንድ ቀን አስቀድሞ ስብሰባ ይጠራና በስፍራው ተገኝተን ስለለውጡ መግለጫ እንድንሰጥ ይጠይቀናል፡፡ አንዴ ስሕተት ተፈጽሟል፤ ምንም ማድረግ አይቻልምና ኑና አስረዱ ተባልን፡፡ መግለጫዎቹ ገና አልተጠናቀቁም፡፡ ለደርግ አባላትና ለሚኒስትሮች ገለጻ ከተደረገ በኋላ ወድያውኑ ስለፕሮግራሙ ሕዝብ እንዲያውቀው ካልተደረገ በሚቀጥለው ቀን ከፍተኛ ውዥንብር እንደሚፈጠር ስለገመትን መግለጫውን የዚያኑ ዕለት ማታ ለማድረግ ወሰንን፡፡ መግለጫዎቹን ለማጠናቀቅ የቀረን ቢበዛ ከሦስት ሰዓት አይበልጥም ነበር፡፡

የደርጉ ሊቀመንበር ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ስለጉዳዩ ሳያውቁ ይህን ያህል ጊዜ መቆየቱ እንዳሳዘናቸው ተናግረው አሁን ወደኋላ የምናይበት ጊዜ ሳይሆን ፕሮግራሙ እንዲሳካ የምንተባበርበት ቀውጢ ወቅት ስለሆነ ሁሉም ትብብሩን እንዲለግስ አሳሰቡ፡፡ ከሚኒስትሮቹ መጀመሪያ የተናገረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ክፍሌ ወዳጆ ነበር፡፡ ባደረግሁት ገለጻ የዲፕሎማቲክ

ከረጢቶች ለሦስት ቀናት እንዳይታደሉ፣ ከረጢቶቹ ካልተሰጡኝ ብሎ የሚያስቸግር ኤምባሲ ወይም ሌላ የዲፕሎማቲክ መብት የተሰጠው ድርጅት ካለ ከረጢቱ ተፈትሾ ይለቀቅለታል የሚል ነበር። የፕሮግራሙ ድንጋጌ ዓላማ ሕግን ጥሶ ድንበር ዘሎ ከአገር የወጣ ባለአምሳና መቶ ብር ኖት ካለ ኖቶቹን በዲፕሎማቲክ ከረጢቶች አስገብቶ የመለወጥ ሙከራ ሊደረግ ስለሚችል እንደዚህ ዓይነቱን ደባ መቋቋም ይገባል በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ ነበር።

ዲፕሎማቲክ ኮረጆ መፈተሽ ዓለም ከተስማማበት ውጭ ነው ብሎ ሚኒስትሩ የከረረ ተቃውሞ አነሳ። ፕሮግራሙ በመሠረቱ የሚለው ዲፕሎማቲክ ፖውቾችን ማደል ለሦስት ቀን ይዘግይ ነው እንጂ ይፈተሹ አይደለም ብለን ብናብራራም ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚከተለው መደበኛ አሠራር መለወጥ የለበትም ብሎ ከአቋሙ ፍንክች አልል አለ። ሆኖም፣ ተቃውሞው ውድቅ ተደረገበት። ያተረፈው ነገር ቢኖር ቢያንስ የኔን ትዝብት ነበር።

በደርግ ዘመን ካየኋቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በአቋሙ የአቶ ክፍሌ ተቃራኒ የነበረው ዶክተር ኮሎኔል ፈለቀ ገድለ ጊዮርጊስ ነበር። የአገር ጥቅም የተነካ ከመሰለው በግንባር ከሚሰለፉት ጋር ነበር። በዚህ ረገድ ምዕራብ ወይም ምስራቅ ሳይል ነጎድጓዳማ ድምፁንና ርቱዕ አንደበቱን አንዳንዴም የጭቃ ጅራፉን መዞ ይወጣ ነበር።

ብዙ ዲፕሎማቶች በውጭ ምንዛሪና ሸቀጣሸቀጥ ጥቁር ገበያ ንግድ ውስጥ ተዘፍቀው ስለነበር ሁኔታውን መልክ ለማስያዝ የክፍያ ሥርዓት ደንብ ስናወጣ ባንደኛ ደረጃ ደጋፊያችንና ጠበቃችን ፈለቀ ነበር። አንዳንድ ሚኒስትሮች ይሄ ነገር አላማረንም፣ ከሌሎች አገሮች ጋር ሊያጣላን ይችላል እያሉ ስጋታቸውን ሲገልጹ ፈሌ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እኔ ነኝ? ወይስ እናንተ? ይላቸው ነበር። እንደሱ አመለካከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ኀላፊነትና ተግባር ያገሩን ጥቅም ማስጠበቅና አገሩን ከውጭ ከሚመጣ ጉዳት መከላከል ነው። ሆኖም፣ አልፎ አልፎ እናንተ

ኤኮኖሚስቶች አስቸገራችሁን እያለ ከመወረፍም አይመለስም ነበር:: ቢሆንም፣ ፈለቀ ብዙ ገጽታዎች በላዩ የተቀነባበሩበት ሰው መሆኑን ስላየሁ አልፎ አልፎ በሚያሳያቸው ለየት ያሉ ጸባዮች ብዙም አልደነቅም ነበር:: በይበልጥ የማስታውሰው ባገር ጥቅም ጠበቃነቱ ነው:: ተዉ እንዲህ ማድረግ ወይም አለማድረግ ከሶሻሊስቱ ጎራ ጋር ያጣላናል በሚባልበት በዘመነ አድርባይነት ሽንጣቸውን ገትረው ላገር ጥቅም ከሚከራከሩት ውስጥ ፈለቀ ጠፍቶ ወይም ጓዳ ተሸሽጎ አያውቅም::

ብዙዎቹን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች እንዳየኋቸው ግን ተግባራቸውን የሚያዩት የውጭ አገር ሰዎችን መሸንገል ወይም መደለል እንደሆነ ነው:: ዋናው ትኩረታችን የውጭ አገር ሰዎች ስለኢትዮጵያ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው ይላሉ:: ውጭ ያሉትም ኤምባሲዎች ቢሆኑ ይህንኑ ፈለግ ተከትለው የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ይሠራሉ እንጂ የአገርን ኤኮኖሚ ለማዳበር በሚረዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ሲሰማሩ ብዙ አይታዩም:: ኤኮኖሚ ነክ ጉዳዮችን እንደ ሥራቸው አድርገው አይወስዱትም:: በእንዲህ ዓይነቱ ተግባር መሰማራት እንደ ክብረነክ የሚቆጥሩም አይጠፉም:: ይህ አጉል አስተሳሰብ ምናልባትም የፊውዳሊዝም ቅሪት ወይም ቅርስ ሳይሆን አይቀርም:: በምርት እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ እንደዝቅተኛ ሥራ በሚቆጠርበት አገር ዲፕሎማቶች ነን ባዮች ኤኮኖሚስቶችን ቢያጥላሉ አስጋራሚ ሊሆን አይችልም:: እንዲያውም አስገራሚ ይሆን የነበረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ኢትዮጵያ ከውጭው ዓለም የምታገኘውን ጥቅም የማስፋፊያ፣ የማዳበሪያና የማስጠበቂያ ማእከል ባጭር ጊዜ ማድረግ ቢቻል ነበር::

ወደ ብር ለውጥ እንመለስና ለደርግና ለሚኒስትሮች የምናደርገው ገለጻ እንደተጠናቀቀ ከባንክ የመጣነው የገንዘብ ለውጥ የሚገልጸውን ጽሑፍ ለማጠናቀቅ ወደ ቢሮ ስንደረደር፣ ከፍተኛ ምስጢር ተብሎ የተነገራቸው አንዳንድ የደርግ አባላት ያላቸውን ባለአምሳና መቶ ብር ኖቶች ለመለወጥ

በየቦታው ተሰማርተው እንደነበር በማግስቱ ሰማን። ይባስ ብሎ ምስጢሩን ለቅርብ ወዳጆቻቸውና ዘመዶቻቸው የነገሩ እንደነበሩም ሰምተናል።

ለውጡ በይፋ ሊታወጅ ሁለት ወይም ሦስት ቀናት ሲቀሩት ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ለመሄድ የተነሳችው ታናሽ እህቴ ጽጌ ቢሮዬ ትመጣና ለዝግጅት የሚረዳት ገንዘብ እንድሰጣት ትጠይቀኛለች። ቼክ ጻፍኩና ካሽ አውጥቶ እንዲያመጣልኝ አንድ ሰው ወደ ንግድ ባንክ ላክሁ። ገንዘቡ ሲመጣ ኖቶቹ ባለአምሳ ነበሩና ፈገግ አልኩ። እህቴ ምነው? አለችኝ። አይ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው አልኳትና አድበስብሼ አለፍኩት። ብፈልግ ኖሮ ምን ዓይነት ኖቶችን እንደምፈልግ በቼኩ ጀርባ ላይ ምልክት ላደርግ ወይም የላክሁትን ሰው የሚያመጣልኝ ኖቶች ካምሳ ብር በታች እንዲሆኑ ልነግረው እችል ነበር። ነገር ግን ከዚህ ቀደም እንዲህ አድርጌ ስለማላውቅ ብቻ ሳይሆን በአምሳ ብርና መቶ ብር ላይ ያገልግሎት ዋጋ እንደሚከፈል እያወቅሁ ከክፍያው መሸሽ አግባብ አይደለም ተባብለን ከጎሊናዬ ጋር ስለተማመንን ነበር። እህቴ በተቀበለችው ገንዘብ ላይ ስምንት በመቶ የአገልግሎት ሒሳብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከፍላለች።

መግለጫውን ለማጠናቀቅ የደርግ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ኮሎኔል ዐስራት መጥቶ ነበር። በእጅ የተረቀቀው ጽሑፍ በጣም ብዙ ስፍራ ላይ በእመጫት የተጨናነቀ፣ ስርዝ ድልዝ የበዛበት ስለነበር ላረቀቅነውም ቢሆን በቀላሉ የሚነበብ አልነበረም። የማስታወቂያ ሚኒስቴር የፍየል ወጠጤ መግለጫ አንባቢ አቶ አሰፋ ይርጉ ተጠርተው መጡና ጽሑፉ ተሰጣቸው። በሙሉ ተናበን ከጽሑፉ ጋር ለመተዋወቅ ጊዜ ስላልነበረን ወረቀቱን በኪሳቸው ከትተው ወደ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ራዲዮ ጣቢያ ብር ብለው ሄዱ። በሁለት ሰዓት ያንን የተወላገደ ጽሑፍ እንዴት አድርገው አቃንተው ሊያነቡት ነው? ብለን በከፍተኛ ስጋት መጠባበቅ ጀመርን። እንዳይደርስ የለምና ሰዓቱም ደረሰ። የሰማነውን ጆሮአችንን ማመን አቃተው። ሰውዬው አስገራሚ ፍጡር ናቸው፤ አንድ ሳያዛንፉ በትክክል መውረድ ብቻ ሳይሆን የተወላገደውን ሁሉ እያቃኑ አነበቡት። እላይ እንደገለጽኩት ይህ ሁሉ

መጠበብና መጨነቅ የመጣው ፕሮግራሙ በስሕተት በሃያ አራት ሰዓታት እንዲያጥር በመደረጉ ነበር።

መግለጫው ከተነበበ በኋላ በሕይወቴ እንደዚያን ቀን እፎይታ ተሰምቶኝ አያውቅም ብል ብዙም ከእውነት የራቀ አይሆንም። ዐሥራ ስምንት ወራት ሙሉ በምስጢር ያረገዝነውን ፕሮጀክት ዱብ አድርገን ስንገላገለው ከመጠን በላይ ደስ አለኝ። ምስጢር ባክኖ ጉድ ሊፈላ ነው የሚለው ስጋት ከትከሻችን ተሽቀንጥሮ ወደቀልን። ሥራውን መርቼ እዚህ በማድረሴ እጅግ ደስ አለኝ። የኮሚቴው አባላት ድላችንን ለማክበር ራስ ሆቴል ሄደን ትንሽ ተጎነጨን። ጋባዡ እኔው ነበርኩ ይመስለኛል።

መግለጫው በወጣ ማግስት ወይም ወደዚያው አካባቢ የአሜሪካን አምባሳደር ወይም ካውንስለሩ ዋናው አዛዥ ቢሮ ድረስ ይመጣና ገንዘብ የመለወጡ እቅድ በምስጢር ተይዞ እዚህ መድረሱ እንዳስደነቃቸው ገልጾ ገንዘብ የመለወጥ እቅዳችሁን ሌላው ቀርቶ የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት እንኳ አያውቀውም ነበር አለ። ሲ አይ ኤስ? ተብሎ ቢጠየቅ ኖሮ እሱም እንደዚሁ ማለቱ የማይቀር ነበር ብዬ እገምታለሁ። ስለስቴት ዲፓርትመንት ሲወሳ አንድ ትዝ የሚለኝ ነገር አለ። ከኮለምቢያ ዩኒቨርስቲ ትምህርቴን እንደጨረስኩ የዩኒቨርስቲው ውጭ አገር ተማሪዎች ማእከል አንድ ፎርም እንድሞላ ሰጥቶኝ ነበር። ከጥያቄዎቹ አንዱ አገርህ ስትመለስ ለአሜሪካዊ ድርጅት ለመሥራት ትፈቅዳለህ? የሚል ነበር። የሰጠሁት መልስ ስኮላርሺፕ የሰጣችሁኝ ተምሬ ያገሬን ሕዝብ እንድረዳ እንጂ ላሜሪካ እንድሠራ አይደለም የሚል ነበር። ተማሪው የሚሰጠውን መልስ ዐይተው ለመልማይ ድርጅቶች፣ ለስለላ ድርጅቶች ጭምር፣ ስም ያስተላልፉ እንደሆነ አላውቅም። በሌላ በኩል ደግሞ አዎንታዊ መልስ የሰጠ ሁሉ የሲ አይ ኤ ቅጥረኛ ወይም ተባባሪ ሆኗል ለማለት ያስቸግራል።

መግለጫው ከወጣ በኋላ ገንዘቡን ከለንደን ማጓጓዝ፣ የመለወጫ ጣቢያዎች መክፈት፣ ሰው መደልደልና ከዚያም ገንዘብ ወደየጣቢያው መውሰድ

በሙሉ ኃይል ተያያዝነው፡፡ ሥራው በሚገባ ተካሄደልን፡፡ ገንዘብ የመለወጡ ሥራ በጥቅምት 5 ተጀመረና ጥር 4፣ 1969 ተጠናቀቀ፡፡

የባንኩን ገንዘብ በጣምራ ኃላፊነት ተረክበው ይይዙ፣ ያከፋፍሉ፣ እንደገናም ይረከቡ የነበሩት በአቶ ምስክር ወልደትንሣኤ የበላይ አስተባባሪነት አቶ ተሰማ ደምሴና አቶ በላይ ብናልፈው ነበሩ፡፡ ሦስቱም ኃላፊዎች እንከን የማይወጣላቸው ወይም የተዋጣላቸው፣ ሥራቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁና ኃላፊነታቸውን በሚገባ የሚወጡ ስለነበሩ ለፕሮግራሙ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ከዚያ በፊት አቶ በላይን እንደፌዘኛ አድርጌ እወስደው ስለነበር ወርቅ በእሳት ይፈተናል እንዲሉ የብር ለውጥ ፕሮግራም ማንነቱን አረጋገጠለት፡፡

ገንዘብ ወደ ማእከላዊ ማከማቻዎች ስናጓጉዝ አንዱ የጭነት መኪና መንገድ ይሳት ወይም ይሰናከል አላስታውስም በተባለው ሰዓት በታሰበለት ስፍራ ሳይደርስ ይቀራል፡፡ አንድ መኪና ጭነት ሙሉ ገንዘብ ጠፋ ወይ ተሰረቀ ተብሎ ተወራ፡፡ የአካባቢው አስተዳዳሪዎች ደርግ ቢሮ ይደውሉና አንድ መኪና ከነተሳቢው የተጫነውን ብር እንደተሸከመ ይዞ ጠፍቷል ብለው ይነግሯቸዋል፡፡ አሉባልታውን የተቀበለው የደርግ ባለሥልጣን ይደውልልኝና ይህ ሁሉ ገንዘብ ሲጠፋ የት ነበራችሁ? ብሎ ቁጣ በተቀላቀለ ድምፅ ይጠይቀኛል፡፡ ስለመጥፋቱ የማውቀው ነገር የለም፣ ለማንኛውም አጣርቼ እደውልልሃለሁ እለዋለሁ፡፡ መኪናው ከነገንዘቡ ዘግይቶ መድረሱን አረጋገጥኩ፡፡

ታዲያ ስላካሄድነው ወደርየለሽ ፕሮግራም ጥሩ ሥራ ሠርታችኋል ብሎ ከመንግሥት አካባቢ አንድም የምስጋና ቃል ያቀረበልን ሰው አልነበረም፡፡ ሌላው ቀርቶ የባንኩ ቦርድ እንኳ ስለተሠራው ሥራ የምስጋና ቃል በቃለጉባኤ እንዲሰፍር ማድረጉን አላስታውስም፡፡

በዚህ አጋጣሚ ስለ ኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ሥነልቦና በውል የተረዳሁት አንድ ነገር አለ፡፡ ዋና ተግባራቸው የሚመስላቸው የበታቾቻቸውን በዐይነ

ቁራኛ መጠበቅና መቆጣጠር ነው። የሚቀድማቸው፣ የበታች ሲያጠፉ መቅጣት፣ ማዋረድ፣ ትቢያ ላይ ማንከባለል፣ ስብእናውን መግፈፍና በሥራው ሳይሆን በነሱ ላይ እንዲንጠላጠል መገፋፋት ወይም ማስገደድ ነው። ክብራቸውን የሚለኩት የበታቻቸውን በማሳነስ ኃይላቸው ነው። ሲደናገር ወይም ሲያጠፉ አይዞህ፣ በርታ፣ አለሁልህ አይሉትም። ደኅና ቢሠራም ደኅና ሠርተሃል አይሉትም። ሲያጠፉ ጥፋቱ ትምህርት ይሁንህና ለበለጠ ውጤት ከመጣር ወደኋላ አትበል ብለው አይመክሩትም።

ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ካሰብኩበት በኋላ የደረስኩበት መደምደሚያ አለ። የአገራችን ኋላ ቀርነት አንዱና ምናልባትም ዋናው መንስኤ በአለቃና ምንዝር መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ አለመሆን ሳይሆንም አይቀርም። ምንዝር በአለቃው አይዞህ፣ አለሁልህ እስካልተባለ ድረስ የዘወትር ጥረቱ በሥራው ውጤት ለማስመዝገብ ሳይሆን ያለቃውን ገጽታ እያነበበ ድክመቱን እያጠና ለማስደሰትና አውጥቶ እንዳይወረውረውም እራሱን የማዳኛ ዘዴዎች ማዘጋጀትና መረብ መሸረብ ይሆናል። ፋሲካ ሲደልል ጓድ ፕሬዚዳንት ዛሬ ደስ ያላቸው ስለማይመስል እንዲህ ዓይነት ጉዳይ እንዳታነሱ ወይም እንዲህ አትበሉ፣ እንዲህ በሉ እያለ መመሪያ ሊሰጠን ይሞክር ነበር። ያልሆነው ሆኗል ማለት የተለመደ ነበር። እውነቱን የሚናገር ባለሥልጣን እንደእግር እሾህ ይታይ ነበር። እውነቱን በመናገሩ እንደ ደፋር ወይም ተቃዋሚ ተቆጥሮ ጥርስ ይነከስበታል። ካርታ ሲጫወቱ፣ ጮማ ሲቆርጡ፣ በዊስኪ ሲራጩ “ያ ጎረምሳ ባለሥልጣኖቻችን ደፈረ እኮ፣ ቆይ እናሳየዋለን” ይባባላሉ። የማሽቀንጠሪያ ጊዜ ይደገስለታል።

አበበ ከበደ እንደ መንግሥቱ አጫዋች ከሚቆጠሩ ባለሥልጣኖች አንዱ ነበር። የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስትር ሆኖ በሥራ ላይ እንከራከራለን። በሥሩ ያሉ ድርጅቶች ብድር ወይም የውጭ ምንዛሪ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለምን? እያልን እንጠይቃለን። እንደ ብዙዎቹ ሚኒስትሮች እሱም ለምን የጠየቅነውን አላገኘንም? ይላል። በስብሰባም ክርክር ይደረጋል። ይህ

የተለመደና የታወቀ አሠራር ነበር። ታዲያ አቤ እኔን ለማሸነፍ ሌላ ዘዴ ተለመ።

አበበ፣ “ጓድ ፕሬዝዳንት፣ አዲሱን የከተማ ቀልድ ሰምተዋል?”

መንግሥቱ፣ “እስቲ እንስማው”

አበበ፣ “በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት መንግሥት አለ?”

መንግሥቱ፣ “አንድ ነዋ”

አበበ፣ “አላወቁም”

መንግሥቱ፣ “እሺ ስንት ነው? ኪኪኪኪ”

አበበ፣ “ሁለት”

መንግሥቱ፣ “ኪኪኪኪ፣ እነማናቸው?”

አበበ፣ “የደርግ መንግሥትና የባንክ መንግስት”

መንግሥቱ፣ “ካ ካ ካ ካ ኪ ኪ ኪ፣ አይ አቤ፣ ያንተ ነገር፣ ካ ካ ካ ካ”

በእንዲህ ያለ ረቂቅ ዘዴ ጥርስ ውስጥ ለማስገባትና አሳኝኮ ለማስተፋት ይሞክር ነበር።

ስለአበበ ሲነሳ ትዝ ከሚሉኝ አንዱ “እኔ የለሁበትም፣ ይሄ አድማ ነው” ብሎ ስብሰባ የበተነውን ነው። የሶቪየት ሰዎች ሽቀጦቻቸውን እንዳሻቸው ወደ አገር ውስጥ አስገብተው መቸርቸር ይፈልጋሉ። የአገሪቱን ሕግጋት እየጣሱ ባመቻቸው ዘዴ ከመጠቀም ወደኋላ አይሉም ነበር። በዚህ ምክንያት ያለመግባባት ይፈጠራል። አገራችሁን ከሶማሌ ወረራ አድነንላችሁ

ይህ ትልቅ ነገር ሆኖ ነው የምታስቸግሩን? ከማለት አይቦዝኑም ነበር:: የኛ ሰው አብዛኛው የተለየ አስተያየት እንዲደረግላቸው አይፈልግም:: ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነው ምርታቸው ወደ አገራችን ባይገባ ይሻላል የሚለው ድምፅ ያይል ነበር:: በነገራችን ላይ የምንነጋገረው የወታደሩ ክፍል ስለሚያስመጣቸው እቃዎች አይደለም:: የሶቪየቶቹ ንግድ ድርጅቶች ጋጥ ወጥነታቸው ሲበዛ የሚመለከትን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ፍስሐ ደስታን አንድ ነገር ብታደርግ ይሻላል እንለዋለን ፣ ስብሰባ ይጠራል:: ሁሉም የነበረውን ቅሬታ መዘርገፍ ጀመረ:: ሁሉም የልቤን ልናገርና ያበጠው ይፈንዳ ያለ ይመስል ነበር:: አበበ ስብሰባው ከተገባደደ በኋላ ይደርሳል፣ ውይይቱን ተጋግሎ ያገኘዋል:: አቅጣጫው ወዴት እያመራ እንደሆነ ወዲያው ገባው:: “እኔ የለሁበትም፣ ይሄ አድማ ነው” ብሎ በሩን ከፍቶ ወጥቶ ሄደ:: ይሄኔ ሁሉም ደንገጥ አለና ምላሱን ከሞላ ጎደል ሰብስቦ እርስ በርሱ ተያየ:: ብዙም ሳይቆይ ስብሰባው ተበተነና ወደየመጣንበት አመራን::

ገሰሰ ወልደኪዳን የኤኮኖሚ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ በርሱ ሊቀመንበርነት ትልቅ ሴሚናር ይደረጋል:: አንድ ነጥብ ላይ አስተያየት ለመስጠት ፈልጌ ደጋግሜ እጄን ባወጣ እድል ሳይሰጠኝ ይቀራል:: ይህን አቶ ኃይሉ ይመኑ ሲመለከት ኖሯል:: ለቡና እረፍት ስንወጣ እንዳጋጣሚ ሦስታችንም አንድ አካባቢ ተገናኘንና አቶ ኃይሉ ገሰሰን “ታደሰ ደጋግሞ እጁን ቢያወጣ አላየኸውም” ይለዋል:: ገሰሰም መልሶ፣ ቀልድ በተቀላቀለ አነጋገር፣ “አይ፣ ዐይቼዋለሁ፣ ታደሰ ሁልጊዜ የሚያወራው መዐት እንደሆነ ስለማውቅ ነው እድል የነፈግሁት” አለ:: በሌላ አነጋገር እውነት መራራ ስለሆነች ልቀምሳት አልሻም ማለቱ ነበር:: መራራ እንክብልን እንዳለች ከማዋጥ በማር ለውሶ መስጠት የተሻለ መሆኑን ዕድሜ ሳያስተምረኝ አልቀረም::

በባንኩ አዛዥነት ከተመደብኩ በኋላ ለቦርዱ በየጊዜው በማቀርበው ሪፖርት መንግሥት ጥንቃቄ ካላደረገ፣ ይኸውም በተለይ ኤኮኖሚው የሚስፋፋበት፣ ገቢ የሚጨምርበትና አገሪቱ ከውጭው ዓለም ጋር ያላት ግንኙነት

የሚለዝብበት መንገድ ካልተፈለገ በቀር ኤኮኖሚው ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ሊገባ ይችላል፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የኤኮኖሚና ሶሻል ፕሮግራሞቻችንን ሊያኮላሽ ይችላል ከማለት ተቆጥቤ አላውቅም። የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት ስለእያንዳንዱ አገር ኤኮኖሚ የሚጽፈው ዘገባ ይደርሰን ስለነበር አገሮች ምን አይነት ፖሊሲ ተከትለው ምን ውጤት አስገኙ? ምን ዓይነት እርምጃ ባለመውሰዳቸው ምን ዓይነት ችግር ደረሰባቸው? ለሚሉት ጥያቄዎችና መልሶቻቸው ማወቅና መከታተል ከመደበኛ ሥራዎቼ አንዱ ስለነበር ስለኤኮኖሚክ ፖሊሲ ማኔጅመንት ደኅና ግንዛቤ ነበረኝ ለማለት እችላለሁ። ከሌላው ልምድና ስሕተት መማር አለብን ነበር የምለው።

ስኬታማነትም ሆነ ውድቀት የሚመራበት የራሱ የሆነ ሎጂክ አለው። እንዲሁ በተአምር የሚሆን ነገር የለም። አለ የሚሉ ካሉ ሕዝቡን አደንዝዘው ለበሽታው፣ ድንቁርናው፣ ረሃቡ፣ ጥማቱና እርዛቱ መድኃኒት ፈልጎ እንዳያገኝ መከልከል ወይም መከላከል ስለሆነ በበኩሌ ሳላወግዛቸው አላልፍም። ለሁሉም ነገር ምክንያት፣ ምንጭ ወይም ወላጅ ክስተት አለው። ለነገሩማ ሁሉም የጁን ያገኛል እንጂ አይደል። ማንም ያልዘራውን አያጭድም ወይም ያተልዘራ አይታጨድም ማለት ነው። በተዋጣለትና ባልተዋጣለት ግለሰብም ሆነ አገር መካከል ልዩነቱ መድረስ የሚፈልጉበትን አውቆ አሰቡበት ለመድረስ አስፈላጊ እርምጃዎችን በወቅቱ በመውሰድና ባለመውሰድ መካከል ነው። ታታሪውና ፈጣኑ ሲቀድም ሌላው ወደኋላ ቀርቶ የበይ ተመልካች ሆኖ ይቀራል፣ ከዚያም ተዋርዶ ወይም ኅሊናውን ሽጦ ፍርፋሪ ለቃሚና በትቢያ ላይ ተንፈራፋሪ ሆኖ ይቀራል። እግዚአብሔር ለፈጠረው ክቡር ፍጡር ከዚህ የበለጠ ውርደት የለም። በዚህ አባባል የሚያዝንብኝ ካለ ይቅርታ እየጠየቅሁ የቁጭቱን ዒላማ እራሱ ላይ አዙሮ እንዲያነጣጥር አሳስባለሁ። የሰውን አእምሮ ከመቆስቆስ ሌላ አቅም ወይም ኃይል ስለሌለኝ በአባባሌ ተናዶ እራሱን ከወደቀበት የሚያነሳ ካለ ስደትን፣ ርቀትን ወይም ሞትን ድል መንሳቴን አዲሱ ዓለም ሲፈጠር እመሰክራለሁ።

አገራችን የነበራት አንዱ ችግር ባለሥልጣኖች ውስብስብ ጉዳዮችን አበጥሮ ወይም አብጠርጥሮ መተንተን፣ አማራጮችን አንጓሎ መለየትና የተሻለውን የመምረጥ ብቃታቸው ማነሱ ብቻ ሳይሆን ተሳክቶልናል ብሎ በባዶ ሜዳ እራስን ከመደለልና ማኩራራት ጋር የተዛመደ ነበር:: ሁኔታው የበለጠ እንዲሳከርና እንዲውሰበሰብ አድርባዩና አሽቃባጩ ተጨማሪ ምክንያት ይሆናል::

መንግሥት መውሰድ ስላለበት ወቅታዊ የፖሊሲ እርምጃዎች አበክሬ አሳስብ የነበረው ለመድኃኒት፣ ለጥሬና መለዋወጫ እቃዎች፣ ለነዳጅ እንዲሁም ለመሳሰሉ መግዣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት አፍጦ ከመምጣቱ በፊት ነበር:: የአገሪቱ የውጭ እዳም ወቅቱን ጠብቆ ይከፈል ነበር:: ማሳሰቢያዬን የቦርዱ አባላት ሰምተው ይሄዳሉ እንጂ ብዙም ፋይዳ አይሉትም::

የሱዳኑ ኑሜሪ ሥልጣን ላይ እያለ ባንድ ወቅት የሁለቱ አገሮች ግንኙነት እሹሩሩ እየተባለ ባንቀልባ ታዝሎ ይዞር ነበር:: የመንግሥት ልዑካን ቡድን ካርቱም ሄዶ ሳለ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ይቋረጣል:: ምነው? ቢባል የቲቪው ጣቢያ የመለዋወጫ እቃ እጥረት ገጥሞት ነው ተባለ:: ኑሜሪ ነጋዴዎችን ይማጸንና የውጭ ምንዛሪ ተሰብስቦ የጎደለውን እቃ መግዛት ተቻለና ፕሮግራሙ መደበኛ ሥራውን እንደገና ሊጀምር ቻለ::

የባንኩ ቦርድ አባል አቶ ዩሱፍ አህመድ፣ የመገናኛና ትራንስፖርት ሚኒስትር፣ የልዑካኑ ቡድን አባል ስለነበር ቲያትሩን ሲያይ ሰንብቷል:: አዲስ አበባ እንደተመለሰ መጣሁ ይለኝና ቢሮዬ ከተፍ ይላል:: ምነው? ደኅና? ብለው ካርቱም ያየውን ቲያትር ያጫውተኛል:: የውጭ ምንዛሪ እጥረት ደርሶ አገራችን እባሰ ችግር ውስጥ ልትዘፈቅ የማትችልበት መንገድ እንደሌለ አሁን እምኛለሁ፣ የቦርዱ አባላት ከጀርባህ ታደሰ ለምንድነው እንዲህ የሚያስፈራራን? እያልን እናማህ ነበር ብሎ አጫወተኝ::

ኢትዮጵያውያን ከሌላው የተለየን ነን ማለት እንወዳለን:: መለየትን መለያችን ያደረግነው ይመስላል:: ይህ አስተሳሰብ ሰርጾ ሥነልቦናችን ውስጥ ስለገባ ችግር በሌላው ላይ እንጂ እኛ ላይ ይደርሳል አንልም ነበር:: ረሐብ፣ ቸነፈር የመሬት መራቆት፣ በረንዳ አዳሪነት አጠገባችንም አይደርሱም እያልን ስንኮፈስ ኖረናል:: ለትምህርት ወደ ውጭ አገር ስሄድ የአዲስ አበባ ባንኩ አለቃዬ አቶ ደበበ የእራት ግብዣ ያደረጉልኝ ዕለት አቶ መሐመድ ሸሪፍ አንድ አስደናቂ ታሪክ ነገረኝ:: የፓሪስ ሴትኛ አዳሪዎች መንገድ ዳር ቆመው ወጪ ወራጁን ተሸከርካሪ በጥቅሻም ይሁን በሌላ ዘዴ ሊያስቆሙ ይሞክራሉ ብሎ ሲነግረኝ አበስኩ፣ ገበርኩ፣ ፈረንጆች እንዴት ተበላሽተዋል? ኩሩዋ ያበሻ ሴት በፍጹም ይህን አታደርግም ብያለሁ፣ በወቅቱ:: በጋንዲ ሆስፒታል አካባቢ ያለፈ ጊዜ ተላዋዋጭ ስለመሆኑንና እኛም ከሌላው ያልተለየን ለመሆኑ ጥሩ ማስረጃ ነው:: አሁን ከአገሬ ርቂ እንደምሰማው የጋንዲ ተወዳዳሪዎች እንደተበራከቱ ነው:: ይህ ብዙም አስደናቂ አይደለም፤ የኤኮኖሚና ሶሻል ፖሊሲዎች መዛባት ምልክት ነው::

ሌላውን እንጂ እኛን ምንም አይነካንም እያልን ስንኩራራ ችግር ከእራስ ጸጉር እስከእግር ጥፍር ወሮን ተቀምጠናል:: የኤኮኖሚ ቀውስን በተመለከተ እኛ እንደ ሱማሌ፣ ሱዳን፣ ወዘተ አይደለንም እንል ነበር:: ስለኮራፕሽን ሲወራ ኬንያን፣ ኮንጎን፣ ናይጄርያን ወዘተን እንጂ እኛን ሲያልፍ አይነካንም እንል ነበር:: የኮንጎ፣ ርዋንዳ፣ ላይቤርያ፣ ሴራሊዮን፣ ወዘተ ሕዝብ በእርስ በርስ ጦርነት ሲፋጅና ጨርቁን ባናቱ ተሸክሞ ከቦታ ቦታ ሲንከራተት ስናይ እኛ የተለየን ስለሆንን ተቻችለን መኖር ለምደናልና የነሱ እጣ ሲያልፍ አይደርስብንም እንላለን:: የሃይማኖት ጦርነት ክትባቱ ስለወጣልን ሲያልፍም አይነካንም እንላለን:: ሌላም ሌላ::

በብዙ የአፍሪቃ አገሮችን ተዘዋውሬ እንዳየሁት በእርግጥም የአገራችን ሕዝብ ታታሪ ነው፤ በሰው እጅ መውደቅ አይወድም፣ ውርደትን ስለሚፈራ ጎላፊነቱን ለመወጣት በቂ ጥረት ያደርጋል:: ሆኖም፣ እነዚህ መልካም ባሕሎቹ ከጊዜ ብዛት እየተሸረሸሩ ስንፍና፣ እጅ መዘርጋት፣ በሌላ ላይ

መንጠላጠል፣ ክብርንና ኅሊናን በገንዘብ መሸጥ እየተለመዱ መጥተዋል:: እዚህ ድረስ ይዘው ደግፈው ያመጡን የምንኮራባቸው ባሕሎቻችን ጠባቂና ተንከባካቢ እያጡ እየፈራረሱ ናቸው:: ስለሆነም፣ አገራችን አደጋ ላይ ወድቃለች::

በሥራዬ አኳያ ይህን እርምጃ ካልወሰድን፣ ያንን ካላስተካከልን ወይም ካልለወጥን ሌሎች እወደቁበት ጉድጓድ መውረዳችን አይቀሬ ነው ስል እኛ የተለየን ነን፣ ችግሩ እኛ ቤት ሊያንኳኳ አይችልም እባል ነበር:: እድሜ ለሱዳን፣ አቶ ዩሱፍ ላስገነዝብ የፈለግሁትን ጉዳይ ቢዘገይም ተረዳልኝ::

ጥንቃቄ ይደረግ፣ የፖሊሲ እርምጃ በወቅቱ ይወሰድ እያልኩ እወተውት የነበረው በደመ ነፍስ መዳከርን ስለምጠላና ውጤት ያለሥራ ሊገኝ እንደማይችል ስለምገነዘብ ነው:: ያልተዘራ እንደማይታጨድ ሁሉ፣ እንክርዳድ ተዘርቶ ስንዴ እንደማይሰበሰብ አውቃለሁ:: ታድያ ለምንድነው አንድ እና አንድ ሁለት መሆኑ እየታወቀ የኛ ባለሥልጣኖች ሦስት ነው ማለት የሚሞክሩት? እያልኩ እንጨረጨር ነበር:: ለኔ በጣም ገሀድ የሚመስለኝ ሐቅ አንዳንድ ባለሥልጣኖች እንዲህ ነው ወይም ይሆናል ሲሉ ሳላውቅ አለም የምትሽከረከርበትን አቅጣጫ ለውጣለች እንዴ? እስከማለት እደርስ ነበር::

እውነቱን ደጋግሞ የሚናገር ወይም ስሕተት መፈጸሙን የሚያሳውቅ ሰው ታቅፎ ተደግፎ ሊያዝ ቀርቶ እንደ መዐት ጠሪ፣ ሽብር ፈጣሪና አሸባሪ እየተቆጠረ እንዲገለልና አድማጭ እንዲያጣ ማድረግ የተለመደ ነበር::

ባንድ ወቅት ለገቢ ንግድና ወጭ ንግድ ድርጅቶች እንዲሁም ለነዚህ አገልግሎት ለመስጠት ለተሰማሩ ድርጅቶች ባንክ ያዘጋጀው አንድ ሴሚናር ስከፍት የአገሪቱ ውጭ ምንዛሪ በአሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝና ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ ካላበረከተ ሁኔታው እንደሚባባስ አስተያየቴን ገለጽኩ:: የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢና ወጪ ሥዕል ለማሳየት ሞከርኩ:: የተጠቀምኩባቸው አኃዛዊ መረጃዎች ባንኩ በይፋ በሚያወጣው መጽሔት

ውስጥ የሚገኙና ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አይ ኤም ኤፍ የሚገለጹ ናቸው፡፡ ስለሴሚናሩ መደረግ በጋዜጣ ሲገለጽ ቁጥሮቹም ተጠቃቀሱ፡፡

ፓርቲው አካባቢ ለመንግሥት ደኅንነት ተቆርቋሪ ነን ባዮች አሽቃባጮች እንዲሁም እወደድ ባዮች ታደሰ የአገር ምስጢር አወጣ ብለው ችግር ውስጥ ሊከቱኝ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ እንይዝ እንደነበርና ሳይባክን ለዋና ዋና ጉዳዮች ብቻ እንዲውል እንታገል እንደነበር ግን አያነሱም ነበር፡፡ እነዚህ ባለሥልጣኖች መደበኛ ሥራቸው አድርገው ይወስዱት የነበረው የማይፈልጉትን ሰው ለማስወገድ ቀን ጠብቆ፣ ስሕተትን ባትሪ ይዞ መፈለግ ይቀናቸው ነበር፡፡ አይዞህ፣ በርታ፣ ተበራታ ማለት አያውቁበትም፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ምናምኖች በተንሰራፉበት አካባቢ ሰው በሠራው ኅልቶ ይወጣል፣ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋል፣ ሥራና ሠራተኛ ይገናኛል፣ ብሎም አገር ታድጋለች ብሎ ማመን በሬ ይወልዳል ብሎ እንደማመን ይቆጠራል፡፡

ቁም ነገሩ ሲጠቃለል፣ የሕዝብ አደራ የተጣለባቸው በርካታ ባለሥልጣኖች ተልእኮዎቻቸውን ወደጎን ትተው ከሥልጣን ኮርቻ ላለመውረድ ሲሉ መሪያቸው መስማት የሚወደውን እየዘመሩ መደለልና ድክመቱን ማስታመም ዓይነተኛ ተግባራቸው አድርገው ተያይዘውት ነበር፡፡

አንድ ጊዜ ለፕሬዚዳንት መንግሥቱና ለጥቂት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ስለክሬዲት ፖሊሲ ከባንኩ ዶክተር ላቀው ዓለሙ ጋር ፕሬዚዳንቱ ቢሮ ውስጥ ገለጻ እናደርጋለን፡፡ የቡና እረፍት ተደርጎ ሰው ወደየወንበሩ ሲመለስ አንዱ ባለሥልጣን ለሌላው "ዚዝ ስሞል ቦይስ፣ እነዚህ ትንንሽ ልጆች፣ ገለጻቸውን መቼ ነው የሚጨርሱት? ጊዜያችንን አባከኑ እኮ" ይለዋል፡፡ ዞር ሲል ያየኛል፡፡ ታዲያ ምን ይዋጠው፡፡ ሰውዬው ያለኔ አዋቂ የለም፣ የመንግሥቱ ዐይኑ ነኝ እያለ እራሱን የሚያኩራራ፣ ነገር ግን በሥሩ ያሉ ኃላፊዎች ሰውን መበዝበዝ እንጂ ማንሳት የማይወድ ምቀኛ እያሉ ሲያሙት እሰማ ስለነበር አሁን ደግሞ ድንበር ተሻግሮ እኛም ላይ ለመዝመት ሲሞክር ሳይ ደሜ ፈላ፡፡ በእሱና በተባባሪ አድማጩ ደካማ

አስተሳሰብ የሱ ትልቅነት የሚታወቀው እኛን አሳንሶ በማስቀመጥ ይመስለዋል፡፡ ሰውዬውን መናቅ ከጀመርኩ ውዬ አድሬ ነበርና ለሱ የነበረኝ የከበሬታ ርዝራዥ የዚያን ዕለት ተሟጠጠ፡፡ ዝቅተኛ ባለሥልጣን በነበረበት ወቅት በእውነት ተናጋሪነቱና አልበገር ባይነቱ የታወቀ ነበርና ከአድናቂዎቹ አንዱ ነበርኩ፡፡ ከፍ እያለ በወጣ ቁጥር ግን የተጠቀሱት በጎ ጎኖቹ እየመነመኑ ሄዱ፡፡ እሱም እንደሌላው የፕሬዚዳንቱ ገጽታና ጠባይ አንባቢ ወይም ያዋቂ ጠንቋይ ሆኖ አረፈው፡፡ ከፍ በተባለ ቁጥር ከተወደቀ መላላጥ ብቻ ሳሆን መሰባበር እንደሚከተል ተረዳና በብልጥነት ጎራውን ይዞ መኖር መረጠ፡፡ መንግሥት እመርታዊ ለውጥ በወቅቱ እንዲያደርግ ሊገፋፉ ከሚችሉት ሰዎች አንዱ ነው ብዬ የምተማመንበት ሰውዬ ለሸሽ ብሎ ጥግ ይዞ ተቀመጠ፡፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ብሩህ አእምሮ ለውጥ ለማምጭያ የትግል መሣሪያ ሊያደርገው ሲችል በራስ ወዳድነት ሥልጣኑን እማስጠበቅ ላይ ብቻ ወሰነው፡፡ የልቤን መተንፈስ ሲያምረኝ አምኜ ከምቀርባቸው ጥቂት ሰዎች አንዱ ስለነበር እያየሁት ያጣሁት ሰው ሆኖ አገኘሁትና አዘንኩ፡፡

የብር ለውጥ ሲካሄድ ለጥቂት ቀናት አንዳንድ ጣቢያዎችን እየተዘዋወርኩ ጎበኘሁ፡፡ አቶ አንዱዓለም ተመስገን አብሮኝ ነበር፡፡ ጣቢያዎቹ መመሪያ ተከትለው ሥራቸውን በሚገባ እንደሚያከናውኑ ተመለከትን፡፡ አስቀድሞም እንደገመትነው አንዳንዱ አካባቢ ከሌላው ይበልጥ ምርት የሚሰጥ በመሆኑ የሚለወጠው ገንዘብ መጠንና የሚፈለገው ባንክ ኖት ዓይነት ከጣቢያ ጣቢያ ይለያያል፡፡ አላባ ቁሊቶና ቡታጅራ ጣቢያዎች ከሌሎቹ ጣቢያዎች ከጠበቅነው በላይ ሆነው አገኘናቸው፡፡ አካባቢው እንደበርበሬና ቦሎቄ የመሳሰሉ ለገበያ የሚውሉ ምርቶችን ስለሚያመርት ቀደም ብሎም በስሌት ውስጥ ማስገባት የነበረብን ጉዳይ ነበር፡፡

ከወላይታ ሶዶ ወደ ሻሸመኔ ስንሄድ የመኪናችን ጎማ ይተነፍስና ሾፌሩ ጎማውን በክሪክ ሲያነሳ አንድ ያካባቢው ሰው ይመጣል፡፡ ሊያነጋግረን ነው ብለን ስንጠብቅ ዐይኖቹ እጎማው ላይ ተተክለው ቀሩ፡፡ በጎኑ ዘንጉን

ተደግፎ፣ እግሮቹን አቆላልፎ፣ አፉን ባንድ እጁ ይዞ፣ አይ ቢላት አይ ቢላት አይ ቢላት ይላል:: ምነው? ብንለው፣ ይህች ትንሽ ብረት ይህን ግዙፍ መኪና በቀላሉ ስታነሳው ከማየት የበለጠ የሚያስደንቅ ነገር የለም አለን:: የሰውዬው ተመልካችነት ወይም ሜካኒካል አፕቲትዩድ ይርጋለም ብሔራዊ አገልግሎት በነበርኩበት ወቅት ያገኘሁትን ብልህ እረኛ አስታወሰኝ::

ከእስካውቶቼ ጋር አቦስቶ ማዶ ለሽርሽር ሄደን ሳለ እረኞች እንደተለመደው ቀርበው የምንሠራውን ያያሉ:: ትምህርት ቤት ይሄዱ እንደሆን ባስተርጓሚ ጠየቅኋቸው:: በጭራሽ አሉ:: ፊደል ዐይተው እንደማያውቁ ተረዳሁ:: ጆሮዋቸውንም ቢቆርጡዋቸው አማርኛ አይሰሙም:: ፊደል የያዘ አንድ እስካውት  አገኘሁና ከእረኞቹ አንዱን ሀ ሁ ሂ ብዬ ማስቆጠር ጀመርኩ:: ሎ ላይ ስደርስ የምነግረውን መድገም አቆመና በጣቱ እያመለከተ አንድ ጥያቄ አቀረበልኝ:: እረኛው ያቀረበው ጥያቄ ነው ተብሎ የተነገረኝ የሆ ቁልምሙ ጆሮው ላይ ሲሆን የሎ ለምን ወገቡ ላይ ሆነ? የሚል ነበር:: አንድ ሳይንቲስትን ማይምነት እንደበላው መስክሬ በከፍተኛ ሐዘን ወደመጣሁበት ተመለስኩ:: የተለየን ነን፣ እኛ ልዩ ጭንቅላት ታድለናል እያሉ የሚመጻደቁ የለየላቸው መሃይማን እረኛውን ቢያገኙ ከበሽታቸው ይፈወሱ ነበር ብዬ አሰብኩ::

እኔን ጨምሮ ባለዕድሎች ትምህርት ቤት ስንሄድና ሕይወታችንን ስንገነባ ዕድለቢሱ የኢትዮጵያ እረኛ ግን ሜዳ ፈሶ ውሎው ከከብት ጋር ሆኖ ቀረ:: በሰዎች መካከል ያለው ልዩነት በመሠረቱ የሥራ አስተዋፅኦ ልዩነት ነው ቢባል እድልም ወሳኝ ሚና እንዳለው እረኛው ጥሩ ምሳሌ ነው:: ደርግ ሥልጣን ላይ እንደወጣ አብዮቱን ለመሸጥ ወይም ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግ ከተጠቀመባቸው ስልቶች አንዱ፣ የድሃ ልጅ እጣው የከብት ጭራ መከተል ሆኗል፤ ይህን መለወጥ መቻል አለብን የሚል ነበር:: በበኩሌ ያ እረኛ ትዝ አለኝና ለኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ ቀን ሊወጣ ነው ብዬ ከፍተኛ የአእምሮ እርካታ ተሰማኝ:: የአብዮቱ ደጋፊ እንድሆን ካነሳሱኝ

ነቁጦች አንዱ የትምህርት እድል ሀብታም ድሃ ሳይባል ለሁሉም ይስፋፋል ስለተባለ ነበር፡፡

የትምህርት ዕድል ሀብታም ብቻ የሚገዛው ሸቀጥ ነው ሲባል በጣም ይገርመኛል፡፡ ይህን ፖሊሲ የሚያራምዱ ሰዎች ሌላውን ጨቁኖ ወይም አፍኖ የመያዝ ስውር ዓላማ ከሌላቸው በቀር በምንም መለኪያ የሚያራምዱት ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ እላይ የተጠቀሰው እረኛ ቢማርና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ቢደርስ ተጠቃሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ነው፡፡ እሱን ማስተማር የሁላችንም ኃላፊነት መሆን ነበረበት፡፡ ኃላፊነቱ ለአባቱና ለእናቱ ብቻ የሚተው መሆን የለበትም፡፡ ይሁን ከተባለ በራሳችን ላይ መፍረድ ነው፡፡

ባንድ ወቅት መንገድ እናሠራለን፣ የትምህርት ዕድል እናስፋፋለን እየተባለ አዲስ አበባ ሚገኙ የሙህር ተወላጆች በወዳጄ በወልደሥላሴ ወልደትንሣኤ አስተባባሪነትና መሪነት አገር ቤት ይመላለሱ ነበር፡፡ እኔም አንድ ሁለቴ ሄጃለሁ፡፡ ባንደኛው ጉብኝታችን የሙህር ባላባት የነበሩትን ዓለሙ ቦንገርን እናገኛለን፡፡ ለምን እንደመጣን ገለጽንላቸው፡፡ ሰውዬው አንደበተ ርቱዕና በእነ ነገደ ጎበዜ ቋንቋ የነቁ አድኃሪ ነበሩ፡፡ "ሐሳቦቻችሁን ሙሉ በሙሉ እደግፋለሁ፤ በሚያስፈልገው መንገድ ሁሉ እተባበራለሁ፤ ብቻ ባንድ ነጥብ ላይ እንግባባ፣ የገበሬውን ልጅ ሁሉ አስተማራችሁ በቅሎ ጎታች እንድታሳጡኝ ግን አልፈልግም" አሉና በፊውዳል ሥርዓት መገርሰስ የሚስማሙት ጥቅማቸው እስካልተነካ ድረስ ብቻ መሆኑን ሊሸሽጉ አልቻሉም፡፡ ንቃት ለሳቸው ብቻ የታደለ ጸጋ ባለመሆኑ ተነቃቅተን ተለያየን፡፡

ባላባቱ ዓለሙን ያገኘን ዕለት ከእሳቸው ጋር በእግር አካባቢውን እየተዘዋወርን ስንጎበኝ አንድ ገበሬ በጎቹን ሲጠብቅ እናገኘዋለን፡፡ አቶ ዓለሙ ከሰውዬው ጋር ሰላምታ ተለዋወጡ፤ ጎበዝ በግ አርቢ መሆኑን ከመሰከሩለት በኋላ ዐይናቸው አንዲት ጠቦት ላይ ያርፍና እንዴት ታምራለች? ይሉታል፡፡ ሰውዬው ፈገግ ብሎ ወደ መሬት አቀርቅሮ

የቆመበትን አፈር በእግሩ አውራጣት መኮርኮር ወይም መቆርቆር ተያያዘው እንጂ መልስ አልሰጠም:: ከአቶ ዓለሙ ከተለያን በኋላ ቅድም ስለጠቦት ቁንጅና የተወሳው ገብቶሃል? ተብዬ ተጠየቅሁ:: የባላባቱ አባባል ቀጥተኛና ምንም ምስጢር የሌለው ነው ብል፣ አይ የዋህ፣ አልገባህም፤ ያችን ጠቦት ፈልጊያታለሁና ተሸክመህ ቤቴ ወስደህ እንድታስረክብ ታዘሃል ማለት ነው ተብሎ ተነገረኝ:: ስለፊውዳሊዝም በመጽሐፍ ካነበብኩትና ከክሮኮዳይል ቡድን አባላት ከተማርኩት ይበልጥ ከአቶ ዓለሙ ጋር ያደረግሁት ያጭር ጊዜ ቆይታ አእምሮዬ ውስጥ ሰርጎ መግባት ቻለ::

የብር ለውጥ እየተካሄደ ሳለ አንድ ቀን ወዳጄ ወልደስላሴ ቢሮዬ ብቅ ይላል:: ዛሬ ምን እግር ጣለህ? እለዋለሁ:: አይ ዝም ብዬ ነው ይለኛል:: ቡና ፉት እያልን፣ እውነቱን ልንገርህና ያ ብሩ ላይ ያለው ነገር አሳስቦኝ ነው የመጣሁት ይለኛል:: ምኑ? ብለው ጽሑፉ ነዋ ይለኛል:: የምን ጽሑፍ? ስለው ቀልድህን አቁም፤ የከተማ ሰው ሁሉ ሲያውቅ አንተ የጉዳዩ ባለቤት ሆነህ ለነገሩ እንግዳ ነኝ አትበለኝ ይለኛል:: አሁንም ምንም የማውቀው ነገር የለም ብለው ከኪሱ አዲሱን ያንድ ብር ኖት ያወጣል:: ያባይ ፏፏቴ ሥዕል ያለበትን ጎን ይዘቀዝቅና ጽሑፍ ነው የተሰኘውን ያሳየኛል:: አሁንም አልታይህ ይለኛል:: አሁንም ግራ እንደተጋባሁ በማጤን፣ "እንግዲያስ ልምራህ" ይልና "ይሄ ኢ ይሄኛው ሕ ይህ ደግሞ አ የመጨረሻው ደግሞ ፓ አንድ ላይ ኢ ሕ አ ፓ ነው" ይለኛል:: ገና ከመጨረሱ ከት ብዬ ሳቅሁ:: ያልተጻፈ የሚያነቡ ሰዎች ቅዥት ነው አልኩት:: አመጣጡ መራራ ጽዋ እንደሚጠብቀኝና ምናልባትም የማደርገው ነገር ካለ ወቅታዊ እርምጃ እንድወስድ ሊያሳስበኝ ነበር:: ነገሩን ሳቃልልበትና ምንም እንዳልተረበሸኩ ሲያይ ግራ ሳይጋባ አልቀረም:: ወልዴ የልብ ወዳጄ ከምላቸው ሰዎች መካከል ስለነበር እንዲያውጣጣኝ በመንግሥት ወኪሎች ተልኮ ሊሆን ይችላል ብዬ በፍጹም አልጠረጠርኩም::

ደግነቱ በአንድ ብር ኖት ላይ ያሉት የፊትና ጀርባ ምስሎች፣ ልጅና ያባይ ፏፏቴ፣ ሁለቱም ፎቶግራፎች ናቸው:: አባይ ፏፏቴ አካባቢ ብዙ ዛፎች አሉ:: ወልዴ ፊደላት ናቸው ብሎ ያሳየኝ የዛፎች ቅርንጫፎችና ሥሩ የተንሰራፋ ግንድ ነው:: ሰማይ ላይ ጉም ወይም ደመና ስናይ አንበሳና ዘንዶ እንደሚመስለን ዓይነት ነው እነወልዴ ያዩት:: ነገሩ ካለፈ በኋላ ቀላል ይምሰል እንጂ በወቅቱ አብዮት ቀልባሾች ወይም የደርግ መንግሥት ተቃዋሚዎች ስማቸውን በብራችን ላይ እስከማጻፍ ደረሱ ተብሏል:: ለአብዮታዊ እርምጃ እንድንዳረግ የገፋፉም ሳይኖሩ አይቀሩም ብዬ እገምታለሁ:: ለዚህ ቀርቶ በጣም ላነሰ ማክንያት የታሰሩ እንዳሉ ያደባባይ ምስጢር ስለነበርም ይሆናል ወልዴ ስጋቱን ሊገልጽልኝ ቢሮዬ ድረስ አንኳኩቶ የመጣው:: ደርግ የሚያደርገው ነገር ካለ ብዬ ተጠባበቅሁ:: የሚናፈሰው ወሬ እየተዳከመ ሄዶ ከጊዜ ብዛት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ:: እኔም ያለኀጢአቴ ከመደፍጠጥ ዳንኩ::

ገንዘቡን ላተመው ኩባንያ፣ ለቶማስ ደላሩ፣ ተወካይ ስለተወራው ወሬ ነገርኩት:: አዲስ የባንክ ኖት ሲወጣ ሁሉም የኖት መርማሪና አጥኚ ስለሚሆኑ ስለኖቱ አቃቂር ማውጣት የተለመደ ነው፤ እንከን የማይወጣለት ኖት ማውጣት ቀላል አይደለም ካለ በኋላ እንግዲያውስ አንድ ታሪክ ልንገርህ ይልና ስለ ሞዛምቢክ ገንዘብ ለውጥ አጫወተኝ::

ሞዛምቢክ ከፖርቱጋል ነጻ እንደወጣች አዲሱን ገንዘባቸውን ያተመላቸው ቶማስ ደላሩ ነበር:: ከሁሉም የገንዘብ ኖቶች ፊት ለፊት ላይ የነበረው የአገሪቱ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት የሳሞራ ማሼል ምስል ሲሆን በአንዱ ኖት ጀርባ የነበረው የአጋዘን ሥዕል ነው:: በዚያን ዘመን ዚምባብዌ ገና ነጻ አልወጣችም ነበርና የደቡብ አፍሪቃና ሮዲሽያ ዘረኞች በመተባበር፤ ጥቁር ሕዝብ እራሱን ለማስተዳደር ብቃት የለውም ብለው ዓለምን ለማሳመን የአካባቢውን አገሮች መቅኖ የሚያሳጡበትና መንግሥቶቻቸውን ደግሞ የሚያናጉበት ወቅት ነበር:: የሞዛምቢክ አዲሱ ገንዘብ እንደወጣ ሞዛምቢክን የሚመለከት አንድ ከፍተኛ ዜና ከሮዲሽያ ይተላለፋል::

እሱም፣ ሳሞራ ማሼል ቀንድ አበቀለ የሚል ነበር:: ኖቱ ከፍ ተደርጎ በብርሃን ሲታይ ያጋዘኑ ቀንድ በፕሬዚዳንቱ ግንባር ላይ ተተክሎ ይታያል:: ነገሩን ስቆ ማለፍ ለማይችልና የሆነ ያልሆነውን፣ ጥቃቅን ነገር እየፈለገ ያለመጠን ኮምጫጫ መሆን ለመረጠና ጠብ ያለሽ በዳቦ እያለ ለሚፈልግ ባለሥልጣን የቀንዱ ጉዳይ አጥፊውን ፈልጋችሁ አምጡልኝ የሚያሰኝ ጥፋት ይመስላል:: ሆደ ሰፊ ለሆነና ለእንደዚህ አይነቱ ትርኪ ምርኪ ቦታ አትስጡት ለሚል ሰው ግን የዘረኞቹ ዜና ያንድ ሁለት ቀን የቡና ወይም ጠጅ ቤት ወሬ ሆኖ የሚከስም ነበር:: አባቴ ገጎ ስራጋ ይሉት እንደነበረው ትናንሹን ለመቻል ወይም ለመደበቅ ሰፊ ሆድ ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ ያልታደለ ግን እንኳን ተነክቶ ከፈሱ ጋር ሲጣላና ጠላት በየኬላው ሲያፈራ ይውላል::

ቀንድ የማብቀሉ ጉዳይ ለግንባሩ ባለቤት ለሳሞራ ማሼል ይቀርብና ፕሬዚዳንቱን ለመሳለቂያነት የዳረገቻቸው ኖት የሞት ፍርድ ይፈረድባታል፣ ቶማስ ደላሩም ሌላ የኅትመት ትእዛዝ ይደርሰዋል:: ኩባንያው የአዞ እንባውን በድሃይቱ ሞዛምቢክ ውድ ውጭ ምንዛሪ ጠራርጎ አዲስ ኖት ሠርቶ አቀረበ:: የኛ ሰዎች በዚህ ረገድ ሆደ ሰፊ ሁነው ስላገኘ ኋቸው ሳላደንቃቸው አላለፍኩም:: ኢ ሕ አ ፓ በኖቱ ላይ ስሜን አስጽፌአለሁ ብሎ የውሸት ፕሮፖጋንዳ በወቅቱ ነዝቶ ቢሆን ኖሮ ኖትዋ ብቻ ሳትሆን እኔም መቀመቅ ወርጄ ይህን ታሪክ የሚናገር አይኖርም ነበር::

የብር ለውጥ በተጠናቀቀ በስድስተኛው ወር ለሥራ ጉዳይ ጎጃም እንደሄድኩ የሥራ ባልደረቦቼን ጢስ አባይን ስላላየሁ እንሂድ እላቸውና ተነስተን እንሄዳለን:: ያልነገርኳቸው መሄድ የፈለግሁበት ዋናው ምክንያት ኢ ሕ አ ፓን ቅጠል ላይ ለመፈለግ እንደነበር ነው:: አንድ ብር ኖት ላይ ያሉት ዛፎች እንዳሉ ናቸው:: እናንት ጉደኞች፣ ቅርንጫፎቻችሁን ዘርግታችሁ፣ ሥራችሁን አንሰራፍታችሁ ለሳርና ቅጠል ጠበቃ የቆምኩትን

ምስኪን በዋዛ ፈዛዛ ለቀን ጅብ አሳልፋችሁ ሰጥታችሁኝ ነበር ብዬ ገስጫቸው ተመለስኩ፡፡

እግረ መንገዴንም በአባይ ወንዝ አማካይነት የኢትዮጵያ ህልውና ተንዶ ወደሱዳንና ግብጽ ሲነጉድ አየሁና አምላኬ ምነው ይህን ልታሳየኝ አመጣኸኝ? ብዬ አማረርኩት፡፡ አለማየት ይሻላል የሚለው አባባል ትርጉሙ የገባኝ የዚያን ዕለት ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ያየሁት የውሃ ፏፏቴ ሳይሆን አፈር እየተናደ ገደል ሲገባ ነበር፡፡ እኔ ያየሁትን ለማየት በሐምሌ ወይም በነሐሴ መሄድ ነው፡፡

ማን ያውቃል? የኢትዮጵያ አምላክ ሊታረቀን ያሰበ ይመስላል፡፡ ይህን ገጽ እያረቀቅሁ እያለ ስልክ ይደወላል፡፡ ወሬው ጢስ አባይ ሄዶ አፍሮ ስለተመለሰ ሰው ነው፡፡ ያሳፈረው በሐምሌ ፏፏቴውና ለማየት ሄዶ ምንም ሳያይ በመመለሱ ነው፡፡ ፏፏቴውን ለማየት ገንዘብ ከፍለው የሄዱ ፈረንጆች ምንም ባለማየታቸው የአስጎብኚውን ድርጅት ሠራተኛ ሲወርፉ ታይተዋል ተብሎ ተነገረኝ፡፡ እውነት ከሆነ ከዚህ የበለጠ መልካም ዜና ሊኖር አይችልም፡፡ ምን ተፈጠረ? ብዬ ብጠይቅ አባይ ተገድቦአል፣ መንደርደሩ ታቅቦአል፣ አርፎ እንዲቀመጥ ተነግሮታል ተብሎ ተነገረኝ፡፡ ታሪኩን ሙሉ ለሙሉ ለማመን ቢያቅትም አዝማሚያው መልካም ነውና የኢትዮጵያ አምላክ አሁንም ይርዳን፡፡

አንድ ብር ላይ የሚታየው ልጅ የወሎ እረኛ ሲሆን ፎቶግራፉ የተገኘው ከአየር መንገድ ወይም ቱሪስት ድርጅት መጽሔት ነው፡፡ የብር ለውጥ ከተደረገ በኋላ ልጁን ልንተዋወቀውና ልንሸልመው ፈልገን አውቀዋለሁ የሚል ግን ጠፋ፡፡ ሰውዬው አሁንም ቢቀርብ ወይም ቢገኝ ብሔራዊ ባንክ በሚገባ እንደሚቀበለውና እንደሚያስተናግደው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የልጁ ፈገግታ ደስታና ተስፋ የማንጸባረቅ ኃይል ስላለው የተስፈኞች አገር ባለሥልጣኖች ምስሉን ሳይለውጡ እንደሚያቆዩት እገምታለሁ፡፡

ስለባንክ ኖት ምስል ሌላም ላጫውታችሁ:: ዐሥር ብር ላይ የነበረው ሥዕል አንዲት ሴት ስፌት ስትሰፋ የሚያሳይ ነው:: እንዲት ወዳጄ "እናንት ጉደኞች፣ ብላችሁ ብላችሁ ሴተኛ አዳሪነትን ሕጋዊ አድርጋችሁ የግብረ ሥጋ ግንኙነትን ዋጋ ወሰናችሁ አይደል?" ትለኛለች:: አልገባኝም እስረጂኝ እላታለሁ:: ስፌት ባራዳ ልጅ ቋንቋ ግብረ ሥጋ መፈጸም መሆኑን አስታውሳኝ ያወጣሽውን ኖት አውጣና እይ ትለኛለች:: ወቸ ጉድ፣ ሰዉ እኮ ፍጹም የማይቻል ነው ብዬ አልጎመጎምኩና አንቺስ የእንዲህ ዓይነት ቋንቋ  አቀባባይ መሆንሽ ምን ይሉታል? አልኩና ዋጋዋን ሰጠኋት::

የብር ለውጥ በተጀመረ በሦስተኛው ወር ጥር አራት በዐሥር ሰዐት ላይ ተጠናቆ የኢዲዩ ጦር ሁመራን በዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ወረረ:: የብር ለውጥ ከመጀመሩ በፊት በየቦታው ፈነዳድቶ የነበረው አመጽ ረጭ በማለቱ ለውጡ በሚካሄድበት ወቅት የመለወጫ ጣቢያዎች በተቋቋሙባቸው አካባቢዎች ሰላም ሰፍኖ ነበር:: ክስተቱ የብር ለውጥ የአመጽን አይነጥላ ከልሎ የያዘ አስመስሎት ነበር:: የኢዲዩ ጦር ወደ ሁመራ መቃረቡን ሰምተን የሁመራ ባንክ ከመዘረፉ በፊት አንድ ነገር አድርጉ ብዬ ለደርጉ አለማየሁ ኃይሌ ባነሳበት ያን የተለመደ ኪ ኪ ኪውን አጠጣኝና፣ ስማ ታደሰ፣ አብዮት በሚካሄድበት አገር ሁሉ የጸረ አብዮት እንቅስቃሴ መኖሩ ሳይንሳዊ ሐቅ ነው፤ እንደ ኢዲዩ አይነቱ ተቃዋሚ ባይኖር ኖሮ በኢትዮጵያ አብዮት መካሄዱ አይታወቅም ነበር፤ የታሪክን ግዴታ ለማሟላት እንዲያው ፊርፊር ይላሉ እንጂ የትም አይደርሱም፣ የሳት እራት ሆነው ይቀሩዋቸታልና ምንም አያሳስባችሁ ይለኛል:: የኔ ፍላጎት ስለትልቁ ሥዕል ፕሮፖጋንዳ መጋት ሳይሆን ሁመራ የላክነው ገንዘብ እንዳይዘረፍብን ነበርና ሰሚ ካጣን መቼስ ማል ጎደኒ፣ እግዚአብሔር አንተ ታውቃለህ ብለን አማትበን ተቀመጥን:: የፈራነው ደረሰ::

ኢዲዩ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሲደርስ የባንኩ ገንዘብ ካዝና ውስጥ ተቆልፎ ያገኛል:: እንደማስታውሰው የቅርንጫፉ ሠራተኞች ቁልፉን ይዘው ሸሽተዋል:: ካዝናውን ለማስተፋት ሁለት ቀን ሙሉ ቢሞክሩም

ሳይሳካላቸው ይቀራል። በመጨረሻ ከሱዳን የብረት ማቅለጫ እሳት አምጥተው ተርክከው እንደከፈቱት ሰማን። ያገኙት ብር ከለውጥ የተረፈና ባንኩ ወደጎንደር ሳይልክ የቀረው ብቻ ስለነበር ብዙም አልተወሰደብንም። የገንዘቡ ዘረፋ እልህ አስጨራሽና አድካሚ እንደነበር ስንሰማ ሳይለፉ መብላት የለም ብለን ከሩቅ ተሣለቅንባቸው።

ሌላ መጠነኛ ችግር ሊገጥመን የነበረው መርሀቤቴ ዋና ከተማ ዓለም ከተማ ነበር። ገንዘብ የመለወጡ ተግባር እንደተጠናቀቀ የገንዘብ መለወጫውን ጣቢያ የሚጠብቁት ፖሊሶች ሠራተኞቹ ይዘውት ለመሄድ ያዘጋጁትን ገንዘብ ሊዘርፉ ነው የሚል መረጃ ይደርሰናል። እነሱ ለነገ ሲያስቡን እኛ ሌሊት ወጥተን አመለጥናቸው።

የብር ለውጥ ተጠናቆ ሒሳብ ሲሰላ ምንም የገንዘብ ጉድለት አልታየም። እንዲያውም ከተሰራጨው አዲስ ገንዘብ የተሰበሰበው በለጠ። ይህም መሳ ለመሳ የተለወጠውን በሚመለከት ነው። ከባንኮች ውጭ በሕዝብ እጅ ከነበረው ገንዘብ 97 ከመቶ መሰብሰቡን አረጋገጥን። በእሳት የሚቃጠል፣ በስብሶ የሚቀር፣ ከተቀመጠበት የሚረሳ፣ አይጥና ብል የሚበላው እንዲሁም ከአገር ወጥቶ ሳይመለስ የሚቀር ገንዘብ እንደሚኖር ስለሚታወቅ ከመጀመርያውኑ ሁሉም ይሰበሰባል ብለን አልገመትንም ነበር። በብዙ አገሮች ብዙ ገንዘብ እንደሚዘረፍና ጉድለት እንደሚደርስ ሰምተን ስለነበር የኛ ፕሮግራም በሁሉም ረገድ የተዋጣለት ሆኖ ስለተገኘ በጣም ደስ አለን። ሥራው ላይ በተሰማሩት ሁሉ ኮራንባቸው።

ትብብር ካለ ብዙ ማከናወን እንደሚቻል የነበረንን እምነት ይህ የተሳካ የገንዘብ ለውጥ ፕሮግራም አፈጻጸም አጠናከረልን። በመሆኑም የገንዘብ ድርጅቶችን በአዲስ ለማደራጀት ከበድ ያሉ ፕሮግራሞችን ለመዘርጋት ተደፋፈርን።

# የባንኮች ኮምፒዩተር ማእከል

ብሔራዊ ባንክ በነበርኩበት ወቅት ካከናወንናቸው ውጤታማ ሥራዎች አንዱ የባንኩንና የንግድ ባንክን ሒሳቦች በኮምፒዩተር እንዲቀመሩ ማድረጋችን ነበር። ብሔራዊ ባንክ በየካቲት 1967 እንደሄድኩ አንድ አሜሪካዊ ድርጅት ምን ዓይነት የኮምፒዩተር ሲስተም እንደሚያስፈልግ አጥንቶ እንዲያቀርብ በኮንትራት መቀጠሩን አረዳለሁ። ያኔ ሰፍኖ በነበረው የጋለ ብሔራዊ ስሜት እገፋፋና ጥናቱን የኛው ልጆች፣ ማለትም ኢትዮጵያውያን፣ ማድረግ ይችላሉ በሚል እምነት ከአሜሪካኑ ኩባንያ ጋር የተፈረመውን ውል በስምምነት ሰረዝነው።

አዲስ አበባ ባንክ በነበርኩበት ወቅት የባንኩ የሒሳብ ክፍል ኃላፊ ፍስሐ አርአያ ዘወትር ስለኮምፒዩተር ሲያወራ እሰማ ነበርና ጥናቱ በርሱ ሰብሳቢነት እንዲካሄድ አደረግሁ። ብዙ ጊዜ ተሰጥቶትም የትም ሊያደርሰው ስላልቻለና ከአቅሙ በላይ ሆኖ ስላገኘው ሌላ ዘዴ ለመፈለግ ተገደድን። በአገሪቱ አሉ የሚባሉትን በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች የኮምፒዩተር ክፍል ኃላፊዎችን ሰበሰብናቸውና እንዲረዱን ወይም እንዲተባበሩን ጠየቅናቸው። ኤክስፐርቶቹን ያሰባሰብናቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ከአየር መንገድ፣ ከቴሌኮሚኒኬሽንና ከመብራት ኃይል እንደነበር ትዝ ይለኛል። ሌሎችን ዘንግቻቸዋለሁ። ኤክስፐርቶቹ ከብሔራዊ ባንክና ከንግድ ባንክ ካወጣጣናቸው ባለሙያዎች ጋር አንድ ላይ ሆነው ሥራውን ተያያዙት። ዋናው ተግባራቸው በባንኮች ውስጥ የሚከናወኑትን ሥራዎች ዓይነታቸውንና መጠናቸውን በትክክል ተረድተው ተስማሚ የኮምፒዩተር ሲስተም መምረጡ ላይ እንዲያማክሩን ነበር። ከነሱ ያገኘነውን ምክር መሠረት አድርገን የኮምፒዩተር ግዢ ጨረታ ከአንዴም ሁለቴ እንዳወጣን ትዝ ይለኛል። በመጨረሻ ከቀረቡት መካከል የ N C R ኩባንያ ያቀረበው 8550 ሲስተም ተመረጠና ተተከለ።

ኮምፕዩተሩ ከገባ በኋላ መሥራት አለመሥራቱ ተሞከረና አስፈላጊው ማስተካከያዎች ተደርገውለት ለማሠራት ጉዞው ተጀመረ፡፡ በሜካኒካል ማሺን አኀዛዊ መረጃዎችን ፖስት የማድረጉ ወይም የመመዝገቡ ሥራና በኮምፕዩተር የመቀመሩ ተግባር ለጥቂት ወራት ጎን ለጎን እንዲካሄድ ከተደረገ በኋላ ኮምፕዩተሩ አስተማማኝ ነውና የቀድሞው አሠራር ይብቃውና በኮምፕዩተሩ ብቻ ተገልገሉ ብለን ለንግድ ባንክና ለብሔራዊ ባንክ የሒሳብ ክፍሎች መመሪያ ሰጠን፡፡ ነገር ግን የንግድ ባንክ ሥራ ኃላፊዎች ኮምፕዩተሩ አስተማማኝ ስላልሆነ የምናውቀውን አሠራር አንለቅም ብለው ሙጭጭ አሉ፡፡ አምስት ዓመት አጥፍተን፣ ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ ከስክሰን እዚህ ከደረስን በኋላ ፕሮግራሙን እርግፍ አድርገን እንድንተወውና መሳለቂያ እንድንሆን የተፈለገ መሰለኝና ውስጥ ውስጡን መብገኔ አልቀረም፡፡

የንግድ ባንክ ችግር ምን እንደሆነ ለመረዳት የሚመለከታቸውን ሁሉ ሰበሰብኩ፡፡ የንግድ ባንክ ኃላፊዎች ሲሰተሙ ይሠራል ብለን አናምንም ብለው አሁንም ድርቅ አሉ፡፡ የኮምፕዩተር አዋቂዎች እነጌታቸው ወልደሥላሴ፣ ይሠራል ብለው ሊያሳምኑ ቢሞክሩም ፍንክች አንል ይላሉ፡፡ በወቅቱ የብሔራዊ ባንክ የሒሳብ ክፍል ኃላፊ የነበረው አቶ አንዱአለም ተመስገን ይነሳና ሲስተሙ እንደሚሠራ እኛ አምነናል፤ ብሔራዊ ባንክ የቀድሞውን አሠራር ትቶ ወደአዲሱ ለመሸጋገር ተዘጋጅቷል፤ መሟላትና መስተካከል ያለባቸው አንዳንድ ጉዳዮች ስላሉ የሚሻለው እነሱን ማሟላቱ ላይ መተባበር ነው ብሎ ተናገረ፡፡ አቶ አንዱዓለም በጠንቃቃነቱና በሥነሥርዓት አክባሪነቱ ከማደንቀው በስተቀር አዲስ ነገር መሞከር አለበት፣ ኀበዝ ተነስ፣ ደፍረን እንግባበት ከሚሉት ጎራ አሰልፌው አላውቅም ነበርና በሚናገርበት ወቅት በሐሳቤ አዳምጥ የነበረው የጥላሁን ገሰሰን ሂድ ወደፊት፣ ይለይለት የሚለውን የዘፈን ስንኝ ነበር፡፡ አቶ አንዱዓለም ይቻላል ሲል የንግድ ባንክ ኃላፊዎች አይቻልም ማለቱ አሳፈራቸውና እየተጠማዘዙም ቢሆን መስመር ገቡ፡፡

በየዓመቱ መጨረሻ የባንክ ሒሳብ ሲዘጋ ውሎ አዳር መሆኑ የፀሐይ መውጣትና መጥለቅ ያህል የማይቀር ነበር። የትርፍ ሰዓት ክፍያም በዚያው መጠን ይኖራል። ኮምፕዩተሩ በገባበት አመት ሒሳብ የተዘጋው የዕለቱ የሥራ ሰዓት ሲያበቃና ሠራተኛ ከሥራ በሚወጣበት ሰዓት ነበርና ጉድ ተባለ። ቢሆንም፣ ከቅርንጫፎች በሚገኙ መረጃዎች መሠረት ማስተካከያዎችን በማግስቱ ማድረግ የማይቀር ነው። ኮምፒዩተሩ ተግባራዊ እንዲሆን ያልተፈለገው አንድም ከትርፍ ሰዓት ክፍያ ጋር የተያያዘ መሆኑን ለመረዳት ጠንቋይ ዘንድ መሄድ አላስፈልገንም።

የኮምፕዩተራይዜሽን ፕሮግራም አስተባባሪያችን የዩኒቨርስቲው ኮምፕዩተር ማእከል ኃላፊ የቀበናው ጌታቸው ወልደስላሴ ነበር። ከጓደኛዬ ከከበደ አድነው ጋር አብሮ አደጎች ናቸው። ዩኒቨርስቲ ሆነን ከበደ በሒሳብ ነክ ትምህርቶች በጣም ጎበዝ ስለነበር የጉብዝናው ምስጢር ምን እንደሆነ እንዲገልጽልኝ ጠይቄው በልጅነቱ ዘመን በሒሳብ ጎበዝ መሆን በቀበና አካባቢ ዝናን የሚያተርፍ ስለነበር የሰፈሩ ልጆች ማትማቲሽያን ነው መባልን ይመኙ እንደነበር አጫውቶኛል። ኮምፕዩተር ስሙ እንጂ አገልግሎቱ በውል በማይታወቅበት ዘመን ነበር ጌታቸው ጥበቡን ለመቅሰም ወደ አሜሪካ የሄደው። ከኒው ጀርሲው ረትገርስ ዩኒቨርስቲ በኮምፒዩተር ሳይንስ በማስትሬት ዲግሪ እአአ 1972 ተመረቀ። በዚህ ሙያ በመጀመሪያ ከሠለጠኑት ኢትዮጵያውያን አንዱ ነው። የ0ሥራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተና በኮምፕዩተር እንዲታረም ዘዴውን ያወጣውና በተግባር የተረጎመው ጌታቸው ነው ይባላል።

የባንኮች የሒሳብ ሥራ ሙሉ በሙሉ በኮምፒዩተር ሊጀመር በዋዜማው ጌታቸው ባንክ ውስጥ ሲሠራ ውሎ አድሯል። አንዳንድ የባንክ ሠራተኞችም ይህን አድርገዋል። ጌታቸው በፈቃደኝነት፣ እንደሌሎቹ ከሌሎች መሥሪያ ቤቶች በአማካሪነት እንዳሰባሰብናቸው ባለሙያዎች፣ ከሞላ ጎደል ያለምንም ክፍያ፣ የተባበረን ሰው ስለነበር ለሱ ያለኝ አድናቆት በጣም ከፍተኛ ነው። ለገንዘብ ሳይሆን ለሙያው ያደረ ሰው ነበር።

በየመስኩ የጌታቸው ዓይነት ሐቀኞች የኢትዮጵያ ልጆች ከተበራከቱ አገራችን በልማት ጎዳና እንድትገፋ ማድረግ ይቻላል። በየመስኩ መልካም አስተዋፅኦ ያደረጉትንና የሚያደርጉትን አገር ወዳዶች መጠበቅና ማበረታታት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነትና ተግባር ሊሆን ይገባል።

የኮምፒዩተራይዜሽን ፕሮግራም በተግባር ውሎ አመርቂ ውጤት እንደተገኘ ስለወሰድናቸው እርምጃዎችና ስለተገኙት ውጤቶች ለባንኩ ቦርድ ገለጻ አደረግሁ። የቦርዱ አባላት ትኩረት ያረፈው በተሠራው ሥራ ላይ ሳይሆን በሥልጣን ጥያቄ ላይ ነበር። ቦርዱ ሳያውቀውና ሳይፈቅድ ለፕሮግራሙ ማስፈጸሚያ ይህን ያህል ገንዘብ እንዲወጣ መደረጉ የሚያስጠይቀኝ ሊሆን እንደሚችል ተነገረኝ። ፕሮግራሙን ለቦርድ አቅርቤ ያላስፈቀድኩት ሆን ብዬ ነው፤ ካቀረብኩት ውድቅ ያደርጉብኛል የሚል ስጋት ስላደረብኝ ነበር።

በተደጋጋሚ የተመለከትኩት የበላይ ባለሥልጣኖች ተግባራቸው ከሥር ያለውን ባለሥልጣን ጨቁኖ ወይም ጠፍሮ መያዝ እንጂ በሥራው ማበረታታትና ውጤት ማስመዝገብ እስከቻለ ድረስ ያሰበውን በተግባር እንዲተረጉም ዕድል መስጠት ሞት ይመስላቸዋል። ለምሳሌ፣ አንድ ብር ወረቀት መሆኑ ቀርቶ እንደሌሎች ቅንስናሽ ገንዘቦች ከብረታ ብረት ቢሠራ ብዙ ገንዘብ ማዳን እንደሚቻል ያቀረብኩትን ሐሳብ በተልካሻ ምክንያት ውድቅ አድርገውብኛል። እንዲሁም፣ የገቢ እቃዎች ዋጋ ትክክለኛነትና ጥራት ለዚሁ በተደራጁ ዓለም አቀፍ መርማሪዎች ቢጣራ አገሪቱ በየዓመቱ ብዙ ሚሊዮን ብር ማዳን እንደምትችል ዝርዝር ጥናት አቅርቤ በተግባር እንዲተረጎም እንዲስማሙ ብጠይቃቸው ያለበቂ ምክንያት ውድቅ አድርገውታል። በእነዚህና በሌሎች ምክንያቶች ቦርዱን እንደሥራ አጋሬ ሳይሆን እንደጎታች ኃይል እንዳየው የተገደድኩበት ወቅቶች ጥቂት አልነበሩም።

የጠቀስኳቸው ዓይነት ገጠመኞችን መሠረት በማድረግ የአዛዡንና የቦርዱን ግንኙነት አስመልክቶ እከተለው የነበረው የአሠራር ፖሊሲ፣ አንድ ጉዳይ ወደመንግሥት በግድ መተላለፍ ያለበት ካልሆነ በቀር ወይም በሕግ ወይም

በመንግሥት መመሪያ የተደነገገ ካልሆነ በቀር ቦርዱ ውሳኔ ያደርግልኝ ብዬ አላቀርበውም ነበር፡፡ ይህን በማድረጌ አንድ ነገር ቢበላሽ ወይም ሳይሰምር ቢቀር ማንቁርቴ እንደሚያዝ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን መሠረታዊ ኃላፊነቴ ውጤት ማስመዝገብ ነው ብዬ ስላመንኩ ሥራ ሠርቼ የመጣው ይምጣ፣ የምጠየቅበትም ከሆነ ልጠየቅበት ብዬ ቆረጥኩ፡፡ ደግነቱ ከሚመለከታቸው የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በቅርብ እየተመካከርኩና የሚሰጡኝን ምክር ሳልንቅ እየተቀበልኩ እራመድ ስለነበር በሠራሁባቸው ዓመታት አንድም የሚያስጠይቀኝ ሁኔታ ሳይፈጠር በሰላም በመገላገሌ ከልብ ደስ ይለኛል፡፡

# የሞቃዲሾ ጉዞ

በሐምሌ ወር 1967፣ የባንኩ ምክትል አዛዥ ሆኜ በተመደብኩ በአምስተኛው ወር፣ በሞቃዲሾ ከተማ በሚደረገው የምሥራቅና ደቡባዊ አፍሪቃ አገሮች ማእከላዊ ባንኮች ስብሰባ ላይ ባንኩን ወክዬ እኔ እንድገኝ ይወሰናል፡፡ በወቅቱ የኢትዮጵያና ሶማልያ ግንኙነት በጣም ሻክሮ ስለነበር ከኢትዮጵያ ወደ ሶማልያ ለሥራ ጉዳይ መሄድ ተቋርጦ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ወቅቱ አምባሳደር አያሌው ማንደፍሮ ከሞቃዲሾ ተመልሶ አዲስ አበባ እንዲቀመጥ የተደረገበት፣ ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት አሜሪካና የሶቪየት ኅብረት ከኢትዮጵያና ሶማልያ ጋር የነበራቸውን ወዳጅነት ለመለዋወጥ የሚዘጋጁበት፣ ሲያድ ባሬ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት የዓመቱ ሊቀመንበር የሆነበትና ሶማልያና ኢትዮጵያ በራድዮ የሚሰዳደቡበት ነበር፡፡

የባንኮች ሥራ ከፖለቲካ የተገለለ ስለሆነ የስብሰባው ጥሪ ሲደርሰን ሞቃዲሾ የማንሄድበት ምክንያት የለም ተባለና እላይ እንደገለጽኩት እኔ በስብሰባው ላይ እንድገኝ ተወሰነ፡፡ የሥራው ጉዞ ለእኔ ከአገር ውጭ ለመውጣት የመጀመሪያው ከመሆኑም በስብሰባው ላይ መሳተፍ ደግሞ ሌሎች የአፍሪቃ ማእከላዊ ባንኮች እምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ ሐሳብ

ለማግኘትና አስተሳሰባቸውን ለመቅሰም ጥሩ አጋጣሚ ይሆንልኛል ብዬ ስላመንኩ የስብሰባውን ቀን በጉጉት ስጠባበቅ ሰነበትኩ::

በመሄጃዬ ቀን ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ስደርስ መውጣት አትችልም ተባልኩ:: ምክንያቱን ብጠይቅ በድፍኑ ትእዛዝ ከላይ ስለመጣ ነው እባላለሁ:: የመውጫ ቪዛ እንዳለኝ ባስታውቅም ምንም ማድረግ እንችልም ተባልኩ:: እዚያው ሆኜ በየቦታው ስልክ ደዋወልኩና በመጨረሻ ሊፈቀድልኝ ቻለ:: ከልካዮቹ የፈሩት ሞቃዲሾ ሄዶ ይከዳል ይሁን ወይስ የሶማልያ ባለሥልጣኖች ይተናኮሉታል ብለው አስበውልኝ እንደሆነ አላውቅም::

በሁለቱ አገሮች መካከል ቀጥተኛ የአየር ጉዞ ግንኙነት ስላልነበረ ወደ ሞቃዲሾ የሚሄድ አውሮፕላን ለማግኘት ወደ ናይሮቢ መብረር ያስፈልግ ነበር:: ከናይሮቢ ሞቃዲሾ የነበረው በረራ በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ነበር:: ናይሮቢ አየር ማረፊያ ስደርስ ከደቡብና ምስራቅ አፍሪቃ ለስብሰባው የሚሄዱ ልዑካን አንግዳ ማረፊያው ተሰብስበው አገኘኋቸው::

አውሮፕላኑ ውስጥ ከኢሚግሬሽን ፎርም ጋር ስለሶማሊያ ውጭ ምንዛሪ ደንብ የሚገልጽ አንድ ወረቀት ሰጡን:: ወረቀቱ ላይ ስምንት ያህል የስፔሊንግ ግድፈቶች አገኘሁ:: ስለሶማልያ ሲነሳ አሁንም ከሚታወሱኝ ነገሮች መካከል ያ ወረቀት ይገኝበታል:: ሶማሌዎች ዝርክርክና ጥንቃቄ የሚጎድላቸው ሳይሆኑ አይቀሩም፣ ስሕተቱ የባሕሪያቸው ነጸብራቅ ከሆነ ኢትዮጵያን እየተንጠራሩ የሚፈታተኑት በከንቱ ነው፣ የትም አይደርሱም የሚል ግምት ወሰድኩ::

ሞቃዲሾ ደርሰን የአውሮፕላን ማረፊያው እንግዳ መቀበያ እንደገባን አንድ ቴፕ ሬኮርደር ያነገበ ጋዜጠኛ በቀጥታ ወደኔ ይቀርብና በአማርኛ ጤና ይስጥልኝ፣ ኢትዮጵያዊ ነህ? ብሎ ይጠይቀኛል:: ገና አዎን ከማለቴ ማይክሮፎኑን ወደ አፌ ያስጠጋና ስለስብሰባው ቃለመጠይቅ ይጀምራል:: ከንግግሩ ፍጥነት የተነሳ ለቃለ መጠይቁ ልተባበር ወይስ አልተባበር?

የሚለውን ጥያቄ ለራሴ ለመመለስ ጊዜ አልሰጠኝም። ለማናቸውም ጥያቄዎቹን መለስኩ። ስንጨርስ የቃለመጠይቁን ምልልስ ምን እንደሚያደርገው ሳይነግረኝ ተሰናብቶኝ ሄደ።

ወደ ተዘጋጀልኝ አውቶሞቢል ልገባ ስል አንድ የሲቪል ልብስ የለበሰ ሰው ይመጣና ስሜ ኮሎኔል እገሌ ይባላል፤ ለአንተ ደኅንነት የተመደብኩኝ ነኝ ብሎ ተዋወቀኝ። ለሌሎቹ መልዕክተኞች ባልደረባ እንዳልተመደበ ተመለከትኩና የሶማልያ ቆይታዬ ትንግርታዊ ሊሆን ነው አልኩ።

የሶማልያ ራድዮ ጣቢያ ከቀኑ ስምንት ሰዓት የሚያስተላልፈውን የዕለቱን አማርኛ ፕሮግራም የከፈተው ዛሬ ከኢትዮጵያ ከመጣ ባለሥልጣን ጋር ያደረግነውን ቃለመጠይቅ እናሰማለን በማለት ነበር። ሞቃዲሾ ያለው ኤምባሲያችን ከመደበኛ ሥራዎቹ አንዱ የራድዮ ጣቢያው በአማርኛ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያስተላልፈውን መከታተል በመሆኑ የኤምባሲው ሠራተኞች የዕለቱን ፕሮግራም ለማድመጥ ጆሮአቸውን ተክለው ሳለ ስለቃለመጠይቁ ሲገለጽ ቴፕ ሪኮርደር ፍለጋ ተራወጡ። ከመንግሥት ጋር ተጣልቻለሁ ወይም ተቃዋሚ ነኝ የሚል አኩራፊ እንዲሁም ከሃዲ ወደ ሶማልያ መሄድ የማይታወቅ ስላልነበረ ዛሬ ከድቶ የመጣው ደግሞ ማን ይሆን? መባባላቸው አልቀረም። የዜናው ፕሮግራም አልቆ ቃለመጠይቁ መተላለፍ ጀመረ። የፖለቲካም ሆነ የሁለቱን አገሮች ግንኙነት የሚመለከት አንድም ጠብታ ስላልነበረበት የኤምባሲው ሠራተኞች እፎይ ሊሉ ቻሉ።

ከመካከላቸው ስድስት ኪሎ አብረን ባንድ ወቅት እንማር የነበረው አቶ ኃይሉ ከበደ ነበረበት። አረፍኩበት ሆቴል ድረስ ሊፈልገኝ መጣና ተገናኘን። እኔም የማውቀው ሰው በማግኘቴ ደስ አለኝ። "ምን ነካችሁ? በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ አለመሆኑ እየታወቀ ትመጣለህ ተብሎ እንዴት አስቀድሞ ሳይነገረን ቀረ?" ይለኛል። እኔም ስመልስ፣ እኔ ምን አውቄ? ስለፕሮቶኮል የማላውቅ፣ አገር ትሻሻል እንደሆን ብዬ ባዲስ ጉልበት ቀና ደፋ የምል አዲስ ባለሥልጣን ነኝ፤ ይህ የመጀመሪያው ጉዞዬ ነው፤ ማሳወቅን በተመለከተ ስለጉዳዩ የዳበረ ልምድ ያላቸው የባንኩ

ፕሮቶኮል ክፍልና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዴት እናዳላሳወቋችሁ አላውቅም አልኩት።

ከሶማልያ እስክወጣ ድረስ ኃይሉ ምንም ሳያዛንፍ በደንብ ተንከባከበኝ፣ አስተናገደኝ። የሶማልያ ባለሥልጣኖች ሕዝባቸው አበሻ ጨካኝ ቅኝ ገዥ ነው እያሉ እንደሚያስተምሩት ገለጸልኝ። ሞቃዲሾን እየተዘዋወርን አሳየኝ። ጠባቂዬ ኮሎኔል ሲከተለን እናየዋለን። ብዙ የአየር መቃወሚያ መሣሪያዎች ተጠምደው፣ እንዲሁም በየአካባቢው ትናንሽ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ሲሠሩና የወታደር ተሽከርካሪዎች ሲርመሰመሱ ዐየሁ።

ኃይሉ ስለሶማልያ ባለሥልጣኖች አሠራር የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረኝ በራሱ ላይ ስለደረሰው በደል አጫወተኝ። በግማሽ ጎኗ ኢትዮጵያዊት የሆነች ሴት ጓደኛ ነበረችው። አንድ ቅዳሜ ቀን እቤቱ ከተጠቀሰችው ጓደኛው ጋር ምሳ ሲመገቡ ዘበኛው ወደእርሷ ይቀርብና ጓደኛሽ ከአጥር ውጭ ሆና አንዴ ላነጋግርሽ ትላለች ይላታል። ኃይሉና ልጅቱ ተያዩ። ጓደኛዬ እዚህ መኖሬን ማን ነገራትና ልትመጣ ቻለች? ብላ ጥርጣሬዋን ከገለጸች በኋላ ፈላጊዋን ለማየት አንገቷን ከአጥሩ ውጭ ገና ብቅ ከማድረጓ አሰፍስፈው ሲጠባበቁ የነበሩት የሲያድ ባሬ ጸጥታ ሠራተኞች አፈፍ አድርገው ያዟት፣ በጥፊና እርግጫ እያዳፉ ይዘዋት ነጎዱ። ኃይሉ ልጅቱን ከዚያን ቀን በኋላ ዐይቷት አያውቅም፣ ትኑር ትሙትም የሚነግረው አጣ። ሞቃዲሾ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልዩ ክትትል እንደሚደረግበትና በከፍተኛ ስጋት እንደሚኖር ነገረኝ።

ያረፍንበት ሆቴል ስሙ ጁባ ሲሆን ሶማሌዎች ያለምንም የውጭ ሰው እርዳታ የሠራነው ነው ብለው ይኮሩበታል። ካንዴም ሁለቴ ወድቆ የተነሳ ሕንጻ ነው። ይህን የገለጸልን እራሱ ሲያድ ባሬ ነበር። ሕንጻው እየተሠራ ሳለ ይደረመሳል። እጅ አንሰጥም ብለው እንደገና ገንብተው አነሱት። ለሁለተኛ ጊዜም ፈርሶ እንደገና ተገነባ ብሎ የነገረን ይመስለኛል።

ስለሆቴሉ መስተንግዶ አንድ የማስታውሰው፣ የፀሐይ ኃይል ያየለበት ወይም ጉልበቱ የደከመበት ተራ መንገደኛ ዘው ብሎ ገብቶ እንግዳ መቀበያው ሶፋ ወንበር ላይ አርፎ የፈቀደውን ያህል ከቆየ በኋላ ተነስቶ ሲወጣ እናይ ነበር፡፡ አሳላፊዎች ሴቶች ደግሞ ነጠላ ጫማቸውን እያነሱ እንደመራመድ መሬት ለመሬት ሲጎትቱና ማስቲካ ቂጭ ቂጭ እያደረጉ ሲያኝኩ ማየት ለእኔ ከፍተኛ የሥነስርዓት ጉድለት ሲሆን ሶማሌዎቹን ግን ድርጊቱ ምንም እንደማይረብሻቸው ተመለከትኩ፡፡ አንዱ አስነዋሪ ነው የሚለው ለሌላው ተቀባይነት ሊኖረው ስለሚችል ወደ ውጭ አገር ሲኬድ ያኗኗርና ያመጋገብ ባሕሎች አስመልክቶ አስተያየት ከመስጠት በፊት ስለሚመለከተው አገር ባሕል ጠንቅቆ መረዳት ከብዙ ችግር ያድናል፡፡

ስለሆቴሉ በተለይ የማስታውሰው ከጀርባው የነበረውን ትልቅ በጎጆ መልክ የተሠራው መዝናኛ ነው፡፡ የስብሰባው ተሳታፊዎች እስቲ ገብተን ምን እንደሚመስል እንይ ተባብለን አንድ ምሽት ተሰባስበን ገባን፡፡ አዳራሹ በጣም ትልቅ ነው፡፡ ማዶ ለማዶ በቀላሉ መተያየት አይቻልም፡፡ አንዱም ምክንያት መብራቱ ሆን ተብሎ ጨለምለም ስለተደረገ ነው፡፡

በጣም የሚያስገርመው የሞቃዲሾ ቆነጃጅት በነቂስ ወጥታችሁ እዚያ ስፈሩ የተባለ ይመስል ነበር፡፡ ሁኔታው በፖለቲካ እይታ ሲገመገም ደግሞ ሶሻሊዝም በሶማልያ እጅ እጅ ያለበትና ሌኒኒዝም ወደ አየር ማረፊያ ጣቢያ ለማምራት ያኮበኮበበት ወቅት ስለነበር አዳራሹ የኤኮኖሚና ማኅበራዊ ችግሮች ያፈናቀላቸው ምስኪን አንስታት የቱሪስት ዶላር የሚቃርሙበት ጎሬ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

የዳንስ ሙዚቃ ጸጥ ሲል የመዝናኛው መዘጊያ ሰዓት ለመቃረቡ ምልክት ስለሆነ እዚያ የታጎረው ጉብልና ኮረዳ ደጅ ፈሰሰና ሌላ አስገራሚ ትርዒት መታየት ጀመረ፡፡ ሴቶቹ እንግዶቹን ይከቡና እኔን ካልወሰድክ እያሉ ያስጨንቃሉ፡፡ እንግሊዝኛ የሚቆጣጥሩት ሴቶች ስለተጫራች ቢጤዎቻቸው ለመጻፍ የሚያሳፍር ነገር ሲናገሩ ሰምቻለሁ፤ በዓይን የሚታየውን ለተመልካች ትተው የውስጥ አካላቸውን በተመለከተ በገሀድ ሲናገሩ ጆሮ

ማመን የሚያቅተው ነገር ነበር፡፡ መሐመድ ሸሪፍ የፓሪስ ሴተኛ አዳሪዎች መንገድን እንደቅርጫ ሥጋ ተከፋፍለው እንደሚቆጣጠሩት ከነገረኝና በኋላም እራሴ ካየሁት የከፋ ትርኢት በጎረቤታችን፣ ያውም በሶሻሊስቷ ሶማልያ መካሄዱን ሳይ በጣም አዘንኩ፡፡ በወንድና ሴት ግንኙነት አኳያ የእያንዳንዳቸው ሚና ምንድነው? ለሚለው የኛም ይሁን የሶማልያ ባሕል ከደነገገው ውጭ አየሁና ዘገነነኝ፡፡ እኔም እንደሌላው ኢትዮጵያዊ ሁሉ እኛ የተለየን ስለሆንን እንደዚህ ዓይነቱ ርካሽነት የኛን ሴቶች ሲያልፍም አይነካካቸውም ብዬ በጊዜው ተመጻድቄአለሁ፡፡ በራስ ደስታ ዳምጠው ጎዳና ሲያልፍ ቀሚስ ተገልቦ ያየ አሽከርካሪ አሁንም እኛ የተለየን ነን ይል እንደሆነ አላውቅም፡፡ የማውቀው ነገር ቢኖር የትም ሆነ የት የሰው ልጅ ምኞቱ፣ ተስፋው፣ ሕልሙ በሰላም፣ በፍቅር፣ በብልጽግናና በክብር ከሌላው ጋር ተስማምቶ መኖር ነው፡፡ ዓላማውን እውን እንዳያደርግ ሰው ሰራሽ ወይም ተፈጥሮአዊ እንቅፋት ሲገጥመው ወይም ሁኔታዎች ሳይቀነባበሩለት ሲቀሩና አሰበው ቦታ መድረስ እንደማይችል ሲያውቅ ኑሮውን ለማሸነፍ የማይፈነቅለው ድንጋይ አይኖርም፡፡ ክብሩንና ኩራቱን አሟጦ የጨረሰው ሥጋውን ወይም ኅሊናውን በገንዘብ እስከመሸጥ ይደርሳል፡፡ ሞቃዲሾ ያየኋቸው ኮረዳዎች ምድባቸው ከዚህ ነው፡፡

ሲያድ ባሬ እጅግ ቢበዛ ለግማሽ ሰዓት ሊያነጋግራችሁ ይፈልጋል ተባልንና ወደሚገኝበት ስፍራ ይዘውን ሄዱ፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ጨርሳችሁ ትመለሳላችሁ ተብለን ስለነበር እራታችንን ሳንበላ ሄድን፡፡ የተወሰድንበት ቦታ የጦር ሰፈር ነበር፡፡ ሲያድ የአገሩ ጦር ኃይሎች የበላይ አዛዥም ስለነበር ጦር ሰፈር ውስጥ እንዲያነጋግረን የተደረገው ልዩ የፖለቲካ መልእክት ይኑረው አይኑረው አስቀድሞ ባላውቅም ንግግሩን ከሰማሁ በኋላ ግን ስብሰባው እዚያ መደረጉ ባጋጣሚ ነበር ለማለት ያዳግታል፡፡

በሁለት ሰዓት ይመጣል የተባለው ሰውዬ አራት ሰዓት ካለፈ በኋላ መጣ፡፡ አንድ በአንድ ሲጨብጠን እኔን በአማርኛ ጤና ይስጥልኝ አለኝ፡፡

ኢትዮጵያዊ መሆኔን አስቀድመው የነገሩት ይመስለኛል። አለዚያም መልኬን አይቶ ገምቶም ይሆናል።

ብዙ በመጠበቃችንና ረኀብም ስለጸናብን ተበሳጭተን ስለነበር ሰውዬውን በደኅና አላየነውም፣ የሚለውንም በደንብ አላዳመጥንም። ቆይታው ግፋ ቢል የእኩል ሰዓት ጉዳይ ነውና እንደምንም እንቻለው ያልነውን ሰዎች ሁለት ሰዓት ከአርባ አምስት ደቂቃ ሙሉ የቆጡን የባጡን ሲቀበጣጥር አስሮ አቆየን። ባመዛኙ የተናገረው በአፍሪቃውያን መካከል አንድነትን ስለማጠናከር ሲሆን አርባ አምስት ደቂቃ ሙሉ የተናገረው ስለኢትዮጵያና ሶማልያ ግንኙነት፣ በተለይ ስለ ኦጋዴን ነበር።

ሞቃዲሾ ከተማ ውስጥ በየሄድንበት ያየሁት አምስት ከዋክብት ያሉበት የታላቋ ሶማልያ ተብዬው ባንዲራ በየግድግዳው ላይ ተስሎ፣ በጨርቅ ላይ ተንጠልጥሎ ነበር። ገና አፍ በመፍታት ላይ ያሉ ሕፃናት ስለሶማልያ የሚያስተምሯቸው አገራቸውን ቅኝ ገዢዎች ተከፋፍለው እንደያዟትና ቀንደኛው ጠላታቸው ኢትዮጵያ እንደሆነች ነበር። ዒላማ ተኩስ የሚለማመዱት በቀኝ ገዢያቸው በኢትዮጵያዊ ላይ እያነጣጠሩና እየተኮሱ ነበር። አበሻ ወይም አማራ ማለት ሰው በላ አውሬ ማለት ነው እያሉ ይነግሯቸው ነበር። ባጭሩ፣ የሶማልያ መንግሥት ሕዝቡን ይመግብ የነበረው ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ ኢትዮጵያውያን መርዘኛ ፕሮፓጋንዳ ነበር። ሲያድ ባሬ ኢትዮጵያን ወሮ መሬትዋን ለመያዝና ኦጋዴንን ገንጥሎ ለመውሰድ የነበረውን ዓላማ ሕዝቡ እንዲደግፍና መስዋዕትነት እንዲከፍል የሚያደርገው ዝግጅት ግልጽ ነበር። የሶማልያ መንግሥትና ሕዝብ እዚህ ውስጥ ተዘፍቆ እያለ ነበር ሲያድ ባሬ አፍሪቃውያን ወንድሞቹን ሊያነጋግረንና ስለ አፍሪቃ አንድነትና ተቻችሎ ስለመኖር ሊሰብከን ያስጠራን።

ሲያድ አፍሪቃ የሰላም አስጠባቂ ጦር ያስፈልጋታል ብሎ ደጋግሞ ወተወተ። ስለኦጋዴን ባደረገው በጣም ረጅም ንግግር ውስጥ አበክሮ ያሰመረበት ጉዳዩን ሁለቱ አገሮች በስምምነት እንደሚጨርሱትና ሶማልያ

"መብቷን" ለማስከበር በኃይል የመጠቀም ፍላጎቱም ሆነ እቅዱ እንደሌላት ነበር።

በነገራችን ላይ የሲያድ ንግግር በእንግሊዝኛ ነበር። የሚጠቀምበት ስዋስው ብዙ ያልተስተካከል ቢሆንም ሐሳቡን የመግለጽ ችግር አይታይበትም ነበር። ለማስተላለፍ የሚፈልገውን መልዕክት መረዳት ችግር አልነበረብንም። የምንጠቀምበት ቋንቋ የተስተካከለ ካልሆነ ምን ይሉኝ ይሆን? የሚለው ስጋት ወደኋላ ሸብቦ እንደማይዘው ተመለከትኩ። ዋና የሚቆጠረው ሐሳቤ ነው እንጂ የቋንቋ ጥራት አይደለም የሚል ይመስል ነበር። እንግሊዝኛ የናቱ ቋንቋ ስላልሆነ ቢሰባብረው እንደማያሳፍረው ተገንዝቧል። በዚህም ሳላደንቀው አላለፍኩም።

የኛ አገር ሰው አቃቂርን በጣም ይፈራል። ከመስመር መውጣት ወይም ወጥቶ መታየት አይፈልግም። ስለሆነም አዳዲስ ነገር ከመሞከር ወይም ያሰበውን ደፍሮ ከመግለጽ ይቆጠባል። በበጎ መልኩ ደግሞ አጓጉል ተግባር ውስጥ መዘፈቅና የራሱንም ሆነ የወገኑን ስም መበከል ነውር መሆኑን ስለሚረዳ እርምጃው ጥንቃቄ አይለየውም። ቢሆንም፣ ተስማምቶ መኖር ትርጉሙ ተሸፋፍኖ መኖር መሆን የለበትም። ይሉኝታ ጥሩ ነው፤ የፍርሀትና ስንፍና መሸፈኛ ግን መሆን የለበትም።

አንድ ኅብረተሰብ ቀደም ብሎ የደነገገውን ወይም የደረሰበትን ደረጃ ብቻ እየተከተለ አገሩን ወይም ኅብረተሰቡን ያስቀደመ ወይም ወደፊት ያራመደ ሰው ታይቶ አይታወቅም። ሥልጣኔ የተስፋፋው ሳይንቲስቶች፣ አርክቴክቶች፣ መሀንዲሶች፣ ደራስያን፣ ሙዚቀኞች፣ ፈላስፎች፣ ፖለቲከኞች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ኤኮኖሚስቶች፣ ገበሬዎች፣ ኢንዱስትሪያሊስቶች፣ ወዘተ አዳዲስ አስተሳሰብ ለማስፈን ወይም አሠራር ለመፍጠር ያላሰለሰ ጥረት ስላደረጉና ስለተሳካላቸው ነው። በወቅቱ ከነበረው የኅብረተሰብ አስተሳሰብ በማፈንገጣቸው አንዳንዶቹ መሥዋዕት ሲሆኑ የሰው ልጅ ግን በተሻለ ዓለም ውስጥ ሊኖር ቻለ። መሥዋዕትነት ለውጥ ለማምጣት የሚከፈል ዋጋ ነው። የለውጥ ሐዋርያት ባይኖሩ ኖሮ

ሰው ለዘለዓለም በጭለማ ውስጥ ይዳክር ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ለኛ ሲል ሞተ ሲሉ ከተባለው የሚለይ አይደለም፡፡ የታላቁን ሮማ መንግሥትና አክራሪ የአይሁድ ሃይማኖትን በአንድነት ተጋፍጦ የዓለም ህዝብ አቅጣጫ ያስለወጠ አስተሳሰብ ማስፈን መቻል ክርስቶስ በእርግጥም መለኮታዊ ኃይል ቢኖረው ነው እንጂ እንዴት ሊሆን ቻለ? የሚያሰኝ ድርጊት ነበር፡፡ አማኝም ሆነ አረመኔ ለእሱ ያልሰገደ ለማንም ሊሰግድ አይችልም፡፡

ባጭር ቋንቋ፣ ለውጥ ከሌለ መሻሻል ሊኖር አይችልምና ለለውጥ የሚታገሉ ግለሰቦች አናት አናታቸውን ከማለት በፊት ምን እንዳሰቡ በቅጡ መረዳት ይጠቅማል፡፡ ታሪክ ከሚያስተምረን ነገሮች አንዱ ለውጥን የማይፈሩ ኅብረተሰቦች ከሌሎች ቀድመው መሄድ እንደቻሉ ነው፡፡ እኛም የለውጥ ሐዋርያትንና ትጉ ሠራተኞቻችንን ተንከባክበን፣ ደግፈን፣ አቅፈን፣ ካያዝናቸው ሌላው ከደረሰበት የማንደርስበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ የነበረውን ይዞ በመንዝ ብቻ የሚለወጥ ነገር የለም፡፡ እንዲያውም ውጤቱ ተያይዞ ገደል መግባት ሊሆን ይችላል፡፡ ወቅቱ ሲጠይቅ መድፈርና አዳዲስ ነገሮችን መሞከር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አኳያ እኛ ኢትዮጵያውያን ደካሞች ነን፡፡ ማሻሻል ወይም መሻሻል አለብን፡፡

መድፈርን በተመለከተ ሶማሌዎች ከኛ እንደሚሻሉ የታወቀ ነው፡፡ ለምሳሌ እዚህ ሰሜን አሜሪካ በዚህ ባሕላዊ ልዩነት የተነሳ አበሻውን ጥለውት እየሄዱ ነው፡፡ እኛ ጭምትነትና ጨዋነትን ስለምናበዛ ፈረንጆች ምን ነካችሁ? ደኅና አይደላችሁም እንዴ? እስከማለት ደርሰዋል፡፡ አንድ ሰው ሐሳቡን ሲገልጽ ቀጥተኛ፣ ደፋር፣ ለመብቱ ታጋይ ካልሆነ ውድድር የካፒታሊዝም ሥርዓት መሠረቱ በሆነበት አገር ሁሉም ተረማምዶበት ያልፋል፡፡ አትንኩኝ ብሎ ተገን ይዞ መቀመጥ ጥላችሁ እለፉኝ እንደማለት ይቆጠራል፡፡

አብዛኛው ያገራችን ሰው ልጁን አኮላሽቶ ነበር የሚያሳድገው፡፡ አንተ ልጅ ነህ፣ አርፈህ ተቀመጥ፣ ዝም በል፣ ታላቅህን ቀና ብለህ አትይ ወይም አንገትክን አቀርቅር፣ ስትናገር ድምጽህን ዝቅ አድርግ እየተባለ ያደገ ልጅ

በፈረንጂ ባሕል ሥነልቦናው የተሰለበ አድርገው ይቆጥሩታል። መታዘዝ እንጂ ማዘዝ ወይም መምራት አይችልም ይላሉ። ሐሳቡን ደፍሮ መናገርና ማሳመን አይሆንለትም ይላሉ። በጠባዩ ማማርና በእሺ ባይነቱ ግን ይወዱታል። ታዛዥ ሎሌ እንደሚወደደው ዓይነት ነው። እኔ የምለው ባጭሩ ልጆቻችን ደፋርና በራሳቸው የሚተማመኑ እንዲሆኑ እናበረታታቸው ነው። በዚህ ረገድ ትምህርት ቤቶችም ኃላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍና በንግግር ደኅና አድርገው እንዲገልጹ ማስተማር አለባቸው። ከሰው ፊት ቆመው እንዲናገሩ ማደፋፈር ያስፈልጋል።

ከውጭው ዓለም ጋር መደራደርና ያገራችንን ጥቅም ማስጠበቅ መቻል አለብን። ተወደደም ተጠላ የምንኖረው ከውጭው ዓለም ጋር ተሳስረን ባንድ ቤት ውስጥ ነው ለማለት ይቻላል። ሌላ ሺህ ዓመት ቤት ዘግተን ለብቻችን መኖር አንችልም። አሁንም አንሶ ላለመገኘት ልጆቻችንን ለሚጠብቃቸው ከፍተኛ የትግል ጉዞ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለብን።

የሶማልያ ባለሥልጣኖች እንደነገሩን ሲያድ ፕሬዚዳንት ከመሆኑ በፊት ጆሮውንም ቢቆርጡት እንግሊዝኛ አይሰማም ነበር። ቁርጠኛ ወይም ቆራጥ ሰው ነው ብለው ያስወሩለት ነበር። ለዚህ ማስረጃ ብለው ከሚያቀርቧቸው ነጥቦች መካከል እንግሊዝኛ ባጭር ጊዜ ተምሮ ለመናገር ያሳየው ትጋት ይገኝበታል።

ወደ ባሬ ገለጻ ስንመለስ፣ መልዕክተኞቹ ቋቅ እንዳለንና በጣም እንደተዳከምን በልዩ ልዩ መንገድ ብናሳይም፣ ለምሳሌ ማዛጋት፣ ሰዓት ማየት፣ መንቆራጠጥ፣ ባሬ ደንታ አልሰጠውም። እኛ መብላትና መተኛት የፈለግነውን ያህል የእሱ አጀንዳ ደግሞ እኛን መልዕክተኞቹን የራሱን መልዕክቶች አሸክሞ ወደየአገራችን መመለስ ስለነበር አጋጣሚውን ሳይጠቀም ማለፍ አልፈለገም።

ስብሰባው አልቆ ሆቴላችን ስንደርስ ምግብ ቤቱን ተዘግቶ አገኘነው፡፡ የሚላስ የሚቀመስ ጠፋና እንጀታችን ታጥፎ አደርን፡፡

እዚያ ካስጎበኙን ብሔራዊ ፕሮጀክቶቻቸው መካከል በረሃማነትን ለመቋቋም ያደርጉት ስለነበረው ጥረትና ማይምነትን ለማጥፋት የሚያደርጉት ዘመቻ ይገኙበታል፡፡ በተለይ በረሃማነትን ለመቋቋም በሚያደርጉት ጥረት የሕዝብ ተሳትፎ ሰፊ እንደነበር ተመልክተናል፡፡ የፕሮግራሙ ዋና ክፍል ከበረሀማ አካባቢዎች አሸዋ እየጠረገ ለም አፈር ላይ ይዘረግፍ የነበረውን ንፋስ ዛፎችና ቁጥቋጦ በመትከል መግታት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ርብርቦሹ በጣም ከፍተኛ ስለነበር ጥረታቸው መለስተኛም ቢሆን ውጤት እያስመዘገበ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡

አንድ ልብ ያልኩት ነገር አንዲት ትንሽ ዛፍ ለማብቀል ይጠይቃቸው የነበረው ገንዘብና ጉልበት በጣም ከፍተኛና እልህ አስጨራሽ እንደነበር ነው፡፡ እያንዳንዱን ተክል እንደልጃቸው ነበር የሚያዩት፡፡

በአንጻሩ የዋሁ ሕዝባችን ሕይወቱን ደግፎ የያዘውን ለም አፈርና ዕፅዋት በዋዛ ፈዛዛ ሲንድና ሲገነድስ ከማየት የበለጠ የሚያሳዝን ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ አገራችንም እንደሶማልያ በረሃማ የማትሆንበት ምንም ምድራዊ ምክንያት የለም፡፡

ማይምነትን የማጥፋት ዘመቻን በተመለከተ በተለይ የማስታውሰው፣ ትምህርት ይካሄድ የነበረው በአብዛኛው ዛፍ ጥላ ሥር እንደነበር ነው፡፡ ሌላ የተመለከትኩት ደግሞ ሶማልኛን በአውሮጳውያን ፊደሎች ለመጻፍ መምረጣቸው ብቻ ሳይሆን በዚህ ድርጊታቸው ያለመጠን ይኮሩና እንደትልቅ ግኝት ይቆጥሩት እንደነበር ነው፡፡ ለምን እንደትልቅ ነገር እንደቆጠሩት ግን አልገባኝም፡፡ የሶማልኛ ቋንቋ በማናቸውም ዓይነት ፊደል መጻፍ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ እንግሊዝኛ በአማርኛ ፊደላት መጻፍ ይቻላል፡፡ ሶማሌዎች ሮኬት የፈለሰፉ ዓይነት አድርገው ሲያወሩት ያልተገለጸልኝ ምስጢር መኖር አለበት ልል ምንም አልቀረኝም ነበር፡፡

አሁን ሳስበው ሕዝብን መደለያ ርካሽ የመንግሥት ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን አይቀርም፡፡

አንድ ምሽት የባንኩ አዛዥ ቤት ለክብራችን የእራት ግብዣ ተደረገልን፡፡ ከፍተኛ ባላሥልጣኖቻቸውም ተገኝተው ነበር፡፡ ከሲያድ ባሬ በቀር የቀረ አልነበረም፡፡ እኔን ያስቀመጡኝ ከአራት ወይም አምስት ሚኒስትሮች ጋር ነበር፡፡ አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያ ውስጥ የተማሩ ስለነበር አማርኛ ይናገራሉ፡፡ አንዱ ሚኒስትር ገና ከመተዋወቃችን "እናንተ አበሾች አሁንም ሽርጥ ለባሽ ሶማሌ እያላችሁ ትሰድቡናላችሁ አይደል?" አለኝ፡፡ ዓረፍተ ነገሩን የደመደመው እ እ እያለ በማቃሰት ነበር፡፡ በውስጡ የታመቀውን የቂም ነበልባል እያማጠ በአፉ ለመትፋት የሚታገል ይመስል ነበር፡፡ ቆይ ጠብቁ፣ ባናሳያችሁ እንዳለኝ ወሰድኩት፡፡ ስለኦጋዴንም ተነሳ፡፡ ይሉኝ የነበረውም በሰላም ለቃችሁ ብትወጡ ይሻላችኋል ነው፡፡ በበኩሌ ደግሞ አንዲት ስንዝር አንሰጥም አልኳቸው፡፡ አንድ ሁለት ፉት ካልን በኋላ አንደበታችን ተፍታትቶ ሁለታችንም ወገኖች የልባችንን እያወጣን ዘረገፍነው፡፡ ነገሩ ጨዋታ ይምሰል እንጂ ለዓመታት ሁለቱን አገሮች ሲያነታርክ የኖረው ጉዳይ መለስተኛም ቢሆን መድረክ ተገኝቶለት እየታሸ ነበር፡፡

እዚያ በነበርኩበት ጊዜ አንድ የተገነዘብኩት ሶማሌዎች ለአጭር ዘመቻ በጣም ስለሚተባበሩና ፈጣን ስለሆኑ ማንንም ሊያዋርዱ እንደሚችሉ ነበር፡፡ ለረጅም ጊዜ ትግል ግን ትዕግስትም ሆነ አቅም እንደሌላቸው ተገነዘብኩና ሶማልያ መቼም ቢሆን የኢትዮጵያን መሬት ይዛ ልትቆይ አትችልም አልኩኝ፡፡ ሲያድ ባሬ የሰላም ጦር እያለ ያናፋው ይህን ስለተገነዘበ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ከሳምንት ቆይታ በኋላ ሞቃዲሾ አውሮፕላን ጣቢያን ለቅቄ ስወጣ እጄን በማውለብለብ አገርህ በደኅና ያግባህ ወይም ወደ ሶማልያ መልሶ አያምጣህ ያለኝ የመጨረሻው ሸኚ ጠባቂዬ፣ ኮሎኔሉ ነበር፡፡ ጭንቅላቴን ቆርጦ ሶማልያ ምድር እስካላስቀረው ድረስ የሄድኩበትን እየተከታተለ በማየት ብቻ ያገሩን ደኅንነት ያስጠበቀ ከመሰለው ተሳስቷል፡፡ ለተዋጣለት የመከላከያ

እቅድ የጠላትን ወታደርና መሣሪያ ዓይነትና ብዛት ማወቅ ጠቃሚ የሆኑትን ያህል ስለሰዉ አስተሳሰብ፣ ሥነልቦና፣ ጽናት፣ ጠባይ ማወቅ ያላነሰ ጠቀሜታ እንዳለው ከሶማልያ ጉብኝቴ የተረዳሁት ጉዳይ ነው።

አዲስ አበባ እንደተመለስኩ ለባንኩ የለውጥ ሐዋርያ ለመቶ አለቃ ፈቃደ ያየሁትንና የሰማሁትን አጫወትኩት። ሶማልያ ኢትዮጵያን ለመውረር እየተዘጋጀች ስለመሆኑ መጠራጠር አይቻልም አልኩት። ሲያድ ባሬ የአፍሪቃ ነጻ አውጭ ጦር ይቋቋም እያለ የሚወተውተው ኦጋዴንን ከያዘ በኋላ አስታራቂ ኃይል መሀላችን ገብቶ እንዲሰፍር ለማመቻቸት ሳይሆን አይቀርም አልኩት። መሬታችን ተይዞ አስታራቂ ኃይል ጣልቃ ይግባ ማለት ሶማልያ ኢትዮጵያን ለማዋረድ ያላት ምኞት ተሳካ ማለት ነው አልኩት። እ እ እያለ ያማጠብኝ ሚኒስትር ሳያውቀው ከፍተኛ የአገር ምስጢር አውጥቶ እንደነገረኝ ነገርኩት። እውነቱን ለመናገር ካየሁትና ከሰማሁት ሁሉ የሚኒስትሩ አነጋገር ነበር ሶማሌዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር እንደደገሱለት ያስገነዘበኝ።

ስለሶማልያ ጉብኝቴ መቶ አለቃ ፈቃደ ለመከላከያ ሚኒስቴር ካድሬ ይነግራል። ካድሬው ተስፋዬ አንድ ቀን ቢሮዬ ድንገት ብቅ ይልና በቅርብ ሶማልያ ሄደህ ነበር አሉ፣ የመጣሁት አንዳንድ ጥያቄዎች ልጠይቅህ ነው ይለኛል። አቀራረቡና አነጋገሩ እንደፖሊስ መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ ዓይነት ስለነበር የመጀመሪያው ስሜቴ በፍጹም ላለመተባበር ነበር። ወድያው መለስ ብዬ ጉዳዩ የአገርን ደኅንነት የሚመለከት ስለሆነ መተባበር እንዳለብኝ ተገነዘብኩ። ለጠየቀኝ ጥያቄዎች መልስ ሰጠሁ። ካድሬውን በኋላ ቀረብ ብዬ ሳውቀው ዐይነአፋርነት የሚያጠቃው ስለሆነ ከሰው ጋር ተለሳልሶ ወይም አለሳልሶ መወያየት ስለማይቀናው አቀራረቡ ደረቅ በደረቅ ይሆንበታል፣ አነጋገሩ  እንጨት እንጨት ይላል።

ካድሬውን ቢሮዬ ባነጋገርኩት በስምንተኛው ወር ይመስለኛል የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት የሶማልያ ሰርጎ ገቦች ኦጋዴን ውስጥ ታዩ ሲል የሰማነው። ሰርጎ ገብ የሚለውን ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ መተዋወቃችን

ነበር፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ የዜና አገልግሎት ቃሉን ሳይጠቀም የሚያልፍበት ቀን በጣም ውስን ስለነበር ሰርጎ ገብ የሚለው አባባል በሕዝቡ ቋንቋ ውስጥ ሰርጎ ገብቶ በሆነ ባልሆነው ቦታ ሲደነቀር ከርሞ አባባሉ እየከሰመ የመጣው የሶማልያ ሰርጎ ገብነት አልቆ መደበኛው ጦራቸው ኦጋዴንን አንድ ወይም ሁለት ዓመት ሰንብቶ ከወረረ በኋላ ነበር፡፡ ሶማልያ ሳይታሰብ ወረረችን ተብሎ ለሕዝብ ሲነገር ስሰማ አስቂኝ ሆኖ አገኘሁት፡፡

# የቻይና ጉብኝት

በሐምሌ 1968 ዐሥራ ሶስት አባላት የሚገኙበት የንግድ ልዑካን ቡድን ቻይናን በጎበኘበት ወቅት ባንኩን ወክዬ ተገኝቻለሁ፡፡ በንግድ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ በዶክተር አሻግሬ ይግለጡ የተመራው ቡድን ተልእኮው በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረውን የንግድ ግንኙነት እንዲያጠናክር ነበር፡፡

ወደ ፔኪንግ፣ ባዲሱ አጠራር ቤዢንግ፣ ስናልፍ አንድ ሌሊት ቦምቤይ፣ በአሁኑ አጠራር ሙምባይ፤ ህንድ፣ አድረናል፡፡ ያረፍንበት ሆቴል አካባቢ ስንደርስ የተጓዝነው የመንገዱን ዳር ዳር ይዘው በተኙ ሰዎች መካከል ነበር፡፡ ያ ሁሉ የተረፈረፈው ሰው ቤት የለሽ መሆኑ ተገለጸልን፡፡ እያንዳንዱ ቤተሰብ መንገዱን ተከፋፍሎ፣ ድንበሩን በጠመኔ አስምሮ እንደሚኖር ተነገረን፡፡

ጠዋት ወደ አየር ማረፊያ ጣቢያ ስንሄድ ሰው መንገድ ዳር ተቀምጦ ያለምንም ኀፍረት ሲጸዳዳ ዐይተን በዚህ ረገድ ከኢትዮጵያም የባሰ አገር መኖሩን መሰከርን፡፡

ፔኪንግ ስንደርስ መጀመሪያ ልብ ያልኩት የአየር ማረፊያውን ትንሽነት ነበር፡፡ በወቅቱ ቻይና ከውጭው ዓለም ጋር የነበራት ግንኙነት በጣም ውስን ስለነበር የአየር ማረፊያው ትንሽነት አስገራሚ ባይሆንም ከአገሩ

ሰፊነትና ከሕዝቡ ብዛት ጋር ሲታይ ግን ያለመጠን ትንሽ ለመሆኑ አያጠያይቅም ነበር፡፡

ወደምናርፍበት ሆቴል የሚወስደን መንገድ በእግረኛና በቢስክሌተኛ የተጨናነቀ በመሆኑ በተለይ ፊት ለፊት ይመራ የነበረው መኪና ጥሩምባውን ሊያሳብደን እስኪደርስ ያለማቋረጥ መንፋት ነበረበት፡፡ እግረኛው መንገዱን የወረረበት ምክንያት አገሩ በዚያን ዘመን የነበረው ተሽከርካሪ በጣም ጥቂት፣ እግረኛው ደግሞ በጣም ብዙ ስለነበር ነው፡፡ የግል ተሽከርካሪ የሚባል ነገር አልነበረም፡፡

ከአዲስ አበባ ሳንነሳ ስለቻይና ከተነገሩን ነገሮች መካከል አንዱ አማርኛ የሚያውቁ ቻይኒዞችን በምንገኝበት ሁሉ የቻይና መንግሥት በጆሮ ጠቢነት ሊያስቀምጣቸው ስለሚችል ተጠንቀቁ የሚል ነበር፡፡ ለመጀመሪያው ጥቂት ቀናት ሥነሥርዓት አክባሪነታችንና ዝምታችን መጠን የዘለለ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ዋጋ ከፍለንበታል፡፡ ታሪኩም እንደሚከተለው ነው፡፡

የመጀመሪያው ምሽት እራት እየበላን ሳለ ቁርስ ምን እንዲሰራላችሁ እንደምትፈልጉ ተናገሩ ተባልን፡፡ ግማሹ ስክራምብልድ ወይም ፍርፍር እንቁላል ሲያዝ ግማሹ ደግሞ ፍራይድ ወይም ቁጭ ቁጭ አለ፡፡ ጠዋት ቁርስ ሲቀርብልን ስክራምብልድ ወይም ፍርፍር ላዘዘው ፍራይድ፣ ፍራይድ ላለው ስክራምብልድ ቀረበለት፡፡ እንደበታችሁ ለከት ይኑረው፣ ጠባይ አሳምሩ የተባልነውን ይዘን ሁሉም የቀረበለትን ድምጽ አጥፍቶ በላ፡፡ በሁለተኛውም ምሽት እራት እየበላን ለቁርስ የምትፈልጉትን ተናገሩ ተባልን፤ ትዕዛዛችንን ሰጠን፡፡ ጠዋት አሁንም ትእዛዛችን ተገለባብጦ ያላዘዝነው ቀረበልን፡፡ ይህን ጊዜ አበሻ አሁንስ ይብቃ፣ በዛ፣ ጎበዝ ይሄ ነገር እንዴት ነው? ተባባለ፡፡ አፋችንንም ፈታን፡፡ ትናንትም ጭጭ ብዬ በልቼ ነው እንጂ እኮ፤ ያዘዝኩት ሌላ ነበር ተባባልን፡፡ ስሕተቱ ለሶስተኛ ጊዜ እንዳይፈጸም ፈራንና የወጥ ቤቱን ኃላፊ አስጠርተን ስሕተት መፈጸሙን ነገርነው፡፡ በትእዛዛችሁ መሠረት ነው ያቀረብንላችሁ ብሎ ድርቅ አለ፡፡ ኋላ የተገነዘብነው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ለቻይና አዲስ ስለሆነ አንድ ያገሩ ጥራዝ

ነጠቅ ተወላጅ የማያውቀውን አውቃለሁ ብሎ ስክራምብልድን ፍራይድ፣ ፍራይድን ስክራምብልድ ብሎ ስሕተት እንዳስታቀፋቸው ገመትን፡፡ የጥብስ እንቁላል ስም አሰጣጣቸው ስሕተት መሆኑን ልባቸው ቢያውቀውም የለመዱትን መልቀቅ አልፈለጉም ወይም ልክ ነን ብለው እራሳቸውን ማታለል ፈልገዋል፡፡ ተጠንቀቅ፤ አፍህን አርም፤ ስለቻይና ክፉ አትናገር ተብሎና ፍርሀትን ተሞልቶ ለተላከ ለእንደኛ ዓይነቱ የውጭ መልዕክተኛ፤ ወይም የፔኪንግ ከባድ የፖለቲካ ደመና አላፈናፍን ላለው ቱሪስት በጥብስ እንቁላል መልክ የቀረበለት ቲያትር አፋችሁን ዝጉ በተባለበት ምድር አፍ መፍቻ እስከ ሆነለት ድረስ ስሕተቱ ሳይታረም እንዳለ ቢቆይ እንደሚሻል ቡድናችን ውሳኔ አሳለፈ፡፡

በጣም አስደናቂ ሆነው ካየናቸው ነገሮች መካከል ሊነጋጋ አካባቢ በየጎዳናው እየተመመ ይሄድ የነበረው የቢስክሌት ብዛት ነበር፡፡ ሆቴላችን ይገኝ የነበረው በከተማው ዋና ጎዳና ላይ ስለነበር በተለይ ሊነጋጋ አካባቢ ተጎዢ ከሆቴላችን መስኮት ሆኖ ሲታይ ያለማጋነን የሚርመሰመስ ትልቅ የጉንዳን ሰራዊት ይመስል ነበር፡፡ ቢሄድ ቢሄድ አያልቅም፡፡ እንደተነገረን በፔኪንግ ከተማ ብቻ ከሰባት እስከ ስምንት ሚሊዮን ቢሲክሌቶች ይገኙ እንደነበር ነው፡፡

ቻይናን የጎበኘነው ሊቀመንበር ማኦ ሲ ቱንግ በሕይወት እያሉና የካልቸራል ሪቮሉሽን ወይም ባሕላዊ አብዮት ማብቂያ ላይ ነበር፤ ይኸውም አዲሲቱ ቻይና ልትወለድ በተረገዘችበት ወቅት ማለት ነው፡፡ በየሄድንበት የሚነገረን ስለ ቀኝ መንገደኛው ወይም ስለካፒታሊስት ሮደሩ ፒንግ፣ በኋለኛው ቋንቋ ዴንግ፣ ነበር፡፡ ሰውዬውን የቁም ስቃይ አሳይተዋቸዋል፡፡ ያላደረጓቸው ነገር የለም፤ ባንድ ወቅት ሥራቸው ሽንት ቤት ማጽዳት ነበር፡፡ ታዲያ እንዲህ የተጣሉና ያለቀላቸው ሰው ከሆኑ ለምንድነው በቁሙ ስለሞተ ሰው የሚያላዝኑት? እያልኩ እገረም ነበር፡፡ ለካስ ሰውዬው ዋዛ እንዳልሆኑና ብዙ ተከታይ እንዳላቸው ባለሥልጣኖች ስለሚያውቁ ኖሯል፡፡

ከፔኪንግ ራቅ ወዳለ አካባቢ ወስደው አንድ የኅብረት እርሻ ወይም ኮምዩን አስጎበኙተውናል:: አባላቱ ለውሎ ጠዋት ሲመጡ ሕፃናት ልጆቻቸውን ይዘው እንደሆነ ነገሩን:: ከመካከላችን አንዱ ሕፃናቱ ኮምዩኑ ውስጥ ምን ሲያደርጉ ይውላሉ? ብሎ ጠየቀ:: መልሱ ግልጽ ሆኖ ሳለ፣ ይኸውም ሲጫወቱ ይውላሉ መሆኑ እየታወቀ፣ እንዴት እንዲህ ዓይነት ጥያቄ ጠየቀ? ብለን ትንሽ መሽማቀቃችን አልቀረም:: የተሰጠውን መልስ ስንሰማ ግን ጥያቄውን የሰው ልጅ ከጠየቃቸው ታላላቅ ጥያቄዎች ጎን አስቀመጥንለት:: የተጠያቂው መልስ በማያወላውል ቋንቋ፣ "ዘይ ለርን ሃው ቱ ክሪቲሳይዝ ፒንግ" ማለትም ፒንግን መኮነን ወይም ማውገዝ ይማራሉ ወይም ሲማሩ ይውላሉ የሚል ነበር:: የምንነጋገረው እድሜያቸው ለትምህርት ቤት ስላልደረሰ ሕፃናት፣ በጎና ክፉን ማመዛዘን ቀርቶ ልብሳቸውን መልበስና በቅጡ መመገብ ስለማይችሉ እንጭጮች ነው:: ጠቢባን የቻይና ፖለቲከኞች ወተት ማቅረብ ቢያቅታቸው ሕፃናትን ፖለቲካ መጋት፣ ባገራችን ቋንቋ ማንቃት፣ መደበኛ ሥራቸው አደረጉት:: አድራጎታቸው በጣም ዘገነነን:: ስለ ፖለቲካ "ትምህርት" እውነተኛ ምንነት ጥሩ ግንዛቤ አስጨበጠን::

ከሕዝብ ቁጥጥር ውጭ የሆነ የፖለቲካ ማሺነሪ በህዝብ ላይ ምን ያህል ደባ ሊሠራ እንደሚችል ባይናችን ዐየን፣ በጆሮአችን ሰማን:: ሶሻሊዝም ይህ ከሆነ የኢትዮጵያ ህዝብ ቢቀርበት ይሻላል ሳንባባል አልቀረንም:: በነገራችን ላይ በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ሶሻሊዝም እንጂ ሳይንቲፊክ ሶሻሊዝም የሚባለው ገና መድረኩን አልያዘም ነበርና ቻይና ውስጥ ያየነው አፍ በመፍታት ላይ ያሉ ህጻናትን ፖለቲካ መስበክ እኛ ዘንድ ቦታ አይኖረውም አልንና እራሳችንን አታለልን:: የተለየን ነን ለሚለው ውሸት ሌላ ምሳሌ:: ማኦ መድረኩን ለቅቀው ፒንግ ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ሕፃናትን ስለመኮነን ያስተምሩ የነበሩት ሰዎች ምን ውጧቸው ይሆን? አሁን ደግሞ ምን ይሉ ይሆን? እያልኩ አስባለሁ::

በሶማልያ ሶሻሊዝም ከተሻረ በኋላ የባንካቸውን አዛዥ ስብሰባ ላይ አገኘ ሁትና ሶሻሊዝም ነግሶ በነበረበት ወቅት የሥርዓቱ ጋሻ ጃግሬዎችና አቀንቃኞች የት ደረሱ? ብዬ ጠየቅሁት:: እየሳቀ "በጣም የሚገርም ነው፣ ቀኝ ኋላ ዙር ሲባል መጨረሻ ይሆናሉ ተብሎ ሲጠበቅ ሁሉንም ቀደመው ፊት ቆመው አገኘናቸው፣ የማይቻሉ ፍጡሮች ናቸው" አለኝ:: በቻይናም የሕፃናት አዕምሮ አጣቢዎች ስለካፒታሊዝም ጥሩነት አስተማሪዎች ሆነው ቢቀርቡ የሚያስገርም መሆን የለበትም፣ በፖለቲካ አለም የማይሆን ነገር የለምና:: ግራና ቀኝ የሚጦዘውና የሚንገላታው የሱ ሕይወት እንዳልሆነ አይነት አሽሟጣጩና አብዛኛው ሕዝብ ከዳር ቆሞ ሲያይ አፈጮሌው ቀድሞ ዋና ዋና አውታሮችን ወጥሮ ለመቆጣጠር ይራወጣል:: ለራሱ ክብር ያለው ሕዝብ በሕይወቱ ላይ ሊነግዱ ወይም በትቢያ ላይ ሊያንፈራፍሩት መሰሪዎች ሲነሱበት አሻፈረኝ ማለት አለበት:: እምቢ ካለ ወይም ለራሱ ካላወቀበት በራሱ ላይ እንጂ በማንም ሊያዝን አይችልም::

ስለክብር ከተነሳ ቡድናችን በቻይና አንድ ታሪክ ሰርቶ ተመልሷል:: ኢትዮጵያ ከአገር ውጭ የምትፈራረማቸው ውሎች የሚዘጋጁት በእንግሊዝኛና ባገሩ ቋንቋ ነው:: ሁለቱ ቋንቋዎች እርስበእርስ የሚቃረኑ ከሆነ ሁለቱም እኩል የበላይነት ይኖራቸዋል እየተባለ ይፈረማል:: ከቻይና ጋር የምንፈራረመው ውል በእንግሊዝኛና በቻይና ቋንቋ እንደሚሆን መግባባት ከተደረሰ በኋላ ለምን በብሔራዊ ቋንቋችን በአማርኛም ጭምር አይዘጋጅም? የሚል ጥያቄ አነሳሁ:: ትርጉሙን መሥራት ጊዜ ይጠይቃል እንጂ ሐሳቡ ጥሩ ነበር ተባለ:: የሚያስፈልገውን መስዋዕት ከፍለን በቋንቋችንም መዘጋጀት ይኖርበታል በሚለው ተስማማንና ትርጉሙን ሥንሰራ አድረን ጨረስነው::

የቻይና ባለሥልጣኖች እንደነገሩን ሸቀጣሸቀጥ ለውጭው ዓለም ሲሸጡ ድሃ አገሮችን ያነሰ ዋጋ ሐብታሞችን ደግሞ ከፍ አድርገው ያስከፍላሉ:: ይህ እውነት ከሆነ የሐብታም አገሮች ነጋዴዎች ከሚያደርጉት በተገላቢጦሹ ነው:: በካፒታሊዝም ሥርዓት ደካማው ዘወትር ሲላጥና ሲጋጥ ይኖራታል

እንጂ ለነፍሴ ብሎ የሚያዝንለት የለም። የሥርዓቱ ወንጌል እንደሚለው ላለው ይጨምራል፣ ከሌላው ይወሰድበታል። ዋናው ምስጢር ደግሞ ደክሞ አለመገኘት ነው።

የቻይና ሰዎች ስለታሪካዊ ስፍራዎቻቸውና ግንባታዎቻቸው ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ አመለካከት አላቸው። ቻይና ውስጥ የተሠራ ነገር ሁሉ ታሪክነቱን መቀበል ብቻ ሳይሆን ይኮሩበታል። ማናቸውም የግንባታ ሥራ የሰፊው ሕዝባችን ድካም ውጤት ነው ይላሉ። ሥራው ጭቆናንና ግፍን አንጸባራቂ ከሆነም በአንድ በኩል በሕዝባቸው ዕፁብ ድንቅ ሥራ ሠሪነቱ መኩራታቸውን እየገለጹ በሌላ በኩል ጭቆናንና ግፍን ለመኮነንና ሕዝባቸውን ለማስተማር ይጠቀሙበታል። በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ማለት ይሄ ነው። ማናቸውንም ታሪካዊ ግንባታ ማፍረስ ወይም ማቃጠል ታሪካቸውን እንደማቃጠል ይቆጥሩታል።

በተለይ የእኛ ባለሥልጣኖች ይህን በውል መረዳት ይገባቸዋል። በአገራችን አንድ መሪ ሥልጣን ላይ ሲወጣ ታሪክ የሚጀመረው እሱ ከነገሠበት ቀን ጀምሮ ነው ብሎ ማመንና ሌላውን ማሳመን ይፈልጋል። በተለይ ከሱ ቀደም ብሎ የነበረው የአገዛዝ ዘመን ጥላሸት ተቀብቶ ማቅ እንዲለብስ ይደረጋል። ቀደም ብሎ እንዳተትኩት የእኛ ሰው ትልቅነቱን መለካት የሚፈልገው ሌላውን ወይም የሌላውን የሥራ ውጤት አሳንሶ በማየት ነው። ይህ ኃይለሥላሴን፣ ደርግን፣ መለስን የተጸናወተ በሽታ ነው። ይብዛ ይነስ እንጂ እያንዳንዱ ዘመን በጎና ደካማ ጎኖች አሉት። ደካማውን ትተን በጎውን ይዘን ወደፊት መራመድ መቻል ይኖርብናል። ያለበለዚያ ሥራችን ዘለዓለም አፍርሶ መገንባት፣ ገንብቶ ማፍረስ፣ አፍሶ መልቀም፣ ለቅሞ ማፍሰስ ይሆንና ጠፍተን እንዳንቀር ያሰጋል። ልጆቻችንን እማይወጡት ውዥንብር ውስጥ ላለመክተት፣ ከታሪክ ተምረው ሰው እንዲሆኑና አገራችንንም አገር እንዲያደርጓት ከተፈለገ ታሪክን በፖለቲካ አኳያ ብቻ ሳይሆን በሐቅ መነጽርም እንዲያዩ መርዳት ይኖርብናል። በዚህ ረገድ

የታሪክ ምሁራን የበለጠ ሊተጉ ይገባል፡፡ የአንዳንዶቹ ጅምር የሚያመረቃ ስለሚመስል በያዙት ጎዳና እንዲገፉበት ሕዝቡ ሊያበረታታቸው ይገባል፡፡

ፔኪንግ ከተማ በእግር ስንዘዋወር ዝነኛውን "**የበረከተ መርገም**" ደራሲን ኃይሉ ገብረዮሐንስን ድንገት አገኘነው፡፡ ከማርስ ዱብ ያለ ነበር የመሰለን፡፡ ከኤምባሲው ሠራተኞች በቀር ሌላ ኢትዮጵያዊ ቻይና ውስጥ እናያለን ብለን በፍጹም አላሰብንም ነበር፡፡ ፔኪንግ ዩኒቨርስቲ እንደሚማርና ሁለት ኢትዮጵያውያን አብረውት እንዳሉ ነገረን፡፡ የመንግሥቱ ኃይለማርያም አለቃ ጄኔራል ኃይሌ ባይከዳኝ "መንግሥቱ ስለማይመለከተው ጉዳይ የሚያፍተለትል አደገኛ ሰው ስለሆነ ባይነቁራኛ ሊጠበቅ ይገባል" አሉ እንደታባለው ሲ አይ ኤም ኃይሉ ገብረዮሐንስን አስተሳሰቡ ጠማማና አፍራሽ ስለሆነ የመንግሥት እይታ ሊያርፍበት የሚገባው ሰው ነው እንዳለ ሰምተናል፡፡

በቻይና የ0ሥራ ሦስት ቀናት ቆይታችን በግብዣ ተምበሽብሸናል፡፡ ምን ያበሉን እንደነበር በዝርዝር አናውቅም፡፡ በጽሑፍ ያልሰፈረው ውለታችን፣ አትንገሩን፣ አንጠይቅም ነበር፡፡ ቢሆንም ኤምባሲያችንን ሳያማክሩ አልቀሩም ብዬ እገምታለሁ፡፡

ብሔራዊ መጠጣቸው ሞታይ ይባላል፡፡ የኛን ዳግም አረቂ ወይም የራሽያን ቮድካ ይመስላል፡፡ የሚጠጣው በትንሽ መለኪያ ነው፡፡ ፉት ሳይሆን ግልብጥ ነው የሚደረገው፡፡ ከምግብ በፊት ከምግብ ጋር ከምግብ በኋላ አንስቶ ግልብጥ ነው፡፡ አሳላፊዎች አንድ መደበኛ ሥራቸው መለኪያዎችን መላልሶ መሙላት ነው፡፡ ጋባዥ ጽዋውን ሲያነሳ ተጋባዥ አጸፋውን መመለስ አለበት፡፡ ዶክተር አሻግሬ አከታትሎ ሲገለብጥ እኛ ታማኝ ጭፍሮቹ እናጅበዋለን፡፡ ጋባዡ ካልጠጣችሁልኝ እሞትባችኋለሁ የሚል ስለሚመስል ሞታይን በሞቴ ብለን ክርስቶስ በማይታወቅበት አገር ክርስትና አነሳነው፡፡

አንድ ቀን እራት እየበላን የዶክተር አሻግሬ ባልደረባ በቋንቋቸው "ዶክተር አሻግሬ፣ ጥሩ ጠጭ ነህ" ይለዋል፡፡ ዶክተር አሻግሬ የሚለው ጠፍቶት ላብ

ሲያስምጠው ሌሎቻችን ሣቃችንን መቆጣጠር አቃተን፡፡ ሰውዬው ሊል የፈለገው ሞታያችን ወይም የቻይና ሞታይ ተስማምቶሃል ነበር፡፡ የሰውዬው አባባል ደረቅ በደረቅ ሲተረጎም ግን አለቃችንን ሰካራም ነህ ብለውብናል፡፡ የሣቅነው የትርጉም ስሕተት መኖሩን ስላወቅን ነበር እንጂ ዶክተር አሻግሬ መጠጥ ወዳድነቱ ታወቀበት ብለን አልነበረም፡፡ ሰውዬው ለምን እንደሣቅን ከተረዱ በኋላ ዶክተር አሻግሬን ለመረዳት አስበው አባባላቸውን ሊያቃኑ ሲሞክሩ ነገሩ ተወለካከፈና እንደገና አሣቁን፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ዶክተር አሻግሬ መጠጥ ሲቀርብለት ሲሽማቀቅ አየው ነበር፡፡ የቻይና ባለሥልጣናት ሞታይ በከንፈሮቻቸው መካከል ደግነው ዶክተር አሻግሬን በሞቴ ሲሉት ከመሞት መሰንበት ይሻላልና ግልብጥን ትተን ፉትን እንምረጥ የሚላቸው ይመስል ነበር፡፡

# የአፍሪቃ ልማት ባንክ ውዝግብ

የአፍሪቃ መንግሥታት ካቋቋሟቸው ድርጅቶች መካከል በውጤታማነቱ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ዋና መሥሪያ ቤቱ አቢጃን ከተማ የነበረው የአፍሪቃ ልማት ባንክን የሚወዳደር ያለ አይመስለኝም፡፡ በልማት ወደኋላ የቀሩ የአፍሪቃ አገሮች የኤኮኖሚና ሶሻል አገልግሎት አውታሮችን ለመዘርጋትና ልማት ለማስፋፋት እንዲችሉ ባንኩ ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር በአነስተኛ ወለድ ለኢትዮጵያ ጭምር ሰጥቷል፡፡ አፍሪቃን የገጠሟት የልማት ችግሮች በአፍሪቃ ልጆች እንዲዳሰሱና መፍትሔ እንዲገኝላቸው የማይናቅ ሙከራ ያደረገ ድርጅት ነው፡፡ አፍሪቃውያን ባንኩን ተንከባክበው መያዝ ያለባቸው ስለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡

ባንኩን ከላይ ሆኖ የሚመራና የሚቆጣጠር፣ እንዲሁም የፖሊሲ አቅጣጫ የሚተልም የአዛዦች ቦርድ አለ፡፡ የቦርዱ አባላት የመንግሥታት ተወካዮች ሲሆኑ እያንዳንዱ አገር አንድ ሙሉ አባልና ተለዋጭ አባል ይሰይማል፡፡ የኢትዮጵያ ዋና ተወካይ የገንዘብ ሚኒስትሩ ሲሆን ተለዋጩ ደግሞ

የብሔራዊ ባንክ አዛዥ ነበር። ቦርዱ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።

የባንኩ የዕለት ተዕለት ሥራ በቅርብ የሚመራ፣ የሚከታተልና የሚቆጣጠር የዲሬክተሮች ቦርድ አለ። የዚህን ቦርድ አባላት መርጦ የሚሾመው የአዛዦቹ ቦርድ ነው። የዲሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የባንኩ ፕሬዚዳንት ነው።

ባንኩ በተቋቋመ በዐሥራ አምስተኛው ዓመት፣ ማለትም የዛሬ ሃያ ሰባት ዓመት፣ ከፍተኛ ችግር ገጥሞት ነበር። ችግሩን ለመመርመርና መፍትሔ ለመፈለግ ልዩ ጉባኤ ተጠራ። በስብሰባው ላይ ኢትዮጵያን ወክዬ የተገኘሁት እኔ ነበርኩ።

በወቅቱ የባንኩ ፕሬዚዳንት የጋናው ተወላጅ ክዋሜ ፍርጆ ሲሆን በሥራው በጣም ጎበዝና ንቁ ሰው ነበር። የዲሬክተሮች ቦርድ አባላትን ብዙዎቹን ይንቃቸው ነበር። ከባንኩ ሥራ ይልቅ በግል ጥቅማቸው ላይ ያተኩራሉ፤ ሰነፎች ናቸው፤ ለስብሰባ በቂ ዝግጅት አያደርጉም፤ ለስብሰባዎች የሚታደሉትን ሰነዶች ሳያነቡ ይመጣሉ፤ የቦርዱን ውድ ጊዜ በጥቃቅን ጥያቄዎች ያቃጥላሉ ይላቸው ነበር። የሰሜን አፍሪቃ አገሮች ፍርጆ ለጥቁር አፍሪቃ እንጂ ለአረቦች ቦታ አይሰጥም እያሉ ጥርስ ነክሰውበት ነበር። የባንኩ ባለቤትነት አፍሪቃዊ ላልሆኑ መንግሥታት ጭምር ክፍት ከተደረገ በኋላ ደግሞ አንዳንድ የምዕራብ አገሮች ተወካዮች በበኩላቸው ፍርጆ ይዘልፈናል፣ አያከብረንም የሚል አመለካከት ነበራቸው።

ፍርጆ አፍሪቃን ለማስቀደም ፈጥኖ ሲራመድ ቀርፋፎች ናቸው ያላቸው ጠላቶቹ አድብተው በሾኬ ጠልፈው ጣሉት። አፈጻጸሙም በዲሬክተሮች ቦርድ አማካይነት ከሥራ መታገድ ነበር። ጭቅጭቅ ወይም ውዝግብ ያስነሳው የባንኩን ፕሬዚዳንት ከሥራ የማባረር ሥልጣን የአዛዦች ቦርድ ወይስ የዲሬክተሮች ቦርድ ነው? የሚለው ጥያቄ ነበር። አንዳንድ መንግሥታት ሥልጣኑ የዲሬክተሮች ቦርድ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ፣

ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ ሥልጣኑ የአዛዦች ቦርድ ስለሆነ የዲሬክተሮች ቦርድ የወሰደው እርምጃ ስሕተት ነው የሚል አቋም ወሰዱ። የፕሬዚዳንቱ ከሥራ መታገድ ያስከተለው ውዝግብና አለመረጋጋት የባንኩን ሥራ አሰናከለው። ስለሆነም፣ ልዩ ጉባኤ መጥራት አስፈለገ። የዲሬክተሮች ቦርድ ለባንኩ አባል መንግሥታት ያስተላለፈው መልዕክት ፎርጆን ከሥራ ያባረረው በሥልጣን ስለባለገና የባንኩን ንዋይ ለግል ጥቅም ስላዋለ ነው የሚል ነበር።

ስብሰባው የተደረገው በአቢጃኑ ሆቴል ኢቮር የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ነበር። አብዛኛዎቹ መልዕክተኞች ያረፍነው እዚሁ ኢቮር ነበር። ስብሰባውን የመራው የወቅቱ የአዛዦች ቦርድ ሊቀመንበር የኮትዲቮር የገንዘብ ሚኒስትር አብዱላሂ ኮኔ ሲሆን እኔ ምክትል ሊቀመንበር ነበርኩ።

ስብሰባው ተከፍቶ ስለመጣንበት ጉዳይ ንግግር እንደተጀመረ አንዱ ይነሳና ምልአተ ጉባኤ ወይም ኮረም ስላልተሟላ ስብሰባው ሊቀጥል አይችልም፣ ሕገወጥ ነው ብሎ ይናገራል። ለስብሰባው የተመዘገበው አባል ብዛት ይቆጠርና ምልአተ ጉባኤ አለ፣ ስብሰባው ሊቀጥል ይችላል ተባለ። ተቃውሞውን ያስነሳው መልዕክተኛ ግን ሳይስማማ ይቀራል። ከተሰብሳቢዎቹ መካካል የሱን አቋም  የሚደግፉ ብዙ ነበሩ። ጭቅጭቅ ያስነሳው ነጥብ የናይጀሪያው ገንዘብ ሚኒስትር ቢመዘገብም ወደ ስብሰባው አልገባም በማለቱ በስብሰባ ላይ እንዳለ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም? የሚለው ጥያቄ ነበር። ሚኒስትሩ ሆቴል ኢቮር ውስጥ በተከራየው ክፍል ውስጥ ተቀምጦ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ማን ምን እንደተናገረ ወሬ ወይም መረጃ ሲመላለስለት ይውላል። ስብሰባው አዳራሽ ውስጥ እንድትገኝ ተብሎ ተደጋግሞ ቢለመን አሻፈረኝ ይላል።

ፎርጆ የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ እንዲለቅ የፈለጉ ወገኖችና የባንኩ ሥራ ቢደናቀፍ ምንም ጉዳት አይደርስብንም ብለው የሚያምኑ አገሮች በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ያልተገኘ ተወካይ በስብሰባው ላይ እንዳልተገኘ ስለሚቆጠር ምልአተ ጉባኤ አልተገኘምና ስብሰባው መበተን አለበት በሚለው ሐሳባቸው

ጸኑ:: ሌሎቻችን ግን ምልአተ ጉባኤ ስላለ የናይጀሪያ ተወካይ በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ተገኘም አልተገኘ ስብሰባው መቀጠል አለበት የሚል አቋም ያዝን::

ስለአንድ አገር ድምፅ ዋጋ ወይም ክብደት አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ አለ:: የእያንዳንዱ አገር ድምፅ ክብደት የባንኩን አክስዮን ለመግዛት በከፈለው ገንዘብ መጠን ይለካል:: በምልአተ ጉባኤ ስሌትም ሆነ በውሳኔ ሐሳብ መጽደቅ ወይም አለመጽደቅ የናይጀሪያ ድምፅ ባልሳሳት ከሁሉም አገሮች የበለጠ ክብደት ነበረው:: የብዙ አፍሪቃ አገሮች ድምፅ ቢደመር የናይጀሪያን አያክልም:: ስለሆነም ናይጀሪያን ወደ ጎን መተው አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው:: ናይጀሪያ ባንኩን ለመመሥረት ካዋጣችው ገንዘብ በተጨማሪ ለትናንሽ አገሮች መርጃ ይሆናል ብላ የመደበችውን ገንዘብ የሚያስተዳድረው ባንኩ ስለነበር እርዳታው ቢቋረጥ ትናንሽ የአፍሪቃ አገሮች ይጎዳሉ የሚል ፍራቻ ነበር::

ብዙ አገሮች የወሰዱት አቋም ምልአተ ጉባኤ አለ? ወይስ የለም? በሚለው ጥያቄ ላይ ጊዜያችንን ከምናቃጥል የሚሻለው የናይጀሪያው ሚኒስትር ወደ ስብሰባው አዳራሽ የሚገባበትን መንገድ እናመቻች የሚል ነበር:: ምልአተ ጉባኤ አለ? ወይስ የለም? በሚለው ላይ ሁለት ቀን ሙሉ ንግግር ተደረገበት፤ ነገር ግን ስምምነት ላይ መድረስ ሳይቻል ቀረ:: ጉዳዩ በድምፅ ብልጫ እልባት ያግኝ የሚለውን ሐሳብ ሊቀመንበሩ ሳይደግፈው ቀረና ንትርኩ ቀጠለ:: እንደ ሊቀመንበሩ አስተሳሰብ በድምፅ ብልጫ ምልአተ ጉባኤ አለ ከተባለ ናይጀሪያ በውይይቱ ባትሳተፍም ምንም አይደለም እንደማለት ስለሚሆን በናይጀሪያ ላይ ከፍተኛ ቅሬታን ስለሚያሳድር፣ በሌላ በኩል ምልአተ ጉባኤ አልተገኘም ተብሎ ስብሰባው ቢበተን ለአፍሪቃ ልማት ባንክ ሕይወት ጠንቀኛ ሊሆን ስለሚችል ሊቀመንበሩ አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ተቀረቀረ::

የኮትዲቯር ፕሬዚዳንት ሁፌት ቧኜ ለአንዳንድ መሪዎች እየደወሉ መፍትሔ የሚገኝበትን መንገድ ማፈላለግ ሥራዬ ነው ብለው ተያያዙት::

ሊቀመንበሩ በየጊዜው እየተጠራ ምክክር እያደረገ ይመለሳል፡፡ አንድ ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ለማነጋገር ወጣ ይልና እኔ ጊዜያዊ ሊቀመንበርነቱን እረከባለሁ፡፡ ምልአተ ጉባኤ አለ? ወይስ የለም? በሚለው ላይ ድምጽ እንዲሰጥ አደርጋለሁ፡፡ ምልአተ ጉባኤ አለ የሚለው ወገን አሸነፈ፡፡ አሸናፊው ወገን በጣም አጨበጨበ፡፡ ከአሁን ጀምሮ ስለመጣንበት ጉዳይ መነጋገር እንችላለን ብዬ ስብሰባውን መምራት ጀመርኩ፡፡ ስብሰባው እንዳይቀጥል የፈለጉ ሰዎችና ናይጄሪያን ማስቀየም ያልፈለጉ ወገኖች ለሊቀመንበሩ አስቸኳይ መልዕክት ያስተላልፉለታል፡፡ እሱም ፈጥኖ ይመለስና እኔ በሌለሁበት የተወሰነው ውሳኔ ሕገወጥ ነው ብሎ ውድቅ አደረገውና ቀድሞ ወደነበርንበት መለሰን፡፡

የናይጄሪያው ሚኒስትር ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንዲመጣ ለመጨረሻ ጊዜ የሚለምን የልዑካን ቡድን ይላክበት ተባለና ስድስት ሰዎች ተመርጠን ወደ ክፍሉ ሄድን፡፡ ስድስታችንም አንድ በአንድ እየተነሳን፣ ናይጄሪያ የአፍሪቃ ዐይን ስለሆነች፣ ሁላችንም አንጋጥጠን የምናያት ታላቅ አገር ስለሆነች፣ ወደፊት አፍሪቃ ከቀድሞ ቅኝ ገዥዎችና ኢምፔሪያሊስቶች ጋር በምታደርገው የማይቀረው ግብግብ ናይጄሪያ ራስ፣ ደጃዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪና የኋላ ደጀን እንደምትሆን ሳይታለም የተፈታ ስለሆነ እኛ አፍሪቃውያን ናይጄሪያን ሳንይዝ ማናቸውም ጉዞ ሊያምርብን ስለማይችል የናይጄሪያ በስብሰባው ላይ አለመገኘት በጣም ስላሳሰበን በስብሰባው ላይ እንዲገኙልን ለመለመን መጥተናል፤ እንዲታወቅላችሁ መግለጽ የምትፈልጉት ነገር ቢኖር ወይም የምታቀርቡት የውሳኔ ሐሳብ ካለ ከስብሰባው አዳራሽ ሌላ የተሻለ ስፍራ ሊኖር አይችልም አልነው፡፡ በተጨማሪ፣ ባንኩን የገጠመውን ችግር ለመፍታት ከመላው አፍሪቃ የመጣው መልዕክተኛ የመጣንበትን ጉዳይ ሳይመረምር ወደ አገሩ ቢመለስና ባንኩ በባሰ ችግር ውስጥ ቢዘፈቅ ለናይጄሪያም ሆነ ለአፍሪቃ ጥሩ ስም እንደማያሰጣት መገመት ቀላል ነው ብለን ለማስገንዘብ ወይም ለማስፈራራት ሞከርን፡፡ መጨረሻ የተናገርኩት እኔ ነበርኩ፡፡

አንድም ቃል ሳይተነፍስ ስድስታችንም የተናገርነውን በጥሞና አዳመጠ:: ሰውዬው በጣም ረጅምና ግዙፍ ነው:: በወርቅ የተከፈፈ ምርጥ የአገሩን ልብስ ለብሷል፤ ልዩ ነጠላ ጫማ አድርጓል፣ እግሩን አንፈራጥጦ ንጉሥ መስሎ ተጀንኖ ተኮፍሷል:: ከጀርባው አንድ ሰው እጆቹን ወደኋላው አድርጎ በተጠንቀቅ ቆሟል:: የክብር ዘበኛው ነው ብዬ እወራረድ ነበር፣ ነገር ግን ከክፍሉ ከወጣን በኋላ የተረዳሁት በባንኩ ውስጥ የናይጄርያ ተወካይ መሆኑን ነበር:: ሌሎች ጠረንገሎዎች ግራና ቀኝ አደግድገው ቆመዋል:: ይህ የቤንዚን ብር የነፋው የሰው ቁልል እኛን አሻግሮ ሲያየን አቤቱታ አቅራቢ ምንደኞቹ እንጂ የየአገሮቻችን ተወካዮች ሆነን የታየነው አይመስለኝም:: እኔ ተናግሬ ስጭርስ "ይህ ማለት እኛን የሚደግፍ የለም ማለት ነዋ" "This means nobody is supporting us!" ይልና ዐይኑን እያገለባበጠ ያንቧርቃል:: በልቤ፣ ለካስ ባለጌን ሲለማመጡት አይወድም? በባርነት የተገዛ ሕዝብ አዬ መከራው፣ የዚህ ዓይነቱን ዝፍጥ ይጭንበታል ብዬ ማሰቤም አልቀረም::

ሚኒስትሩ ለምን ወደ ስብሰባው አዳራሽ ለመግባት ፈቃደኛ ሳይሆን እንደቀረ ለመረዳት የምዕራብ አፍሪቃን ፖለቲካ መረዳት ይጠይቃል:: ናይጄሪያ በአካባቢው ፈላጭ ቆራጭ ነኝ፤ በሐብቴ የማንንም ድምፅ ሆነ ታማኝነት መግዛት እችላለሁ የምትልበት ዘመን ነው:: አሁንም ቢሆን ከዚህ ብዙ የተለየ አይመስለኝም:: የአፍሪቃ ድምጽ በውጪው ዓለም እንዲደመጥ ከተፈለገ በየመድረኩ የአፍሪቃውያን ግንባርቀደም ተወካይ ናይጄሪያዊ መሆን አለበት እያሉ የናይጄሪያ ባለሥልጣኖች የሚፏልሉበት ዘመን ነው:: ከጥቁር አፍሪቃውያን መካካል በዚህ እንደማንስማማ በግልጽ የምንናገር ወይም የምንቃወም የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ብቻ ነበርን ለማለት ይቻላል:: ዚምባብዌ ነጻነቷን ካገኘች በኋላ ጠንካራ አጋር አገኘን:: በአንድ ስብሰባ ላይ የናይጄሪያ መልዕክተኞች መሪ በተለመደ የትእቢት ቋንቋቸው የጥቁር አፍሪቃ ውክልና ለኛ መሰጠት አለበት፤ ትናንሹ አገር ሁሉ እየተነሳ አፍሪቃን ልወክል ቢል ውጤት አልባ ሆነን እንቀራለን ብሎ ቢናገር በዚምባብዌ ነጻነት ትግል ወቅት የነጻ አውጪውን የጦር ግንባር የመራውና

ከነጻነት በኋላም የመከላከያ ሚኒስትር የነበረው፣ ከዚያም የአገሩ የገንዘብ ሚኒስትርነት የተሾመው ሚስተር ንካላ ይነሳና "እኛ ዚምባቤውያን የነጻነት ትግል ያካሄድነውና ደማችንን ያፈሰስነው ነጻነታችንን ከነጮች ነጥቀን ለጥቁር ልናስረክብ አደይለም" ብሎ አንጀታችንን አርሶታል። ከዚያ ጀምሮ የናይጄሪያ ዐይን ያወጣ ስገዱልኝ ባይነት ለከት አግኝቶ ነበር።

የናይጄሪያው ሚኒስትር "እኛን የሚደግፍ የለም ማለት ነዋ!" ሲል ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንድንገባ ከተፈለገ ፎርጁ ሥልጣኑን እንዲለቅ ናይጄሪያ ያላትን አቋም ቤቱ እንደሚደግፍ አስቀድሞ ቃል ይግባልን ያልነው ተቀባይነት ስላላገኘ ተከፍቻለሁ ማለቱ ነበር። በሌላ አነጋገር፣ ተሰብስባችሁ መንጫጫት ትችላላችሁ፣ ነገር ግን ፎርጁን ማውረዱ ላይ አስቀድማችሁ ተስማሙልን ማለቱ ነበር።

ታላላቅ ነን የሚሉ መንግሥታት ሌሎቹን በይፋ ብቻ ሳይሆን በአሳቻ ስፍራዎችም ምን እንደሚያደርጓቸው፣ እንዴት እንደሚያስፈራሩዋቸው፣ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ምንም ከማድረግ እንደማይመለሱ ትልቁ ወንድማችን፣ የናይጄሪያ ተወካይ፣ ፊት ለፊት እስቀምጦ ትምህርት ሰጠን። ታላላቅ የሚባሉት መንግሥታት በዓለም አቀፍ መድረኮች ስለዴሞክራሲ፣ ፍትሕ፣ ሕጋዊነት፣ ወዘተ ሲሰብኩና ሲወተውቱ ለይስሙላ መሆኑንና የአገራቸውን ጥቅም ለማራመድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ እንደሌለ ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ ማለት ዴሞክራሲ፣ ፍትሕና ሕጋዊነት አያስፈልጉም ማለት ሳይሆን ታላላቅ ነን የሚሉት መንግሥታት ፍላጎታቸውን የሚያስፈጽሙት በሐቅ ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊ አሠራር ተከትለው ሳይሆን ያላቸውን ኃይል ሁሉ ተጠቅመው በማስፈራራት መሆኑን ለመግለጽ ነው። ከዚህ መውሰድ የምንችለው ትምህርት አጓጉል ተጽዕኖዎችን ለመቋቋም መፍትሔው ጠንክሮ መገኘት ብቻ መሆኑን ነው። ደካማን ማንም አይወደውም፤ ማንም አያከብረውም። ከብዙ ትግል በኋላ ግብረገባዊነትና ሰብኣዊነት ከፍተኛ ስፍራ እንዲኖራቸው ተደርጎ ነበር። ፋሺዝምና ናዚዝምን ማሸነፍ የተቻለው ግፍንና ጭቆናን ለማስወገድ

መስዋዕትነት መክፈል ትክክል ነው ስለተባለ ነበር:: ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ግን ኃይለኞች ኃይላቸውን ተጠቅመው ፍላጎታቸውን ለማሟላት ወደኋላ እንደማይሉ ገሀድ እየወጣ ስለሄደ ዓለም ወደ አስጊ ጎዳና እያመራች ናት::

ስድስቱ ለማኞች ወደ ሚኒስትሩ ክፍል ከማምራታችን በፊት በአንድ ጉዳይ ላይ ተማምነን ነበር:: ይኸውም፣ ተግባራችን ሚኒስትሩ ወደአዳራሹ እንዲገባ ማግባባት እንጂ የየአገራችንን አቋም መግለጽ አይደለም ተባብለን ተስማምተን ነበር:: እላይ እንደተገለጸው ሁላችንም ያንጸባረቅነው ይህንኑ መንፈስ ነበር:: ከመካከላችን የአንጎላው ገንዘብ ሚኒስትር ሎፔዝ ግን የናይጄሪያው አቻው አለመደሰቱን ሲረዳ "እርሶ እንዳሰቡት አይደለም፣ የተወደዱት ሚኒስትር፣ የእርስዎን አቋም የሚደግፉ ብዙ አሉ፣ ለምሳሌ አንጎላ እርስዎን ትደግፋለች" ይልና ስለየአገሮቻችን አቋም ለሰውዬው መናገር አይገባም ብለን የተስማማነውን ገደል ከተተው:: ሎፔዝ የገንዘብ ሚኒስትር ከመባሉ በፊት ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረ ሰው ነው:: በልቤ አሁንም እንደገና ቁልቁል ያውርድህ ብዬ ተራግሜ፤ እናንተ እያላችሁ አፍሪቃ ወደታች እንጂ መቼም ወደላይ ልትወጣ አትችልም ብዬ አሰብኩ::

የናይጄሪያ መንግሥት ፎርጃ እንዲነሳ የፈለገበት ዋናው ምክንያት ጋና ውስጥ ተካሂዶ ከነበረው መፈንቅለ መንግሥት ጋር የተያያዘ ለመሆኑ ፍንጭ የሰጠን የናይጄሪያው ሚኒስትር ካነሳቸው ነጥቦች መካከል አንዱ አዲሱ የጋና መንግሥት ሰዎችን ያለአግባብ ገድሏል ማለቱ ነበር::

የጋናው የዐሥር አለቃ ሮውሊንግስ መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን ሲይዝ ብዙ ጄኔራሎችን ያስራል:: የናይጄሪያው ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ ለሮውሊንግስ ይደውልና እነእገሌ አብረን የተማርን ጓደኞቼ ስለሆኑ ሕይወታቸው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፣ አደራህን ብሎ ያሳስበዋል:: ሮውሊንግስ ሲመልስ፣ ምንም አይደርስባቸውም፤ ስጋት አይደርብህ ብሎ በምስጢር ቃል ይገባለታል:: መፈንቅለ መንግሥት ያካሄደው ቡድን በጄኔራሎቹ ላይ

ስለሚወሰደው እርምጃ በሮውሊንግስ ሰብሳቢነት ውይይት ያካሂዳል፤ አዝማሚያው ወደ ሞት ቅጣት ማዘንበሉን ሲያይ ሮውሊንግስ የጄኔራሎቹን ሕይወት ለማትረፍ ጥረት ያደርጋል፤ ነገር ግን ለአባሳንጆ በምስጢር የገባውን ቃል ለቤቱ መግለጽ በክህደት የሚያስጠይቅ ስለሆነ ሳያነሳው ያልፋል:: ሙያው መግደል፣ መጋደል የሆነው ወታደር አሻፈረኝ ይልና በድምጽ ብልጫ ጄኔራሎቹ በሞት እንዲቀጡ ይበይናል:: ብያኔው ወዲያው ተግባራዊ ይሆናል:: ኦባሳንጆ ይህን ሲሰማ ይሄ የጠገበ የዐሥር አለቃ ቃሉን ሰጥቶኝ ሸወደኝ አይደል እንዴ? ኅበዝ፣ እንዴት ቢንቀኝ ነው? ይልና ይናደዳል:: ኦባሳንጆ ለጋና ጄኔራሎች ያሰበ ይምሰል እንጂ እነሮውሊንግስ ለናይጄሪያም የበታች መኮንኖች ትምህርት እያስተማሩብን ነው ብሎ ሳይሰጋም አይቀርም:: ሮውሊንግስና የቡርኪናፋሶው ቶማስ ሳንካራ ጄኔራል የመገልበጥ ትምህርታቸውን የቀሰሙት ከኢትዮጵያው ደርግ ነው ተብሎ ይታመናል:: ኦባሳንጆ ጋናን የሚቀጣበትን ልዩ ልዩ ዘዴዎች ማፍተልተል ይጀምራል:: ፎርጆ የአፍሪቃ ልማት ባንክን ለቆ መሄድ አለበት የሚለው አንዱ ነበር::

በመጨረሻ የናይጄሪያው ሚኒስትር በስብሰባው ላይ ይገኝ አይገኝ አላስታውስም:: ለማናቸውም፣ የመፍትሔ ሐሳብ ተብሎ ሁሉም የተቀበለው ውሳኔ ፎርጆ ላልተወሰነ ጊዜ እረፍት ይውሰድ የሚል ነበር:: ከሞላ ጎደል እንግሊዝኛ ተናጋሪ አገሮች የፎርጆን መነሳት ሲቃወሙ ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎቹ ደግሞ መነሳቱን ፈልገዋል:: የመፍትሔ ሐሳብ የተባለውን እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች የተረዱት ፎርጆ እረፍት እንደወሰደ እንጂ ከሥራ እንዳልተባረረ ነበር:: የነበረን አስተሳሰብ የአዛዦች ቦርድ ከወሰነ፤ ከእረፍት ተመልሶ ቦታውን እንደገና መያዝ የማይችልበት ምንም ምክንያት የለም የሚል ነበር :: ፈረንሳይኛ ተናጋሪዎቹ ደግሞ ላልተወሰነ ጊዜ ሲባል በፈረንሳይኛ ቋንቋ ለዘለዓለም ማለት ስለሆነ ፎርጆን አባረርነው ብለው ፈነደቁ::

ያም ተባለ ይህ የአፍሪቃ ልማት ባንክ ከመንኮታኮት ተረፈ፡፡ ባንኩ ለአንድ ዓመት ያህል በጥብቅ ወይም ጊዜያዊ ፕሬዚዳንት ካዘገመ በኋላ የዛምቢያው ሙንጎምባ በፕሬዚዳንትነት ተመረጠ፡፡ ሙንጎምባ የፎርጆ ተቃራኒ ጸባይ የነበረው ሰው ነበር፡፡ በሱ የአስተዳደር ዘመን ባንኩ ረጭ አለ፡፡ ከአምስት ሰዓት በፊት ቢሮው አይገባም ነበር ይባላል፡፡ ሙንጎምባ ለምርጫ የቀረበ ጊዜ የናይጄሪያው ሚኒስትር «የኛ ሰው ነው» ብሎ በይፋ አስተዋውቆት ነበር፡፡ በእርግጥም ፕሬዚዳንቱ በናይጄሪያ ቁጥጥር ሥር ነበር ለማለት የሚያስደፍሩ በርከት ያሉ ሁኔታዎች ይታዩ ነበር፡፡ ከሙንጎምባ ቀጥሎ የተመረጠውን የሴኔጋሉን ተወላጅ እንዲያዩን ደግሞ አሜሪካኖች በተራቸው «የኛ ሰው ነው» ብለው ያቀረቡት ሰው ነበር፡፡

እንደ ፎርጆ ዓይነቱ ጠንካራ አፍሪቃዊ አፍሪቃ ውስጥ ሳይቀር ቦታ እንደሌለው ምስክሩ እራሱ የአፍሪቃ ልማት ባንክ ታሪክ ነው፡፡

# የኑሮ ውድነት አስወጋጅ ኮሚቴ

በ1972 በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ምርት አንሶ ዋጋ ከፍ ብሎ ነበርና የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ዝቅ ስላለ በየአቅጣጫው እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ተብሎ መንግሥት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን አቋቁሞ ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል የኑሮ ውድነት አስወጋጅ ኮሚቴ ይገኝበት ነበር፡፡ አባላቱ፣ ተስፋዬ ዲንቃ የኢንዱስትሪ ሚኒስትርና ሊቀመንበር፣ ተፈራ ወልደሰማዕት የገንዘብ ሚኒስትር፣ ካሳ ገብሬ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር፣ ካሳ ከበደ የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የኋላሸት ግርማ የቡናና ሻይ ልማት ሚኒስትር ነበሩ፡፡ ሌሎች አባላት ስለመኖራቸው በውል አላስታውስም፡፡

ባንክም ለዋጋ ንረትና ኑሮ ውድነት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ባንኮች ስለሚያስከፍሏቸው ክፍያዎች ኮሚቴው ዘንድ ቀርባችሁ ገለጻ እንድታደርጉና ለሚቀርብላችሁ ጥያቄዎች መልስ እንድትሰጡ ፕሮግራም

ተይዞላችኋል ተባልን፡፡ ለኮሚቴው ገለጻ ለማድረግ ሰባት ቀን የፈጀ ዝግጅት አደረግን፡፡

በቀነ ቀጠሮው የንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዓለሙ አበራንና የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ መቆጣጠሪያ መምሪያ ኃላፊ አቶ በቀለ መልሴን ይዤ ቀረብኩ፡፡ በተመደበልን ስፍራ ተሰየምንና ያዘጋጀናቸውን ሰነዶችና መግለጫዎች በትልቁ ጠረጴዛ ላይ አውጥተን በመልክ በመልኩ አስቀመጥንና የሚቀርብልንን ጥያቄ መጠባበቅ ጀመርን፡፡ ሊቀመንበሩ መድረኩን ለጥያቄ ክፍት ከማድረጉ በፊት ስለባንክ ክፍያዎች ገለጻ እንዳደርግ በጋበዘኝ መሠረት አጭር ገለጻ ያደረግሁ ይመስለኛል፡፡ ከዚያም መድረኩ ለጥያቄና መልስ ክፍት ሆነ፡፡ የመጀመሪያው ጥያቄ ተጠይቆ መልስ መመለስ ከመጀመሬ የኋላሸት ከመሬት ተነስቶ በዚያ በመረዋ ድምፁ፣ ለመሆኑ ባንኩን የሚቆጣጠረው ማነው? ብሎ ይጠይቃል፡፡ በፍጹም ያልጠበቅሁትና ለምን እንኳ እንደተጠየቀ ያልገባኝ ጥያቄ ነበር፡፡ የገንዘብ ሚኒስትሩ ተፈራ፣ በለሰለሰ አንደበት ድምፁን ሰበር አድርጎ፣ ለስሙማ የቦርድ ሊቀመንበር እኔ ነበርኩ፣ ነገር ግን በባንኮች ውስጥ ምን እንደሚካሄድ አላውቅም ይልና ድራማውን የበለጠ አጓጊ ያደርገዋል፡፡ አሃ፣ የኋላሸት ፊታውራሪ፣ ተፈራ ቀኝ አዝማች፣ ግራዝማች ደግሞ ማነህ? ተነስ አልኩ፣ በልቤ ወይም በሐሳቤ፡፡ ካሳ ገብሬ ተነሳና ወረደብኝ፡፡ የተናገረው ስሜቴን ያደፈረሰው መሆኑን እንጂ ይዘቱን አሁን አላስታውሰውም፡፡ ካሳ የተናገረው ደሜን አፈላውና በዚህ ብልሹ መንግሥት ውስጥ ውጤት አስመዘግባለሁ ማለት ከንቱ ነው ያልኩ ይመስለኛል፡፡ ካፌ ከወጣ በኋላ አልመልሰው ነገር የግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ ያልኩትን ባልናገረው፣ አባቴ ገጎ ስራጋ ይሉ እንደነበረው በሆዴ አምቄ ብይዘው ይሻለኝ እንደነበር ተገንዝቤአለሁ፡፡ በሌላ በኩል ያለ ጥፋቴ ከግራና ከቀኝ ተነስተው ሲተጋገዙብኝ ሳይ የመጣው ይምጣ የሚልም ስሜት ተጸናወተኝ፡፡ የካሳ ገብሬ ሸንቆራ እኔን እንጠጥ አሰኝቶ ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት የታቀደ መሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለኝም፡፡ ያባቴን ምክር አልሰማ ብዬ ልክ እንደተመኘው ባጠመደልኝ ወጥመድ ውስጥ ዘልዬ ገባሁለት፡፡ ካሳም ዘለለና

"ያለውን ሰምታችኋል፣ ይመዝገብልኝ፣ ልብ አድርጉልኝ፣ ምስክር ናችሁ" ይላል።

የኋላሸት ከሥነሥርዓት ውጭ፣ መድረኩን ቀምቶ ከተጠየቅሁት ጥያቄ ጋር ግንኙነት የሌለው ጥያቄ አንስቶ ሲጠይቅና ስብሰባው አቅጣጫውን ሲስት ዝም ብሎ የነበረው ተስፋዬ ዲንቃ የነገሩ አዝማምያ ከቁጥጥር ውጭ ሄዶ ያላሰበውን አቅጣጫ መያዙን ሲያይ በተቀጣጠለው እሳት ላይ ውሃ ቸላሽ ሆኖ ቀረበ። ተስፋዬ በመራው መድረክ ታደሰ ተባርኮ፣ በሆዳሚት አብዮት ታርዶ ተበላ እንዲባል የፈለገ አልመሰለኝም።

ነገሩን ካለፈ በኋላ ስገመግመው ታደሰ ከመንግሥት ችግሮች አንዱ ነው ብለው ለፍስሐ አሳልፈው ሊሰጡኝ አስበው ነበር ይመስለኛል። ምናልባት እቅዱን አስቀድመው ከፍስሐም ጋር ሳይነጋገሩበት አይቀሩም።

ተስፋዬ ማጣፊያ ፈለገና ያልኩትን እንዳላልኩ አስመስሎ ታደሰ ሊል የፈለገው እንዲህ ነበር እንጂ ያለውን ቃል በቃል መውሰድ ትክክል አይደለም ብሎ ሊያቃናልኝና ከችግር ጎትቶ ሊያወጣኝ ሞከረ። የስብሰባው መንፈስ ስለደፈረሰና ትርጉም ያለው ጥያቄና መልስ ማካሄድ እንደማይቻል ስለተረዳ ሊቀመንበሩ አሰናበተንና በሚቀጥለው ሳምንት እንደገና ተዘጋጅተን እንድንቀርብ ይሁን አለ።

ከስብሰባው አዳራሽ እንደወጣሁ ያመራሁት በቀጥታ ከዐሥር ሜትር በማይበልጥ ርቀት ወደነበረው ወደጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍስሐ ደስታ ቢሮ ነበር። ጸሓፊውን አሁን ላየው እፈልጋለሁ ብላት፣ አሁን በሥራ ተጠምደዋልና ሊቀበሉህ የሚችሉ አይመስለኝም አለችኝ። የለም፣ አሁኑኑ ማየት አለብኝ ብዬ ጥሼ ገባሁ። ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ምን አስቸኳይ ጉዳይ አጋጥሞህ መጣህ? ይለኛል። ስመልስ፣ ታደሰ ጥፋት አጥፍቷልና ይሰቀል፣ ይገደል የሚባል ከሆነ ደንበኛ የፍርድ መድረክ ተቁቁሞ ነው እንጂ በአሳቻ ቦታ በተቋቋመ የካንጋሩ ፍርድ ቤት አልዳኝም፣ እዚሁ አጠገብህ የተሰየመው ኮሚቴ እንደወንጀለኛ አድርጎ ሲያብጠለጥለኝ፣ ሥራ

በሠራሁ የመንግሥት ሚኒስትሮች እንደ አገር ጠላት እየተቀባበሉ ሲወርዱብኝ ዓላማቸው እኔን ለማጥፋት ስለሆነ ጥፋቴ በገሀድ ሳይመረመር በጅቦች መንጋጋ ውስጥ አልጣልም እለዋለሁ። ነገሩ ምን እንደሆነ ያላወቀ መስሎ ታየ። ማምረሬንና አንገቴን በቀላሉ ላራጆቼ እንደማላቀርብና ከርብተው ቢጥሉኝ ለመወራጨት ዝግጁ መሆኔን ሲያይ ይመስለኛል ሊያረጋጋኝ ሞከረ። ጉዳዩ ምን እንደሆነ በቅርብ እከታተላለሁ፤ አንተ ወደ ቢሮህ ተመለስና ሥራህን ተረጋግተህ ሥራ ብሎ አሰናበተኝ።

ከግቢው ወጥተን ወደ ባንክ ስናመራ ዓለሙና በቀለ ስለሥራህ ምስክሮች እኛ ነን። ይህ ሁሉ ውርጅብኝ የሚደርስብህ ለምንድን ነው? አሉና በጣም አዘኑ። ችግር እንዳለብህ እንሰማ ነበር፤ እንደዚህ የከፋ መሆኑን ግን አናውቅም ነበር፤ ዛሬ በዐይናችን ለማየት ስለቻልን ሕያው ምስክሮች ለመሆን በቅተናል አሉኝ።

ዝግጅታችንን አጠናክረን በቀነ ቀጠሯችን ሄድን። ምን እንደሚጠብቀኝ እርግጠኛ አልነበርኩም። አስቸጋሪ ሁኔታን ተጋፍጦ ማለፍ ለኔ አዲስ ነገር ባለመሆኑ ፍርሐት ልቤ ውስጥ አልነበረም። ለሰሚው ግራ የሚያጋባ ቢመስልም መፍትሔ የሚሻ ችግር ካጠገቤ ሲጠፋ መንፈሴ ቅር ይለዋል፤ ሥራ የሠራሁ አይመስለኝም። ችግርን ስፈታ፣ ተጋፍጬው ሳልፍ የመኖርን ግዴታ እንዳሟላሁ ስለምቆጥር የሚሰማኝ ደስታ ወሰን የለውም። ሁሉ ነገር ተስተካክሎ ሲመጣና ጥረት የሚጠይቅ ሁኔታ ሲጠፋ ቅር ቅር ይለኛል፣ ባዶነት ይሰማኛል። ለኔ የደስታ ትርጉም መሰናክሎችን ታግሎ ማለፍ፣ ውጤት ማስመዝገብ ወይም ለውጥ ማምጣት ነው። ተማሪ ሆኜ ፈተና አዳራሽ ገብቼ ጥያቄ ለማየት እጓጓ ነበር። ያላግባቡ ስገፋ የበለጠ እተባለሁ። መግለጽ የማልችለው ኃይል እውስጤ ይሰባሰባል፤ አእምሮዬም የሰላ ይሆናል። ስለሆነም፣ ሚኒስትሮቹ ያላግባብ ሲወርፉኝ ፊርቼ ወደኋላ ማፈግፈግ ሳይሆን በተቃራኒው በልበ ሙሉነት እንደገና እስክገጥማቸው ቸኮልኩ።

አጠገቤ የተቀመጠው ካሳ ከበደ ነበር:: ስብሰባው እንደተጀመረ ወደ ጆሮዬ ጠጋ አለና አይዞህ መናገር ያለብህን ሳትፈራ በልበሙሉነት ተናገር፣ ከመሬት ተነስተው እንዳያብጠለጥሉህ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል አለኝ:: ብቻዬን አንዳልሆንኩ አወቅሁና ልቤን ሞቀው፤ የደስታ እንባም ተናነቀኝ:: በልቤ እናንተ ጅቦች፣ አንበሳ መጣባችሁ አልኩ:: ካሳ በመጀመርያው ስብሰባ ምንም ሳይናገር ሁሉንም በጥሞና ያዳምጥ ነበር::

ካሳና መንግሥቱ የቅርብ ወዳጆች ናቸው:: እንዲያውም ዝምድና አላቸው ብለን እናምን ነበር:: ለዚህ እምነት መሠረቱ የዐይናቸው የላይኛው ሽፋን ተመሳሳይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ካሳ ከኛ ጋር ሲጫዋወት መንግሥቱን ጋሼ እያለ ስለሚጠራው ነበር:: ሰዎች መንግሥቱና ካሳ ዘመድማማቾች ናቸው ሲሉ ካሳ ማስተባበሉን አላውቅም:: ቢያደርገው ኖሮ መስማታችን አይቀርም ነበር:: አሉባልታው ካሳን ስለጠቀመው ወይም ስለተጠቀመበት መናፈሱን የጠላው አይመስለኝም:: ሁለቱም ዘመዳሞች አይደለንም ብለው ሲገልጹ የሰማነው የደርግ መንግሥት ከፈረሰ በኋላ ነው::

ካንዳንድ ሁኔታዎች እንደገመገምኩት ታደሰ ሥራውን በሚገባ ይሠራል ብሎ ካሳ ያምን ስለነበር ሚኒስትሮቹ መቅኖ አሳጥተው ከቦታዬ ሊያፈናቅሉኝ ሲሞክሩ ሲያይ በቀውጢ ወቅት ሊደርስልኝ አስቦ በስብሰባ ላይ የተከሰተውን ለወዳጁና ለሁላችንም አለቃ ለመንግሥቱ የተናገረ ይመስለኛል::

ስብሰባው ሲቀጥል ባለፈው ሳምንት የነበረው ዓይነት ድራማ አልነበረም:: ያ የሾለ ምላስ ሁሉ በሰገባው ገብቶ ተኝቶ አገኘሁት:: ተቻችሎ ከመኖር ብዙም ምርጫ የለም አልኩና ነገሩን ባለበት ተውኩት::

የመንግሥት ሥራ ለቅቄ ካናዳ በስደት ስኖር አንድ ጊዜ አሜሪካ ሄጄ ሳለ አንድ ውስጠ አዋቂ ወዳጄ እንዳጫወተኝ ከሆነ ተስፋዬ ዲንቃ የገንዘብ ሚኒስትርና ብሎም የቦርድ ሊቀመንበር ከሆነ በኋላ የቦርዱ አባላትን አስተባብሮ ከባንኩ አዛዥነት እንድነሳ ለመንግሥቱ ሐሳብ ለማቅረብ

ሁሉንም ቃል ካስገባ በኋላ የማዕድን ሚኒስትሩ ተከዘሸዋ አይተንፍሱ አልተባበርም ስላላቸው አድማቸው እንደ ከሸፈ ነው፡፡

እንዲሁም፣ ፍስሐ ደስታ የባለሥልጣኖች ዝውውር ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ለመንግሥቱ አንድ የሹም ሽር ሊስት ያቀርብለታል፡፡ የአየር ኃይል አዛዡ ፋንታ በላይ ከቦታው ካልተነሳ መንግሥቱን ያሰጋዋልና ሌላ ቦታ ይፈለግለት የሚባልበት ወቅት ነበር፡፡ መንግሥቱ ሊስቱ ላይ ያሉትን ያይና የታደሰን ጉዳይ ግድየለም ለኔ ተውልኝ እንዳለው ሰምቻለሁ፡፡ እንደተረዳሁት ፍስሐ ሊስቱን ያቀረበበት ዋና ምክንያት እኔን ለማስነሳት እንደነበር ነው፡፡

ለምንድነው ሚኒስትሮቹ እንደዚህ የተረባረቡብኝ? ለሚለው መልሱን ለማግኘት ስለባንክ ሥራ ጸባይ ማወቅ ወይም መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሁሉም ብድርና የውጭ ምንዛሪ ፈላጊ ነው፡፡ ሁሉም ቁጥጥር ሲደረግበት ወይም ጥያቄ ሲቀርብለት አይወድም፡፡ አንዳንድ ባለሥልጣኖች ለወዳጆቻቸውና ቤተሰቦቻቸው አማላጅ ሆነው ይቀርባሉ፡፡ የባንክ ገንዘብና ውጭ ምንዛሪ ሽምቀቆ የምቆጣጠር፣ ከሞላ ጎደል፣ እኔ ነኝ፡፡ ሁሉም እንድተባበረው ይጠይቀኛል፡፡ አይሆንም የተባለው ጥርስ ነክሶ ይሄዳል፤ እንዴት ደፍሮ እምቢ አለኝ? ይላል፡፡

ከስብሰባው አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ እራሱ ተስፋዬ ቢሮዬ ድረስ በመምጣት የሱ ሚኒስቴር ለሚያስተዳድረው ለምጽዋ ሲሚንቶ ፋብሪካ ተጨማሪ ብድር እንድንሰጥ ጠየቀኝ፡፡ ብድሩ ካልተሰጠ ሠራተኛው ይበተንና የወንበዴውን ጎራ ያጠናክራል አለኝ፡፡ ድርጅቱ አክሳሪ ስለሆነ መጠየቅ ያለብህ የባንክ ብድር ሳይሆን የምትፈልገውን ገንዘብ መንግሥት በበጀት ይዞ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል እንዲሰጥህ ነው አልኩት፡፡ ቢያገላብጠኝ፣ ወዲህ ቢለኝ፣ ወዲህ ቢለኝ የማይሆን ነገር ነው አልኩት፡፡ እሱም እንደ ሌላው ጥርሱን ነክሶብኝ ሄደ፡፡ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር ደግሞ በንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ በነበረው በአሰፋ ጸጋዬ ምክንያት ሆድና ጀርባ ሆነናል፡፡ ካሳ ገብሬ ለኮንስትራክሽን ድርጅቶች ብድር ሲጠይቅ ብድር

ጠያቂ ድርጅቶችህ የብድር መስኪያ አላሟሉም ስንለው የሚፈለገውን ለማሟላት ጥረት እንደማድረግ፣ ታደሰ ለግል ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ብድር በገፍ እየሰጠ ለኔ ድርጅቶች ግን ከለከለ እያለ ስሜን ማጥፋቱን መረጠ። ታደሰ ሚስቱን የግል ኮንስትራክሽን ድርጅት ያላግባብ በከፍተኛ ደመወዝ አስቀጥሮ ለቀጣሪው ድርጅት የጠየቀውን ብድር ሲሰጥ ለኔ ድርጅቶች ግን ከለከለ ብሎ በሊቀመንበር መንግሥቱ ላይ ከሁለቴም ሦስቴ እንደከሰሰኝ ሰው ነግሮኛል። ስለባለቤቱ ቅጥር በምስጢር በመርማሪ ቡድን ተጣርቶ አሉባልታው ፍሬ ከርስኪ ሆኖ እንደተገኘም ሰምቻለሁ። ከፍስሐ ደስታ ጋር ደግሞ በተለይ በአንድ የትግራይ ተወላጅ ጥቅም ምክንያት ውስጥ ውስጡን ተቋስለን ጥርስ ነክሶብኝ አይጥና ድመት ሆነን እንጠባበቃለን። ፍስሐን የሚመለከተው ጉዳይ ከመንግሥቱና በጣም ጥቂት ባለሥልጣኖች በቀር ሌላ ማንም አያውቀውም።

አስቸገረን ወይም በጉሮሮአችን ላይ ቆመ የሚሉ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች የኑሮ አስወጋጅ ኮሚቴ ሲቋቋም አንድ ላይ የመሰባሰብ እድል አገኙና የማርያም ጠላት አድርገው ሊወግሩኝ ተነሱ። ነገሩ ከዚህ የተለየ ሌላ ምንም ምስጢር የለውም።

# የሊብያ ጉዞ

በአንድ ወቅት ኢትዮጵያ፣ ሊብያና ደቡብ የመን በኩባው ፊደል ካስትሮ አስተባባሪነት የአንድነት ግንባር ፈጥረው ነበር። የሊብያው ቀጣፊ (በሊብያኖቹ አጻጻፍ መሪያቸው Qattafi ነው፤ የስድቡ ቃል አይደለም) ወይም ጋዳፊ በአፍሪቃና መካከለኛው ምስራቅ ያለውን ተደማጭነት ከፍ ለማድረግ ከነዳጅ የሚያገኘውን ገቢ ግራና ቀኝ ሲረጭ አገራችንም ከበረከቱ ተቋድሳለች።

ሊቀመንበር መንግሥቱ በሶሻሊስት አገሮች በ1970 ያደረገው ጉብኝት የተደመደመው በሊብያና በመጨረሻም በደቡብ የመን ቆይታ ነበር።

የምስራቅ አውሮጳ ጉብኝት አልቆ ትሪፖሊ አየር ማረፊያ እንደደረስን ጣቢያው በሰው ተወሮ አየንና ምን ጉድ ነው? አልን:: በየሄድንበት ያጋጥመን የነበረው ወታደር ተሰልፎ፣ ቀይ ምንጣፍ ተነጥፎ ስለነበር የትሪፖሊ አውሮፕላን ጣቢያ የመርካቶ ገበያ መስሎ ስናይ ተገረምን:: ከመካከላችን አንዱ፣ ያ፣ በዚያ በኩል የቆመው፣ እንዲህ ዓይነት ልብስ ከለበሰው ሰውዬ አጠገብ የቆመው ቀጣፊ ወይም ጋዳፊ እኮ ነው ይለናል:: የትኛው እንደሆነ ለመለየት ደቂቃዎች ፈጅቶብናል:: የአገሩ መሪ እንዴት ተራ ሰው መስሎ ከሌሎቹ ጋር ተደባልቆ ቆመ? ብለን ተገረምን:: ይህ ሁሉ ሲሆን አውሮፕላኑ ወደተመደበለት ስፍራ እያመራ ነው:: በመጨረሻም ደርሶ ቆመና በሩ ሲከፈት ከሰዎቹ መካከል አንደኛው ተነጥሎ ቀረበ:: ያኔ ቀጣፊን በደንብ ለይተን ማየት ቻልን:: ባለሥልጣኖቹ በሰልፍ ቢጤ ቆሙና ከመንግሥቱና ከልዑካኑ ቡድን አባላት ጋር ትውውቅ ከተደረገ በኋላ ወደአየር ማረፊያው እንግዳ መቀበያ አመራን:: ቀጣፊና መንግሥቱ አንድ ሁለት ቃል ከተለዋወጡ በኋላ ቀጣፊ እንዳከረፈ ሰው አንገቱን ትንሽ ዞር በማድረግ ወደ ላይ ቀስሮ ግድግዳ እያየ አንጋጦ ቀረ:: ልሳኑ ተዘጋ:: ዝም ዝም:: ግራ ተጋባን:: መንግሥቱም ቢሆን በሰውዬው አእምሮ ውስጥ ምን እየተጉላላ ነው ብሎ ሳይገረም የቀረ አይመስለኝም:: ከቀጣፊ ፕሮቶኮል ሰዎች አንዱ ወደ መንግሥቱ አጃቢዎች ቀረበና መንግሥቱንና ቀጣፊን ለብቻቸው ትታችሁ ውጡ ብሎ አዘዘን:: ወደ ሌላ ማረፊያ ተወሰድን::

ማረፊያው ውስጥ አንድ በጣም ትልቅ ካርታ በግድግዳው ላይ ተስሏል ወይም ተሰቅሏል:: ካርታው የአረቡ ዓለም የሚባለውን የሚያሳይ ነው:: ኤርትራም ከእናት አገርዋ ከኢትዮጵያ ተቆርጣ ከአረቡ ዓለም ጋር ተለጥፋለች:: ያየነውን ማመን አቃተን:: በአሉባልታ መልክ ስንሰማው የነበረውን ነገር ባይናችን ዐየን:: የምድር ጦር፣ የአየር ኃይል፣ የባሕር ኃይል አዘዦቻችን ሁሉም አሉ:: የመከላከያ ሚኒስትሩም የነበሩ ይመስለኛ ል:: አበሻ ከመቀመጫው ተነሳና ቡራከረዩ አለ:: ሊብያኖች እዚያ አዳራሽ ያስገቡን ሆን ብለው ካርታውን እንድናይ አስበው ሳይሆን አይቀርም ተባባልን:: የምንላችሁን እሺ ካላላችሁ የሚጠብቃችሁን እወቁት ለማለት

ፈልገው ሳይሆን አይቀርም ተባባልን፡፡ አረቦች ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ አላቸው የሚባለው ለካስ እውነት ነው ተባባልን፡፡ ሆኖም፣ በተለመደው የአበሻ ይሉኝታ የእነሱ እንግዶች ስለሆንን ጠባያችንን አሳምረን፣ ያየነውን እንዳላየን ሆነን እንለፈው ተባለና ከጠላታችን ጋር በልተን ጠጥተን ተለያየን፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ ሊብያን የረገጥኩት ከሁለት ወይም ሦስት ዓመት በኋላ ነበር፡፡ ሊብያ ለኢትዮጵያ የ150 ሚሊዮን ዶላር ብድር ለመስጠት ተስማምታ የሁለቱ አገሮች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ውል ተፈራርመዋል፡፡ ገንዘቡ የሚለቀቀው የሁለቱ አገሮች ማእከላዊ ባንኮች ስለገንዘቡ አከፋፈል ውል ሲፈራረሙ ነው ተብሏል፡፡ በኛ በኩል የባንኮች ውል በተቻለ ፍጥነት እንዲፈረምና ገንዘቡ በሒሳባችን ገቢ እንዲደረግ ፈልገናል፡፡ የውጪ ምንዛሪ እጥረት ስለነበረብን ብቻ ሳይሆን ቀጣፊ ሐሳቡን ሊለውጥ ይችላል ብለን ስለፈራን ነበር፡፡ የሊብያ ባንክ ተስፋ ደግሞ ቀጣፊ ሐሳቡን ለውጦ ወይም በሁለቱ አገሮች መካከል ያለው ወዳጅነት ደፍርሶ ገንዘቡ የማይለቀቅበት ሁኔታ እንዲፈጠር ነበር፡፡ ስለሆነም፣ ዋናው ስምምነት በደነገገው መሠረት ተገናኝተን ውል እንደራደር ብንላቸው ለጥያቄዎቻችን መልስ መስጠት ሳይፈቅዱ ይቀራሉ፡፡ ደግነቱ አዲስ አበባ የሚገኘው የሊብያ ኤምባሲ ውሉ በተግባር እንዲተረጎም ይፈልግ ስለነበር ጉዳዩን ከሊብያ ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግሮ ቀጠሮ አስያዘልን፡፡ ለድርድሩ እኔ እንደምመጣ ገልጬ ለባንኩ መልዕክት አስተላለፍኩ፡፡ አሁንም መልስ ሳይመጣ ይቀራል፡፡ ቀጠሮ ተሰርዟል የሚል መልዕክት ከእነሱ ዘንድ እስካልመጣ ድረስ ተነስቶ መሄድና በራቸውን አንኳኩቶ እንደራደር ብሎ ወጥሮ መያዝ ይሻላል አልኩና ተነስቼ ሄድኩ፡፡ ረዳት ከውጭ ባንኮች ግንኙነት መምሪያ ክፍሌ ጌታቸውን አስከትያለሁ፡፡

ወደ ትሪፖሊ ለመሄድ አውሮፕላን የሚገኘው ከሮም ስለሆነ ወደዚያ አመራን፡፡ በመሄጃችን ቀን በሊብያ አየር መንገድ ወደ ትሪፖሊ የሚሄደው ተሳፋሪ መሳፈርያው አጠገብ ተኮልኩሎ ተሳፈሩ የሚል ጥሪ ይጠባበቃል፡፡

የአየር መንገዱ ወኪል ወደ ተሳፋሪዎቹ ይቀርብና የሊብያ ተወላጆች የሆናችሁ ቅረቡ ይላል፡፡ ከዚያም አውሮፕላኑ ውስጥ ግቡ ይላቸዋል፡፡ ገብተው ሲያልቁ ወደሌሎቻችን ይመጣና ፍጹም ሥነሥርዓት በጎደለው ቋንቋ ሂዱ ግቡ ብሎ ያመናጭቀናል፡፡ አውሮፕላኑ ውስጥ ስንገባ ምርጥ ምርጥ የተባሉ ቦታዎች በሊብያኖቹ ተይዘዋል፡፡ የውጭ አገሩ ሰው አስተናጋጅ ሳይረዳው ቦታ እየፈለገ ተቀመጠ፡፡ የሊብያ አየር መንገድ ዓለም አቀፍ የበረራ ድርጅት ሳይሆን የክፍለ ሀገር አውቶቡስ መሰለኝ፡፡

ትሪፖሊ ማረፊያ ስንደርስ የኢሚግሬሽን ፎርም እንድንሞላ ተሰጠን፡፡ ፎርሙ ሙሉ በሙሉ በአረብኛ ነው፡፡ ደግነቱ በሊብያ አምባሳደራችን መሐመድ አብዱራህማንና ከአገሩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሊቀበሉን መጥተው ስለነበር እያንዳንዱ መስመር ምን እንደሚል እየተተረጎመልን መልሱን ሞላን፡፡ ከጥያቄዎቹ አንዱ ሃይማኖትህ ምንድነው? የሚል ነበረበት፡፡ የደጉ አባቴ የስራ አምላክ ይቅር ይበለኝና ግጥም አድርጌ "ሳይንስ" ብዬ ሞላሁ፡፡ እንደዚህ ብዬ መሙላቴን ለእስልምና ሃይማኖት ተከታዩ ለአምባሳደር መሐመድም አልነገርኩትም፡፡ አገር መጎብኘትና ሃይማኖት ምን አገናኛቸው? ብዬ ተቃውሞዬን ለመግለጽ አስቤ ነበር መልሱን የሰጠሁት፡፡ የመለስኩትን መልስ አይተው ይተናኮሉኝ ይሆን? ብዬ ትንሽም ቢሆን ሆዴ ባርባር ማለቱ አልቀረም፡፡

ሊብያ ስገባ የመጣኸው እስላሞች አገር ነው ተብሎ በተዘዋዋሪ ማስፈራርያም ይሁን ማስገንዘቢያ እንደቀረበልኝ ሁሉ አሜሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ስገባ በተዘዋዋሪ የተነገረኝ ነጮች የነገሡበት አገር ነው የሚል ነበር፡፡ ኒውዮርክ ኬኔዲ አየር ማረፊያ ስገባ የሞላሁት የኢሚግሬሽን ፎርም ከሚጠይቃቸው ጥያቄዎች አንዱ የቆዳ ቀለም የሚል እንደነበር ቀደም ብሎ ገልጫለሁ፡፡ የገላዬ ቅላት ቾኮላት ይመስላል ብዬ ስመልስ እንደሊብያው በማሾፍ ሳይሆን በእርግጥ በዚያን ወቅት ዘረኞች ዓለምን ነጭ፣ ብጫና ጥቁር ብለው ከፋፍለው እንደነበር ስለማውቅ ነበር፡፡ ለዚህም ነበር ምን እመስላለሁ? ብዬ የቆዳዬን ቀለም ትኩር ብዬ ለማጥናት የተገደድኩትና

ምን እንደምመስል ለፈረንጁ ለመግለጽ ቃላት ፍለጋ የሄድኩት፡፡ ወቅቱ በአሜሪካ ውስጥ ሰው በሰውነቱ ወይም በጠባዩና በችሎታው ሳይሆን በቀለም መነጽር የሚታይበትና ለሰው ልጆች እኩል መብት መከበር እነማርቲን ሉተር ኪንግ መስዋዕት የሆኑበት ማግስት ነበር፡፡ የአሜሪካ ነጭ ሕዝብ ጥቁሩ የተፈጸመበትን ግፍ ለመበቀል አይተኛልንም ያለበትና ብጫ ሕዝብ ደግሞ ኮሙኒዝምን ተፈናጦ ደጃፌን በርግዶ ከመግባቱ በፊት ቀድሜ አናት አናቱን ልበለው ብሎ ወደ እስያ የዘመተበት ወቅት ነበር፡፡ ይህ ሲታይ ካርል ማርክስ እንዳለው የሰው ልጅ ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ሳይሆን በዘር ላይ የተመሠረተ የሚመስልበት ወቅት ነበር፡፡ ዘረኛነትን ነጮች የሚያራምዱት ጥቁርና ብጫ ሕዝቦች አንድነት መሥርተው ያጠፉናል ብለው ስለሚያምኑ ይመስላል፡፡ ስለሆነም፣ የሦስተኛው ዓለም ሕዝብ በትውልድ መንደር እየተከፋፈለ ሲፋለጥ ዘረኞች መሣሪያ የሚያቀብሉት ከልብ የመነጨ ደስታ እየተሰማቸው ነው ብዬ እገምታለሁ፡፡

ትሪፖሊ የገባን ዕለት ሙቀቱ ኃይለኛ ስለነበር ማረፊያ ሆቴላችን እንደደረስኩ ቀዝቃዛ መጠጥ እንዲያመጡልኝ አዘዝኩ፡፡ ብጠብቅ አይመጣም፡፡ ሃያ ደቂቃ ያህል ከጠበቅሁ በኋላ ለአገልግሎት ሰጭው ክፍል ስልክ ደወልኩና ቀዝቃዛውን መጠጥ ላኩልኝ፣ እባካችሁን፣ በጥም ልሞት ነው እላለሁ፡፡ እሺ ጌታዬ ቢቀር እየመጣ ነው የሚል መልስ ስጠብቅ በቀጭኑ ሽቦ ውስጥ የመጣልኝ መልስ “ጊዜውን ጠብቆ ይመጣልሃል፣ ችኮላው ምንድነው?” የሚል ነበር፡፡ ጆሮዬን በፍጹም ማመን አቃተው፡፡ በልቤ የለየላቸው ባለጌዎች፣ የመስተንግዶ ሀ ሁ የማያውቁ፣ ጓደኛዬ አስፋው አገኘሁ መጥቶ ባስተማራቸው አልኩ፤ ምን ዓይነቱ አገር መጣሁ ብዬ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ ከሰውዬው ጋር በስልክ ስንጨቃጨቅ አምባሳደር መሐመድ ከተፍ አለ፡፡ የስልኩ ምልልስ ደስ ስላላለው ምንድነው ነገሩ? ይለኛል፡፡ ነገርኩት፡፡ “ቆይ፣ ቆይ፣ ለኔ ተውልኝ” ብሎ ስልኩን ከጄ ወሰደና ከሰውዬው ጋር በአረብኛ መነጋገር ጀመረ፡፡ ቢያንስ አምስት ደቂቃ ያህል በስልክ እየተሣሣቁ ካወሩ በኋላ አምባሳደሩ ስልኩን ዘጋና ወደኔ ዞር ብሎ

“አየህ፣ ይህ አገር ከሌላው ለየት ያለ ነው፤ ሰዎቹን በአመል መያዝ ያስፈልጋል፤ እንዲህ እያስታመምን ነው የምንኖረው» አለኝ:: ይሄ እኮ ገንዘብ የምከፍልበት ሆቴል እንጂ ሰው ማስታመሚያ ቦታ አይደለም፣ በየትም አለም እንዲህ አይነት አገር አይቼ አላውቅም ብለው “የለም፣ እዚህ ሊብያ የተለየ ነው” አለኝ:: በማስረጃነትም የሚከተለውን ደረደረልኝ:: እንድ አምባሳደር ወይም ሾፌሩ በመንገድ ሲያሽከረክር ጥሩንባ የነፋ እንደሆነ ወዮለት:: ሊብያኖች መኪናውን ይከቡና አምባሳደር ብትሆን ማን ሊፈራህ ነው? ብለው ያፈጡበታል፤ ያንጓጥጡታል:: ስለዚህ ዲፕሎማቶች መኪና ሲነዱ እየተሳቀቁ ነው:: ጥቁር መልክ ያላቸው የሊብያ ዜጎች በብዛት አሉ፤ ብዙዎች በግፍ ይገደላሉ:: ገዳዩ ከወንጀል ለመንጻት ማለት ያለበት መሪያችንን ሲሰድብ አገኘሁት ብቻ ነው:: ስለሆነም የጥቁሮች ደም ደመከልብ ነው:: በእኛም ዲፕሎማት ላይ ሰሞኑን የደረሰውን አጫወተኝ:: አንድ ተወላጅነቱ አፋር የሆነ ዲፕሎማት ከካይሮ ወደ ትሪፖሊ ይዛወራል:: ከሻንጣዎቹ ሁለቱ ሳይደርሱለት ይቀሩና አየር ማረፊያ ሄዶ ያመለክታል:: ሳይመጣለት ሲቀር ከጥቂት ቀናት በኋላ ተመልሶ ይሄዳል:: ይሄኔ፣ “እኛ ያንተ ሻንጣ ሌቦች ነን?” ብለው በቡጢ ነርተውት ፊቱ ተነፋፍቶ ተመለሰ:: አምባሳደራችን “የውጭ አገር ሰው እዚህ ተዋርዶ ነው የሚኖረው:: ከኛ አገር ተቃራኒ ነው” አለኝ:: ታዲያ ልባቸውን ቤንዚን አሳብጦታል አትለኝም? ብዬ መለስኩለት::

ከሊብያ ጉዞዬ አንድ ዓመት ቀደም ብሎ ይመስለኛል ሉሳካ የአፍሪቃ ልማት ባንክ ዓመታዊ ስብሰባ ላይ የሳውዲ አረቢያ መልዕክተኞች ቡድን መሪ ለጉባኤው ባደረገው ንግግር ሳውዲ አረቢያ በየዓመቱ ከሠላሳ የማያንሱ የታዳጊ አገሮች መሪዎችን እንደምታስተናግድ ገልጾ ንግግሩን ሲያጠቃልል ታዲያ እነዚህ ሁሉ የሚመጡት እርዳታ ፍለጋ ነው እንጂ በቤንዚን ለመዋኘት አይደለም ብሎ በእብሪት የተሞላ ንግግር አድርጓል:: ሰውዬው ይህን ንግግር ባደረገበት ወቅት አዳራሹ ውስጥ ነበርኩ:: ግፍና ትዕቢት ተዋጊ አምላክ ካለህ ለምን ብቅ አትልም? ነበር ያልኩት፣ በልቤ:: ሊብያኖችና ሳውዲዎች ቤንዚናቸው ያለቀ ዕለት ወይም ተለዋጭ የኃይል

ማመንጫ የተገኘ ዕለት ምን እንደሚሉ መስማት እፈልጋለሁ:: እኔ ባልሰማው የልጅ ልጆቼ ይሰሙታል::

ሆቴሉ በንጽሕናውም ሆነ በአገልግሎት አሰጣጥ ዝቅ ያለ ሆኖ ስላገኘነው በባሕር ላይ ወደሚገኘና እስፓኒሾች ወደሚያስተዳድሩት የመርከብ ሆቴል ተዛውረንና የአምባሳደር መሐመድን ወዳጅ ከጭቅጭቅ ነጻ አወጣነው::

ማረፊያ ከያዝን በኋላ ማእከላዊ ባንካቸው ደወልኩና አዛዡን እንዲያገናኙኝ ጠየቅሁ:: የለም ተባለ:: እሺ ምክትሉን አገናኙኝ አልኩና አገናኙን:: ለድርድሩ ትሪፖሊ መግባቴን ገልጨለት ቀጠሮ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት:: በነገረኝ ሰዓት ቢሮው ድረስ ሄድኩ:: በሩን ከፍቼ ስገባ ከወንበሩ ሳይነሳ፣ ግባ ሳይለኝ፣ እንኳን ወደ አገራችን በደኅና መጣህ ሳይለኝ ተላላኪውን እንደሚያነጋግር ዓይነት "አይመችንም፣ አትምጣ አላልንህም ነበር?" ብሎ ቁጣና ቀልድ በተቀላቀለ አነጋገር ወረፈኝ:: ኦ ኦ እውነትም የለየላቸው ባለጌ ሰዎች አገር ነው የመጣሁት አልኩ:: ትሪፖሊ የመጣሁት ለ150 ሚሊዮን ዶላር መሆኑን ስለማውቅ የፈለገውን ቢለኝ ተነጥፌለት የፈለገውን ያድርገኝ እንጂ ብልግናን በብልግና አልዋጋም የሚል አቋም ወሰድኩ::

የውሉ ድርድር ከሁለትና ሦስት ሰዓት በላይ መፍጀት አልነበረበትም:: ነገር ግን የሊብያ ባንክ ኃላፊዎች ውሉ ተጠናቅቆ ገንዘቡን መልቀቅ ስላልፈለጉ ጥቃቅን ምክንያት እየፈለጉ ድርድሩን አጓተቱት:: ድርድሩ ሁለት ወይም ሦስት ቀን የፈጀ ይመስለኛል:: ውሉ የተዘጋጀው በአረብኛና በእንግሊዝኛ ነበር:: ጣጣ ፈንጣጣ ወጣለት ብዬ በሐሳቤ ስፈነጥዝ ያልተጠበቀ ድንቃራ አመጡና ቸነከሩ:: ችግር የተፈጠረው ሁለቱ ስምምነቶች በትርጉም ባይስማሙ የበላይነት የሚኖረው የትኛው ነው? በሚለው ላይ ነበር:: እኛ ያልነው ዓለም በተቀበለው አሠራር ሁለቱም እኩል ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ስንል በነሱ በኩል ደግሞ አረብኛው የበላይነት ይኖረዋል ብለህ ካልተስማማህ ስምምነቱን በምንም ዓይነት እንፈራረም ብለው ድርቅ አሉ:: የማናውቀው፣ የማንሠራበት ቋንቋ እንዴት የበላይነት ይኖረዋል ብለን እንድንፈርም እንጠየቃለን? በአረብኛው የስምምነት ረቂቅ ውስጥ ምን

እንደተጻፈ እንኳ አናውቅም ብዬ ተከራከርኩ፡፡ በምንም ዓይነት ሐሳባችንን አንለውጥም፤ ካልፈለግህ ትተኸው ወደ አገርህ መመለስ ተችላለህ፤ ሁሉም ገንዘብ ፈላጊ የአፍሪቃ አገር የሚፈራረመው አረብኛው የበላይነት አለው እያለ ነው፤ ከፈለግህ የተፈረሙ ስምምነቶችን አምጥተን እናሳይህ ብለው ሊያሳምኑኝ ወይም ሊያግባቡኝ ሞከሩ፡፡

የውጫሌ ውል ትዝ አለኝ፡፡ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ያተኮሩት በአማርኛው ቅጂ ውስጥ በተጻፈው ላይ ስለነበር በጣልያንኛ የተጻፈው ችግር ያመጣል ብለው አላሰቡም፡፡ ዐይኔ እያየ እንዴት ዳግማዊ የውጫሌ ውል እፈራረማለሁ? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ አረብኛው የበላይነት አለው ብዬ መፈረም ያልፈለግሁበት ዋና ምክንያት ግን ሊብያ ገንዘብ ስላላት ብቻ ድሃ አገሮችን ኀትታ እያመጣች ክብረነክ ውል እንዲፈራረሙ ማስገደዷ ወይም ለማስገደድ መሞከርዋ መንፈሴን ስላሸፈተውና እውስጤ የሚንቦገቦግ ንዴት ስለነበረ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ክብር በገንዘብ የመሸጥ መብት ማንም አልሰጠኝም፣ ለማንም አልተሰጠም አልኩ፡፡ አረቦች በኢትዮጵያ ላይ ሸር ከመሥራት ወደኋላ አይሉም የሚለውም በአእምሮዬ አለ፡፡ በአረብነታቸው ስለ ኤርትራ መገንጠል የደገሱልንን ከሁለት ዓመታት በፊት በመስተንግዶ አዳራሻቸው ያቀረቡልን መራራ ቅምሻ ከእምሮዬ አልጠፋም፡፡ ይህን ሁሉ አገናዘብኩና አረብኛው ቅጂ የበላይነት ይኖረዋል ብዬ በምንም ዓይነት ላልፈራረም ወሰንኩ፡፡

ውሉን ለመፈራረም እንዳልተቻለ ገልጩ መልዕክት አዲስ አበባ አስተላለፍኩ፡፡ የሊብያው ባንክ ሐሳቡን እንዲለውጥ አዲስ አበባ ባለው ኤምባሲያቸው በኩል ግፊት እንዲደረግበት ሐሳብ ሰጠሁ፡፡ መልዕክቱን የላክሁት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍስሐ ደስታ ነበር፡፡ መልስ ሳይመጣልኝ ዘገየ፡፡ ደጋግሜ ማስታወሻ ላክሁ፡፡ ዘግይቶ የመጣልኝ መልስ የሚለው፣ እምቢ ካሉ ምንም ማድረግ አይቻልም፣ ከነሱ የሚጠበቀው ገንዘብ በጣም ብዙ ስለሆነ እነሱ ባሉት መሠረት ውሉን ተፈራርመህ እንድትመጣ የሚል ነበር፡፡

የመጣ ይምጣ እንጂ በምንም ዓይነት አረብኛው የበላይነት አለው ብዬ አልፈራረምም፤ ከፈለጉ አዲስ አበባ ስገባ ይዘው ይስቀሉኝ አልኩና ሻንጣዬን ቀርቅቤ ከትሪፖሊ ለመውጣት ተነሳሁ።

የሆቴል ሒሳብ ለመክፈል ገንዘብ ያዥው ዘንድ ሄደን ሒሳቡን እንዲሠራልን ጠየቅነው። የሆቴሉ መስተንግዶ ኃላፊነት የስፓኝ ኩባንያ ሲሆን ገንዘቡን የሚሰበስቡት ሊብያኖች ናቸው። ሒሳብ ተከፍሏል ተባልን። እንዴት ሆኖ? ብንል የሊብያ ማእከላዊ ባንክ እንግዶቼ ናቸው እከፍላለሁ ብሏል አሉን። በልባችን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ካንቋሸሸን ባንክ በምንም ዓይነት ግብዣ አንቀበልም አልንና፣ እግዜር ይስጥልን፣ እራሳችን እንከፍላለንና ሒሳቡን ሥሩልን ብለን ደጋግመን ጠየቅን። በጭራሽ አይሆንም ብለው ተከራከሩን። እኛም በአቋማችን ጸናን። አውሮፕላናችን ቢያመልጠን ኃላፊ ትሆናላችሁ ብለን ለማስፈራራት ሞከርን። ግማሽ ሰዓት ያህል ከተጨቃጨቅን በኋላ ሒሳቡ ተሠራና ከፍለን ወደ አየር ማረፊያ ነጎድን።

ግማሽ መንገድ ያህል እንደተጓዝን የትራፊክ ፖሊስ ተሽከርካሪዎች በማስጠንቀቂያ መብራት አስቆሙን። ሾፌሩ ምን አጥፍቼ ነው? ቢላቸው፣ የምንፈልገው አንተን ሳይሆን እንግዶቹን ነው፤ ያስቆምናቸሁ የሊብያ ባንክ የላከላችሁን መልዕክት ልንነግራችሁ ነው፤ ውሉን ለመፈራረም ተዘጋጅተናልና ተመልሳችሁ እንድትመጡ ብለዋል ተብሎ ተነገረን። ይሄኔ ደስ አለኝ፤ ሞቀኝ፤ ያሸናፊነት ስሜት ተሰማኝ። ምንም ደሃ ብንሆን ክብራችንን አልሸጥንም አልኩ።

ባንኩ እንደደረስን ምክትል አዛዡ ሲያደርቁን ከሰነበቱት ተደራዳሪዎች ጋር ተቀምጦ አገኘነው። ገና ከመቀመጤ "ሐሳብህን ለውጠህ እኛ ባልነው መሠረት ልትፈራረም ተመለስካ?" ይለኛል። ብልጭ አለብኝና ተነስቼ ቆምኩ። ወደበሩም አመራሁ። ሰውዬው እንደማልበገር ሲያይ፣ እኔስ ቀልዴን ነበር አለና እንድቀመጥ ጋበዘኝ።

ሰነዱ ባልከው መሠረት ተስተካክሎ ተጽፏል፤ አሁን ከሁለታችን የሚጠበቀው መፈረም ብቻ ነው ካለ በኋላ በእንግሊዝኛና በአረብኛ የተዘጋጁትን ሰነዶች ከዴስኩ መሳቢያ አውጥቶ መፈረም ጀመረ:: ከመፈረሜ በፊት የእንግሊዝኛውን ማንበብ አለብኝ እለዋለሁ:: ምነው አታምነንም እንዴ? ይለኛል:: ተስተካክሏል ያለው አንቀጽ ሳይስተካከል እነሱ በፈለጉት ዓይነት የተጻፈው ሆኖ አገኘሁት:: በፍጹም ማመን አቃተኝ:: እንዲህ ዓይነት ውንብድና አይቼ አላውቅም:: የፈለገው አጭበርብሮ ሊያስፈርመኝ ነበር:: ይሄኔ በእርግጥም በጣም አምርሬ ቦርሳዬን አንጠልጥዬ ተነሳሁ:: ግንኙነታችን መጨረሻው ምዕራፍ ላይ መድረሱን ሰውዬው ስለተገነዘበና ካሁን በኋላ በማባበልም ሆነ በማታለል ሊመልሰኝ እንደማይችል ስላወቀ «አንተ የማትቻል ሰው ነህ፤ ይልቅስ ናና ተቀመጥ፤ እንፈራረም» ብሎ የተስተካከለውን ጽሑፍ ከሌላ የጠረጴዛ ኪስ አውጥቶ እንድፈርም ሰጠኝ::

ውሉን ተፈራርሜ እንደጨረስኩ ተቃራኒ ስሜቶች ተፈራረቁብኝ:: በአንድ በኩል የበላይ ነኝ ባዩን ድል እንዳደረግሁት ሳውቅ በኢትዮጵያዊነቴ ትልቅ ኩራት ተሰማኝ:: በሌላ በኩል ደግሞ እንዳሰብኩት ባይሳካልኝና ውሉን ሳልፈራረም አዲስ አበባ ብመለስ ኖሮ እነዚያ የማይተኙልኝ ጠላቶቼ ሥጋዬን ይመትሩት ነበር የሚለው ስጋት በአእምሮዬ ተጉላላ:: እንደዚያ በገደል አፋፍ ላይ መዳከሬ ኢትዮጵያ በእርግጥም ከእኔ የምትፈልገው ወይም የምትጠብቀው እርምጃ ነበር? ወይስ ጀብደኝነት? ብዬ እራሴን መጠየቁ አልቀረም:: ለማንኛውም ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም እንዲሉ የአባቴና የኢትዮጵያ አምላክ ከጉድ አወጡኝ::

ከትሪፖሊ ወደ ሮም የሚወስደን አውሮፕላን የሊብያን ግዛት ለቆ ዓለም አቀፍ ክልል መግባቱን አብራሪው ሲነግረን፣ የኢትዮጵያ አምላክ እባክህን ይህን አገር ዳግመኛ እንዳታስረግጠኝ ብዬ ተማጽኜዋለሁ:: እስካሁን ሰምቶኛል::

ከትሪፖሊ መልስ እኔ ለአይ ኤም ኤፍ ስብሰባ ወደ ዋሺንግተን መሄድ ስለነበረብኝ ከክፍሌ ጋር ሮም ተለያየን፡፡ ከመለያየታችን በፊት ከትሪፖሊ ጉዞዬ ጋር የተያያዙትን ወጪዎች በባንካችን ደንብ መሠረት እንዲያወራርድልኝ የሆቴል ደረሰኞች አውጥቼ ሰጠሁት፡፡ ከዋሺንግተን ጉዞዬ ጋር የተያያዙትን ወጭዎች አይ ኤም ኤፍ ስለሚከፍል ሒሳብ ማወራረዱ አዲስ አበባ እስክመለስ እንዲጠብቅ አልፈለግሁም፡፡ ደረሰኞቻችንን በጽሞና ስንመረምር ላልበላነውና ላልጠጣነው ብዙ ትርፍ ገንዘብ እንዳስከፈሉን ተረዳን፡፡ ምን ዓይነት ወራዶች ናቸው ተባባልን፡፡ ለካስ የሆቴሉ ገንዘብ ቤት ሠራተኛ ገንዘብ ከኛ መቀበል ያልፈለገው እንግዶቼ ናቸው ያላቸውን ባንካቸውን ከተሰጠን አገልግሎት በላይ ሊያስከፍሉት አቅደው ስለነበር መሆኑን ደረስንበት፡፡ ከፋይ እኛ ከሆንን ግን ሒሳቡን በዝርዝር ዓይተን ጥያቄዎች እንደምናነሳ ያውቃሉ፡፡ ሆኖም፣ የፈሩት ሳይደርስ ቀረ፤ ምክንያቱም ከጊዜ እጥረት የተነሳ ዝርዝሩን ሳናይ ቀረንና ላቀዱት ብዝበዛ ተመቻቸን፡፡ ሲጨቃጨቁ ጊዜ ያቃጠሉብን የጊዜ እጥረት ስለሚያጋጥመን ደረሰኞቹን አንድ በአንድ መርምረን እንደማናይ ስለገመቱ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ጥበበኛ ሌቦች፡፡ የሊብያ ቱጃር የኢትዮጵያን ድሃ ሲሰርቅ ከማየት የበለጠ የሚያስቆጣ ነገር የለም፡፡ ወደ ትሪፖሊ አልመለስ ነገር አምላኬ እንዳይመልሰኝ ተማጽኜዋለሁ፡፡ በእርግማኔ ያልተስማማው የሊብያ አምላክ ሁኔታዬን ዐይቶ ሳይሥቅብኝና ምላሱን ሳያወጣብኝ የቀረ አይመስለኝም፡፡

ክፍሌ አዲስ አበባ የገባ እለት የከፍተኛ የመንግሥት ልዑካን ቡድን አባል ሆነህ ወደ ትሪፖሊ መሄድ አለብህ ተባለና ሳያስበው ወደቀማኞቹ ተመልሶ የመሄድ ዕድል አጋጠመው፡፡ እነዚያን የተጭበረበሩ ደረሰኞች ይዞ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ በረረ፡፡ ትሪፖሊ እንደደረሰ ሆቴሉ ድረስ ሄዶ ጉዳዩን ቢያስረዳ ገንዘብ ተቀባዩ ወጣ ብሏል፣ ዛሬ አልገባም፣ ነገ ተመለስ እያሉት እግሩ እስኪቀጥን ቢመላለስም ገንዘቡን ሳያገኝ ወደ አገር ተመለሰ፡፡

በነገራችን ላይ 150 ሚሊዮን ዶላሩ በሙሉ እጃችን ገብቷል። ገንዘቡ ኒው ዮርክ ባንክ ሒሳባችን ውስጥ እስኪገባ ድረስ ሊብያኖቹ ቃላቸውን ጠብቀው ይለቁልናል ብዬ አላመንኩም ነበር። ይህን ያህል ገንዘብ ባንድ ጊዜ ለአንድ ትንሽ አገር በሌላ አገር ሲሰጥ በታሪክ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። በብድሩ ውል ስምምነት መሠረት ገንዘቡ ተከፍሎ የሚያልቅበት ዘመን ያለቀ ይመስለኛል።

የገንዘቡ መገኘት ገጥሞን የነበረውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለጊዜውም ቢሆን ልንቋቋመው አስችሎናል። ስለሆነም፣ በተለይ ቀጣፊ ባለውለታችን ነው። ይህን ስሜታችን አዲስ አበባ የሚገኘው የሊብያ አምባሳደር ያውቅ ስለነበር በየጊዜው ቢሮዬ ድረስ እየመጣ ይህን፣ ያን አድርጉልኝ እያለ ሲጠይቀን እንተባበረው ነበር። ለምሳሌ፣ በባንካችን ፖሊሲ መሠረት ወደ ውጭ ለሚሄድ ሰው እንጂ ለአገር ውስጥ ነዋሪ የውጭ ምንዛሪ በጥሬ ገንዘብ አንሰጥም ነበር። ፖሊሲው የተቀየሰው ገንዘቡ ጥቁር ገበያ ለማስፋፊያ እንዳይውል ለመከላከል ነበር። አምባሳደሩ ግን ምክንያት እየፈጠረ ለዚህ ጉዳይ ጥሬ ገንዘብ አስፈልጎኛልና ከሒሳቤ ወይም ከኤምባሲው ሒሳብ ወጪ ተደርጎ ይሰጥኝ ሲል እንተባበረው ነበር። የሚጠይቀው ገንዘብ መጠን በጣም ጥቂት፣ ማለትም ከጥቂት ሺህ የማይበልጥ፣ በመሆኑ ግድየለም እንተባበረው እያልኩ ፍላጎቱን እናሟላ ነበር። ወደ ኋላ ግን ቀጣፊ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ሊቀመንበር መሆን ፈልጎ ሳይሳካለት ሲቀር ኢትዮጵያ አደናቅፋኛለች ብሎ ሸር ለመሥራት ስለተነሳሳ ያን አምባሳደር ያላከበርነው ያህል ዐይንህ ላፈር ብለነው ነበር። በፕሮቶኮል ቦታዎች ስናገኘው የሚያነጋግረው እንኳ ነበር ለማለት ያስቸግራል። ሁላችንም እንዳላየነው እንሆን ነበር። በበኩሉ እነዚህ ውለታ ቢሶች ሳይለን አይቀርም። ባገራችን ላይ ለመጣ ምንም ይቅርታ እንደማናደርግ ገብቶታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

በገንዘብ ሀብታም በሞራል ግን ድሃ የሆነ አገር ምን እንደሚመስል ዐየን፡፡ ሞራል የሌለው ሕዝብ በራሱ ወይም በሌላ እጅ መጥፋቱ የማይቀር ነውና አገራችን ሀብታም ስትሆን ልጆችዋ ሞራለቢስ እንዳትሆኑ ተጠንቀቁ፡፡

ስለትሪፖሊ ጉዞዬ በጥር 1985 የደረስኩት ግጥም "ባለጸጋን መለማመጥ" በገጽ 485 ሰፍሯል፡፡

# ፕሬዚዳንት ባንዳ

የአፍሪቃ ማእከላዊ ባንኮች ማኅበር ሊቀመንበር በነበርኩበት ወቅት የአፍሪቃ አገሮች ስለገጠማቸው የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመወያየት በ1974 ወይም 1975 በብላንታየር፣ ማላዊ ውይይት አካሂደናል፡፡ ስብሰባውን የከፈቱልን የአገሩ ፕሬዚዳንት ካሙዙ ባንዳ ነበሩ፡፡

ስለካሙዙ ባንዳ ማንነት መጀመሪያ የሰማሁት ከአብሮ አደጌ ከጸጋዬ ኃይለማርያም እንደሆነ ቀደም ብሎ ገልጫለሁ፡፡ ለማስታወስ፣ ካሙዙ ባንዳ ማለት "አፍሪካን ሊደርስ አር ፕሌዩንግ ዘ ፓን አፍሪካኒዝም ኦርኬስትራ ሁዌን ዘየር ሆምስ አር በርኒንግ፤ አፍሪካን ሊደርስ አር ላይክ ሃይናስ፣ ዘይ ሃውል ኤንድ ግራውል በት ዘይ ዱ ኖት ባይት" ያሉት ሰው ናቸው፡፡ ሴሚናሩ ብላንታየር ይደረጋል ከተባለ ጀምሮ ሰውዬውን ፊት ለፊት የማገኝበትን ቀን በጉጉት ስጠባበቅ ሰነበትኩ፡፡

ውይይቱ የሚካሄድበት ግቢ ስንደርስ ከስድስት ሺህ የማያንሱ ዩኒፎርም የለበሱ ሴቶች ወደ ስብሰባው አዳራሽ በሚያመራው መንገድ ግራና ቀኝ ተኮልኩለው መዝሙርና ጭፈራ ያቀልጣሉ፡፡ እንደተነገረኝ መዝሙሮቹ ባንዳን የሚክቡና ተቀናቃኞቻቸውን የሚያኮስሱ ነበሩ፡፡

ፕሬዚዳንቱ የሚመጡበት ሰዐት ሊደርስ ሲል እኔና የአገሩ ማእከላዊ ባንክ አዛዥ ልንቀበላቸው አዳራሹ በራፍ ቆመን እንጠባበቃለን፡፡ የሴቶቹ

መዝሙርና ጭፈራ በእጥፍ ጨምሯል:: ፕሬዚዳንቱ በክፍት ላንድሮቨር ላይ ቆመው ነጭ ጭራ ግራና ቀኝ እየነሰነሱ ብቅ ሲሉ የሴት ምላስ በኅብረት ተቃጠለ፤ አየር፣ መሬት እንዲሁም ስሜት አብሮ ተቀጣጠለ:: ሴቶቹ መኪናውን ከበቡና ውዱን መሪያችንን ማን ሊወስድብን? የብቻችን ነው፣ አንለቅም አሉ ተባለ:: የላንድሮቨሩ ፍጥነት ወደ አንድ ኪሎ ሜትር በሰዓት ስለወረደ የፈረስ ጉልበት ሴቶቹ ለመሪያቸው ባላቸው ፍቅር ተብረከረከ ተባለ:: ቲያትር በቲያትር:: መዝሙሩ፣ ጭፈራው፣ ዳንኪራው ቅልጥልጥ አለ:: ትዕይንቱ ሠላሳ ደቂቃ ፈጀ:: ስብሰባው አዳራሽ ተቀምጠው የሚጠባበቁት ሌሎቹ ልዑካን ትንግርት አመለጣቸው አልኩ:: የቲያትሩ የበላይ አቀናባባሪ እራሳቸው ሰውዬው ነበሩ ለማለት ያስደፍራል፤ ትዕይንቱ ለጊዜውም ቢሆን ይብቃ፣ እረፍት ይደረግ፣ መጋረጃ ይውረድ ለማለት ፈልገው የሾፌራቸውን አናት በጭራቸው መታ ሲያደርጉት ያ ሁሉ ሴት ከመቅጽበት መንገዱን ለቀቀላቸውና የፍቅርን መረብ በጣጥሰው ስብሰባው አዳራሽ በራፍ በድል አድራጊነት ለመድረስ ቻሉ! የአፍሪቃውያን ቲያትር::

ከፕሬዚዳንቱ ጋር በማላዊ ባንክ አዛዥ በቴምቦ አቅራቢነት ተዋወቅሁ:: የጨበጥኩት እጅ ተደጋግፎ የተቀመጠ ሰባራ ሽክላ መስሏል:: ነካኳቸው እንጂ ጨበጥኳቸው ለማለት አያስደፍርም:: ምላስ ብቻ፣ አቅመቢስ አልኩኝ:: ልዩ ረዳታቸው ናት የተባለች ከአጠገባቸው የማትጠፋ ቀውላላ ነጭ ሴት ፊት ፊት ትመራለች:: እሾህን በእሾህ እንዲሉ ለነጭ የነበራቸውን ጥላቻ ለማርከስ የተሰጠቻቸው ሳትሆን አትቀርም ብዬ ገመትኩ:: ሰውዬው በቅጡ መራመድ ስለተሳናቸው እግሮቻቸውን መጎተት ጀምረዋል::

ስብሰባው አዳራሽ ውስጥ እኔ እንድቀመጥ የተደረገው ከፕሬዚዳንቱ ጀርባ ከባንኩ አዛዥ ጎን ነበር:: እሳቸው ብቻቸውን ፊት ለፊት ፈንጠር ብለው እንዲቀመጡ ተደርጓል:: የባንኩ አዛዥ ከውጭ የመጡትን እንግዶችና ያገሩን ባለሥልጣኖች እንዲሁም ዲፕሎማቶች እንኳን ደኅና መጣችሁ ካለ

በኋላ ስለውይይቱ ዓላማና ስለማኅበራችን ገለጻ እንዳደርግ ጋበዘኝ። ዐሥራ አምስት ደቂቃ የፈጀ ንግግር አደረግሁ።

ፕሬዚዳንቱ ስብሰባችንን በንግግር እንዲከፍቱልንና እንዲባርኩልን ተጋበዙ። የተዘጋጀ ጽሑፍ ሰዎቻቸው ሰጧቸው። የውይይቱ አርእስት "ዘ ባላንስ ኦፍ ፔይመንትስ ፕሮብሌምስ ኦፍ አፍሪካን ካንትሪስ" "The Balance of Payments Problems of African Countries" የሚል ነበር። ባላንስ ኦፍ ፔይመንትስ ፕሮብሌምን አውቀዋለሁ ብለው ንግግራቸውን ጀመሩ። ባላንስ ኦፍ ፔይመንት ሰው መሰላቸው እንዴ? ምን ይዘባርቃሉ፣ ብለን ብዙዎቻችንን ሣቅ አፈነን፣ የሣቀም አልጠፋም። «መጀመሪያ የተዋወቅሁት ካሱንጉ ሆኜ ነው» ብለው ቀጠሉ። ይሄኔ በገሀድ ሣቅን። ሰውዬው ስተዋል አልን። ካሱንጉ የትውልድ መንደራቸው ናት። ሲያስረዱ፣ "በካሱንጉ እንደ ማንኛውም ስፍራ ሁለት ዓይነት ገበሬዎች አሉ፣ ሀብታምና ደሃ። ምርት እስኪሰበሰብ ደሃዎቹ ገበሬዎች የገንዘብ እጥረት ሲያጋጥማቸው ሀብታሞቹ ዘንድ እየሄዱ ሲበደሩ ዐይ ነበር። ይህም ማለት የካሱንጉ ደሃ ገበሬዎች የባላንስ ኦፍ ፔይመንት ችግር ይገጥማቸው ነበር ማለት ነው" ብለው አስቀመጡት። አፌን በዳቦ፣ ሰውዬው ያሰቡኩትን ያህል ቀባዣሪ አይደሉም አልኩ። አያይዘው፣ በአፍሪካ የእርሻ ምርት መዳበር መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን አውስተው ጣታቸውን ወደ ሰሜን ወይም ኢትዮጵያ አቅጣጫ ቀስረው ሶሻሊዝም የሚከተሉ አገሮች ይኸው ለረኀብና ቸነፈር ተዳርገዋል አሉና ሶሻሊዝምንና ኮምዩኒዝምን እንደልባቸው ወረፉ።

ለሁለተኛ ጊዜ የባላንስ ኦፍ ፔይመንት ችግርን ያገኘሁት እንግሊዝ አገር ነበር አሉ። ሲያስረዱ፣ እንግሊዝ አገር ሆኜ ጠቅላይ ሚኒስትር አትሌ የእንግሊዝ የክፍያ ሚዛን ችግር ከአሜሪካ ባለሥልጣኖች ጋር ለመነጋገር ወደ አሜሪካ ሲመላለሱ እናይ ነበር አሉ።

ለሦስተኛ ጊዜ ያገኘሁት እዚህ ማላዊ ነው፣ አብረን እንኖራለን አሉ። ችግሩን እኔና የገንዘብ ሚኒስትሬ ልንቋቋመው በመታገል ላይ ነን አሉና

ቆም ብለው ግራና ቀኝ በዐይናቸው እየቃኙ፣ ለመሆኑ የገንዘብ ሚኒስትሬ የት ነው ያለው? ብለው ይጠይቃሉ። ለካስ ሚኒስትሮቹ የተወሰነ ቦታ ስላልተመደበላቸው በስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ፈንጠር ፈንጠር ብለው ከሌላው ተጋባዥ ጋር ተደባልቀው ተቀምጠው ኖሯል። ከጀርባችን፣ እዚህ ነኝ ጌታዬ የሚል ድምፅ ሰማን። በተለይ ከውጭ የመጣነው ዞር ብለን አየነው። ተነስቶ ቆሟል። ባንዳ ስለሰውዬው ማንነት ወይም ምንነት ዓለም ሁሉ እንዲያውቅላቸው ፈለጉና "እሱ ለእናንተ ትልቅ ሰውና ሚኒስትር ነው፣ ለኔ ግን አንድ ትንሽ ልጅ ነው" ካሉ በኋላ እንደገና ፊታቸውን ወደሱ አዞሩና፣ "አይደለህም እንዴ?" ይሉታል። ልክ ነዎት ጌታዬ ካለ በኋላ መላ አካላቱን የወረረውን የኀፍረት ወይም ውርደት ስሜት በውሸት ሣቅ ለመሸፈን ሲሞክር ሳይ በሱ ፈንታ መሬት በዋጠኝ አልኩ።

በኢትዮጵያችንም ደኅና አድርገን እንደምናውቀውና ደጋግሜ እንዳነሳሁት ደካማ ባለሥልጣን ትልቅነቱን የሚለካው ሌላውን አሳንሶ በማየት ይመስለዋል። ለዚህም ሳይሆን አይቀርም አፍሪቃውያን የዓለም ጭራ ሆነን የቀረነው። ባንዳም ያደረጉት አዲስ ነገር አልነበረም። እንግሊዞች እንደሚሉት የገንዘብ ሚኒስትራቸውን በቦታው ካስቀመጡት በኋላ ተቀመጥ ብለው አዘው ከመሬት ጋር ደባለቁት።

"ዐያችሁ" አሉ ባንዳ፣ "ቅኝ ገዥዎች ወደ አፍሪቃ ከመምጣታቸው በፊት እኛ አፍሪቃውያን ፍርድ ቤታችን የዛፍ ጥላ ነበር። ኮሎኒያሊስቶች መጡና ካቅም በላይ ሕንጻ አንድንገነባ አስገደዱን። ይህም ለውጭ ምንዛሪ ችግራችን መባባስ ተጨማሪ ምክንያት ሆነ። የእርስ በርስ ግጭት ሲከሰት በሽማግሌዎች ዳኝነት ችግሮቻችንን እንፈታ ነበር። ኮሎኒያሊስቶች ፖሊስና ጦር ሰራዊት ካልተቋቋመ ብለውን በጣም ብዙ ደመወዝ በሊታ ስለፈጠርን የውጭ ምንዛሪ ችግራችን ተባባሰ።" እንዲህ እንዲህ እያሉ ዘመናዊ ተቋሞችን ሁሉ ኮነኑ። ባለሥልጣኖቻቸውንም አንድ በአንድ እያነሱ አፈረጡ።

እንደገናም ስለእርሻው ዘርፍ ወሳኝነት አወሱና ቆም ብለው፣ ለመሆኑ የእርሻ ሚኒስትሬ የት ነው ያለው? ብለው ጠየቁ። ካንዱ አሳቻ ስፍራ እዚህ ነኝ ጌታዬ የሚል ድምጽ ሰማን፤ ሰውዬው ተነስቶ ቆመ። ና ውጣ፣ ና እዚህ አሉትና ቀረበ። ማይክሮፎኑን ወደ ሰውዬው ጠጋ አድርገው፣ በል ትናንት ቢሮዬ መጥተህ የነገርከኝን ምንም ሳታስቀር እዚህ ላሉት አሁን ተናገር ይሉታል። ያንን ሰውዬ አያድርገኝ። ላብ አሰመጠው፤ የሚለው ጠፋው። ምንም ምርጫ ስላልነበረው ለማይመለከተን ሰዎች ባጭሩ የነገረን ብዙ ሚኒስትሮችን እንዳማላቸውና ድርጊታቸውን እንዳሳበቀ ነበር። ያስቀረው ነገር ቢኖር ኖሮ ፕሬዚዳንቱ ፊት ለፊት ያፋጥጡት እንደነበርና በዋሾነት እጅ ከፍንጅ ተይዞ ወደ በለጠ ችግር ውስጥ እንደሚገባ ስለሚያውቅ ምንም ሳያስቀር ዘከዘከው። የተጋለጠው ሰውዬው ብቻ ሳይሆን የፕሬዚዳንቱ ተራ ወይም ርካሽ የከፋፈለህ ግዛው ፈሊጥም ነበር። ታዲያ ያልገባኝ ነገር ቢኖር ጉዳቸውን ለምን ዓለም ሁሉ እንዲያውቅ እንደፈለጉ ነበር። ሚኒስትሩ ዝርገፋውን ሲጨርስ ባንዳ ማይክሮፎኑን አንደገና ከተቆጣጠሩ በኋላ፣ እዚያ ከተሰባሰብነው ፍርድ ይጠብቁ ይመስል፣ "አያችሁልኝ፣ ከእንደዚህ ዓይነት ወሸከሬዎች ጋር ነው የምሠራው" አሉና የመንግሥት ባለሥልጣኖቻቸውን ብሎም መንግሥታቸውን ድራሹን አጠፉት። ፕሬዚዳንቱ ሳይወርፉ ያለፉት የባንኩን አዛዥ ብቻ ነበር። እንደሰማነው አዛዡ የእህታቸው ወይም የወንድማቸው ልጅ ሲሆን ለፕሬዚዳንትነት ያጬት ሰው ነበር ይባላል።

የመክፈቻው ሥነሥርዓት አልቆ ልንሸኛቸው በአጀብ ከስብሰባው አዳራሽ ወጣን። በራፍ ስንደርስ ሴቶቹ መዝሙርና ጭፈራቸውን እንደገና አጧጧፉት። ባንዳ ላንድሮቨራቸው ላይ ቆመው ጭራቸውን ግራና ቀኝ እየነሰነሱ ያ የኤሊ ጉዞ ተጀመረ። ከየአገሩ የመጣውም መልዕክተኛ አስገራሚውን ትዕይንት የማየት ዕድል አጋጠመው።

ከፕሬዚዳንቱ ጋር ተሰነባብተን ትዕይንቱን ለሁለተኛ ጊዜ ቆሜ ስመለከት አጠገቤ ቆመው የነበሩት የቀድሞ የጋና ማእከላዊ ባንክ አዛዥና አንድ ናይጀሪያዊ ባለሥልጣን ነበሩ:: ሁለቱም ስለባንዳ የሚያውቁትን ነገሩኝ::

የጋናው ፕሬዚዳንት ክዋሜ ንክሩማህ ለንደን በነበሩበት ወቅት ከባንዳ ጋር ጓደኛሞች ነበሩ:: ሁለቱም የተናጋሪዎች መድረክ የሚባለው ስፍራ ወይም የስፒከርስ ኮርነር አዘውታሪዎች ስለነበሩ ዕድሉ ምላሳቸውንና አንደበታቸውን ለማፍታታት፣ አእምሮአቸውን ለመሳል፣ ከቅኝ ግዛት ባለሥልጣኖች ጋር ለመቆራቆዝና ለነጻነት ትግል ለመዘጋጀት እንደረዳቸው ይታመናል:: ንክሩማ የነጻነት ንቅናቄ ለማካሄድ እአአ በ1950 አጋማሽ ወደ አገራቸው ሲመለሱ ባንዳ እዚያው ለንደን መቆየት መረጡ::

ጋና ነጻ ከወጣች በኋላ ንክሩማህ ባንዳን "ፈረንጅ አገር ምን ታደርጋለህ? እኔ ዘንድ ብትመጣና አገርህ ነጻ የምትወጣበትን መንገድ ብትፈልግ ይሻልሃል" ያሏቸዋል:: ባንዳ ጓዛቸውን ጠቅልለው ጋና ገቡ፤ ተቀማጭነታቸው ኩማሲ በሚባለው ከተማ ሆነ:: ባንዳ የሕክምና ዲግሪ ከእንግሊዝ አገር አግኝተው ስለነበር ኩማሲ የሕክምና ሥራ ጀመሩ:: አጠገቤ የቆመው ጋናዊ አባቱን ልብሱን አስወልቀው ከራስ ጸጉር እስከ ጥፍር ይመረምሩት ወይም ይፈትሹት የነበሩት ባንዳ አሁን የቲያትር መድረክ አቀነባባሪ ሆነው ሲያይ፣ ባንዳ አባቴን አሁን እዚህ ቢያገኙት ኖሮ ና ውጣና ያኔ አለብህ ያልኩህን በሽታዎች በሙሉ እዚህ ለተሰበሰበው ሕዝብ አንድም ሳታስቀር ተናገር ብለው ያስገድዱት ነበር ብሎ ማሰቡ አይቀርም::

ባንዳ በኩማሲ ከሕክምናው ሥራቸው ጎን ለጎን የፖለቲካ ሥራ ጀመሩ:: በዚያን ዘመን ባንዳ ስለነጮች ክፉነት የሚናገሩት ደም የሚያስቀምጥ ነበር ይባላል:: ከማልኮም ኤክስ ጋር ቢወዳደሩ ምናልባት ያሸንፉት ነበር:: የከፋው ጥቁር የባንዳን ንግግር ሲያዳምጥ የበላውን ያከኩለት እየመሰለው እፎይ፣ ጎሽ ተመስገን ጌታዬ ይል ነበር ይባላል:: የናይጀሪያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉላቸው ባንዳን ይጋብዛሉ:: አጠገቤ ቆሞ

የነበረው ናይጄሪያዊ ያን ጊዜ የዩኒቨርስቲው ተማሪ ነበር፡፡ ባንዳ ባደረጉት ንግግር ሰይጣንና ነጮች አንድ ናቸው አሉ፡፡ አድማጩ በባንዳ ንግግር በጣም ከመደሰቱና ከመነሳሳቱ የተነሳ ባንዳ የተቀመጡበትን አውቶሞቢል ተሜ ተሸክሞ ከመሬት አነሳው፡፡ ነጻነት የጠማው አፍሪቃዊ ሁሉ ባንዳንም በጭንቅላቱ ተሸክሞ ለኔ ሲሉ ይቀመጡብኝ፣ አላወርድዎትም ጌታዬ የተባሉ ውድ የአፍሪቃ ልጅ ነበሩ፡፡

ባንዳ ፕሬዚዳንት በሆኑ ማግስት "አፍሪካን ሊደርስ አር ፕሌዩንግ ዘ ፓን አፍሪቃኒዝም ኦርኬስትራ ሁዌን ዘየር ሆምስ አር በርኒንግ" ብለው ከደቡብ አፍሪቃ ዘረኞች ጋር አፍ ለአፍ ገጥመው፣ እጅና ጓንት ሆነው በአፍሪቃውያን ወንድሞቻቸው ላይ የፕሮፓጋንዳ ጦርነት ያወጁና በአፍሪቃ መሪዎች ስብሰባ አንዴም ያልተገኙ ወራዳ ሰው ሆነው ተገኙ፡፡

የብላንታየር ውይይት እንደተጠናቀቀ ሊሎንግዌ የሚባለውን አዲስ ከተማ ሊያስጎበኙን ወሰዱን፡፡ የከተማው ቅየሳ በጣም ግሩም ነው፡፡ ሕንጻዎቹና መንገዶቹ በጣም ያምራሉ፡፡ ከተማውን ለመሥራት ገንዘብ ከየት እንዳገኙ ጠየቅናቸው፡፡ የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት እርዳታ መሆኑን ገለጹልን፡፡ ሊሎንግዌ የሚገኘው ማዕከላዊ ባንካቸው ሕንጻ በጣም ውብና ዘመናዊ ነው፡፡ ከታች ቀጠን ብሎ ከላይ ሰፋ ያለ ስለሆነ የተቸከለ ዊጅ ወይም ባናቱ የተተከለ ሦስት መዕዘን እንጨት ይመስላል፡፡ ሕንጻውን የሠራላቸው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት መሆኑን ገለጹልን፡፡ ዲዛይኑን ሲመርጡ መሬት ቀደው ከደቡብ አፍሪቃ ጋር የመቀላቀል ሐሳብ እንደነበራቸው ጠየቅናቸው፡፡ የለም፣ ዲዛይኑን የመረጥነው ማዕከላዊ ባንካችን የማላዊን ኤኮኖሚ እንዳይንገዳገድ እንደ ችካል ወጥሮ ወይም ደግፎ የያዘ መሆኑን ለማብሰር አቅደን ነው አሉን፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የንግድ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት የነበረው ሕንጻ ኮምፕሌክስ ፕላኑ ግሩም ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም፡፡ ሕንጻውን ያሠሩትና የሠሩት ሰዎች ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ ስለሕንጻው ፕላን ሠዓሊ ጥበበ ተርፋ የሰጠውን ትርጉም ወዳጄ ሰለሞን ገብሬ፣

ሁለታችንም አገር ጥለን ከወጣን በኋላ፣ እንደሚከተለው ነግሮኛል:: ከመከላከያ ሚኒስቴር አቅጣጫ ወይም ከበስተምስራቅ ወደ ንግድ ባንክ ትልቁ ቅርንጫፍ ሲገባ ብዙ ደረጃዎች ተወጥቶ ነው፤ ይህ የሚያመለክተው ገንዘብ ለማግኘት ቀላል እንዳልሆነና ብዙ ውጣ ውረድ እንዳለበት ነው:: ክቡ ህንጻ የሚያመለክተው ደግሞ ቁልል ሳንቲም ወይም ገንዘብ ነው:: ሁለቱ በአንድ ላይ ሲተረጎሙ መውጣት መውረድን ወይም ድካምን ያልፈራ ሰው የተመኘውን ነዋይ ለማግኘት የሚያግደው ነገር እንደሌለ ነው:: ብሔራዊ ባንክን በተመለከተ ደግሞ፣ ባንኩ በአራቱም ማዕዘን አርቆ ማየት በሚያስችለው በረዥሙ ሕንጻ ውስጥ፣ ከክቡ ሕንጻ ወይም ከቁልሉ ገንዘብ በስተጀርባ ተቆናጦ፣ የሕዝብ ገንዘብ አላስነካም ወይም አላስበላም ብሎ የሚጠብቅ ዘብን ይመስላል::

የብሔራዊ ባንክን አርማ በውድድር አሸንፈው የነደፉልን ዝነኛው ሠዓሊ አለፈለገሰላም ናቸው:: እላይ የተጠቀሰው የሠዓሊ ጥበበን ትርጉም ባንክ እያለሁ ብሰማ ኖሮ ይህን ጥበበኛ አቅርቡልኝና ልተዋወቀው ማለቴ የማይቀር ነበር::

እንደታማኝ ውሻ ባንዳ ላጎረሳቸው ቢጮሁ ብዙም አያስገርምም:: በእኔ እይታ ግን ወንድሞቻቸውን በመክዳታቸውና ከጥቁር አራጆች ጋር በመተባበራቸው ታሪክ መቀመቅ አውርዶ ጥሏቸዋል:: ባይፈጠሩ ይሻላቸው ነበር:: ስም ከመቃብር በላይ ይውላል ሲባል ሚች ሁሉ በደጎና ወይም በክፉ ለዘላዓለም ሲታወስ ይኖራል ማለት ነው:: ደግ የሠሩት ሲወደሱ ክፉዎች ደግሞ ሲረገሙ ይኖራሉ:: ሲኦልና ገነት ትርጉሙ ይኸው ነው:: በፈራጅና ተፈራጅ ሥነልቦና ውስጥ የተቀረጹ የማይዳሰሱ ዓለማት ናቸው:: ሲኦልና ገነት እኛ ውስጥ ይኖራሉ እኛም እውስጣቸው እንኖራለን:: ጽድቅና ኩነኔ ለኔ ሌላ ምስጢር የለውም:: የላይኛው ጌታ ይቅር ይበለኝና ሲኦልንና ገነትን ለማግኘት ክንፍ አውጥቶ ወደ ሰማይ መብረር ወይም አሎሎ ባንገት አንጠልጥሎ ወደ ከርሰ ምድር መውረድ አያስፈልግም:: ሁለቱም የሚገኙት እያንዳንዳችን ውስጠ ኅሊናና እይታ ውስጥ ነው::

ሁሉም ሰው፣ መሪዎችን ጨምሮ፣ ይህን ሐቅ በውል ቢረዳ ታሪኩን አበላሽቶ ዘርማንዘሩን የሚያሳፍርበት ምክንያት ሊኖር ስለማይችል ሲኦል ይዘጋና ዲያብሎስ ሥራ ይፈታ ነበር፡፡

ከባንዳ ታሪክ የምንማረው ነገር ቢኖር ብዙ ፖለቲከኞች ሥልጣን ላይ እስኪወጡ ድረስ መራጩ መስማት የሚፈልገውን ያንቆረቁሩና በሥልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጡ በኋላ ግን የቆሙለትን ዓላማ እርግፍ አድርገው በመተው የራሳቸውን ቦታ ማመቻቸትና ተቀናቃኞቻቸውን ባላቸው ኃይል ሁሉ መምታት መደበኛ ሥራቸው አድርገው እንደሚይዙት ነው፡፡

መራጮች እንክርዳዱን ከስንዴ መለየት፣ ስንዴ ነኝ ብሎ ተሸሎክልኮ የገባውን እንክርዳድ ደግሞ አንጓለው መጣል ሲችሉ በአፍሪቃ ሰላም፣ መረጋጋትና ብልጽግና ይሰፍናል፡፡ ተለማማጭ የሕዝብ ተመራጭ እራሱን ወደ እባብነት ለውጦ ከሕዝብ አናት አልወርድም እስካለ ድረስ ወይም የሕዝብ መሪ ለመሆን ብቃት የሌላቸው ወሮበሎች መድረኩን እስካጣበቡት ድረስ ጥቁር አፍሪቃውያን የነጭና ብጫ ሕዝቦች መሣቂያ እንደሆንን እንቀራለን፤ አዘቅት ውስጥ መንደፋደፍ እንቀጥላለን፡፡ ሕዝብ መብቱን ማስከበር የሚችለው በትግሉ ብቻ ነው፡፡ እጅን አጣጥፎ ተቀምጦ አምላኬ አንተ ታውቃለህ ማለት የትም አያደርስም፡፡ እግዜር እራሳቸውን ለመርዳት ያልተዘጋጁትን አልረዳም፣ አታስቸግሩኝ ብሏል፡፡ ስለሆነም፣ ቁም ነገሩ ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ፤ ያለበለዚያ ድንጋይ ነህ ተብለህ እንደምትጣል እወቅ መሆኑን አንርሳ፡፡

# ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የነበረው ግንኙነት

ሊቀመንበር መንግሥቱ ከሶሻሊስት አገሮች ጋር የወዳጅነት ውል ለመፈራረምና እርዳታ ለመጠየቅ በ1971 ጉብኝት ባደረገበት ወቅት ባንክን ወክዬ መገኘቴን ቀደም ብሎ ገልጫለሁ፡፡

አፍሪቃን ረግጣችሁ ወይም ተረማምዳችሁ ሄዳችሁ እንዳንባል ከምስራቅ አፍሪቃ ታንዛንያን፣ ከምዕራብ አፍሪቃ ደግሞ ናይጄሪያን ነብኝተን እንለፍ ተባለ:: መገመት እንደሚቻለው መጀመሪያ ያመራነው ወደ ታንዛንያ ነበር:: እዚያ በተለይ የማስታውሳቸው ሁለት ነገሮች አሉ:: በሥልጣን መባለግ መጥፎ መሆኑን ወጣት አርቲስቶች ለአዋቂዎች ትምህርት ሲሰጡ አይቻለሁ:: ሌላው፣ ፐሬዚዳንት ጁሊየስ ኒሬሬ ለመሪያችን ክብር ባደረጉት የእራት ግብዣ ላይ ንግግር ሳይደረግ ቀርቷል:: በእንደዚህ ዓይነት የእራት ግብዣ የመሪዎች ንግግር የሚጠበቅ ነው:: መሪዎቹ የሚያደርጉትን ንግግር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቻቸው ረቂቁን ይለዋወጡና ያዩታል:: በውስጡ ሌላውን ወገን የሚያስቀይም ወይም የሚያስኮርፍ ነገር ካለበት ንግግሩ በስምምነት እንዲስተካከል ይደረጋል:: ግብዣ የሚደረገውና በሞቴ ካልበላኽልኝ ካልጠጣኽልኝ የሚባለው ወዳጅነትን ለማደርጀት ስለሆነ ተጋባዡን የሚያስቀይም ወይም የእራቱን መንፈስ የሚያበላሽ አከራካሪ ነጥብ በመሪዎች ግብዣ ላይ አይነሳም::

በዚያን ወቅት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ዶክተር ኮሎኔል ፈለቀ ገድለጊዮርጊስ ሲሆን የደርጉ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ደግሞ ብርሃኑ ባይህ ነበር:: ሊቀመንበር መንግሥቱ ሊያደርግ በተዘጋጀው ንግግር ውስጥ ቻይናን የሚወርፍ ነጥብ ነበረበት:: ቻይና የታንዛንያ ወዳጅ ናት:: ቻይናና ሶቭየት ዩኒየን ደግሞ ግንኙነታቸው በጣም የሻከረበት ወቅት ነበር:: ከሁለት ዓመት በፊት ቻይናን በጎበኘንበት ወቅት ቻይኒዞች ደጋግመው ያነሱልን ስለሶቪየቶች ከዳተኛነት ነበር:: ሶቪየቶች ቻይናን ለመርዳት የጀመሯቸውን በርካታ ፕሮጀክቶች ሳይጨርሱ ጥለውባቸው ስለሄዱ ቻይኒዞች በሶቪየቶች ላይ ከፍተኛ ቅሬታ እንዳላቸው ተረድተን ነበር::

በቻይና ቆይታችን ወቅት ዶክተር አሻግሬ ያደርጋቸው በነበሩት ንግግሮች ሶቪየት ዩኒየንን በአግቦ ሲወርፍ ከርሟል:: ይህም ቻይኒዞችን ለማስደሰት ታቅዶ የተደረገ ነበር:: ከሁለት ዓመት በኋላ ሁኔታው ተገልብጦ የፖለቲካ ዳንኪራ ከቻይኒዞች ጠላት ጋር ከሶቪየቶች ጋር እንዲሆን ሲወሰን ከትናንቱ

ወዳጃችን ጋር ደግሞ አፍ መካፈት ተመረጠ:: በፖለቲካ ሳይንቲስቶች አባባል አንድ አገር የሚያሳድዳቸው ብሔራዊ ጥቅሞች ቋሚ ሲሆኑ ወዳጆቹ ግን ከጊዜ ጋር ተለዋዋጭ ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ ማለት አንድ አገር ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ወዳጆቹን እንደሚጠጋና እንደሚወዳጅ፣ ጎጂ ናቸው ከሚላቸው ደግሞ እንደሚርቅ የሚጠበቅ ነው:: የማይጠበቀው ግን አንድ አገር የራሱን ጥቅም በሚጎዳ መልኩ የሌላ አገር ጥቅም ጠባቂ ወይም ጠበቃ ሆኖ መገኘት ነው:: በማያገባው ገብቶ ወይም በአጉል አድርባይነት ተገፋፍቶ የባዕድ አገር አፈ ቀላጤ ለመሆን ከተነሳ ይዋል ይደር እንጂ የራሱን ጥቅም መጉዳቱ የማይቀር ነው:: ሶቪየቶችና ቻይኒዞች ባላቸው ጥል አገራችን ጣልቃ ገብታ ቻይኒዞችን በይፋ ብትሳደብ ሶቪየቶችም ሆኑ ቻይኒዞች የዚህን አድርባይነት ወይም ወዶገባነት አራማጅ መንግሥት በልባቸው ሳይንቁትና ሳይታዘቡት የሚቀሩ አይመስለኝም::

የታንዛንያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለቻይና የጻፋችሁትን አውጡት ብለው የኛን ሰዎች ይጠይቃሉ:: የኛዎቹ ካልተሳደብን ሞተን እንገኛለን ይላሉ:: ቤታችን ድረስ መጥታችሁ፣ የኛ እንግዶች ሆናችሁ፣ ምግባችንን እየበላችሁ፣ መጠጣችንን እየጠጣችሁ እንዴት አለን የምንለውን ወዳጃችንን ለመሳደብ ወይም ለመውረፍ ትደፍራላችሁ? ዓለም በተቀበለው የፕሮቶኮል ደንብም ቢሆን በእራት ግብዣ ላይ አጨቃጫቂ ነጥብ መነሳት ስለሌለበት ብታወጡት ይሻላል ይላሉ:: የኛዎቹ ምንችክ አሉ:: እንግዲያውስ ንግግር ማድረጉ ይቅር ተባባሉና ተስማሙ:: ቻይናን ለመስደብ ለምን እንደፈለጉ በግልጽ ባይነገረንም አላማው ሶቪየቶች ጉያ ጭልጥ ብለን መግባታችንን ዓለም እንዲያውቅልን የታቀደ መሆን አለበት ብለን ደመደምን::

አብዛኛዎቻችን ንግግሩ በመቅረቱ ተደሰትን እንጂ አልተከፋንም፤ ምክንያቱም እራት ላይ የሚደረግ ንግግር እራት ከመጀመሩ በፊት ከሆነ የተጋባዡ አትኩሮት የተራበ ሆድ መሙላት ላይ ስለሆነ ተናጋሪውን በልቡ ይረግማል፤ ንግግሩ የሚደረገው ከእራት በኋላ ከሆነ ደግሞ ሆድ በምግብ ከተነረተና ጭንቅላት በአልኮል ከነበዘ በኋላ ከእንቅልፍ ጋር ግብ ግብ

ስለሚያዝ አሽልቦኝ የታየሁ እንደሆነ ሞቴ ነው እያለ ተጋባዥ ይሳቀቃል:: ሊቀመንበር መንግሥቱና ፕሬዚዳንት ኒሬሬ ኦፊሴል ንግግር ማድረግ ሳያስፈልጋቸው ከመቀመጫቸው ተነስተው አንድና ሁለት ቃላት ተወራውረው ለጤናችን ተባብለው ብርጭቆአቸውን አቃጭለው ሻምፓኝ ተጎንጭተው ሲቀመጡ በቃላት ጋጋታ ጤና ስላልነሳችሁን ጤና ይስጣችሁ አልናቸው፣ በልባችን:: ደስታችንን ለመግለጽ በጣም አጨበጨብንላቸው::

ስለናይጄሪያ ጉብኝት በተለይ የማስታውሰው ሊቀመንበራችን ላደረገው ንግግር ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ የሰጠው መልስ ነው:: ሊቀመንበር መንግሥቱ የኢትዮጵያ አብዮት ስላፈራረሳቸው አድኀሪ ተቋማትና ስላጠፋቸው ኋላቀር ባሕሎች ሰፊ ገለጻ አደረገ:: ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ በሰጠው መልስ ሥርዓታችንና ባሕላችን ለኛ ተስማሚ ሆነው ስላገኘናቸው የምንለውጠው ነገር አይኖርም አለ:: ይህን አባባል አብዮታችሁን አልወደድንላችሁም እንዳለ አድርገን ወሰድነው:: እንዲሁም በቼኮዝሎቫኪያው ጉብኝት ወቅት ሊቀመንበር መንግሥቱ ስለማፈራረስ ብዙ ተናግሮ ስለነበር የአገሩ ፕሬዚዳንት ሲመልሱ "የኛ ልምድ የተለየ ነው፤ የነበረንን አሻሽለን ገነባነው እንጂ ያፈራረስነው ነገር አልነበረም" ብለው ተናገሩ:: እርግጥ የሁለቱ አገሮች ታሪክና ችግር ብሎም መፍትሔው ለየቅሉ ቢሆንም ፕሬዚዳንቱ ለሊቀመንበራችን በተዘዋዋሪም ቢሆን የነገሩት ወይም የመከሩት ብዙ ማፈራረስ ብዙ ጠላት እንደሚያስነሳና ተመልሶም ለግንባታ ጸር እንደሚሆን ነበር:: በአብዮት መንፈስ የሰከረ ጭንቅላት እንዲህ ዓይነቱን ጥልቀት ያለው ምክር ያድኀሪ ወይም የበራዥ ከላሽ አመለካከት ነው ብሎ ያልፈው ነበር እንጂ፣ ኀበዝ፣ ቅድም ሰውዬው ስለተናገሩት ምን ሐሳብ አላችሁ? እስኪ እንወያይበት አይባልም ነበር::

ጎርባቾቭ በሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ለጉብኝት ሞስኮ ሄዶ ጎርባቾቭ እንደ ሶቪየት ዩንየን ሁሉ በኢትዮጵያም በየአቅጣጫው ለውጥ ስለማስፈለጉ ሰፊ ገለጻ ያደርጋል ወይም ትምህርት ይሰጣል:: መንግሥቱ ሰውዬው የሚለው ስላልጣመው አንገቱን ዞር

አድርጎ፣ ይሄ ቀልባሽ ከላሽ ብሎ ያልጎመጉማል፡፡ ምንድነው የሚለው? ብሎ ጎርባቾብ አማርኛ የሚያውቀውን ተርጓሚው ሽራዬቭን ይጠይቀዋል፡፡ ሽራዬቭ በበኩሉ አይ፣ ምንም አይደለም፣ ወይም በቅጡ አልሰማሁም ብሎ ነገሩን አድበስብሶ እንደማለፍ ፍርጥርጥ አድርጎ ቀልባሽ በራሹ ይልዎታል አለው፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ጎርባቾብ የመንግሥቱን ዐይን አታሳዩኝ አለ ይባላል፡፡

በአገራችን ለውጥ ለውጥ መባል ከጀመረ ቆይቶ ነበር፤ ነገር ግን የኛ ሰዎች እራሳቸውን ከጳጳሱ የበለጡ ቄሶች አድርገው ስላስቀመጡ ጊዜና ታሪክ ተረማምዶ ጥሏቸው ነጎደ፡፡ ሽራዬቭ የሠራውን ስሰማ እኔ አራተኛ ወይም ሦስተኛ ክፍል ሆኜ መምህር ጀምበሬ ተሰማ ለጠየቀኝ ጥያቄ አማረ ይልማን አሳልፌ የሰጠሁትን አስታወሰኝ፡፡ ልዩነቱ የኔ ባለማወቅ የተፈጸመ ሲሆን ሽራዬቭ ግን ሆን ብሎ መንግሥቱን ከጎርባቾቭ ለማቆራረጥ ያደረገው ሸር ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በናይጄሪያ ቆይታችን ዕይታችንን የማረከው ጉቦ መብላት አሳፋሪ መሆኑን የሚያሳስብ ጽሑፍ በየቢሮው በራፍ መለጠፍ ነበር፡፡ በናይጄሪያ ያለአግባብ መበልጸግ አብዛኛውን ባለሥልጣን የተጸናወተና ስር የሰደደ በሽታ ነው ስለሚባል ማ ማንን መከረ? ወይም አስጠነቀቀ? የሚለው ቀላል መልስ ያለው አይመስልም፡፡ የማሳሰቢያው ጋጋታ የሚያመለክተው ጸሓፊውም ይጻፍ ጉቦ በላተኛውም ይብላ ተባብለው አገርአቀፍ ስምምነት ያወጁ ያስመስልባቸዋል፡፡ ፕሬዚዳንት ኦባሳንጆ በናይጄሪያ ለውጥ አያስፈልግም ሲል የተጠቀሰውንም ስምምነት ሳይጨምር አይቀርም፡፡

ገሰሰ ወልደኪዳን የብሔራዊ ኤኮኖሚ ዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ሆኖ አንድ ቀን ይጠራኝና ቢሮው እሄዳለሁ፡፡ ስማ ታደሰ፣ አንድ የኦሮምኛ ተረት ልንገርህ ይለኛል፡፡ እንቁራሪቶቹ እንዳይሞቱ ኩሬውም እንዳይደርቅ ይባላል አለኝ፡፡ ከፖሊሲና ከደንብ ውጭ የሚመጡ ጥያቄዎችን አናስተናግድም፣ መንገድ አንለቅም እል ስለነበር መንግሥታዊና የግል ድርጅቶች ባንክ ጠነከረብን እያሉ በየጊዜው ስሞታ ስለሚያቀርቡ ስለጉዳዩ እንድንወያይ ነበር ገሰሰ

የጠራኝ። በወቅቱ የነበረኝ ተግባራዊ ምላሽ፣ ለተረት ጊዜ የለኝም፤ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ለማስጠበቅ እየተጣደፍኩ ነኝ የሚል ነበር። የምንኖርባት ዓለም በቀይና ብጫ ወይም ነጭና ጥቁር ብቻ ሳይሆን በብዙ ቀለማት ያሸበረቀች ናት፤ እውነት አንደተርጓሚው ነው፤ የሰው ልጅ ፍላጎቱና አመለካከቱ እንደፊቱ ውጥንቅጠጥ ስለሆነ ዓላማችን መሆን ያለበት የአብዛኛውን ፍላጎት ለማርካት እንጂ የዓላማ ጽናት ወይም ሞት እያልን መንገታገት መሆን የለበትም፣ ያለበለዚያ ብዙ ጠላት እናፈራለን፤ ያንዱ ሽምቀቆ ማጥበቅ የሌላውን መታነቅ ያስከትላል ብሎ አዝማች ገሰሰ ትምህርት ሊያስተምረኝ ፈልጎ እንደነበር የተረዳሁት ከዕድሜ መግፋትና ልምድ ሽመታ በኋላ ነበር። በዚያን ዘመን ቆም ብሎ አለማሰብ አብዛኛውን የተጸናወተ በሽታ ነበር፤ መራመድ፣ መፍጠን ነው፤ እንቅልፍና እረፍት የለም፤ ጥድፊያው የተዋረደችውን ኢትዮጵያ ክብሯን ለማስመለስና ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለማስቀመጥ ነበር። የሕልም ጉዞ። ሁሉም ነገር በነበር አለቀ።

በሕዝብ ስም አደራ የተቀበለ የመንግሥት ባለሥልጣን ዋና ሥራው የተለያየና ተጻራሪ ፍላጎት ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ማስማማትና ወደ ቀና ጎዳና መምራት መሆኑን አሁን የበለጠ ግንዛቤ አግኝቻለሁ። አንድ የሕዝብ ተወካይ የራሱን ጥቅም ለማካበት ወይም ዘመድ አዝማዱን ለመጥቀም አቅዶ እስካልሆነ ድረስ አቻችሎ ወይም ተቻችሎ ለመኖር የሚያደርጋቸውን ጥረቶች መደገፍ አግባብ ነው። ዴሞክራሲ የሚገነባውም በዚህ ጽንሰ ሐሳብ ላይ ነው። አማራጩ የኅብረተሰብ ችግሮች ምን እንደሆኑ አውቄአለሁ፣ መፍትሔዎቻቸውንም ደርሼባቸዋለሁና ነገሩን ሁሉ ለኔ ተዉት የሚል አምባገነን ማንገሥ ነው። የዚህ ስልት ውጤት አያምሬነት ወይም አስከፊነት በየአገሩ፣ በአገራችንም ጭምር፣ ተደጋግሞ የታየ ስለሆነ፣ የፖለቲካ አዋቂዎች መቼም የሚለውን ቃል መቼም አትጠቀሙ ቢሉም፣ መቼም የምንመለስበት አይመስለኝም።

ከናይጄሪያ ወደ ሞስኮ የበረርነው በሳይፕረስ በኩል ነበር። ምዕራብ አፍሪቃን ያቋረጥነው በማታ ሲሆን ዐይተነው በማናውቀው ከፍተኛ

የመብረቅ ብልጭታ መካከል እያለፍን ነበር። ሞስኮ ከደረስን በኋላ ከፓይለቱ የተረዳነው አውሮፕላኑን መብረቅ ስምንት ጊዜ መትቶት እንደነበር ነው። ታዲያ የወሬ ነጋሪ ለመሆን እንዴት ተረፍን? ብለን ብንጠይቀው አውሮፕላኑ የመብረቅ መከላከያ እንዳለው ነገረን። ከኤኮኖሚ ዘመቻ መታወጅ ጋር ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን የሚለው መፈክር ሲወጣ ደርግን የኢትዮጵያ ሕዝብ አበስኩ ገበርኩ ምን ዓይነቱን ጭራቅ ነው የላከብን? አሁንስ እግዚአብሔርን ሊመቱ ተዘጋጅተዋል ብሏል። መብረቅ በቁጥጥር ሥር ስለመዋሉ ደርግ ሕዝብን ቢያስተምር ኖሮ ጭራቅ መባሉ ተሻሽሎለት አጋንንት ጎታች ይባል ነበር።

ሞስኮ አየር ማረፊያ ስንደርስ ፕሬዚዳንት ብሬዥኔቭና የሥራ ባልደረቦቻቸው ከፍተኛ አቀባበል አደረጉልን። መንግሥቱና የቅርብ የሥራ ባልደረቦቹ በክሬምሊን ቤተመንግሥት ሲያርፉ ሌሎቻችን ወደ ሆቴል ተወሰድን። በማግስቱ ጠዋት ሁለቱ መሪዎች በክሬምሊን የመክፈቻ ንግግር ተለዋወጡ። መንግሥቱ ስለኢትዮጵያ አብዮት ሲገልጽ እዚህም ያተኮረው እማፈራረሱ ላይ ነበር። አቀራረቡ ዋጋ ወይም ቦታ ያገኘው የዚያን ዕለት ነው። መንግሥታችን አድኀሪ ሥርዓቶችንና ተቋማትን አፈራርሶ ለሶሻሊዝም ግንባታ ስለተዘጋጀ ሶሻሊስት አገሮች ድረሱልን ተብለው ሶቪየቶች ተጠየቁ።

ስለዚያን ዕለት ስብሰባ ሳስታውስ ካሳ ገብሬ እፊቴ ድቅን ይላል። የሁለቱ መሪዎች ንግግር እስኪጀምር ጋዜጠኞችና የመንግሥት ሰነድ አጠናቃሪዎች ፎቶግራፍ እያነሱ እያለ መንግሥቱ በወረቀት ላይ አንዲት ነገር ሲጭር እናያለን። ምን ይሆን? ብለን አትኩሮታችን ከፎቶግራፍ አንሺዎችና ውብ ድንቅ የሆነውን አዳራሽ በዐይን ከመቃኘት ወደ ጸፊው መንግሥቱ ዞረ። ወረቀቱን አጠገቡ ለነበረው፣ ለብርሃኑ ባይህ ይመስለኛል፣ ይሰጠውና ለካሳ አስተላልፍ ይለዋል። ካሳ ወረቀቱን አንብቦ ኪሱ ውስጥ ከከተተው በኋላ አንገቱን አቅንቶ፣ የሰማይ ስባሪ ወደሚያክለው ሰፊ ጠረጴዛ ተጠግቶ እጆቹን ደረቶቹ ላይ አጣጥፎ በወንበሩ ላይ በደንብ ተቆናጥጦ ተቀመጠ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ሁሉም ያያል፣ ብሬዥኔቭ ጭምር። ሁላችንም ስለ ወረቀቱ ምስጢር ለማወቅ ቸኩለናል። ስብሰባው እንዳበቃ ካሳን ከበን ካልነገርከን አንለቅህም አልነው። እየሣቀ፣ ሰውዬው ጉድ አደረጉኝ እኮ፣ ካገሬ ጭነው አምጥተው፣ ብሬዥኔቭን ምስክር አድርገው «ካሳ፣ እንዳትተኛ» የሚል መመሪያ ነው የሰጡኝ ብሎ ነገረን። ካሳ በስብሰባ ላይ እንቅልፍ ወይም ሽልብታ ይዞት እንደሚነጉድ የማያውቅ የለም። ካሳ እንደሚለው ከሆነ ግን ዐይኑን የሚጨፍነው ነገር በአእምሮው ሲያፍተለትል ዐይኑ ጣልቃ ገብቶ የአእምሮውን ኤፊሸንሲ ወይም ውጤታማነት እንዳይቀንስበት ሆን ብሎ የሚጠቀምበት ፍቱን ዘዴ ነው። በማስረጃነት የሚያቀርበው እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወስዶታል ስንል አጅሬ በኃይለኛ ክርክር መካከል ድንገት ይነቃና ውይይቱን አስመልክቶ አስተያየትና ሐሳብ መስጠት ይጀምራል።

በሶቪየት ቆይታ ወቅት የተሠራው ዋና ሥራ የወዳጅነት ውል ወይም ትሪቲ መፈራረም ነበር። ውሉ በየመስኩ የሚደረገውን ትብብር ዓይነትና የሁለቱ ወገኖች መብትና ግዴታ የሚዘረዝር፣ ወደፊት ለሚደረጉ ትብብሮች መሠረት የሚጥል፣ ገደብ የሚያበጅና አቅጣጫ የሚያስይዝ ሰነድ ነው። ላይ ላዩን ሲታይ ውሉ የሁለቱንም ወገኖች ጥቅም የሚያስጠብቅ ይምሰል እንጂ በመሠረቱ ኢትዮጵያን የሶቭየት ዩኒየን ጥገኛ የሚያደርግ ነበር ማለት ይቻላል። በኢትዮጵያ በኩል የነበረው አስተሳሰብ ሶቪየት ዩኒየን ውሉን በመፈረም የኢትዮጵያ አንድነት ለማስጠበቅና ኤኮኖሚዋን ለመገንባት ቃል ገብታልናለች ነው። የሶማልያን ወረራ መክቶ ለመመለስ በተለይ የሶቪየት ኅብረት ያደረገችው የመሣሪያና የምክር አስተዋጽኦ በቀላሉ የማይታይና ኢትዮጵያን ከውርደት ያወጣ በመሆኑ ከነሱ ጋር የወዳጅነት ውል መፈራረም ልክ አይደለም ብሎ መከራከር በወቅቱ የሚደፍር አልነበረም።

ፕሬዚዳንት ካርተር በኢትዮጵያ ላይ የመሣሪያ ሽያጭ እገዳ ባያደርግና አገራችን ፊቷን ወደ ሶቭየት ዩኒየን እንድታዞር ባትገደድ ኖሮ የኢትዮጵያ ታሪክ የተለየ ይሆን እንደነበር ለመገመት ልዩ እውቀት አይጠይቅም።

አሁን ቁም ነገሩ ያለፈው አልፏል፣ ላለፈ ክረምት ቤት አይሠራምና ለወደፊቱ ምን እናድርግ በሚለው ላይ ነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ማተኮር ያለበት።

በሞስኮ በነበርንበት ወቅት ዋናውን ባንካቸውን እንድጎበኝ ወሰዱኝ። ብሬዥኔብ መንግሥቱን በከፍተኛ ክብር እንደተቀበለው ሁሉ፣ አንባቢ ወዴት ከፍ ከፍ አይበለኝና፣ እኔም ዋናው ባንካቸው ስሄድ የተደረገልኝ አቀባበል ተመሳሳይ ነበር ለማለት ይቻላል። የተሳፈርኩበት ተሽከርካሪ ባንኩ በራፍ ሲደርስ አስተናጋጆች ውጭ ቆመው መምጣቴን ሲጠባበቁ አገኘሁ። ውስጥ ስገባ በየደረጃው ተቀባይ ተመድቦልኝ ነበር። በመጨረሻም የባንኩ ዋና እንግዳ መቀበያ ስገባ የባንኩ ፕሬዚዳንት፣ ማለትም የአገሩ ባንኮች ሁሉ የበላይ፣ ምክትሎቻቸውንና የመምሪያ ኃላፊዎቻቸውን ይዘው በሰልፍ ተቀበሉኝ። የተሸኘሁትም በከፍተኛ ሥነሥርዓትና ከከፍተኛ የወዳጅነት ስሜት ጋር ነበር።

በባንኩ አዛዥነት በመስከረም 1971 ተመድቤ በመጋቢት 1979 ወደ ውጭ ንግድ እስክዛወር ድረስ ወደ ሞስኮ ብዙ ጊዜ ተመላልሻለሁ። በሄድኩ ቁጥር ይደረግልኝ የነበረው አቀባበል ባለማቋረጥ እየቀነሰ መጥቶ በመጨረሻው ጉዞዬ ሆቴል ክፍል እንዳልገባ ተከልክዬ እንግዳ ማረፊያ ወንበር ላይ ተኮማትሬ ከአራት ሰዓት በላይ ተቀምጫለሁ። የሆነው ምንድነው? አየር ማረፊያ ጣቢያ የተቀበሉኝ የፕሮቶኮል ሰዎቻቸው የኢሚግሬሽን ፎርማሊቲ እንደኔ ሆነው ለማሟላት ፓስፖርቴን ይቀበሉኛል። ይህ የተለመደ አሠራር ነው። ሆቴል ስንደርስ ፓስፖርትህን እንሰጠው ይሉኛል። ለሰዎቻችሁ እንደተለመደው አስረክቤአለሁ እላቸዋለሁ። እንደ ሌላ ጊዜ አሠራር ቢሆን ኖሮ በሆቴል በኩል ያለውን ጣጣ የሚጨርሱት እነዚያው የፕሮቶኮል ሰዎቻቸው መሆን ነበረባቸው። ከአየር ማረፊያ አጅቦኝ የመጣው የፕሮቶኮል ሠራተኛ ፓስፖርቱን አየር ማረፊያ ትተነው መጥተናል ይለኛል። እሺ ሄዳችሁ አምጡት፤ እኔ ደክሞኛልና ወደተያዘልኝ ክፍል ገብቼ ልረፍ እላቸዋለሁ። ሆቴሉ ፓስፖርትህን ካላየሁ አልፈቅድም ይላል።

እሺ ምን ይሁን? ብላቸው አናውቅልህም ይሉኛል። አራት ሰዓት ካንገላቱኝ በኋላ ፓስፖርትህ አሁን መጥቷልና ክፍል መያዝ ትችላለህ ተባልኩ። ይመደቡልኝ የነበሩት ተሽከርካሪዎች እንደዚሁ ደረጃቸው በተመሳሳይ እየወረደ መጥቶ በመጨረሻው ጉብኝቴ የተመደበችልኝ መንኮራኩር ከሶማሌ ተራ ብልት አውጭዎች ዕይታ ያመለጠች ትመስል ነበር።

የአቀባበላቸው መዳከም የብሔራዊ ባንክ ከሶቪየት መንግሥት ጋር ከነበረው ግንኙነት የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም። ወዳጆቻችሁ ስለሆን የምናቀርባቸውን ጥያቄዎች ያለጥያቄ ማስተናገድ አለባችሁ የሚል አመለካከት ነበራቸው። እኛ ደግሞ ማናቸውም ጥያቄ ሆነ ውል የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብን እንላቸው ነበር። ለምሳሌ፣ ነዳጅን አስመልክቶ የነበረንን ግንኙነት እንመልከት። ለአሰብ ነዳጅ ማጣርያ የነዳጅ ድፍድፍ አቅራቢዎች እነሱ ናቸው። ድፍድፍ የሚደርሰን ብዙ ጊዜ እየጎደለ ስለነበር ለጎደለው አንከፍልም እያልናቸው ብዙ ጭቅጭቅ ነበር። በአገራችን ነዳጅ ፍለጋ የሚያካሂዱት እነሱ ነበሩ። ለፍለጋ ያስፈልጋሉ የሚሏቸውን መሣሪያዎች ከእነሱ በብድር እንገዛለን። ለነዳጅ ፍለጋ በውጭ ብድር የሚያካሄድ ሌላ የለየለት ድሃ አገር ስለመኖሩ ሰምቼም አላውቅም። እሺ፣ ነዳጁ መቼ ነው የሚወጣው? ተብለው ሲጠየቁ መልሳቸው እየፈለግን ነው፣ ትንሽ ቀርቶታል የሚል ነው። ሥራውን ለማጣደፍ ተጨማሪ ብድር እንዲፈረም ይወተውታሉ። በባንክ በኩል የነበረን አቋም እነሱ ለኛ ነዳጅ በውጭ ምንዛሪ አቅራቢ ሆነው፣ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ የነዳጅ አምራችና ገበያ ፈላጊ ሆነው፣ ነዳጅ ብናገኝ ከኛ የሚያገኙት ጥቅም እንደሚቀርባቸው እያወቁ ነዳጅ ያገኙልናል ብለን እንዴት ልናምናቸው እንችላለን? የሚል ነበር።

የአገራቸውን ምርቶች በኢትዮጵያ አስገብተው መሸቀጥ ለሚፈልጉ የንግድ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ ካልሰጣችሁ እያሉ ይጨቀጭቁን ነበር። አይሆንም ስንላቸው ፓርቲው ጽሕፈት ቤት እየሄዱ ባንክ ያስቀመጣችኋቸው አድኀሪዎች ግንኙነታችንን ለማበላሸት አስበው

*ያስቸግሩናል እያሉ ስሞታ ያቀርባሉ። የብድርና ክፍያ ድርድር የአገራችንን ጥቅም የሚጎዳ መሆን የለበትም እያልን ስንከራከራቸው ባመቻቸው መንገድ ተጽዕኖ ለማምጣት ይሞክራሉ። ባንድ ወቅት አቶ አጥናፉ መንግሥቱ፣ የውጭ ባንኮች ግንኙነት መምሪያ ኃላፊያችን፣ ከነሱ ጋር ውል ሲደራደር ይጠነክርባቸዋል። ለማባበልና ለማስፈራራት ቢሞክሩም አጥናፉ የማይበገር ይሆንባቸዋል። ኤምባሲያቸው ተመልሰው ሁኔታውን ያስረዳሉ። አቶ አጥናፉን የሚያስፈራራ ሰው ለመላክ ይወስናሉ። መልዕክተኛው ስሜ ኮሎኔል እገሌ ይባላል ብሎ እራሱን ካስተዋወቀ በኋላ አቶ አጥናፉን አንተ አቀባባይ ከበርቴ ነህ ይለዋል፤ ቆንጆ ቤት እንዳለውና ኑሮው የተደላደለ መሆኑን እንደሚያውቅ ይነግረዋል። ወቅቱ አድኀሪው ቢሮክራሲ ይወድማል የሚባልበት ስለነበር በኮሎኔል ነኝ ባዩ አቀራረብ አቶ አጥናፉ ተደናግጦ፣ ማሩኝ ብሎ የተጠየቀውን ይለቃል በሚል እምነት ላይ የተመሠረተ ነበር። ሰውዬው ኮሎኔል መሆኑን የገለጸው የኬ ጂ ቢ አባል ነኝና በሕይወትህም ቢሆን ልመጣብህ እችላለሁ ለማለት ፈልጎ ሳይሆን አይቀርም። ድርድሩ በሚፈልጉት ዓይነት ካልተደመደመ ችግራቸውን ለሁለቱ አገሮች ፓርቲዎች ማሳወቅ እንደሚገደዱ ያስፈራራል። ጉዳዩ ከውል ድርድር ወደ ብሔራዊ ክብር ማስጠበቅ ተሸጋግሯል ማለት ነው፤ ይሄ ነጫጭባ እንዴት ኢትዮጵያዊነቴን ሊፈታተን ቤቴ ድረስ እንኳኩቶ ይመጣል? ይልና ሲቪሉ አጥንሽ ኮሎኔሉ ላይ አፈጠጠበት፤ ማን ይፈራሃል? የፈለግህበት መሄድ ትችላለህ ብሎ አሰናበተው። የሆነውን፣ ሰውዬው የተናገረውን መጥቶ ነገረኝ። በያዝከው መንገድ ቀጥልበት፣ ጥያቄ ቢነሳ ኃላፊ እኔ ነኝ አልኩትና የልብ ልብ ሰጠሁት። ቢወጡ ቢወርዱ ምንም ማድረግ ስላልቻሉ የውሉ ድርድር እኛ በፈለግነው ዓይነት ተደመደመ።*

*ሶቪየቶቹ ያሰቡትን ለማስፈጸም ችግር ሲገጥማቸው አንድ ይከተሉት የነበረው ስልት ጉዳዩን ለጊዜው ያስተኙትና አገራችን ችግር ውስጥ ገብታ የነሱን እርዳታ ማስፈለጉን ሲያረጋግጡ እንደገና አንጠልጥለውት ብቅ ብለው ጥያቄያችንን ካላስተናገዳችሁ ምንም አናደርግላችሁም ይሉ ነበር።*

የሚከተለውን ታሪክ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቀው ይገባል፡፡ ከአስገንጣዮችና ተገንጣዮች ጋር ከፍተኛ ትንቅንቅ እየተካሄደ የጦር መሣሪያ መለዋወጫ እቃዎች እጥረት ያጋጥማል፡፡ ሶቪየቶች እቃዎቹን ስጡን ቢባሉ ክፍያው በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋስትና ካልተደገፈ በቀር አናቀርብም ይላሉ፡፡ ይሄ ጥያቄያቸው አዲስ ሳይሆን የከረመ ነበር፡፡ ብሔራዊ ባንክ እንዲህ ዓይነቱን ዋስትና አይሰጥም፤ የገንዘብ ሚኒስቴር በመንግሥት ስም የሰጣችሁ ዋስትና በቂ ነው እያልን ጥያቄውን ለረጅም ጊዜ ውድቅ ስናደርገው ቆይተን ነበር፡፡

በእኛ በኩል የነበረው ፍራቻ ዋስትናውን ብሔራዊ ባንክ ከሰጠ የባንኩ የውጭ ምንዛሪ፣ ይኸውም የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ማለት ነው፣ በውጭ አገር ፍርድ ቤት የመታገድ አደጋ ይደርስበታል የሚል ነበር፡፡ የክፍያ ዋስትና ለሶቪየቶች ከሰጠን ሌላው እቃ አቅራቢ ሁሉ የማይጠይቅበት ምንም ምክንያት ስለማይኖር የአገሪቱ ውጭ ምንዛሪ ገቢ ከቁጥጥራችን ውጭ ሊሆን ይችላል የሚል ትልቅ ስጋት ነበረን፡፡ እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ብሔራዊ ባንክ ዋስትና ከሰጠ ዋስትናው የሚመለከተው የውጭ ምንዛሪን ብቻ ሳይሆን የአገር ውስጥ ገንዘብ አቅርቦትንም ነው፡፡ ስለሆነም ባንኩ ለጣምራ አደጋ ወይም ጥቃት ሊዳረግ ይችላል ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ዋስትና የተሰጠለት የአገር ውስጥ ተበዳሪ ቢከስር ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የገንዘብ እጥረት ቢያጋጥመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተበዳሪው እግር ተተክቶ እንዲከፍል ይገደዳል ማለት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ ባንኩ ገንዘቡን ወደውጭ ምንዛሪ ቀይሮ ወደ ውጭ የማስተላለፍ ኃላፊነት አለበት ማለት ነው፡፡ ለዚህ ነበር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋስትና መጠየቅ የለበትም የምንለው፡፡

የሶቪየቶች ድርጊት ሲገመገም ከቅርብ ወዳጅ የሚጠበቅ አልነበረም ብሎ ነገሩን ማለፍ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለውጭ ግንኙነትና ሰርቫይቫል በትክክል ሊረዳው ወይም ሊገነዘበው የሚገባ ትልቅ ቁም ነገር

አለ:: ወዳጅ መስሎ የሚቀርብን ፈረንጅ ወይም ብጫ ሕዝብ ሁሉ የራሱን ብሔራዊ ጥቅም ሊያስጠብቅ፣ ሊያካብት ወይም ሊያጋብስ አቅዶ ነው:: በተለይ ፈረንጆች ስለወዳጅነት ያላቸው አመለካከት ኢትዮጵያውያን ከምናውቀውና ከምናምንበት የተለየ ነው:: ፈረንጆች ነገሮችን የሚያዩት በሚያስገኝላቸው ጥቅም ወይም በሚያስከትልባቸው ጉዳት አንጻር ነው:: ስለሆነም ጥቅም የማያስገኝላቸው ወይም ጉዳት የማያስከትልባቸው አገር በስሌታቸው ውስጥ ቦታ የለውም:: ግሎባላይዜሽን ጥሩ ነው ሲሉ ሌሎች አገሮችን እንዴት አድርገን እንቦጥቡጥ፣ በቁጥጥራችን ሥር እናድርግ፣ ሌሎች አገሮች ሊያስከትሉብን የሚችሉትን ጉዳቶች እንዴት እንመክት? ማለታቸው ነው:: የሰው ልጅ ሁሉ በአንድ አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ፣ እጣው የተቆራኘ ነውና እንረዳዳ ማለት አይደለም:: በእነሱ አመለካከት ጥቅም የማይሰጥ ነገር ሁሉ ቦታ የለውም:: የዳርዊንን የሥነፍጥረት መላምት ተከትለው ደካማው በኃይለኛው መዋጡ የማይቀር ነው ብለው ያምናሉ:: እያንዳንዱ ፍጡር እንዳይጠፋ አስፈላጊ የመከላከያ ስልት አዘጋጅቶ ማንገብ የራሱ ኃላፊነት ነው:: በዐይን የማይታዩ በእጅ የማይዳሰሱ ሕዋሳት ሳይቀሩ ከመጥፋት ለመዳን ሲሉ ላንዲት አፍታ እንኳ ዘዴ ከማውጠንጠን አያርፉም:: ለምሳሌ፣ ወባ እንደገና የሚያንሰራራው በሽታውን ተሸካሚ ትንኝ እንዲያጠፋው የተረጨበትን መርዝ ትንኙ የመቋቋሚያ ዘዴ ፈልጎ ማግኘት በመቻሉ ነው:: ሰውም ለራሱ ካላወቀበት ሕይወቱ ዋስትና የለውም:: እራስን ለመደለል ወይም ለማጽናናት ካልሆነ በቀር ሌላ ምድራዊ ወይም መለኮታዊ ኃይል ሊደርስለት አይችልም:: ለህልውናው ተጠያቂው እራሱ ነው:: ተስፋ ቆርጦ፣ የዚህም ዓለም ነገር ትቶ በላይኛው ቤት ሕይወቴ ተደላድላ እኖራለሁ ማለት ሕይወት የጣለችብንን ግዴታ አለመወጣት ብቻ ሳይሆን ፍጹም የዋህነት ነው:: ወደድንም ጠላን ይህች ያለንባት ዓለም የብላ ተባላ መድረክ ናት:: የሰው ልጅ ከማይዳሰሱ ሕዋሳት አንሶ ተሸንፌአለሁ ብሎ እጁን ቢሰጥ እግዚአብሔር እጁን ታጥቦ በጥበቡ የሠራውን ትልቁን ፍጡር ከመርገም ተለይቶ የሚታይ አይሆንም:: ስለዚህ፣ የአገሬ ሰው፣ በሰውና ተፈጥሮ

ትብብር ጉድጓድህ የተማሰው፣ ለችግሮችህ መፍትሔ ለመፈለግ ተጨማሪ ጊዜ ሳታጠፋ በኅብረት ተነሳ።

ሁሉም አገር ብሔራዊ ጥቅሙን ለማካበት ይሯሯጣል ብለናል። ይህ ሶሻሊስት ካፒታሊስት ሳይባል ሁሉንም ጎራ ይመለከታል። ከሰባት ዓመት በፊት ይመስለኛል ዋሺንግተንና አካባቢው የሚኖሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያን አዲስ አበባ እንዲሄድ የተሾመውን አዲስ የአሜሪካ አምባሳደር ቀጠሮ ጠይቀው ያነጋግራሉ። ስለኢትዮጵያ ታሪክ፣ የወያኔ ከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ አደገኛነትና ኢትዮጵያን ስለሚጠብቃት የመገነጣጠል ወይም መፈራረስ እጣ ልባቸው ውልቅ እስኪል ይገልጹታል። ሌላም ሌላ። ሰውዬው በአንክሮ ከሰማቸው በኋላ እንዲህ ይላቸዋል። አንድ ያልተረዳችሁት ጉዳይ አለ፤ እኔ እኮ የአሜሪካ አምባሳደር ነኝ እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንባ ወይም ጥቅም ጠባቂ አይደለሁም፤ እያንዳንዱን አገር የመጠበቅ ኃላፊነት የተጣለው በዜጎቹ ላይ ነው፤ እኔ ኢትዮጵያ ስሄድ እንድከታተል መንግሥቴ የሚልከኝ የአሜሪካን ጥቅም እንዳስጠብቅና በአሜሪካ ላይ ሊመጣ የሚችለውን ጉዳት ወይም ጥቃት እንድከላከል ነው አላቸው። ሰዎቻችን ጉድ አሉ። እውነት መራራ ናት፤ ሲቀምሷት ታንገሸግሻለች። ተደጋግሞ እንደተባለው ኢትዮጵያ ከልጆቿ የበለጠ ሊያውቅላት የሚችል አይኖርም።

ሶቪየቶች ኢትዮጵያ ከማትወጣው ችግር ውስጥ መግባቷን ሲያረጋግጡ የብሔራዊ ባንክ ዋስትና ጥያቄያቸውን መዘው አውጥተው ፍስሐ ደስታ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጠው ዋስትናውን ወይም የተገንጣይን ዱላ ምረጡ አሉት። ቢያገላብጧቸው፣ ምን ቢሏቸው፣ ቢወጣ፣ ቢወረድ ሞተን እንገኛለን አሉ። ምን ማድረግ እንችላለን? አገራችንን ዐይናችን እያየ አስቆርጠን አንሰጥም፣ ዋስትናው ይሰጣቸው ተባለ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከሶቪየት ኅብረት ለተደረጉ የመለዋወጫና ሌሎች ግዢዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዋስትና ሰጥቷል። የፈረምኳቸው ዋስትናዎች ብዙ ናቸው። ፊርማዬን ባሰፈርኩ ቁጥር ገንዘቡ አይዋጥላችሁ ወይም በጉሮሮአችሁ

ይሰንቀር እያልኩ በልቤ እረግማቸው ነበር፡፡ በተዘዋዋሪም ስሜታችንን እንዲያውቁት ለማድረግ በዓል አስታከው በየባለሥልጣኑ ቢሮ እያዞሩ የሚያድሉትን ያገራቸውን መጠጦች እኔ ቢሮ እንዳያመጡ ትእዛዝ ሰጠሁ፡፡

አንድ በጣም ያናድደኝ የነበረው ደግሞ የሚገዙት እቃዎች ዋጋቸው ተገቢ ስለመሆኑ የማወቂያ ምንም መንገድ አለመኖር ነበር፡፡ እግዚአብሔርን ካልፈሩ፣ መኖሩን ስለማያምኑ ምኑን ይፈሩታል፣ የጠየቁትን ከመስጠት ሌላ የማጣሪያ መንገድ አልነበረንም፡፡

ውሎቹ ከመፈረማቸው በፊት ክፍያን የሚመለከቱት አንቀጾች ካልተሻሻሉ እያልን ወጥረን ስንይዝ ለዚህ እንደማደንዘዣ ወይም ማታለያ ይጠቀሙበት የነበረው ዘዴ፣ ተደራዳሪዎቹ ውስጠ አዋቂ በመምሰል፣ ውሎቹን ለይስሙላ እንድትፈራረሙ ይደረጋል እንጂ፤ የማትከፍሉት ገንዘብ ስለሆነ ለምን ጊዜ ታባክናላችሁ? ዝም ብላችሁ ተፈራረሙ እያሉ የሚመለከታቸውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ያግባቡና ይደልሉ ነበር፡፡ ይህ በተለይ የሚመለከተው መከላከያንና የማዕድንና ኃይል ማመንጫ ሚኒስቴሮችን ነበር፡፡ ብሔራዊ ባንክ የነበረው አመለካከት ግን ውል አንዴ ከተፈረመ ይዋል ይደር እንጂ ክፊሉን ማለታቸው ስለማይቀር ውሎቹ ከመፈረማቸው በፊት ለኛ ተስማሚ ስለመሆናቸው ይረጋገጥ የሚል ነበር፡፡ የክፍያ አንቀጾች አስመልክቶ፣ በብሔራዊ ባንክ በኩል ጥያቄ ስናነሳ ከሶቪየቶች ጋር ተደርበው ያስቸግሩን የነበሩት በተለይ ሁለቱ መሥሪያ ቤቶች ናቸው፡፡ እኛ የኢትዮጵያን ጥቅም ከማስከበር ውጭ ሌላ ስውር ዓላማ ያለን ይመስል እነሱም እንደ ሶቪየቶች እናንተ የባንክ ሰዎች አስቸጋሪዎች ናችሁ ይሉን ነበር፡፡

በጣም ውስን የሆነው የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ክምችት ከተሟጠጠና ኤኮኖሚው ከተዳከመ ብሎም አብዮት መጣልህ የተባለው ሰፊ ሕዝብ በልቡ ከሸፈተ በኋላ ጠላት ጥይት ሳይተኩስ ማንቁርታችንን እንደሚይዝ አብዛኛዎቹ የመከላከያ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች በትክክል ያልተረዱት ጉዳይ ነበር፡፡ ጠላት የሚወረው ድንበር ጥሶ መሣሪያ ጭኖ ብቻ

ይመስላቸዋል። ዋናው ጦርነት ያለው በኤኮኖሚው መስክ መሆኑን በቅጡ አይገነዘቡም። ሁሉን ነገር ወደ ጦር ግንባር የሚለው መፈክር ከቁጥጥር ውጭ ሄዶ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ዋና ኃላፊነት መዋጋትና ማዋጋት የመሰለበት ወቅት ነበር።

የኤኮኖሚ ጥንካሬ የሌለው አገር ጠላትን መከላከል አይችልም። በደካማ ኤኮኖሚ ላይ ከፍተኛ የመከላከያ ጫና ሲጫንበት ይጨፈለቃል። የወታደር ጫና ያለቅጥ የበዛበት አገር፣ አቶ አሰፋ ይርጉ ቶፕ ሄቪ ለሚለው በአማርኛ የሰጡትን ትርጉም ልዋስና፣ እግረ ጭራሮ እራሰ ከበሮ ይሆናል። ከበሮ በጭራሮ ላይ ቢጫን ጭራሮው ተሰባሪ እንደሚሆን ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግንባር ከተባለ የኤኮኖሚ መጫጫትና የማኅበራዊ አገልግሎቶች መዳከም የማይቀር ነው። በኢትዮጵያም የሆነው ይኸው ነው። የመከላከያ ሚኒስቴር ሰዎች የጥያቄዎቻቸውን ሊስት በየጊዜው በማስፋት ኤኮኖሚው መሸከም የማይችለውን ጫና ጭነውበት እንዲብረከረክና ብሎም ተገንጣዮች ሰተት ብለው እንዲገቡ ተጨማሪ ምክንያት ሆነዋል። የወታደሩ ክፍል በጦር ሜዳ ውጤት ማስመዝገብ ሲሳነው ሲቪሎች የምንፈልገውን ስላላቀረቡልን ነው እንጂ እናሸንፍ ነበር እያሉ ድክመታቸውን በሲቪሉ ላይ አልፎ አልፎ ማላከክ ይቀናቸው ነበር። ሐቁ ግን ኤኮኖሚው በይበልጥ እንዳይዳከምና ለጦሩ ክፍል ተፈላጊው ገንዘብና ቁሳቁስ እንዲቀርብለት በየስፍራው የነበሩ ሲቪል ቴክኖክራቶች ጠንክረው ባይዙ ኖሮ የደርግ እድሜ ያጥር እንደነበር ጥርጥር የለውም።

በተባበሩት መንግሥታት፣ ኒው ዮርክ፣ አምባሳደራችን የነበረው ብርሃኑ ዲንቃ ከእስር ቤት መለቀቁን ምክንያት በማድረግ ደስታዬን ልገልጽለት እቤቱ ሄጄ በነበረበት ወቅት፣ ለዘለዓለም እንቅልፍ በጣም የሚፈለጉ ሰዎች ብሎ ኢ ህ አ ፓ ባወጣው ዝርዝር ውስጥ የሁለታችን ስም ስለመኖሩ አውቅ እንደሆነ ጠየቀኝ። መቼም ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ መሆኑን አውቃለሁና፣ አልሰማሁም፣ እንዲህ ከሆነማ የደርግን ወህኒ ኪራይ ሳትከፍል ከጥይት መሸሸጊያ አድርገህ ተጠቀምክበት ማለት ነዋ ብዬ ከቀለድኩበት በኋላ፣

ለመሆኑ የጥፋታችን ዝርዝር ምን ይላል? ብዬ ጠየቅሁት። ኀጢአታችን፣ ቀጠለ ብርሃኑ፣ የተመደብንበትን ሥራ በሚገባ መሥራታችን ነው። እንደኔና እንዳንተ በየመስኩ የተሰማራን ቴክኖክራቶች በተዘዋዋሪ ደርግን ደግፈን ባንይዘው ኖሮ እድሜው ብሎም ኢ ህ አ ፓ ሥልጣን ላይ የሚወጣበት ጊዜ ያጥር ነበር፤ መፍትሔው የዕድሜ ቀጣዮችን ዕድሜ ማሳጠር መሆኑን ኢ ህ አ ፓ ተመራምሮ ደርሶበታልና መግቢያህን ብትፈልግ ይሻልሃል ብሎ ነግሮኛል።

ደፈጣ ተዋጊን እንዴት በመደበኛ ጦር ማሸነፍ ይቻላል? 300ሺ 400ሺ ወታደር ከማሳለፍና ከመመገብ እሾህን በእሾህ እንዲሉ እኛስ ለምን ደፈጣ ተዋጊ ኃይል አደራጅተን አናሰማራም? ስንል እናንት ሲቪሎች አርፋችሁ ተቀመጡ፣ ስለውጊያ ሳይንስ የምታውቁት ነገር የለም እንባላለን። አብዮቱ እንደፈነዳ አመጽ በየቦታው ሲቀጣጠል ሁኔታው ሲዳሞ ውስጥም የተለየ አልነበረም። እዚያ ጫካ የገባውን ሽፍታ ሻሸመኔ የነበረ ልዩ ተዋጊ ኃይል ፈልፍሎ ከተደበቀበት እንዳወጣ ይታወቅ ነበርና ተመሳሳይ ኃይል ተደራጅቶ ወደ ሰሜኑ ግንባር ብንልክስ የሚል ሐሳብ ቢቀርብ መንግሥቱ «ሞኛችሁን ፈልጉ፣ ይህ ምንም የማይበግረው ኃይል ግዳጁን ከፈጸመ በኋላ አፈሙዙን እኛ ላይ እንደሚያዞር እንዴት ዘነጋችሁት?» ብሎ ሐሳቡን ውድቅ አደረገው ይባላል።

እላይ የገለጽኩት ብርሃኑ ዲንቃ መግቢያህን ብትፈልግ ይሻልሃል ሲለኝ ወዳጄ ጀግናው ኮሎኔል ሙሉጌታ ማሞ ይለኝ እንደነበረው አገር ለቅቀህ ጥፋ ለማለት ፈልጎ እንደሆነ አላውቅም። ከሙሉጌታ ጋር በተገናኘን ቁጥር፣ እንዳንተ ዓይነቱ እዚህ ቦታ የለውም፤ በየጊዜው ወደ ውጭ ስትመላለስ አያለሁ፤ ለምን በዚያው እንደወጣህ አትቀርም? አገሩንና ጦርነቱንና የሚመሩት ወታደሮች እኛ ጠልቀን እናውቃቸዋለን፤ የሚረቡ አይምሰልህ፤ አብዛኛዎቹ የሚታገሉት ለራሳቸው እንጂ ለአገርና ሕዝብ ጥቅም አይደለም፤ ጦርነቱን ዳር ማድረስ ያልተቻለው አንድም ለመረጃ ማሰባሰቢያና ለመሳሰለው የሚመደበውን ገንዘብ ከፍተኛ የጦር አለቆች

ኪሳቸው ውስጥ ስለሚከቱት ነው፤ የሰራዊቱን እምነት ለማግኘት ብዙዎቹ ብቃት የላቸውም፤ ሁላችን እንዲሁ እንደክማለን እንጂ ነገሩ የማይሆንና ፈራሽ መሆኑን አውቃለሁ ይለኝ ነበር፡፡

ይህም ሆኖ ሁኔታዎች ተሻሽለው ሁሉም ነገር መስመር ይይዝና ሻል ያለ ቀን ይመጣል እያልኩ እራሴን አታልል ነበር እንጂ እራሴን ለማግለል ወይም ለማዳን በጽኑ አስቤ አላውቅም፡፡ ሙሉጌታ እንደተመኘልኝ ከምወደው አገሬ ባላሰብኩት መንገድ ለጊዜውም ቢሆን ተለይቻለሁ፡፡ ሙሉጌታ ደግሞ የውድ አገሩን አንድነት ለማስከበር ሲዋደቅ የጀግና ሞት ሞቷል፡፡ ውድ ባለቤቱ ገበያነሽና ልጆቹ እነብንያም በዚህ እንደሚጽናኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እኔን የሚገርመኝ ሥራ በሠራሁ ለሞት የታጨሁት በደርግና በኢ ህ አ ፓ ብቻ ሳይሆን በአገር አስተዳደር ሚኒስትሩና እራሱን ወጣት መኮንኖች ብሎ ይጠራ በነበረውና ከተገንጣዮች ጋር ተባባሪ በነበረው የወታደሮች ቡድንም ጭምር መሆኑ ነው፡፡ መንግሥቱም በአብዮቱ ስም ለፍርድ እንደሚያቀርበኝ በይፋ ተናግሮ ነበር፡፡ ዝርዝሩን ወደኋላ አቀርበዋለሁ፡፡

መንግሥቱ የጦርነቱ ዘመቻ ዳር ሳይደርስ ወደ ኤኮኖሚ ዘመቻ ቸኩለን በማምራታችን ስትራተጂክ ስሕተት ፈጽመናል እንዳለ አንብቤአለሁ፡፡ የሶማልያ ጦር ከአገር እንደተባረረ ሊቀመንበር መንግሥቱ ቢሮ ሄጄ የአገሪቱ ኤኮኖሚ ስላለበት ሁኔታ ስንወያይ የጦርነቱን በዘመቻ እንዳሸነፍን ሁሉ አሁን የሚያስፈልገን የኤኮኖሚ ዘመቻ ነው፤ ኤኮኖሚው ስለተዳከመ የሕዝባችንን ኑሮ ለማሻሻልና መከላከያችንንም ባስተማማኝ መሠረት ላይ ለማቆም የኤኮኖሚ እድገታችን እመርታ ማሳየት ይኖርበታል እንዳልኩት አስታውሳለሁ፡፡ የተጠቀሰውን ሐሳብ ስላስጨበጥኩት ይሁን ወይም ስለጉዳዩ መንግሥቱ እራሱ ቀደም ብሎ አስቦበት እንደነበረ አላውቅም ቢሮው በሄድኩ ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የኤኮኖሚ ዘመቻ

እንደምናደርግና ለዚህም ከፍተኛ ተቋም እንደሚቋቋም መግለጫ ወጣ፡፡ ብዙዎቻችን በጣም ደስ አለን፡፡

መንግሥቱ የኤኮኖሚ ዘመቻችንን ብናዘገየው ኖሮ ጥሩ ነበር ሲል እነታደሰ ስሕተት ውስጥ ከትተውኛል ብሎ አስቦ ይሆናል ብዬ ገመትኩ፡፡ እርምጃው ስሕተት ሳይሆን ትክክለኛ እንደነበር ሁሉም የተስማማበት ጉዳይ ነበር፡፡ ጦርነቱን ማካሄድ የተቻለው ሶቪየቶች መሣሪያ ስለሰጡ ብቻ ሳይሆን ኤኮኖሚው በማንሰራራቱና በየግንባሩ ለተሰለፈው ወታደር ምግብና ሌላም ማቅረብ በመቻሉ ነው፡፡ ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ መንግሥቱ የኤኮኖሚ ዘመቻው ሊዘገይ ይችል ነበር ለምን እንዳለ ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡

ወደ መንግሥቱ የሶሻሊስት አገሮች ጉብኝት እንመለስና ካየናቸው አገሮች ሁሉ በጣም ያስደነቀን የዩጎዝላቪያ ኤኮኖሚ መዳበርና የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከፍተኛነት ነበር፡፡ ቤልግሬድ በጣም የሚያምር ከተማ ሆኖ አገኘነው፤ ብዙ ዘመናዊ ሕንጻዎች አሉት፤ የከተማው መንገዶች በተሽከርካሪ የተጨናነቁ ነበሩ፡፡

ዮጎዝላቪያ ከሁለቱም ኃያላን መንግሥታት፣ ከአሜሪካ ወይም ከሶቪየት፣ ጎራ አልተሰለፍኩም፤ ገለልተኛ ነኝ ትል ስለነበር ሁለቱም ኃያላን መንግሥታት በጥንቃቄና በአመል የያዟት አገር ነበረች፡፡ እነቲቶ በዚህ አቋማቸው በደንብ ነግደው እንዳተረፉበት ጥርጣሬ የለውም፡፡ ገደብ ሳያልፉ ሶቪየት ዩኒየንን መጋፋትና መጎንተል እንደ ዓይነተኛ ስልት ይዘውት ስለነበር አሜሪካኖች አይዟችሁ፣ በርቱ እያሉ ይገፋፏቸው ነበር፡፡ ከሌሎች የሶሻሊስት ነገሮች ተነጥለው የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት አባል እንዲሆኑ አሜሪካኖች ስለፈቀዱላቸው ወይም እንዲፈቀድላቸው መንገዱን ስላመቻቹላቸው ግንኙነታቸው ከምዕራቡ ዓለም ጋር እንዲጠናከር አድርገው ነበር፡፡ ነገር ግን ሶቪየት ዩኒየን ከፈራረሰችና የዩጎዝላቪያ ጠቃሚነት ሲያበቃ የምዕራቡ ዓለም ዩጎዝላቪያን ጭዳ አድርጎ እንደገነጣጠላት ሁሉም ልብ ሊለው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በቤልግሬድ ቆይታ የተፈረመው የንግድ ውል የእኔ አሻራ አለበት:: ነገሩ እንዲህ ነው:: የንግዱን ውል የተደራደረው ቡድን የኢትዮጵያን ጥቅም ያስጠብቃል ብሎ ያመነበትን ለበላይ አካል ያቀርባል:: እኔም የቡድኑ አባል ነበርኩ:: ዩጎዝላቮቹ በበኩላቸው አንዳንድ እንቀጾች ካልተሻሻሉ አንቀበለውም ይላሉ:: ጉዳዩን የሁለቱ አገሮች የበላይ አካላት ዐይተው እንዲጨርሱት ተባለና ወደነሱ ተመራ:: በመጨረሻም ድርድሩ አልቆለታል ተባለ:: በየመስኩ የሚፈረሙ ውሎች በነጋታው ጠዋት በቲቶና መንግሥቱ ፊት ሊፈረሙ ተዘጋጅተዋል:: አለቀለት የተባለውን የንግድ ውል ሳነበው የአገራችንን ጥቅም የሚጻረርና ምርቶቻችንን ለዩጎዝላቭያ ማቅረብ እንዳለብን የሚያስገድድ ሆኖ አገኘሁት:: ውሉ ምርቶቻችንን በተሻለ ዋጋ፣ በነጻ ገበያ ሸጠን የውጭ ምንዛሪ እንዳናከማች የሚያግደን ስለሆነ በፍጹም የተሳሳተ ነው አልኩና ነገር ጫርኩ:: ከውጫሌ ውል ጋር ተመሳሳይነት ነበረው፤ ጣሊያኖች ከሌላው ዓለም ጋር የምታደርጉት ግንኙነት በኛ በኩል እንዲሆን ተፈራርማችኋል እንዳሉት ሁሉ ይኸኛውም ውል ቢፈረም ኢትዮጵያ ምርቶችዋን ለዓለም ገበያ የምታቀርበው በዩጎዝላቪያ በኩል ነው የሚል ትርጉም የሚያሰጥ ነበር::

የኤኮኖሚው ዘርፍ የበላይ ተጠሪ ለነበረው ለገሰ ወልደኪዳን ስጋቴን ወይም ቅሬታዬ ገለጽኩለት:: አሁን ሁሉም ነገር አልቆለታልና ምንም ማድረግ አይቻልም ቢለኝ በምንም ዓይነት ካልተሻሻለ ሞቼ እገኛለሁ አልኩት:: ምሽቱ ተጋምሷል:: ጉዳዩን በጣም አጠናክሬ ስላነሳሁት የሚመለከታቸውን ሚኒስትሮች ለመሰብሰብ ተገደደ:: አስረዳ ተባልኩ:: ከማስታውሳቸው ሚኒስትሮች አሻግሬ ይግለጡ፣ ዩጎዝላቪያ የተማረ የንግድ ሚኒስትርና የውሉ ተቀባይ፣ ተፈራ ወልደሰማዕት የገንዘብ ሚኒስትርና ተስፋዬ ዲንቃ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ነበሩ:: አሻግሬ እንዲህ አለኝ፣ እኔ የንግድ ሚኒስትሩ ይበጃል ብዬ የተስማማሁበትን ትክክል አይደለም፣ የአሻግሬን ስምምነት ያገኘ ጉዳይ ብቃት የለውም ብለህ የምታጥላላና የምትቃወም ለመሆኑ አንተን ማን ሆነህ ነው? ብሎ ወረፈኝ:: ስለእኔ ማንነት በስብሰባው ላይ ለነበሩት ሚኒስትሮችና ለገሰ የገለጸላቸው፣

ምንነቴ የማይታወቅና በአብዮት ስም ተግበስብሼ የመጣሁ ሰው እንደነበርኩ አድርጎ ነበር:: የኔን ማንነት የሚመሰክረው ታሪኬና ሥራዬ እንጂ ዶክተሩ ስላልሆነ ስድቡን ይፋ በማድረጌ ባለጌን አንዴ ስደበውና እራሱን ሲሰድብ ይኖራል እንደማልባል ተስፋ አደርጋለሁ::

ለአሻግሬ የተያዘለት የስድብ ፕሮግራም ካበቃ በኋላ ስለውሉ መሻሻል ምክክር ተደረገ:: በዩጎዝላቮች በኩል የተሰየመው የበላይ ተደራዳሪ ይጠራና ውሉን ችግር እንደገጠመው እንግለጽለት ተባለ:: ለሰውዬው ቢደወልለት "ምን ትቀልዳላችሁ፣ ግማሽ ሌሊት ሆኗል እኮ፣ ፒጃማዬን ለብሼ አልጋ ውስጥ ነው ያለሁት፤ የውሉን ድርድር ምነው ጨርሰነዋል አይደለም እንዴ?" ይላል:: "አይ እንደምታስበው ቀላል አይደለም፤ እንደገና መታየት ያለበት ጉዳይ ተገኝቷልና ይልቅስ በተቻለህ ፍጥነት መጥተህ ብንጨርሰው ይሻላል" ተባለ:: ሰውዬው ፒጃማውን ከውስጥ እንደለበሰ ሰዎቹን ይዞ ከተፍ አለ:: በኛ በኩል ያየነውን ስጋት ገለጽንለት:: ካልተሻሻለ እንደማንፈርም ነገርነው:: አማራጭ ስላጣ ውሉ እኔ ባቀረብኩት ሐሳብ መሠረት ተስተካከለ:: ውሉ ስለተስተካከለ ከፍተኛ የመንፈስ እርካታ ተሰማኝ፤ አሻግሬ በስድብ ያሻከረውን ስሜቴንም ሞረደልኝ::

ስለዩጎዝላቪያ ጉብኝታችን ሌላ ትዝ የሚለኝ የንግድ ሱቆች የእቃ ግዥ ብድር በገፍ ይሰጡ እንደነበር ነው:: በአገራችን ብድር ለአምራች እንጂ ለሸማች መስጠት የተለመደ አይደለም:: በኛ በኩል የነበረው አስተሳሰብ ለፍጆታ የሚሰጥ ብድር የመከፈል ዕድሉ ዝቅተኛ ነው ብቻ ሳይሆን የዋጋ ንረትንና የውጭ ምንዛሪ መሟጠጥን ያስከትላል የሚል ነበር::

በካፒታሊስት አገሮች ለሸማች ብድር ካልተሰጠ የምርት እድገት ሊስፋፋ አይችልም ተብሎ ይታመናል:: አንድ ካፒታሊስት ሥራውን የሚያስፋፋው ወይም ፋብሪካ የሚያቋቁመው ሸመታ ሲደራ ወይም እንደሚደራ አስተማማኝ ግምት ሲኖር ብቻ ስለሆነ ምርትን ማስፋፋት ከተፈለገ ሸመታን ማበረታታት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ:: በሰሜን አሜሪካ

የሚገኙ ነዋሪዎች ያላቸው ንብረት ግምት በጠቅላላ ካለባቸው እዳ ጋር ሲነጻጸር መሳ ለመሳ ነው:: ለምሳሌ፣ የአንድ ቤተሰብ የንብረቱ ጠቅላላ አማካይ ግምት 300ሺህ ዶላር ቢሆን ዕዳውም ያን ያህል ነው ማለት ነው:: በሌላ አነጋገር ቤተሰቡ ያለው ንብረት ሙሉ በሙሉ በዕዳ የተገዛ ነው ማለት ነው:: ቤተሰቡ ዕዳውን ለመገፍገፍ ሌትና ቀን መዳከር አለበት:: አንድ ሰው ከሥራ ቢወጣና ሥራ ሳያገኝ ብዙ ቢዘገይ ንብረቱ ተሽጦ ለዕዳው መክፈያ ይውላል::

በዩጎዝላቪያ ለማስፈን ሲሞከር የነበረው የኤኮኖሚ ሥርዓት ከሞላ ጎደል ይህንኑ የሚመስል ነበር:: ታዲያ በወቅቱ ያልኩት የኢንቬስትመንት ገንዘብ ምንጭ አስተማማኝ ባልሆነበት ሁኔታ ሽመታን በብድር ኃይል መገፋፋት ወይም ማስፋፋት፣ በውጭ ብድር የተገዛ ሸቀጥ ለሕዝቡ በገፍ ማቅረብ፣ ያውም በብድር፣ ሲውል ሲያድር ችግር አይፈጥርባቸውም ወይ? ከአቅማቸውም በላይ እንዲንጠራሩና እንዲኖሩ አይገፋፋም ወይ? ነበር:: ብዙም ሳይቆይ ኤኮኖሚው ቀውስ ውስጥ ገብቶ፣ የዋጋ ንረት ሰማይ ደርሶ፣ የአገሩ ባለሥልጣኖች ኮረጆ ይዘው ከአይ ኤም ኤፍ ብድር ለመጠየቅ ዋሺንግተን ሲመላለሱ አይ ነበር::

ቲቶ ከሞተ በኋላ የኤኮኖሚው ቀውስ ስለለየለትና ማጣፊያው ስላጠራቸው ባለሥልጣኖቹ እርስበርስ መወነጃጀል ሥራዬ ብለው ተያያዙት:: በብሔር የተሸነሸኑት ክልሎችም እንዲሁ መወነጃጀልና ሁላቸውም የየራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ መሯሯጥ ጀመሩ፤ ቀጥሎም ብዙዎቹ ማእከሉ ከተዳከመ የጋብቻው ጥቅም አይታየንምና ፍቺ ይሻለናል፣ የጋብቻው ውል ይቀደድልን አሉ:: የዩጎዝላቪያን ውድቀት ሲመኝና ገፋ አድርጎ ወደ ገደል ሊጥላት መሣሪያ ይዞ ዳር ቆሞ ሲጠባበቅ የነበረው የውጭ ኃይል የውሉን መቅደጃ ካራ ለፍቺ ፈላጊዎች አደላቸውና ዩጎዝላቪያን ብትንትኗን አወጧት:: ዩጎዝላቪያ የሚለው ስም ከአፍቃሪዎቹ አእምሮ ባይሆንም ከመዝገብ ግን ተፍቋል:: ቲቶ አስቀድሞ መሞቱ ምንኛ የታደለ ሰው ነው:: ከሃያ አምስት ዓመት በፊት አንድ ሰው የዩጎዝላቪያ የወደፊት ዕጣ

የተገለጸውን ይመስላል ብሎ ተናግሮ ቢሆን ኖሮ ከአማኑኤል ያመለጠ እብድ ይባል ነበር፡፡

ያገሬ ሰው፣ የዩጎዝላቪያ ታሪክ ተረት አይደለም፡፡ ትናንት የሆነ ነገር ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን፣ አገራችንን ሊበታትኑ የተሰለፉ ኃይላት ብዙ ናቸው፡፡ አገራችንን ለመጠበቅ እንድንችል ብንተባበር ይሻለናል፡፡ አንዝናጋ፡፡

ከሶቪየት ዩኒየን ቀጥሎ ከኢትዮጵያ ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረው ሶሻሊስት አገር ምስራቅ ጀርመን ነው፡፡ የምስራቅ ጀርመንን ሰዎች የሚቀመስ ምን አላችሁ? ብላ ከሳሎን ወደ ጓዳ ተንደርድራ በምትገባ ሳተና የሴት እንግዳ መመሰል ይቻላል፡፡ በጣም ፈጣኖችና ለአገራቸው ሃያ አራት ሰዓት የሚሠሩ ናቸው፡፡ ለሁሉም ዓይነት ችግር ደራሽ ለመሆን ይጥራሉ፡፡ በሌላ አንጻር ደግሞ አዲስ አበባም መጡ በርሊን ተሄደ የሚነግሩን ከምዕራቡ ዓለም በተለይም ከምዕራብ ጀርመን የሚንቆረቆረው ጸረ ሶሻሊዝም ፕሮፓጋንዳና በቴሌቪዥን የሚታየውን የተንደላቀቀ ኑሮ የሕዝባቸውን ልብ እያሸፈተባቸው እንደሚቸገሩ ነበር፡፡ ይህን ነጥብ የሚያነሱት በድርድር ስንጠነክርባቸው ወይም አንድ ነገር ካላደረጋችሁልን እያልን ወጥረን ስንይዛቸው ወይም እንደቡና የመሳሰሉ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶችን በውጭ ምንዛሪ ካልሆነ በቀር እቃ በእቃ አንለውጥም ስንላቸው ነበር፡፡ ያም ተባለ ይህ ንቁነታቸውን፣ ታታሪነታቸውንና አገር ወዳድነታቸውን ሁላችንም እናደንቅላቸው ነበር፡፡ ሶቪየቶች እንደነሱ ቢሆኑ ኖሮ የሶሻሊዝም ፍልስፍናን በተግባር መተርጎም ይቻል ነበር እንባባል ነበር፡፡

ምሥራቅ ጀርመኖች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር የነበራቸው ግንኙነት በቀላሉ ከአእምሮ የሚጠፋ አይደለም፡፡ ስለሶሻሊስት ባንኪንግ የምታውቁትን አካፍሉን ብለናቸው ዶክተር ጆስዊግን ልከውልናል፡፡ በ1967 ቻይና ከነዶክተር አሻግሬ ጋር ሄጄ በነበረበት ወቅት ባንካቸው ድረስ ሄጄ ስለሶሻሊስት ባንኪንግ አደረጃጀትና አሠራር ልትረዱን ትችላላችሁ? ብዬ ብጠይቃቸው፣ እንኳን እናንተን ልናስተምር ይቅርና እኛ እራሳችን ከናንተ

ብዙ የምንማረው ይኖራል፤ ሲስተማችን ከምታስቡት በታች ኋላቀር ነው ብለው እውነቱን ነግረውኛል። ዶክተር ጆስዊግ ከባንኮች ባለሙያዎች በተጨማሪ ለልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞችና ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አስተማሪዎች ጭምር የሚያውቀውን አካፍሏል። ሰውዬውን ጠጋ ብዬ ሳየው ትምህርቱ የተመረሠተው ከሳይንሳዊ እውቀት ይበልጥ በእምነት ላይ ስለነበር የቅጥር ኮንትራቱን ሳናድስ ወደ አገሩ ተመልሷል።

ከምሥራቅ ጀርመኖች ጋር በደንብ ያስተዋወቀኝ ቡናችን ነው። በሶማልያ ወረራ ወቅት የትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች እንዲገዙ የንግድ ሚኒስትሩ አሻግሬና የደርጉ የኤኮኖሚ ጉዳይ ኃላፊ ገሰሰ ወልደኪዳን ወደ ምስራቅ ጀርመን ይላካሉ። አስር ሺህ ቶን ወይም አንድ መቶ ሺህ ኩንታል ቡና ኢትዮጵያ ልታቀርብ፣ ምስራቅ ጀርመን ደግሞ አይፋ የተሰኙ የወታደር ማጓጓዣና የጭነት ተሽከርካሪዎችን፣ እንዲሁም ለጦርነቱ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ለኢትዮጵያ እንድትሸጥ ተዋውለው ተመለሱ።

የተፈራረሙት ውል ገንዘቡንና የሒሳቡን አያያዝ በጀርመኖች ቁጥጥር ሥር የሚያደርግ በመሆኑ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ አስተማማኝ ሰላልነበር ስሕተት መፈጸሙንና ውሉ ሊስተካከል እንደሚገባው ብሔራዊ ባንክ መንግሥትን አሳሰበ። ወትሮ ይደረግ እንደነበረው እነገሰሰም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባለሙያ ይዘው ቢሄዱ ኖሮ ስሕተቱ አይፈጸምም ነበር። የችግሩ ይዘት በአጭሩ እንደሚከተለው ነበር። ቡናው ለጀርመኖቹ ከቀረበና እነሱም በምትኩ እቃ ካቀረቡ በኋላ ሒሳቡን እንተሳሰብ ተባሉና ያላችሁ ወይም ያልተጠቀማችሁበት ገንዘብ ይህን ያህል ነው ይላሉ። ሰለሒሳቡና ስለቀሪው ገንዘብ መጠን ትክክለኛነት ተጠራጠርን። በባንካችን በኩል የነበሩት አቋሞች የሚከተሉት ነበሩ። አንደኛ፣ ቡና የሸጥንበት ገንዘብ የኢትዮጵያ ገንዘብ ስለሆነ ገንዘቡን በእጅ አስገብታ መቆጣጠር ያለባት ኢትዮጵያ ናት፤ ሁለተኛ፣ ጀርመኖች በሒሳቡ ወጪ አድርገው ገንዘብ ከመውሰዳቸው በፊት የገንዘቡን ባለቤት ጠይቀው ማስፈቀድ አለባቸው፤ ያለበለዚያ ላልተላከ እቃ ሁሉ ከሒሳባችን ወጭ

እየተደረገ ቢወሰድ የምናውቅበት መንገድ የለም፤ ሦስተኛ፣ ከጀርመን ወደ ኢትዮጵያ ተላከ የተባለ እቃ በእርግጥም መድረሱ ከጉምሩክና እቃውን ከተቀበለው መሥሪያ ቤት ማረጋገጫ ይቅረብልን የሚሉ ነበሩ።

ስለገንዘቡ ቁጥጥርና ሒሳቡ አያያዝ በባንኩ በኩል የነበረውን ስጋት በይፋ ያነሳሁት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ነበር። ጊዜውም ነሐሴ ወይም መስከረም 1970 ይመስለኛል። የባንኩ አዛዥ አቶ ለገሰ ጥቀሄር ለስብሰባ ወደ ዋሺንግተን ሄዶ ስለነበር ባንኮችና የውጭ ምንዛሪያችን ያሉበትን ሁኔታ ለምክር ቤቱ መግለጫ ለመስጠት ሄድኩ። ስብሰባው የተደረገው ታላቁ ቤተመንግሥት ግቢ ነበር። ሚኒስትሮቹ ስብሰባው አዳራሽ ገብተው የሊቀመንበር መንግስሥቱን መምጣት ይጠባበቃሉ። እኔና አንድ ከሌላ መሥሪያ ቤት የመጣ አስረጅ እንግዳ ማረፊያው ውስጥ ተቀምጠናል። መንግሥቱ ሲገባ ተነስተን ቆምን። ሌላ ጊዜ እንደሚያደርገው እንደምን አደርክ? ታደሰ፣ እንደምን አደርክ? እገሌ ብሎ ቀረብ ብሎ ጨብጦን ወደ ስብሰባው አዳራሽ ይገባል ብዬ ስጠባበቅ ልክ እንዳልተፈጠርን፣ እንደሌለን፣ እንዳላየን ዓይነት ወደ አዳራሹ ገባ። ያ የማውቀው ትሑት፣ ሰው አክባሪ በግል ሲያነጋግሩት የማይከብደውና እራሱን የማያመጻድቀው መንግሥቱ ሳይሆን ጅንን፣ ወጣራ፣ በአየር ላይ የሚንሳፈፍ ሰው ነበር ያየሁት። ምን ተፈጠረና? ብዬ ባስብ ለካስ እኔ የሚቱ የአለማየሁ ጓደኛ ነኝ። አሃ፣ ድግስ ተደግሶልኛላ! ብዬ አሰብኩ። እነአለማየሁ ከተገደሉ በኋላ ከመንግሥቱ ጋር ብቻ ለብቻ ወይም ፊት ለፊት ስንገናኝ ይህ የመጀመሪያው ይመስለኛል።

አለማየሁ ከምሁራን ጋር ብዙ ግንኙነት ነበረው። አብዮቱ መስመር እንዲይዝ ምን ቢደረግ ይሻላል? እያለ መጠየቅ ይወድ ነበር። በየመስኩ ያሉትን ምሁራን እያሰባሰበ በልዩ ልዩ ጥናቶች ውስጥ ያሳትፋቸው ነበር። በመሆኑም በተለይ በአብዮቱ መጀመሪያ ዓመታት ደርግ ከምሁራን ጋር የነበረው ግንኙነት ሊጠናከር የቻለው አንድም በአለማየሁ ጥረት ነበር ለማለት ይቻላል። የሕዝብ ድርጅት ጽሕፈት ቤት ከተቋቋመና ሁሉም ነገር

በፖለቲካ መነጽር መታየት ከጀመረ በኋላ ግን በአገር ወዳድነት ስሜት እየተገፋፉ አብዮቱ መስመር እንዳይስት እንረዳለን የሚሉ ሰዎች ቁጥር እየቀነሰ መጣ:: እነአለማየሁ ከተገደሉ በኋላ ነገሩ ለየለትና ደርግን ከምሁሩ ጋር ልብ ለልብ ያገናኝ የነበረው ድልድይ ተሰብሮ በመሀላቸው ትልቅ ጉድባ ተፈጠረ:: ደርግን ሥልጣናችንን ስላስከበርን ማን አባቱ ይደፍረናል? የሚል ስሜት የተጸናወተው መሰለኝ:: አሻፈረኝ የሚለውን በኃይል እናስገብረዋለን የሚለው ስሜት እያየለ የመጣ ይመስለኛል:: በዚህ መሀል በአጠገቤ እየተጎማለለ እንደማያውቀኝ መስሎ ያለፈው ያ የማውቀው፣ የተቀደደ ካኒቴራ ለብሶ በማየቴ አንጀቴን የበላው መንግሥቱ ነበር:: የስብሰባው አዳራሽ የጃንሆይ አንበሳ፣ መኩሪያ፣ ከሚኖርበት ትንሽ ከፍ ብሎ ስለነበር መንግሥቱ በአንበሳው መኖሪያ አጠገብ ሲያልፍ እሱም አንበሳነትን የተላበሰ መስሎት እንግዳ ማረፊያው ውስጥ የነበርነውን ሰዎች ጓደኞቻችሁን ጅብ በላባችሁ አንጼ? ብሎ አስቦም ይሆናል::

ተራዬ ሲደርስ ግባ ተባልኩና የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ገለጻ አደረግሁ:: የውጭ ምንዛሪ ችግር እንዳለ ገልጬ ምስራቅ ጀርመኖች ከወሰዱት ዐሥር ሺህ ቶን ቡና ያልተጠቀምንበትን ገንዘብ ወደ ውጭ ምንዛሪ ለውጠው እንዲሰጡን ይጠየቁ የሚል ሐሳብ አቀረብኩ:: ገና ተናግሬ ከመጨረሴ ቢያንስ አምስት ስድስት እጅ አንድ ላይ ወጣ:: ሁሉም ያሉት ተመሳሳይ ነበር፣ አገራችን በሶማሌዎች ስትወረር መጀመሪያ ከደረሱልን አገሮች መካከል ምስራቅ ጀርመን አንዷ ናት፣ ለኛ ሲሉ ይህን አድርገው፣ ያን ፈጥረው፣ ሰራዊታችን በጦር ሜዳ ድል እንዲያደርግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገው አሁን የውጭ ምንዛሪ አምጡ ማለት በፍጹም ተገቢ አይደለም አሉና ተረባረቡብኝ:: በበኩሌ ስመልስ፣ ችግር አንጻራዊ መሆኑን፣ የኛ ችግር ከነሱ ጋር ሲነጻጸር በጣም የላቀ መሆኑንና የውጭ ምንዛሪ ችግራችን ካልተቃለለ ወይም እየከፋ ከሄደ ሁሉም ነገር ፈራሽ ስለሚሆን የሚበጀው ወዳጆቻችን ለኛ ሲሉ እንዲችገሩልን መጠየቅ ይሻላል አልኩ:: እንደገናም የጀርመን ደጋፊዎች ተነሱና ዲስኩር አደረጉ:: ታደሰ ያለው ትክክል ነው ብሎ የደገፈኝ ሰው

መኖሩን አላስታውስም። እንደጉባኤው መንፈስ ቢሆን ኖሮ ታደሰ ጸረ አብዮተኛ ወይም ጸረ አገር መከላከያ ስለሆነ ቢያንስ ቢያንስ ከተሰጠው የኃላፊነት ቦታ መነሳት አለበት የሚያሰኝ ነበር። በእኔ በኩል ሚኒስትሮቹን ታዘብኳቸው እንጂ እራሴን ችግር ውስጥ ዶልኩ ብዬ በፍጹም አልተረበሽኩም፣ ምክንያቱም ምስራቅ ጀርመኖች የሚሠሩት ለአብዮቱ ወይም የኅሊና እረፍት ለማግኘት ሲሉ ብቻ ሳይሆን ችግራችንን ተገን አድርገው ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይሉ የራሴ ግንዛቤ ስለነበረኝ ነው። ቢሆንም መንግሥቱ የሚለውን ለመስማት ጓጉቻለሁ። መንግሥቱ ውይይቱን ሲያጠቃልል፣ ታደሰ ያለውን፣ እናንተም ያላችሁትን ሰምቻለሁ፣ ታደሰ ወደ ሥራ ገበታው መሄድ ይችላል አለ እንጂ እንደነሱ አቋሜን አላጥላላም ወይም እናንተ ሁላችሁም ተሳስታችኋል ወይም ልክ ናችሁ አላለም። እኔ ከተሸኘሁ በኋላ ምን እንዳላቸው ወይም እንደተባባሉ የሰማሁት ነገር የለም።

በእኔ አስተያየት መንግሥቱ ቢያንስ ሁለት ገጽታዎች አጣምሮ የያዘ ሰው ነው። እንደሁኔታው ቀያይሮ ይለብሳቸዋል። ለተገፋና ለተበደለ አዛኝና ተቆርቋሪ ይመስላል። ክብሩ ወይም ስብዕናው ተደፍሯል ብሎ ካመነ ደግሞ ቂም ይይዛል፤ ከመበቀል ወደኋላ አይልም። ሥልጣኑን የሚቀናቀን ወይም አመራሩን የሚያጥላላን ሰው ባይነ ቁራኛ መጠበቅና ጊዜና ሁኔታ ሲያመች ከማስወገድ ወደኋላ የማይል ሰው ነው። ስለሆነም ለጭካኔ ያለው ሆድ ሰፊ ነው። መንግሥቱን መድረክ ተቆጣጥሮ ትልቅ ስብሰባ ወይም ጉባኤ ሲመራ ያየውና በግል ቢሮው ውስጥ ያነጋገረው ሰው እውነት ይሄ ያ ያነጋገረኝ መንግሥቱ ነው? የሚያሰኝ ነው። በግል አንድ ለአንድ ሲያነጋግሩት ትሑት፣ የማይከብድ፣ የማያውቀውን አስተምሩኝ ባይ፣ የተለያዩ ሐሳቦችን በውል ሳይመረምርና ሳያገናዝብ በጭፍኑ እንዲህ ካልሆነ የማይል ሰው ሲሆን ትልቅ መድረክ ላይ ሲወጣ ግን ምንም እንኳን ደኅና አድማጭ ቢሆንም ሁሉን አውቃለሁ፣ ሁሉም ነገር ተገልጦልኛልና ብትከተሉኝ ይሻላችኋል የሚል አምባገነንነት የሚያጠቃው ሰው ነው፡ በአጭር ቋንቋ

መንግሥቱ ሁለት ተቃራኒ ሰዎች አንድ ላይ ተጨፍልቀው የተሠራ ሰው ነው::

ሰዎች ስለመንግሥቱ ምንነት ወይም ማንነት ያላቸው አስተያየት አከራካሪ ወይም የተራራቀ ሊሆን ይችላል:: ግን አብዛኞዎቹ በአንድ ነገር የሚስማሙ ይመስለኛል፤ ይኸውም፣ አገሩን እንደሚወድና ያገሩን ጥቅም ያለአግባብ አሳልፎ እንደማይሰጥ ነው:: ከሶሻሊስት አገሮች ጋር በነበረው ግንኙነት እነሱ እጅ መውደቁን ስለሚያውቅ ማጣፊያው አጥሮት ነው እንጂ ኢትዮጵያን ለቡጥቦጣ ያመቻች ነበር ብሎ ለመፍረድ ያስቸግራል:: ይህም ሲባል ሁኔታው ቢያመቸው ኖሮ የሶሻሊስቱን ካምፕ እርግፍ አድርጎ ጥሎ ወደ ካፒታሊስቱ ጎራ ለመቀላቀል ዝግጁ ነበር ለማለትም አይደለም:: በተቃራኒው ሥርነቀሉ ለውጥ በሌላ ሥር ነቀል ለውጥ ቢተካ ሥልጣኑን እንደሚያጣ ስለተረዳና በኢትዮጵያ ለፈሰሰው ደም ተጠያቂ ያደርጉኛል ብሎ ስለሰጋ ለውጥ እንዲደረግ የፈለገ አይመስለኝም:: ጎርባቾቭ መንግሥቱን ለችግሮቻችሁ መፍትሔው በአገርህ ለውጥ ማምጣት ነው እንጂ እኛ ዘንድ መመላለስ አይደለም ስላለው መንግሥቱም፣ ይህ ቀልባሽ ብሎ ጎርባቾቭን በክሬምሊን ቤተመንግሥት ውስጥ ሲሰድበው በልቡ፣ ሞኝህን ፈልግ፣ እጅ የሚሰጥ ሂድና ፈልግ ማለቱ ሊሆን ይችላል:: በሥር ነቀል ለውጥ አማኙ፣ አራማጁና ተራማጁ መንግሥቱ ቀውጢ ወቅት አፍጦ ሲመጣ ለውጥ ለምኔ ስላለና ኢትዮጵያን ሳይሆን እራሱን ስላስቀደመ ተቃራኒ ገጽታዎችን የተላበሰ ሰው ነው ለሚለው አባባል ተጨማሪ ማስረጃ ነው:: በኢትዮጵያና መንግሥቱ መካከል የነበረው መንፈሳዊ ግንኙነት በጴጥሮስና በክርስቶስ መካከል እንደነበረው መመሰል ይቻላል:: የክርስቶስ ደቀመዛሙርትና ክርስትያኖች ጴጥሮስን ይቅር ብለውታል፤ ታሪክ ስለመንግሥቱ ምን እንደሚል ከወያኔ ወይም ከዘውድና ፊውዳሊዝም አቀንቃኞች ሳይሆን ከሐቀኛ የታሪክ አዋቂዎች ወደፊት እንሰማለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

እላይ የተገለጸው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ በተደረገ ሰሞን ወደ ምስራቅ ጀርመን አንድ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን ሲሄድ እኔም አብሬ

እንድሄድ ይደረጋል፡፡ ከሚነሱት ጉዳዮች አንዱ ስለቡናው ገንዘብ ነው ተብሎ ተነግሮኛል፡፡ የኔ ምድብ በአሻግሬ በሚመራው ንግድ ኮሚቴ ውስጥ ነበር፡፡ ስብሰባው በሁለቱ ቡድኖች መሪዎች ንግግር ከተከፈተ በኋላ ልዑካኑ በየኮሚቴው ተከፋፈሉና ዝርዝር ውይይትና ድርድር ተጀመረ፡፡ የቡናውን ሒሳብ ጉዳይ የሚመረምረው ንዑስ ኮሚቴ በአሻግሬ መመራት ሲኖርበት እርሱ ግን "ስለቡናው ሒሳብ የሚያነሳውና የመነጋገሪያ ርእስ ማድረግ የሚፈልገው ይሄ የምታዩት ታደሰ፣ የባንኩ ምክትል አዛዥ፣ ስለሆነ ሄዳችሁ ከሱ ጋር ተነጋገሩ" ብሎ ለጀርመኖቹ አሳልፎ ሰጠኝ፡፡ እነአሻግሬ ከአገሬ አውጥተው ሰው አገር ወስደው እንደካዱኝ ወይም አሳልፈው እንደሰጡኝ ተሰማኝ፡፡

በኮሚቴው መሰብሰቢያ አዳራሽ ቢያንስ ሰባት ወይም ስምንት ጀርመኖች ተቀምጠው መሪያቸውን ብሩክነርን ይጠባበቃሉ፡፡ ብቸኛው ታደሰ ወረቀቶቹን ከቦርሳው አውጥቶ ዐየት ዐየት ማድረግ ከመጀመሩ ብሩክነር እየተንደረደረ ገባና ቦርሳውን ጠረጴዛው ላይ አስቀምጦ ሳይቀመጥ ወረቀቶቹን እያወጣ፣ "ስማ ሰውዬው፣ ስለቡናው ገንዘብ ጉዳይ የያዝከውን አቋም ፓርቲያችን ቢያውቅና ለአገራችሁ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ስሞታ ቢነገር ምን እንደሚደርስብህ ትገነዘባለህ?" ብሎ ጠየቀኝ፡፡

ብሩክነር ከኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ጋር ስለነበረው ግንኙነት ትልቅ መጽሐፍ መጻፍ ይቻላል፡፡ ስለማንነቱ በጥቂት ቃላት ለማጠቃለል፣ ለአገሩ ሃያ አራት ሰዓት የሚሠራ፣ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ምንም ከማድረግ የማይመለስ፣ አፉ ለከት የሌለው ሰው ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ስለቡና አቅርቦት ተነሳና ለምንድነው እናንተ ጀርመኖች ሁሌ ቡናችንን በእቃ ካልለወጣችሁን የምትሉን? ለምን ውጭ ምንዛሪ ከፍላችሁ አትገዙንም? ተብሎ ቢጠየቅ፣ "ምን ትቀልዳላችሁ፣ በውጭ ምንዛሪ ለመግዛት እነኮሎምቢያ እያሉልን ምን እናንተ ዘንድ ያመጣን ነበር?" ያለ ሰው ነው፡፡ አንዴ ደግሞ ስለኢራቅ ተነሳና እነሱ እኮ ተገንጣዮችን የሚረዱብን ስለሆኑ ጠላቶቻችን ናቸው፣ በጣም እንጠላቸዋለን ብንለው፣ እሱ ግን "የእኛ አስተያየት የተለየ ነው፤

ኢራቅ ብዙ እቃ ስለምትገዛን ሰዎቹንና አገሩን እንወዳቸዋለን" ብሎ እቅጩን የነገረን ሰው ነው። አንድ ጊዜ ደግሞ ከአገርህ ውጭ ብዙ ጊዜ ትጓዛለህ? ብለን ጠየቅነው፣ ሲመልስልን "አንድና ሁለት የለውም፣ እንዲያውም ውጭ የምሆንበት ጊዜ ስለሚበዛ አንድ ቀን ልጆቼ አጎታችን አንጂ አባታችን አይደለህም ብለው እንዳይክዱኝ እፈራለሁ" አለን። ብሩክነርን በደንብ ካወቅነው በኋላ ለአገር መሥራት እንደ ብሩክነር ነው እንጂ እንባባል ነበር። አይፋ የጭነት ተሽከርካሪዎች በየቦታው በቀላሉ ሲፈነገሉና በጀርባቸው ተንጋለውና እግሮቻቸውን ወደሰማይ ሰቅለው ያየ አበሻ፣ ለተሽከርካሪው አይፋ ላገሬ ልደፋ ብሎ የክርስትና ስም አወጣለት። ብሩክነርንም እንደአይፋ ግንባሩን ለአገሩ የሚደፋ ትጉህ ሰው ነበር።

የብሩክነር ፍላጎት እኔን አስፈራርቶ የፈለገውን ለማስፈጸም ነበር። በበኩሌ ምንም መልስ ሳልሰጠው በጠረጴዛው ላይ የዘረጋኋቸውን ወረቀቶች ሰበሰብኩና በቦርሳዬ ከትቼ ተነስቼ ቆምኩና በቀጥታ ወደ በሩ አመራሁ። አንድ ቃሌን ብቻ ለማስፈራራት እንጂ ለመደራደር ስላልተዘጋጃችሁ ከናንተ ጋር አልነጋገርም፤ የፈጸማችሁት አስነዋሪ ተግባር ለመሪያችን አሁን ሄጄ እናገራለሁ አልኩና ወደ በሩ አመራሁ። ይሄኔ ሰዎቹ ተደናግጡ። የወሰድኩት አቋምና እርምጃ ዱብ ዕዳ ሆነባቸው። ሦስት ወይም አራቱ ከመቀመጫቸው ዘለው ተነሱና አንዱ ቦርሳዬን ሌሎቹ ወገቤ ይዘው፣ ብሩክነርን ስለማታውቀው ነው፤ ቀልደኛ ሰው ነው፤ እባክህን ተመልሰህ ተቀመጥ ብለው ተማጸኑኝ። ትንሽ ከተግደረደርኩ በኋላ፣ በልቤ ይሄ የነጫጭባ ውላጅ ሁሉ፣ ልበ ደንዳና ኩሩ ያበሻ ልጅ መሆኔን ዐሳየሁት፣ አልኩና ተመልሼ ተቀመጥኩ። ድርድሩም ቀጠለ።

የቡናው ገንዘብ ጉዳይ ለረጅም ዓመታት ሲያነጋግር የቆየ ጉዳይ ነበር። እንደማስታውሰው ያለአግባብ ከሒሳባችን ወጭ አድርገው የወሰዱትን ስድስት ሚሊዮን ዶላር አስመለስናቸው። ገንዘቡን በቁጥጥራችን ሥር ስላደረግነው እኛን ሳያስፈቅዱ ከሒሳቡ ውጪ አድርገው መውሰዱን አስቆምናቸው። የገንዘቡ አስተዳደር ጉዳይ ከንግድ ሰዎች ከነብሩክነር ወደ

ባንኮቻቸው ተላለፈና ከባንኮቻቸው የበላይ ኃላፊ ከዶክተር ካሚንስኪና ከውጭ ንግድ ባንካቸው ፕሬዚዳንት ከዶክተር ፓልዘ ጋር እንነጋገርበት ነበር፡፡ ከሁለቱ ባለሥልጣኖች ጋር ከፍተኛ ወዳጅነት መሠረትን፡፡ ከሁለቱም ጋር እናደርገው የነበረው ውይይትና ድርድር በጣም ቀጥተኛና የታወቀ የባንክ አሠራርን የተከተለ ስለነበር የነበረንን ወዳጅነት ልባዊ አደረገው፡፡ ከብሩክነር ጋር ያደረግሁትን ፍጥጫ ሳይሰሙ የቀሩ አይመስለኝም፣ ምክንያቱም ከነሱ ጋር በምናደርገው ንግግር መረጃ ወይም ሎጂክ ቁልጭ አድርጎ ከሚያሳየው ውጭ በማድበስበስ ወይም በመብለጥለጥ አይቀርቡኝ ስለነበር ነው፡፡ ሰዎቹ የተዋጣላቸው የባንክ ባለሙያዎች ስለሆኑ ትክክለኛ አሠራር ይስፈን ብዬ ስለታገልኩ የልብ ወዳጃቸው አደረጉኝ ብዬ አምናለሁ፡፡

ብሔራዊ ባንክን ለቅቄ ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር ከተዛወርኩ በኋላ ላይፐዚግ ከተማ ለሥራ ጉዳይ ሄጄ በነበረበት ወቅት ዶክተር ካሚንስኪ ሊጠይቀኝ ከበርሊን ተነስቶ መጥቷል፡፡ ሁለቱም ሰዎች በሥራቸው ምስጉንና በጣም የተከበሩ፣ በጠባያቸው ደግሞ ጨዋ ስለነበሩ ምሥራቅ ጀርመንና ምዕራብ ጀርመንን ከተዋሃዱ በኋላ ምሥራቅ ጀርመንን ያገለገሉት ባለሥልጣኖች ዐይናችሁ ላፈር ሲባሉ ሁለቱን ሰዎች ምን ይውጣቸው ይሆን? ብዬ እሰጋላቸው ነበር፡፡ እነሱም በበኩላቸው ታደሰ በደርግ መንግሥት ውስጥ በማገልገሉ እንደ ኀጢአት ተቆጥሮበት ይሄኔ ተወርውሮ ይሆናል ብለው ማሰባቸው አይቀርም፡፡

ሰውን ወርውሮ ስለመጣል ሲወሳ የብሔራዊ ባንክ የአስመራ ቅርንጫፋችን ኃላፊ የነበረው ፍቅረየሱስ ገብረክርስቶስ ትዝ ይለኛል፡፡ ብሔራዊ ባንክ እንደተዛወርኩ ባንኩ ውስጥ ያሉት ሙያተኞች እነማናቸው? ብዬ ፋይል ስመረምር ካገኘኋቸው የተዋጣላቸው ሠራተኞች መካከል አስመራ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ ፍቅረየሱስ አንዱ ነበር፡፡ አዲስ አበባ አምጥቼው ከተለማመደ በኋላ የመምሪያ ኃላፊ ላደርገው ፈለግሁና ለመዛወር ዝግጁ እንደሆነ ብጠይቀው፣ ብትተወኝ

ይሻለኛል፣ እዚህ የምጦራቸው እናትና አባት አሉኝ፣ በገንዘብ አቅርቦት ረገድ ለሰፊ ቤተሰብ ኃላፊ ስለሆንኩ እዚሁ አስመራ ብሆን ይሻለኛል፣ በተጨማሪ አዲስ አበባ ከፍተኛ የቤት እጥረት አለ ስለሚባልና እዚህ የራሳችን ቤት ስላለን እባክህን ተወኝ ይለኛል፡፡ ቅር እያለኝ እሺ አልኩት፡፡ ከዓመታት በኋላ የአስመራን የውጭ ምንዛሪ መቆጣጠሪያ ጽሕፈት ቤትን ሙሉ የብሔራዊ ባንክ ቅርንጫፍ አድርገን አደራጀነውና ፍቅረየሱስን የቅርንጫፉ ኀላፊ አደረግነው፡፡ የምንኮራበት የሥራ ኃላፊ ነበር፡፡ የኤርትራ ተገንጣዮች ሥልጣን ከያዙ በኋላ ማእከላዊ ባንክ ማቋቋማቸው ስለማይቀር ፍቅረየሱስን አሠልጥነን አስረክበናቸዋልና አዛዥ አድርገው ይሾሙታል ብዬ ገምቼ ነበር፡፡ የት እንደደረሰ የሚነግረኝ ሰው ሳላገኝ ለብዙ ዓመታት ከቆየሁ በኋላ የብሔራዊ ባንክ ሠራተኛ ከነበረ አንድ ሰው ጋር በምኖርበት በኦታዋ ከተማ ተገናኘንና ስለፍቅረየሱስ የሚያውቀው ነገር ካለ እንዲነግረኝ ጠየቅሁት፡፡ እነኢሳያስ ሥልጣን እንደያዙ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ተባብረህ ሠርተሃል ተብሎ ሦስት ወር ድንጋይ ሲያስፈልጡት አቆይተውት በተራ የባንክ ጸሓፊነት እንደመደቡት ነገረኝና በጣም አዘንኩ፡፡ አፍሪቃ የሰው መቀመቅ ከመሆን የምትገላገዩው መቼ ይሆን? አልኩኝ፡፡ የኛ የሶሻሊዝም አይዶሎጎች አሜሪካን ሰው በላው አገር ይሉት ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር ሰው በላ አገሮች ያሉት አፍሪቃ ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ካልተማመንንና የእርምት እርምጃዎች ካልተወሰዱ በቀር አፍሪቃ ልጆች አይወጡላትም፡፡

ወደ ምስራቅ ጀርመን ታሪካችን ስንመለስ፣ ብዙም ሳይቆይ የሰማነው ምስራቅ ጀርመኖች ከኛ የወሰዱትን ቡና አገራቸው ሳያስገቡ በውጭ ምንዛሪ እንደሸጡት ነው፡፡ በተጨማሪ የተረዳነው ደግሞ በወሰዱት ቡና ምትክ ለሚሊሺያኖቻችን ያቀረቡት ልብስ እራሳቸው ያመረቱት ሳይሆን ከደቡብ ኮሪያ በርካሽ እንደገዙትና ብዙ እንዳተረፉብን ነበር፡፡

በኢትዮጵያና ሶማልያ መካከል ጦርነት ሲነሳ ጀርመኖች የታያቸው በአጋጣሚው ተጠቅመው ለአገራቸው ትርፍ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት

ስለነበር ክፍት ሆኖ ባገኙት ቀዳዳ ሁሉ ተሹለክልከው በመግባት ተጠቅመዋል፡፡ ይህ አባባል ሶማሌዎችን ለማባረር በተደረገው ርብርቦሽ ምስራቅ ጀርመኖች የነበራቸውን የማይናቅ አስተዋፅኦ ለማቃለል አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ የክፉ ጊዜ ወዳጆቻችን ስለሆኑ ለምን የሚሉንን ሁሉ አንፈጽምም? የሚለው አቀራረብ ተራ የዋህነት ከመሆን አልፎ በነሱም በኩል ቢሆን ንቀትን የሚያተርፍ አቋም ነው፡፡

የውጭ ንግድ ሚኒስትር በነበርኩበት ወቅት በኢትዮጵና በምሥራቅ ጀርመን መካከል የነበረውን የንግድ ግንኙነት ማስተባበርና መከታተል አንዱ ኃላፊነቴ ስለነበር ቀደም ብሎም ከምሥራቅ ጀርመን ሰዎች ጋር የነበረኝ የሥራ ግንኙነት በሌላ መልኩ ቀጠለ፡፡ ባንክም ሆኜ አውቀው እንደነበረው የምሥራቅ ጀርመን ባለሥልጣኖች በተቻለ መጠን የሚፈልጓቸው ምርቶች ከኛ መውሰድና በምትኩ በቀላሉ በውጭ ምንዛሪ መሸጥ ያቃታቸውን ምርቶቻቸውን እንድንገዛቸው መገፋፋት ነበር፡፡ በኛ በኩል እናደርገው የነበረው ትግል በቀላሉ በውጭ ምንዛሪ የምንሸጣቸውን ምርቶች በእቃ ለእቃ ልውውጥ ሊስት ውስጥ እንዳይገቡ መከላከል ነበር፡፡

ውጭ ንግድ ሚኒስቴር በተዛወርኩበት በመጋቢት ወር፣ 1979፣ ፔዦ-1 አውቶሞቢሌ ትገጭና ተሠርታ እስከምትወጣ ድረስ ከሥራ ሰዓት ውጭ ለሳምንታት እግረኛ እሆናለሁ፡፡ ከዚያም በውስት መኪና ለጥቂት ወራት ስገለገል ቆየሁ፡፡ ደግነቱ የገጨኝ ሰውዬ ኢንሹራንስ ስለነበረው መኪናዬ የተሠራችበትን ሒሳብ ሊከፍልልኝ ቻለ፡፡ የስምንት ዐይን ያልከፈቱ ሕፃናት ወላጆችን፣ በተለይ የባለቤቴን ውድ እህት አሳመረችን ወደሞት አፋፍ ይዛ ልትነጉድ የነበረችውን ተሽከርካሪ መንዳቱ ሁላችንንም ስለዘገነነን እኔና ባለቤቴ ተመካከርንና እንድንሸጣትና በምትክዋ ሌላ እንድንገዛ ወስነን ሸጥናት፡፡ መኪና የመግዛት እቅድ አለኝ ስል የሰማ የሚኒስቴሩ ሠራተኛ ምሥራቅ ጀርመኖች የሚሸጧት ያገለገለች መኪና አለቻቸው፤ እንደሚታወቀው በመንግሥት መመሪያ መሠረት መኪናዋን መሸጥ ያለባቸው ለመንግሥት ነው፤ መንግሥት ከነሱ ከገዛው በኋላ አንተ

ከመንግሥት ልትገዛት ትችላለህ ብሎ ይጠቁመኛል። በሌላ በኩል ደግሞ መኪና እንደምፈልግ ሄዶ ለጀርመኖቹ ይነግራቸዋል። እነሱም ቢሆኑ የመኪና አደጋ እንደደረሰብኝና መኪናዬ ከአገልግሎት ውጭ መሆኗን ሳይሰሙ የቀሩ አይመስለኝም። ስለዚህ እኔን የረዱ መስለው ባጋጣሚው ለመጠቀም ያስቡና አስፈላጊውን ሁሉ በወቅቱ አከናውነው መኪናዪቱን ለመንግሥት ሸጧት። እኔም መኪና እንደሌለኝ ለመንግሥት ገልጬ ከምሥራቅ ጀርመኖች የተገዛችዋ ቶዮታ እንድትሸጥልኝ አመለክታለሁ። ተፈቀደልኝና ገዛኋት። ወያኔ በሥልጣን ኮርቻ ከተፈናጠጠ በኋላ በደርግ መንግሥት ሥር ያገለገሉ ባለሥልጣኖችን ኀጢአት በመብራት ሲፈለግ እኔም ከመንግሥታዊ ድርጅት ተሽከርካሪ ገዛ ተብዬ ክስ ተመሥርቶብኛል።

አውቶሞቢሏን አንድ ወይም ግፋ ቢል ሁለት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስለመኪናዋ መሸጥ መረጃ የሰጠኝ የሚኒስቴሩ ሠራተኛ ይመጣና ምሥራቅ ጀርመኖች የበርበሬ ጭማቂ እቃ በእቃ ለውጥ እንዲሸጥላቸው ይፈልጋሉና ብንተባበራቸው ምን ይመስልሀል? ይለኛል። የተጠቀሰውን ምርት በውጭ ምንዛሪ ካልሆነ በቀር በተባለው ዘዴ አንሸጥም ብለናቸው ፋይሉ የተዘጋ መስሎኝ ነበር። በነሱ አስተሳሰብ መኪና እንዳገኝ ስለረዱኝ ይህን እንደ ውለታ ቆጥሬላቸው ሽያጬን እንድፈቅድላቸው መቅረባቸው ነበር። የበታች ሠራተኛዬም የነሱ ጥቅም ጠባቂ ሆኖ መቅረቡ ነበር። ደጋግመው ሞከሩ ነገር ግን በምንም ዓይነት አቋማችን አይለወጥም አልኳቸው። በአቋማችን እንድንጠነክር ያደረገኝ በጥቅም መደለልን ተገን አድርገው በመቅረባቸው ነበር። እኔን በዚህ ዘዴ እንደቀረቡኝ ሁሉ ይሄኔ በየቢሮው ሲልከሰከሱና ሲያልከሰክሱ ይውላሉ ብዬ ገመትኩ።

በሁለቱ አገሮች መካከል ስለሚካሄደው የንግድ ግንኙነት ለመወያየትና ለመደራደር የሁለቱ አገሮች የንግድ ሚኒስትሮች በየዓመቱ በአዲስ አበባና በምሥራቅ በርሊን እያፈራረቁ እንዲገናኙ ስምምነት ነበር። ውጭ ንግድ ሚኒስቴር በሄድኩ በሁለተኛው ዓመት ስብሰባው ሊደረግ የታቀደው

በበርሊን ሲሆን ዝግጅቱ በሁለቱም ወገኖች በኩል ተጧጡፎ እያለ በጋራ የወሰንነው የስብሰባው ቀን መሰረዙን ያስታውቁኛል፡፡

በነበረው አሠራር መሠረት ሚኒስትሮቹ ከመገናኘታቸው በፊት የንግድ ግንኙነት ያላቸው የሁለቱ አገሮች መንግሥታዊ የንግድ ድርጅቶች አዲስ አበባ ከሚገኘው የምሥራቅ ጀርመን የንግድ ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ልዑካን ጋር ተገናኝተው ይወያያሉ፡፡ ጽሕፈት ቤቱ ምሥራቅ ጀርመን ካሉት የንግድ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እያደረገ በኛ በኩል ስላሉት ሁኔታዎችና አቋሞች ያስተላልፍና መልስ ሲያገኝ ለሚመለከታቸው የንግድ ድርጅቶቻችን ያሳውቃል፣ ይደራደራል፡፡ እንዲሁም በርሊን የሚገኘው የውጭ ንግድ ጽሕፈት ቤታችን ከጀርመኖች ያገኘውን መረጃ ለዝግጅቱ እንጠቀምበታለን፡፡ በዚህ መንገድ ሚኒስትሮቹ ከመገናኘታቸው በፊት አብዛኞቹ ጉዳዮች እልባት ያገኙና የሚኒስትሮቹ ግንኙነት ወዳጅነት ለማጠናከር ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በድርጅቶች ደረጃ መፍታት ያልተቻሉ ጉዳዮች ካጋጠሙም በስብሰባው ወቅት ሚኒስትሮቹ ተወያይተው እንዲፈቷቸው ይደረጋል፡፡ በሚኒስትሮቹ ደረጃ መፍታት ያልተቻለ ችግር ወይም ዐቢይ ጉዳይ ካጋጠመ ወደ ሁለቱ አገሮች ከፍተኛ የፖለቲካ ባለሥልጣኖች ይመራና ውሳኔ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

እላይ የተጠቀሰው ዝግጅት በሚደረግበት ዓመት የምሥራቅ ጀርመን ሰዎች በአንዳንድ ጉዳዮች መንገድ እንድንለቅላቸው ይጠይቁና ሳይሳካላቸው ይቀራል፡፡ የፈለግነውን ካላገኘን ስብሰባውን ማድረግ አይጠቅመንም ይሉና ሳያማክሩን ስብሰባውን ይሰርዛሉ፡፡ ሚኒስትሩ መስሎት የነበረው፣ በምን ተቀይማችሁ ነው? ምን ብናደርግላችሁ ቁርጥ የስብሰባ ቀን ትነግሩናላችሁ? ብለን እንድንለማመጣቸው ነበር፡፡ እላይ እንደጠቀስኩት የስብሰባው ቀን የተቆረጠው በሁለቱም ወገኖች ስምምነት ሆኖ ሳለ አንዱ ወገን ብቻውን ስብሰባውን መሰረዝ አይችልም፣ በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገው ውል ተጥሷል ብዬ ተቃውሞ አቀረብኩ፡፡ ልምምጫ ሳይሆን ተቃውሞ ሲገጥማቸው ተለዋጭ ቀን ወስነን እናሳውቃችኋለን አሉን፡፡ የለም፣ ይህ

በቂ አይደለም፤ በጋራ የወሰንነውን የስብሰባ ቀን መሰረዛችሁ ጥፋት መሆኑን አምናችሁ ይቅርታ ካልጠየቃችሁን ስለ ተለዋጭ የስብሰባ ቀን መነጋገር አንችልም፤ ተለዋጩንም ቀን ቢሆን ለብቻችሁ የመወሰን መብት የላችሁም አልናቸው:: በቃል ይቅርታ ጠየቁን:: ተቃውሟችንን የገለጽነው በጽሑፍ ስለሆነ መልሳችሁን በጽሑፍ ማግኘት አለብን አልናቸው:: እኛን የበታች እራሳቸውን የበላይ አድርገው ከማየታቸው የተነሳ በራሳቸው ላይ የጠመጠሙትን ችግር መፍታት ተሳናቸው:: ሁኔታው ወደ ፖለቲካ ችግር ተሸጋገረ:: የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በጉዳዩ ገቡበት:: መንግሥቱ ዘንድ ደርሶም እንደሆን የማውቀው ነገር የለም:: በወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትራችን ለነበረው ለብርሃኑ ባይህ በኛ በኩል ስላለው አቋም ገልጬለት ካዳመጠ በኋላ ወዳጆቻችን ስለሆኑ ብናልፋቸው ይሻላል አለኝ:: በጽሑፍ ይቅርታ ካልጠየቁን እንደገና ንግግር አልከፍትም አልኩት:: በመጨረሻም ምንም ማድረግ ስላልቻሉ የጠየቅነውን የይቅርታ ደብዳቤ ጻፉና ተለዋጩ የስብሰባ ቀን በስምምነት ተቆረጠ::

ድርጊታቸውን አቃልዬ ወይም አሳንሼ ማየት ያልፈለግሁበት ምክንያት ሚኒስትሩ ስብሰባ እንዲደረግ ከፈለጋችሁ እኛ የምንጠይቀውን ለመፈጸም ዝግጁ እስከሆናችሁ ድረስ ብቻ ነው ማለቱ ሁለቱ አገሮች ከተስማሙበት ፕሮቶኮል ውጭ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ስብሰባው የሚደረገው አንድም የንግድ ድርጅቶቹ መፍታት ያልቻሏቸውን ጉዳዮች ለማየት መሆኑ እየታወቀ ባከራካሪ ነጥቦች ላይ አስቀድሞ ካልተስማማችሁ መባሉ ሥነሥርዓትን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ፣ ተጽዕኖ በማምጣት ፍላጎታቸውን ለማርካት መሞከራቸው ክብራችንን ስለሚነካ ነው:: ምንም እንኳን እኛ በልማት ኋላቀር ብንሆንም ድርድሩ በሁለት ነጻ አገሮች መካከል በእኩልነት የሚካሄድ እንጂ የጌታና ሎሌ ግንኙነት አለመሆኑን ለማስገንዘብና ትምህርት ማስተማር ይገባል ብዬ ስላመንኩበት ነበር::

እኔ ወደ ውጭ ንግድ ከመምጣቴ በፊት የጀርመኖቹ የውጭ ንግድ ሚኒስትር ሥራ ይበዛብኛል እያለ በሁለቱ አገሮች ስብሰባ ላይ አይገኝ

ስለነበር በውጭ ንግድ ሚኒስትሩ የሚመራው የኛ ልዑካን ቡድን በበርሊን ቆይታው ይነጋገርና ይደራደር የነበረው በውጭ ንግድ ምክትል ሚኒስትራቸው ከሚመራ ቡድን ጋር እንደነበር ከሚኒስቴራችን ሠራተኞች ተረድቼ ስለነበር እኔ ንግግር ማድረግ የምፈልገው ከአቻዬ ከሚኒስትሩ ጋር ነው ብዬ አስቀድሜ አስጠንቅቄ ስለነበር በርሊን ስንደርስ የተቀበለኝ እራሱ ሚኒስትሩ ነበር፡፡ በኔ ደረጃ መደረግ ያለባቸው ውይይቶችና ድርድር ያካሄድኩት በመጨረሻም የተፈራረምኩት ከሚኒስትሩ ጋር ነበር፡፡

# የኢትዮጵያ መድን ድርጅት

ብሔራዊ ባንክ በምክትል አዛዥነት የተመደብኩት የገንዘብ ድርጅቶችና ዐሥራ ሦስቱ የመድን ድርጅቶች በተወረሱ ማግስት ነበር፡፡ የተወረሱትን የመድን ድርጅቶች ከበላይ ሆኖ እንዲያስተዳድር፣ እንዲቆጣጠርና እንዲያደራጅ ደርግ አምስት አባላት ያሉት ጊዜያዊ ቦርድ አቋቋመ፡፡ አባላቱ የሚከተሉት ነበሩ፣ ጥላሁን ኃይለሥላሴ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሰብሳቢ፣ መርስኤ እጅጉ ከፕላን ኮሚሽን፣ ሺፈራው በቀለና ሙሉጌታ ፋላስ ከመድን ድርጅት፣ ታደሰ ገብረኪዳን ከብሔራዊ ባንክ፡፡ የኮሚቴው ጸሐፊ ኢዮቤድ ጥበቡ ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር ከመደበኛ ሥራዬ ያላነሰ አድካሚና እልህ አስጨራሽ ሆኖ ያገኘሁት የመድን ዘርፍ ሥራ ነበር፡፡ የኮሚቴው አባላት አብዛኛዎቻችን ስለመድን አገልግሎት የምናውቀው በጣም ውስን ስለነበር ውሳኔዎች የምናስተላልፈው በኮሚቴው ውስጥ የነበሩት ሙያተኞችና የምንጋብዛቸው አስረጅዎች የሚነግሩንን እያዳመጥንና እየተማርን ነበር፡፡ ይህም ሆኖ ብዙ ስሕተት የፈጸምን አይመስለኝም፡፡

ዐሥራ ሦስቱን የመድን ድርጅቶች አጠቃሎ አንድ ድርጅት ለማድረግ የሚጠይቃቸው ብዙ ሥራዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ፣ የሠራተኛ አስተዳደር ፖሊሲና ደንብ፣ የአንደርራይቲንግና የካሳ ጥያቄ መስተንግዶ ፖሊሲና የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት አስቀድሞ ማመሳሰል ያስፈልግ ነበር፡፡ ጊዜያዊው

ቦርድ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን አቋቁሞ የማመሳሰሉን ሥራ እየሠራ እያለ ለመሆኑ የሚፈጠረውን ድርጅት ማን ሊመራው ነው? የሚለው ጥያቄ ከሁሉም በላይ ያሳሰበን ጉዳይ ነበር።

ኢንዱስትሪው ውስጥ ያሉት ባለሙያዎች እነማን ናቸው? ብለን ስንመረምር ዘርፉ በሰው ኃይል ረገድ የደኸየ መሆኑን ተረዳን። ዘርፉን የሚቆጣጠሩትና የሚመሩት በአመዛኙ የውጭ አገር ሰዎች አብዮቱ ሲፈነዳና ድርጅቶቹ ሲወረሱ ጥለው ሄደዋል። በርከት ያሉ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞች ደግሞ የድርጅት ባለቤት ስለነበራችሁ ሥራ ታውካላችሁ ተብለው ከሥራቸው ተገልለው፣ ከሙያቸው ተፈናቅለው በየቤታቸው ተቀምጠዋል፤ አንዳንዶቹም አገር ጥለው ኮብልለዋል።

ለአዲሱ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ለማግኘት ምን ማድረግ ይሻላል? ለሚለው ጥያቄ የእያንዳንዱን ድርጅት ጊዜያዊ ሥራ አስኪያጅና የድርጅቶቹን የሠራተኛ ተጠሪዎች ጠርተን ማንን ብናሾም ይሻላል? ብለን አስተያየታቸውን አንድ በአንድ እንጠይቅ በሚለው ተስማማን። ካነጋገርናቸው ሥራ አስኪያጆችና የሠራተኛው ተጠሪዎች ከሰማንያ በመቶ በላይ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ቢመደብ ድርጅቱን በሚገባ ሊመራው ይችላል ብለው ያላቸውን እምነት ገለጹልን።

ለደርጉ የአስተዳደር ጉዳይ ኃላፊ ለአለማየሁ ስለሁኔታው አስረድተን ኢየሱስ ወርቅን እንዲሾሙልን ጠየቅነው። ሁሉም ያመነበት ሰው ከሆነ ምንም ችግር የለም፤ ቦታውን ሊይዝ ይችላል፤ ሰሞኑን የተሿሚዎች ዝርዝር ስለሚወጣ የሱ ስም አብሮ ይወጣል፤ እስከዚያው እናንተው ጊዜያዊ ዋና ሥራ አስኪያጅ ብላችሁ መድቡትና ሥራውን መሥራት ይጀምር አለን። የመድን ሠራተኞችን በሙሉ ስድስት ኪሎ ዩኒቨርስቲ በራስ መኮንን አዳራሽ ሰብስበን ኢየሱስ ወርቅን ከሠራተኛው ጋር አስተዋወቅን። ተባብረው እንዲሠሩ አደራ አልናቸው።

ኢያሱስ ወርቅ ሠራተኛውንና የሥራ ኃላፊዎችን አስተባብሮ መድን ድርጅትን የማቋቋሙን ተግባር ሙሉ በሙሉ ተያይዞት ነበር። የሠራተኛው ሞራልና የመሥራት ፍላጎቱ ከፍተኛ ነበር። እስከ ውድቅት ሌሊት ድረስ በቢሮዋቸው እየቆዩ ይሠሩ የነበሩት ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቁጥር በርካታ ነበር።

ሆኖም በጥቂት ቀናት ውስጥ ይመጣል የተባለው የሹመት ደብዳቤ ሳይመጣ ይቀራል። አለማየሁን በየጊዜው እየሄድኩ አስታውሰዋለሁ። ለውጭ ግንኙነት ስኬታማነትም ቢሆን አንድ ሥራ አስኪያጅ ተጠባባቂ ከተባለ የጠለፋ ዋስትና የሚሰጡ ዓለም አቀፍ የመድን ድርጅቶች ተሿሚውን በጥርጣሬ ዐይን ስለሚያዩት ጥሩ አይመጣም እያልኩ እነዘንዝዋለሁ። ከአሁን በኋላ ጥቂት ቀኖች ቢቀሩ ነው እያለ ይሸኘኛል።

አንድ ቅዳሜ ምሽት ከታላቅ ወንድሜ ከዶክተር ብርሃኔና ከጓደኞቹ ጋር ራስ ሆቴል ተገናኝተን ቢራ እንጎነጫለን። የእንግሊዝ እግር ኳስ ጨዋታ ሰዓት ሲደርስ ቴሌቪዥን ያለበት ክፍል ሄደን ብናይ ምን ይመስላችኋል? እላቸውና ተያይዘን ወደ ፎቁ እንወጣለን። የኳሱ ፕሮግራም ካለቀ በኋላ የሁለት ሰዓት ዜና ስለሚጀመር ሰምተን ብንሄድ ይሻላል ተባብለን መጠባበቅ ጀመርን። ዜና አቅራቢው መጀመሪያ ያበሰረው በዛሬው ዕለት ደርግ ሹመት ሰጥቷል የሚል ነበር። ሁላችንም በጉጉት ጠበቅን። የተሿሚዎች ሊስት እየተነበበ ሄደና ዐሥራ ሦስተኛው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ብርሃነ ገብራይ በሚል ተደመደመ። ብራቅ እንደመታው ሰው በተቀመጥኩበት ደንዝዤ ቀረሁ።

አለማየሁን ምን መሥራታችሁ ነው? እንዴት ቃላችሁን ታጥፋላችሁ? ነውር አይደለም እንዴ? ብዬ አምርሬ ተናገርኩት። "እባክህን ምን ላድርግ ብለህ ነው? ተቸግሬ ነው፤ ያ ፍስሐ ደስታ ‹እናንተ ጓደኞቻችሁን እየሾማችሁ እኔን ችላ አላችሁኝ፤ ብርሃነን ለመድን ድርጅት ወይም ሞት›

ብሎ ግራና ቀኝ ስለተወራጨ ነው የኢየሱስ ወርቅን ምደባ ማጽደቅ ያልቻልነው» ይለኛል።

ኢየሱስ ወርቅ ተባርሮ ብርሃነ ገብራይ የተሾመ ዕለት አብዮት የሚለው ቋንቋ ማደንዘዣ ወይም ማታለያ ነው ብያለሁ። ስለሚጠብቀኝ ማጥ ዐይኔን የከፈትኩት የዚያን ዕለት ነው ለማለት እችላለሁ። በወቅቱ የነበረኝ ስሜት ከነዚህ ሰዎች ጋር ምን አዳረቀኝ? እዚያው ዓለም ባንክ ብሄድ ይሻለኝ ነበር ብያለሁ። በሌላ በኩል በአብዮት ስም የሚነግዱትን ለመቋቋም መዘጋጀት እንዳለብኝ ጥሩ ማስገንዘቢያ ሆነኝ።

ባለቤትነቱ የእነሃረጎት አባይ የነበረው ብሔራዊ ኢንሹራስ ከውጭ መድን ድርጅቶች ጋር ቀደም ብሎ የተዋዋለው ውል ያስከተለው የክፍያ መዘዝ ከአቅም በላይ ሆኖ ስላገኘነው ችግሩን እንዴት እንደምንወጣው ጊዜያዊ የኢንሹራንስ ቦርድ አባላትን በጣም የከበደንና ጭንቅላታችንን የበጠበጠ ጉዳይ ነበር። ስለውሉ እንዲያስረዳን የድርጅቱን የቀድሞ ሥራ አስኪያጅ ብርሃነ ገብራይን እየጠራን መግለጫ ይሰጠን ነበር። ባጭሩ ለመግለጽ፣ ብሔራዊ ኢንሹራንስ የመድን ውል ከሸጠ ወይም ከተቀበለ አንድ ዓለም አቀፍ ድርጅት የውሉን ቁራሽ ወይም ክፍልፋይ ይገዛል። ትርፍም ሆነ ኪሳራ ከሻጩ ድርጅት ጋር የጋራ ነው። የትርፉን ወይም ኪሳራውን መጠን የሚወስነው የተገዛው ክፍልፋይ መጠን ነው። ታዲያ ዳርዊን የተባለችውን የአውስትራሊያ ከተማ ኃይለኛ አውሎ ንፋስ ይመታትና ክስተቱ ከፍተኛ የኢንሹራንስ ካሳ ክፍያ ጥያቄ ያስከትላል። ብሔራዊ ኢንሹራንስ ሳያውቀው የገዛው እንዲህ ዓይነት ከፍተኛ ኪሣራ ሊያስከትል የሚችል ውል ነበር። በብሔራዊ ኢንሹራንስ ስም የተደረገው የካሳ ክፍያ ጥያቄ ከፍተኛና ከአቅም በላይ ነበር። አሁን ደርግ የሾመው ለዚህ ጥፋት መንስኤ የነበረውን ሰው ነበር።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ሥራ ከላይ ሆኖ የሚመራውና የሚቆጣጠረው ብሔራዊ ባንክ እንዲሆን ድርጅቱን ያቋቋመው አዋጅ ደነገገ፤ የጊዜያው ኢንሹራንስ ቦርድ የሥራ ተልእኮም አከተመ።

ብርሃነ እንደተሾመ እኔን አልፎ በመሄድ ግንኙነቱን ሙሉ በሙሉ ከዋናው አዛዥ ጋር አደረገ፡፡ የጊዜያዊው ቦርድ አጽድቋቸው የነበሩትን አንዳንድ አስተዳደር ነክ ፖሊሲዎችን ሰረዘና የድርጅቱ የበላይ ኃላፊ እኔ ስለሆንኩ ምክክርና ውይይት የምትሉትን አላውቅላችሁም ብሎ ሠራተኞቹን አገለላቸው፡፡ የሚያስገርመው ለወሰደው አጥፊ እርምጃ በዋቢነት ያቀረበው እኛው ያረቀቅነውን የድርጅቱን አዋጅ ነበር፡፡ አዋጁ ከሠራተኛ ጋር ተባበሩ፣ ተመካከሩ የሚል አንቀጽ ስለሌለው፣ የሕግ አዋቂ ስለሆንኩ፣ አሠራሬ ሕጋዊ ነው አለ፡፡ ነገሩ አቋሙን እስከደገፈለት ድረስ ዲያቢሎስ መጽሐፍ ቅዱስን ይጠቅሳል እንደሚባለው ዓይነት ነው፡፡ በሙሉ ልብና ኃይል ተሰልፎ የነበረው የመድን ድርጅት ሠራተኛና ኃላፊ እጁን ሰብስቦ አፉን ለጉሞ የተሻለ ቀን ያምጣ ብሎ አርፎ ተቀመጠ፡፡

በመስከረም 1971 የባንኩ ዋና አዛዥ ሆኜ ስመደብ ብርሃነ ገብራይ ወደ በላይ ጠባቂው ፍሰሐ ደስታ ዘንድ ይሄድና ከታደሰ ጋር መሥራት ስለማልችል እባክህን ገላግለኝ እንዳለው ሰማሁ፡፡ ወድያው አምባሳደር ተብሎ ወደ ውጭ ሄደ፡፡

አያሌው በዛብህ የመድን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ብዙ ነገሮችን ለማስተካከልና በምክክር ለመሥራት ተቻለ፡፡ ቢሆንም፣ አያሌው እልክ ስለሚያበዛ ከውስጥና ከውጭም ሰዎች ጋር ይጋጭ ነበር፡፡ አያሌውን ብዙ ጊዜ እንዳየሁት ስለወሰደው አቋም ሰውን ከማግባባት ይበልጥ ወደመከላከሉ ስለሚያደላ በተቃራኒው ጎራ የተሰለፈው ወገን ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስድ ይገፋፋል፡፡ ክርክሮችን አርግቦ ወይም አለሳልሶ በመያዝ ባላጋራውን መንገድ አስለቅቆ መጓዝ የሚቀናው ሰው አይደለም፡፡ እንዲያውም እንደዚህ ዓይነቱን አቀራረብ እንደድክመት የሚቆጥር ሰው ነው፡፡

አንድ ጊዜ አያሌው ከድርጅቱ የሠራተኛ ማኅበር ጋር ይጣላና ለእርቅ ቢሮዬ ድረስ ይመጣሉ፡፡ የማኅበሩ ሊቀመንበር ታፈሰ ቦጋለ አያሌው በአቋሙ ፍንክች ባለማለቱ ስለተብከነከነ፣ እኔም የአያሌውን አቋም ስሕተት

ስላገኘሁበት ታፈሰ ስሜቱን መቆጣጠር አቃተውና እንባው ዱብ ዱብ ማለቱን አስታውሳለሁ።

ሌላ ጊዜ ደግሞ አፍሪቃን ከሚያገለግለው ከኢንተርናሽናል የእንሰሳት ማእከል ወይም ከኢ ል ካ ጋር ካሳ ክፍያን አስመልክቶ ከፍተኛ ክርክር ይነሳል። እንግሊዛዊው የድርጅቱ ኃላፊ ጥያቄያችን ካልተስተናገደ ድርጅታችን ከኢትዮጵያ እንዲነሳ ለሚመለከታቸው ሐሳብ ማቅረብ እንገደዳለን ብሎ ያስፈራራል። እንግሊዞች በኢትዮጵያ ላይ ችግር ለመፍጠር አስተባባሪና ፊታውራሪ ሲሆኑ እናይ ስለነበር ኢ ል ካ አተካራ መፍጠሩ ብዙም አልደነቀኝም ነበር። ሆኖም የክርክራቸውን ይዘት ጠጋ ብዬ ስመረምረው ጥያቄያቸው በአስተያየት ሊስተናገድ የሚችል መሆኑን ተረዳሁኝ አያሌውን አግባብቼ ጉዳዩ እልባት እንዲያገኝ ያደረግሁ ይመስለኛል።

ሦስተኛ የማስታውሰው አያሌውና አበበ የነበራቸውን ጭቅጭቅ ነው። አበበ የሳንቲም መቅረጫ ፋብሪካ ስናቋቁም ቴክኒሽያን አድርገን የቀጠርነው ሠራተኛ ነበር። የአየር ኃይል ወታደር የነበረ ነው። ፋብሪካው ሥራውን ካገባደደ በኋላ የሠራተኛ ቅነሳ ስናደርግ አበበ ወደ መድን ድርጅት ይዛወራል። እሱም እንደአያሌው አትንኩኝ ባይነት ስለሚያበዛ ይጋጫሉ። አንድ ምሽት አያሌው ከባለቤቱ ጋር እራቱን ሊበላ ቪላ ቬርዴ ሬስቶራንት ይሄዱና ከአበበ ጋር ይገናኛሉ። አበበ የአያሌውን ማንቁርት አንቆ ይይዝና አሁን እዚህ አፍርጬ ብገድልህስ? ብሎ ይደነፋበታል። ሰው ሃይ ሃይ ብሎ ይገላግላቸዋል። አያሌው በቀጥታ ወደ መኪናው ያመራና ሽጉጡን መዞ ሄዶ አበበን በተቀመጠበት መትቶ ያቆስለዋል። አበበ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል ሲወሰድ አያሌው ደግሞ ስድስተኛው ፖሊስ ጣቢያ ተወስዶ ይታሰራል። ስለሁኔታው እንደሰማሁ አያሌውን ሄጄ ብጠይቀውም፤ አበበን የመጠየቁ ሐሳብ ግን ለምን እንዳልመጣልኝ አሁን ቁጭ ብዬ ሳስበው ይገርመኛል። ሥራ ላይ ብቻ በማተኮሬ አያሌው ቢፈናቀል የመድን ድርጅት ሥራ እንዳይበደል አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ አለብኝ ብዬ

ስለተነሳሁ ሊሆን ይችላል፡፡ አያሌው በዋስ ተለቀቀና የፍርድ ቤት ክርክር ቀጠለ፡፡ አያሌው ድርጊቱን የፈጸመው በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ እንደበየነለት ሰምቻለሁ፡፡

ሌላ ትዝ የሚለኝ አያሌውና በቀለ ታደሰ የፈጠሩት ከፍተኛ አተካራ ነው፡፡ ዓለም ባንክ ይሁን የአውሮጳ ማኅበረሰብ ከነፋስ ስልክ ትንሽ ዝቅ ብሎ የቁጠባ ቤቶች ማሠሪያ ገንዘብ ያበድራል፡፡ እዚያ አካባቢ መድን ድርጅት ካሳ ከከፈለባቸው በኋላ የሚረከባቸው ተሽከርካሪዎችንና ሌሎችንም ንብረቶች የማከማቻ መጋዘን አለው፡፡ በጸደቀው ፕላን መሠረት መኖሪያ ቤቶቹ አካባቢ የሚሠሩ መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛው መንገድ መጋዘኑ ያረፈበትን መሬት ገምሶ ያልፋል፡፡ እነአያሌው ተባበሩ ይባላሉ፡፡ አያሌው ሞቼ እገኛለሁ ይላል፡፡ በቀለ ታደሰ የቤቶቹን ሥራ ሂደት እንዲከታተል፣ እንዲያስተባብርና እንዲያስፈጽም በመንግሥትና በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተወከለ ሰው ነው፡፡ ከአያሌው ያላነሰ እልከኛ፣ በተራ አነጋገር ኃይለኛ ሰው ነው፡፡ እሳት ለእሳት ተገናኙና አገር ተጫጫሰ፡፡ በግልም ጭምር እንፈላለጋለን የተባባሉ ይመስለኛል፡፡ ቦታውን ዞሬ አይቼ፣ በእግሬ ረግጬ የማስታረቂያ ሐሳብ አቀረብኩና ውዝግቡ እንደረገበ አስታውሳለሁ፡፡

እዚህ ላይ እኔ ስለአያሌው ኃይለኛነት ብዙ ብዘበዝብም ቅሉ፤ ሰው ስለእኔ ምን እንደሚል አላውቅም፡፡ ደጋግሜ እንዳነሳሁት ጆሮ ለባለቤቱ ብዙ ጊዜ ባዳ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ እኛ ኢትዮጵያውያን ስለክርክርና የሐሳብ ልዩነት ያለን አመለካከት ደካማና የተዛባ ነው፡፡ የሚከራከረንን ወይም ካለን አስተያየት የተለየ ሐሳብ የሚገልጸውን በበጎ አናየውም፡፡ አልፎም እንደ ተቃራኒና እንደ ጠላት ስለምንቆጥረው ጤናማ ክርክርና ውይይት ማካሄድ አይሆንልንም፡፡ ስለሆነም ቂማችንና ሐሳባችንን በሆዳችን አምቀን መያዝ እንወዳለን፡፡ የታመቀ ነገር ሁሉ መፈንዳቱ የማይቀር መሆኑን እንዘነጋለን፡፡ መንገድ መልቀቅን እንደተሸናፊነት የማየት ዝንባሌ አለን፡፡ በነገራችን ላይ ይህ ድክመት የኛ ብቻ ይመስለኝ ነበር፡፡ ከአገር

ከወጣሁ በኋላ ድክመቱን እኛ ብቻችንን በሞኖፖል እንዳልያዝነው ተገንዝቤአለሁ።

ጥል፣ ጭቅጭቅ፣ አለመግባባት የሚበዛው በመሠረቱ በሰዎች መካከል መሠረታዊ የአስተሳሰብ ልዩነት ኖሮ ሳይሆን ካለመደማመጥና እራስን በሌላው ሰው ቦታ ላይ አስቀምጦ ካለማየት የሚመነጭ ችግር ነው። መተሳሰብ ሲባል እንደሌላው ሆኖ ማሰብ ማለት ነው። ሁሉም እኔ ልክ ነኝ ካለ የትም አይደረስም፤ ውጤቱ የሚሆነው የክፍፍል ፈርጆችን ማብዛትና ማባዛት ብቻ ነው። ሰው ሁሉ ሰላምን ይፈልጋል፤ መውደድንና መወደድን ይፈልጋል፤ በሕይወቱ ደስ ብሎት እንዲኖር ይፈልጋል። ማንም ስቃይን፣ መጠላትን፣ ጉስቁልናን፣ መራብን፣ መጠማትን፣ መታረዝን አይፈልግም። ታዲያ የሰው ልጅ ሁሉ የሚወደውና የሚጠላው በመሠረቱ አንድ ከሆነ ለምንድነው ለበጎ ተግባር መተባበር ያልተቻለው? በሌላ ላይ ስቃይ አዝንቦ ወይም ሲዘንብበት ዐይቶ እኔን ምንም አይነካኝም ብሎ ተዝናንቶ የሚቀመጥ ምን ዓይነቱ ሞኝ ወይም ተላላ ነው? መጽሐፉ በአንተ ላይ እንዲደርስብህ የማትፈልገውን በሌላው ላይ አታድርስ ወይም እንዲደርስበት አትመኝ ብሏል። ሁሉም ሃይማኖቶች ይህን ይሰብካሉ። ነገር ግን አማኝ ነን የሚሉ ሁሉ መርሁን ሲጥሱት ይታያሉ። ለምን? አንዱ የሕይወት እንቆቅልሽ ይህ ነው። የሰው ልጅ ስለጥፋት ሲያወሳ ስለማዕበል፣ ስለጎርፍ፣ ስለእሳተገሞራ፣ ስለሰማይ ድንጋይ እንጂ ወንድም በወንድሙ ላይ ስለሚያዘንበው ጥፋት ብዙም አይወሳም። ሰውን የሚያጠፋው ሰው ነው።

በመጨረሻ ትዝ የሚለኝ ስለአዲሱ የመድን ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት ሕንጻ ነው። እነአያሌው ያወጡትና እኛም ያጸደቅነው ፕላን ሕንጻው የኢትዮ-ሊቢያ ድርጅት የሚያመርተውን ነጭ የእብነበረድ ድንጋይ እንደሚለብስ ነበር። የሕንጻው ሥራ በሚያመረቃ ግስጋሴ ሄዶ እብነበረድ መለጠፍ ላይ ሲደረስ የኮንስትራክሽን ሚኒስትር ካሳ ገብሬ መለጠፍ ያለባችሁ በሚኒስቴሩ ሥር የሚገኙ ድርጅቶች የሚያመርቱትን ሸክላ ነው

እንጂ ነጩን እብነበረድ አይደለም ብሎ ሥራውን ያግዳል፡፡ ትእዛዝ የተሰጠው ለሕንጻው ኮንትራክተር ነበር፡፡ ኮንትራክተሩ አሻፈረኝ ብሎ መድን ድርጅት ባዘዘው መሠረት ቢገነባ ሚኒስቴሩ የሥራ ፈቃዱን ስለሚሰርዝበት ካሳ ካዘዘው ውጭ መሥራት የማይታሰብ ነበር፡፡ ካሳን ቢለማመጡት፣ ቢያሞካሹት፣ ቢያገላብጡት አሻፈረኝ ይላል፡፡ በመጨረሻ እነአያሌው ይመጡና ሁኔታውን ይገልጹልኛል፡፡

ከካሳ ጋር የነበረን ግንኙነት ውስጥ ውስጡን ሻካራ ስለነበር አቋሙን እንዲለውጥ ብጠይቀው እንደማይተባበረኝ ገመትኩ፡፡ በሌላ በኩል ካሳ ስለኔ የነበረው አመለካከት የለየለት እንዳልነበረም አውቃለሁ፡፡ ወዳጄ ብሆን ደስ እንደሚለው ግምት ወስጃለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ የሚፈልጋቸውን ነገሮች ባለመፈጸሜ ቅሬታ ስላለው የተከፋብኝ ሰው ነው፡፡ ድርጅቶቹ ብድር እንዳያገኙ ከልካይ አድርጎ ወስዶኛል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ቀደም ብሎ ተናግሬአለሁ፡፡ በሥሩ ስላሉት መንግሥታዊ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም በብሔራዊ ቁጥጥር ጉባኤ ላይ ሲናገር አመርቂ ውጤት ስለማስመዝገባቸው ባንክም ያውቅልናል ላለው በበኩሌ ስመልስ እኛ ይበልጥ የምናውቀው ብኩንነታቸውን ነው በማለቴ በጣም ተናዶብኝ እንደነበር አውቃለሁ፡፡ ቀደም ብሎ በጠቀስኩት በኑሮ ውድነት አስወጋጅ ኮሚቴ ላይ ያሳየነው ቲያትር ከሁላችንም አእምሮ የሚጠፋ አይደለም፡፡ ሁኔታው እዚህ ደረጃ ላይ መሆኑ እየታወቀ አሁን ሄጄ እንዲተባበረን ብጠየቀው አዎንታዊ መልስ ማግኘታችን በጣም አጠራጣሪ ነው፤ ቢሆንም፣ ይህን የመሰለ ሕንጻ ያልሆነ ማቴርያል አሽክመውት እንዳይበላሽ አስፈላጊውን ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለብኝ አልኩና ላነጋግረው ቢሮው ድረስ ሄድኩ፡፡

ኮንትራክተሩና አርኪቴክቱ አንድ አስጨብጠውኝ የነበረው ነጥብ ካሳ የሚለው ሸክላ ቢለጠፍ ብዙ ሳይቆይ እንሚረግፍ ነበር፡፡ ካሳ የወሰደው እርምጃ ሕገወጥና ከሥልጣኑ ውጭ ቢሆንም ወደ ላይ ሄጄ ከምከሰውና ሌላ የአተካራ መስኮት ከመክፈት የሚሻለው፣ ፈረንጆች እንደሚሉት፣

ትኩስና ቀዝቃዛ አየር እያናፋሁበት የጠየቅነውን እንዲፈጽምልን መሞከሩ የተሻለ ነው ብዬ ወሰንኩ::

ቡና ከጠጣንና የቆጡን የባጡን ጥቂት ከቀበጣጠርን በኋላ የመጣሁበትን ጉዳይ አስረዳሁት:: ቀጠሮ ስጠይቀው የጉዳዩን ጫፍ አስጨብጬው ስለነበር አስቦበት ጠብቆኝ ሳይሆን አይቀርም:: ብዙም ሳላናፋ፣ ግድየለም በጠየቃችሁት መሠረት ይፈጸማል አለኝና አስደሰተኝ:: ስለትብብሩ አመስግኜው የድል አድራጊነት ስሜት ተላብሼ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ:: ጉዳዩ እንደተሳካ ለአያሌው ደውዬ ስነግረው ምን ብታስነካው ነው? ብሎ ቢጠይቀኝ አፍዝ አደንግዝ መሆኑን ነገርኩት::

ሕንጻው አልቆ እንደተገባበት እኔ ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር ተዛወርኩ:: ከብሔራዊ ባንክ ገና እግሬን ከማውጣቴ ፍቅረሥላሴ ሚኒስትሮችን አስከትሎ ሕንጻውን ሊጎበኝና ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚችልበትን መንገድ ለመፈለግ ተነስቶ ይሄዳል:: ችግር ላይ መሆናችን እየታወቀ ለምንድነው እንዲህ ዓይነት ትልቅ ሕንጻ እንዲሠሩ የተፈቀደላቸው? ለምንድነው ነጭ እብነበረድ ድንጋይ እንዲለጥፉ የተፈቀደላቸው? አለና ጠየቀ:: ፈቃጅና ሠሪ ከፍተኛ ግሳጼ ደረሰባቸው:: እንደሰማሁት ካሳ ሲመልስ፣ እኔ እብነበረዱን እንዳይለጥፉ ታግዬ ነበር፤ ታደሰ ሰላስቸገረኝ ለመፍቀድ ተገደድኩ እንዳለ ነው:: የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ክቡ ሕንጻ እንዳለቀ የወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍስሐ ደስታ ሕንጻው ወደ ሆቴልነት የሚለወጥበት መንገድ አጥንታችሁ አቅርቡልኝ ብሎ እንደነበር ሰማሁ:: ከባንኮች ክበብ ፊትለፊት፣ ከብሔራዊ ወመዘክር ጎን ባለው ባዶ መሬት ላይ መለስተኛ ሕንጻ ሠርተን የገጠመንን የቦታ ጥበት ችግር ለማቃለል አስበን የሕንጻውን ፕላን ረቂቅ ከዝርዝር መግለጫ ጋር ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስትሩ ለተስፋዬ ማሩ አቅርበን መሬቱን እንዲፈቀድልን እንጠይቀዋለን:: ፈቃዱን ከሰጠን በኋላ በጎን ወደ ፍቅረሥላሴ ይሄድና ባንኮች ስላስቸገሩኝ መሬቱን ፈቅጃለሁ እንጂ ልፈቅድ አልፈለግሁም ነበር ይለዋል:: ፍቅሬ ቢሮው ድረስ ይጠራኝና መንግሥት ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ገጥሞታል፣

እናንተ ደግሞ ሕንጻ ሕንጻ ስትሉ እንሰማለን፣ ገንዘብ ከተረፋችሁ ለምን ለእኛ አትሰጡንም? ብሎኛል፡፡

የሕንጻዎቹን ጉዳይ አስታክኬ ስለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የተመለከትኳቸውን ሁለት ነጥቦች ማንሳት እፈልጋለሁ፡፡ በአብዛኛው ባለሥልጣን አእምሮ ውስጥ የሚጉላላው በሥሩ የተመደበውን ሰው እንዴት ጠፍሮ እንደሚይዘው እንጂ የምንዝሩ የሥራ ውጤት አመርቂና የተቃና እንዲሆን ጥረት ማድረግ ኃላፊነቱ ውስጥ መካተቱን አይገነዘበውም፡፡ ነጥቡን ቀደም ብሎ ያነሳሁት ቢሆንም ጉዳዩ መሠረታዊ ስለሆነ ተደጋግሞ ቢነሳ አይከፋም፡፡ ለኢትዮጵያ ኋላ መቅረት አንዱ ምክንያት ነው ብዬ ስለማምን በየቦታው ውይይት ቢደረግበት ይጠቅማል የሚል አመለካከት አለኝ፡፡ ሁለተኛው ነጥብ፣ ሌላው የጎላና የተሻለ ውጤት አስመዝግቦ ስናይ አንወድም፡፡ መስፍን ወልደማርያም እንዳለው እኛ ኢትዮጵያውንን የሚገዛን ፍልስፍና ማንም አይቀድመኝም፣ እኔም ማንንም አልቀድምም የሚለው ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ቀድሞ የተራመደ ካገኘን በሐሳባችን የሚጉላላው እሱ ላይ ለመድረስ ሳይሆን በመንገዱ ላይ ደንቃራ ጥለንበት እንዴት እንደምናሽመደምደው ነው፡፡ ለብሔራዊ ባንክ ቦርድ አባላት በየጊዜው አቀርባቸው በነበሩ ዘገባዎች ያስገኘናቸውን የሥራ ውጤቶች አባላቱ እንዲያውቁት አደርግ ነበር፡፡ አንድ ቀን አንዱ የቦርድ አባላችን፣ ካሳ ገብሬ «ባንክ ይህን አደረግሁ፣ ያንን ፈጸምኩ እያለ በየጊዜው ያሰለቸናል፣ ኤኮኖሚው ምን ላይ እንዳለ ያደባባይ ምስጢር ስለሆነ ባንክ ብቻውን ጠንካራ መሆን አይችልም» አለ፡፡ በመሠረቱ አባባሉ ከእውነት የራቀ ባይሆንም ያኔ ሰፍኖ በነበረው ሁኔታ አንጻር ሲታይ ግን ጥሩ መሥራት ጥሩ ያልሠሩትን ማሳጣት ስለሆነ ከሰልፍ የወጣችሁት ግሳጼ ይገባችኋል ማለቱ ነበር፡፡

ስለካሳ ከተነሳ ዘንድ ስለሱ ሌላ የማውቃቸውን አንዳንድ ነገሮችን ባክል ደስ ይለኛል፡፡ በሥራ ዓለም ካገኘኋቸው ከአእምሮዬ የማይጠፉ ሰዎች ካሳ አንዱ ነው፡፡ እንኳን ነቅቶ ቀርቶ ተኝቶም ቢሆን የሰውን ትኩረትና እይታ

የሚያስብ ሰው ነው፡፡ በተገኘበት ቦታ እራሱን ማእከል አድርጎ ቁም ነገርም ሆነ ቀልድ እሱ ዙሪያ እንዲሽከረከር የማድረግ ችሎታ አለው፡፡ እንደ ካሳ ከበደ እሱም አንደበቱ ርቱዕ ነው፡፡ ከስብሰባ ውጭም ሆነ ውስጥ መናገር የሚፈልገውን ቁም ነገር በደረቁ ሳይሆን በቀልድ አስመስሎ ወይም ድራማቲክ አድርጎ የማስተላለፍ ወይም የመግለጽ ችሎታ ያለው ሰው ነው፡፡ አባባሉ ሰምጦ የሚገባ ዓይነት ስለሆነ መልዕክቱን አድማጩ በቀላሉ ሊያልፈው ወይም አልሰማሁም ሊል የሚችለው ዓይነት አይደለም፡፡ ከሰማኋቸው ሁለቱን ላካፍል፡፡ የደርግ አባላት በየክፍለ አገሩ የበላይ ሆነው እንደተመደቡ የከፋው ተሰማ በላይ ሴተኛ አዳሪነትን የሚገታ መመርያ ያወጣል፡፡ ካሳ ለሥራ ጉዳይ ጅማ ሄዶ ሳለ ተሰማ ለካሳ ክብር የእራት ግብዣ ያደርጋል፡፡ ተጋባዥ ሁሉ እየሰማ፣ ካሳ "ጓድ ተሰማ፣ ብለህ ብለህ እንትንና እንትን እንዳይገናኙ አዋጅ አውጥተሃል አሉ" ይልና የደርጉ ተጠሪ የሠራውን ሥራ አፈር ድሜ ያስግጥበታል፡፡ እንደገባኝ የካሳ መልዕክት እንዲህ ዓይነቱን ሥር የሰደደ ማኅበራዊና ኤኮኖሚያዊ ችግር የሚፈታው አዋጅ በማውጣት ብቻ አይደለም ለማለት ነበር፡፡

ይህን መጽሐፍ በኦታዋ ከተማ እየጻፍኩ ሳለ የካሳን ማንነት የሚገልጽ አንድ ታሪክ ሰማሁ፡፡ እንደሚታወቀው ካሳ ከሌሎች የቀድሞው መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ለረጅም ጊዜ ያለፍርድ ታስሮ ነበር፡፡ በእስር ላይ በነበረበት ጊዜ ሥራ አልፈታም፡፡ ካቦነቱን ቀጠለ፡፡ ካሳ ካቦው የሚለው አባባል የመጣው ካሳ ካቦነትን እንጂ ሚኒስትር መሆንን የማያውቅበት ሰው ነው እየተባለ ይቀለድበት ስለነበር ነው፡፡ በካሳ አስተባባሪነትና መሪነት እስር ቤቱን ለማሻሻል ሰፊ ፕሮግራም ተዘረጋና ውጤቱ አመርቂ ከመሆን አልፎ ስፍራው፣ በወኅኒው ቤት አስተዳዳሪዎች አመለካከት፣ እዚያ ለታጎረው እስረኛ የመቅጫ ሳይሆን የእረፍትና መዝናኛ ማእከል ሆነ የሚል ቅሬታ ይቀርብና የማሻሻሉ ፕሮግራም እንዲቋረጥ ይደረጋል፡፡ ካሳ ቀጠሮ ይጠይቅና የወኅኒውን አስተዳዳሪ ሊያነጋግረው ይሄዳል፡፡ "ስማ፣ ሰውዬው፣ እኛ የደርግ ባለሥልጣኖች ተሞኝተናል፤ እዚህ እንደምንገባ አስቀድሞ ብናውቅ ኖሮ የሕንጻ ግንባታ ሚኒስትር በነበርኩበት ወቅት ይህችን ጎስቋላ

እስር ቤት ቤተመንግሥት አድርጌ አሠራት ነበር፤ አሁንም እናንተ አትሞኙ፤ በደንብ አስጨርሷት፣ እኔ አሁን የምሠራው እኮ ለናንተ ነው" ብሎ አስተዳዳሪውን የድንጋጤ ሣቅ ያስቀዋል። ሰውዬውም "እርስዎ የማይቻሉ ነዎት" ይልና የተጀመረውን ፕሮግራም እንዲቀጥል ፈቀደ ይባላል።

ስለካሳ አንድ ታሪክ ልመርቅ። ባንክ ሆኜ በአንድ ወቅት ለሥራ ጉዳይ ወደ አሰብ እንደሄድኩ በፍቅረሥላሴ ወግደረስ የሚመራ የሚኒስትሮች ቡድን በአሰብና አካባቢው የሥራ ጉብኝት ሊያደርግ ሄዶ ኖሮ አገኘቸዋለሁ። ካሳ እንደተለመደው የንጉሥ አጫዋችነቱን በሚገባ ተያይዞታል። ፍቅሬ ካሳ የሚለውን ሁሉ በትዕግስት ያዳምጣል እንጂ እንደመንግሥቱ አይንከተከትለትም። ግፋ ቢል ትንሽ ፈገግ ይልለታል። ወደ አዲስ አበባ በእነሱ አውሮፕላን እንድሳፈር ይጋብዙኝና አብሬ ተመለስኩ። አዲስ አበባ ደርሰን አውሮፕላኗ የተመደበላት ስፍራ ትደርስና ሞተርዋ ከጠፋ በኋላ ፍቅሬ ለመውረድ ተነስቶ እንደቆመ፣ "ስማ" ይለዋል ካሳን "እዚህ ድረስ ተሸክመን አምጥተንሃል፣ ካሁን በኋላ እራስህን ቻል" ብሎት ከአውሮፕላኑ ወርዶ ሄደ። ካሳ በቃላት ጨዋታ ወይም ጦርነት የሚሸነፍ ሰው እንዳልሆነና ሰውና ቦታ መርጦ ተስማሚ መልስ ሳያምጥ መውለድ የሚችል መሆኑን ሁላችንም ስለምናውቅ ለፍቅሬ ምን ሊመልስ ነው? ብለን በጉጉት ስንጠባበቅ የሚለው ጠፍቶት አፉ ሲተሳሰር አይተን ዛሬስ ካሳ እንኳ ተረታ ተባባልን።

ሶማሊያ የኢትዮጵያን ድንበር ጥሳ ገብታ ድሬዳዋ በደረሰችበትና የኢትዮጵያ ሕዝብ የውርደት ማቅ ተከናንቦ በነበረበት ወቅት ሚሊሺያ ለማሠልጠን ሥጋ ሜዳ የተሠራውን ሰፈር አስተባብሮ በአጭር ጊዜ ያሠራው ካሳ ነው። በማእከሉ የሠለጠኑት የኢትዮጵያን ጠላት ያባረሩ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ሳይሆኑ ዚምባብዌን ነጻ ያወጡት የሮበርት ሙጋቤና የጆሽዋ ንኮሞ ደፈጣ ተዋጊዎችም ናቸው። ካሳ ተራ ካቦ ብቻ ሳይሆን የቀውጢ ጊዜ አለኝታም መሆኑን ስላስመሰከረ ውለታው ለረጅም ጊዜ ሲታወስ ይኖራል።

# የመንግሥት እርሻዎችና ጣጣቸው

መሬትንና የትርፍ ቤቶችን የወረሰው አዋጅ እንደወጣ የእርሻ ምርት እንደሚቀንስ ያልተገመተ አልነበረም። የምግብና የጥሬ እቃ አቅርቦት አቆልቁሎ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ዝቅ እንዳይልና ብሎም አብዮቱ እንዳይቀለበስ በመፍራት መንግሥት በእርሻ ሥራ ውስጥ በቀጥታ እንዲሳተፍ ተወሰነ። ባንኩም ብድር እንዲሰጥ ስምምነት ተደረሰ።

ለመንግሥት እርሻዎች ብድር የሚሰጣቸው የእርሻና ኢንዱስትሪ ባንክ ነበር። የባንኩ የገንዘብ አቅም በጣም ደካማ ስለነበር ለእርሻዎቹ ይሰጥ የነበረውን ገንዘብ ያገኝ የነበረው ከብሔራዊ ባንክ በብድር መልክ ነበር። ብሔራዊ ባንክ ብድሩን ሲሰጥ የነበረው እምነት እርሻዎቹ የሚሰበስቡትን ምርት ሸጠው ገንዘቡን ለአበደራቸው ባንክ በወቅቱ መመለስ ስለሚችሉ ብሔራዊ ባንክም እንዲሁ ገንዘቡን ከተበዳሪው ባንክ ያለችግር መቀበል ስለሚችል ሁሉም ወገን ተጠቃሚ ይሆናል የሚል ነበር።

ምርት ተሰብስቦ ከተሸጠ በኋላ ተበዳሪው ባንክ ገንዘቡን አምጥቶ ያስረክበናል ብለን ብንጠብቅ ገንዘቡ የውሃ ሽታ ሆኖ ይቀራል። ምነው? ብንል፣ እርሻዎቹ መነሻ ካፒታል ስላልተሰጣቸው በእጃቸው የገባውን ገንዘብ ለሥራ ማስኬጃ ተጠቀሙበት፤ ለሚቀጥለው እርሻ ወቅት ዝግጅት በአጣዳፊ መደረግ ስለነበረበት ገንዘቡ በሥራ ላይ ውሏል፤ ምርት ከተጠበቀው በታች ሆኖ ስለተገኘ የባንክ ብድሩ ኪሳራ ለመሸፈን ውሏል፤ ወዘተ፣ የሚሉ ምክንያቶች ተደረደሩልን። በየዓመቱ ይሰጥ የነበረው ምክንያት ከሞላ ጎደል ከዚህ ያልተለየ ነበር። በአምሳ ሚሊዮን ብር የተጀመረው ብድር በየዓመቱ እያደገ መጥቶ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር።

በባንኮች ይዞታ ሥር የነበረው የገንዘብ መጠን በጥቅሉ ሲታይ ለተበዳሪ የሚሰጥ የገንዘብ ችግር ነበር ለማለት አይቻልም። የግሉ ክፍለ ኤኮኖሚ

በመዳከሙ ወይም እንዲዳከም በመደረጉ በተለይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብድር ሥራውን የማስፋፋት ችግር ስለገጠመው በብሔራዊ ባንክ ያስቀምጠው የነበረ ገንዘብ መጠኑ ከፍተኛ ነበር። ብሔራዊ ባንክ ለእርሻ ባንክ የሰጠው ብድር ንግድ ባንክ ሊጠቀምበት ያልቻለውን ነበር ለማለት ይቻላል። ስለሆነም ለእርሻ ባንክ የተሰጠው ብድር ብሔራዊ ባንክ ሥልጣኑን ተጠቅሞ ያወጣው ተጨማሪ ገንዘብ ስላልነበረ ለእርሻ ባንክ የተሰጠው ብድር በመሠረቱ የዋጋ ግሽበትን ሊያስከትል የሚችል አልነበረም። ሁኔታው ተለውጦ፣ ንግድ ባንክ የሰጠው ብድር መጠኑ ከፍተኛ እመርታ ቢያሳይ ኖሮ በብሔራዊ ባንክ ውስጥ ያስቀመጠው ገንዘብ መጠኑ በጣም ስለሚቀንስ ለእርሻ ባንክ የሚሰጠው ገንዘብ ኅብረተሰቡ ካፈራው ንዋይ እየተቆነጠረ የሚሰጥ ሳይሆን ብሔራዊ ባንክ በሕግ በተሰጠው ገንዘብ የመፍጠር ሥልጣን ተጠቅሞ ከሚያቀርበው ተጨማሪ ገንዘብ በሆነ ነበር። አሠራሩም የዋጋ ግሽበትን የሚያስከትል ይሆን ነበር።

ብሔራዊ ባንክ ገንዘብ የመፍጠር ሥልጣን ስላለው ባንኩን የሚመሩትና የሚስተዳድሩት ኃላፊዎች ችሎታና ጠንካራነት ኅብረተሰቡ ዐይኑን ከፍቶ ሊጠባበቀው የሚገባ ጉዳይ ነው። የባንኩ ፖሊሲና አሠራር ብልሹ ከሆነ የኤኮኖሚ ቀውስ ይከተላል። የደካማ ፖለቲካ ሰዎች ዓላማ ሕዝብን ደልሎና ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ለመመረጥ እስከሆነ ድረስ ባንኩ ከፖለቲካ ሰዎች ቁጥጥር ነጻ መሆን ይኖርበታል። ይህን ነጥብ ቀደም ብሎ የተጠቀሰ ቢሆንም ተደጋግሞ ቢነሳ አይከፋም።

የመንግሥት እርሻዎች ገንዘብ መውሰድ እንጂ መመለስ እንደማይሆንላቸው ስናይ ለመሆኑ አሠራራቸው እንዴት ነው? ብክነት አለ ወይ? መንግሥት በቂ ካፒታል ለምን አይሰጣቸውም? ለአክሳሪ እርሻዎች ባንክ ብድር መስጠት ይኖርበታል ወይ? የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎችን በአንክሮ መጠየቅ ጀመርን። በሌላ በኩል መንግሥት በበኩሉ የመንግሥት እርሻዎችን ማስፋፋት የእርሻው ዘርፍ ልማት አንኳር ስልት አድርጎ ወስዶታል። ምርት ከማግኘቱ ባሻገር ኋላቀር አሠራር የሚከተለውን ገበሬ

ዘመናዊ የእርሻ አሠራር ዘዴ የማስተማሪያ ዓይነተኛ ስልት ነው ተብሎ ተወስዷል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ጎን ለጎን ገበሬውን በማኅበር ማደራጀትና በመንደር ማስፈር ሊታለፍ የማይገባው ስትራተጂ ነው ተብሎ ታምኖበታል፡፡

አጋርፋ ላይ የተቋቋመው የመንግሥት እርሻ በመጀመሪያው ዓመት ጥሩ ምርት ከሰጠ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ይከዳና መደናገጥና ግራ መጋባት ይከተላል፡፡ እንደተረዳሁት መሬቱ ያካባቢው ገበሬዎች ለከብት ግጦሽ መድበውት የነበረ በጣም ሰፊ ሜዳ ነው፡፡ መገመት እንደሚቻለው ለአጋርፋ እርሻም የተሰጠው ብድር ዕጣው ከሌሎች የተለየ ሳይሆን ቀረ፡፡

እርሻዎቹ በቂ ምርት ስላለማግኘታቸው ሳነሳ ታላቅ ወንድሜ ብርሃኔ ይሰማል፡፡ የእርሻ ምሁር ነው፡፡ «የናንተ ባለሥልጣኖች ስለእርሻ ያልተገነዘቡት ዋና ቁም ነገር አለ፤ እርሻ እኮ በሁለት ሰዓት ተገብቶ በዐሥር ሰዐት ሥራዬን ጨርሻለሁ ተብሎ የሚወጣበት የሥራ መስክ አይደለም፣ አንድ ገበሬ ወይም የእርሻ ባለሙያ እጁን፣ እግሩን መንፈሱን ልቡን ለእርሻው ሃያ አራት ሰዓት መመደብ አለበት፣ እናንተ ይህን ከባድ ኃላፊነትና ከፍተኛ የሥራ ፍቅር የሚጠይቀውን ሥራ ጥቂት ሰዓት ብቻ በሚሠራ ለዚያውም በአልማጭ ቅጥረኛ ልታካሄዱት ትፈልጋላችሁ፣ አሠራራችሁ የማያዋጣ ነው፣ አጋርፋን በተመለከተ ደግሞ አንድ በቅጡ ያልተረዳችሁት ነገር አለ፣ ያካባቢው ገበሬ መሬቱን ያላረሰው እህል እንደማይሰጥ ስላወቀ ነው፣ የዝናብ እጥረት ይኖራል ወይም የአፈሩ ለምነት አብቅቶለታል ማለት ነው» ብሎ ያስረዳኛል፡፡ ባጭር ቋንቋ፣ ስለመንግሥት እርሻዎች ውጤታማነት ተጠራጣሪ እንድሆን አድርጎኛል፡፡ የማእከላዊ ፕላን ሰዎችና የመንግሥት እርሻዎችን በበላይነት የሚመሩትና የሚቆጣጠሩት ኃላፊዎች ይህን ያህል አርሰን ይህን ያህል ለማምረት አቅደናል እያሉ ሲናገሩ በልቤ እነዚህ የሕልም እንጀራ መጋቢዎች ማለት ከጀመርኩ ውዬ አድሬአለሁ፡፡ የእርሻዎቹ ሥራ አመራርና ውጤታማነት

እንዲሻሻል በተገኘው መድረክ መናገር፣ ተጠቅሞ ማሳሰብ መደበኛ ሥራችን ከሆነ ወሎ አድሯል።

አንድ ቀን ቢሮዬ ስልክ ይደወልና የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ኃላፊዎችን ይዤ በማግስቱ ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት በኤኮኖሚ ዘመቻ መምሪያ መሥሪያ ቤት በሚደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ እንድገኝ ትዕዛዝ ይደርሰኛል። በስብሰባው ላይ የተገኙት አንዳንድ ሚኒስትሮችና የዘመቻ መምሪያ ኃላፊዎች ነበሩ። ዘገየ አስፋውን የተካው አዲሱ የግብርና ሚኒስትር ገረመው ደበሌም አለ። የስብሰባው ሊቀመንበር መንግሥቱ ነው። የዘመቻ መምሪያ ኃላፊ ገሰሰ የመግቢያ ንግግር አደረገ። ስብሰባው የተጠራው በሁመራ እንዲጀመር የታሰበው የሰሊጥ እርሻ ችግር ስለገጠመው መንግሥት ሁኔታውን እንዲያውቀውና ለሚመለከታቸው መመሪያ ወይም አመራር እንዲሰጥልኝ ብሎ የእርሻ ሚኒስትሩ ስለጠየቀ መሆኑን ገለጸ። ኋላ እንደደረስኩበት ግን ገረመው መንግሥቱ ዘንድ ይሄድና እናንተ እጅ አጣጥፋችሁ ተቀምጣችሁ ባንክ አብዮት እየቀለበሰ ነው፤ ፕላን ፕላን ትላላችሁ፤ በፕላን የተፈቀደልንን ገንዘብ ባንክ ከልክሎናል፤ ስለሆነም ሁሉም ነገር ከአቅሜ በላይ ሆኖ ስላገኘሁት የመጣሁት ሁኔታውን እንድታውቀው ነው ይለዋል። መንግሥቱም በጣም ይናደድና አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ያዛል።

ገረመው ችግርህ ምን እንደሆነ አስረዳ ይባላል። ሰውዬው ሚኒስትር ተብሎ ከተሾመ በኋላ በቡና ቦርድ ስብሰባ ላይ አይቼዋለሁ። ስብሰባው ላይ ሲናገር አልሰማሁትም። በዚህኛው ስብሰባው ላይ አስረዳ ሲባል መጥፎ ቅጠል አንደበላች ፍየል የቆጡን የባጡን አንበለበለው። ድምጹ ቀጭንና ከፍ ሲያደርገው ጆሮ የሚሰረስር ዓይነት ስለሆነ፣ በተለይም የሚለው ነገር ላልጣመው ሰው መቼ በጨረሰ የሚያሰኝ ዓይነት ነው። የተናገረው ባጭሩ፣ እኛ ለመሥራት ተዘጋጅተን ሳለ ባንክ ገንዘብ ከለከለን፤ እጃችንን አጣጥፈን ቁጭ ብለናል፤ የእርሻው ወቅት እያለፈ ነውና ለባንክ ትእዛዝ ይሰጥልን የሚል ነበር። ገሰሰም ሚኒስትሩን ቢደግፍም እኛን ሙሉ በሙሉ

አሳልፎ ለመስጠት አልፈለገም:: መንግሥቱ በቁጣ ቃል፣ ተነስተህ አስረዳ ይለኛል:: እኛ ያልነው ብድር ከመስጠታችን በፊት ስለእርሻው ሥራ ምን እቅድ እንዳላቸውና ገንዘቡን እንዴት አድርገው ሊጠቀሙበት እንዳሰቡ እንዲገልጹልን፣ መንግሥት ምን ያህል የመነሻ ካፒታል እንደሚሰጣቸው እንዲነገረን፣ በአጠቃላይ መልኩ የወሰዱትን ገንዘብ ሰርተው በወቅቱ እንደሚመልሱልን ማረጋገጫ ወይም አሳማኝ ገለጻ ያደርጉልን አልን እንጂ እርሻ አይታረስ ለማለት ምንስ ሥልጣን አለን? ሚኒስትሩ ሰዎቹን አስተባብሮ እኛ ለጠየቅናቸው ጥያቄዎች መልስ መስጠት ሲገባው እኛን በመንግሥት ላይ መክሰስ መረጠ ብዬ ተናገርኩ:: ከዐሥራ ሁለት ዓመት በላይ ስለመንግሥት እርሻዎች የነበረው ጭቅጭቅና ንትርክ ተመሳሳይ ነበር:: መንግሥት በዚህ ጉዳይ ላይ ያጠፋው ጊዜና ገንዘብ በገበሬው፣ በአፈርና ተፈጥሮ ጥበቃ ላይ አውሎት ቢሆን ኖሮ የተሻለ ውጤት ይገኝ እንደነበር በጽኑ አምናለሁ::

ሁመራ ላይ ብዙ መቶ ጋሻ መሬት ሰሊጥ ከተዘራ በኋላ ሥራው ስላላዋጣ እርግፍ ተደርጎ ተተወ:: የከሰረው ገንዘብ መጠኑ በጣም ከፍተኛ ስለመሆኑ በቀላሉ መገመት ይቻላል::

አንድ ቀን መንግሥቱ ቢሮ ጥቂት ሰዎች የሚገኙበት ስብሰባ ተደርጎ በቡና እረፍት ጊዜ ውጭ ቆመን ሁለት ሦስት ሆነን እናወራልን:: መንግሥቱም ላቅ ካሉ ባለሥልጣኖች ጋር እንዲሁ ይጨዋወታል:: ድምፁን ከፍ አድርጎ “መሬትን አረንጓዴ በማልበሳችን ብቻ እርሻ የተስፋፋ፣ ምርት የተገኘ መስሎን ተታለልን” አለ:: ይህን የኑዛዜ ቃል የሰማሁት ባንክን ለቅቄ ለመሄድ ግፋ ቢል አንድ ዓመት ሲቀር ነበር:: ዐሥራ ስንት ዓመት ሙሉ ባንኮች ስንል የነበረውም በአንድ ዐረፍተ ነገር ቁልጭ አድርጎ ሲያስቀምጠው “አለቃዬ፣ ኑዛዜህን ተቀብዬ ይቅርታ አድርጌልሃለሁ” አልኩ፣ በልቤ::

ይህም ሆኖ መንግሥቱ ሙሉ በሙሉ ንስሐ ገብቶ ነበር ለማለት አይደለም:: ስለእርሻውም ሆነ ስለሌላው ዘርፍ መንግስት ያራምደው

የነበረውን ፖሊሲና የሚከተለውን አሠራር አንዴ ስለተዘፈቅንበት ምንም ማድረግ ስለማይቻል ያለን አማራጭ እንዳንሰምጥ መንቦጫረቅ ብቻ ነው የሚል ይመስል ነበር፡፡

እአአ የ1978ቱ የሶሻሊስት አገሮች ጉብኝት አልቆ አዲስ አበባ የተገባ ዕለት ምሳ የተበላው ቤተመንግሥት ነበር፡፡ በጉዞው ላይ የነበሩት ሁሉ፣ የአየር መንገድ ሠራተኞች ጭምር ተገኝተዋል፡፡ የምሳ ግብዣው አልቆ ከመለያየታችን በፊት መንግሥቱ የመሰነባበቻ ንግግር አደረገ፡፡ ሆድ ጠግቦ፣ አእምሮ በመጠኑም ቢሆን ነብዞ በጽሑፍ ላይ ቀደም ብሎ የሰፈረ ሳይሆን አፍ እንዳመጣ የሚደረግ ንግግር ትዝብት ላይ ሊጥል ይችላል፡፡ መንግሥቱ በዚያን ዕለት ያልተጻፈ ንግግር ነው ያደረገልን፡፡ ንግግሩን ሲጨርስ አንድ ቃል ገባ፡፡ እሱም፣ በአጭር ጊዜ ኢትዮጵያን በቡና ምርት ከዓለም አንደኛ እናደርጋታለን የሚል ነበር፡፡ እዚያ የነበረው ሰው በጣም አጨበጨበ፡፡ በበኩሌ ግን በጣም ደነገጥኩ፡፡ ለዚህም ሁለት ምክንያቶች ነበሩኝ፤ አንዱ ባንኮች በጣም ብዙ ገንዘብ በብድር መልክ እንዲሰጡ ይገደዳሉ የሚል ፍራቻ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ በቡና ላይ ከልክ በላይ ስለሚመካ ሚዛኑን ለማስተካከል ወደሌሎች የእርሻና ኢንዱስትሪ ምርቶች መሸጋገር መቻል አለብን የሚለው አስተሳሰብ ወይም አመለካከት ተቀባይነት ያገኘና ወደኋላ የማንመለስበት መስሎኝ ስለነበር ነው፡፡

የመንግሥት እርሻዎችን በማቋቋም የቡና ምርት ማስፋፋትን መንግሥቱ ሙጭጭ ብሎ ከያዛቸው የኤኮኖሚ ፕሮጀክቶች ዋነኛው ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ ትልቁ እርሻ ከፋ ውስጥ በበቃ የሚባለው ቦታ ነበር፡፡ መንግሥቱ ስለቡና የነበረውን አመለካከት የሚያውቁት ባለሥልጣኖች የጠየቅነውን ካልፈጸማችሁ ለመንግሥቱ እንነግርባችኋለን እያሉ ከማስፈራራት አይመለሱም ነበር፡፡ የኋላሸት ግርማ የቡናና ሻይ ልማት ሚኒስትር በነበረበት ወቅት ለበበቃ እንደተለመደው ብድር ይጠይቃል፣ እንደተለመደው እኛም ጥያቄዎቻችንን መደርደር አላቆምንም፤ እሱም

በፕላን የተያዘ ነውና ለምን እጠየቃለሁ ማለቱን አልተወም፡፡ ስለሆነም፣ ጥርስ ነክሶ በጥርስ ሊያስነክሰን ታጥቆ ተነስቷል፡፡

በዓመት ሁለት ጊዜ በሚደረገው የፕላን አፈጻጸም ግምገማ ላይ የዘመቻ መምሪያ ኢንስፔክተሮች እንደተለመደው የበበቃ የሥራ ውጤት አመርቂ አለመሆኑን ይገልጻሉ፡፡ የቡናና ሻይ ልማት ሚኒስትሩ የኋላሸት አፈጻጸማቸው ለምን እንደደከመ አስረዳ ይባላል፡፡ ጥፋቱ የኛ ሳይሆን የባንክ ነው፤ የጠየቅነውን ብድር በወቅቱ አይሰጡንም፣ የሥራ እቅዳችንና የገንዘብ ፍላጎታችን መንግሥት ባጸደቀው ዕቅድ ውስጥ ታይቶ እያለ ባንኮች ሀ ብለው የተደራረቡ ጥያቄዎች እያቀረቡ አስቸገሩን፤ መሥራት አልቻልንም፤ አንድ ነገር ቢደረግ ይሻላል ብሎ ይቀመጣል፡፡

"ለመሆኑ ታደሰ የታለ?" ይላል፣ መንግሥቱ፡፡ እዚህ ነኝ ብዬ እጄን አወጣሁ፡፡ በቁጣ ቃል፣ ተነስና አስረዳ አለኝ፡፡ ንግግሬን "ያቀረቡት የብድር ጥያቄ የባንክን የብድር መለኪያዎች ስለማያሟላ ብድር መስጠቱን አላመንበትም" ብዬ ስጀምር መንግሥቱ ቱግ ይልና "ያንተን እምነት ማን ጠየቀህ? ያንተ እምነት እዚህ ቦታ የለውም" ካለ በኋላ "አብዮታችንን የሚፈታተኑትን እንፋረዳቸዋለን" ብሎ ተናገረና ከመቀመጫው ተነስቶ ከአዳራሹ ወጣ፡፡

ስብሰባው የተደረገው ዘመቻ መምሪያ ዋና መሰብሰቢያ አዳራሽ ነበር፡፡ አዳራሹ ሦስት ወይም አራት በሮች አሉት፡፡ መንግሥቱ የስብሰባውን አዳራሽ ጥሎ ወደ ውጭ ሲወጣ እዚያ የነበረው ተከትሎት ወጣ፡፡ እኔ ተቀምጬበት በነበረው ስፍራ አጠገብ ባለው በር በኩል ማንም መውጣት አልፈለገም፣ ምክንያቱም ተሰብሳቢዎቹ በዚያን ወቀት እኔ አጠገብ መገኘት የሞትን አፍንጫ ተጠግቶ እንደማሽተት ዐይተውት ስለነበር ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም ከኔ ርቆ ለመሄድ የሚሽቀዳደም ይመስል ነበር፡፡ በዚያ ትልቅ አዳራሽ ብቻዬን ጉልት ብዬ ቀረሁ፡፡ ሁለት ሰዎች ብቻ ወደኔ መጡና አነጋገሩኝ፡፡ እነሱም ምክትል የገንዘብ ሚኒስትሯ ደስታ ቢሻውና የገንዘብ ሚኒስትሩና የባንኩ ቦርድ ሊቀመንበር ተስፋዬ ዲንቃ ናቸው፡፡ ደስታ

እንዲህ አለችኝ፣ "አንተ የምትለውን ሙሉ ለሙሉ እረዳለሁ፣ ችግሩ ሰውዬውን ሰዎች በጎን እየሄዱ ስለሚያሳስቱት ነው፤ አይዞህ" አለችኝ:: ደስታ የብሔራዊ ባንክ የሠራተኞች ማኅበር ሊቀመንበር በነበረችበት ወቅት ችግር ትፈጥርብኝ ነበር፣ ገንዘብ ሚኒስቴር ከሄደች በኋላም የባንክ ተቃዋሚ ሆነች በሚል እምነት ግንኙነታችን ይህን ያህልም አልነበረም:: በዚያች ቀውጢ ወቅት ግን አጠገቤ መጥታ አይዞህ ስትለኝ በጣም አከበርኳት፤ ለካስ ስለሷ የማውቀው በጎ ያልሆነውን ጎኗን ብቻ ነበር አልኩና እራሴንም ሳልታዘበው አልቀረሁም:: ተስፋዬም በበኩሉ ስለበበቃ እርሻ ብድር አንዳንድ መረጃዎችን አዘጋጅተህ ስጠኝና መንግሥቱን እኔ እራሴ ሄጄ አነጋግረዋለሁ አለኝ::

ከአዳራሹ ተቻኩሎ ከወጣው ሰው መካከል አንዳንዱ ከተማ ደውሎ ታደሰ አብዮታዊ እርምጃ ሊወሰድበት ነው ብሎ ይናገራል:: ወሬው ከተማውን በአንድ ጊዜ አዳረሰው:: ቢሮ ስመለስ አንድ የቅርብ ጓደኛዬ ቢሮ ድረስ ይመጣል:: ምን እግር ጣለህ? ብለው፣ አይ ክፉ ወሬ ስለሰማሁ መኖርክን ለማረጋገጥ ነው አለኝ::

ወሬ አስተላላፊዎቹ ብዙም አይፈረድባቸውም:: መንግሥቱ በስብሰባ ውስጥ አብሮት ስለተቀመጠ አንድ ባለሥልጣን እንዲህ ዓይነት ኃይለ ቃል በይፋ ሲናገር ከዚያን ቀን በፊት አልሰማሁም:: አብዮታችንን የሚፈታተኑትን እንፋረዳቸዋለን ማለት በዘመኑ ቋንቋ ለጥብስ እናደርሳቸዋለን ማለት ነው:: አንድና ሁለት የለውም:: እንደሚታወቀው ሌላው ተመሳሳይ አባባል አብዮታዊ እርምጃ እንወስዳለን ነበር:: ሁለቱም አባባሎች ትርጉማቸው አንድ ነው:: ጣረሞትን የሚጠሩ ናቸው::

ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ በተገደለ ጊዜ ጓደኞቹንና ወዳጆቹን ታዘብኩ እንዳልኩት ዛሬም እኔንም ሰው ሲሸሽኝና ከመቅጽበት ሲከዳኝ ሳይ አዘንኩ፤ ሰውን ታዘብኩ:: ሰው እራሱን ለማዳን የማያደርገው ነገር እንደሌለ አሁንም መሰከርኩ:: ጭቅጭቅ ስለፈጠረው ጉዳይ የነበረኝ አቋም ትክክል መሆኑን ስለማውቅ የመንግሥቱ ዛቻ አላሸበረኝም:: እነሱ መሣሪያ ይዘው

ቢመጡብኝ እኔ እውነትን ተገን አድርጌ እቋቋማቸዋለሁ፣ ዞሮ ዞሮ እውነት ታሸንፋለች ብዬ እራሴን አጽናናሁ:: የዛቻው ወላፈን ከቀዘቀዘም በኋላ በሥራዬ የበለጠ ተጋሁ እንጂ ተሸማቅቄ ወይም አኩርፌ ወደኋላ አልሸሸሁም::

ባንክን ከኢትዮጵያ ሕዝብ በአደራ ተረክቤ የማስተዳድረውና እንደዐይን ብሌን መጠበቅ ያለብኝ ድርጅት ስለሆነ የፖለቲካ ሰዎች በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንዳያበላሹት የተቻለኝን ሁሉ ማድረግ አለብኝ የሚል ጽኑ እምነት ነበረኝ:: ባንኩ አላማውን ስቶ የእድገት ሳይሆን የቀውስ መሣሪያ ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለከፋ መከራ እንደሚዳረግ በቂ ግንዛቤ ስለነበረኝ የኢትዮጵያ ሕዝብ አደራ እንዳልበላ የአባቴን አምላክ ጠብቀኝ እለው ነበር::

የኋላሸት በዚያው ሰሞን ከሚኒስትርነቱ ተነሳ:: ውስጠ አዋቂ ነን የሚሉ ሰዎች እንደነገሩኝ መንግሥቱ የኋላሸትን "ከሚሰሩልኝ ሰዎች ጋር ልታጣላኝ ትፈልጋለህ፣ ሥራ መሥራት ሲያቅትህ ድክመትህን በሌላ ሰው ላይ መላከክ ትወዳለህ፤ የያዝከው ቦታ ለአንተ አይገባም" ብሎ እንዳባረረው ሰማሁ:: ተስፋዬም መንግሥቱ ዘንድ ሄዶ ስለሚኒስቴሩ የብድር ጥያቄ ባንክ ስለወሰደው አቋምና ሚኒስቴሩ አቅርብ ስለተባለው መረጃ ገለጻ እንዳደረገ ዜናው ደረሰኝ::

# የፓርቲ አባልነት

ከጥቂት ወራት በኋላ መንግሥቱ ሊያነጋግርህ ይፈልጋል ተባልኩና ቢሮው ድረስ ሄድኩ:: ለምን እንደጠራኝ ምንም ዓይነት ሐሳብ አልነበረኝም:: ቢሮው ስገባ ያገኘሁት ያ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ የዛተብኝን መንግሥቱ ሳይሆን ያንን ለብቻው ሲያገኙት ትሑቱና አንደበተ ለስላሳው መንግሥቱን ነበር::

"ጓድ ታደሰ፣ እንግዲህ ለረጅም ጊዜ አብረን እዚህ ድረስ ተጉዘን መጥተናል፤ ብዙ ውጣ ውረድ አይተናል፤ አሁን አብዮቱ የደረሰበት ደረጃ በፓርቲያችን እየተመራን የኢትዮጵያን ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እመርታ የምናሳይበት ወቅት ላይ ነን፤ ታዲያ አንተን በተመለከተ ፋይልህን እንደማየው ከሆነ የፓርቲያችንም አባል አይደለህም፤ ለመሆኑ ስለአብዮታችንና ስለፓርቲያችን ያለህ አስተያየት ምንድነው?" ብሎ ይጠይቀኛል:: ለጥያቄው በምሰጠው መልስ ሌሎች ስለእኔ የተናገሩትን የሚያረጋግጥበት ወይም እኔን ነጻ የሚያወጣበት ወሳኝ ቀን መሆኑን ገመትኩ::

ወቅቱ የአብዮቱን ዐሥረኛ ዓመት ለማክበር ፓርቲና መንግሥት በከፍተኛ እንቅስቃሴ ላይ የነበሩበት፣ በሌላ በኩል ድርቅ አይሎ ድግስ ለማበላሸት ከደጋሽ ጋር ትንቅንቅ የያዘበት፣ ጠኔ ሕዝቡን እየጨረሰ ነው እየተባለ ያለዊስኪ ምን ድግስ ይኖራል? ተብሎ ስኮች ዊስኪ በብዛት የታዘዘበት፣ የቀይ መስቀል ባርኔጣዬን ደፍቼ ዐይን ያልከፈቱ ሕፃናት እንደዝንብ ሲረግፉ በዐይኔ ዐይቼ ያለቀስኩበት ወቅት ነበር:: ስለመዐቱ ያየነውን ለማሰማት ስንሞክር ድግሳችንን ሊያበላሹ ጸረአብዮተኞች ተሰልፈውብናል ተብሎ በጋዜጣ ርዕስ አንቀጽ የተጻፈበት ወቅት ነው:: በዚህ ታሪካዊ ወቅት ነበር መንግሥቱ ጠርቶ ያነጋገረኝ::

የኢትዮጵያ ሠራተኞች አደራጅ ኮሚሽን ኢ ሰ ፓ አ ኮ ከተቋቋመ ጀምሮ እጩ አባላት፣ ከዚያም አባላት ሲመለመሉ፣ ሲማማሉ ታደሰ ከሥዕሉ ውጭ ነበር:: ከዚያም የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ አባላት ሲመለመሉ ታደሰ የውጭ ሰው ሆኖ መታየቱ ቀጥሏል:: ባንኩ ውስጥ የነበሩት የፓርቲ አመራር አባላት፣ እነታምሩ ከበደ፣ ታደሰ እንዴት በፓርቲ አባልነት አልተመለመለም? ብለው ይቆረቆሩና የበላይ አካላትን ያነጋግራሉ:: የተሰጣቸው መልስ ታደሰ ዴሞክራት ስለሆነ ለኮሙኒስት ፓርቲ አባልነት አያመችም፤ ካላመነበት በስተቀር ሰው በነገረው መንገድ መሄድ ስለማይፈልግ እኛ ልናራምድ ለምንፈልገው ሥርዓት ተስማሚ ሰው

አይደለም የሚል ነበር። ልጆቹ ይህን ሲነግሩኝ በልቤ በጣም ደስ አለኝ። አንደኛ፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ጭንቅላት ይጠቀምበታል ብለው በመመስከራቸው የመንፈስ ኩራት ተሰማኝ። ሁለተኛ፣ ከሥራዬ እስካላፈናቀሉኝ ድረስ የፓርቲ አባል አለመሆኑን ወድጄዋለሁ። የኅብረተሰብ አደረጃጀትና ኤኮኖሚ እድገት ምስጢሩ ተገኝቷልና እናንተ ያለባችሁ የምትነገሩትን መከተል ብቻ ነው የሚለው በፍጹም ኅሊናዬ ሊቀበለው አልፈለግም። እነታምሩ የበላይ አካል ነገረን እንዳሉትም እኔ ጥያቄ መጠየቅ እወዳለሁ፤ ነጩን ጥቁር ነው ቢሉኝ አይዋጥልኝም። ስለሆነም የሥርዓቱ አቀንቃኞች የጎሪጥ ያዩኛል። አክራሪዎቹ ደግሞ እንደባንክ በመሳሰሉ ቁልፍ ቦታዎች በሶሻሊዝም ርእዮተ ዓለም የማያምን ሰው ሊቀመጥበት አይገባም እያሉ ዘመቻ ያካሄዳሉ። በሌላ በኩል ግን ለኤኮኖሚው መስክ አስተዳደር ቀጥተኛ ኃላፊነት ያለባቸው ባለሥልጣኖች ታደሰ የባንክን ዘርፍ ደኅና ይዞልናል ብለው ስለሚያምኑ ለሥራ ይፈልጉኛል። መንግሥቱን አልፎ አልፎ ያስቸገርኩት ሲመስለው ይናደድብኝ እንጂ ከበረደለት በኋላ፣ ምን ይደረጋል? ያው የምናውቀው ታደሰ ይሻለናል ሳይል የሚቀር አይመስለኝም። በአብዮቱ ዐሥረኛ ዓመት ዋዜማ ላይ አክራሪዎቹ የጽዳት ዘመቻ ተካሂዶ እንደታደሰ የመሳሰሉት ተጠራጣሪዎች ወይም በመንፈስና አስተሳሰብ ዴሞክራቶች የሆኑት ተንጓለው እንዲጣሉ ይፈልጋሉ።

እኔ የፖርቲ አባል ባለመሆኔ "ከአለበት ቦታ መነሳቱ የማይቀር ነው" በማለት በባንክ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ኃላፊዎች የታደሰን ቦታ እንወስዳለን ብለው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ጀምረዋል፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ እኔን ማስቸገር ሥራዬ ብለው ተያይዘውታል። አንዳንድ ተቆርቋሪ ሠራተኞችም እየቀረቡ በተጠቀሰው የባንክ ኃላፊዎች ድርጊት አለመደሰታቸውን ይገልጹልኛል።

ከያዝኩት የኃላፊነት ቦታ ብነሳ ያልነውን አይሰማም፣ አይተባበረንም ለሚሉት ለእነፍስሐ ደስታ ጭምር ደስታን እንደሚያጎናጽፋቸው አውቃለው። ፍስሐ ደስታ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ኃላፊ ሆኖ እኔ የባንክ

ኃላፊ ሆኜ የጻፈልኝ ደብዳቤ ቅጂውን ባለማስቀረቴ አሁን ይቆጨኛል፡፡ ማን ያውቃል? አንድ ቀን አገኘው ይሆናል፡፡ ፍስሐ በጻፈልኝ የግሳጼና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ያለው በአጭሩ፣ ሲያዙህ ለምን? ብለህ መጠየቅ ትወዳለህ፤ የበላይ አካል አመራር ሲሰጥህ ሌላ ሐሳብ አለኝ እያልክ ታስቸግራለህ የሚል ነበር፡፡ ለምን? ማለትና የተሻለ ሐሳብ ሊመጣ ይችላልና እስቲ ጉዳዩን አገላብጠን እንየው ማለት ለወታደሮች የማይዋጥላቸው አሠራር ነበር፡፡ የወታደርን አመራር ለመቃወም ሲቪሎች የሚሸርቡት ተንኮል ነው ብለው ያምኑ ነበር፡፡ በመሠረቱ በፍስሐም ሆነ በሌሎቹ የወታደር ትምህርት በቀሰሙ የሥራ ጓደኞቼ መፍረድ አይቻልም፡፡ ትምህርታቸው የሚለው የበታች የበላይን ትእዛዝ ያለጥያቄ መቀበል አለበት ነው፡፡ ይህ በጦር ሜዳ ለተሰማራ ሰራዊት ሊሠራ ይችላል፡፡ በሲቪሉ ዓለም ግን አይሠራም ብቻ ሳይሆን እንዲሠራ መደረግ የለበትም፡፡ የወታደራዊው የአመራር ሥርዓት ተገልብጦ ሲቪሉ እንዲመራበት ማድረግ አምባገነንነትን ማስፈን ስለሆነ በዴሞክራሲ የሚያምን ሕብረተሰብ ማውገዝና መቃወም ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ሕዝብን አረጋግቶ ለማስተዳደርና የኤኮኖሚ እድገትን ለማምጣት በሚደረጉ ሙከራዎች አንድ ፕሮብሌም ሲገጥም በመጀመሪያ ደረጃ ፕሮብሌሙ ምን እንደሆነ በቅጡ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ይህ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት መፍትሔ ይገኝለት ዘንድ አንድን ፕሮብሌም ከሥሩ ገብቶ እውነተኛ ገጽታውን ገልጦ ለማየት እንዲቻል ነው፡፡ ለሌለ ችግር መፍትሔ ሲፈለግ ጊዜና አቅም እንዳይባክን ለመከላከል ነው፡፡ የችግሩ ዓይነት፣ ስፋት፣ ጥልቀት ምን እንደሆነ ከተደረሰበት በኋላ ወደ መፍትሔ ፍለጋ ይኬዳል፡፡ የመፍትሔ ሐሳቦችን ማንም በሞኖፖል የያዘ ሊኖር ስለማይችል ሐሳብ አለኝ የሚለው ሁሉ ይደመጣል፤ ያሉት አማራጮች በጽሞና ይመረመራሉ፤ በመጨረሻም የተሻለው ይመረጣል፡፡ ለተግባራዊነቱ ሁሉም ተሰልፎ ያቅሙን ይወረውራል፡፡ ኅብረተሰቡ የተስማማበትን የሚያፋልስ ወይም ተግባራዊ እንዳይሆን ደንቃራ የሚሆን ከተገኘ ኅብሰረተሰቡ በሕግ ይፋረደዋል፡፡

ወታደር የሚሰለጥነው ጠላት ለመመለስ ወይም ቃታ ስቦ ለመግደል ስለሆነ ጠላት ደጅ እያንኳኳ ምን ማድረግ እንደሚገባን እስኪ አረፍ ብልን እናውጋ የማይባልበት ሙያ ነው። እነፍስሐና መንግሥቱ ይህን፣ ትዕዛዝ ለመቀበል ሁሉም በተጠንቀቅ ይቁም የሚለውን፣ አመለካከት አንግበው ሲቪሉን ሊመሩና ሊያስተዳድሩ ሞከሩ፣ ነገር ግን ሁለቱ ወገኖች ልብ ለልብ ሳይገናኙ ቀሩ። ፍስሐ ደስታ የጻፈልኝ ደብዳቤ ቁልጭ አድርጎ ያስቀመጠው በወታደርና በሲቪል መካከል ያለውን የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ልዩነት የሚያንጸባርቅ ነው። ከወታደሮቹ ጋር ለረጅም ጊዜ ከሠራሁ በኋላ የደረስኩበት መደምደሚያ ወታደር ሲቪልን ሊመራ እንደማይገባ ነው። ቢሆንም፣ ስለ አለመዝረክረክ፣ ሥራን በተወሰነ ጊዜ አጠናቆ ስለማቅረብ፣ ዐይንና ጆሮን ክፍት አድርጎ በአካባቢ የሚካሄደውን ነቅቶ ስለመጠበቅ ሲቪሉ ከወታደሩ ብዙ የሚማረው አለ። ከዚያ ባሻገር ግን በየጠበላቸው።

ሥልጣን የሚወደደው ለሥልጣንነቱ ነው የሚለውን አባባል ወደ ጎን ትተን እነጄኔራል መርዕድ ንጉሤና ፋንታ በላይ መንግሥቱን ገልብጠው ሥልጣን ለምን ለመያዝ እንደፈለጉ በዝርዝር የማውቀው ነገር የለም። ውስጠ ምስጢር አዋቂዎች ነን የሚሉ ሰዎች እንደነገሩን ከሆነ በእነመርዕድ አመለካከት መንግሥቱ የሲቪሉን ክፍል ከሚገባ በላይ ያቀረበ፣ ምርጥ ወታደሮችን አግልሎ ወታደሩ ግዳጁን በሚገባ እንዳይወጣ ያሰናከለ ሰው ስለነበር አገሪቱ ጠበቅ ያለ ወታደራዊ አገዛዝ ያስፈልጋታል የሚል ነበር። ዓላማቸው ይህ ከነበረ አድማቸው እንኳን ከሸፈ ብያለሁ። አሁንም እላለሁ። ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት በመሣሪያ ኃይል የሚገዛት ወታደር ወይም የወንበዴ ቡድን ሳይሆን ሕዝቡ ይሆኑኛል፣ ይመሩኛል፣ የበላኝን ያኩልኛል የሚላቸውን ሐቀኛ ተወካዩቹን ፈልፍሎ ማውጣት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጉልበተኛ አገዛዝ ወደ አስተዋይና ጥበበኛ አመራር እስካልተሸጋገረ ድረስ ሲያለቅስ ይኖራል።

መንግሥቱ ከላይ የጠቀስኩትን ጥያቄ ሲያቀርብልኝ ከፊቴ ድቅን ብለው የታዩኝ በዙሪያዬ ተሰልፈው አሰፍስፈው የሚጠባበቁት ባላንጣዎቼ ነበሩ።

ጦርነት የገጠምኩት ከነሱ ጋር እንጂ ከመንግሥቱ ጋር አይደለም አልኩ:: መንግሥቱን እንደ ተከራካሪ ሳይሆን እንደ ዳኛ አድርጌ ወሰድኩት:: ስለሆነም፣ የምመልሰው መልስ ጠላቶቼን አሳፍሮ የሚመልስ እንዲሆን ለቀረቡብኝ ክሶች ማፍረሻ መፈለግ ነው አልኩ:: ደጋግሜ እንደገለጽኩት ወሳኝ ወቅት ሲያጋጥመኝ እግዚአብሔር የሰጠኝ ጭንቅላት ኃይሉን ሁሉ አሰባስቦ ከጉድ ማውጣት ልማዱ ነው:: ዛሬም እንደማያሳፍረኝ ተማመንኩበት::

የሰጠሁት መልስ ባጭሩ እንደሚከተለው ነበር:: እኔ የመደብ ጀርባዬ ቢታይ አብዮቱን ከሚደግፉት ወገን ስለመሆኔ በቀላሉ መረዳት ይቻላል፤ ተቃዋሚ ልሆን አልችልም፤ አገሬን ስለምወድና አብዮቱንም ስለምደግፍ ነው በአገር ውስጥ ቆይቼ ለማገልገል የወሰንኩት፤ በባንክ ኃላፊነቴ ብዙ ባለሥልጣኖች አይተባበረንም፣ ያስቸግረናል፣ ይህን የሚያደርገው በአብዮቱ ስለማያምን ነው የሚሉት ሐሰት ነው:: ከታወቀ የባንክ አሠራር ደንብ ውጭ ጥያቄ ሲያቀርቡ ይህን ያንን አሟሉና ተመለሱ ሲባሉ፣ አይተባበርም ይላሉ፤ እውነቱን ለመናገር፣ ለመተባበር ተብሎ የሚሉት ሁሉ ቢፈጸም ኖሮ ባንክ ድራሹ ይጠፋ ነበር፤ በአጠቃላይ ደግሞ ትክክል የመሰለኝን ሐሳብ ከመሰንዘር ወደ ኋላ እንደማልል አንተም ታውቃለህ፤ ለዚህም እንደተቃዋሚ እንድታይ የሚፈልጉ ጥቂቶች አይደሉም፤ እንደባለሥልጣንነታችን የመሰለንን ሐሳብ መናገር መብታችን ሲሆን፣ ከሚቀርቡት ሐሳቦች መካከል መምረጥ ደግሞ የበላይ ኃላፊዎቻችን ፋንታ ይመስለኛል፤ እውነቱ እየተደበቀ መንግሥቱን የሚያስደስተው ብቻ እየተመረጠ ቢንቆረቆር የሚጠቅምህ አይመስለኝም፤ እንደብዙ ባለሥልጣኖች መሸንገል ወይም ትክክል ያልሆነ ነገር ሲሠራ ሳይ ወይም ሲባል ስሰማ ዝም ብዬ ማለፍ አይሆንልኝም፤ እኔ የማወቀው አሠራር ይህ ነው፤ ትክክልም ይመስለኛል፤ ይህን ሁሉም ቢከተለው የተሻለ ውጤት ይገኛል የሚል እምነት አለኝ አልኩት:: በተናገርኩት ላይ ብዙም አስተያየት ሳይሰጥ ወደቢሮህ መመለስ ትችላለህ አለኝ:: ስለሥራህ አውቃለሁ፤ በያዝከው መንገድ ቀጥል ያለኝ ይመስለኛል::

ከአንድ ወይም ሁለት ቀን በኋላ ለማ ጉተማ፣ የፓርቲው የአዲስ አበባ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፣ ደውሎ ቢሮ ድረስ እንድትመጣ ይለኝና እሄዳለሁ:: ቢሮው ስገባ ከመቀመጫው ጀርባ ቆሞ አገኘሁት:: ተቀመጥ ሳይለኝ ማዶ ለማዶ እየተያየን፣ ቢሮ ቁጥር ምናምን ሄደህ ማመለከት ትችላለህ ይለኛል:: ምን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ አልሆነልኝም፤ ማመልከት ሲል ምንድነው የማመለክተው? አልኩና ግራ ተጋባሁ:: የተናገረውን ሲደግምልኝ ለፓርቲ አባልነት ፎርም ሙላ ማለቱ እንደሆነ ገመትኩ:: ሆኖም ወደ ተባለው ክፍል ብሄድ ምን እንደፈለጉ በግልጽ ማወቅ ስለምችል ወደዚያው ልሂድና ላጣራ ብዬ ሄድኩ:: የተባለው ቢሮ ውስጥ ስገባ የውሃ ሀብት ልማት ኮሚሽነርን አለም አልአዛርን እንደኔው ተጠርቶ አገኘሁት:: እሱም የአባልነት ፎርም እንዲሞላ መጠራቱን ነገረኝ:: ተረስተን የነበርን ጭቁኖችን አብዮቱ ዛሬ በመብራት ፈልጎ አገኘን ተባባልንና ተቀላለድን::

ፎርሙ ከሚጠይቃቸው አንዱ ያደረግኸውን አብዮታዊ አስተዋፅኦ ዘርዝር የሚል ነበር:: በሌላ አነጋገር አባል ለመሆን የአብዮተኛነት መለኪያ ታሚላ እንደሆነ ግለጽ ማለት ነው:: ተማሪ ሳለሁ ፊውዳሊዝም ይውደም፣ መሬት ላራሹ ይሁን ብያለሁ፣ በተማሪ ሰላማዊ ሰልፎች ተሳትፌአለሁ፣ አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ደግሞ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ከፍ እንዲል የገንዘብ ድርጅቶችን በአዲስ መልክ በማደራጀት ረድቻለሁ ብዬ ሞላሁ::


ለማ የተለጠጠብኝ ታደሰ የፓርቲ አባል መሆን የለበትም ከሚሉት ሰዎች ወገን ስለነበረ መሆኑን አውቃለሁ:: ጭራውን ከማን ከማን ጋር እንደቆለፈ ለማወቅ ከባድ አልነበረም:: መንግሥቱ ካነጋገረኝ በኋላ በአባልነት እንዲመዘግቡኝ ያስተላለፈው መመርያ ሲደርሰው የተናደደ ይመስለኛል::

ብዙም ሳይቆይ ዐሥረኛው የአብዮት በዓል ተከበረ:: በተደረገው የፓርቲው ስብሰባ ላይ የማእከላዊ ኮሚቴ አባላት ስም ሲዘረዘር ታደሰ ገብረኪዳን ሲባል የኔም ሆነ የብዙ ሰው ጆሮ አላመነም ነበር:: ከነዚህ መካከል የቅርብ ወዳጄ የታደሰ ኪዳነ ማርያም ጆሮ ይገኝበት ነበር:: የሱ ስም የተጠራ መስሎት ተነስቶ ቆመ፤ መንግሥቱም፣ አይ፣ አንተን አይደለም፣ የባንኩ


ኮሚሽነራችንን ነው አለና ስሕተት እንዳልተፈጸመ ለሚሰማው ሁሉ ግልጽ አደረገው፡፡ እንኳን የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ልሆን ይቅርና የፓርቲ ዕጩ አባል እንዳልሆን ታግጄ የነበርኩ ሰውዬ ከመቅጽበት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆኔ የሰሞኑ ዜና ሆኖ ሰነበተ፡፡

የስብሰባውን ስነሥርዓት ሕዝቡ በራዲዮ እንዲከታተል ተነግሮት ስለነበር የባንክ ሠራተኞችም በየቢሮ ውስጥ ተሰባስበው ያዳምጡ ነበር፡፡ አንድ ወዳጄ እንዳጫወተኝ በዚያን ቀን ከአለቃው ጋር ፕሮግራሙን አብረው ይከታተሉ ነበር፡፡ እንደነገረኝም "የማእከላዊ ኮሚቴ አባል መሆንህ ሲነገር አለቃዬ ከመደንገጡ የተነሳ እንደ እንጨት ደርቆ ቀረ፤ ደኅና ነህ? ብዬ ብጠይቀው ምንም ሳይመልስለኝ እይታውን በጠረጴዛው ላይ ተክሎ አልነቅል አለ፤ ሁኔታው ስላላማረኝ፣ የምለውም ሆነ የማደርገው ስለጠፋኝ ቀስ ብዬ በሩን ከፍቼ ወጥቼ ሄድኩ" ብሎኛል፡፡ ሰውዬው የደነገጠው ታደሰ የፓርቲ አባል ባለመሆኑ በቅርብ ቀን ከቦታው መነሳቱ አይቀርም ብለው በማመናቸው እራሳቸውን በሐሳባቸው ለቦታው በእጩነት ካቀረቡት ሰዎች መካከል አንዱ ስለነበር ነው፡፡

የማእከላዊ ኮሚቴ አባል ከተባልኩ በኋላ ተቃዋሚዎቼ ለጊዜውም ቢሆን አፋቸውን ዘግተው፣ የመኀንተያ ጣታቸውን ሰብስበው ስለተቀመጡልኝ ሥራዬን ተረጋግቼ መሥራት ቻልኩ፡፡ የፈለግሁትም ይኸው ነበር፡፡ የባንክን ዘርፍ በደኅና ሁኔታ ይመራል ብለው ላመኑብኝም አስደሳች ዜና ሆነ፡፡ ከባንኮቻችን ጋር የሥራ ግንኙነት የነበራቸው የምዕራቡ ዓለም ባንኮችም ቢሆኑ ምንም እንኳ በሶሻሊዝምም ሆነ በፓርቲያችን ባያምኑም ከሙያዬ ሳልፈናቀል በሥራ ገበታዬ ላይ የሚያስቆየኝ ሁኔታ መፈጠሩን ሲያዩ ደስ ሳይላቸው አልቀረም፡፡




በ 12 አመቴ



ከሙህር ሰፈር አብሮ አደጎቼ ጋር ፤ ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ይልማ አሶሬ ፣ እንዳለ አሶሬ ፣ ጸጋዬ ኪዳነማርያም ፣ ደራሲው ፣ ባረጋ ፣ ኀይለየሱስ አሶሬ



ከሰፈር ጓደኞቼ ጋር ፤ ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ጌታቸው ፣ ታፈሰ
ሺፈራው ፣ አሰፋ ፣ ክንፉ ተድላ ፣ ወልደጊዮርጊስ ጋሼ ፣ አማረ



አባቴ አቶ ገብረኪዳን አትጋቦ



ከግራ ወደ ቀኝ ፣ የደንብርጋ ልጅ ፍቃዱ ፣ ወንድሞቼ ብሩክና አብርሃም ፣ የአኅቴ ሽምብር ልጅ ግዛው



ከእህቴ ጽጌና ከወንድሜ ብሩክ ጋር




አባቴና አሳዳጊ እናቴ ወይዘሮ እልፍነሽ ወቢሳ



አባቴ አቶ ገብረኪዳን አትጋቦ



የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ዐሥራ አንደኛ ክፍል ጓደኞቼ በከፊል ፧ ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ተስፋዬ ቀጸላ ፣ ደራሲው ፣ ገዛኸኝ ታደሰ ፣ ? ፣ ? ፣ ጌታቸው ገብረሚካኤል ፣ ተመስገን ሳሙኤል ፣ ኀይሉ ቸርነት ፣ ብርሃኑ ዘለቀ ፣ ካሳዬ ተፈራ ፣ ሞገስ ፋሲል ፣ ከበደ ፣ በፍቃዱ ደግፌ ፣ ግርማ ሞገስ



የንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ጓደኞቼ ፧ አሰፋ ወልደኪዳን ፣ የተቀመጠው ፣ ከግራ ወደቀኝ ደመላሽ አለሙ ፣ አብርሃም ተስፋዬ ፣ ሰለሞን ሉሉ ፣ ደራሲው ፣ አጥናፉ ፣ ቶቶ መልካ ፣ መኮንን ተሰማ ፣ አባይ አብርሃ ፣ ታዬ በቀለ



ከራስ ደስታ ዳምጠው ትምህርት ቤት ፣ ይርጋለም ስካውቶች ጋር


፣ 1960



ንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ፣ የክፍል ጓደኞቼ



ምረቃ ፣ ሐምሌ 1961



ከተሸለምኩት የወርቅ መዳልያ ጋር ፣ ከግራ ወደ ቀኝ ሻቃ ፣ ወርቁ ጌታሁን ፣ የኑስ ጌታሁን ፣ ተከስተብርሃን ገብረሚካኤል ፣ ሰለሞን ሉሉ



በብሔራዊ ባንክ አዛዥነት በቢሮ ውስጥ



በአፍሪካ ማዕከላዊ ባንኮች ማኅበር ስብሰባ ላይ ከተገኙልን የልዑካን መሪዎች ጋር



ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ሃይለማርያም ባንክን በሰኔ 20 ፣ 1978
በጎበኙበት ዕለት ከፍቅረስላሴ ወግደረስና ከፋሲካ ሲደልል ጋር



ፕሬዝዳንት መንግሥቱ ባንክን በጎበኙበት ዕለት መግለጫ ስሰጥ



ፕሬዝዳንት መንግሥቱ የባንክን ካዝና በጎበኘበት ወቅት የገንዘብ ናሙና ሳበረክትለት




በለንደኑ የናሽናል ኤንድ ግሪንድሌይስ ባንክ የሥልጠና ተቋም ውስጥ



የአፍሪቃ ማዕከላዊ ባንኮች ሊቀመንበር በነበርኩበት ወቅት የዚምባብዌ ገንዘብ ማተሚያ ድርጅት በተመረቀበት ዕለት ፤ ከፕሬዚደንት ሙጋቤ በስተግራ የዚምባብዌ ማዕከላዊ ባንክ አዛዥ



የአባይ ፏፏቴ ጉብኝት ፣ ሰኔ 1969 ፤ ከኋላ ፣ ከግራ ወደቀኝ ፣ አቶ ዩሱፍ ኢብራሂም ፣ አቶ ጥምቀቱ ፣ አቶ ለይኩን ብርሃኑ ፣ ደራሲው ፣ ? ፣ ፊትለፊት ፣ ከግራ ወደ ቀኝ ፣ አቶ ታዬ ተፈሪ ፣ ? ፣ ?



የቻይና ጉብኝት



ከሚስተር ፌስተስ ሞሃይ ፣ የእንግሊዝኛ ተናጋሪ አፍሪቃ አገሮች የአይ ኤም ኤፍ ተወካይ ጋር ፤ ሰውዬው አሁን የቦትስዋና ፕሬዚዳንት ናቸው




የኢትዮያጵያ ቀይ መስቀል ብሔራዊ ቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ፤ ከግራ ወደቀኝ ወይዘሮ መአዛ ቅጣው ፣ ዶክተር መኮንን ሙሉነህ ፣ ዶክተር ዳዊት ዘውዴ ፣ ደራሲው ፣ አቶ ኀይሉ ወልደአማኑኤል ፣ አቶ ጌታቸው ደስታ



ከቀይ መስቀል የበላይ ጠባቂ ከፍቅረስላሴ ወግደረስ እጅ የወርቅ ሜዳልያ ስቀበል



በቀይ መስቀል ሜዳልያ ሽልማት ዕለት ከአቶ ስሜ ኩላላ ፣ ከወይዘሮ አሳመረች ወልዴና ከባለቤቴ ከዕፀገነት ወልዴና ከልጄ ከኀሊና ጋር



ከምሥራቅ ጀርመን የውጭ ንግድ ሚኒስትር ጋር ውል ፊርማ ሥነሥርዐዓት ላይ



በላይፐዚግ የንግድ ትርዒት ወቅት የምሥራቅ ጀርመን ፕሬዚዳንት ሆኔከር ሲያነጋግሩኝ



ከኩባው የውጭ ንግድ ሚኒስትር ጋር የንግድ ስምምነት ስፈራረም



ፕሬዚዳንት መንግሥቱ የቆዳ ትርዒትን በጥር 1982 በከፈተበት ዕለት



ቤተሰቤ ወደ ካናዳ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ወቅት



አሳመረች፣ ዕፀገነት ፣ ወዳጆቻችን ወይዘሮ አቦዘነች ፣ ወይዘሮ ጽጌና ዶክተር አቦነሽ በስንብት ግብዣ ላይ



ጣልያን ከተባረረ በኋላ የንጉሡ አማካሪ ከነበሩት ከካናዳዊው ከዶክተር ሮበርት ቶምፕሰን ጋር በኦታዋ ቢሮዬ ውስጥ



ከካናዳ የውጭ ትብብር ሚኒስትር ከማዳም ሞኒክ ላንድሪ ጋር



የካናዳ ጠቅላይ ሚኒስትር ብራየን ሙልሮኒና ባለቤታቸው ከባለቤቴ ጋር
ሲቀበሉን



የባለቤቴ አባት ቀኛዝማች ወልዴ አያኖ ፣ አቶ ስሜና ባለቤቱ ወይዘሮ አሳመረች፣ እንዲሁም አቶ ታዬ በጋብቻችን ውል ፊርማ ሥነሥርዓት ላይ



ከጓደኞቻችን ከታዬ ተፈሪ ፣ ከከበደ አድነውና ከአስፋው አገኘሁ ጋር



በስደተኛው መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ውስጥ የተክሊል ጋብቻ ሥነሥርዓት




የሰርጋችን በዓል የተከበረበት ዕለት ፣ ህዳር 4 ፣ 1970 ከሚዜዎቻችን ከታዬ ፣ አስፋውና ከበደ ጋር



ከአብሮ አደጎቼ ከነጋሽ ኀይሌ ፣ ከእንዳለ አሶሬ ፣ ከታፈሰ ሺፈራና
ከታከለ ደበላ ጋር




ወንድሞቼ ብርሃኔ ደንባርጋ ከባለቤቴና ልጆቼ ጋር




ኬፕታውን ፣ ደቡብ አፍሪካ



ከቤተሰቤ ጋር በኦታዋ ፣ ካናዳ



ከጓደኛዬ ከገዛኸኝ ታደሰ ጋር ፣ በሾላ ሚካኤል ቤተክረስቲያን ቅጥር ግቢ

# ምዕራፍ አምስት

# የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርን በብሔራዊው ቦርድ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነትና በክብር አቃቤ ንዋይነት ከ1971 እስከ 1979 ለዘጠኝ ዓመታት በነጻ አገልግያለሁ፡፡ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳለሁ የ«ዝሆኖች» እስካውት ፓትሮል መሪ፣ ከዚያም የሮቨርስ ማለትም የትላልቅ እስካውቶች መሪ፣ ዩኒቨርስቲ ከገባሁም በኋላ በንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ከጓደኛዬ ከአስፋው አገኘሁ ጋር ያቋቋምነው የእስካውት ማኅበር መሪ ስለነበርኩ ለቀይ መስቀል አገልግሎት እንድሰጥ ስጠየቅ ለረጅም ጊዜ የተዋወቅሁት ሰብአዊ አገልግሎት በሌላ መልኩ የሚቀጥልበት ዕድል ስለተገኘ በመሠረቱ ደስ ብሎኛል፡፡

ማኅበሩን እንዳገለግል የተጠየቅሁት ስለብሔራዊ ቁጥጥር በዩኒቨርስቲው የልደት አዳራሽ የተደረገው ሴሚናር የተጠናቀቀ ዕለት ነበር፡፡ የሴሚናሩ ተሳታፊ ወደየመጣበት ለማምራት ሲሰማራ የማኅበሩ የበላይ ጠባቂ የፍቅረሥላሴ ወግደረስ ልዩ ረዳት ተሾመ ተስፋዬ የተወሰንን ሰዎችን ትፈለጋላችሁ ብሎ ያስቆየናል፡፡ ለቀይ መስቀል አገልግሎት የተፈለግን ወይም የተመረጥን መሆኑን ይነግረንና እንድንስማማ ይጠይቀናል፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት ጥያቄው ለእኔ ወደ እስካውትነት ዘመንህ ተመለስ እንደማለት ስለነበረ በልቤ ደስ ብሎኛል፡፡ ነገር ግን እስካውትነት የልጆች ጨዋታ ይኸኛው ግን ለተጎዳ ሕዝብ ሕይወትና ደኅንነት ኃላፊነት

የሚያሸክም በመሆኑ ለአገልግሎት የምሰለፈው ከእነማን ጋር እንደሆነ እንዲገለጽልኝ ጠየቅሁ:: ለሊቀመንበርነት የተመረጠው ዶክተር ዳዊት ዘውዴ እንደሆነ ተነገረኝ:: የባለሥልጣን ልጅ ስለነበረ ተማሪዎች ሆነን ስለማንነቱ እንሰማ ነበር:: አብረን መሥራት ስለመቻላችን ተጠራጠርኩና ሥራ ስለሚበዛብኝ ሌላ ሰው ብትፈልጉ ይሻላል ብልም ካልገባህ የሚለው ግፊት ስለበዛብኝ እሺ ልሞክረው ብዬ ገባሁበት::

ማኅበሩን በክብር አቃቤ ንዋይነት ማገልገል እንደጀመርኩ መጀመሪያ ያጤንኩት የማኅበሩን የሒሳብ ክፍል የሥራ እንቅስቃሴ ነበር:: በአንድ ወይም ሁለት ቀኖች መጠናቀቅ ያለበት ሥራ ብዙ ወራት ተወዝፎ አየሁና ተሳቀቅሁ:: የክፍሉን ሠራተኞች ምን ነካችሁ? ብዬ ብጠይቃቸው የቆጡን የባጡን መቀበጣጠር ተያያዙት:: የበላይ አለቆቻቸውን ስለሥራው አዝጋሚነት ባነጋግር ቀይ መስቀል በሰብአዊ አገልግሎት አቅራቢነት የተሰማራ ድርጅት ስለሆነ ሠራተኞቻችንን ሳንጫናቸው አለሳልሰን መያዝ አለብን አሉኝ::

ከኔ በፊት የማኅበሩ የክብር አቃቤ ንዋይ የነበረው በባንኩ ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ቁጥጥር መምሪያ ኃላፊ፣ ከዚያም የዚሁ መምሪያ አማካሪ አቶ መስፍን በለጠ ነበር:: የማኅበሩ ሊቀመንበር ሲስተር የሺ ቀንአ፣ የታወቀው የዐይን ሀኪም የዶክተር ፓውሎስ ቀንአ እህት፣ ቢሮዬ ድረስ መጥተው አቶ መስፍን ፈቃድ ሲጠይቀኝ እንድተባበር አደራ ስላሉኝ ምንም ችግር እንደማይኖር ቃል ገብቼላቸው ነበር:: እኔም የተፈሪ መኮንን እስካውት በነበርኩበት ጊዜ በየዓመቱ በቀይ መስቀል ቀን ጃንሜዳ በሚደረገው በዓል የማኅበሩ አገልጋይ እንደነበርኩ ሳልጠቅስላቸው የቀረሁ አይመስለኝም::

አቶ መስፍን ብዙ ጊዜ ቀይ መስቀል ውሎ ሲመጣ እያየሁ ለመሆኑ እዚያ እንዲውል የሚያደርገው ምን ዓይነት ሥራ ቢሆን ነው? እያልኩ እራሴን ስጠይቅ ሰነበትኩና አንድ ቀን እራሱን ጠየቅሁት:: የማኅበሩን ሒሳብ እንደሚሠራ ነገረኝ:: ማኅበሩ የሒሳብ ሠራተኞች እያሉት እሱ እንዴት የሒሳብ ሥራ ይሠራል? ብዬ መገረሜ አልቀረም:: ወጣቶቹ የሒሳብ

ለሰጠሁት አገልግሎት የወርቅ መዳልያ ከማኅበሩ የበላይ ጠባቂ ከፍቅረሥላሴ ወግደረስ እጅ በ1977 ተቀብያለሁ። ሽልማቱን ማግኘቴን ምክንያት በማድረግ የአብዮታዊ ኢትዮጵያ ራዲዮ ቃለመጠይቅ አደረገልኝ። ምልልሱ በየሳምንቱ በተከታታይ ለሦስት ሳምንታት ተላለፈ። ለቀይ መስቀል ያደረግሁት አስተዋፅኦ በጣም እንዳረካኝ ገለጽኩ። የቀይ መስቀል ቦርድ ያቀደውን ተግባራዊ ከማድረግ የሚያግደው ወይም የሚያደናቅፈው የበላይ ኃይል ስለሌለ እያንዳንዱ የቦርድ አባል ጥረቱ የበለጠ ውጤት የሚገኝበትን ዘዴ መሻት እንደሆነ ገለጽኩ። በተዘዋዋሪ ለአድማጭ መንገር የፈለግሁት በቢሮክራሲ የተተበተበው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥራ በእራስ መተማመንን የማያደፋፍርና እርካታ የማይገኝበት ውሃ ወቀጣ መሆኑን ነበር።

ከአንድ ጥያቄ መልስ ጋር አስታክኬ ዶክተር ዳዊት የቦርድ ስብሰባ የሚጠራው ማኅበሩን የገጠሙት ችግሮች ለመፍታትና ወደፊት ለማራመድ እንዲቻል የቦርድ አባላት የሚያመነጪቸው ጥሩ ጥሩ ሐሳቦች ሳይበታተኑ ተሰብስበው በሥራ እንዲተረጎሙ እንጂ አስቀድሞ የወሰነውን ቦርዱ እንዲያጸድቅለት እንዳልነበረና አሠራሩም ፍሬያማ ሆኖ ማኅበሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን የምስክርነት ቃሌን ሰጥቻለሁ። ለአድማጭ ማስተላለፍ ፈልጌ የነበረውን መልዕክት የመንግሥትና የፓርቲ የበላይ አመራር አካላት ስብሰባ የሚጠሩት በአጀንዳ በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ነጻ ውይይት ተደርጎ አብዛኛው የሚስማማበት ሐሳብ እንዲያልፍና በሥራ እንዲተረጎም ለማድረግ ሳይሆን ጥቂቶች በዝግ ችሎት አስቀድሞ የወሰዷቸውን አቋሞች ወይም ያደረጓቸውን ውሳኔዎች ስብሰባው እንዲያጸድቅላቸውና ዴሞክራሲያዊ አሠራር ያለ ለማስመሰል የሚዶለት ከንቱ ሙከራ መሆኑንና ሕዝቡ ይወክሉኛል ብሎ የመረጣቸውና መንግሥትም ይጠቅማሉ ብሎ ያሰለፋቸው ሰዎች በቂ አስተዋፅኦ ሳያበረክቱ ጥረታቸው ተኖ ስለሚጠፋ ብሔራዊ ችግሮቻችን ሥር እየሰደዱ እንደሚሄዱ በተሰጠኝ ዕድል ተጠቅሜ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ለሚረዳልኝ ለመግለጽ ሞክሬአለሁ።

ማኅበሩን ከማገልገል ከዘጠኝ ዓመት በኋላ ስሰናበት፣ መጀመሪያ የተረከብነው ትቼው ከሄድኩት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ለውጥ እንደነበረው የማይታበል ሐቅ ነው:: አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ የተቻለው የማኅበሩ አመራር የሥራ ችሎታና ሰብኣዊ ዝንባሌ ባላቸው ሰዎች ተይዞ ስለነበረ ነው:: ከብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ቦርድ አባላት መካከል ዶክተር ዘውድነህ ይምታቱን፣ አቶ አሰፋ ይርጉን፣ ዶክተር መኮንን ሙሉነህን፣ አቶ አበበ እንግዳሰውን፣ ወይዘሮ መዐዛ ቅጣውን፣ አቶ ጌታቸው ደስታን፣ አቶ ኃይሉ ወልደአማኑኤልን፣ ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌን አስታውሳለሁ:: እኔ ባገለገልኩበት ዘመን በተለያየ ጊዜ ማኅበሩን በዋና ጸሓፊነት ያገለገሉት አቶ ተሠራ ክፈተው፣ አቶ ጌታቸው አርአያ፣ አቶ ተፈራ ሺያውል፣ አቶ በቀለ ገለታና አቶ ንዋይ ነበሩ::

የማኅበሩ ሊቀመንበር፣ ዶክተር ዳዊት፣ በሰው የመጠቀም ችሎታው ተወዳዳሪ የለውም:: ዓላማውን ለማሳካት ለስልሶና አለሳልሶ፣ ካስፈለገም ቡናም ሆነ አረቄ አስጎንጭቶ ወይም ተጎንጭቶ፣ የሚጠቅመውን ሰው የሙጥኝ ብሎ መያዝ ያውቅበታል:: ቁምነገር ብቻውን ያለጥሩ አቀራረብ ዋጋ እንደሌለው ዶክተር ዳዊት በውል የተረዳ ሰው ነው:: በመረጃ አሰባሰብና አጠቃቀም በጣም ጎበዝ ነው::

እገሌ እንዳይሰማ እያለ አንዳንድ ነገሮችን ወደ ጎን ያሸሸ እንደነበር ሰዎች መጥተው ይነግሩኝ ነበር:: የሚባለውን እስካላየሁት ወይም እስካልደረስኩበት ድረስ ምንም ማድረግ አልችልም፤ ልጅን ይወዷል ከእነእንትኑ ነው እያልኩ አብሬው ሠርቻለሁ:: ማኅበሩን እንደገና አጠናክሮ ለማደራጀትና ለመገንባት ከውጭ፣ በተለይም ከስዊድን ቀይ መስቀል ማኅበር፣ ከፍተኛ እርዳታ ተገኝቷል:: እኔ እንዳየሁት ከሆነ ለእርዳታው መገኘት ከፍተኛውን ሚና የተጫወተው ዶክተር ዳዊት ነበር::

ይህም ሲባል ዶክተር ዳዊት መልአክ ወይም ሱፐርማን ማለትም ላዕለ ሰብ ነበረ ለማለት አይደለም:: እንደማናችንም የራሱ ድክመቶች የነበሩት ሰው ነው:: አንዳንድ ምሳሌዎችን እጠቃቅሳለሁ:: ታደሰ እንዳይሰማ ብሎ

የማኅበሩን ሠራተኞች ካስጠነቀቀ በኋላ አንድ በእርዳታ የተገኘች አውቶሞቢል አንስቶ ለማኅበሩ የበላይ ጠባቂ መጠቀሚያ ይመድባል:: ቆይቶ አንዱ መጥቶ ሹክ ይልልኛል:: ጉዳዩን በቦርድ ስብሰባ ላይ አነሳዋለሁ:: መኪናዋ ለማኅበሩ ገቢ የተደረገች ይመስለኛል:: ወደ ካናዳ ለመጓዝ ጥቂት ቀናት ሲቀሩኝ ለቤት መሥሪያ የወሰድኩትን ብድር ከፍዬ ለመዝጋት ወደ ቤቶችና ቁጠባ ባንክ እሄዳለሁ (የወያኔ መንግሥት ሲመሠረት ታደሰ ከባንክ ብድር ወስዶ ቤት ሠርቷል የሚል ክስ ቀርቦብኝ እንደነበረ ሰምቼ፣ የተፈለገው በረንዳ እንዳድር ነበር እንዴ? ብያለሁ):: ጉዳዬን ጨርሼ ልሄድ ስል "ጓድ ታደሰ" የሚል ድምፅ እሰማለሁ:: ወይዘሮ ሐረገወይን፣ የፍቅረሥላሴ ባለቤት፣ የቤቶችና ቁጠባ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ጸሓፊ ነበረች:: ሰላምታ ከተለዋወጥንና የተመደብክበት አገር አድባር ትቀበልህ ብላ ከመረቀችኝ በኋላ ስለተጠቀሰችው አውቶሞቢል አነሳች:: "ፍቅሬ ለማኅበሩ ካደረገው እርዳታና ካበረከተው አስተዋፅኦ አኳያ አንዲት ትንሽ መኪና ትልቅ ነገር ሆና ነው ካልተመለሰች ብለህ የተሟገትከው?" ብላኛለች::

የቦርዱ ሥራ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ በስብሰባዎቻችን ላይ ማን ምን እንዳለ በምስጢር ይጠበቅ ብንባባልም ዳዊት "እኔ ምን ላድርግ  ታደሰ ነው እንዲህ ያለው፣ እንዲያ ያለው" እያለ መውጫ ቀዳዳ ሲያጣ አሳልፎ ይሰጠኝ እንደነበረ ብዙ ጊዜ ግምት ወስጄ ስለነበር ሐረገወይን ቅሬታዋን እኔ ላይ ስትደፈድፈው ብዙም አልገረመኝም:: ለጊዜውም ቢሆን ዐይኔ ቁልጭልጭ እንዳለና ጉዳዩ ከሷ ጋር ክርክር የምገጥምበት እንዳልሆነ ስለማውቅ አንደበቴ እንደተሳሰረና የምላት እንደጠፋብኝ ትዝ ይለኛል::

"ታደሰ እንዳይሰማ" ይል የነበረው ዳዊት ብቻ ሳይሆን ትልቁ አለቃችንም ነበር:: በአንድ ወቅት አንድ የመንግሥት መልዕክተኞች ቡድን ወደውጭ አገር በጣም በአስቸኳይ መላክ ይፈልጋል:: ባንክ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ለተጓዦቹ የውጭ ምንዛሪ ለመስጠት በጊዜ እጥረት ምክንያት ሳይቻል ይቀራል:: ምን ይሻላል? ሲባባሉ ቆዩና፣ የመንግሥቱ ልዩ ረዳት፣

መንግሥቱ ገመቹ፣ "እስቲ እንደምንም ብለን እዚሁ አካባቢ ካዝናችንን ከጉድ አውጣን እንለዋለን" ይላል:: "ለመሆኑ የውጭ ምንዛሪውን ከየት አመጣችሁት?" ብሎ አለቃው ይጠይቀዋል:: ገንዘብ ያዢያችን "ክፍላችን ላንዳንድ አስቸኳይ ጉዳዮች ይሆናል ብሎ አሰባስቦ የያዘው ነው" ብሎ ይመልስለታል:: መንግሥቱም፣ "እኔ የለሁበትም፣ ታደሰ የሰማ እንደሆነ ወዮላችሁ!" ብሏቸው እንደተሣሣቁ በቦታው የነበረ ሰው ነግሮኛል:: (በባንክ ደንብ መሠረት ባንክ በተለይ የፈቀደለት ድርጅት ካልሆነ በቀር ከባንክ ውጭ ማንም በአገር ውስጥ ነዋሪ የሆነ ሰው ወይም ድርጅት የውጭ ምንዛሪ በጁ ሊይዝ አይችልም የሚል መመሪያ ነበር:: ይህ ማለት፣ የውጭ ምንዛሪ ያገኘ ወይም በእጁ የገባ ሰው በልዋጩ የኢትዮጵያ ብር ተቀብሎ ምንዛሪውን ለባንክ የማስረከብ ግዴታ ነበረበት::)

ወደ ቀይ መስቀል ስንመለስ፣ እነዳዊት አንድን ሰው በአስተዳዳሪነት ሊቀጥሩ ያመጣሉ:: ቅጥሩ በቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መፈቀድ ስለነበረበት ጉዳዩ ለኮሚቴው ይቀርባል:: በክብር አቃቤ ንዋይነቴ ኃላፊነቴ የማኅበሩ ገንዘብና ንብረት እንዳይባክን መጠበቅ ነበር:: ቦታው ችሎታንና ታማኝነትን የሚጠይቅ ስለሆነ ስለአመልካቹ ማንነት ላጣራ እልና ጉዳዩ በይደር ይታለፋል:: ሳጣራ ሰውዬው የታወቀ የእጅ አመል ያለበት መሆኑ ይነገረኛል:: መቀጠር የለበትም እላለሁ:: ዳዊት ግለሰቡንና ከግለሰቡ ጀርባ የነበሩትን "ታደሰን ካሸነፋችሁልኝ እኔ ልቀጥረው ተዘጋጅቻለሁ" ሳይላቸው አልቀረም:: ካሳ ከበደ አማላጅ ሆኖ ቢሮዬ ድረስ መጥቷል:: ይህም ሆኖ አሁንም ተዉ ይሄ ነገር አላማረኝም፤ ባይቀጠር ይሻላል የሚለውን አቋሜን ሳልለቅ እቀራለሁ:: በአቋሜ የጸናሁት መረጃውን ያገኘሁት ግለሰቡን በቅርብ ከሚያውቀውና አስተያየቱን ከማከብረው ሰው ስለነበር ነው:: እነዳዊት ስለግለሰቡ አገኘሁት ያልከው መረጃ የተሳሳተ ሳይሆን አይቀርም፤ በሥራ ኀበዝ ስለሆነ ይልቅስ ሳያመልጠን እንቅጠረው ብለው ወጥረው ይይዙኛል:: ግፊቱን መቋቋም ያቅተኝና ይቀጠራል::

ሰውዬ በሥራው በእርግጥም ጎበዝ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደፈራሁት በእርዳታ የተገኘ እቃ ሲያሸሽ ተደረሰበትና ከሥራው ታገደ፤ ከዚያም ተባረረ፡፡ ስርቆቱን የፈጸመው ከሥሩ የተመደበለትን ሠራተኛ የቃል ትእዛዝ በመስጠት ነበር፡፡ ቢሮዬ ድረስ መጥቶ፣ ያሳገድከኝ አንተ ነህ ብሎኛል፡፡ ማን ነገረህ? ብዬ አልጠየቅሁትም፡፡ "ትእዛዝ ለመስጠቴ ምን ማስረጃ አላችሁ? ትእዛዝ ተቀበልኩ ያለው ሠራተኛ ዋሽቷል፤ ትእዛዝ እኔ አልሰጠሁትም" ብሎ ካደ፡፡ ቀደም ብሎ ስለሰውዬው ማንነት የነገረኝ የመረጃ አቅራቢዬ "ሰውዬው አካሄዱ ስውር ነው፤ ስርቆቱን በቀላሉ ለመያዝ ያስቸግራል" ያለኝ ትዝ አለኝ፡፡ ስለስርቆት በቀይ መስቀል ውስጥ ትምህርት ሰጥቶ የሄደው ይኸው ግለሰብ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ ለማኅበሩ እሰጠው የነበረው አገልግሎት ከተቋረጠ በኋላ ማኅበሩን በፍርድ ቤት ከሶ እንደነበረ ሰማሁ፡፡ ፍርድ ቤት ሐቀኛን ብቻ ሳይሆን "በመረጃ እጦት" ወንጀለኛንም አልፎ አልፎ ነጻ እንደሚያወጣ ያኔም አሁንም ስለማይ ተፈርዶለትም ከሆነ ብዙም አይገርመኝም፡፡

ሦስተኛው ምሳሌ፣ ማኅበሩ ከዓለም አቀፍ የቀይ መስቀል ማኅበር ከ I C R C ጋር የነበረውን ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ ድርጅቱ ዓለም አቀፍ የሚል አርማ ያንግብ እንጂ የስዊስ ድርጅት ነው፡፡ ነጻ ሆኜ ያለቁጥጥር ልሥራ እያለ ይወተውታል፡፡ ውስጥ ውስጡን ወንበዴዎችን እንደሚረዳ እንሰማለን፡፡ የብሔራዊ ማኅበሩ የበላይነት በማያሻማ መንገድ መረጋገጥ አለበት፤ ፈረንጅ የሚመራው ድርጅት ካልሆነ በቀር እርዳታ በቅጡ ሊዳረስ አይችልም የሚለውን የዘረኞች አመለካከት በምንም ዓይነት መቀበል የለብንም ብለን በቦርድ ላይ ተነጋግረን ተስማምተናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ዓለም አቀፍ ስምምነት ስላለ I C R Cን በሥራችን ማድረግ እንደማንችል እናውቃለን፡፡ ጭብጡ ትክክለኛውን ሚዛን መጠበቅን የሚመለከት ነው፡፡

ዳዊት ለብሔራዊ ቀይ መስቀል ማኅበሮች ማኅበር ወይም ፌደሬሽን ፕሬዚዳንትነት ተወዳድሮ ስለነበር ጥቂቶቻችን ድጋፍ ልንሰጠው ጄኔቫ ላይ

ተገኝተናል:: ሙከራው ሳይሳካ ቀርቷል:: እኔ እዚያ የተገኘሁት ለዓመታዊው የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅትና የዓለም ባንክ ጉባኤ ወደ ዋሺንግተን ስሄድ ወይም ከዚያ ስመለስ እግረመንገዴን እንደነበረ ትዝ ይለኛል:: አጋጣሚውን በመጠቀም በማኅበሩና በ I C R C መካከል ስለነበረው ግንኙነት፣ ይኸውም እልባት ሳይደረግባቸው በእንጥልጥል ስለከረሙ ጉዳዮች፣ ከፕሬዚዳንቱ ከሚስተር ሶማሩጋ ጋር ለመነጋገር ቢሮው ድረስ ሄድን:: በኛ በኩል ዳዊትን ጨምሮ ሦስት ወይም አራት ነበርን:: ሰውዬው ሲያነጋግረን ዐይኑን ከኔ ለመንቀል አልፈለገም ነበርና ይሄኔ ዳዊት "እኔ ምን ላድርግ? ማሽነፍ ታደሰን ነው" ብሎት ሊሆን ይችላል ማለቱ አልቀረም::

አራተኛው ምሳሌ ሹመትን ይመለከታል:: የማኅበሩ ዋና ጸሓፊ በቀለ ገለታ በመንግሥት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ምክትል ሚኒስትርነት ይሾምና የዋናው ጸሓፊ ቦታ ክፍት ይሆናል:: በነበረው አሠራር መሠረት የብሔራዊው ቦርድ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ብቃት አለው የሚለውን ሰው ይመርጥና ሹመቱ እንዲጸድቅ ለበላይ ጠባቂው ያቀርባል:: የፎርማሊቲ ነገር ነው እንጂ የበላይ ጠባቂው አልስማማም የሚልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም:: የተጠቀሰውን ክፍት ቦታ በተመለከተ የበላይ ጠባቂው እገሌ የሚባል ሁነኛ ሰው አግኝቼላችኋለሁና እንድትሾሙት ይሁን ይለናል:: የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ሥልጣኔን ተነጠቅሁ ይልና አልተባበርም ይላል::

የበላይ ጠባቂው፣ የቦርዱ ሊቀመንበርና ሹመቱን እንድናጸድቅለት የቀረበው ሰው ሦስቱም የመርሃቤቴ ሰዎች ናቸው:: የበላይ ጠባቂውንም ሆነ ዳዊትን በዘረኛነት ወይም በጎጠኛነት አምቻቸው አላውቅም ነበር:: አዲሱን ክስተት ሳይ ግን ሰዎቹን የሹመቱ ነገር አጋለጣቸው እንዴ? ማለቱ አልቀረም:: ሦስቱም ከአንድ የትውልድ ስፍራ መሆናቸው አጋጣሚ ነው? ወይስ በወንዜ ልጅነት መሰባሰብ? ቀይ መስቀል በዘር ወይም በሃይማኖት

ምክንያት ልዩነት አያደርግም እየተባለ እነሱ ለካስ ውስጥ ውስጡን አግባብ ያልሆነ ሥራ ይሠራሉ? ብዬ ተጠራጠርኩ፡፡

የቦርዱን ውሳኔዎች በተግባር እማዋሉ ላይ የማኅበሩ ጽሕፈት ቤት በተለይ በበቀለ የአመራር ዘመን አስተማማኝ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ እዚህ ለመድረስ የተቻለው እሱም ከመቀጠሩ በፊት ጀምሮ ከብዙ ዓመታት ድካም በኋላ ስለነበር ብቃት የሌለው ዋና ጸሓፊ ከተመደበ ማኅበሩ እንደገና የኋሊት ሊንሸራተት ይችላል የሚል ፍራቻ ነበረን፡፡ በቦርዱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና ዋና ጸሓፊው በሚመራው ጽሕፈት ቤት መካከል መኖር ስላለበት የሥራ ክፍፍል ኮሚቴውን ዘወትር የሚያነጋግር ጉዳይ ነበር፡፡ የወሰድነው አቋም ጽሕፈት ቤቱን አጠናክረን ሥራ አፈጻጸምን ለጽሕፈት ቤቱ ልንተው ይገባል የሚል ነበር፡፡ ደካማ ጸሓፊ ከተመደበ ግን የቦርዱ አባላት ሳይወዱ በዝርዝር አፈጻጸም ውስጥ እንደገና እንዲገቡ ይገደዳሉ የሚል ስጋት ነበረን፡፡

ዳዊት ከቀይ መስቀል አካባቢ መለየት ፍጹም አይሆንለትም ነበር፡፡ ይህ በአንዳንድ መልኩ ተደጋፊነት ሲኖረው በሌላ አንጻር ግን ዳዊት በማኅበሩ የቀን ተቀን ሥራ ውስጥ ለመግባት የሚያስችለው ሁኔታ ስለሚፈጠር ከሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ጋር ብቻ ሳይሆን ከማኅበሩ ዋና ጸሓፊም ጋር መጋጨትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ደካማ ጸሓፊ ቢመደብ ዳዊትን በዝርዝር አፈጻጸም ውስጥ ለመግባት የሚያስችለው መንገድ የበለጠ ይሰፋለታል ማለት ነው፡፡ እውነቱን ለመናገር ጠንካራ ጸሓፊ ጠንካራ ጽሕፈት ቤት ስንል የነበረው የአስተሳሰቡ መሠረት አንድም ዳዊት በዝርዝር የአፈጻጸም ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ እየገባ ውስብስብ ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ለመከላከል ነበር፡፡ ለውዝግብ መንስኤ የሆነውን ዋና ጸሓፊ ያገኘው የበላይ ጠባቂው ነው ተባለ እንጂ እኔ በበኩሌ የዳዊት እጅ ሳይኖርበት አይቀርም ብዬ ጠርጥሬአለሁ፡፡

የነበረው አሠራር ተጥሶና ተገልብጦ የበላይ ጠባቂው የዋና ጸሓፊውን ሹመት ኮሚቴው እንዲያጸድቀው ሲያቀርብ ኮሚቴው የወሰደው አቋም

የማያወላዳ ነበር፤ ኮሚቴው ያልመረጠው፣ የዋና ጸሓፊነት መለኪያዎችን ማሟላቱ ያልተረጋገጠለት ሰው በቦታው ላይ እንዲመደብ አንስማማም የሚል ነበር:: የተቃውሞው መሪ እኔ ነበርኩ ለማለት ይቻላል:: ስለጉዳዩ በኮሚቴው ስብሰባዎች የሚባለውን ዳዊት ለፍቅረሥላሴ የሚነግረው ይመስለኛል:: ከኛ ጋር ሲሆን ግን እሱም እንደኛው ትእዛዝ ከላይ ተጭኖበት ከአቅሙ በላይ እንደሆነበት አድርጎ ይነግረን ነበር:: እኔ ግን አላመንኩትም ነበር::

ፍጥጫው ረዘም ላለ ጊዜ ቆየ:: የሥራ አስፈጻሚው ኮሚቴ አባላት የነበረን አማራጭ ማኅበሩን ጥለን መሄድ መሆኑን ብንገነዘብም ማኅበሩን እዚህ ድረስ አድርሰነው ፈተና ሲገጥመው ጥለነው ከምንሄድ መቼስ ምን ይደረጋል ለሰውዬው ድጋፍ እንስጠውና ማንነቱን በሚያሳየው የሥራ ውጤት እንዲያስመሰክር ዕድል እንስጠው ብለን በመጨረሻ ተስማማን:: እንደፈራነው ሰውዬው በሥራው ጠንካራ አልነበረም:: ጠባዩን ግን በጣም ሸጋ ሆኖ አገኘነው::

ሰው ሁሉ በጎና ደካማ ጎን አለው:: ጥያቄው የትኛው ያመዝናል? ነው:: ዳዊትን በተመለከተ ያም ተባለ ይህ ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በጣም ጠቃሚ ሰው እንደነበር የዐይን ምስክር ነኝ:: ለማኅበሩ አለኝታው ነበር:: ዳዊት አብረነው ከተሰለፍን ሰዎች አስተዋፅኦ ጨምቆ ወይም አልቦ የማውጣት ችሎታው ከፍተኛ ነበር፤ ከመደበኛ ሥራዬ ያላነሰ አርኪ የሥራ አካባቢ በማመቻቸት ሕዝብን የማገለግልበት መድረክ ስለዘረጋልኝ ከልብ አመሰግነዋለሁ:: በትውልዱ ወይም በወገኑ ሳይሆን ባደረገው አስተዋፅኦ መታወቅ ለሚፈልግ ሰው የእንደ ዳዊት ዓይነቱ የሥራ መሪ ወይም አስተባባሪ መኖር ወሳኝነት አለው:: ጉዳዩ በስፋት ሲታይ ደግሞ አገር የሚሠለጥነው ግለሰቦች ጥረት ከማድረግ ወደኋላ እንዳይሉ በየደረጃው የሚያበረታታና ጥረታቸውን የሚያሰባስብና የሚያቀናጅ አይዞህ ባይ መሪ ሲበዛ መሆኑን እግረመንገዴን እንደገና ሳልጠቁም አላልፍም::

እላይ የጠቀስኩት የመዳልያ የሽልማት ፕሮግራም የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል የተቋቋመበትን 50ኛ ዓመት ለማክበር የተደረገው በዓል አንዱ ክፍል ሲሆን የሽልማቱ ሥነሥርዓት የተካሄደው ሚያዝያ 30፣ 1977 በግዮን ሆቴል አዳራሽ ውስጥ ነበር። የማኅበሩ ሊቀመንበር ዶክተር ዳዊትና የስዊድን ቀይ መስቀል ዋና ጸሓፊ አንደርስ ዊክማን እንደኔው የወርቅ መዳልያ ተሸላሚዎች ነበሩ። ወዳጄና የልጅ አዋቂው መስፍን ሃለፎምም የባቲ እርዳታ ጣቢያን በመምራት ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅኦ የብር መዳልያ ተሸላሚ ነበር።

በሥነሥርዓቱ ላይ ከተገኙት የመንግሥት ባለሥልጣኖች መካከል ሽመልስ አዱኛ የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርና ጄኔራል ኃይለጊዮርጊስ የመከላከያ ሚኒስትሩ ነበሩበት። ከሽልማቱ ሥነሥርዓት በኋላ፣ በሻይ ግብዣ ጊዜ፣ ሽመልስ እንኳን ደስ ያለህ ካለኝ በኋላ "የባንክ ሰዎች አዛኝ ልብ ያላቸው አይመስለኝም ነበር" አለኝና ተሣሣቅን። አባባሉ ቀልድ ቢመስልም በጥልቀት ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ነው።

ሽመልስ የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኃላፊ በነበረበት ወቅት የድርቅ ኮሚሽነር ሲባል ይናደድ ነበር። በድርጅቱ ውስጥ የተሰገሰጉ የእጅ አመል የነበረባቸው አንዳንድ ሠራተኞች ድርጅቱን ይበዘብዙት እንደነበር በየጊዜው ሲወራና ዘገባ ሲቀርብ እንሰማ ነበር። በሌላ በኩል ሽመልስ ለኤኮኖሚስቶችና ሒሳብ አስሊዎች ዝቅተኛ ግምት እንደነበረው ከንግግሮቹና ከትረባዎቹ መገመት ይቻል ነበር። በሽመልስ አመለካከት እሱ ሕይወት ለማዳን ሲራወጥ የሒሳብ አስሊዎችና ኦዲተሮች ከሥር ከሥሩ እየተከተሉ አባካኞችንና ሌቦችን ተከላከል ሲሉት ስለሕይወት ምንነት ያልገባቸው ልበድንጋይ ጠዝጣዦችና ጨቅጫቃዎች ወይም መሰሪዎች አስቸገሩኝ ሳይል የቀረ አይመስለኝም።

ሽመልስ ሕይወትን ማዳንና ተረጂን መንከባከብ እንጂ የእርዳታ ሒሳብ መቀመር እንደ አንገብጋቢ ጉዳይ ያየው የነበረ አይመስልም ብለናል። በበጎ አድራጎት ድርጅት ውስጥ የሚባክን ወይም የሚሰረቅ ገንዘብ ለሕይወት

መጥፋት ወይም መጎሳቆል ቀጥተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው በትክክል ያላጤነው ጉዳይ ነበር ማለት ነው፡፡ ብክነትንና ስርቆትን መዋጋት ከሰብኣዊ ድርጅቶች ቀዳሚ ተግባራት ውስጥ መካተት እንዳለበት ዘንግቶ ከሆነ አምላክ መቼም ሁሉንም አሟልቶ አይሰጥምና ምን ማድረግ ይቻላል? እያልኩ አልፈው ነበር፡፡

በመንግሥቱ ሊቀመንበርነት በሚመራ በአንድ ዓመታዊ የበጀትና ዕቅድ ጉባኤ ላይ የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመቋቋም ወጪ ምርቶችን፣ ጥራጥሬን ጭምር፣ በብዛት አሰባስበን መላክ እንዳለብን አበክሬ አሳስባለሁ፡፡ ገና ተናግሬ ከመጨረሴ ሽመልስ እጁን ያወጣና "ድሃው የቀረው ሽሮው ብቻ ነው፤ እሱንም እንንጠቀው ነው የምትሉት?" ብሎ እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም የጉባኤውን አባላት ጠይቋል፡፡ ሽመልስን የማከብረውና የማደንቀው ሰው ነው፤ ነገር ግን ተገኘነቱን ከጭንቅላቱ ይልቅ ለልቡ ማድረጉን አልወድለትም ነበር፡፡ ይህም ሲባል ግን አልሚዎች ነን ባዮችንና አስሊዎችንና ልባሞችን ከዳር ቆመው ዋ! ባይሏቸው ኖሮ ኢሰብኣዊነት መንሰራፋቱና የተበደለውና የተጨቆነው ወገን ስቃዩ መጨመሩ የማይቀር ነበር፡፡ ስለሆነም፣ እንደ ሽመልስ የመሳሰሉት ለዘለዓለም ይኑሩልን፡፡ ብዙዎቻችን በልዩ ልዩ ምክንያት አገር ጥለን ውጭ እንኖራለን፤ ሽመልስ ግን ልቡ እምቢ ብሎት አሁንም ከሚወደው ሕዝብ ጋር እዚያው በሰብኣዊ አገልግሎት ሥራዎች ተሰማርቷል፡፡ የኢትዮጵያ አምላክ እንዲጠብቀው እጸልያለሁ፡፡ የቀይ መስቀል ሊቀመንበር ሆኖ መመረጡን ስሰማ በሐሳብ አብሬው ተሰልፌአለሁ፡፡

የብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በአንድነት አደጋ ላይ ወድቀን በተአምር ተርፈናል፡፡ ታሪኩም እንዲህ ነው፡፡ የ1976 ከባድ ድርቅ ያስከተለውን ችግር ለመመልከትና ቀይ መስቀል ሊያቀርብ ስለሚችለው እርዳታ ለመወሰን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል አውሮፕላን ተሳፍረን ወደ ሰሜናዊ ኢትዮጵያ በረርን፡፡ በጉዞ እቅዳችን መሠረት መጀመርያ የሚጎበኘው ላሊበላ ነበር፡፡ እኔ በግሌ

ላሊበላንና ገዳማቱን የምጎበኝበትን ጊዜ ለረጅም ጊዜ በጉጉት እጠባበቅ ስለነበር አጋጣሚው ስለተፈጠረልኝ ደስ ብሎኛል፡፡

አውሮፕላኑ ወደ ማረፊያው ያመራው በከተማው ላይ አልፎ ስለነበር ጭስ በብዛት አይተናል፡፡ ምን ሊሆን እንደሚችል ተጠያየቅን እንጂ ብዙ ዋጋ ሳንሰጠው አውሮፕላኑ አረፈና ወረድን፡፡ የቀይ መስቀል ሠራተኞች እንዲቀበሉን ተነግሯቸው ስለነበር ማንም ባለመገኘቱ ተበሳጭተናል፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች ጥበቃ በኋላ በርከት ያሉ ሰዎች ወደኛ እየሮጡ ሲመጡ ዐየን፡፡ የቀይ መስቀልን አውሮፕላን አይተው እርዳታ ሊጠይቁ የሚመጡ ችግረኞች መሰሉን፡፡ ገና ከመድረሳቸው ከመካከላቸው በዕድሜ ጠና ያለው ሰው እጁን በኃይል እያወዛወዘ "ቶሎ ሂዱ፣ ተነሱ፣ ሂዱ ነው የምላችሁ" ይለናል፡፡ ምን ለማለት እንደፈለገ ሳይገባን ይቀራል፡፡ ለካስ አውሮፕላኑ ውስጥ የሕዝብ ደኅንነት ሠራተኛ ኖሮ ሰውዬውን ወደጎን ይዞት ይሄድና ምን ሊል እንደፈለገ እንዲገልጽለት ይጠይቀዋል፡፡ ወንበዴዎች ከተማውን ከመንግሥት ወታደር ልክ አሁን አስለቅቀው መያዛቸውንና አውሮፕላኗን ሲያዩ ወደዚህ ማምራታቸው እንደማይቀር ያለውን አስተያየት ይገልጽለታል፡፡ ይህን ስንሰማ ነፍሴ አውጪኝ ብለን ወደአውሮፕላኗ ተመልሰን ገብተን ተጨማሪ ደቂቃ ሳይጠፋ በርረን አመለጥን፡፡ ኮምቦልቻ ያረፍን ይመስለኛል፡፡

ደሴ ስንገባ የክፍለሀገሩ ባለሥልጣኖች ከላሊበላ ጋር የነበራቸው የስልክና የራዲዮ ግንኙነት ተቋርጦባቸው የሚያደርጉትን አጥተውና ግራ ተጋብተው አገኘናቸው፡፡ የላሊበላ ከተማን መያዝ የተረዱት ከኛ ነው፡፡

እንደተገመተው ወንበዴዎቹ አውረፕላኗን ሲያዩ ወደአየር ማረፊያ ገስግሰው ደረሱ፡፡ ከተማ ውስጥ አግኝተው የያዟቸውን የቀይ መስቀል ሠራተኞች በመጠየቅ አውሮፕላኑ ውስጥ የነበርነውን ማንነታችንን ሲያውቁ ጭፍርር ጸጉራቸውን ሳይነጩ አልቀሩም፡፡ ከተማው ውስጥ ያገኟቸውን ብዙ ሰዎች፣ የቀይ መስቀል ሠራተኞችን ጭምር፣ ወደ ሱዳን ነድተው ከወሰዱ በኋላ ብዙ አቆይተው ለቀቋቸው፡፡ እኔን ቢይዙኝ ኖሮ

ደስታውን አይችሉትም ነበር የሚል ግምት አለኝ፡፡ ይህን የምልበት ምክንያት አለኝ፡፡ ወያኔ ሥልጣን እንደያዘ አንድ የማውቀው ሰው ከአዲስ አበባ ኦታዋ ከተማ ይመጣና እንገናኛለን፡፡ "አመራር አካባቢ ያሉ ባለሥልጣኖች ስለአንተ አንድ ነገር ሲሉ ሰማኋቸው፤ 'በሥልጣን መባለግ ወይም በኮራፕሽን አንፈልገውም፤ ነገር ግን የተወጋንበትን ገንዘብና የውጭ ምንዛሪ ለደርግ ሲያቀርብ የኖረ ሰው ስለሆነ ካገኘነው እንፋረደዋለን' ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ" ብሎኛል፡፡

የግምገማው ጉዞ እስከ ኮረም ወስዶናል፡፡ እግረመንገዳችንን ቆቦና አላማጣ ተሰብስቦ የነበረውን እርዳታ ፈላጊ ረሀብተኛ ዐይተን አለፍን፡፡ ኮረም የተመለከትነው ከሁሉም በጣም አስደንጋጭ ሆነብን፡፡ ሰው የሚቀምሰው የሚልሰው አጥቶ ሞትን በቁሙ ሲጠባበቅ ብዙዎቻችን ዐይተን አናውቅ ስለነበር ብዙ ዓይነት ስሜት በውስጣችን ተደበላለቀ፡፡ ያገራችን ሰው መፈጠሬን ጠላሁት ሲል ምን ለማለት እንደፈለገ ለመረዳት ብዙ ሺህ ሰው በሞት አፋፍ ላይ ቆሞ ማየት ብቻ ነው፡፡ የተረጂው ቁጥር በጣም ከፍተኛ፣ የቀረበለት እርዳታ ግን በዓይነቱም ሆነ በመጠኑ በጣም ውስን መሆኑን ዐየን፡፡ አንዳንድ የውጭ ድርጅቶች ለሕፃናት መጠለያ ሠርተው ሲመግቧቸው ተመለከትን፡፡ ረሀቡ የጠናባቸው ሰዎች ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ሲያጣጥሩ ዐየን፡፡ የቀይ መስቀል ሠራተኞች እያዞሩ ሲያስጎበኙን የማይተርፉትን ረሀብተኞች በጣት እየጠቆሙ ያሳዩን ስለነበር ልናድናቸው ባለመቻላችን ለሞታቸው እኛም ተጠያቂ የሆንን እየመሰለን እንበረግግ ነበር፡፡

ካናዳ ከመጣሁ በኋላ አዲሱ ገዢዎችን ላሊበላና አክሱም ለወላይታና ለጉራጌ ሕዝብ ምኑም አይደሉም ማለቱን ሰማሁና ከልብ አዘንኩ፡፡ በ1976 የወሎና የትግራይ ሕዝብ በረኀብ ቸነፈር ሲቆላ ሳይ ወሎዬዎች ወይም ትግሬዎች ስለሆኑ ግድ የለኝም አላልኩም፡፡ ወገኖቼ፣ የአጥንቴ ፍላጮች፣ የደሜ ፍሳሾች ምን ልሁንላችሁ? ነው ያልኩት፡፡ ለኔ ሁሉም ኢትዮጵያዊ አንድ ነው፤ ልማቱም ጥፋቱም የጋራ ነው፤ መብትና ግዴታው አይበላለጥም፡፡

መሪዎቻችን በዚህ ቢያምኑ የኢትዮጵያ ችግር ግማሹ ከመቅጽበት ይወገድና ለቀሪው መፍትሔዎች ፈልጎ ለማግኘት በጣም ይቀል ነበር ብዬ አምናለሁ::

ከተረጂዎቹ መካከል የተሻለ አቅም ያላቸው እየተመረጡ የማገዶ እንጨት ሰብስበው ሲመለሱ አየን:: ያካባቢው ዛፍ ሁሉ ስላለቀ ተልእኳቸው ራቅ ወዳለ ስፍራ ሄዶ ጉቶ ከመሬት ፈልፍሎ ማምጣት መሆኑን ተረዳንና አካባቢው ወደባሰ ጥፋት እያመራ ስለመሆኑ በዐይናችን ዐየን::

የእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ተጠሪን አፈላልገን አገኘነው:: መንግሥት ስለዚህ መዐት ያውቃል? የት አለ እርዳታ የምታከፋፍሉት? ለመሆኑ ኮሚሽነር ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ወደዚህ ብቅ ብሎ ያውቃል? ብለን በጥያቄ አጣደፍነው:: ሰውዬውን ስናየው ከማንም ይበልጥ የችግሩ ስፋትና ጥልቀት የጎዳው ይመስላል:: ውስጡ የታመቀው ንዴትና ሐዘን የሰባበረው ሰው ይመስላል:: መቼም የመንግሥት ተወካይ ስለሆነ በተለይም ለእርዳታ ማስተባበሪያ ኮሚሽን እንደተወዳዳሪ ለሚቆጠረው ለቀይ መስቀል ሰዎች የልቡን አውጥቶ መናገር አልፈለገም:: ለተረጂዎቹ እንዳዘንነው ለሱም አዘንለት:: ዳዊት መጥቶ ያውቃል? ብለን ለጠየቅነው ሲመልስ "መምጣት ብቻ? በደንብ እንጂ፣ አንድ ቀን በሄሊኮፕተር መጥቶ አንድ ሰዓት ሙሉ ከቆየ በኋላ በርሮ ሄደ፣ መምጣት ብቻ? በሚገባ መጥቷል፣ እባካችሁን ተዉኝ ወዳጆቼ" ብሎ በምጸት ተናገረ:: "ከዚያስ ምን ሆነ?" ብለን ጠየቅነው:: "ከዚያን ቀን በኋላ ምንም አልሰማሁም፤ ምንም አላየሁም" አለ:: ሁላችንም በጣም ተገረምን፤ እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? ተባባልን::

ቀጥሎ ያመራነው ወደ ባቲ ነበር:: ባቲ ስንገባ ከሰዓት በኋላ ወደ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ነበር:: የከተማው ዋና ጎዳና ስንደርስ አንዳንድ ሕፃናት መንገዱ ላይ ወድቀው ዐየን:: አንዳንዶቹ ከድካም ብዛት አንገታቸውን እንኳን ቀና ማድረግ ያቃታቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ መቆም አቅቷቸው እየተንፏቀቁ አውራ ጎዳናው መሀል ሆነው ከተሽከርካሪ የረገፈ ስንዴ አንድ ሁለት እያሉ ሲለቅሙ ዐየናቸው:: ቀኑን ሙሉ ሲለቅሙ ቢውሉ እፍኝ

የሚሞላ ጥሬ ማግኘት እንደማይችሉና ረኀባቸውን ለማስታገስ እንደማይበቃ ሳያውቁት ቀርተው ሳይሆን ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ነፍሳቸውን ለማዳን የሚያደርጉት የሞት ሽረት ግብግብ ነበር፡፡ ከዋናው መንገድ ገባ ብሎ ወደሚገኘው ገበያ ብንገባ ከወረቀት ካርቶን፣ ከቁርጥራጭ ቆርቆሮና ከፕላስቲክ የተሠሩት ሱቆችና ገላጣ መደቦች በሙሉ ወደ ረኀብተኞች መናኸሪያነት ተለውጠዋል፡፡ ግማሹ በጎኑ ጋደም ብሎ ሞቱን ይጠባበቃል፤ ሌላው ጉልበቱን አቅፎ ፍዝዝ ብሎ ማዶ ማዶ ያያል፡፡ ካነጋገርናቸው መካከል አንድ አባወራ በአእምሮዬ ተቀርጾ ቀርቷል፡፡ "ከቤቴ ሰባት ሆኜ ወጣሁ፤ አሁን የተርፍነው እኔና ይህች የምታይዋት ሕፃን ብቻ ነን፤ ሌሎቹ፣ እናታቸው ጭምር፣ በመንገድ አለቁብኝ" ብሎ ነገረን፡፡ ስንት ቀን አምቀነው የነበረው እምባ እንደጎርፍ ወረደልን፤ ወጣልን፡፡

አካባቢውን ዞረን ካየን በኋላ እዚያው ስብሰባ አድርገን መውሰድ ስላለብን እርምጃ ተወያየን፡፡ ባቲ ላይ ትልቅ የእርዳታ ጣቢያ በተቻለ ፍጥነት እንዲቋቋም ወሰንን፡፡ ለጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች ወድያው አዲስ አበባ ደውለን አስፈላጊውን የግንባታ ቁሳቁስ አዘጋጅተው ባቲ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ደርሰው ጣቢያውን የማቋቋም ሥራ እንዲጀመሩ ትእዛዝ አስተላለፍን፡፡ ተወዳዳሪ በሌለው ፍጥነት ጣቢያው ተቋቋመ፡፡ በእድሜ ልጅ ቢሆንም በሥራ ውጤቱ ማኅበሩ የሚኮራበት መስፍን ሃለፎም የጣቢያው ኃላፊ እንዲሆን ተመረጠ፡፡

የባቲ ጣቢያ እንዲከፈት ውሳኔ አድርገን ወደ አዲስ አበባ አመራን፡፡ መንገዱ ግራና ቀኝ እጅግ ከመድረቁ የተነሳ መሬቱ ሳር የሚባል ነገር በቅሎበት የሚያወቅ አይመስልም ነበር፤ መልኩ ቡናማ ወይም የቀይ ዳማ ይመስላል፡፡ በሰማይ ላይ የሚታይ አንድ የደመና ምልክት የለም፡፡ በየመንገዱ ሕዝቡ ከብቱን እየነዳ ሲሄድ ይታያል፡፡ ወደገበያ መሄዳችን ነው ይሉናል፡፡ አንድ ከብት የሚያወጣው ሃያ ብር ገደማ እንደነበር ትዝ ይለኛል፡፡ ሰንበቴ፣ ሰሜን ሸዋ፣ ስንደርስ አንድ የጣልያን ተወላጅ የተራበው ሕዝብ የሚሸጠውን የብር ጌጣጌጥ ሲገዛ አየን፡፡ ከኔ ግዛ ከኔ ግዛ የሚል

ብዙ ሰው ከቦታል:: ሰውዬው የሚገዛበት ዋጋ ጌጦቹ በገበያ ከሚያወጡት ዋጋ አንድ መቶኛ እንኳ እንደማይሆን ግልጽ ነበር:: ጣልያኑ ከአዲስ አበባ ድረስ የመጣው ሕዝቡ ከመቸገሩ የተነሳ ከመቶ ዓመታትና ከዚያም በላይ ከትወልድ ትውልድ ሲተላለፍ የመጣለትን ቅርሱን እንደሚሸጥ ደርሶበት በሰው ችግር ነግዶ ለማትረፍ ነበር:: ሁኔታው በጣም ስላሳዘነን ሰውዬን ወረፍነው፣ አካባቢውንም ለቆ ሄደ::

አዲስ አበባ በተመለስን ማግስት ባህል ሚኒስትሩ ሻለቃ ግርማ ይልማ ቢሮ ሄጄ በተለይ በሰንበቴ ያየነውን ነገርኩት:: "የባሕል ሚኒስቴር ጌጦቹን በተወሰነ ዋጋ ይግዛ፣ የሻጮቹን ስምና አድራሻ በቅጡ መዝግቦ ይያዝ፣ ክፉው ቀን ካለፈ በኋላ ሚኒስቴሩ የከፈለውን ገንዘብ ተቀብሎ ጌጦቹን ለባለቤቶቻቸው ይመለስ" የሚል ሐሳብ አቀረብኩለት:: ጥሩ ሐሳብ ነው፣ አስፈላጊውን አደርጋለሁ ብሎ አሰናበተኝ:: ጥቂት ወራት ቆይቼ ምን እንዳደረገ ጠየቅሁት:: ወደ ሰንበቴ ሠራተኞቹን ልኮ ከሚሸጡት ጌጦች በያይነቱ ገዝተው እንደተመለሱና በናሙናነት ተመዝግበው እንደተያዙ ነገረኝ::

አዲስ አበባ እንደገባን የበላይ ጠባቂውን ፍቅረሥላሴን በአስቸኳይ ልናነጋግርህ እንፈልጋለን ብለን አስጠራነውና በጽሕፈት ቤቱ ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ተገናኘን:: ስለመዐቱ በዝርዝር ገለጽንለት፣ ባቲ ያየነውን በቪዲዮ ቀርጸነው ስለነበር አሳየነው:: ተንሰቅስቆ ማልቀሱ ትዝ ይለኛል::

ፍቅረሥላሴ ወድያው ለመንግሥቱ ነገረው:: የፖሊት ቢሮ ስበሰባ በአስቸኳይ ተጠራና ስለተከሰተው ድርቅ እንደሚከተለው ተነጋግረውበታል::

የፖሊት ቢሮ አባላት፣ "ይህ ሁሉ ውርጅብኝ በሕዝቡ ላይ ሲዘንብ እንዴት አልተነገረንም?"

የድርቅ ኮሚሽነር ዳዊት፣ "ምነው ጌቶቼ፣ ብዙ ጊዜ ነግሬአችሁ፣ ተዉ እንጂ፣ ጆሮ ዳባ ልበስ ብላችሁ እንዳልሰማ አልሆናችሁም? የ10ኛው አብዮት በዓላችን እንዳይበላሽብን ነገሩ በጥንቃቄ ይያዝ አላላችሁኝም? ተዉ እንጂ፣ ጌቶቼ"

የፖሊት ቢሮ አባላት፣ "ስማ ዳዊት፣ አልነገርከንም ካልን አልነገርከንም ነው፤ ቢገባህ ይሻላል፤ እምቢ ካልክ እንዲገባህ እናደርጋለን።"

የባቲ እርዳታ ጣቢያ ሙሉ በነበረበት ወቅት ከ10ሺ በላይ ረኀብተኛ አርፎ ተስተናግዶበታል። ጣቢያውን መንግሥቱ ኃይለማርያምና ዝነኞች ሰዎች፣ ለምሳሌ፣ የፕሬዚዳንት ጆን ኤፍ ኬነዲ ወንድም ሴኔተር ኤድዋርድ ኬነዲና ከአክተሮች ደግሞ ቻርልተን ሄስተንና ጃክ ኒክልሰን ጎብኝተውታል።

የጣቢያውን እንቅስቃሴ ለመመልከት ሁለት ጊዜ ሄጃለሁ። በመጀመሪያው ጉብኝት ወቅት ባቲ ገብተን ያደርን ዕለት ሌሊቱን 97 የሞቱ ሕፃናት ከየማረፊያቸው በማግስቱ ጠዋት ተሰብስበው ተቀብረዋል ። ከጣቢያው ሠራተኞች መደበኛ ሥራዎች አንዱ ጠዋት ጠዋት እየዞሩ አስከሬን መሰብሰብ ነበር። በተለይ ሕፃናቱ ከረጅም የእግር ጉዞ በኋላ ጣቢያ ደርሰው ሰውነታቸው ዘና ሲልና የሚቀመስ ነገር አፋቸው ውስጥ ሲገባ የሚሞቱት ጥቂት አልነበሩም።

ባቲ የምትገኘው በስምጥ ሸለቆ አናት ላይ ነው። በከተማው ምሥራቅና ደቡብ ምሥራቅ የሚታየው ዝቅተኛ መሬት በምላጭ ተላጭቶ ቀይ አፈር የተነሰነሰበት ይመስላል። ዛፍም ሆነ ጢሻ ለመሐላ አይታይም። ጥቂት ሰዎች ሆነን የተጋለጠውን መሬት እያየን የኢትዮጵያ መሬት በያለበት እየተጋለጠና አፈሩ እየተጠራረገ ስለመሄዱና ድርቅ እየከፋ ስለመምጣቱ እናወራለን። ከመካከላችን አንዱ አካባቢውን ለረጅም ጊዜ የሚያውቀው ኖሯል። ከከተማው ግርጌ ስላለው ስለተጋጠው ስፍራ የሚከተለውን ነገረን።

ስፍራው ከሃያ ዓመታት በፊት መቶ በመቶ በደን የተሸፈነ ነበር፡፡ ከላይ ሲታይ ትልቅ አረንጓዴ ምንጣፍ መስሎ ይታይ ነበር፡፡ ከብት ውስጡ ከገባ ፈልጎ ለማግኘት ረጅም ጊዜ ይፈጅ ነበር፡፡ ውስጡ ሲገባ ስፍራው ከፀሐይ ንዳድ የተጠለለ ስለነበር ቅዝቃዜው በጣም ተናፋቂ ነበር፡፡ መሬቱ ርጥበት የማይለየው ውሃ የሚተፋ ይመስል ነበር፡፡ በሌላ አንጻር የሽፍታ መደበቂያም ነበር፡፡ ሁሉም ነገር በነበር አለቀ፡፡

በሃያ ዓመት የታየው ልዩነት እንደ ሰማይና መሬት ርቀት ነበር ማለት ነው፡፡ እዚያ ቆመን ይህን ታሪክ ከሰማን ሌላ ሃያ ዓመታት አልፈዋል፤ አካባቢው አሁን ምን ይመስል ይሆን? እያልኩ አሰላስላለሁ፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ የሄድኩበት፣ ከአራት ወይም አምስት ዓመታት በኋላ፣ የአካባቢው መሬትና ሰው መልሶ እንዲያገግም ለመርዳት ቀይ መስቀል ከእህት ማኅበራት ባገኘው እርዳታ የሚያካሄዳቸው የልማት ፕሮጀክቶችን፣ ለምሳሌ፣ ደን ተከላን፣ የውሃ ግድብ ሥራንና የተጎዳ መሬት እንዲያገግም ከብት እንዳይገባበት ለመከላከል የሚካሄደውን እንቅስቃሴ ለመመልከት ነበር፡፡ ፕሮግራሙ ሌሎችም ዘርፎች ነበሩት፡፡

ባቲ ውስጥ ያየሁት ሕልም እንጂ እውነት አልመስልህ አለኝ፡፡ ጣቢያው የለም፡፡ ሕይወትን ተላብሶ ላይ ታች የሚራወጥ እንጂ በጣረሞት ተይዞ የሚንፏቀቅ ወይም የአልጋ ቁራኛ የለም፡፡ ጠዋት ጠዋት አስከሬን የሚከማችበት ስፍራ የጓሮ አትክልት ማብቀያና የችግኝ ማፍያ መደብ ሆኗል፡፡ እራሱን መቻል ለተሳነው ምግብ የማብሰያ ቦታ የነበረው አሁን የልማት ማስፋፊያ ማእከል ሆኗል፡፡ በከተማው እራስጌ የውሃ ግድብ ተሠርቷል፤ የጓሮ አትክልት በመስኖ ይጠጣል፤ ዝናብ ቢከዳ መጠነኛ ምርት የሚገኝበት ዘዴ ተቀይሷል፡፡ ይህን ሁሉ ማየት በመቻሌ ምን ያህል የመንፈስ እርካታ እንደተሰማኝ መገመት አያዳግትም፡፡ ሰው ለበጎ ሥራ ከተነሳሳና ከተባበረ የማይቻል ነገር የለም የሚለውን እምነቴን አጠናከረልኝ፡፡ ድርቅ አገራችንን በተደጋጋሚ እንደሚመታ የታወቀ ስለሆነ የሚቀጥለው ውርጅብኝ ምን መስሎ በየት በኩል ጭኖ ይመጣ ይሆን? ብዬ

ስለነገው መተከዜ ባይቀርም ዛሬ በተገኘው ውጤት ለጊዜው ረክቼ የነገውን ለነገና ለማያልቅበት አምላክ ተውኩት፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ባለሙያዎች ማኅበር

የ1975 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ምሩቃን አንድ ምሽት አምስት ኪሎ አካባቢ በዓል ያዘጋጁና ከውጭ የተወሰኑ ሰዎችንና አስተማሪዎቻቸውን ይጋብዛሉ:: እኔም ከተጋባዦቹ አንዱ ነበርኩ:: ምሩቆቹ ተጋባዡን የጠሩት ለመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን ለሌላም ቁም ነገር እንደነበር ገልጹልን:: ዋና ጉዳይ አድርገው ያቀረቡት በአገሪቱ የሥራ አመራር ሙያ የቀሰሙ ሰዎች የሙያ ማዳበሪያ ማኅበር ስለሌላቸው አንድ ምሩቅ ዩኒቨርስቲውን ለቆ ከወጣ በኋላ ከዩኒቨርስቲው ጋር የነበረው ግንኙነት ስለሚቋረጥ ሙያውን ለማዳበር ዕድል ስለሌለው የወደፊት ዕድላቸው እንዳሳሰባቸው ገለጹ:: አያይዘውም፣ በዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብና በሥራ አመራር ላይ በተሰማሩት ሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት በጣም ደካማ ስለሆነ የዩኒቨርስቲው ኮምዩኒቲ ስለሥራው ዓለም በተጨባጭ የሚያውቀው በጣም ውስን ስለሆነ በዚያው ልክ ጠቃሚነቱ በጣም ውስን ሆኖ ቀርቷል:: እንዲሁም፣ በሥራ ዓለም ያሉት የሥራ አመራር ሙያተኞች ደግሞ ስለዘመናዊ ሥራ አመራር የሚቀስሙበት መድረክ ውስን ስለሆነ የሚከተሉት የሥራ አመራር ዘይቤ ኋላ ቀርና የዘመኑን ግኝት ያልተከተለ መሆኑ ስለማይቀር ውጤታማነታቸው የተገደበ ሆኖ ይቀራል:: ስለዚህ፣ ሙያውን ለማዳበርም ሆነ በሁለቱ ክፍሎች መካከል ግንኙነት ለመመሥረትና ለማጠናከር የሥራ አመራር ባለሙያዎች ማኅበር ማቋቋም

እንደሚያስፈልግ ያላቸውን አስተያየት ገልጸው ተጋባዦች በበኩላቸው ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ ፈለጉ::

ውይይት ተደረገ:: ሐሳቡ በጣም ጥሩ ስለሆነ ግፋበት ብለን መከርናቸው:: እነሱም ሲመልሱ እኛም የፈለግነው የናንተን ድጋፍ ነበር፤ ስለጉዳዩ ቀደም ብለን አስበንበታል፤ የመሥራቹ ኮሚቴ ሰብሳቢ ታደሰ እንዲሆን ሐሳብ እናቀርባለን አሉ:: ቤቱም ተስማማላቸው:: እኔም እሺ አልኩ::

በዩኒቨርስቲው ኮምዩኒቲና በሥራ ላይ በተሠማሩ የሥራ አመራር ባለሙያዎች መካከል ግንኙነት ስለአለመኖሩ ዘወትር አስብ ነበር:: ብሔራዊ ባንክ ውስጥ እስከዚያን እለት ከስምንት ዓመት በላይ ከዚያም በኋላ አምስት ዓመት ያህል በጠቅላላው ዐሥራ ሦስት ዓመት ሠርቻለሁ:: ከዩኒቨርስቲው የንግድ አስተዳደር ኮሌጅም ሆነ ከኤኮኖሚክስ ዲፓርትመንት አንድም ሰው ቢሮዬ ድረስ መጥቶ ስለሞኒታሪ ፖሊሲ፣ ስለኤክስቼንጅ ሬት ፖሊሲ፣ ስለወለድ ፖሊሲ፣ ስለገንዘብ ድርጅቶች አሠራርም ሆነ አደረጃጀት፣ ወዘተ ያነጋገረኝ ስለመኖሩ አላስታውስም:: በዚህ እገረም ነበር:: የዩኒቨርስቲው አስተማሪዎች በኃላፊነት ላይ ያሉትን ሰዎች ቢያነጋግሩና አስተሳሰባቸውን ቢያውቁ ጠቀሜታው ለተማሪዎቻቸው ብቻ ሳይሆን ለባንክም ሆነ ሌላ ለሚመለከተው ዘርፍ ኃላፊዎች ነው::

አንድ ሰው የሚሠራውን የሚያይለትና እንዲህ ብታደርግ፣ ያን ባታደርግ የሚለው ሰው ካለ ፖሊሲውንና አሠራሩን ለማሻሻል የሚኖረው ዝንባሌ ከፍ ይላል:: ይህም ሲባል በነበረው የጊዜው ሁኔታ ሥር ነቀል ለውጦች ማምጣት ይቻል ነበር ለማለት ሳይሆን አንድ ባለሥልጣን አስተሳሰቡም ሆነ አፈጻጸሙ ትክክል አለመሆኑን ደጋግሞ የሚነግረው ሰው ካለ በጉዳዩ እንዲያስብበት ይገፋፋል:: ለውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነም ጊዜ ጥሎት ያልፍና ቦታውን ለሌላ እንዲለቅ ይገደዳል:: የዩኒቨርስቲው ኮምዩኒቲ የካታሊስትነት ሚናውን በትክክል መጫወት መቻል ይኖርበታል:: መንግሥት ይመጣል፣ መንግሥት ይሄዳል፤ ዩኒቨርስቲው ከእውቀትና

ዐዋቂዎች አመንጪነት በተጨማሪ እራሱን የሕዝብ ጥቅምና እንባ ጠባቂ አድርጐ ማቅረብ ሲችል ባለሥልጣኑ እነዚያ ሰዎች ምን ይሉ ይሆን? ብሎ አንገቱን አዙሮ ማየቱ አይቀርም፡፡ በዩኒቨርስቲው ኮምዩኒቲና በሥራ ላይ በተሰማሩት ባለሙያዎች አንድ ትልቅ ጉድባ በመካከላችን እንዳለ ይሰማኝ ነበር፡፡ አገናኝ ድልድይ የሚገነባ ኃይል ብቅ ሲል ወቅቱ አሁን ነው ብዬ ታጥቄ ተነሳሁ፡፡

ስድስት ኪሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ቅዳሜ ቅዳሜ እየተሰበሰብን የመተዳደሪያ ደንቡን አርቅቀን በጥቅምት 1976 መጨረሻ ጨርሰን ከዚያም ማኀበሩን ለማስመዝገብ በሀገር ውስጥ ደኅንነት ጥበቃ ድርጅት ውስጥ ወደሚገኘው ማኀበሮች ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሄድን፡፡ አባላት ከመመዝገባቸው በፊት ማኀበሩ ሕጋዊ ሰውነት ማግኘት ነበረበት፡፡ ለምዝገባ በቀረበው መተዳደሪያ ደንብ ላይ አምሳ ሰባት ባለሙያዎች በመሥራች አባልነት ፈርመናል፡፡ መስፍን ገናናው፣ አስማማው እነቁባህሪ፣ መክብብ ክፍሌ፣ ሺፈራው መታፈሪያ፣ አርአያ ብርሃኑ፣ ትዕግስቱ ገዛኸኝ፣ መንጋው ይሁኔ፣ በቀለ ገሙ፣ ሰይፉ ደምሴ፣ አድማሱ አስፋው፣ አሸብር አበራ፣ ፍስሐ አፈወርቅ፣ ኃይሌ መንግሥቱና አየለ ደምሴ ይገኙበታል፡፡

የመሥራች አባላት ተጠሪዎች፣ ማለት የጊዜያዊው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት፣ ሜክሲኮ አደባባይ ላይ ወደሚገኘው ወደ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ ሄደን የዐሥሩንም ጣቶቻችንን አሻራ ሰጠን፡፡ የደኅንነት ሚኒስቴር ደግሞ የሕይወት ታሪክ ቅጽ አስሞላን፡፡ ቅጹ፣ አድራሻ፣ የትውልድ ስፍራ፣ አሁን ያለበት መሥሪያ ቤት፣ በፊት ተቀጥሮበት የነበረው ሥራ፣ የተማረበት ትምህርት ቤት አድራሻ፣ በትምህርት የሚሰጠውን በመፈጸም ያገኘው ውጤት፣ ለምን በማኀበሩ አባል ለመሆን እንዳቀደ፣ ከዚህ በፊት በሌላ ማኀበር ወይም ድርጅት አባል እንደሆነ የሚጠይቅ ነበር፡፡

የምዝገባው ማረጋገጫ አንድ ሳምንት ባልበጠ ጊዜ ውሰጥ ይመጣል ብለን ስንጠብቅ ሰርተፊኬቱን ያገኘነው ከሁለት ወር ተኩል በኋላ በጥር አጋማሽ ነበር፡፡

የምዝገባው ጉዳይ እልባት እንዳገኘ የአባላት ምዝገባ ጀመርን:: የተጠቀምንበት ዘዴ ማስታወቂያ ሳናወጣ የሰማው ላልሰማው በማስተላለፍ ስማ በለው ዘዴ ነበር:: ባጭር ጊዜ ከአምስት መቶ በላይ አባላት መዘገብን:: ምዝገባው በንግድ አስተዳደርና በሕዝብ አስተዳደር የተመረቁትን ያጠቃልላል:: እኛ የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች በነበርንበት ወቅት የንግድ አስተዳደር ኮሌጅ እራሱን የቻለ ነበር፤ ከአብዮት ፍንዳታ በኋላ ይመስለኛል ኮሌጁና የፐብሊክ አድሚኒስትሬሽን ዲፓርትመንት እንዲዋሃዱ ተደረገ:: አንዳንድ የንግድ አስተዳደር ኮሌጅ ምሩቃን እንደሚሉት ይህ እርምጃ የተወሰደው የንግድ አስተዳደር ሙያን ለማዳከም ታቅዶ ነው::

ባለሙያው የደፋውን አንገት ቀና አድርጎ ሙያውን ለማዳበር የነበረው ፍላጎት በጣም የጋለ መሆኑን ተረዳን:: በጣም ደስ አለን:: የኢትዮጵያን ተስፋ የሚያለመልሙ ባለሙያዎች ተሰባሰቡ አልን:: ሁሉም በየመስኩ ተመሳሳይ እርምጃ ቢወስድ አገሪቱ ኋላቀርነትን ከኋላዋ የምታደርግበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም አልን::

የመጀመርያውን የአባላት ጉባኤ ለመጥራት ዝግጅት ጀመርን:: የስብሰባው ዓላማ መተዳደሪያ ደንቡን ለማጽደቅና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ለማስመረጥ ነበር:: በደኅንነት ሚኒስቴር መመሪያ መሠረት ስብሰባ ከመጥራታችን በፊት ስብሰባው መቼና የት እንደሚደረግና ስንት ሰው እንደሚገኝ ገልጸን ሚኒስቴሩን ፈቃድ መጠየቅ ነበረብን:: ጥያቄያችንን ደንቡን ተከትለን አስገባን::

የስብሰባውን ፈቃድ እየተጠባበቅን እያለ አንድ ቀን ሁለት ፖሊሶች በሁለት ሞተር ቢሲክሌት ሆነው ባንክ ድረስ ይመጡና ታደሰን በእግር በፈረስ እንፈልገዋለን ይላሉ:: እንዳጋጣሚ ከመሥሪያ ቤት ውጭ ስለነበርኩ ሳያገኙኝ ይቀራሉ:: ጸሓፊዬ ብርቱካን አለሁበት ድረስ ትደውልና በጥብቅ እንደምፈለግ ትነግረኛለች:: የሚፈልጉኝን ሰዎች በስልክ አነጋገርኳቸው:: ለማኅበሩ የተጠሰውን የምዝገባ ሰርተፊኬት በ0ሥራ ሁለት ሰዓት ውስጥ

ለመዝጋቢው መሥሪያ ቤት እንድመልስና ማኅበሩ እንደሌለ እንድንቆጥር ተነገረኝ:: አለቀ፣ ደቀቀ::

መንግሥት ሐሳቡን ለምን እንደለወጠ በይፋ የነገረኝ ሰው የለም:: የሰማሁት እንደሚከተለው ነው:: የሶሻሊዝም ርእዮተዓለም ጠባቂዎች ነን ባዮች እነመንግሥቱን እናንተ ምን ማድረጋቸሁ ነው? የወዛደር መንግሥት እናቋቁማለን እያላችሁ የወዛደሩን ጠላቶች እንዴት ታደራጃላችሁ? አብዮቱን የሚፈታተን ኃይል እንዴት ትፈጥራላችሁ? ብለው እንደገሰጿቸው ሰማሁ::

የጊዜያዊው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላት ደጃች ውቤ ሰፈር በሚገኘው አዲስ አበባ ምግብ ቤት የመጨረሻውን እራት በላንና ተለያየን:: ሌላ መንግሥት ሲመጣ የማኅበሩን አስፈላጊነት ማመኑ ስለማይቀር ሰነዶቹ ተሰባስበው አንድ ስፍራ እንዲቀመጡ ተስማማን:: ብሔራዊ ባንክ ካዝና ውስጥ እንዲቀመጡ አደረግሁና ከባንኩ ደረሰኝ ተቀበልኩ:: በተለይ ዋጋ ያላቸው የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብና አባላት የሞሏቸው የአባልነት ፎርሞች ናቸው:: የደረሰኙን ፎቶኮፒ ለባልደረባዎቼ ሰጠኋቸው::

አንድ ቀን መንግሥቱ ቢሮ ስለአንድ ጉዳይ ስንወያይ የሥራ አመራር ባለሙያዎችን ስለማደራጀት አነሳብኝ:: ማኅበሩን ለማደራጀት ስላደረግሁት ጥረት እንደተነገረው ግልጽ ሆነልኝ:: ጠቃሚነቱን አበክሬ ነገርኩት:: እንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ወይም እንደሚያስቡት የአሠሪዎች ማኅበር ሳይሆን የሥራ አመራር ሙያን ለማዳበር የታሰበ መሆኑን፣ ባለሙያዎቹ የድርጅቶች ባለቤቶች ሳይሆኑ አነሱም እንደማናቸውም ሠራተኛ ተቀጣሪዎች መሆናቸውን፣ ያገሪቱ ትልቅ ችግር በሥራ አመራር ሙያ የሠጠለኑ ሰዎች ቁጥር አናሳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሙያቸውን ማዳበር የሚችሉበት ሁኔታ እንዳልተመቻቸ አስገነዘብኩት:: ሌላም ቦታ ደጋግሜ እንዳነሳሁት መንግሥቱን በግሉ ሲያገኙት የማይከብድ ሰው ነው፤ የማድመጥ ችሎታው ከፍተኛ ነው:: እኔ በግሌ እሱ ዘንድ ስቀርብ ምንም ዓይነት ፍራቻ ወይም መርበትበት ስለማይሰማኝ የልቤን ለመናገር

አልፈራውም ነበር፡፡ በከፈተልኝ ቀዳዳ ገብቼ ስለሥራ አመራር ማኅበር አስፈላጊነት የምችለውን ያህል አስረዳሁት፡፡

ፈቃዱ በተሰረዘ ልክ በአምስተኛው ዓመት የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስኪያጅ ካፕቴን አየለ ኃይሌ በጻፈው ደብዳቤ ማኅበሩ እንዲቋቋም መንግሥት መፍቀዱን ገለጸ፡፡ እኔ በዚህ ጊዜ ያለሁት ውጭ ንግድ ሚኒስቴር ነው፡፡ ብሔራዊ ባንክ ሰነዶቹን ለኢንስቲትዩቱ ተወካዮች እንዲያስረክቡ ጻፍኩላቸው፡፡

ማኅበሩን የማደራጀት ኃላፊነት መንግሥት ተረከበ ማለት ነው፡፡ የመተዳደሪያው ደንብ ሲረቀቅ የነበረው ዋና ክርክር ማኅበሩ ከመንግሥት ቁጥጥር ሙሉ በሙሉ ነጻ ይሁን? ወይስ መንግሥት ስለማኅበራት መደራጀት ባወጣው መመሪያ መሠረት ይፈጸም? የሚለው ነበር፡፡ ነጻ ማኅበር ሆኖ ካልተደራጀ በጉዳዩ እንደማልኖርበት አቋሜን ግልጽ አድርጌ ነበር፡፡ ደንቡ የተዘጋጀው ምንም ዓይነት የመንግሥት ቁጥጥር እንደማይኖርበት ተደርጎ ነበር፡፡፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# ውጭ ንግድ ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ ማእከላዊ ኮሚቴ አባል በተባልኩ በሁለተኛው ዓመት አንድ ቀን መንግሥቱ ቢሮው ያስጠራኝና “ከአብዮቱ ፍንዳታ ጀምሮ ከኛ ጋር አብረህ ተጉዘህ መጥተሃል፤ የገንዘብ ድርጅቶች አደረጃጀትና አመራር አመርቂ እንዲሆን ስላደረግኸው ውጤት በሚገባ እናውቃለን፤ ለድካምህ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብን ተገንዝበናል፤ ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር ተዛውረህ እዚያ ያለውን ሥራ እንድትመራልን አስበናልና አንተስ ምን ታስባለህ?” ብሎ ይጠይቀኛል።

የሰው ልጅ አካሄዱን እንጂ የሚሄድበትን አያውቀውም። የዩኒቨርስቲ አራተኛ አመት ተማሪ በነበርኩበት ወቅት አቶ በቀለ ትንሣኤ ቃል የገባልኝን የትርፍ ሰዓት ሥራ ሰጥቶኝ ቢሆን ኖሮ የኔ ሙያ በሒሳብ ሠራተኛነት ትምባሆ ሞኖፖል ይጀመር ነበር እንጂ ባንክን ገንዘብ ለማስቀመጥና ለማወጣት ካልሆነ በቀር አልረግጠውም ነበር። ባንክ ከገባሁ በኋላ ግን ሌላ የሥራ ዘርፍ እቀይራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። አሜሪካን አገር ተማሪ ሆኜ እወስዳቸው የነበሩት የትምህርት ዓይነቶች ባንክና ገንዘብ አስተዳደር ነክ ነበሩ። ከባንክ ውጭ የሥራ ዓለም ያለ አይመስለኝ ስለነበር መንግሥቱ በሹመት ስም ከባንክ አውጥቶ ሊጥለኝ መሆኑን ሲያሳውቀኝ በጣም ደነገጥኩ፤ ከባሕር ውስጥ አውጥተው እንደሚጥሉት ዐሣ የምሆን መሰለኝ።

የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እራሱን ችሎ መቋቋሙ ስሕተት ነው ከሚሉት ውስጥ እኔም ነበርኩበት። ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርባቸው ምርቶች ዓይነታቸውም ሆነ መጠናቸው በጣም ውስን ስለሆነ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ይቋቋም ቢባል እንኳን ወቅቱ ገና ነው የምንል ጥቂቶች አልነበርንም። በሚኒስቴሩ ስም ስለሚሠሩ ሥራዎች ወይም ስለሚደረጉት እንቅስቃሴዎች ከዳር ሆኜ እያየሁ እታዘብ ነበር። አልፎ አልፎም ማሽሟጠጤ አልቀረም። ሚኒስቴሩ ለራሱ ሥራ ከመፍጠር አኳያ ከግል ነጋዴዎች ጋር እየተወዳደረ ጥሬ ቆዳና ሌጦ፣ የቅባት እህልና ጥራጥሬ ወደ ውጭ የሚልኩ ሁለት ድርጅቶችን አቋቋመ። እንዲሁ ሸቀጣሸቀጥ ኢምፖርት የሚያደርግ ድርጅት አቋቋመ። የመንግሥት የረጅም ጊዜ ዓላማ ወጪና ገቢ ንግድን ቀስ በቀስ መንግሥት በሞኖፖል እንዲሠራው ጉዞውን መጀመሩ ነበር። ፖሊሲውን በብሔራዊ ባንክ በኩል ስንመረምረው የግሉ ዘርፍ ተሯሩጦ ምርት አሰባስቦ የመላክ አቅምና ፍላጎት ስላለው በውጭ ምንዛሪ ግኝት አኳያ የሚኒስቴሩ መፈጠር አስፈላጊነቱ አልታየንም ነበር። በተጨማሪ፣ ሌሎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ በተለይ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና የመንግሥቱ የቡና ገቢያ ድርጅት በኤክስፖርት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል። በገቢ ንግድም በኩል መንግሥት የሚያስፈልጉትን ዋና ዋና ሸቀጣሸቀጦች በቀጥታ ያስመጣል ቢባል እንኳ ለዚህ ተብሎ አንድ ሚኒስቴር ማቋቋም አያስፈልግም ነበር። በብሔራዊ ባንክ ውስጥ የገቢና የወጭ ንግድ መቆጣጠሪያ መምሪያዎች ስላሉ ወደ ውጭ የተላከ ምርት ክፍያው በውጭ ምንዛሪ ሳይገባ እንዳይቀር፣ እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ የተከፈለበት እቃ ወደ አገር ውስጥ ሳይገባ እንዳይቀር ለመቆጣጣር ባንኩ በሚገባ የተደራጀ ስለሆነ የሚኒስቴሩ መቋቋም የውጭ ምንዛሪ ብክነትን ለመቆጣጠር ታስቦ ከሆነ ከብሔራዊ ባንክ የተሻለ ውጤት ያስመዘግባል ብለን ስላላመንን የሚኒስቴሩ መቋቋም ዋጋቢስ ነው የሚል አቋም ወስደናል። ባጭሩ፣ በማናቸውም መለኪያ የሚኒስቴሩን መቋቋም የደገፍነው ነገር አልነበረም።

ሚኒስቴሩ ስለውጭ ምንዛሪ በጀቲንግና አመዳደብ እንዲሁም ስለአገሪቱ የውጭ ክፍያ ሚዛን ወይም ባላንስ ኦፍ ፔይመንት የዳበረ ግንዛቤ ሳይኖረው በብሔራዊ ባንክ ሥራ እየገባ ለእንዲህ ዓይነት ጉዳይ የውጭ ምንዛሪ እንዲሰጥ እያለ ተጽዕኖ ሊያመጣብን ይሞክር ነበር:: እሱን ለኛ ተዉልን! እናንተ የውጭ ምንዛሪ ግኝት የሚስፋፋበት መንገድ ላይ አተኩሩ፣ ለወጭ ንግድ ተስማሚ የሆነ ፖሊሲ አስቀይሱ እያልን እንመልሳቸው ነበር::

አንድ ትዝ የሚለኝ የጨርቅ እጥረት አለ ተባለና ሁሉም ባመቸው መንገድ ጨርቅ ከውጭ አስገብቶ መነገድ የፈለገበት ወቅት ተፈጠረ:: የኢትዮጵያ አርበኞች ማኅበር ኀላፊዎች ውጭ ንግድ ሚኒስትሩ ዘንድ ይሄዱና የአባሎቻችንን አነስተኛ ገቢ ለመደጎም ከውጭ ጨርቅ አንድናስገባና እንድንሸጥ ይፈቀድልን ብለው ጥያቄ ያቀርባሉ:: ለጠየቁት ጉዳይ የውጭ ምንዛሪ ይፈቀድላቸው ብሎ ሚኒስትሩ ለባንክ ደብዳቤ ይጽፋል:: አንደኛ፣ የውጭ ምንዛሪ ለምን ጉዳይ እንደሚፈቀድ መደልደል የሚኒስቴሩ የሥራ ድርሻ አይደለም፤ ሁለተኛ፣ የተከበረው የአባት አርበኞች ማኅበር የጨርቅ ቸርቻሪ ማድረጉ አሳፋሪ ነው፤ የገንዘብ እጥረት ካጋጠማቸው ጥያቄያቸውን ማቅረብ ያለባቸው ለመንግሥት ነው ብለን ጥያቄውን ውድቅ አደረግነው:: የማኅበሩ መሪዎች በመጀመርያ ተቀይመውን ነበር፤ አቋማችንን ከተረዱት በኋላ ግን ቅሬታቸውን ያነሱልን ይመስለኛል::

ባጭሩ፣ መንግሥቱ ያጨኝ መፈጠሩን ላላመንኩበት የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ኀላፊነት ነበር:: የጠሉት ይወርሳል፣ የፈሩት ይደርሳል የሚለው አባባል ትዝ አለኝና ምን ባጠፋሁ ነው ለዚህ የተዳረግሁት? ማለቴ አልቀረም::

ለመንግሥቱ በሰጠሁት መልስ፣ እኔ ከባንክ ውጭ የማውቀው ሥራ የለም፣ እራሴን የማየው እንደባንክ ባለሙያ ነው፤ በሕልሜም በውኔም ለሌላ ቦታ እታጫለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም፤ በባንክ የሥራ መስክ ገና ብዙ

የሚሠሩ ሥራዎች አሉ፤ ዘርፉን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ብታገል ይሻላል፤ አይ አይሆንም ከተባለም በመደባችሁኝ ቦታ አገሬን ለማገልገል ወደኋላ አልልም አልኩት፡፡

ከባንክ ለምን እንድወጣ እንደተደረገ በይፋ የማውቀው ነገር ባይኖርም አንድና አንድ ሁለት ብዬ የደረስኩባቸው መደምደሚያዎች አሉኝ፡፡ የፓርቲው የኤኮኖሚ ጉዳይ ኀላፊ፣ ፋሲካ ሲደልል፣ የባንክ ፖሊሲዎች የሶሻሊስት ኤኮኖሚ ግንባታን በሚረዱ መልካቸው መቀየስና መቀናጀት ይኖርባቸዋል፤ ይህን እንዳናደርግ የታደሰ በባንክ ውስጥ መኖር እንቅፋት ሆኗል የሚል እምነት የነበረው ይመስለኛል፡፡ አንድ ገዜ ባንኮችን የሚመለከት ስብሰባ በእሱ አስተባባሪነት በፓርቲው ጽሕፈት ቤት ይደረጋል፡፡ ስለስብሰባው እሰማና ምነው ሳትጠሩኝ ቀራችሁ? እለዋለሁ፡፡ በስብሰባው ላይ ከተገኘህ የተሰበሰቡትን ታሳምንብኛለህ ብዬ ሰግቼ ወይም ፈርቼ ነው አለኝ፡፡ አባባሉን ለማመን ቢከብድም እውነት ነው፡፡

እኔን ከቦታው ለማስነሳት ቀደም ብሎም ከተለያየ አቅጣጫ ብዙ ሙከራዎች ስለነበሩ መንግሥቱ አቤቱታ ሲበዛበት አነሳኝ የሚል ግምት ነው ያለኝ፡፡ ስለባላንጣዎቼ ፍላጎት መናገር ብደፍር፣ ብድር በቀላሉ የሚያስታቅፋቸው፣ የውጭ ምንዛሪ ሲጠይቁ በቀላሉ የሚተባበራቸው፣ ብሔራዊ ባንክ ያከማቸው ንዋይ እየተነደለ በፈሰስ መልክ ለመንግሥት የሚገብር፣ መንግሥት ተጨማሪ የብድር ጥያቄ ሲያቀርብ ሳያስቸግር የሚተባበር፣ የሚያስበውን ለራሱ ይዞ የነገሩትን ብቻ የሚያስተጋባ ሰው ተፈልጎ ይምጣልን ያሉ ይመስለኛል፡፡ እኔ ባንክን ለቅቄ ከሄድኩ በኋላ ፍላጎታቸው ተሟላላቸው? ለሚለው ጥያቄ መልሱን መስጠት ባልችልም እኔን የተካኝ በቀለ ታምራትን የምኞታቸው ያህል አንጥፈው የተረማመዱበት አይመስለኝም፡፡

መንግሥቱ ባንክን ለቅቄ እንደምሄድ ወይም ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደምዛወር ቁርጥ ሐሳብ መሆኑን ካሳወቀኝ በኋላ በቦታዬ ማን ቢመደብ

እንደሚሻል ጠየቀኝ፡፡ በቀለ ቢመደብ ይሻላል አልኩት፡፡ በዚሁ መሠረት ስለተፈጸመ በሠራነው ላይ የሚገነባ እንጂ የሚያፈርስ ሰው አልተመደበም ብዬ ደስ አለኝ፣ መጽናኛም ሆነኝ፡፡

ከመንግሥቱ ቢሮ እንደተመለስኩ ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደምዛወር መወሰኑን ለባንኩ ምክትል ኀላፊ ለለገሰ ሞታ በምስጢር ነገርኩት፡፡ ባንኩን ለቆ እንደሚሄድ አውቆ ያልሆነውን ሠርቶ ወይም ወስኖ ሄደ እንዳልባል ከዛሬ ጀምሮ ውሳኔ የሚጠይቁ ጉዳዮችን አብረን እያየን እንወስናለን አልኩት፡፡ በሦስተኛው ወይም በአራተኛው ሳምንት ባንኩን ለቅቄ እስክሄድ ድረስ እየተመካከርን ስንሠራ ቆየን፡፡

በመጋቢት 9፣ 1979 ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር መዛወሬ በሕዝብ መገናኛዎች ተነገረ፡፡

ሚኒስቴሩ ሄጄ ሥራ እንደጀመርኩ የመጀመርያው መጥፎ ገጠመኝ ጸሓፊዬን የሚመለከት ነበር፡፡ የሥራ ሰዓት አልቆ ሠራተኛው ወደየቤቱ ከሄደ በኋላ ጸሓፊዬ ብቅ እንድትል ፈልጌ የውስጥ ስልክ እደውልላታለሁ፡፡ መልስ ባጣ ወደ ቢሮዋ ሄድኩ፣ ግን የለችም፡፡ ወዴት ሄደች? ብዬ ብጠይቅ ወደ ቤቷ ተብሎ ተነገረኝ፡፡ ሌላው ይቅርና እንዴት መሄዶ ነው ብላ ሳትነግረኝ ትሄዳለች? ብዬ በጣም ተናደድኩ፡፡ ከተማሪ ቤት ከወጣሁ ጀምሮ ጸሓፊዎቼ ደኅና እደር ሳይሉኝ ሄደው አያወቁም ነበር፡፡ ይህችኛዋ ሹልክ ብላ ስትሄድ ከኔ ጋር መሥራት የምትችል አይደለችም አልኩና ሌላ ጸሓፊ እንዲያመጡልኝ ጠየቅሁ፣ በማግስቱ እታፈራሁን አመጡልኝ፡፡ ታዲያ ቀን አንድ የተመለከትኩት ነገር ነበር፡፡ ወሌ ሊያረካክበኝ ቢሮ ብቅ ብሎ በነበረበት ወቅት ከሴትዮዋ ጋር ሰላም ሲባባሉ ስላላየሁ በጣም ገርሞኝ ነበር፤ ግር ብሎኝም ነበር፡፡ ሰላም ሊባባሉ ቀርቶ የጎሪጥ ሲተያዩ ነበር ያየሁት፡፡ እኔ ከጸሓፊዎቼ ከሁሉም ጋር የነበረኝ ግንኙነት እንደ እህትና ወንድም ስለነበር ምን ዓይነት ቦታ ነው የመጣሁት? አልኩ፡፡

ሚኒስቴሩ ውስጥ ያለው የሥራ ባሕል ከማውቀው የተለየ ሆኖ አገኘሁት:: ሚኒስትሩ ቢሮ ከሌለ ወይም ወደ ውጭ አገር ከሄደ የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት ሥራ ሚኒስትሩን ተከትሎት የሄደ ይመስል በሥራ ገበታው ላይ የማይገኘው ሠራተኛ ቁጥር ብዙ ነው:: ሚኒስትሩ ቢሮ ሲመለስ ሠራተኛው በቢሮው ሆኖ የሱን ትእዛዝ ይጠባበቃል፣ በፕሮግራም ተይዞ በቋሚነት የሚሠራ ሥራ ያለ አይመስልም:: ሚኒስትሩ ይፈልጉሃል ሲባል ብቻ ተንደርድሮ ሄዶ ማደግደግ ነው :: በባንክ ውስጥ አለቃ አለ የለም ሳይባል ሥራ ይሠራል:: ቀድሞም ስለሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤት የነበረኝ አስተያየት ጤናማ እንዳልነበረ ተናግሬአለሁ:: በጥቂት ቀናት ውስጥ ያየሁትና የሰማሁት የነበረኝን አስተያየት አጠናከረው እንጂ አልሻረውም::

የመምሪያ ኀላፊዎችንና ሚኒስቴሩ የሚያስተዳድራቸው የንግድ ድርጅቶች ኃላፊዎችን ለመተዋወቅና ስለሥራ ፕሮግራም ለመወያየት ፈለግሁና ስብሰባ ተጠራ:: በሰዓቱ ወደ ስብሰባው አዳራሽ ሄድኩ:: ከዐሥራ አምስት እስከ ሃያ የሥራ ኃላፊዎች ሲጠበቁ በአዳራሹ አንድም ሠራተኛ የነበረ አይመስለኝም:: ወደ ቢሮዬ ሳልመለስ እዚያው ቁጭ አልኩና እየተንጠባጠቡ የሚመጡትን መመልከት ጀመርኩ:: መጨረሻ የመጣው የሥራ ኃላፊ የደረሰው አንድ ሰዓት ዘግይቶ ነበር::

ለታደሰ ሦስት ማለት ሦስት፣ አራት ማለት አራት ነው፤ ሌላ ቋንቋ አላውቅምና በሚቀጥለው ጊዜ ለስብሰባ ስትጠሩ ሰዓት አክብራችሁ እንድትገኙ ይሁን አልኳቸው:: ሰዓት በማክበር ረገድ ሁለተኛውም ስብሰባ ከመጀመሪያው ብዙ የተለየ አልነበረም:: ስለሆነም፣ ከንዴት የተነሳ እራሴን ስቼ ነበር ለማለት ይቻላል:: ሥነሥርዓትና የሥራ ክቡርነት ከሰፈነበት ከባንክ አካባቢ አፈናቅለው ማጥ ውስጥ ከተቱኝ ብዬ አዘንኩ:: ሲውል ሲያድር ሥራው በምፈልገው ዓይነትና አቅጣጫ መሄድ ጀምሮ ነበር:: ቢሆንም እራሴን እንደባንክ ሰው እንጂ እንደሚኒስቴሩ ሠራተኛ ዐይቼ አላውቅም:: በትውስት ለተወሰነ ጊዜ እንደመጣሁ አድርጌ ነበር እራሴን የምቆጥረው::

# ጫት

ሌላው ትልቁ ችግሬ ጫት ነበር። ነጋዴዎች ናቸው የተባሉ ግለሰቦች በማኅበር ተደራጅተው ጫት ወደ ጂቡቲ ይልካሉ። ያደራጃቸውም ሚኒስቴሩ ነው። ማኅበሩን ከላይ ሆኖ የሚመራውና ጽሕፈት ቤቱን የሚያስተዳድረው ሚኒስቴሩ ነው። በዚሁ ሳቢያ የጂቡቲው የንግድ ሚኒስትርና የኛ የውጭ ንግድ ሚኒስትር የቅርብ ግንኙነት መሥርተዋል። አዲስ አበባ የሚገኘው የጂቡቲ አምባሳደር ከውጭ ንግድ ሚኒስትሩ ጋር የቅርብ ግንኙነት አለው። የሐረርጌ የፓርቲ ጽሕፈት ቤትና አስተዳደሩ የጫት ጉዳይ መከታተል አንዱ ሥራቸው ነው። ማእከላዊው መንግሥትም አንዳንድ ግለሰቦች ያለአግባብ በጫት ተጠቃሚ ሆነዋል እያለ ሁኔታውን የሚያጣሩ ኢንስፔክተሮችን ይልካል።

ስለሆነም፣ ጫት ባንቅመውም ናላችንን ያዞረ ምርት ነበር። የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ስለጫት ብቻ ለመከታተል የተቋቋመ የሚመስልበት ወቅትና ሁኔታ ትንሽ አልነበረም። በኔ ግምት ሚኒስትሩ ከሥራ ጊዜው ቢያንስ እሩቡን የሚያጠፋው ስለጫት በመከታተል ነበር። ባንድ በኩል ጫት ጎጂ ዕፅ ነው እየተባለ ሶሻሊዝም መመሪያዬ ነው የሚል መንግሥት ምርቱን በፖለቲካና ኤኮኖሚ መሣሪያነቱ በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ መንከባከቡ አሳፋሪ ድርጊት ሆኖ ይታየኝ ነበር። በመሆኑም ጫትን ለሚያመርቱ፣ ለሚነግዱም ሆነ ለሚቅሙ ከበሬታ አልነበረኝም። ከጫት ይህን ያህል ውጭ ምንዛሪ አገኘን ብሎ ዘገባ ማቅረቡ ዘወትር ይተናነቀኝ ነበር።

ውጭ ንግድ እንደሄድኩ መጀመርያ ደውሎ ቀጠሮ የጠየቀኝ የጂቡቲ አምባሳደር ነበር። ቀጠሮውን የጠየቀው ጫት ለጂቡቲ በጣም ተፈላጊ ምርት መሆኑን ሊነግረኝ ብቻ ሳይሆን በተጨማሪም ጂቡቲ ብዙ የውጭ ምንዛሪ ለኢትዮጵያ ገቢ ስለምታደርግ ባለውለታቸው እንደሆንን ሊያስገነዝበኝና ቢሮህ ቢሮዬ ነው ሊለኝ ፈልጎ ነው። በልቤ ጫት በጠፋና ገንዘቡም በቀረብን አልኩኝ እንጂ እሱ እንዳሰበው አያ የውጭ ምንዛሪያችን

አባት ብዬ ሽር ጉድ አላልኩለትም፡፡ በጂቡቲ በኩል ጫቱን የሚቀበለውን ነጋዴ ከኔ ጋር ሊያስተዋወቀው ቀጠሮ እንድሰጠው ጠየቀኝ፡፡ አሁን ገና እዚህ መምጣቴ ስለሆነና ብዙ መመርመርና መከታተል ያለብኝ ፋይሎች ወይም ጉዳዮች ስላሉ ጊዜ ሳገኝ ወደፊት እንነጋገራለን ብዬ ሸኘሁት፡፡ አንድ ሳምንት ያህል ቆይቶ እንደገና ቀጠሮ ጠየቀኝ፡፡ እውነትም ቢሮዬ ቢሮው መሰለው እንዴ? አልኩና መልስ ሳልሰጠው ቀረሁ፡፡ ደጋግሞ ለጸሓፊዬ ደወለ፡፡ ብዙ ሥራ ስላለብኝ አሁን ቀጠሮ መስጠት እንደማልችል ንገሪው አልኳት፡፡ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዘንድ ሄዶ ታደሰ ቀጠሮ ከለከለኝ ብሎ ከሰሰኝ፡፡ ቀጠሮ ሰጠሁትና መጣ፡፡ ቢሮዬ ሲገባ እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ ማስቲካ እያኘከ ነበር፡፡ በሱ ቤት ቀጠሮ ስለከለከልኩት አጸፋውን መመለሱ ነው፡፡ ምነው ቀጠሮ ከለከልከኝ? ቢለኝ፣ ስማ ሰውዬው፣ እኔ እኮ የውጭ ንግድ ሚኒስትር እንጂ የጫት ሚኒስትር አይደለሁም አልኩና ለብልግናው ሒሳብ አስከፈልኩት፤ እብጠቱንም ትንሽ ሳላስተነፍሰው አልቀረሁም፡፡ በምላሹ፣ እሺ የውጭ ንግድ ሚኒስትር ነኝ ስትል እንደጫት የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝልህ በቁጥጥርህ ውስጥ ያለ ሌላ ምርት ጥራልኝ ቢለኝ ዐይን ፍጥጥ ነበር፡፡

ባንክ ሆኜ መንግሥት ያቋቋመው የጂቡቲ ኮሚቴ አባል ነበርኩ፡፡ የኮሚቴው ዓላማ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ሁለገብ ግንኙነት ለማጠናከር ነው፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የመድን ድርጅት በጂቡቲ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች እንዲከፍቱ አድርገናል፡፡ ጽሕፈት ቤቶቹን ለመክፈት ወደ ጂቡቲ ለመጓዝ አንድ ቀን ሲቀረኝ፣ ማለትም ታህሳስ 30፣ 1972፣ ባለቤቴን ሁለተኛውን ልጃችንን ለመውለድ ምጥ ይከጅላትና ዘውዲቱ ሆስፒታል ወስጄ አስተኛኋት፡፡

የበኩር ልጃችን ኅሊና ሁለተኛ ዓመቷን ለማክበር መንፈቅ ያህል ይቀራታል፡፡ ኅሊና የተሰኘውን ስም ያወጣችላት ጸሓፊዬ ብርቱካን ናት፡፡ አንደኛው አያቷ ቀኛዝማች ወልዴ አያኖ የሰጧት ስም ወሰንየለሽ ነበር፡፡ ባለቤቴ የዶቢ ጉራጌ ናት፡፡ የ1966 አብዮት ሲፈነዳ አካባቢ ሙህርና ዶቢ

በድንበር ይጣላሉ:: ሁለቱም መሣሪያ ያከማቻሉ:: በዶቢዎች አመለካከት ድንበር ሲጋፉ የኖሩትን ሙህሮችን ለመቋቋምና የማይረሳ ትምህርት ለመስጠት ጊዜው የኛ ነው ብለው የተነሱ ይመስላል:: መሬታቸውንና፣ ክብራቸውን በጦርነት ለማስመለስ ቋምጠዋል:: ታድያ የዚህ ትርኢት አውጠንጣኞች ስለሚላስና ስለሚቀመስ ሃያ አራት ሰዓት የሚያልሙት ምስኪን ያገርቤት ገበሬዎች ሳይሆኑ በአዲስ አበባ የሚገኙት የሁለቱ አካባቢዎች ተስፈንጣሪ ተወላጆች ናቸው:: ደግነቱ አብዮት መጣና በያሉበት አረጋቸው:: የሙህሩ ታደሰና የዶቢዋ ዕፀገነት ተጋብተን ጎሊና በመወለዷ ልጃችን የሁለቱን ክልሎች ድንበር ሰብራ ባላጋራዎቹን አንድ አደረገቻቸው፣ አሉ ቀኛዝማች ወልዴ:: ክስተቱን ለመግለጽ ከወሰንየለሽ የተሻለ ስም አይኖርም አሉ:: በነገራችን ላይ ሙህርና ዶቢ ፍጥጫ እንደነበራቸው የሰማሁት ቀኛዝማች ቤት ከገባሁ በኋላ ነው:: እዚሁ ስለጦርነት ሌላ የሰማሁት ቀኞ ከራስ መስፍን ስለሺ ጋር ገጥመውት ስለነበር ትግል ነው::

የጠላት ንብረት ተብለው ለራስ መስፍን ከታደሏቸው ሕንጻዎች ውስጥ ባንደኛው የወልዴ ታላቅ ወንድም ገብሬ አንድ ደጃፍ ቤት ተከራይተው ጠጅ ይነግዳሉ:: የኪራይ ውለታ አላቸው:: ገበያ ሲደራላቸው ያየ ምቀኛ ወይም ተቀናቃኝ ንግዱን ሊያስጥላቸው ይፈልግና የተሻለ ኪራይ ልክፈል ብሎ ራስ ወኪል ዘንድ ይቀርባል:: ገብሬ ለቀው እንዲሄዱ ይነገራቸዋል:: ገብሬ ስለገጠማቸው መጥፎ እድል ፍርድ ቤት ሄዶ ክርክር ሲካሄድ ማድመጥና ለተበደለ በነጻ ጥብቅና መቆም ለሚወደው ለታናሽ ወንድማቸው ለወልዴ አስተዛዝነው ይነግራሉ:: ገብሬ ለወልዴ መንገራቸው በወንድምነታቸው ሁኔታውን አውቀው በከንፈር መጠጣ እንዲያግዟቸው እንጂ ከራስ መስፍን ጋር ሙግት እንዲገጥሙላቸው አስበው አልነበረም:: ራሱ የጊዜው ሰው ስለነበሩ እንኳን መሞገት ቀርቶ ቀና ብሎ የሚያያቸው አልነበረም::

ቀኛዝማች ፍርድ ቤት ሄደው ራስ መስፍንን ወይም ወኪላቸውን ይከሳሉ:: ራስ መስፍን ያህን ሲሰሙ ማመን ያቅታቸውና ለመሆኑ ይህ ሰው ማነው?

ብለው ይጠይቃሉ:: ይነገራቸዋል:: "ደፍሮ የከሰሰኝ ለዚያውም ጉራጌ ነው እንዴ?!» ይሉና ቡራ ከረዩ ይላሉ:: ጉዳዩ በሚሰማበት ዕለት ነገሩን የሰማ የከተማ ወሬ አብጠልጣይ ፍርድ ቤቱን ያጣብበዋል:: ራስ መስፍንን ደፍሮ የሚከስ በመገኘቱ ጉድ ተባለ:: ሕዝብ ግልብጥ ብሎ የመጣው ራስ መስፍንን ብቻ ሳይሆን ደፋሩን ወልዴን ጭምር ለማየት ነበር:: ራስም ወልዴን ለማየት ቸኩለዋል:: ፍርድ ቤት ወንበር ቀርቦላቸው እግራቸውን አንፈራጥጠው ይቀመጣሉ፤ ወልዴ ግን እንዲቆሙ ይነገራቸዋል:: ጉዳዩ መሰማት ሲጀምር፣ ወልዴ "ሥነሥርዓት" ይላሉ:: "ምንድነው?" ቢባሉ፣ "ወድቃ በተነሳችው በኢትዮጵያ ባንዲራ፣ ራስ ይነሱ፣ በሕግ ፊት እኔም እርስዎም እኩል ነን፤ በፍርድ ቤት ሥርዓት መሠረት እርስዎም መቆም ይኖርብዎታል" ይሏቸዋል:: ራስ መብቱን አስከባሪ፣ እልኸኛና ጎበዝ ተከራካሪ እንደገጠማቸው አወቁ፤ ያለውዴታ ተነስተው ለመቆም ተገደዱ:: ተመልካቹም ያልጠበቀውን ትንግርት አይቶ ጉድ እያለ ወደየመጣበት ተመለሰና የምስክርነት ቃሉን ባራቱም ማእዘናት አሰራጨው::

በሌላ ወቅት ደግሞ፣ በወልዴ ነገር አደራደርና የክርክር ይዘት የተደነቁ ወይም የረኩ አንድ አፈንጉሥ አፋቸውን ሞልተው "አይ ወልዴ፣ ጉራጌ ባትሆን ኖሮ" ቢሏቸው፣ ወልዴም "ምነው ጌታዬ፣ ሠርቶ ማደር ወንጀል ነው እንዴ? ጉራጌ ሠርቶ ባደረ፣ የሌላው ሕይወት የተሟላ እንዲሆን ጥረት ባደረገ ለምን ስም ይሰጠዋል? አንዳንዱ እንደሚያደርገው እጁን እንደ በሽተኛ በጨርቅ ሸፍኖ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ይለምን ነው ወይስ እንደ ወሮበላ ነጥቆ ይብላ ነው የሚሉት?" ብለው መልሰውላቸዋል:: በኢትዮጵያ ስለራሶችና አፈንጉሦች እንጂ ስለወልዴዎች ገድል ወይም ተጋድሎ ተጽፎ ስላላነበብን የድህነታችን ፈርጁ ስነጽሑፋዊም ታሪካዊም ነው::

ስለጠባብነት፣ ስለትዕቢት፣ ስለድንቁርና፣ በሥልጣን ስለመባለግ፣ ስለማናህሎኝነት፣ ስለማናለብኝነት፣ ስለግፍ፣ ስለአድልዎ፣ ስለ ስንፍና ተነስቶ እነዚህ ሁሉ ለአገራችን በሥልጣኔ ወደኋላ መቅረት ያደረጉት አስተዋፅኦ ሲወሳና ሲጤን የቀኛዝማች ወልዴ ታሪክና መሰሎቹ መነገር

ይኖርበታል፡፡ ያለበለዚያ፣ ችግራችን ችግሩን የደበቀ መድኃኒት አይገኝለትም ሆኖ ይቀርና መጥፊያችን እንዳይሆን ያሰጋል፡፡

ወደ ጅቡቲ ጉዞዬ ስንመለስ ጠዋት ወደ አየር ማረፊያ ከመሄዴ በፊት ነፍሰጡርዋ ባለቤቴ እንዴት እንዳደረች ለመጠየቅ ወደ ሆስፒታሉ ጎራ አልኩ፡፡ የደረስኩት ዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ነበር፡፡ ነፍሰጡሮች የሚገኙበትን ክፍል በሩን ሳንኳኳ አንዲት ነርስ ብቅ አለች፡፡ ባለቤቴ ዕፀገነት ወልዴ ትባላለች፤ ምን ደረጃ ላይ እንዳለች እባክሽን ንገሪኝ ስላት፣ “ገና አሁን ተገላገለች” ብላ መልካሙን ዜና አበሰረችኝ፡፡ ምን? ብላት መልሱ ወንድ የሚል ነበር፡፡ ሳላስበው ዘልዬ እቅፍ አድርጌ ሳምኳት፣ ከንፈርዋን ሳይሆን ጉንጯን፡፡ ከዚያም ደረጃውን እንጣጥ እንጣጥ እያልኩ እንደ ልጅ ተንደርድሬ ወረድኩ፡፡ ሳይነጋ እብድ ከየት መጣ? የሚል ይመስል አንድ ሰው እንዳልደፈጥጠው ጥግ ይዞ እዳሳለፈኝ አስታውሳለሁ፡፡ ከጂቡቲ ጉዞ እንደተመለስኩ አንድ ወዳጄ ይደውልና ጥር ሁለት ቀን በወጣው ጋዜጣ ላይ ከጂቡቲ ጉዞህ ጋር በተገናኘ የታየው ፎቶግራፍህ በጣም ደስ ብሎህ እንደነበር ይገልጻል፤ ምን ብታገኝ ነው? ብሎ ይጠይቀኛል፡፡ ለካስ የአንድ ሰው ፊቱን በማየት ብቻ ስሜቱን ማንበብ ይቻላል? ካልኩ በኋላ፣ የሰጠሁት መልስ ኖላዊ የሚባል ልጅ ከነቃጭሉ የሚል ነበር፡፡ ይኸው ወዳጄ ቤት ብቅ ብሎ ዕፀገነትን እንኳን ማርያም ማረችሽ በማለቱ ገንፎ ሳናበላው የቀረን አይመስለኝም፡፡ አንዳንድ ቀን ሴቶቹ ልጆቼ አድማ አድርገው እጅ ወደላይ ሊያስደርጉኝ ከፈለጉ የመጀመሪያውን ጥይት የሚተኩሱት አንተ እኮ እኛ ስንወለድ ሳትዘል ቀረህ በማለት ነው፡፡ እንዴት አወቃችሁ? ስላቸው የትግል ጓዳችን እናታችን በምስክረነት ተጠራ ይሉኛል፡፡ እኔ የተማርኩት ስለመደብ ትግል ነው፤ ምስክሬ ጄኔራል ብርሃነ፣ ስለጾታ ትግል ያልገባኝ ነኝና እባካችሁን ተዉኝ እላቸዋለሁ፡፡ እርቃችን ጸጉሬን አበስ አበስ፣ ፊቴን ዳሰስ ዳበስ በማድረግ ይደመደማል፡፡

ሰለመደብ ትግል ሲነሳ ጄኔራል ብርሃነ ተፈራ፣ አብዩቱ እንደፈነዳ የፖሊስ አዛዥ የነበሩት፣ ትዝ ይሉኛል፡፡ እነሰናይ ልኬ በቀድሞው ፓርላማ ሕንጻ

ውስጥ ሰብስበው ስለመደብ ትግል ያስተምሩናል:: ጄኔራሉ ትምህርቱ ስላልተዋጠላቸው ስሜታቸውን በአሽሙር ለመግለጽ ይፈልጋሉ:: “ስሙ ወዳጆቼ፣ ሕዝቡ የምናስተምረውን እንዲቀበል ከፈለግን አባባላችንን ማስተካለል አለብን፤ እንደሚታወቀው መደብ ማለት አልጋ ወይም የመኝታ ስፍራ ነው፤ በአልጋ ላይ የሚደረግ ትግል ያው የታወቀው ስለሆነ ሕዝቡን ግራ እንዳናጋባው እንጠንቀቅ» ብለው አሳሰቡ:: ሰናይና ጓደኞቹ እንደበታቸው ለመናገር የሰላ፣ ለማመዛዘኛ የታደላቸው አእምሮ ግን በቀኖና የተሞላ ስለነበር ጄኔራሉ ያተረፉት የአድሃሪ ርዝራዥ መባልን ብቻ ቢሆንም የበላቸውን ጄኔራሉ ያከኩላቸው ተሰብሳቢዎች ስለአባባላቸው ሳይሥቁላቸው፣ እግረመንገዳቸውንም በአስተማሪዎቹ በውስጠ ወይራ ሳይሥቁባቸው አላለፉም::

በጂቡቲ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የጂቡቲ ባለሥልጣኖችን እሹሩሩ ማለት፣ የሚሰበሩ እቃ እንደሆኑ አድርጎ መያዝና የጠየቁትን ሁሉ በቀላሉ መልቀቅ ወይም ማቅረብ ውጤቱ ንቀትን ማትረፍ ወይም በአናታችን ላይ እንዲቀመጡ መፍቀድ ስለሚሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጠንከር ማለት እንደሚያስፈልግና እኛ ጂቡቲን ከምንፈልጋት ይበልጥ እነሱ ያለ ኢትዮጵያ መኖር እንደማይችሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል እያልኩ አሳስብ ነበር:: አምባሳደሩ እጁን ኪሱ ውስጥ ከቶ ማስቲካ እያኘከ ቢሮዬ ሲገባ ሳይ፣ ያልኩት ነገር ይኸው ደረሰ፤ የዘራነውን እያጨድን ነው አልኩና አዘንኩ::

ቆይቶም በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የንግድ ግንኙነት መልክ ለማስያዝ ከንግድ ሚኒስትራቸው ጋር ንግግር ተከፈተ ወይም ድርድር ተጀመረ:: ለጂቡቲ ከጫት ሌላ በተለይ አትክልትና ፍራፍሬ እንሸጣለን::

በ1967 ብሔራዊ ባንክ እንደሄድኩ ለአገር ጥቅም ተቆርቋሪ የነበሩ የባንኩ ሠራተኞች፣ እነዘመረ ጆማነህ፣ ለጂቡቲ የምንሸጠው ፍራፍሬና አትክልት ለአገራችን በውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚደረገው ዐሥራ አምስት ሳንቲም በአንድ ኪሎ ሒሳብ ብቻ መሆኑን ይነግሩኛል:: ስለሆነም አገራችን ተራቁታ የሰው

ቤት አዳባሪ እንደሆነች ተረዳሁ:: ገቢ መሆን ያለበት በኪሎ አምሳ ሳንቲም ነው የሚል ደንብ አወጣን:: እንደተለመደው የጂቡቲ ሰዎችና አቀባባይ ነጋዴዎች ከፍተኛ ተቃውሞ አስነሱ:: አትክልትና ፍራፍሬ ወደ ጂቡቲ መላኩ ተቋረጠ:: ከፍተኛ ውዝግብ ተነሳ:: ነጋዴዎቹ ያደርጉት የነበረው ለሚልኩት አትክልትና ፍራፍሬ ከሚቀበሉት የውጭ ምንዛሪ ውስጥ ጥቂቱን ብቻ ለባንክ ገቢ ያደርጉና አብዛኛውን ውጭ ያስቀሩታል ወይም ለኮንትሮባንድ እቃ መነገጃ ያውሉታል::

እዚህ ውጭ ንግድ ሆኜ የተከፈተውን ንግግር ወይም ድርድር ዳር ማድረስ ስላልተቻለ ወደ ጂቡቲ የሚላከው ጫት ከነአካቴው ቆመ:: የጂቡቲ ጫት ቃሚ ሰማይ የተደፋበት መሰለው:: ሰዎቹ የፈለጉትን ለማግኘት የመጪጫህ፣ ላይ የመውጣት፣ አግድም የመሄድ፣ ታች የመውረድ ዘዴአቸው አሁን አልሠራ አላቸውና ግራ ተጋቡ:: አዲሱ የውጭ ንግድ ሚኒስትር የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ለማበላሸት ታጥቆ የተነሳ ነው የሚል የቅስቀሳ ዘመቻ አወጁብኝ:: አንዳንድ ሰዎቻችንንም የዘመቻቸው ተካፋይ አደረጉ:: የኔ አቋም የኢትዮጵያ ጥቅም ይከበር ስለነበር ቅምም አላለኝም:: ጂቡቲ ትንሽ አገር ስለሆነች እንጫናት አላልኩም:: ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነና ጂቡቲ ኢትዮጵያን ለመጫን ስትሞክር አሻፈረኝ አልኩ እንጂ ሌላ ምንም ምስጢር የለውም:: ጉዳዩ የፖለቲካ ጠባይ ያዘ፤ የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ገቡበት:: ከአቅማቸው በላይ ሆኖ አገኙትና ፋይሉ ወደመንግሥቱና ሐሰን ጉሌድ ተላለፈ:: ሁለቱ መሪዎች ድሬዳዋ ላይ ተገናኝተው ስለሁለቱ አገሮች ግንኙነት በመረመሩበት ወቅት ጉዳዩ እልባት አገኘ:: በኔ ግምት መሪዎቹ የተገናኙበት ዋና ዓላማ እክል የገጠመውን የንግዱን ግንኙነት መልክ ለማስያዝ ሳይሆን አይቀርም::

ስለድሬዳዋ ጫት ማኅበር ሲወሳ ታዬ ጥቁሩና ታዬ ፈረንጁ ትዝ ይሉኛል:: ሁለቱም በንግድ አስተዳደር ኮሌጅ የክፍል ጓደኞቼ ናቸው:: ስለታዬ ፈረንጁ ማንነት ቀደም ብዬ አትቻለሁ:: እኔ ባንክ ሆኜ በአንድ ወቅት የድሬዳዋ ጫት ላኪዎች ማኅበር ሥራ አስኪያጅ ታዬ ጥቁሩ ወይም ታዬ በቀለ

ነበር፡፡ የማኅበሩ አባላትም ሆኑ ሠራተኞች የታዬን የሥራ አመራር ችሎታ በጣም ያደንቁ ነበር፡፡ እንደማስታውሰው የድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካን በዋና ሥራ አስኪያጅነት እንዲመራ በመንግሥት ትእዛዝ ከጫት ማኅበር እንዲዛወር የተደረገ  ይመስለኛል፡፡ በውጭ ንግድ ሚኒስትርነት ስመደብ የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ የደርግ አባል የነበረው ደምሴ ዴሬሳ ነበር፡፡ የሥራ አመራር ችሎታውን ደካማ ሆኖ ስላገኘሁት የጫትን ጉዳይ ቀጥ አድርጎ የሚይዝልኝና ከጫት ጣጣ ሙሉ በሙሉ ሊገላግለኝ ባይችልም ጫናውን የሚያቃልልኝ ሰው መፈለግ አለብኝ ብዬ እያሰላሰልኩ እያለ ደምሴ እራሱን ለማዋደድ ይሁን ወይም ስለሱ ያለኝን አስተያየት ለመፈተሽ ፈልጎ ይሁን በጻፈልኝ ደብዳቤ ሥራውን ሊለቅ እንደሚችል ፍንጭ ያሳየኛል፡፡ ተስማምቻለሁ ብዬ ጻፍኩለት፡፡ ቦታው ክፍት መሆኑን ማስታወቂያ አወጣን፤ ብዙ ሰው አመለከተ፤ ነገር ግን ከቀረቡት ውስጥ ለሥራው የሚመጥን ሰው ሳናገኝ ቀረን፡፡ ታዬ ጥቁሩን አስፈልጌው ቢሮዬ ድረስ መጣ፡፡ ከጉድ እንዲያወጣኝ ጠየቅሁት፡፡ "ደስ ይለኝ ነበር፣ ነገር ግን ከድሬዳዋ የወጣሁት በነፍስ ስፈለግ አምልጬ ነው፤ አሁን ብመለስ ይገድሉኛል፤ ትእዛዛችንን አልቀበልም አለ የሚሉ የፖለቲካ ሰዎች በጥብቅ ይፈልጉኛል፤ ከድሬዳዋ ከወጣሁም በኋላ ለረጅም ጊዜ ተደብቄ ነው የኖርኩት፤ ስለሆነም እባክህን ተወኝ፤ ድሬዳዋ ተመልሼ ክፉ ነገር ቢደርስብኝ ለአንተም የኅሊና ጸጸት ይሆንብሃል» አለኝ፡፡ እሺ ብዬ ተወኩት፡፡

ከዚያም ታዬ ፈረንጁን እንዲተባበረኝ ጠየቅሁት፡፡ በወቀቱ አንድ የዓለም ባንክ ፋይናንስ በሚያደርገው ድርጅት ውስጥ የሒሳብ ኀላፊ ሆኖ ይሠራ ነበር፤ በሥራው ደስተኛ ስለነበር ወደ ድሬዳዋ ሄዶ በተጨማለቀ ቤት ውስጥ ለመዘፈቅ ፍላጎት እንደሌለው ተረዳሁ፡፡ ችግር ውስጥ ገብቻለሁና እርዳኝ አልኩት፡፡ ለኔ ሲል እሺ አለኝ፡፡ ማኅበሩን መልክ አስይዞ ሥራውን ቀጥ አድርጎ ያዘልኝ፡፡ ያለመጠን ይፏልሉ የነበሩትን የጂቡቲ ጫት አስመጭ ነጋዴዎችን ልክ አስገባቸው፡፡ ባሳየው ከፍተኛ የሥራ ውጤት በጣም ተወዳጅ ሆነ፡፡ ጥቅም ያለአግባብ ሲያግበሰብሱ የነበሩትን

የመጠቀሚያ ቀዳዳዎቻቸውን ስለደፈነባቸው ሥራውን ለማበላሸትና ወቀሳ እንዲደርስበት ለማድረግ ሙከራ ያደርጉ ነበር:: መንግሥት ሲለወጥ በታዬ ላይ ተጨባጭ ያልሆነ ክስ መሥርተው ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንዳንገላቱት ሰማሁና በጣም አዘንኩ:: መንግሥት በተለወጠ ቁጥር የሐቀኛ ሥራ አስኪያጆች በሽፍጠኞችና በደካሞች መነደፍ የሚቆመው መቼ ነው? ብዬ መጠየቄ አልቀረም::

ሚኒስቴሩን በመጋቢት 1982 ከለቀቅሁ በኋላ አንድ ወዳጄ አለቃውን ተከትሎ መንግሥቱ ቢሮ ይሄዳል:: መንግሥቱ ኢትዮጵያ ስለጂቡቲ መከተል ያለባትን ፖሊሲ ሲናገር እንደእገሌም ጨርሰን አንለስልስ፣ እንደታደሰም አብዝተን አንጠንክር እንዳለ ነገረኝ:: እውነቱን ለመናገር በጂቡቲ ላይ ከመጠን በላይ እንጠንክር ብዬ አላውቅም:: እል የነበረው፣ ከበሬታ ለማጣት ካልፈለግን በቀር የአገራችንን ጥቅም በቀላሉ አሳልፈን መስጠት የለብንም ነው::

ወደ አምባሳደሩ እንመለስና "እኔ እኮ የፈለግኩህ" አለኝ ሰውዬው፣ "ያኔ ካነሳሁልህ የጫት ነጋዴ ጋር ላስተዋውቅህና የወዳጅነት መግለጫ ስጦታ ልንሰጥህ ነው" ይለኛል:: ሰውዬውን የምተዋወቅበት አንድም ምክንያት የለም፤ የሱ የሥራ ግንኙነት ከጫት ማኅበር ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ጋር ስለሆነ ወደዚያ መሄድ ይችላል፤ ስጦታ የምትለውን አልቀበልም፤ የምትፈልገኝ ለእንዲህ ዓይነት ጉዳዮች ከሆነ ግንኙነታችን እንደሚቋረጥ ማወቅ አለብህ አልኩት:: ሲመልስ፣ አንተ ሞኝ ሰው ነህ ፤ ከአንተ በፊት ለነበረው ሰው ምን እናደርግ እንደነበር ብታውቅ ይቆጭሃል አለኝ:: እኔ ታደሰ ነኝ፤ አሁን የምትነጋገረው ከታደሰ ጋር መሆኑን አትዘንጋ ብዬ አሰናበትኩት::

አንዴ ከመጣሁ አይቀር ሚኒስቴሩን ውጤታማ ለማድረግ አንድ መሠረት መጣል አለብኝ በሚል አስተሳሰብ ሁለት መሠረታዊ እርምጃዎች ቢወሰዱ አገሪቱ ከውጭ ምርቶች የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ እመርታ ሊያሳይ

ይችላል ብዬ አሰብኩ:: አንደኛ፣ ቆዳ በጥሬነቱ መላኩ ቀርቶ ያለቀላቸውን ምርቶች እንደ ወንድ ጃኬቶች፣ የሴቶች ቀሚስና ሱሪ እንዲሁም ጫማና የመሳሰሉትን መላክ፤ ሁለተኛ፣ ከፍጆታ የተረፉ ምርቶችን ለቃቅሞ ወደውጭ ከመላክ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች አምርቶ መላክ የተሻለ ውጤት ያስገኛል የሚሉ ነበሩ:: ስለኤክስፖርት በተነሳ ቁጥር ሽመልስ አዱኛን አስታውሰዋለሁ:: በየጊዜው ባንክና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር እየተጋገዙ ይህን ያህል መጠን ያለው ጥርጥሬ ወደውጭ ተልኮ ይህን ያህል የውጭ ምንዛሪ ተገኘ የሚለውን ዘገባ ሽመልስ የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ባርኔጣ ደፍቶ ሲያዳምጠው ከደሃ አፍ የተነጠቀ ሽሮ የሀብታም መኪና በሚጠጣው ቤንዚን እንደተለወጠ አድርጎ ስለወሰደው፣ ከድሃ ሽሮውን ከወሰድንበት ምን ቀረው? ያለው ለረጅም ጊዜ ኅሊናዬን ሲቧጥጥ የኖረ ጉዳይ ነው::

# ቆዳ

ቆዳን አስመልክቶ የነበረው አሠራር በጣም አወዛጋቢ ነበር:: የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቆዳ ማልፊያ ፋብሪካዎች የጥሬ ቆዳ እጥረት እንዳጋጠማቸውና በፋብሪካ ተለፍቶ ወይም አልቆ ወደ ውጭ የሚላክ ቆዳ ከጥሬ ቆዳ ይበልጥ ከፍተኛ ገቢ እንደሚያስገኝ እየታወቀ የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ያቋቋመው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ላኪ ድርጅትና የግል ጥሬ ቆዳ ላኪ ድርጅቶች ከመንግሥት ቆዳ ፋብሪካዎች ጋር እየተሻሙ ወደ ውጭ ይልኩ ነበር:: መፍትሔው ቆዳ በጥሬነቱ ከአገር እንዳይወጣ ማገድና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ያቋቋመው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ላኪ ድርጅትን መዝጋት መሆኑን አመንኩበት::

ድርጅቱን ዘግተን ሠራተኞቹን በልዩ ልዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲደለደሉ አስደረግን:: የድርጅቱ ንብረቶች ተሸጠው ዕዳው ከተከፈለና ሒሳቡ ከተጣራ በኋላ ተራፊውን ገንዘብ በቼክ ለመንግሥት አስረከብን:: አብዮቱ ከፈነዳ ጀምሮ መንግሥት አቋቁሞት የነበረ ድርጅት አስፈላጊነቱ

አክትሟል ተብሎ ሲታጠፍ የቆዳና ሌጦ ላኪ ድርጅት የመጀመርያው ሳይሆን አይቀርም፡፡

ቆዳ በጥሬነቱ ወደ ውጭ መላክ የተከለከለ መሆኑን ደንብ አወጣን፡፡ እርምጃውን በመውሰዳችን ተቃውሞ ገጠመን፡፡ የበላይ አለቆቼ ሦስት ጊዜ ጠርተው አነጋግረውኛል፤ ፖሊሲው ባይሠራ፣ ይኸውም የቆዳ አሰባሰብ ችግር ቢገጥመውና ከቆዳ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ገቢ ቢያቆለቁል በግሌ እንደምጠየቅበት አስጠንቅቀውኝ ነበር፡፡

ስለአዲሱ ፖሊሲ ገለጻ ልናደርግላቸው የቆዳ አሰባሳቢዎችንና ላኪዎችን በንግድ ምክር ቤት አዳራሽ ሰበሰብናቸው፡፡ ቆዳ በጥሬነቱ ሳይሆን ቢያንስ ተለፍቶ ቢቻል ደግሞ ባለቀ ምርት መልኩ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ብንችል አገሪቱ ከምርቱ የምታገኘው ጥቅም በጣም ከፍ ይላልና ተባበሩን አልናቸው፡፡ ገለጻዬን ገና ከመጨረሴ የፖል ሪዩስ ባለቤት ሚስተር ሩ ይነሳና ፖል ሪዩስ ጥሬ ቆዳ ሲልክ አንድ መቶ ዓመት ሆኖታል፤ አሁን ቆዳ በጥሬነቱ አይላክም በማለታችሁ ውለታችንን እረስታችሁታል ማለት ነው፤ በሥራው ላይ ያሰማራናቸውን ሠራተኞች ምን እናድርጋቸው? ብሎ አምርሮ ተናገረ፡፡ ሌሎቹም ተመሳሳይ ነገር ተናገሩ፡፡ የምታሰባስቡትን ቆዳ ለአልፊ ድርጅቶች በተስማሚ ዋጋ መሸጥ ስለምትችሉ የሚቀርባችሁ ጥቅም አይኖርምና ሐሳብ ሊገባችሁ አይገባም ብዬ ላግባባቸው ሞከርኩ፡፡

ፖል ሪዩስን በተመለከተ፣ ሚስተር ሩ ያልጠቀሰው ጉዳይ፣ የሱ ኩባንያ ጥሬ ቆዳ ወደ ባሕር ማዶ አንድ መቶ ዓመት ባሸጋገረበት ጊዜ ውስጥ የሰው ልጅ ከኩራዝ ወደ ኮረንቲ ተሸጋግሯል፤ መኪና ሠርቶ ከእግር ጉዞ ተገላግሏል፤ አውሮፕላን ፈልስፎ መብረር ችሏል፣ የጠፈር መንኮራኩር ሠርቶ ጨረቃን ረግጦ ተመልሷል፤ የአቶሚክ ቦምብ፤ ቴሌቪዥን፤ ቴሌፎን ሠርቷል፡፡

ፈረንሳዊው ሚስተር ሩና መሰሎቹ እኛ ለበለጸጉት አገሮች ዘለዓለም የጥሬ እቃ አቅራቢ ሆነን እንድንቀር ይፈልጋሉ:: በበለጸጉትና በድሃ አገሮች መካከል ያለው አንድ ዋና ልዩነት የበለጸጉት አገሮች ጥሬ ምርቶችን ከፍተኛ ዋጋ ወደሚያወጡ ምርቶች ለመለወጥ መቻላቸው ነው:: የሚጥሉት ነገር የለም ለማለት ይቻላል:: ለምሳሌ በቆሎን የወሰድን እንደሆነ ከሠላሳ በላይ የተለያዩ ምርቶች ይወጡታል:: በአገራችን የተጀመረው የእርሻ ትምህርት ደረጃው ከፍ ተደርጎ ጥሬ ምርቶቻችን ከፍ ያለ ገንዘብ ወደሚያስገኙ ምርቶች መለወጥ የምንችልበት ትምህርት መሰጠት ይኖርበታል:: አሁን ያሉን የትምህርት ተቋማት ይህ ከሥራ ድርሻችን ውጭ ነው ካሉም መንገዱን የሚያሳዩ ድርጅቶች መፈጠር ይኖርባቸዋል:: ጎን ለጎን የኬሚካልና ሜካኒካል ኤንጂነየሪንግ ትምህርት ማስፋፋት ያስፈልጋል:: ተአምርን ሳይሆን ጥበብን ለማቀፍ ከተነሳሳን ሰው የደረሰበት ቦታ የማንደርስበት አንድም ምክንያት የለም:: የሚያስፈልገው በራሳችን ማመንና መተማመን ብቻ ነው:: ከሁሉም በላይ ግን ለልማት አመች ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል:: አገሪቱ የጥቂት ሰዎችን ፍላጎት ለማሟላት የተደራጀች ሳትሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ አለኝታ ሆና ሁሉም ለግስጋሴዋ ኃላፊነት አለብኝ እንዲል ለፍትህ ተገዥ፣ ፈሪሀ ሕዝብ የሆነ አመራር ሥልጣን እንዲይዝ መታገል ያስፈልጋል::

የበለጸጉት አገሮች በጣም ትንሽ ገንዘብ ብቻ አውጥተው ከኛ የሚገዟቸውን ምርቶች በጣም ብዙ ገንዘብ ወደሚያስገኙ ምርቶች ስለሚለውጧቸው የልፋታችን ተጠቃሚዎች እነሱ ናቸው:: የበለጸጉት አገሮች መንግሥታት ለታዳጊ አገሮች ለጥሬ እቃ ምርት ማስፋፊያ እንጂ ለኢንዱስትሪ ማዳበሪያ እርዳታ አይሰጡም፣ ምክንያቱም የምናመርተው ጥሬ እቃ ለእነሱ ቀርቦላቸው ጥቅሙን ለራሳቸው ማድረግ ስለሚፈልጉ ነው:: ከኋላቀርነታችን የተነሳ ረኀብና ቸነፈር ሲጠናብን አዛኝ መስለው እርጥባን በመጣል ከጣረሞት ሊያስጥሉን ፍርፋሪ ቋጥረው ይቀርባሉ እንጂ ከድህነታችን እንድንላቀቅ መንገዱን አያመቻቹልንም:: በመሠረቱ ለልማታችን ኀላፊነት የለባቸውም፤ ሁሉም ሕዝብ ለእድሉ እራሱ ኀላፊ

መሆን ይኖርበታልና፡፡ ስለሆነም ያዋጣናል፣ ለሕዝባችን ይበጃል የምንላቸውን እርምጃዎች መውሰድ መቻል ይኖርብናል፡፡ ስለሶሻሊዝም ሲያስተምሩን እራሱን መከላከል የማይችል አብዮት ዘላቂነት እንደማይኖረው ተነግሮን ነበር፡፡ በተመሳሳይ፣ ለራሱ አለኝታ መሆን ያልቻለ ሕዝብ ህልውናው አጠራጣሪ ስለመሆኑ ማንም ሊጠራጠር አይችልም፡፡

የነጻ ገበያ ሥርዓት ችግሮቻችንን በተአምር አያስወግዳቸውም፣ እንዳውም ሥር እንዲሰዱ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ አሁን ባለው የኃይል አሰላለፍ፣ ለምሳሌ፣ አሜሪካና ኢትዮጵያ በነጻ ገበያ ይወዳደሩ ማለት ነብርና በግ ይዋጣላቸው እንደማለት ነው፡፡ አቅማቸው ባልተመጣጠነ ተፋላሚዎች መካከል የሚደረግ ትግል በማን አሸናፊነት እንደሚደመደም ለማወቅ ልዩ እውቀት የሚጠይቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ልጆች ሆነን ካነበብናቸው ልብ ወለድ ታሪኮች አሊባባና አርባዎቹ ሌቦች በሚለው መጽሐፍ ውስጥ አሊባባ በሩን ተከፈት ብሎ ሲያዘው ይከፈትለታል፡፡ አሁን በነገሠው የዓለም ኤኮኖሚ ሥርዓት ነጻ ገበያ ለችግራችን ማቃለያ መንገድ ያመቻችልናል ብሎ ማመን የሕልም እንጀራ ነው፣ ተረት ነው፡፡

የነጻ ገበያ ሥርዓት የኢትዮጵያ ሕዝብን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሆኑን ለማረጋገጥ በአገር ደረጃ መሟላት ያለባቸው ብዙ ሁኔታዎች አሉ፡፡ የውጭ ኢንቬስትመንት ወደ አገራችን በብዛት ገብቶ ለልማታችን አለኝታ የሚሆንበት ጊዜ ገና ነው፡፡ ለአገር ውስጥ አምራች ሆነ ለውጭ ኢንቬስተር አመቺ ሁኔታዎች ሳይፈጠሩ፣ ማለትም የአገር ውስጥ አምራች በዓለም ደረጃ ለመወዳደር ሳይዘጋጅና የውጭ ኢንቬስተር ደግሞ ወደ አገር ውስጥ ንዋይ በብዛት ለማስገባት ፍንጭ ሳያሳይ በነጻ ገበያ ሥርዓት ስም የጉምሩክ በሮችን ወለል አድርጎ ከፍቶ አገሪቱን የውጭ ሸቀጥ ማራገፊያ ማድረግ እያቆጠቆጠ ያለውን የአገር ውስጥ ምርትና የአገር ተወላጅን ኢንቬስት የማድረግ ፍላጎትና አቅም የሚያኮላሽ ይሆናል፡፡

የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ እንዲቻል ዘርፉን ተብትበው የያዙት ችግሮች ተለይተው መፍትሔዎቻቸውን ፈልጎ በተግባር መተርጎም ያስፈልጋል፡፡ ይህ በጥቅሉ ሲታይ የአገሪቱን ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና ሕጎች ማሻሻልንና፣ እንዲሁም የቢሮክራሲውን የአፈጻጸም ችሎታና ብቃት ማሳደግን ይመለከታል፡፡

ሕግ የሕዝብ ጥቅም ማስጠበቂያ መሣሪያ እንጂ የጥቂቶችን ፍላጎት ወይም ከንቱ ሕልም ወይም መናኛ እምነት ማራመጃ መሣሪያ አለመሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ የሕዝብ ተወካዮች የሕዝብን አደራ እንደማይበሉ መቆጣጠር ያስፈልጋል፤ ፍርድ ቤቶችን ከልዩ ልዩ ተፅእኖዎች ነጻ ብቻ ሳይሆን የፍትሕ ማእከል ማድረግ ያስፈልጋል፤ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ያለውጣ ውረድ ወይም ጭቅጭቅ ተፈጻሚ መሆን ይገባዋል፤ በኃላፊነት ላይ የተመደበ የመንግሥት ሠራተኛ ሥልጣኑን ተገን በማድረግ አምራችን፣ አከፋፋይን ወይም ቸርቻሪን አለመጋፋቱን ማረጋገጥ ይገባል፤ ባንጻሩም በገንዘቡ ኃይል ወይም በወገኑ ተማምኖ ሕግ እንዲጣስና ፍትሕ እንዲዛባ የሚዶልተውን ሳያወላውሉ መዋጋት ያስፈልጋል፤ የመሬት ይዞታ ሕግ ልማትን የሚያደፋፍር፣ የንብረት ምዝገባ ሥርዓት ደግሞ ከውዝግብ ወይም ከሸፍጥ የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ የአገሪቱ ተወላጆች የሚወዳደሩባቸው ወይም የሚሰለፉባቸው የሥራ መስኮች ለሁሉም በእኩልነት ክፍት መደረግ  ይኖርባቸዋል፤ አንዱን ወገን እንደ በኩር ልጅ ሌሎችን ግን እንደ እንጀራ ልጆች በማየት ዜጎችን ማበላለጥ ጸረ ሰላም ብቻ ሳይሆን ጸረ ልማትና አፍራሽ ድርጊት መሆኑ ታውቆ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይገባል፤ ያላሰለሰ ጸረ ጉቦ ዘመቻ ማድረግ ያስፈልጋል፤ የሕዝብ ደኅንነት ጠባቂዎች ዋና ትኩረት ከግለሰቦች ሥልጣን ጥበቃ ወደ አገርና ሕዝብ አንድነት ጠበቃነት ማሸጋገር ያስፈልጋል፤ በኤኮኖሚው መስክ ደግሞ የትራንስፖርት ዘርፍን እንዲሁም የኃይል ማመንጫንና የቴሌኮሚኒኬሽን ግንኙነትን ማስፋፋትና ዘመናዊ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ታክስ አጣጣል ሚዛናዊነት ያለው መሆኑንና አፈጻጸሙን በግል ጥቅም አሳዳጆች አለመደናቀፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ የባንክንና ኢንሹራንስ

አገልግሎት አስተማማኝና ዘመናዊ እንዲሁም ከቅሌት የጸዳ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ የትምህርት ዕድል ያለገደብ እንዲስፋፋ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።

በጥቅሉ፣ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ኃላፊነት ሕዝብ ተረጋግቶ ኑሮውን እንዲያሸንፍ ሁኔታዎችን ማመቻቸት መሆኑንና እነሱ የሕዝብ አገልጋዮች እንጂ ሕዝቡ የነሱ አገልጋይ አለመሆኑን በውል ሊገነዘቡ ይገባል። ያለበለዚያ በሰላማዊ ተቃውሞ ካስፈለገም በኃይል ከሥልጣን ሊያስወግዳቸው ይገደዳል። ሕዝቡ ምስጋናው ለፈጣሪው ብቻ ሳይሆን በምድር ላይ ለሚጠብቀው መንግሥትም እንዲሆን ከተፈለገ የመንግሥት ባለሥልጣኖች ልባቸውን፣ ጭንቅላታቸውን፣ አቅማቸውንና ጊዜአቸውን ለሕዝብ በሚጠቅሙ ተግባራት ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

በእርግጥ እላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ሙሉ በሙሉ ያሟላ አገር በታሪክ ታይቶ አይታወቅም፤ ወደፊትም አይታይም። ሆኖም፤ ሁሉም ነገር አንጻራዊ ስለሆነ ወደተጠቀሱት ግቦች ሳያሰልስ ያመራ አገር ከሌሎች ይቀድምና የነዋሪዎቹን ፍላጎት ማሟላት ይችላል፤ አለኝታም ይሆናል። ጉዞውን ከመጀመር የተዘናጋው ወይም እርስበርስ ሲጓተት ወይም ሲጣለዝ ጊዜውን ያባከነው ወገን ግን ኋላ ይቀራል፤ በድህነት ውስጥ ይማቅቃል፤ ተስፋው ይጫጫል። ሕዝቡ በመንግሥት ላይ እምነት ስለማይኖረው መንግሥት የሚነግረውን መስማት ካለመፈለግ አልፎ የሚነገረው ሁሉ ፕሮፖጋንዳ ወይም ውሸት ሳይሆን አይቀርም ይላል። ሥርዓተ አልበኝነትና ሕግጋትን መጣስ ባሕል ይሆኗል። ስለሆነም ልማትና እድገት ሕልም ሆነው ይቀራሉ፤ ወሮ መብላትና ዋትቶ ማደር አይነተኛ ተግባራት ይሆናሉ። ሁሉም በመሰለው አቅጣጫ ጥቅሙን ለማግበስበስ ይራወጣል። የዚህ ዓይነት ውጥንቅጥ ሁኔታ በሰፈነበት አካባቢ ትርምስና ሥርዓተአልበኝነት ይነግሳሉ። መንግሥት የሚይዘውና የሚጨብጠው ሲጠፋው ፈላጭና ቆራጭ መሆን ይጀምራል። የዚህ ዓይነቱ ድርጊት ሁኔታውን የበለጠ ያውሰበስበዋል፤ የነገር ሁሉ ውሉ ስለሚጠፋ አፍርሶ መገንባት፣ ገንብቶ

ማፍረስ፣ አፍስሶ መልቀም፣ ለቅሞ ማፍሰስ፣ ውሃ ቀድቶ ውሃ መመለስ፣ ከዚያም ጊዜ ሲነጉድ ላለማየት ተከናንቦ መተኛት ዓይነተኛ ተግባር ይሆናል:: በአንጻሩ፣ ስንፍና ለምኔ ብሎና ሥርዓተ አልበኝነትን አውግዞ በሕግ ለመገዛት በማለዳ ቆርጦ የተነሳውና የተዘጋጀው ወገን ወደሚፈለገው አቅጣጫ ሳያሰልስ ከተንዘ ካለመው ግብ ይደርሳል:: ሥራን፣ ሥርዓትንና፣ ሕግ አክባሪነትን ለምኔ ያለው ክፍል ግን ተስፋውና ዕድሉ ዘቅጦ ይቀራል፤ ወደኋላ መንሸራተት ይጀምራል፤ በመጨረሻም ታሪክ በአተላነት ይመዘግበዋል::

የአንድ መንግሥት ዋና ኃላፊነት የዜጎቹን ተስፋ ማለምለም ነው:: እስካሁን እንዳየነው ከሆነ ግን የኛ መንግሥታት በዚህ ረገድ ኃላፊነታቸውን መወጣት ተስኗቸዋል:: የኋላ ቀርነታችን ምስጢሩ እዚህ ላይ ነው:: አንድ መንግሥት የሕዝቡን ጥረቶች ማስተባበር ተስኖት ሕዝቡ በልማት ጎዳና መጓዝ ያቅተውና መንግሥቱ መፍትሔ ነው ብሎ የአገሪቱን የንግድ በሮች ወለል አድርጎ ከፍቶ የውጭ ሰዎች ምርትና አገልግሎት በገፍ ያቀርባሉ በሚል እምነት በእነሱ ላይ እንንጠላጠል ወይም ገበናችንን ለነሱ ከፍተን እናሳይ ማለት ፍጹም የዋህነት ነው:: እራስን ለኒዎኮሎኒያሊስቶች ቡጥቦጣ ማመቻቸት ነው::

አንድ አገር በጦርነት ተሸንፎ ይያዛል ወይም መንግሥት አገሩን በቅጡ ማስተዳደር አቅቶት ከውጭ የመጡ ሰዎች ቤተኛ ሆነው በንብረቱ ላይ ብቻ ሳይሆን በህልውናውና በወደፊት እድሉም ላይ አዛዥ ሆነው ባናቱ ላይ ተፈናጥጠው ይቀመጡበታል:: አንድ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን ዕድሉ ከእጁ እንዳይወጣና እንዳይዋረድ ከፈለገ በኤኮኖሚ አስተዳደር ጭምር ብቁ መሆን ይኖርበታል::

ጥቅሙን ለማስጠበቅ ያልተዘጋጀ ሕዝብን ማንም አያከብረውም:: ቀደም ብሎ እንደጠቀስኩት አንድ ሕዝብ ጥቅሙን አሳልፎ ላለመስጠት ከታገለ ሌላው ቀርቶ በዝባዡ እንኳ ያከብረዋል:: ያለበለዚያ መሳለቂያ ሆኖ ይቀራል:: ክሪስቶፈር ኮሎምበስ ስለአሜሪካ ጉዞው ጉዞውን ፋይናንስ

ላደረገችው ለእስፓኝ ንግሥት በቀረበው ዘገባ "ሰዎቹ፣ ማለትም ቀዮቹ ህንዶች፣ የማይረቡ ናቸው ምክንያቱም ድሆች ሆነው ሳለ ንብረታቸውን እያነሱ ስጦታ እያሉ ይሰጡን ነበር፤ ሳይተርፋቸው ለኛ መስጠታቸው ኋላቀርነታቸውን ያሳያል ብሎ" ጽፏል፡፡ በብልጦች አገር ደግነት ከሞኝነት ተለይቶ አይታይም፡፡ ለደግ ደግ ለብልጥ ብልጥ መሆን ነው፡፡

ሚስተር ሩና መሰሎቹ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት ጥሬ ቆዳና ሌጦ በፋብሪካ ተለፍቶና ሲሸጥ የሚያስገኘው የምርት ዋጋ ጥሬው ቆዳ ከተገዛበት ጋር ሲነጻጸር እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዐሥር እስከ መቶ እጥፍ ሊያወጣ ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለምሳሌ በዐሥር ብር የተሸጠ ጥሬ ቆዳ አልቆለት ሲሸጥ ከአንድ መቶ ብር በላይ ሊሸጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ ቆዳን በተመለከተ አገሪቱ ማራመድ ያለባት ስትራተጂ ቆዳው አገር ውስጥ እንዲለፋና የቆዳ ልብስና ጫማ ፋብሪካዎች እንዲበራከቱ ማበረታታት ነው፡፡

የቆዳ ሥራ በአገሪቱ እንዲስፋፋ ከወሰድናቸው እርምጃዎች ማካከል የደቡባዊና ምስራቃዊ አፍሪቃ የንግድ ቀጠና ፒ ቲ ኤ የቆዳ ቴክኖሎጂ ማእከል በአዲስ አበባ እንዲቋቋም መታገል ነበር፡፡ የኬንያ ባለሥልጣኖች ማእከሉ በአገራቸው ውስጥ እንዲቋቋም ከፍተኛ ግፊት ቢያደርጉም እኛ አሸንፈን አዲስ አበባ ውስጥ እንዲቋቋም አስወሰንን፡፡ የጥረታችን መሳካት እርካታን ያስገኘልኝ ጉዳይ ነው፡፡

በቡጁምቡራ ከተማ ተቋቁሞ የነበረው የፒ ቲ ኤ ባንክ ለቆዳ ዘርፍ ሥራ ማስፋፊያና ቴክኖሎጂ ማዳበሪያ በውጭ ምንዛሪ ብድር እንዲሰጥ ግፊት አድርገን ጉዳዩ በንግግር ላይ እያለ ሚኒስቴሩን ለቀቅሁ፡፡

በአገር ውስጥ የቆዳ ውጤት አምራቾች የሥራቸው ውጤት ከአፍሪቃ አገሮች አቻዎቻቸው ጋር ሲነጻጸር ምን ደረጃ ላይ እንዳለ እንዲመለከቱና የቆዳ ሥራ ቴክኖሎጂ የደረሰበትን ደረጃ ተገንዝበው የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ለመገፋፋትና ለማበረታታት ከኢንዱስትሪ

ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ዓለም አቀፍ የቆዳ ትርኢት መስቀል አደባባይ ራስጌ በሚገኘው በንግድ ምክር ቤት ኤግዚቢሽን ማእከል በጥር 1982 ታላቅ ትርኢት ታየ፡፡ ትርኢቱ በዘርፉ ወይም በመስኩ ለተሰማሩ ባለሙያዎችና ነጋዴዎች ዐይን ከፋች እንደነበር ጥርጥር የለውም፡፡

ትርኢቱን የከፈተልን መንግሥቱ ነበር፡፡ የእንኳን ደኅና መጣችሁልን ንግግር ካደረግሁ በኋላ መንግሥቱና የተጠሩት እንግዶች ትርኢቱን ተዘዋውረው ተመለከቱ፡፡ ከዚያም የፋሽን ትርኢት ለማሳያ ወደተዘጋጀው ስፍራ አመራን፡፡ ለትርዒቱ ተመርጠው ሲለማመዱ የሰነበቱት የሊሴ ገብረማርያም ወንድና ሴት ተማሪዎች ነበሩ፡፡ በተለይ ሴቶቹ እምቡጥ አበባ የመሳሰሉ የሚያሳሱ ልጆች ናቸው፡፡ የፋሽን ትርኢቱ ሲጀመር ልጃገረዶቹ ብልታቸውን ብቻ የሚሸፍን ስስ የውስጥ ልብስና የጡት መያዣ ለብሰው ብቅ ሲሉ አንዳንዱ ደነገጠ ሌላው ዐይኑን በለጠጠ፡፡ ከፍ ብሎ በተሠራው መረማመጃው መድረክ ላይ ልጆቹ ወዲያና ወዲህ ቂን ቂን ሲሉ ተመልካች ከሥር ቆሞ አሻቅቦ ያያቸዋል፡፡ እኔና መንግሥቱ ጎን ለጎን ቆመናል፡፡

እኔ የጠቅላላው ትርኢት ፕሮግራም አስተባባሪና መሪ ስሆን የቆዳና ሌጦ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስኪያጅ ይልማ አዳሙ የአፈጻጸም ኃላፊ ነው፡፡ የፋሽን ትርኢቱን ጉዳይ የሚከታተለው እሱ ነው፡፡ ለዚሁ ጉዳይ አንድ አዋቂ ነው የተባለ ሰው ከጣልያን እንዲመጣ ተደርጎ ልጆቹን ሲያለማምድ ሰንብቷል፡፡

መንግሥቱ ልጃገረዶቹ በሙታንታ ሲውረገረጉ ዐይቶ “የቆዳ ፋሽን ሾው ማለት ይሄ ነው እንዴ?” ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ነገራ ነገሩ ጥያቄ ሳይሆን ግሳጼና መከፋቱን የሚገልጽበት ቋንቋ መሆኑ ገባኝ፡፡ እኔም እንደሱ ያልጠበቅሁትን ስላየሁ በመጠኑም ቢሆን ተደናግጫለሁ፡፡ ፕሮግራሙን አስቀድሞ በዝርዝር ዐይቼው ቢሆን ኖሮ መግቢያውን አስቀረው ነበር ብዬ አሰብኩ፡፡

አብዮቱ ከፈነዳ ጀምሮ መዝናናትና መደሰት እንደ ኀጢአት ተቆጥሮ ስለነበር መንግሥቱና ሌላውም የተረሳ ባሕልን ከመቃብር ቆፍረን

እንዳወጣን ሳያይ የቀረ አይመስለኝም:: መንግሥቱ ለጠየቀኝ ጥያቄ ስመልስለት፣ ይህ መግቢያ ነው፣ ዋናው ትርኢት ይከተላል አልኩት:: ቁጣ ያስከተለው በተለይ ያቆጠቆጠ ብልት በሻሽ ተሸፍኖ የመቅረቡ ጉዳይ ስለነበር መግቢያ ነው ስለው ምን እንዳሰበ ባላውቅም መግቢያ የሚለው ቃል ከአፌ አምልጦ ከመውጣቱ ለምን ሌላ ቃል አልተጠቀምኩም ብዬ እራሴን ተቆጣሁት:: ሰውዬው አኮረፈ፤ ጥሎ ለመሄድ የከጀለውም መሰለኝ:: ለማናቸውም ትርኢቱ ቀጠለና ያ የተጋለጠ ገላ በጣም በሚያማምሩ የተለያዩ የቆዳ ልብሶች ተሸፍኖ፣ ቆዳና ገላ ሰምና ወርቅ ሆነው ሲያይ የመንጌ ሰውነት ዘና ሲል አየሁት፤ የእኔም እንደዚሁ::

ይልማም ኋላ እንዳስረዳኝ በትርኢቱ ለማሳየት የተሞከረው ቆንጆ ልብስ ለቆንጆ ገላ ወይም ለቆንጆ ገላ ቆንጆ ልብስ የሚለውን መልእክት ለማስተላለፍ ነበር:: ቀድሞስ አበሻ የተማረ ይግደለኝ ይል አይደል? እኔም የደነገጥኩት መንግሥቱም ያኮረፈው ባለማወቅ ነበር::

በውስጥ ልብስ ስለተደረገው ቂን ቂን የሰጋሁበት ሌላ ዐቢይ ምክንያት ነበረኝ:: ወቅቱ ተገንጣይና አስገንጣይ ቡድኖች በኢትዮጵያ ሰራዊት ላይ መረባረብ ብቻ ሳይሆን የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ያጧጧፉበት ወቅት ስለነበር እነዚህ ተቃዋሚዎች ስለፋሽን ሾዉ ወሬ ደርሷቸው ከሆነ መንግሥቱና የሥራ ባልደረቦቹ የልጃገረዶችን ሙታንታና ዐይን ዐይን ማየት እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ችግር መቼ ማስተናገድ ያውቃሉ? ይላሉ ብዬ ሰግቼ ነበር:: ለብዙ ቀናት ተጠባበቅሁ፤ ምንም ሳይሉ ቀሩና እፎይ አልኩ:: የፈራሁት ደርሶ ቢሆን ኖሮ እነመንግሥቱ አይተዉኝም ነበር የሚል ግምት አለኝ::

# ገጠመኞች በያይነቱ

መስፈርት የማያሟሉ የጫት ላኪዎች፣ ተመላላሽ ወይም ድንበር አቋራጭ ነጋዴዎችና አስመጪ ነጋዴዎች በየአቅጣጫው ተፅእኖ ሊያመጡብን

ይሞክሩ ነበር፡፡ አቤቱታ አለኝ እያለ ወደ ቢሮ የሚመጣው ባለጉዳይ አብዛኛው ከሕግ ወይም ከደንብ ውጪ እንዲፈጸምለት የሚፈልግ ነበር፡፡ ለሌላው የማይፈቀደው ለአንተ ብቻ አይፈቀድም ሲባል አኩርፎ ይሄዳል፤ ትክክል ነው ብሎ መቀበል አይፈልግም፡፡ ለአንተ ፈቅዶ ለሌላው መከልከል አሠራሩ ፍትሕ የጎደለው ነውና ጥያቄህ ሥጋ በለበሱ ፍጡራን ብቻ ሳይሆን በሰማዩ አባታችንም አይደገፍም ሲባል መልሱ ዛሬ ፍላጎቴ ይሟላና ነገ ከተፈረደብን ተያይዘን ወደ ሲኦል እንንጎድ ነው፡፡ ይህን የሚለው ያ ለማኝ ሳይጸዳዳ ጽድቅን ፍለጋ ወደ እግዚአብሔር ደጃፍ በጠዋት የሚንደፋደፈው ሰው ነው፡፡

እያወቁ ኀጢአት ሰርቶ ይቅርታ መጠየቅ ተቀባይነት አይኖረውም ቢባል ኖሮ ኢፍትሐዊ አሠራሮች ቁጥራቸው በጣም ይቀንስ ነበር ብዬ አምናለሁ፡፡ የታላላቆቹ ሃይማኖቶች መሪዎች የጋራ ጉባኤ አድርገው በጉዳዩ ላይ እንዲነጋገሩበት ሐሳብ አቀርባለሁ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥሩ ዳኛ ይወዳል ይባላል፤ ሐቁ ግን የግል ጥቅሙን በተመለከተ የሚጠይቀው ካልተፈጸመለት እንኳን ሰው አምላክንም ከማኩረፍ አይመለስም፡፡ በሌላ በኩል ግን አድልዎ ግራና ቀኝ ሲቸረቸር ሲያይ የበይ ተመልካች እንዳይሆን የሚያደርገው ትግል ነው ለማለትም ይቻላል፡፡ ስለሆነም፣ ትኩረቱ ይበልጥ መሆን ያለበት የአንድ አቤቱታ አቅራቢ ጥያቄ ትክክለኛነት ላይ ሳይሆን አቤቱታ ሰሚው ለሕግ ተገዥ መሆን አለመሆኑ ላይ ነው፡፡

የአየር መንገዱ ወዳጄ በሽር አንድ ቀን ቤት ድረስ ይመጣና ጉራጌ ዘመዶቻችን ድቤ እየመቱ፣ ጫት እየቃሙ ታደሰን አንሳልን እያሉ አላህን እንደሚለምኑ አውቅ እንደሆን ጠይቆኛል፡፡ በሽር ግልጽና ተጫዋች ስለሆነ እወደዋለሁ፡፡ ትክክል ያልመሰሉትን ድርጊቶች ከማጋለጥ ወደኋላ የማይል ሰው ስለነበር በቀልድም አስመስሎ የሚነግረኝን ነጥቦች በጽሞና አዳምጠው ነበር፡፡ ስለድቤው ታሪክ የነገረኝ እነሱ የሚሉትን ልክ ነው ለማለት ፈልጎ እንዳልሆነ አውቃለሁ፡፡

የውጭ ንግድ ሚኒስትር ተብዬ ስመደብ አንገታቸውን ቀና ቀና በማድረግ ላይ የነበሩ በንግድ ላይ የተሰማሩ የቅርብ ዘመዶቼና ወዳጆቼ በጣም ደስ ብሏቸው እንደነበር አውቅ ነበር። ውሎ ሲያድር ግን የኔ ቦታውን መያዝ ለነሱ ምንም ማለት አለመሆኑን ሲያውቁ አንዳንዶቹ ክደውኝ ነበር ለማለት እደፍራለሁ። ሌሎች ባለሥልጣኖች ለወገኖቻቸውና ለዘመዶቻቸው ሲያዳሉ እሱ ብቻውን ሐቀኛ ነኝ ብሎ መንገታገቱ ትርጉም የለሽ ነው፣ ነገሩ እንዲህ ከሆነ ሌላ የዘመድ ጎራ ይፈልግ ብለው ከልባቸው አውጥተው ተፍተው እንደጣሉኝ ይሰማኝ ነበር። የተጠቀሰውን አስተሳሰባቸው ወይም አመለካከታቸው እኔ እገመግመው የነበረው እነሱ እኔን ወይም እኔ እነሱን ስለማጣት ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ የበላይነት ታውቆ ዘመናዊ የሥራ አስተዳደርና አመራር ለማስፈን ምን ያህል እልህ አስጨራሽና ረጅም ጉዞ እንደሚጠብቀን ነበር። የፈጀውን ያህል ጊዜ ይፍጅ እንጂ ፍትሐዊ አሠራር ይሰፍናል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ። ለተግባራዊነቱ ሁሉም ዘብ ይቁም።

የምዕራቡ ዓለም የሥልጣኔ ምስጢር ሕዝቡ ለሕግ ለመገዛት ያለው ፍላጎትና ፈቃደኛነት ነው ብያለሁ። እርግጥ ሕጎቻቸው የሁሉንም መብትና ግዴታ በእኩልነት የሚያስጠብቁ አይደሉም፣ እንደማናቸውም አገር ሕግን የሚደነግገው በዚህም በዚያም ብሎ ሥልጣን በአሸናፊነት የያዘው ወገን ሥልጣኑን እንዳይቀማ ለማረጋገጥ ቢሆንም በምዕራቡ ዓለም ያለው ሕግና ሕግ አክባሪነት ግን እኛ አገር ከሚታየው ጋር ሲነጻጸር የነሱ በጣም የተሻለ ነው። በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት በሕግ የተደነገገ ነው። ሰውን የሚዳኘው ሰው ሳይሆን ሕግ ነው። አንድ ሰው ያልተሰጠውን መብት ጉልበቱን ተማምኖ መዝገን ከፈለገ ከዳኛ ፊት ቀርቦ እንደሚቀጣ ስለሚያውቅ አርፎ ይቀመጣል። እነእገሌ አሉልኝ ብሎ ሕግን አይዳፈርም። በሕግ ፊት ሁሉም እኩል ነው፣ ደሃና ሀብታም፣ ደካማና ጉልበተኛ፣ ትንሽና ትልቅ ሁሉም እኩል ናቸው። እርግጥ ሀብታም የተሻለ ጠበቃ የመግዛት አቅም ስላለው ከስሶ ለማሸነፍ ወይም ከተከሰሰበት ወንጀል ወይም ሌላ ዓይነት ክስ በነጻ ለመገላገል የተሻለ እድል እንዳለው አይካድም።

ግዴታንና መብትን ማወቅ፣ ሕግን ማክበር የሰላምና ብልጽግና መሠረቶች ናቸው:: ገበሬ ተግቶ ለማረስ የሚደፋፈረው ያመረተውን ምርት ቀማኛ እንደማይቀራመተውና መሬቱን እንደማይነጠቅ ሲያምን ብቻ ነው:: ነጋዴ ከአገር አገር ተዘዋውሮ አምራች ያመረተውን ለሸማች በማቅረብ የሕዝብ ኑሮ እንዲሻሻል የሚያደረገው ሽፍታ በመንገድ ላይ ጠብቆ እስካልዘረፈው ድረስ ወይም ባለሥልጣን ሕግን ተገን አድርጎ ወይም ሥልጣኑን ተላልፎ እስካልቀማው ድረስ ነው:: አንድ ሀብታም ፋብሪካ ሰርቶ ድርጅት አቋቁሞ የሥራ እድል የሚያስፋፋው ሰላም ሰክኖ ይቆያል፣ ሕግ ይከበራል፣ ከቁጥጥር ውጭ የወጣ ዘራፊ ወይም አስዘራፊ አያንገላቱኝም ብሎ እስካመነ ድረስ ነው:: ሥራ፣ ሠራተኛና ሕግ በሚረገጡበት አገር ብልጽግናና የሥራ ዕድል ይስፋፋሉ ብሎ ማመን በሬ ይወልዳል ብሎ እንደማመን ነው:: ስለሆነም፣ ሕግ አውጪዎች፣ አስፈጻሚዎችና አስከባሪዎች ከሁሉም በላይ እራሳቸው ለሕግ ለመገዛት ፈቃደኛ መሆን ይኖርባቸዋል::

አንድ ሕግ በመንፈሱም ሆነ በአፈጻጸሙ የገዢውን መደብ ወይም ክፍል ጥቅም ብቻ ለመጠበቅ ወይም ለማዳበር፣ አብዛኛውን ሕዝብ ግን ወደ ኋላ ለማስቀረት እስከዋለ ድረስ ሕዝቡ በልቡ መሸፈቱ የማይቀር ነው:: ጨቋኞቹን በልዩ ልዩ መንገድ መፈታተን ይጀምራል፤ ሕግ አለማክበርን ብሔራዊ ግዴታና ቅዱስ ተግባር አድርጎ ይያያዘዋል:: መንግሥት በሕዝቡ ይተፋል:: በመጨረሻም ይገረስሳል:: ሕዝብ የኔ ነው የሚለው መንግሥት ግን በሕዝብ ታቅፎ ለረጅም ጊዜ ይቆያል፤ ከውስጥና ከውጭ ጠላት ተከላክሎ ይጠብቀዋል፤ ፍሬ አፍርቶ ያልፋል:: ለዘለዓለምም ሲታወስ ይኖራል::

በተለይ አፍሪቃ ውስጥ፣ ኢትዮጵያ ጭምር፣ ያለው አመለካከት ግን ባለሥልጣኖች ከሕግ በላይ እንደሆኑና የፈለጉትን ማድረግ እንደሚችሉ ነው:: የአፍሪቃ ሕዝቦች በድንቁርና፣ በረሃብና በበሽታ እንዲዘፈቁ ያደረገው ይህ ጤናማ ያልሆነ አመለካከት ነው:: መሪዎች የሕዝብ አገልጋዮች ናቸው

እንጂ ሕዝብ የመሪዎች አገልጋይ አይደለም:: አፍሪቃውያን ይህ እውን እንዲሆን ታግለው ማሸነፍ እስካልቻሉ ድረስ የዓለም ጭራ መሆናቸው የማይቀር ነው::

ባንክ በነበርኩበት ጊዜ እንደነበረው ሁሉ ውጭ ንግድም ሕግ እንድጥስ፣ ደንብ እንዳዛባ ሕግ አውጪና አስከባሪ ነን ከሚሉ ጭምር ልዩ ልዩ ዓይነት ሕገወጥ ጥያቄ ይቀርብልኝ ነበር:: አንድ ጊዜ የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ይደውልና አንዲት ሴት ልታነጋግረኝ ስለምትፈልግ ቀጠሮ እንድሰጣት ይጠይቀኛል:: እሺ እለውና ቢሮዬ ድረስ ትመጣለች:: ቆንጆ ናት፤ ግዮን ሆቴል ውስጥ ክፍል ተከራይታ እንደምትኖርና የገቢ ችግር እንዳጋጠማት ነገረችኝ:: ጥያቄዋ የንግድ ፈቃድ እንዲሰጣት ነበር:: የጠየቀችው ፈቃድ ዓይነት በወቅቱ የማይሰጥ ነበርና ይህንኑ እነግራትና ትሄዳች:: ያሰበችው ባለመሳካቱ ቅር እንደተሰኘች በግልጽ አሳውቃኝ ሄደች::

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ሰኞ ጠዋት፣ አንድ ጓደኛዬ ይደውልና ቢሮ ብቅ ለማለት ፈልጌአለሁና ልመጣ እችላለሁ ወይ? ይለኛል:: አዎን አልኩትና መጣ:: ከአገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ጋር ችግር አለህ እንዴ? ብሎ ይጠይቀኛል:: ሚኒስትሩ እራሱን የሚያኩራራ የጦርሰራዊት አባል ቢሆንም ተጫዋችና ግልጽ ሰው ስለነበር ዕጣችን አልተገጣጠመም እንጂ ያው በጠበሉ ይቀመጥ ያልኩት ሰው አልነበረም:: አንድ ቀን በገፈርሳ ጫካ ውስጥ ከዘመቻ ለተመለሱ ወታደሮች ግብዣ ተደርጎ በነበረበት ቀን የተናገረውን ዘወትር እያስታወስኩ ሰውዬው ልቡ በክፋት ያልተበከለ ነው ብዬ አምን ነበር:: በግብዣው ላይ መንግሥቱ ተገኝቷል:: ሚኒስትሮቹን አንድ አካባቢ አስቀምጠውናል:: ከተበላ፣ ከተጠጣና ምላሶችም መቀነቶቻቸውን ካላሉና አንገቶችም ዐይኖችን የግራ የቀኙን እንዲያማትሩ ካዟዟርዋቸው በኋላ የአገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ድምጹን ከፍ አድርጎ፣ ይህ መንግሥት እኮ የጉራጌ መንግሥት ሆኗል ይላል:: አድማጩ የሣቅ ካካ ካካ ካካውን በደንብ ካንካካ በኋላ፣ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትራችን፣ እስኪ ነገሩ እውስጡ ግባና ገለጥለጥ አድርገህ አስረዳን ይባላል:: ግርማ ይልማ የማስታወቂያ

ሚኒስትር፣ ተስፋዬ ማሩ የቤቶች ሚኒስትር፣ መርሻ ወዳጆ የአገር ውስጥ ንግድ ሚኒስትር፣ ታደሰ ገብረኪዳን የውጭ ንግድ ሚኒስትር፣ ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ የደኅንነት ሚኒስትር ብሎ ዘረዘረ። ሁሉም በአንድ ቃል ተስፋዬ ጉራጌ አይደለም ይለዋል። ስለሱ እኔ ነኝ የምነግራችሁ፤ እናንተ አትነግሩኝም፤ ተስፋዬ እንዲህ የሚባል ቦታ የተወለደ የመስቃን ጉራጌ ነው ይላል።

ጓደኛዬ በመካከላችሁ ችግር አለ እንዴ? ብሎ ሲጠይቀኝ የግብዣው ዕለት ትዝ አለኝና ሰውዬው የተናገረውን በክፋት ሳይሆን በየዋህነት ነው ብዬ እንደዋዛ ረስቼው የነበርኩት ሰውዬ የጓደኛዬ አመጣጡ ለጤና እንዳልሆነ ስረዳ ለካስ ያኔ ሆዱ ያባውን ብቅል አውጥቶበት ይሆን? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ። ሚኒስትሩ አርሲ ነጌሌ ተወልዶ ካደገ ከአንድ የሩቅ ዘመዴ ጋር አብረው መማራቸውንና ዘመዴን ወደነበሩበት ትምህርት ቤት ቀለብ በማመላለስ ይተባበረው እንደነበር ሰምቼ ስለነበረ ሚኒስትሩን ባየሁት ቁጥር ያ የሩቅ ዘመዴና በዝምድና ከሱ የምትቀርበኝ ደጓ ባለቤቱ እትዬ ጣጢቄ ትዝ ይሉኝ ስለነበር ሚኒስትሩን በሐሳቤ ወዳጄ ያደረግሁት ሰው ነበር።

ስጋት አስበርግጎና አክንፎ ላመጣው ጓደኛዬ ስመልስለት በመካከላችን ምንም ዓይነት ችግር የለም እለዋለሁ። መልሴ አልዋጥለት ይለውና ለመሆኑ እርግጠኛ ነህ? ብሎ ደግሞ ይጠይቀኛል። አዎን እለዋለሁ። እንግዲያውስ የምትውለው ካራጅህ ጋር መሆኑን አውቀህ ጥንቃቄ እንድታደርግ፤ “ታደሰን እኔ ያላስጠፋሁት እንደሆነ ሰው አይደለሁም፣ ቆዩ ታዩኛላችሁ” ብሎ ባለፈው ዊክኤንድ አንድ አብረን በተገኘንበት ግብዣ ላይ ሲፎክር በጆሮዬ ሰምቻለሁ ብሎ ነገረኝ። እንዴት ሊሆን ይችላል? በምንስ ምክንያት? ብዬ ከጥቂት ሴኮንዶች በጽሞና ሳሰላስል ከቆየሁ በኋላ ያቺ የግዮኗ ቆንጆ ሴት ከፊቴ ድቅን አለች። በወል ኢትዮጵያ ትቀደም ሲባልና ይህ መፈክር እሱ በሚመራው መሥሪያ ቤት አማካይነት በኢትዮጵያ ግዛቶች በሙሉ በአራቱም ማእዘን ሲሰራጭ የሚኒስትሩ የግል መፈክር ግን

አላስበላ ያለ ይበላ የሚል ነበር ማለት ነው። ኢትዮጵያ እንኳን ልትቀድም ተንደርድራ በአፍጢሟ ስትደፋ ሚኒስትሩና መሰሎቹ በሁለት ዐይኖቻቸው እያዩ፣ ሚኒስትሩ ታደሰን አስጠፋዋለሁ ሲል የሚያዩ መስለው ማየት በተሳናቸው ሰዎች አገር አንድ ዐይናዎች ቦታ የላቸውም ማለቱ ነበር። እውነቱን ለመናገር እነዚህ ሰዎች መካከል ምን አደርጋለሁ? ማለት ከጀመርኩ ውሎ አድሮ ነበር። ኮሎኔል ሙሉጌታ ማሞ እነዚህን ሰዎች እኮ አንተ አታውቃቸውም፤ ከነሱ ጋር መሰለፍ የለብህም የሚለኝ ትዝ አለኝ።

ውጭ ንግድ ሆኜ በባንክ የደርግ ተወካይ ከነበረው ከመቶ አለቃ ፈቃደ ማሞ ጋር አንድ ሐዘን ቤት እንገናኝና ጦር ሰራዊቶችን ምን አደረግሃቸው? ይለኛል። እንኳን እኔ ሲቪሉ ሌላውም ቢሆን ምንም አላደረጋችውም አልኩት። ቀልድ አይደለም የማወራህ፣ ጉዳዩ አሳሳቢ ነው ይለኛል። ለአየር ኃይል ባልደረቦች ሚስቶች እንዲህ አድርጎ የእኛዎቹን ችላ ስላላቸው በጣም ተከፍተንበታል ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ይለኛል። እርግጥ ነው ባሎቻቸው በግዳጅ ለሞቱባቸው ለጥቂት የአየር ኃይል ባልደረቦች ሚስቶች በልዩ አስተያየት የንግድ ፈቃድ እንዲሰጥ አድርገን ነበር። እንደማንም ሰው እኔም ለልቤ የሚቀርቡ ነገሮች ስላሉ ለአየር ኃይል ሰራዊት የነበረኝ በጎ አመለካከት አንዱ ነበር። የምድር ጦር ሰራዊት ከብዛቱ የተነሳ ልዩ አስተያየት ቢባል መቆሚያ ስለማይኖረው የማይታሰብ ነው። ታዲያ ይህ አስመራ ውስጥ ወታደሮቻችን ያደረጉንን ያስታውሰኛል። አብዮቱ እንደፈነዳ የሥራ እንቅስቃሴ ስለተዳከመ ሁኔታውን ለማሻሻል ባንኮች የቤት እቃ ግዢ ብድር ቢያስፋፉ የቤት እቃ አምራቾች ሥራቸውን ያስፋፋሉ በሚል እምነት ለዚህ ጉዳይ በርከት ያለ ገንዘብ ተመደበና በተግባር መተርጎም ተጀመረ። ኤርትራ፣ በተለይም አስመራ፣ ውስጥ የነበሩ የምድር ጦር ባልደረቦች ብድሩን ማግኘት መብታችን ስለሆነ ለኛም ይሰጠን ብለው አስቸገሩ። የምትኖሩት ካምፕ ውስጥ ነው፤ ብድሩ የታሰበው ቋሚ መኖሪያ ለሌለው ለእንደእናንተ ዓይነቱ አይደለም ቢባሉ፣ ዋ! ማለት ጀመሩ። ውጭ ንግድ ሆኜ በግዳጅ ለሞቱ የአየር ኃይል ሚስቶች ልዩ አስተያየት ይደረግ ብዬ ስወስን የምድር ጦር አባላትም ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርባሉ ብዬ

አላሰብኩም ነበር:: አስበነው ቢሆን ኖሮ ባሎቻቸው በግዳጅ የሞቱባቸው የምድር ጦር ሰራዊት አባላት ሚስቶች በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ስለነበር እነሱን ሁሉ ማስተናገድ ስለማይቻል ለአየር ኃይል ልዩ አስተያየት ከማድረግ እንቆጠብ ነበር::

ለማናቸውም ምድር ጦር ተቀይሞሃል ተብሎ ሲነግረኝ ልቤ ተሸበረ:: የበዓሉ ግርማ ሕይወት ያለፈው በወታደሮች እጅ ነው፣ በእንረዳዳው አበበ ወርቁ ቤት ላይ የተጣለው ቦምብ የወታደሮች እጅ አለበት ሲባል እንሰማ ስለነበር የሳንቃው አቦ፣ የእምብወሉ ኢየሱስ፣ የመርካቶው ተክልዬ፣ የጉለሌው ሩፋኤል፣ የቦሌው መድኃኔ ዓለም እባካችሁን ጠብቁኝ ብዬ ለምኛ ቸዋለሁ:: ስለት ግን አልተሳልኩም፣ አማልክት እንደሰው መደለያ ይቀበላሉ ብዬ ስለማላምን::

ውጭ ንግድን ለቅቄ ልሄድ ጥቂት ሲቀረኝ ከሕዝብ ደኅንነት ባለሥልጣኖች አንዱ ቢሮ ድረስ ይመጣና ለአብዮቱ ቀና ደፋ ስንል ለኑሮ ዋስትና የሚሆን ቅርስ ስላላበጀን ቤተሰቦቻችን በቋፍ ላይ ናቸውና የውጭ ንግድ ሚኒስቴር ፈቃዶችን በመስጠትና በሌላም መንገድ ይተባበረን ብሎ ጠየቀኝ:: ብዙ የሲቪልና የወታደር ባለሥልጣኖችም ትልልቅ ቤቶች እያሠሩ ስለመሆኑ ይነገር ነበር:: መንግሥታዊ የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ተባባሪ እንደነበሩ እንሰማ ነበር:: በጥቅሉ ሁኔታው ቀኑ ሊጨልም ሲል ሕፃናትና አእዋፍ እንደሚያጧጥፉት ጨዋታ ዓይነት ነበር:: ሕይወት ሲያልፍ መንፈራገጥ፣ ቀን ሲጨልም መራወጥ ተፈጥሮ በጂናችን ውስጥ ቀብሮ የደነገገው ሕግ ሳይሆን አይቀርም::

አንድ ቀን ገና ቢሮ ከመግባታችን ጸሓፊዬ ትደውልና የፕሬዚዳንቱ አባት ነኝ የሚሉ አንድ ሰው መግባት ይፈልጋሉ ትለኛለች:: አስገቢያቸው እላታለሁ:: ሰውዬውን በፓርቲ ምሥረታ ሥነሥርዓት ላይ ሰው እየተጠቃቀሰ የመንግሥቱ አባት እኛውልህ ሲባባል አይቻቸዋለሁ:: ቢሮዬ የመጡት ብቻቸውን ሳይሆን ከአንድ ሰው ጋር ነበር:: ማነው ይህ ሰው?

ብላቸው፣ ነጋዴ ነው፤ ፈቃድ ይፈልጋል፤ እንድትሰጠው ልጠይቅህ ነው የመጣሁት ይሉኛል:: ወደ ሰውዬው ዞርኩና ጥያቄህ ምንድን ነው? ብዬ ጠየቅሁት:: ሐሳቡን በትክክል በአማርኛ መግለጽ የማይችል የኤርትራ ክፍለሀገር ተወላጅ ነው:: የጠየቀው ፈቃድ ለሌላም የማይፈቀድ ስለሆነ ለሱ ብቻ መፍቀድ እንደማይቻል ነገርኩት:: ሁለቱም ተቀባብለው ለመኑኝ:: አይሆንም ብዬ መለስኳቸው:: አቶ አማላጅ “እዚህ ድረስ መጥቼ እንዴት ታሳፍረኛለህ?” አሉኝ:: አዝናለሁ አልኳቸው:: አንድ ወር ያህል ቆይቶ ጸሓፊዬ “የፕሬዚዳንቱ አባት እዚህ ቆመዋል፣ ልግባ ይላሉ” ብትለኝ ጊዜ የለኝም ብዬ መለስኳቸው::

ከመንግሥቱ ታናሽ ወንድም ከጌታነህ ጋር አዲስ አበባ ባንክ ውስጥ አብረን እንሠራ ነበር:: እኔ የፕላን ክፍል ኀላፊ ሆኜ ጌታነህ የመልዕክት ክፍል ሠራተኛ ነበር:: መንግሥቱ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ጌታነህ አምስት ዓመት ያህል ታስሮ ይፈታል:: ያሳሰረው ወንጀል ከእምነት ማጉደል ጋር የተያያዘ እንደሆነ ወሬ ሰምቻለሁ:: አንድ ቀን ቢሮዬ ይመጣል፤ የመጣውም በሚኒስቴሩ ሥር በሚተዳደሩ የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ክፍት የእቃ ግዥ ቦታ ፈልጌ እንዳስቀጥረው ነበር:: ጥያቄው ቀበሮ ዶሮዎችን ልጠብቅ አለች ዓይነት ነው አልኩና በፈገግታ ሸኘሁት:: መንግሥቱ አባቱም ሆኑ ወንድሙ በየቢሮው እየዞሩ በስሙ ለመጠቀም ይሞክሩ እንደነበር ያውቅ ነበር ለማለት ያዳግታል::

ውጭ ንግድ ሆኜ ከሁሉም ክስተቶች ይበልጥ ለሕይወቴ ጠንቀኛ የነበረው አልማማው ኃይሌን ማወቄ ነበር:: ከአልማማው ጋር የተዋወቅነው ባንክ እያለሁ ነው:: ያስተዋወቁኝ ባንክ ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ ካድሬዎች ናቸው:: የተዋወቅነው ሲቪል አቪዬሽን ሆኖ ይሁን ወይም የባሕል ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ይሁን በትክክል አላስታውስም:: የባሕል ሚኒስቴር መሥሪያ ቤትና ብሔራዊ ባንክ በጣም ቅርብ ለቅርብ ናቸው:: አልማማው የአካባቢው የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ የነበረ ይመስለኛል:: ባንክ ውስጥ የነበሩ የፖለቲካ ካድሬዎች ስለምንሠራው ሥራ በየጊዜው

ይነግሩት እንደነበር እገምታለሁ፡፡ ስለኔ የነበረው አመለካከት ከበጎም አልፎ ጥሩ እንደነበር ግምት ወስጃለሁ፡፡ ይህም ሲባል ካድሬዎቹ እንዲወዱኝ የተለየ ነገር አደርግ ነበር ማለቴ አይደለም፡፡ እኔ እስከምረዳው ድረስ፣ የባንክ ሰዎች የሚሠሩትን የሚያውቁ ስለሚመስል አስፈላጊ ካልሆነ በቀር በሥራቸው ውስጥ ገብታችሁ አታስቸግሯቸው የሚል አመለካከት የነበረ ይመስለኛል፡፡ እኛም አጋጣሚው ሲገኝ ሕዝቡ የቆጠበውን ገንዘብ በባንክ የማስቀመጥ ልምዱን እንዲያዳብርና የባንክ ሙያ እንዲስፋፋ ከተፈለገ መንግሥትና የፖለቲካ ሰዎች የባንክን ሥራ ለባለሙያተኞቹ ይተዉልን እንል ነበር፡፡ ይህም ሲባል ያኔ በነበረው ሁኔታ የፖለቲካ ካድሬዎች ያም ይሄም ይመለከተናል፤ ከፖለቲካ ተነጥሎ የሚታይ ነገር ሊኖር አይችልም የሚሉበት ወቅት ስለነበር ከነሱ ጋር መሥራት የግድ ነበር፡፡ ሥራዬን እሠራለሁ፣ ፖለቲካ የሚፈተፍቱትን ግን አላውቃቸውም ወይም በሥራዬ በምንም ዓይነት አላስገባቸውም ማለት ፍጹም የማይቻል ነገር ነበር፡፡ ዘዴው እነሱን ብዙም አለማራቅ፣ ብዙም አለማስጠጋት ነው፡፡ ያለበለዚያ በንዳድ ወይም በቅዝቃዜ መጥፋት ይከተላል፡፡ ከነሱ ጋር መሥራት በፍጹም አይሆንልኝም ያለ በቦሌም ሆነ በባሌ ጨርቁን ጠቅሎ አገር ጥሎ ጠፍቷል፡፡

የኤርትራ ክፍለሀገር የበላይ ኃላፊ ዳዊት ወልጊዮርጊስ በነበረበት ወቅት አልማማው የፖለቲካ ጉዳይ ኃላፊ ሆኖ ሄደ፡፡ ወደ አስመራ ለሥራ ጉዳይ ሄጄ ሳለ ተገናኝተናል፡፡ ብዙም ሳይቆይ እንደበኩር ልጅ ይታይ ከነበረው ከዳዊት ጋር ይጣላና አውጥተው ይወረውሩታል፤ አዲስ አበባ ይመለሳል፤ ሥራ ማጣቱን አስተዛዘኖ ይነግረኛል፤ እግረመንገዱንም “እነዚህ ፋሺስቶች” አገሩን ገደል እየሰደዱ ናቸው ይለኛል፡፡

የፖለቲካ አምቢሽን ያላቸው ሰዎች ያሉበትን ሥርዓትና የሥርዓቱን አራማጆች በጣም ይክቡና ከሥልጣን ሲወርዱ ወይም የተመኙት ሳይሳካላቸው ሲቀር ብዙ ብዙ ሲሉ ስለሰማሁ አልማማው ያለውንም ሰምቼ ዝም አልኩ፡፡ ዳዊት ከአገር የኮበለለ ዕለት ጎን ለጎን ተቀምጠን ነው ከአገር

የወጣነው:: መንግሥትን ከመጠን በላይ ሲያጥላላ ሰምቼ በልቤ እውነት ያ የማውቀው ዳዊት ነው? ብያለሁ:: በቀይ ኮከብ ዘመቻ ወቅት ስንት ጊዜ "ቆራጡ መሪያችን" "አብዮታዊው መሪያችን" ብሎ መንግሥቱን እንዳሞካሸው አንዳንዶቻችን እየቆጠርን ከጀርባው መሣለቂያ አድርገነው ነበር:: ዳዊት የፖሊት ቢሮ አባል መሆን ስለፈለገ ቲያትር እየሠራ ነው እንባባል ነበር:: ያሰበው ሳይሆን ሲቀርና ከፖለቲካ ሥራ ወደ መንግሥት መሥሪያ ቤት ሲዛወር ገጽታው ከመቅጽበት ተለወጠና ኃይለኛ አኩራፊ ሆኖ ቁጭ አለ:: አልማማው "እነዚህ ፋሺስቶች" ሲል ከሥልጣን ስለተነሳ አኩርፎ ነው አልኩ እንጂ አልማማው ከሥልጣን በመውረዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድል ሊዳፈን ነው ብዬ ስጋት አላደረብኝም:: የፖለቲካ ቋንቋው መራራ ስለነበር እንዲያውም ግልግል ነው ሳልል አልቀረሁም::

አንድ ሰው አምኖኝ ምስጢር ከነገረኝ ወይም ምስጢር ብነግረው አሳልፎ አይሰጠኝም ብሎ ካመነኝ የሰማሁትን ውጬ የማስቀረት ችሎት አለኝ:: አልማማው ያለኝንም አሁን ያወጣሁት እሱም ሆነ ያ ያጥላላው የነበረ መንግሥት በሕይወት ስለሌሉ ነው::

አልማማውን የእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ ይቀጥረዋል:: በኔ አሳሳቢነት ይሁን ወይስ እራሱ አመልክቶ ይሁን በውል አላስታውስም:: ባንክ እያለሁ አልፎ አልፎ ቢሮ ብቅ እያለ ሰላም ይለኝ ነበር:: አንድ ቀን ቀጠሮ ይዤለት ይመጣል:: ማርክስና ኤንግልስ፣ እንዲሁም ከነሱም በኋላ የመጡት የሶሻሊዝም ምሁራን ያስተማሩት ያልተሟላና የዘመኑን ተጨባጭ ሁኔታ የማያንጸባርቅ ስለሆነ የነሱን ሥራ የሚያሻሽል ጽሑፍ አዘጋጅቻለሁ ብሎ አንድ ትልቅ ቀይ መጽሐፍ አውጥቶ ይሰጠኛል:: ካነበብኩት በኋላ አስተያየቴን እንድሰጠው ይጠይቀኛል:: ጽሑፉን ባገላብጠው ብዙም ሳይጥመኝ ይቀራል:: እውነቱን ለመናገር፣ የሰከነ ጭንቅላት ያፈለቀው ነው ለማለት ተቸገርኩ:: በሌላ በኩል እኔ መንሳፈፍ እንጂ ውሃ ዋና የማይሆንልኝ ሰው በመሆኔ ምናልባት አልማማው ጠልቆ የገባበትን ባሕር አለማወቁ ሊሆን ይችላልና በእንገግሊዝኛው አባባል the benefit of the

doubt መስጠት ያስፈልግ ይሆናል ብዬም አሰብኩ። ለማናቸውም፣ መጽሐፉን በቅጡ ሳላነበው ደብቄ አስቀመጥኩት። ዳግማዊ ኤንግልስና ማርክስ ሲነሱ ሊመረምሩት ይችላሉ።

ወደ ውጭ ንግድ ከተዛወርኩ በኋላ አልማማው አንድ ቀን ቢሮዬ ይመጣና አንድ ምሥራቅ አውሮፓ ተምሮ የተመለሰ "ጓዳችን" ሥራ አጥቶ ተቸግሯልና እባክህን ቅጠረው ይለኛል። ሥራ ፈላጊውን ላከው አልኩት፤ መጥቶም አነጋገርኩት። የተማርከው ትምህርት ለእንዲህ ዓይነት መሥሪያ ቤት እንኳ ለውጭ ንግድ ሚኒስቴር ተስማሚ አይደለም፤ ቦታ የለንም ብዬ መለስኩት። ሌላ መሥሪያ ቤት ቀጥሮት አልፎ አልፎ እየተያየን ሰላም እንባባል ነበር።

አልማማው ቦሌ መንገድ ገባ ብሎ፣ ወንዙ አካባቢ፣ ከመንግሥት ወታደሮች ወይም የጸጥታ አስከባሪዎች ጋር ተታኩሶ መሞቱን ሰማሁ።

በዚያው ሰሞን አንድ በፓርቲው ቁጥጥር ቢሮ ውስጥ የሚሠራ የሙህር ተወላጅ የሆነ የሩቅ ወዳጄ ቢሮ ድረስ ይመጣል። ከጥቂት ዓመታት በፊት ድሬዳዋ ተገናኝተናል። ወደ አዲስ አበባ ከተዛወረም በኋላ የተገናኘን ይመስለኛል፤ እቤቱ ሳልጋበዝ የቀረሁም አይመስለኝም። ዛሬ ምን እግር ጣለህ? ብዬ እጠይቀዋለሁ። አይ ዛሬ መሥራት ስላላሰኘኝ ፈቃድ ላይ ነኝ፤ ቀኑን የረሳኋቸውን ዘመዶቼን ለመጠየቅ ልጠቀምበት ብዬ ነው ይለኛል። ቡና እየጠጣን የቆጡን የባጡን ከቀላመድን በኋላ "ለመሆኑ አልማማውን ታውቀው ነበር?" ብሎ ይጠይቀኛል። ተቆጣጣሪው ዘመዴ ለምን እንደመጣ ወይም ማን እንደላከው ወዲያው ገባኝ። አለማየሁ ኃይሌን ከገደሉት በኋላ የሆነውና ሊሆን ተቃርቦ የነበረው ትዝ አለኝና አሁንም ታሪክ እራሱን ሊደግም ነው? ብዬ ትንሽ ደንገጥ አልኩ። አልማማውን እንደማውቀው ገለጽኩለት። ውጭ ንግድ ከመጣሁም በኋላ ስላደረግነው ግንኙነት ሳልሸሽግ ነገርኩት። "በል፣ አንጠፋፋ" ተባብለን ተለያየን። ያን ወዳጄን ከዚያን ቀን በኋላ ማየቴን አላስታውስም።

አልማማው እነመንግሥቱን ገልብጦ የራሱን መንግሥት የመመሥረት እቅድ እንደነበረው፣ በሚያቋቁመው መንግሥት ውስጥ ይጠቅማሉ ያላቸውን ሰዎች የስም ዝርዝር አዘጋጅቶ እንደነበረና ዝርዝሩን መንግሥት እንዳገኘው፤ የኔም ስም ዝርዝሩ ውስጥ ተጽፎ እንደነበረ፣ ካድሬዎቼ ናቸው የሚላቸውን ሰዎች በአንዳንድ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሰግስጎ እንደነበር ሰማሁና ወቸ ጉድ፣ እኔም ጉያ ውስጥ ካድሬውን ሊቀብር አስቦ ነበራ ሰው ቅጠርልኝ ያለኝ? ብዬ ተገረምኩ::

እውነቱን ለመናገር አልማማው እሱ ቢፈልገኝም እኔ ግን የምፈልገው ዓይነት ሰው አልነበረም:: በሕይወት ስለሌለ የሙት አምላክ ይቅር ይበለኝና መንፈሴ ይህን ያህልም አይፈቅደውም ነበር:: ለዚህ ምክንያቱ ለሥልጣን ለሚቋምጡ ፖለቲከኞች፤ ካለኝ ዝቅተኛ አስተያየት ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል:: "ሰይ ብል ባከረባብት" ለሚል ተኳሽ አልማማውና እኔ ጥሩ ዒላማ እንሆንለት ነበር:: ስለሆነም፣ ጅምላ ፍርድ ምን ያህል ስሕተት ውስጥ ሊጥል እንደሚችል የአልማማውና የኔ ግንኙነት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችል ነበር::

በሌላ በኩል፣ የአልማማው ተባባሪ ተብዬ ሕይወቴ ቢያጥር ኖሮ ይህን ታሪክ ለአንባቢ ለማቅረብ አልችልም ነበርና የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሚያስፈልገው የምክር ክምር አንድ ኪሎ ይጎድልበትና ቀን ይጨልምበት ነበር:: ሙህር ውስጥ አንድ ቀልደኛ ሰው ነበር ይባላል:: ሲሞትም በራሱ እየቀለደ ነው ነፍሱ ከሥጋው የተለየችው:: "ሙህር ጉድሽ ፈላ፤ እኔ ከሞትኩብሽ ማንም የለሽም" አለ ይባላል:: የዚህም ሆነ ስለኔ ምክር ወሳኝነት የተነገረው ተቃራኒ ትርጉሙ ማንም መጣ ማንም ሄደ የኢትዮጵያን ወይም የሙህርን ሕይወት መለወጥ አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱ ነው:: አቶ ይልማ ደሬሳ ማሞም መጣ፣ ማሚቱም መጣች ቀውስ የገጠመውን የኢትዮጵያን ኤኮኖሚ ማንም አያስተካክለውም አሉ እንደተባለው ነው::

ፌዙ ለጊዜው ይብቃና የእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ክቡርና ቅዱስ ነው፤ ማንም እንዲያጠፋው መብት የለውም። የታደለች ሕይወት ለሌላም ትተርፋለችና ሁሉም ተንከባክቦ ሊይዛት ይገባል። ስለዚህ ለሕይወት ደንታ የሌላቸው አጥፊዎችን ቢቻል ወደ ቀና ጎዳና መመለስ፣ ካልተቻለ ግን መግታት ያስፈልጋል። ይህ የሚመለከተው ግለሰቦችንና ቡድኖችን ብቻ ሳይሆን መንግሥታትንም ይጨምራል። የሕይወትን ክቡርነት ያልተረዱ ባለሥልጣኖች የሕዝብን ደኅንነት እንዲጠብቁና ተስፋውን እንዲያለመልሙ አደራ ማለት በጎችን ተኩላዎች ይጠብቁ እንደማለት ነው።

ለደጎና መሪዎች መውጣት እድልም ያስፈልጋል። ደጎና መስለው መድረኩን ከያዙና ከተደላደሉ በኋላ ወደ ሰይጣንነት የመለወጥ ችሎታ ያላቸውን መሪዎች በታሪክ በብዛት ዐይተናል። የሮማው ቄሳር ኔሮ ልጅ ሳለ ችግረኛ ሲያይ ያለቅስ ነበር ይባላል። ከነገሠ በኋላ ግን ሰዎችን ጧፍና ሰም እየቀባ ያነደደ ሰው ነው። የሮማ ከተማን በአዲስ መልክ ለመገንባት ፈልጎ የድሆችን መኖርያ ያቃጠለ ሰው ነው። በአገራችንም ሰውን ጧፍ ቀብቶ ያነደደ መሪ ስለመኖሩ በመጽሐፍ አንብቤአለሁ። መጽሐፉን የታሪክ አዋቂዎችም ሳያነቡት የቀሩ ስለማይመስለኝ የሚሉትን ወደፊት እንሰማለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ታሪኩ ጭብጥ ያለው ከሆነ የነበሩትን የዐይን ምስክሮች ሞተው ሳያልቁ የሚሉትን መስማት ያስፈልጋል። ለዚህም የታሪክ አዋቂዎች ኃላፊነት አለባቸው እላለሁ።

በአዲስ አበባ ከተማ ምስማር ተራ ይባል የነበረውና የብዙ ሺህ ሕይወት ደግፎ ይዞ ያቆየው የንግድና የእጅ ሙያተኞች መናኸሪያ ሲቃጠል የጊዜው ከንቲባ በቦታው ላይ ደርሶ እሳቱ እንዳይጠፋ እንደከለከለ የትናንት ትዝታ ነው። ልጅ ሆኜ እሳቱን እኔም አይቼዋለሁ። አድራጎቱ ኔሮ የሮማን ከተማ በማቃጠል ከፈጸመው ወንጀል ተለይቶ የሚታይ አይደለም። ኔሮ እንኳ ሮማን እንደገና አስውቦ ሠራት። መደብራቸው የተቃጠለባቸው ሰዎችን በተመለከተ ግን አዲስ መደብር በቦታው ላይ ይሠራላችኋል፣ ገንዘብ ክፈሉ ተብለው ከከፈሉ በኋላ አሠራላችኋላሁ ያላቸው ኮሎኔል ገንዘባቸውን በልቶ

ቀረ:: በጥፋት ላይ ጥፋት፣ በወንጀል ላይ ወንጀል:: ተበዳዮቹ አቅም አጥተው ወንጀለኞቹን መፋረድ ባይችሉም እግዚአብሔርና ታሪክ ግን ይፋረዱላቸዋል ብለን እናምናለን::

በደፈናው መሳደብና መራገም እንጂ የስሕተቶችና የወንጀሎች መንስኤያቸው ምን እንደሆነ ተንትነን በመፍትሔ ሐሳብ ላይ መድረስ አናውቅበትም:: ስለሆነም፣ ዐይናችን ለማየት እንዳይችል ስለሚከለል ተመሳሳይ ስሕተቶችን በተደጋጋሚ ሲፈጸሙ ኖረዋል:: በዚህች ዓለም ስለተመኙት ብቻ የሚሆን ነገር የለም:: ከሕልም ውጭ ማለቴ ነው:: ወሳኝነት ያላቸውን ድርጊቶችና ክስተቶች ገሀድ አውጥቶ መመርመር ወይም መገምገም ያስፈልጋል:: ደኅና የተሠራውን በአንድ ቋት፣ የተበላሸውን በሌላ ማድረግና ጥቁሩን ጥቁር ነጩን ነጭ ማለት መልመድ ይኖርብናል:: ሽፋፍኖ ማለፍ የትም አላደረሰንም:: አንድ ትውልድ፣ ግለሰብ፣ ታሪክ ጸሓፊ ሥራው የወደደውን አጡዞ ሰማይ ማድረስ፣ የጠላውን ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ጸጉር ጥላሸት ቀብቶ መቀመቅ ማውረድ ከሆነ ሕይወት የምታስተምረንን ልምድ ሳንቀስም እንቀራለን:: የወደቀን በመርገጥ፣ ጊዜ ያነሳውን በማወደስ ትንሣኤ እናገኛለን ብለን ካመንን የዋሆች ነን:: ተደጋግመው መፈጸም የሌሉባቸው ስሕተቶች ተንጓለው መውጣት ይኖርባቸዋል:: አርአያነት ያላቸው ሥራዎች በኅብረተሰቡ ታውቀው ሁሉም የሕይወት መመሪያው እንዲያደርጋቸው ከትምህርት ቤት ጀምሮ ሕዝቡን ማስተማር ይገባል:: ይህን ማድረግ ከቻልን የተሻለች ኢትዮጵያን መገንባት እንችላለን:: በመላው ዓለም የተበታተንነው የኢትዮጵያ ልጆች እንደገና ተሰባስበን ለግንባታው ጠቃሚ አስተዋፅኦ ማድረግ እንችላለን:: ያለበለዚያ የኛ ነገር ዘለዓለም ታጥቦ ጭቃ፣ ዘለዓለም ጥሬ ይሆንና የዓለም መሳለቂያ ሆነን እንዳንቀር ያሰጋል::

ስለውጭ ንግድ ገጠመኞቼ ከመጨረሴ በፊት የጣሊያን መንግሥት ስለሰጠው እርዳታ ማውሳት እፈልጋለሁ:: የጣሊያን መንግሥት ከጣሊያን አገር ኩባንያዎች ሸቀጣሸቀጥና ቋሚ እቃዎች ለመግዣ የሚውል፣

በትክክል ባስታውስ የሰባ አምስት ሚሊዮን ብር ወይም የሠላሳ ሰባት ሚሊዮን ዶላር እርዳታ ይሰጣል። ገንዘቡን የሚያስተዳድረው በውጭ ንግድ ሚኒስትሩ የሚመራ የሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ተወካዮችና የጣሊያን መንግሥት የመደበው አማካሪ የሚገኙበት ኮሚቴ ነበር። የፕሮግራሙን ይዘት ባጭሩ ለመግለጽ፣ ገንዘቡ ለምን ዓይነት ግዢዎች ሊውል እንደሚችል ዝርዝር ወጣ፤ በገንዘቡ መጠቀም የሚፈልግ ግላዊም ሆነ መንግሥታዊ ድርጅት ከጣሊያን ማስመጣት የሚፈልገውን እቃ ለመግዛት ጨረታ ያወጣል፤ ጣልያኑ አማካሪ የጨረታውን ሂደት እየተከታተለ አስፈላጊውን የቴክኒክ እርዳታ ያደርጋል፤ የጨረታውን ውጤት ለኮሚቴው ያቀርባል፤ ኮሚቴው ጨረታውን መርምሮ ግዢውን ይፈቅዳል፤ እቃው ይታዘዛል፤ አስመጪው ገንዘቡን በብሔራዊ ባንክ ውስጥ በተከፈተ ሒሳብ ውስጥ ለመንግሥት ገቢ ያደርጋል፤ ከዚያም እቃውን ይረከባል። በብሔራዊ ባንክ ውስጥ የሚጠራቀመው ብር ሁለቱ መንግሥታት ለተስማሙባቸው ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ እንዲውል ስምምነት ተደርሶ ነበር። ስለተጠራቀመው ገንዘብ አጠቃቀም የውጭ ንግድ ሚኒስቴርን የሚመለከት ጉዳይ አልነበረም።

አንድ ቀን ከፕሬዚዳንቱ የፕሮቶኮል ቢሮ ይደወልና እገሌ የሚባል ሰው ሊያነጋግርህ ስለሚፈልግ ቀጠሮ ብትሰጠው ተብዬ እጠየቃለሁ። ባንክም ሆኜ ሆነ ውጪ ንግድ የታወቀ የቀጠሮ አሰጣጥ ሥርዓት እከተል ነበር። ቀጠሮ የጠየቁ ሰዎች ስም፣ ቀጠሮ መቼ እንደጠየቁ የሚገልጽ ዝርዝር በየጊዜው ጸሓፊዬ ታቀርብልኛለች። ሊስቱ ላይ ቀንና ሰዓት ምልክት አደርጋለሁ። ጸሓፊዬም ለባለጉዳዮቹ ደውላ ታሳውቃቸዋለች። ስለዚህ ቁጥራቸው በርከት ያለ ባለጉዳዮች በቢሮዬ አካባቢ ተኮልኩለው ማየት የተለመደ አልነበረም። በሌላ ባለሥልጣን አማካይነት ቀጠሮ ይጠይቁ የነበሩት አብዛኛዎቹ ጥያቄዎቻቸው ትክክለኛነት የጎደላቸው መሆኑን ስለሚያውቁ በተዘዋዋሪ ተፅእኖ ለማምጣት ስለሚፈልጉ ወይም ስለሚሞክሩ ነበር። ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ባለጉዳዮች ከበሬታ አልነበረኝም። እንዲያውም በመጠኑም ቢሆን እጠየፍባቸው ነበር ለማለት እደፍራሁ።

በተመሳሳይ፣ ጉዳያቸውን ወይም ችግራቸውን በቀጥታ ለኔ ሊነግሩኝ ሲችሉ ከፍተኛ ባለሥልጣን ዘንድ ቀርበው ስሞታ ያቀርቡ በነበሩትም ላይ እንደዚሁ እጠነክርባቸው ነበር::

ቀጠሮ የተጠየቀለት ሰው ከስሙ የጣሊያን ተወላጅ መሆኑን ገመትኩ:: ሰውዬው ቢሮ ሲመጣ ግምቴን ትክክል ሆኖ አገኘሁት:: አመጣጡ እሱ የሚወክላቸው የጣልያን ኩባንያዎች የግዥ ትእዛዝ እንዲያገኙ ሁኔታውን በማመቻቸት የምተባበር ከሆነ ለወሮታዬ እንደሚከፈለኝ ሊገልጽልኝና ቃል እንድገባለት ነበር::

ተመሳሳይ ጥያቄ ወይም መደለያ ሲቀርብልኝ ይህ የመጀመሪያው አልነበረም:: አንዳንዶቹን እጠቅሳለሁ:: በ1967 ወደ ብሔራዊ ባንክ እንደሄኩ መጀመሪያ የቀረበኝ አንድ ንግድ ሚኒስቴር ውስጥ ይሠራ የነበረ ቼኮዝሎቫኪያዊ አማካሪ ነበር:: የውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ መላክ ለጊዜው ታግዶ ስለነበር ገንዘቤን እንዳወጣ የምትፈቅድልኝ ከሆነ የምትጠይቀኝን ለመፈጸም ዝግጁ ነኝ ብሎኛል:: ያኔ ወኔውም፣ ጉርምስናውም ስለነበር ሰውዬውን አዋርጄ ከቢሮዬ አስወጣሁት:: ኢ. ሲ. ኤ ቀጥሮት ኖሮ አፍሪቃ አዳራሽ ስሄድ አልፎ አልፎ እንተያይና መግቢያ ጉድጓድ የሚፈልግ ሰው ሆኖ ይታየኝ ነበር:: ከብር ኅትመት ጋር በተያያዘ ደግሞ የባንኩ ገንዘብ አታሚ ድርጅት የቶማስ ዶላሩ የቅርብ ተወዳዳሪ የነበረው ብራድበሪ ዊልክንሰን የኅትመቱን ሥራ ለኛ ከሰጣችሁን አስፈላጊውን እናደርግልሃለን ብሎ ወኪላቸው ነኝ በሚል ሰው በኩል ቀርቦኝ ነበር:: ወኪል ነኝ ባዩ ተቀማጭነቱ ናይሮቢ ከተማ የሆነ ወዳጄን እንዲያግባባኝ አዲስ አበባ ድረስ ልኮብኛል::

አንድ ጉቦ ወይም የእጅ መንሻ አቅራቢ በመጀመሪያ ደረጃ የባለሥልጣኑን ድክመቶች ያጠናል:: ገንዘብ የሚወድ ከሆነ ገንዘብ ይሰጣል:: ባለሥልጣኑ በገንዘብ የማይደለል ከሆነ በቅርብ ቤተሰብና ወዳጅ አማላጅነት ይገባበታል:: የባለቤቴ አባትና አንዳንድ የቅርብ ወዳጆቼ ከፍተኛ ችግር ይደርስባቸው እንደነበር አውቃለሁ:: አንዱ ወዳጄ ታደሰን ካገኘሁት በጣም ረጅም ጊዜ

ነው ለማለት እንዲያመቸው ርቆኝ እንደነበር አውቃለሁ:: እኔን በተመለከተ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ፍላጎታቸው እንዲሟላላቸው ሳያፍሩ ይጠይቁ የነበሩት በብዛት የኤርትራ ክፍለሀገር ተወላጆች ነበሩ:: ከናይሮቢ ወዳጄን ባማላጅነት የላከብኝ የዚሁ ክፍለሀገር ተወላጅ ነበር:: ብዙ ቆይቶ ሁኔታዎችን ሳገናዝብ የኤርትራ ተገንጣይ ቡድን እጅ ሳይኖርበት አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አድሮብኝ ነበር::

አንድ በሕግ ሥራ ላይ የተሰማራ የቅርብ ጓደኛዬ ፍትሕ እንዲያዛባ ባለጉዳዮች በገንዘብ ሊደልሉት ይሞክሩና አልሳካ ይላቸዋል:: ምን ይወዳል? ብለው ቢጠይቁ ውስጠ አዋቂ፣ "ቆንጆ ሴት" ብሎ ይጠቁማቸዋል:: ባለጉዳዮቹ አንድ ቀን የእምዬ ማርያምን ሥዕል የምትመስል ቆንጆ ቢሮው ድረስ ይዘው ከቸች ይላሉ:: ሲያያት ልቡ ወከክ ይላል:: ያስተዋውቁታል:: ከዚያ የሚሠራውን ሠራ:: ታሪኩን ካጫወተኝ በኋላ አንተ የማትረባ፣ ልክስክስ ብዬ የጓደኛ ስድብ ከሰደብኩት በኋላ፣ ለመሆኑ ፍርድ ወይም ፍትሕ አዛባህ? ብዬ ጠየቅሁት:: "በጭራሽ" ብሎ ማለልኝ:: ስለማምነው የምጠራጠርበት ምክንያት አልነበረኝም::

ጣሊያኑ ከሁኔታውና ካነጋገሩ የማፊያ ድርጅት አባል ሳይሆን አይቀርም ብዬ ገመትኩ:: እሱ የሚጠይቀውን በምንም ዓይነት እንደማላደርግ፣ ለዚህ ሲል ቢሮዬ ድረስ መምጣቱ በራሱ ክብረነክ መሆኑን ስነግረው "አንተ ሞኝ ሰው ነህ፤ እንድትጠቀም አስበን ነው እንጂ በዚህም በዚያ ፍላጎታችን መሟላቱ አይቀርም" ብሎኝ ተነስቶ ሄደ:: አንተ ሞኝ ሰው ነህ የሚለው አባባል የጂቡቲን አምባሳደር አስታወሰኝ:: በኋላ እንደሰማሁት ጣልያኑ አማካሪ "መንገድ በማመቻቸት" ይተባበራቸው እንደነበር ተነግሮኛል:: በኮሚቴው ውስጥ የሚሠራው ሥራ ግልጽና ንጹሕ ይመስል ነበር:: ሰውዬው እንዴት አድርጎ ይረዳቸው እንደነበር ለኔ ግልጽ ባይሆንም በእቃ አቅራቢዎችና በገዢዎች መካከል እየገባ የደላላነትም ሥራ ሳይሠራ የቀረ አይመስለኝም:: የጨረታዎቹ ውጤት ኮሚቴው ዘንድ ሲቀርብ ውስጥ ውስጡን ያልሆነ ሥራ ተሠርቶ ከሆነም ኮሚቴው የሚያውቅበት መንገድ

አልነበረውም፡፡ አማካሪው ነገር ፈልጎ እርዳታው እንዲቋረጥ ምክንያት እንዳይሆን በጥንቃቄ የያዝነው ሰው ስለነበር የሱንም ሆነ የኮሚቴውን ሥራ የዓለም ባንክ እንዲገመግመው ሁለቱ መንግሥታት ስምምነት አድርገው ስለነበር የኮሚቴው ዋና ትኩረት ገንዘቡ በተቻለ ፍጥነት በሥራ ላይ የሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት ነበር፡፡

የእርዳታው አሰጣጥ ጉዳይ በስፋት ሲታይ መጀመሪያውኑ ገንዘቡን የጣሊያን መንግሥት የፈቀደው ለኢትዮጵያ ብቻ ታስቦ ሳይሆን የጣሊያን ኩባንያዎችና በነሱ ዙርያ የተኮለኮሉት ቃራሚዎች እንዲጠቀሙ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል፡፡ ስለእርዳታው ጽንሰ ሐሳብ ማርክስና ኤንግልስ ቢጠየቁ የጣልያን መንግሥት የሕዝብን ገንዘብ ወደ ጣልያን ግል ድርጅቶችና ግለሰቦች ኪስ ውስጥ ለማስገባት የቀየሰው ዘዴ ነው ባሉ ነበር፡፡ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ ኢትዮጵያ ሦስት አራተኛውን ማግኘት ከቻለች በጣም ጥሩ ውጤት ነው ብለው ስለዓለም አቀፍ እርዳታ አጠቃቀም እናውቃለን የሚሉ ሰዎች ይናገሩ ስለነበር ግልጽ ሽፍጥ እስካልተፈጸመ ድረስ በሆነው ባልሆነው አንጃ ግራንጃ ፈጥረን እርዳታው ከሚቋረጥ ገንዘቡ በተቻለ ፍጥነት በሥራ ላይ በሚውልበት መንገድ ላይ እንድናተኩር ተስማምተን ነበር፡፡ የአፈጻጸም ችግር ቢያጋጥም ኖሮ እርዳታው የማይሰረዝበት ምክንያት ስላልነበረ ገንዘቡን ሙሉ በሙሉ መጠቀም በመቻላችን በጣም ደስ አለን፡፡ አጋጣሚውን ተጠቅመን የቆዳውን ዘርፍ ለመደገፍ በመቻላችን በደስታ ላይ ደስታ ጨመረልን፡፡

ገንዘቡን ተጠቅመን ሌላ ልናስፋፋበት ፈልገን የነበረው በተለይ የተሽከርካሪ ጋራዦችን ነበር፡፡ በአገሪቱ ብዙ ጋራዦች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ የተሟላ መሣሪያ ስለሌላቸው የሥራ ውጤታቸው ደካማ እንደሆነ የታወቀ ነበር፡፡ ስለሆነም፣ የሚያስፈልጓቸውን መሣሪያዎችና የባለሙያ እቃዎች ከውጭ አስመጥተው ሥራቸውን በዘመናዊ መልክ እንዲያደራጁና እንዲያስፋፉ አስበን አንድ ጥናት ተደረገ፡፡ ባልሳሳት ሠላሳ ጋራዦች ተመረጡ፡፡ ስለነበረን አስተሳሰብ ለጋራዦቹ ባለቤቶች ከተገለጸላቸው በኋላ እንደሌሎች

እቃ አስመጪዎች እነሱም አጭርተው የሚፈልጉትን ሊገዙ እንደሚችሉ ብንነግራቸው አሻፈረን አሉ፡፡ ምን ነካቸው? ብለን ብናጠያይቅ "ሞኞችሁን ፈልጉ፤ አወፍራችሁ ልትበሉን እንደሆነ ደርሰንበታል" እንዳሉ ተነገረን፡፡ መንግሥትና ሕዝብ እስካልተማመኑ ድረስ ብዙ መሥራት አይቻልም፡፡ ምንም ማድረግ አንችልም ብለን ለጋራዦች መድበነው የነበረውን ገንዘብ ወደ ሌላ አዞርነውና ሌሎች ተጠቀሙበት፡፡

# ምዕራፍ ስምንት

# አምባሳደርነት

የቆዳው ትርኢት በተደረገ በሁለተኛው ወር፣ ማለትም በየካቲት 1982፣ አጋማሽ አንድ ቀን ቢሮ አምሽቼ ገብቼ ከባለቤቴ ጋር እራት እየበላን ሳለ አምባሳደር ተብዬ ከአገር እንድወጣ መወሰኑን በሁለት ሰዓቱ የዜና ፕሮግራም ሰማን።

አምባሳደር በተባልኩበት ወቅት ብዙ ባለሥልጣኖች ከአገር ለመውጣት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥያቄ  ያቀርቡ እንደነበር ይወራ ስለነበር ብዙ ሰዎች አንተ በጣም እድለኛ ሰው ነህ አሉኝ። በእርግጥ በሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት አስተሳሰቡን፣ ፖሊሲውንና አሠራሩን አስተካክሎ አገሪቱን ወደተሻለ ጎዳና ይመራታል የሚለው እምነቴ ተሟጥጦ አልቆ ስለነበር የኔና የመሰሎቼ መቆርቆርና መሯሯጥ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ከተገነዘብኩ ውሎ ያደረ ቢሆንም በጊዜው ከሥራ ገበታዬ ላይ መነሳቴን ያየሁት ባላጋራዎቼ ከነበርኩበት ቦታ እንዳስነሱኝና እንዳሸነፉኝ ስለነበር ከፍተኛ ቅሬታ አደረብኝ። ከእኔ ጋር አምባሳደር ተብለው የተመደቡት ሰዎች ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እየሄዱ የት እንደተመደቡ ያጠያይቁ እንደነበር እሰማ ነበር። በበኩሌ ካናዳ መመደቤ እስኪነገረኝ ድረስ፣ ማለትም ለሁለት ወር ያህል ወደ ሚኒስቴሩ ብቅ አላልኩም።

አንድ አምባሳደር ወደተመደበበት አገር መሄድ የሚችለው የተመደበበት አገር መንግሥት ሲቀበለው ብቻ ነው። በአገራችን የካናዳ አምባሳደር ከአገሩ መንግሥት በደረሰው ትእዛዝ መሠረት አንድ ጥያቄ አቀረበልኝ።

ይኸውም፣ ቀበሌ ውስጥ ሠርቼ እንደሆነና ለሰው ሕይወት ማለፍ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠያቂ እንደሆንኩ ነበር፡፡ እንደማይመለከተኝ ነገርኩት፡፡

ስለቀበሌ ሲነሳ እኔም እንደ ብዙ ሰው ብዙ ትዝታዎች አሉኝ፡፡ ሁለቱን ላጫውታችሁ፡፡ አብዮቱ እንደፈነዳ ከጓደኞዬ ከአስፋው አገኘሁ ጋር አንድ ላይ ቂርቆስ አካባቢ፣ ከአራተኛ ክፍለጦር ዝቅ ብሎ እንኖር ነበር፡፡ በትዳር ምሥረታ ቀደምኩትና ሩፋኤል ቤተክርስትያን ዝቅ ብሎ ቤት ተከራይቼ ወጣሁ፡፡ በጋብቻችን ሰሞን አስፋው መልስ ይጋብዘንና እሱ ዘንድ እናመሻለን፡፡ ከዚያም ከሦስት ሴት ሚዜዎቻችን ጋር አምስት ሆነን ወደ ሰፈራችን ወደ ሰሜን አዲስ አበባ በመስፍን ሐረር መንገድ አድርገን አመራን፡፡ ወደ ሰፈራችን መታጠፊያ መንገድ ስንደርስ የቀበሌ ሰዎች አንድ ሰው ተኩሰው ገድለው ሰውዬው ሲንፈራፈር ደረስን፡፡ እኔንም አቁም አቁም ብለው መሣሪያ ደግነው አስቆሙኝ፡፡ ከአውቶሞቢሏ አስወረዱን፡፡ ሴቶቹ ከድንጋጤ ብዛት ሽንታቸውን ለቀቁት፡፡ መታወቂያ ሲባል ሴቶቹ ቦርሳቸውን በርብረው አወጡና ሰጡ፡፡ ባለቤቴ ከፈለጋችሁ ሌላም መታወቂያ አለኝ አለቻቸው፡፡ በዚያን ዘመን ሌላ መታወቂያ አለኝ ማለት የተጭበረበረ መታወቂያ አለኝ እንደማለት ይቆጠር ስለነበር ምን ሊሉ ነው ብለን ተጠባበቅን፡፡ ሰዎቹ ጉዳያቸው ከሴቶቹ ጋር ሳይሆን መኪና ከያዝኩት፣ ክራቫት ካንጠለጠልኩትና ከነሱ የተሻለ ልብስ ከለበስኩት ከኔ ጋር ስለነበር ተኩሶ ገድሏል ብዬ የጠረጠርኩት ሰውዬ እጁ እየተንቀጠቀጠ ወደኔ አነጣጥሮ ኪሴን ዳበስ ዳበስ ለሚያደርገው ባልደረባው “አልተባበር አለህ አይደል? ዞር በል” አለው፡፡ ፈታሹ ዞር ቢል አቶ አነጣጣሪ አድኀሪ ብሎ ሊደፋኝ ያሰበ ይመስላል፡፡ ፈታሹ የአነጣጣሪው ሁኔታ ደስ ስላለው የሚፈትሸኝ መስሎ በሰውነቱ ከልሎኝ ቆመ፤ “ሰውዬው፣ ዞር በል ነው የምልህ!” ቢለውም ቆይ ገና እየፈተሽኩት ነው፣ አልጨረስኩም አለው፡፡ ድምፁን ዝቅ አድርጎ “አይዞህ” አለኝ፡፡ እኔም ተረጋጋሁ፡፡ ፈታሹ አነጣጣሪው እንደበረደለት ካወቀ በኋላ ቀስ ብሎ ከፊቴ ዞር አለ፡፡

እላይ የተገለጸው የዚህን ዓለም ውጥንቅጥነት ያስረዳል። የብዙ ሰው ሕይወት በቀበሌ ሰዎችና በሌሎችም እጅ ጠፍቷል። የምወደው ውድ ወንድሜን አብርሃምን በአደባባይ ረሽነውታል። በአንጻሩ የሰውን ሕይወት ለማዳን መሥዋዕት የከፈሉ እንዳሉ መካድ አይቻልም። የተጠቀሰው ሩፋኤል ቤተክርስትያን ግርጌ እንኖርበት የነበረው ቀበሌ ሊቀመንበር የገዳዮች ተባባሪ አልሆንክም ተብሎ ልቡ እስኪጠፋ ድረስ ገርፈውት ቤት ውስጥ ሲያገግም እንደነበር የዐይን ምስክር ነኝ።

ሁለተኛውም ታሪክ እዚያው ሩፋኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ስንኖር የደረሰብኝ ነው። በሰርጋችን በሁለተኛው ሳምንት፣ ህዳር 1970፣ ሠራተኛ ትሄድብናለች፤ ሙሽሪትንም ያምብኛል። እሁድ ቀበሌ ስብሰባ እንዳትቀሩ ተብሎ መነገሩን ባውቅም ታማሚዋን ጥዬ መሄድ አልችልም ብዬ ቀረሁ። የቀበሌ ወታደሮች በአጥር ዘለው ገብተው፣ የመኝታ ክፍላችንን በር በሰደፍ ይሁን በእርግጫ እየደበደቡ ና ውጣ እያሉ ፎከሩ። ባለቤቴ ውሃ ሆነች። የልብ ሕመም ቢኖርባት ኖሮ ያን ቀን መሰናበቻዋ ይሆን ነበር። በር አስከፍተው እጅ ወደላይ ካስደረጉኝ በኋላ ሁለት ከፊት ሁለት ከኋላ ሁለት ከግራ ሁለት ከቀኝ ሆነው አጅበው ቀበሌው ወሰዱና ለሊቀመንበሩ አስረከቡኝ። ከየቤታችን ተነድተን የመጣነው ስብሰባው እስኪያልቅ ድረስ ቆመን ሁሉም እንዲያየንና መቀጣጫ እንድንሆን ተፈረደብን።

ወደ አምባሳደርነቴ ስንመለስ፣ የካናዳ መንግሥት እንደሚቀበለኝ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ካስታወቀ በኋላ ወደተመደብኩት አገር የምነሳበትን ቀን ገልጬ ፕሬዚዳቱን ለመሰናበት ቀጠሮ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁ። ለመሄድ አንድ ወይም ሁለት ቀን ሲቀረኝ ዛሬ ያነጋግሩሃልና እቤት ሆነህ ተጠባበቅ ተብሎ ተነገረኝ። ቀኑን ሙሉ ከቤት ሳልወጣ ስልክ ስጠባበቅ ዋልኩ። ሳልጠራ ቀረሁ። ኦታዋ የምገባበት ቀን ለካናዳ መንግሥት የተገለጸ ስለሆነና ሊቀበሉኝ ተዘጋጅተው ስለሚጠብቁ የጉዞዬን ፕሮግራም መሰረዝ አልችልም ብዬ ቤተሰቤን ይዤ ወደ አየር ማረፊያ አመራሁ።

የቤታችንን ግቢ ለቅቀን ስንወጣ ውሻችን ቡቺ ያሰማችው ኡኡታ ወይ ተቃውሞ በፍጹም የማንረሳው ነው። ቡቺ በተለይ ለመጨረሻው ልጃችን ለዮሐንስ የተለየ ፍቅር ነበራት። ዮሐንስ ስለኢትዮጵያ ምን ታስታውሳለህ? ብለን ስንጠይቀው ትዝ የሚሉት ሁለት ሰዎችና ቡቺ ብቻ ናቸው። ዕድሜውም አምስት ዓመት ከሶስት ወር ነበር። ቡቺ ግቢውን ለቅቀን እንደምንወጣ ስታይ በምላሹ ያሳየችው መወራጨትና ያሰማቸው ልዩ የሐዘን ድምፅ ሁላችንንም ረበሸን። የፈለግነው ጎረቤቶቻችንና ወዳጆቻችን እነአቶ ታፈሰና ወይዘሮ ጽጌ ዘንድ ልንተዋት ነበርና ልንይዛት ፈልገን ስንጠጋት ትሸሻለች፣ ትተናት ልንሄድ ስንል ደግሞ ሮጣ መጥታ ያንን አሳዛኝ ድምፏን ታሰማናለች። ባጭሩ ትነግረን የነበረው መሄዳችንን እንዳወቀችና በዚህ በፍጹም እንደማትስማማ፣ ነገር ግን ከኖረችበት ቤት መውጣት እንደማትፈልግ ነበር። ምርጫ ስላልተገኘ ባለችበት እንተዋትና ቤቱን የሚገባበት ሰው እንደኛ ሆኖ እንዲጠብቃት ይጠየቅ ተባብለን ትተናት ግቢውን ጥለን ወጣን።

የባለቤቴ ታላቅ እህት የአሳመረችና የጓደኛዬ የስሜ የበኩር ልጅ ግሩም በሕፃንነቱ በተከፈተ የአጥር መዝጊያ ይወጣና ከቤታቸው ጓሮ ከወሎ ሰፈር ግርጌ ወደሚገኘው ገደላማ ስፍራ ሲግተረተር ይወርዳል። ከውሻቸው ሌላ ማንም ያየው ሰው አልነበረም። ውሻይቱ ስትታይ ፈዛዛ፣ ተኝታ የምትውልና ሳትሠራ የምትበላ ሰነፍ ትመስላለች። ወይዘሮ ውሺት ግን ግሩምን መጠበቅና በየሄደበት መከታተል መደበኛ ሥራዋ አድርጋ ይዛዋለች። እንቅልፋም ናት፣ ምን ትረባለች፣ ለፓስተር ኢንስቲትዩት ብትበረከት ይሻላል ተብሎ በቤተሰብ ደረጃ ሳይቀር አቋም የተወሰደባት፣ ጠበቃ ያልቆመላት ምስኪን ነበረች። ግሩም ከቅጥር ግቢው ሲወጣ ተከትላው ወጣች። ግሩም እየተንደረደረ ገደሉ ውስጥ ገብቶ ሊወድቅ ሲል ውሻዩቱ ከኋላው ሱሪውን በጥርሷ ይዛ ወደኋላ ጎትታ አዳነችው። ትርኢቱን አንዲት ቅጠል ለቃሚ ትክ ብላ ታስተውላለች። ከዚያም ግሩምን ታቅፋ ወደቀበሌ ጽሕፈት ቤት ታመራለች። ውሻዩቱም ትከተላለች። የቤቱ ሰው ግልብጥ ብሎ ግሩምን ፍለጋ ወጥቶ አካባቢውን ሲያስስ ከሴትዮዋ

ጋር ይገናኛሉ:: ሴትዮዋ የሰዉ ብዛት ይገርማትና፣ “ይህ ሁሉ ሰው ቤት ውስጥ እያለ ነው ሕፃኑ ጠባቂ አጥቶ ከአጥር ውጭ የሄደው? በይ፣ ወይዘሮ እናት፣ ይህን ሁሉ ሰው ከመቀለብ ይህችን ውሻ ደኅና አድርገሽ ተንከባከቢ” ብላ ግሩምን አስረክባት ወደምትሄድበት ሄደች::

አበሻ ሰውን ለምን ውሻ ብሎ እንደሚሳደብ ለእኔ እንቆቅልሽ ነው:: ከእንስሳት ሁሉ እንደውሻ ታማኝ የለም:: ያስተማሩትን በደንብ ይቀበላል:: ውሻ ለሰው ልጅ አጋሩ እንጂ ጠላቱ አይደለም:: ስለሆነም፣ መሰደብ የለበትም:: እንደዚሁም፣ አህያ ባይኖር ኖሮ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርቱን ከቦታ ቦታ ማመላለስ ይሳነውና እንደ አህያ መሆኑ አይቀርም ነበር:: ስለዚህ ለአህያ የሚገባው ስድብ ሳይሆን ቋሚ ሐውልት ነው::

ነገሩ በጥቅሉ ሲታይ የሚመግበንን እጅ የመንከስ በሽታ የተጸናወተን ይመስላል:: ታማኝን መስደብ፣ አጋዥን መደብደብና መርገጥ፣ ሠራተኛን ማንቋሸሽ፣ ሙያተኛን ስም መስጠት እናውቅበታለን:: እንዲህም ብሎ “እውቀት” የለም:: ሽፍታን ወይም ቀማኛን እናደንቃለን፤ ለኃይለኛ እናጎበድዳለን፤ ደካማን ተረባርቦ እንደመጠበቅ ኃይለኛው ሲያንቀራጥጠውና አንስቶ ሲያፈርጠው በአድናቆት እንመለከታለን:: አንዱ የሌላው ምግብ በሆነበት በእንስሳት ዓለም እንደዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል፤ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯልና እሱም እንደ አምላክ ነው ከተባለው ከሰው ልጅ ግን በፍጡር ላይ መጨከን በፍጹም የማይጠበቅ ነው::

ወደ ኦታዋው ጉዞአችን እንመለስና ሊሸኘን ተሰብስቦ ከነበረው ዘመድና ወዳጅ መካከል አንድ የማላውቀው ሰው ከቤታችን አጥር ውጭ ማሲንቆ ይዞ ቆሞ አየሁ:: ማንነቱን ሳጠያይቅ የልጅነት ጓደኛዬ ተስፋዬ በየነ ኬነዲ ቤተሰቤን እስከ አውሮፕላን ማረፊያ በሙዚቃ እያዝናና አጅቦ ሊወስደን አስቦ እንዳስመጣው ተነገረኝ:: ወቅቱ የመዝናኛና የመደሰቻ ሳይሆን

ከዘመድና ወዳጅ ስለምንለይ ሆዳችን ባር ባር ያለበትና ተሰደን እንደምንሄድ ስለተሰማኝ ሰውዬውን ማዜሙ ይቅር አልኩት፡፡

አየር ማረፊያ ስንደርስ በጣም ብዙ ሰው ሊሸኘን ተኮልኩሎ አገኘን፡፡ ፓስፖርቴ በውጭ ጉዳይ ሠራተኛ እጅ ስለነበር በመሄጃዬ ቀን ጠዋት ቤቴ ድረስ አምጥቶ የሚሰጠኝ ወይም ሚኒስቴሩ ለመደበው ሸኚ የፕሮቶኮል ክፍል ሠራተኛ የሚያስረክብ መስሎኝ ነበር፡፡ ቀኑ እሁድ ስለነበር ፓስፖርቱን የያዘውን ሠራተኛ ማግኘት ሳይቻል ቀረ፡፡ ጉዟችን ተሰናክሎ ወደቤታችን መመለስ የግድ ሆነ፡፡ ከለንደን ኦታዋ የአየር በረራ የነበረው በሳምንት አንድ ቀን ብቻ ስለነበር ጉዟችንን በአንድ ሳምንት አራዘምነው፡፡ ሰኞ ቢሮዎች ሲከፈቱ ስናጠያይቅ ሠራተኛው ፓስፖርቱን በጠረጴዛው ኪስ ውስጥ ቆልፎበት ከከተማ ወጥቶ ሄዶ እንደነበር ደረስንበት፡፡

ፕሬዚዳንቱን ለማነጋገር እንደገና ቀጠሮ ጠየቅሁና ቀጠሮ ተሰጥቶኝ ሄድኩ፡፡ ቢሮው ገብቼ ሰላምታ ተለዋውጠን ገና ከመቀመጤ “ሳትሰናበተኝ ሄደሃል ተብሎ ተነግሮኝ ስለነበር እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? ብዬ ገርሞኝ ነበር” አለኝ፡፡ ታነጋግረኛለህ በተባለው ዕለት ቀኑን ሙሉ ከቤት ሳልወጣ ስልክ ስጠባበቅ ነው የዋልኩት አልኩት፡፡ ለኔ የተነገረኝ ስልክ ደውለው እንዳጡህ ነው አለኝ፡፡

መሰናበት ሲባል በመሠረቱ ከርእሰ ብሔሩ መመሪያና ምክር መቀበል ማለት ነው፡፡ አንድ ሰዓት የፈጀ ውይይት አደረግን፡፡ ዋናው የመነጋገሪያችን ርእስ የነበረው የአገራችንን አንድነት ስለማስከበር ነበር፡፡ ኮምዩኒዝም በመዳከሙ ጊዜው ያነሳቸው አሜሪካኖች ፊታቸውን ወደአረቦችና አክራሪ እስላሞች ማዞራቸው ስለማይቀር የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እጃቸውን የሚሰበስቡበት ወቅት የተቃረበ ስለሚመስል ካርዳችንን በደንብ መጫወት መቻል ይኖርብናል እንዳልኩት አስታውሳለሁ፡፡

ባላጋራዎቼ ናቸው ከምላቸው ባለሥልጣኖች አንዱ ቤቴ ይደውልና ቢሮው ብቅ እንድል ይጠይቀኝና እሄዳለሁ፡፡ አንዳንድ ባለሥልጣኖች አምባሳደር

ተብዬ ያለሥራ በቤቴ እንድቀመጥ አሲረው እንደነበር፤ እሱ ባደረገው ጥረት ጭምር እንድመደብ እንደተወሰነ፣ ሁሉም በተመኘው በካናዳ የተመደብኩት በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አሳሳቢነት እንደሆነ ነገረኝ። ውስጠ አዋቂ እስካላረጋገጠልኝ ድረስ ሰውዬው ስለራሱ ጥረት የነገረኝን የምቀበልበት ወይም የማምንበት ምክንያት የለም። እንዲያውም፣ አንድና አንድ ሁለት ብዬ በደረስኩበት መደመደሚያ መሠረት ሰውዬው ያለሥራ እንድቀመጥ ከዶለቱት ውስጥ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለኝ። መሄዴ ቁርጥ መሆኑን ሲያውቅ ግን በወዳጅነት እንድመዘግበው ፈልጎ የተጠጋኝ መስሎ ታየኝ።

የፓስፖርቴ መጥፋትና መንግሥቱ ሊያነጋግረኝ ፈልጎ ልናገኘው አልቻልንም ተብሎ መነገሩ ወዳጅ መሳዩ ባላጋራዬ ከአገር እንዳልወጣ ዱለታ ነበር ብሎ ከነገረኝ ጋር የተያያዘ ሆኖ አገኘሁት። መንግሥቱን ሳላገኘው ብሄድ ኖሮ ይናደድና ተመልሶ ይምጣ ሊል ይችል ነበር። የዱለታው ተዋናዮች በኔ ስፍራ ተተክቶ የሚሄድ ሰው አዘጋጅተው ነበር ቢባል አይገርመኝም።

ለንደን አንድ ሌሊት አሳልፈን በማግሥቱ ወደ ኦታዋ ለመብረር ወደ አውሮፕላን መሣፈሪያው ስንገባ የደሕንነት ሠራተኛ በእጄ ያንጠለጠልኩትን ትራንዚስተር ራዲዮ ከመያዣው አውጥቼ እንዳሳየው ይጠይቀኛል። መያዣውን ለመክፈት ሞክሬ ሳይሳካልኝ ይቀራል። ራድዮው ያንተ ከሆነ እንዴት መክፈት አቃተህ? ብሎ ይጠይቀኛል። ዐይ፣ የኔ አይደለም፤ ሰው አድርስልኝ ብሎኝ ነው እለዋለሁ። ስልክ ደወለ። ፖሊሶች ከመቅጽበት በብዛት ፈሰሱና ዙሪያችንን ከበቡን። ከጥቂት ዓመታት በፊት በራዲዮ ውስጥ የተቀበረ ቦምብ አየር ላይ ፈንድቶ ከሦስት መቶ ሰዎች በላይ ሕይወታቸው አልፎ ስለነበር ፖሊሶቹ ያሰፈሰፉት ወንጀል ሊሠራበት የተዘጋጀ ሌላ ራዲዮ ያገኙ መስሏቸው ነው። ሬዲዮኑ ከማን፣ ለማን እንደተላከ ጠየቁኝ።

ለውዝግብ የዳረገኝ ራዲዮ ፕሬዚዳንቱን ለመሰናበት ቢሮው የሄድኩ እለት ልዩ ረዳቱ መንግሥቱ ገመቹ ለባለቤቱ ለጣይቱ እንዳደርስለት ያስረከበኝ ነበር፡፡

ፖሊሶቹ እንደከበቡኝ አንድ ሰው ጠጋ ይልና ጤና ይስጥልኝ ይለኛል፡፡ በለንደን የኤምባሲያችን ሠራተኛ መሆኑንና እዚያ የተገኘው ጣይቱን ለመሸኘት እንደሆነ ነገረኝ፡፡

ጣይቱ የኔ ጸሓፊ ለመሆን ወደ ኦታዋ ተመድባ መሄዷ ነው፡፡ ከኛ ጥቂት ቀናት ቀደም ብላ ለንደን ደርሳ ኤምባሲው ሲንከባከባት ሰንብቷል፡፡

ካናዳ መመደቤን እንዳወቅሁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ተስፋዬ ዲንቃን ለማነጋገር ፈልጌ ላነጋግረው የቻልኩት ቢያንስ ዐሥራ አምስት ቀኖች ጠብቄ ነው፡፡ ሚኒስትሩን ሳገኘው ዋና ጉዳይ አድርጎ ያነሳበኝ ስለጣይቱ ነበር፡፡ ሴትዮዋ ከባሏ ርቃ፣ ልጆቻቸውን ይዛ ስለምትሄድና ባለቤቷም የሥራ ውጥረት የሚበዛበትና ጤንነቱ ያልተሟላ ስለሆነ በደንብ አድርጌ እንድይዛት አደራ አለኝ፡፡ ሥራዬን ወይም ተልእኮዬን አስመልክቶ ፋይዳ ያለው ነጥብ ማንሳቱን አላስታውስም፡፡ ዐሥራ አምስት ቀን ሙሉ ያስጠበቀኝ ስለግለሰብ ጉዳይ ሊነግረኝ ነበር? ያገር ጉዳይ ተረሳ? ነገሩ ሁሉ በእከከኝ ልከክህ አለቀለት ማለት ነው? አልኩና ታዝቤና ተስፋ ቆርጬ ከቢሮው ወጣሁ፡፡

ጣይቱም ብትሆን ለኔ ጸሓፊ ሆና መመደቧንና እኔ እዚያው አዲስ አበባ አጠገቧ መሆኔን እያወቀች ታደሰን ልተዋወቀው ሳትል ወደ ለንደን አመራች፡፡ በሥልጣን ቁንጮ ላይ ከተቀመጡ ሰዎች ጋር ስለተጋባችና ስለተወዳጀች ታደሰ አንሶ ታያት፡፡

ወደ ኦታዋ በለንደን አድርጌ እንደማልፍ እዚያ ላለው ኤምባሲያችን እንዲያስታውቅና ተቀብሎም እንዲያሸጋግረኝ ሚኒስቴሩ መልዕክት እንዲያስተላልፍልኝ ከአዲስ አበባ ከመነሳቴ በፊት በጊዜ አሳስቤ ነበር፡፡

ለንደን ስንገባ ማንም አልተቀበለንም፤ ቪዛ የላችሁም ተብለን ወደ እንግሊዝ አገር መግባት እንደማንችል ተነገረን፡፡ ከአዲስ አበባ ስንነሳ ተነግሮን የነበረው ትራንዚት መንገደኞች ስለሆንን ቪዛ እንደማያስፈልገን ነው፡፡ ከአንድ ሰዓት በላይ አስቀምጠው ቪዛውን በልዩ አስተያየት ሰጠናችሁ ብለው ለቀቁን፡፡ ስለ ቪዛ ጉዳይ አጣርቶ አስፈላጊውን የመፈጸም ኃላፊነት የውጭ ጉዳይ ፕሮቶኮል መሆን ነበረበት እላለሁ፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርም ሆነ ለንደን ያለው ኤምባሲ ጉዳያችን ብለው የተከታተሉት የጸሓፊዋን እንጂ የአምባሳደሩን ጉዳይ አልነበረም፡፡ ስለሆነም፣ በውጭ አገር የኢትዮጵያ አምባሳደር ዕጣው ውርደት ሆነ፡፡

የለንደን ፖሊሶች የኢትዮጵያን አምባሳደርና ቤተሰቡን ከበው እንደወንጀለኛ ሲያዋክቡ የራዲዮው ባለቤት ወይዘሮ ጣይቱ በክብር ታጅባ አውሮፕላን ውስጥ ገብታ ተቀምጣለች፡፡ ፖሊሶቹ የራዲዮው ምርመራ ሳይጠናቀቅ መሄድ አትችልም የሚል አቋም ወሰዱ፡፡ ይህ ማለት አንድ ሳምንት ሙሉ ለንደን መቆየት ግድ ሊሆን ነው፤ ያልተቀበለኝን ኤምባሲ ሄጄ ላይ ነው፤ ስለጉዞዬ መሰናክል ለካናዳ ባለሥልጣኖችና እዚያ ለሚገኘው ኤምባሲያችን ለሁለተኛ ጊዜ እንዲያውቁት ሊደረግና ፕሮግራማቸውን ልናበላሽ ነው ብዬ ሐሳብ ገባኝ፡፡ ስለሆነም፣ አውሮፕላኑ ሳይዘን እንዳይሄድ አበክሬ አስገነዘብኩ፡፡ የኤምባሲው ሠራተኛም በመሀል ገብቶ ስለራዲዮው ፍተሻ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሙሉ ኃላፊነት እንደሚወስድ ለፖሊሶቹ አረጋገጠላቸውና እኛ ጉዟችንን ብንቀጥል የሚሻል መሆኑን አሳሰባቸው፡፡ አውሮፕላኑም እንዳይነሳ ወይም እንዲጠብቀን ተነገረው፡፡ ራዲዮው ወደኋላ ቀረ፤ እኛም ወደ ኦታዋችን አመራን፡፡

በኦታዋ የኢትዮጵያ ኤምባሲ የተከፈተው እአአ በ1968 ነበር፡፡ የበጀት እጥረት አጋጠመ ተብሎ አንድ ዓመት ያህል ቆይቶ ተዘጋ፡፡ እርግጠኛው የተዘጋበት ምክንያት ግን ባለሥልጣኖች አምባሳደሩን ዳዊት አብዱን አይወዷቸው ስለነበር እሳቸውን ለመጉዳት ወይም ለማናደድ ተብሎ ነው ይባላል፡፡ እንደገና የተከፈተው ከሃያ አንድ ዓመት በኋላ እአአ በ1989 ነው፡፡

አምባሳደሩ መቶ አለቃ ጥበቡ ሺፈራው ጥቂት ወሮች ከሠራ በኋላ ይታመምና ወደ አገር እንዲመለስ ሲደረግ በቦታው እኔ ተመደብኩ፡፡

አዲስ አበባ ሆኜ ስለካናዳ ካገኘኋቸው መረጃዎች አንዱ በኦታዋ ከተማ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ቁጥር 200 ገደማ እንደነበር ነው፡፡ ከዐሥራ አምስት ዓመት በኋላ ቁጥሩ ከ3000 እስከ 5000 እንደሆነ ይገመታል፡፡

ኤምባሲው ኬንትና አልበርት መንገዶች መጋጠሚያ ላይ ሁለተኛው ፎቅ ላይ፣ መኖሪያችን ደግሞ ከኦታዋ ወንዝ ማዶ በክዌቤክ ግዛት ውስጥ ኤልመር ነበር፡፡

የባለቤቴን ታላቅ እህት የአሳመረችና የጓደኛዬን የስሜን ልጅ ግሩምን ካናዳ ከኛ ጋር ይዘነው የገባነው በቱሪስት ቪዛ ስለነበር ከአገር ወጥቶ የተማሪ ቪዛ በፓስፖርቱ ላይ ተመትቶለት ካልተመለሰ በቀር ትምህርት ቤት ሊገባ ወይም የመኖሪያ ፈቃድ ሊያገኝ አይችልም ተብሎ ተነገረን፡፡ ስለሆነም፣ ኒውዮርክ የሚገኘው የካናዳ የቆንሲል ጽሕፈት ቤት ቪዛ እንዲመታለት ይዤው ሄድኩ፡፡ ይህ የሆነው ኦታዋ በገባን በሁለተኛው ወር ነበር፡፡ ወቅቱ የተባበሩት መንግሥታት አመታዊ ጉባኤ የሚደረግበት ስለነበር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ተስፋዬ ዲንቃን አግኝቼው ወደ ኒውዮርክ ለምን እንደመጣሁ ገለጽኩለት፡፡

የመስቀል ዕለት ቀድሞ በኖርኩበት በኢንተርናሽናል ሃውስ ፓርክ ውስጥ በአካባቢው የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተሰባስበው በዓሉን እንደሚያከብሩ ሰምቼ ስለነበር እዚያው ይኖሩ ከነበሩት ጓደኞቼ ጋር ሆነን ወደ ተጠቀሰው ስፍራ ሄድን፡፡ ብዙ የማውቀው ሰው አገኘሁና ደስ አለኝ፡፡

ኦታዋ እንደተመለስን ከአዲስ አበባ ከማንጠብቃቸው ሰዎች ጭምር ስልክ በብዛት ይደወልልናል፡፡ ከባለቤቴ ጋር እገሌ ዛሬ ምን ታይቶት ነው የደወለው? እንባባላለን፡፡ ከደወሉልን መካከል ወደጄ የአየር መንገድ ምክትል ኃላፊ ወልደገብርኤልም ይገኝበት ነበር፡፡ ወልደገብርኤል ከሁለት

ሳምንት በፊት ከባለቤቱ ጋር መኖሪያችን ድረስ መጥተው አብረን ውለን አድረናል፡፡

ስልኮቹ የተደወሉበት ምክንያት ብዙም ሳይውል ሳያድር ደረስኩበት፡፡ የአየር መንገድ ኃላፊ ካፕቴን መሐመድ ደክሞኛልና ከሥራ አሰናብቱኝ ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ኃይሉ ይመኑን ይጠይቃል፡፡ ካፕቴኑ በሥራው ምስጉንና ወላዋይነት የማያጠቃው ሥራ አስኪያጅ ነበር፡፡ ከኔ ጋር መጀመሪያ የተዋወቅነው በ1969 በብር ለውጥ ሳቢያ ነበር፡፡ ያኔ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ጄኔራል ታፈሰ ነበሩ፡፡ ካፕቴን መሐመድ ያንድ ሥራ ዘርፍ ኃላፊ ነበር፡፡ የብር ኖቶችን ከለንደን ወደ አዲስ አበባ ስለማመላለስ ከአየር መንገድ ኃላፊዎች ጋር ተነጋግረን እኛ በጠየቅነው መሠረት ለመፈጸም አስቸጋሪ እንደሚሆን ሲገልጹልን ያወጣነው የብር ኖቶች ለውጥ ፕሮግራም ተዛንፎ ችግር ውስጥ ልንገባ ነው ብለን ባንክን ወክለን በስብሰባው ላይ የተገኘነው ተረበሽን፡፡ ካፕቴን መሐመድ ይነሳና ባንክ በጠየቀው መሠረት መፈጸም የማይቻልበት ምክንያት የለም፤ የሚጠይቀው ጠንክሮ መሥራትና ጥረታችንን ማስተባበር ብቻ ነው ብሎ ተናገረ፡፡ እሱ እንደሚቻል ሲናገር ሌሎች አይቻልም ለማለት ሳይደፍሩ ቀሩ፣ ያ ቀድሞም የምንኮራበት አየር መንገድ የጠበቅንበትን ብሔራዊ ግዴታውን ተወጣና እንጀታችንን አራሰው፡፡ በዚህም የተነሳ ካፒቴኑ የአየር መንገድ ኃላፊ ሆኖ ሲሾም በጣም ደስ አለኝ፡፡

ካፕቴኑ አሰናብቱኝ ብሎ ሲጠይቅ ኃይሉ ይበሳጭና “ሁላችሁም ለመሄድ ከፈለጋችሁ በየመስኩ ያለውን ሥራ ማን ሊሠራው ነው? ትናንት የካናዳ አምባሳደር ብለን የላክነው ሰው ከአገር እግሩን ከማውጣቱ የሥራ ገበታውን ጥሎ ጠፋ” ይለዋል፡፡ ካፕቴን የሚናገረው ጠፍቶት፣ እሺ ጉዳዬን በይደር እንለፈው፣ ሌላ ጊዜ እንነጋገርበታለን ይልና ወደ ቢሮው ይመለሳል፡፡ ቢሮ ከመግባቱ ወልደገብርኤልን ባስቸኳይ ብቅ በል ይለዋል፡፡ ወልዴም ምን ተፈጠረ? ቢለው፣ አንተ፣ ያ ወደ ካናዳ የተላከው ጓደኛህ ጠፋ እንዴ? ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ የቱ ጓደኛዬ? ቢለው አምባሳደሩ ነዋ ይለዋል፡፡ ወልዴም፣

ሊሆን አይችልም፤ የዛሬ ሁለት ሳምንት አብረን ነበርን፤ ከሁኔታው ጠፍቶ የሚሄድ ሰው አይመስልም ነበር ይለዋል:: ወልዴ ለኛ ስልክ የደወለው ያኔ ነው:: አለመጥፋታችንን አረጋገጠ፤ ለካፕቴንም ነገረው::

እላይ እንደገለጽኩት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ተስፋዬ ዲንቃን ኒውዮርክ አግኝቼዋሁ:: አምባሳደሮች ተጠሪነታቸው ለርእሰ ብሔሩ ነው ብለው እራሳቸውን ቢያሞካሹም የቅርብ አለቃቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ነው:: እነኃይሉ ይመኑ በወሬኛ ተማምነው ከነሱ የማይጠበቅ አሉባልታ ከማናፈስ ስልክ ደውለው ተስፋዬን ቢጠይቁ ኖሮ ትክክለኛውን ሁኔታ ይነግራቸው ነበር:: መሐመድ፣ ወልደገብርኤል፣ እኔም ጭምር እነኃይሉን በጣም ታዘብናቸው::

የአሉባልታው ምንጭ ከየት ነው? የሚለው የኔ ግምት እንደሚከተለው ነው:: ወደ ውጭ ንግድ ሚኒስቴር እንደሄድኩ በኃላፊነት ላይ የተመደቡትን ሰዎች ችሎታና ብቃት ሳጠና አንዳንዶቹ በወሬ አነብናቢነት ግዙፎቹ በሚጨበጥ የሥራ ውጤት አኳያ ግን ድንኮች ሆነው አገኛ ቸዋለሁ:: ስለሆነም፣ ሥራና ሠራተኛ እንዲገናኙ አስፈላጊውን እርምጃ ወሰድኩ:: ሽግሽጉ ጥቅሜን ጎድቷል ያለ አንድ ሠራተኛ በወቅቱ የገንዘብ ሚኒስትር፣ ከኔም በፊት የውጭ ንግድ ሚኒስትር ወደነበረው ወሌ ዘንድ ይሄድና የአንተ ሰው በመሆኔ አዲሱ ሚኒስትር የሚገባኝን ከለከለኝ ይለዋል:: ወሌም ይደውልልኝና እገሌን አንድ ከፍተኛ ኃላፊነት ለሚጠየቅ ስፍራ ስለምንፈልገው ብትለቅልኝ ይለኛል:: ለአንድ አፍታም ሳላመነታ እሺ አልኩት:: ይህ ሰው አዲስ አበባ በመንገድ ስንተያይ እንዳላየኝ ማለፍ የመረጠ ሰው ነበር:: የመስቀል ዕለት ኒውዮርክ ኢንተርናሽናል ሃውስ ፓርክ ውስጥ ተያይተናል፣ ነገር ግን ሰላምታ አልተለዋወጥንም:: እኔ የምጠረጥረው ሰውዬው እዚያ ሲያየኝ ጠፍቼ አሜሪካ የገባሁ መስሎት ሳይሆን አይቀርም:: አዲስ አበባ እንደተመለሰ ለእንባ ጠባቂው ለወሌ ነገረው፣ ወሌ ደግሞ አሉባልታውን ለእነኃይሉ አስተላለፈው የሚል ግምት

አለኝ:: ታደሰ ሥራውን ጥሎ ጠፋ የሚለው ወሬ ለረጅም ጊዜ ተናፈሰ:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠፍቷል ካለ ሌላው እንዴት አልጠፋም ይበል?

ተቀማጭነቱ ኦታዋ የሆነው የኢትዮጵያ አምባሳደር ውክልናው ለሜክሲኮም ጭምር ነው:: ኒውዮርክ በታየሁ አምስተኛው ወር በሜክሲኮ ከተማ ተገኝቼ የአምባሳደርነት የሹመት ደብዳቤ ለአገሩ ፕሬዚዳንት ማቅረቤ በኢትዮጵያ ዜና ማሰራጫዎች ተነገረ:: ከዚያ በኋላ የመጥፋቴ ወሬ ቀስ በቀስ እየከሰመ ሄደ፤ ብዙም ሳይቆይ የመንግሥት ህልውና አጠያያቂ የሚሆንበት ደረጃ ላይ ስለተደረሰ የታደሰ መጥፋት አለመጥፋት ማንም ጉዳዬ ነው የሚለው መሆኑ ቀረ::

ክስተቱ የታሪክን ሂደት ያንጸባርቃል:: የታሪክ መድረክ አንድ ነው፤ ተዋናዮቹ ግን ሳያሰልስ ይለዋወጣሉ:: ታደሰ፣ ወሌ፣ ኃይሉ፣ መርቆሬዎስ፣ ወልደማርያምና ገብረማርያም መድረኩን ለሌሎች አስረክበው አልፈዋል:: የሰው ትችትና ትኩረት በወቅቱ ሰዎች ላይ ነው:: ቢሆንም፣ ጊዜ የማይሽረው አንድ ሐቅ አለ፤ ተዋናዮች ከመድረኩ ቢወርዱም ድርጊታቸው ግን ለዘለዓለም ተቀርጾ ይቀራል:: ታዲያ የሁሉም ምኞትና ጸሎት በዚያች በምትሰጠን አጭር የተውኔት ጊዜ ስማችንን በደጎና የሚያስነሳ ተግባር አከናውነን እንድናልፍ መሆን ይኖርበታል፤ ነገር ግን ሰዎች ደካሞች ስለሆንን መድረክ ላይ ስንወጣ የሚጸናወተን በሽታ ስላለ እንረሳዋለን:: ስለሆነም፣ አብዛኛዎቻችን ከመቅጽበት በሚያልፍ ጊዜ ለዘለዓለም የማያልፍ ስም ተክለን ማለፍ ሳንችል እንቀራለን::

መንግሥት ተለውጦ አምባሳደርነቱ በቀረ በስምንተኛው ዓመት በአቢጃን ከተማ፣ ኮትዲቯር፣ በኩል ሳልፍ ወዳጄ ሀብቴ እቤቱ እራት ይጋብዘኛል:: ባለቤቱ ወይዘሮ የእውነትሰው ለጉብኘት ወደ ሌላ አገር ሄዳ ስለነበር ቤት ውስጥ ያለው ብቻውን መሆኑን፣ ነገር ግን ከአዲስ አበባ ለሥራ ጉዳይ የመጣ አንድ ወዳጁን በእራቱ ላይ እንዲገኝ እንደጋበዘው ይነግረኛል:: ከአዲስ አበባ የመጣ ሰው ማየት ናፍቆኝ ስለነበር ደስታውን አልችልም አልኩት:: በቀጠሯችን ሰዓት ቤቱ ስደርስ እላይ ከገለጽኩት ሰው ሳንወድ

ጊዜና ቦታ ግጥምጥም አደረገን:: ሁለታችንም ማመን አቃተን:: ስምምነት እንዳልነበረን ጋባዣችን እንዳያውቅብን ሁለታችንም ትልቅ ጥረት አደረግን:: ውጭ ንግድ ሚኒስቴር ውስጥ ስለነበሩ ሰዎች ነገረኝ አልኩትና የት የት እንዳሉ፣ የሞቱትንም ነገረኝ:: ከሰውዬው ጋር ስንለያይ፣ ሰው ከወዳጁም ሆነ ከጠላቱ ጋር የትና እንዴት እንደሚገናኝ አያውቅም ተባብለን ተለያየን:: ይህን ስንባባል ሀብቴ ሳይሰማ የቀረ አይመስለኝም፣ ነገር ግን የቋንቋችንን ውስጠ ምስጢር አልተረዳውም:: አጥብቆ የጠየቀ የእናቱን ሞት ይረዳል እንዲሉ ሀብቴ ምን ማለታችሁ? ብሎ ሊያወጣጣን ቢሞክር ኖሮ ምናልባት የውስጣችንን ገልጠን እናሳየውና እናሳዝነው ነበር:: ከዚያን ዕለት በኋላ ከሀብቴ ጋር በኦታዋ ከተማ ብዙ ጊዜ ተገናኝተናል፣ ነገር ግን ከሰውዬው ጋር ስለነበረን መጥፎ ግንኙነት ነግሬው አላውቅም:: በበኩሌ የነበረው አመለካከት ሰውዬው ወዳጁ ከሆነ እኔ ስለሰውዬው ያለኝን አመለካከት ለሀብቴ ገልጬለት በመካከላቸው የነበረውን ግንኙት የማበላሸት ወይም የመመረዝ መብት የለኝም የሚል ነበር:: ቢሆንም፣ ይህን መጽሐፍ እንዳያነብ እፈልጋለሁ ማለቴ አይደለም!

በአምባሳደርነቴ ቀደምት ተልእኮዬ አድርጌ ይዤው የነበረው የኤርትራ የመገንጠል እንቅስቃሴ ቢሳካ ጠቃሚነቱ ለኤርትራ ተወላጆች ሳይሆን ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች እንደሚሆንና ለኢትዮጵያ ህልውናም አስጊ እንደሚሆን ማስገንዘብ ነበር:: በየቦታው እየዞርኩ የአገሪቱ አንድነት መጠበቅ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ገለጻ ሳደርግ አብዛኞዎቹ የምለውን አዳምጠው በትሕትና ይሸኙኛል:: አንድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን የተናገረኝ የብዙዎቹን አመለካከት የሚያጠቃልል ይመስለኛል:: «የምትለውን ተረድቼልሃለሁ፤ ትክክልም ይመስላል፤ ነገር ግን የመገንጠል ዓላማ የሚያራምዱት የኤርትራ ተወላጆች ቢያንስ ዐሥራ አምስት ዓመታት ቀድመዋችሁ በየቢሮው አንኳኩተው ገብተው የነሱን መስመር አስጨብጠዋል፤ አሁን ጉዳዩ ካለቀለት በኋላ የምታደርጉት ጥረት ጅብ ከሄደ በኋላ ውሻ ጮኸ እንደሚሉት ዓይነት ነው» አለኝ::

ሌላው መሠረታዊ ችግር የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያን መንግሥት ከኢትዮጵያ ለይቶ ማየት ያለመቻል ወይም ያለመፈለግ ነበር፡፡ ከ እስከ ሳይባል ሁሉም መንግሥቱና የሱ መንግሥት እንዲወድቁ ይፈልጋል፡፡ መንግሥት ይመጣል፣ መንግሥት ይሄዳል፤ ነገር ግን ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ጥቅም ግን መጠበቅ ይኖርባቸዋል፤ በተለይ የአገሪቱና የሕዝቧ አንድነት መጠበቅ ይኖርበታል፤ መከፋፈል ወደ ጥፋት እንጂ ወደልማት ጎዳና አያመራም፤ የጠላችሁትን መንግሥት የጎዳችሁ እየመሰላችሁ ተገንጣዮችንና አጋሮቻቸውን መደገፍ ኢትዮጵያንና የሕዝቧን ጥቅም መጻረር ነው ሲባሉ ይህን የምንሰማበት ጆሮ የለንም ይሉ ነበር፡፡

ኤምባሲውን ገጥሞት የነበረው ሌላ ችግር የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ እጥረት ነው፡፡ መንግሥት የመደበው በጀት ከደመወዝ ክፍያና መሠረታዊ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ከመሸፈን አያልፍም ነበር፡፡ የሌሎች አገሮች ኤምባሲዎች እንደሚያደርጉት ከቦታ ቦታ በመዘዋወርና ባለሥልጣኖችንና ዲፕሎማቶችን በመጋበዝ ማግባባት ወይም ጠቃሚ መረጃ መሰብሰብ የሚቻልበት መንገድ አልነበረም፡፡ ለምሳሌ፣ የአፍሪቃ አምባሳደሮች በየመኖሪያ ቤታቸው እየተገባበዙ መረጃ ይለዋወጣሉ፤ ሚስቶቻቸውም ማኅበር አቋቁመው ይገባበዛሉ፣ የባሎቻቸው ተልእኮ የተሳካ እንዲሆን በማሰብ ሐሳብ ለሐሳብ ይለዋወጣሉ፤ ባለሥልጣኖችን እየጋበዙ ስለአገሮቻቸው ባሕል ለማስተማር ይጥራሉ፡፡

ተወደደም ተጠላ የአንድ ዲፕሎማት ሕይወት የሚሽከረከረው መብልና መጠጥ ዙርያ ነው፡፡ ሥራው  መስሎና አስመስሎ መዋልንና ማምሸትን ይጨምራል፡፡ ሁሉም የአገሩን ተደማጭነት ከፍ ከፍ ለማድረግ ይጥራል፡፡ መታየትና መደመጥ የማይፈልግ አገር ሌላ አገር ሄዶ ኤምባሲ እንዲያቋቁም አይጠበቅበትም፡፡ አድርጎትም ከሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ማመዘኑ የማይቀር ነው፡፡ አንድ ዲፕሎማት በተመደበበት አገር በአስፈላጊው ስፍራ ሁሉ እየተገኘ የሕዝብን አመለካከት አቅጣጫ የሚያስይዙትን፣ እንዲሁም የፖሊሲ ቀያሾችን ማግኘት፣ ሊታወቁለት የሚፈልጋቸውን ነጥቦች ማሳወቅ

ወይም ማሰራጨት፣ ሌላው የሚለውን መስማት በጣም አስፈላጊ ነው:: ዲፕሎማት ማለት በሕግ የተፈቀደለት ሰላይ ነው:: ጆሮውን በቢሮው ውስጥ ቆልፎ እንዲያስቀምጠው አይጠበቅበትም:: ለአገሩ ጠቃሚ መረጃ ለመላክ በይፋ የሚለፈፈውን ብቻ ሳይሆን በሹክሹክታ የሚነገሩትን ሁሉ ቃርሞ ጠቃሚ የሚመስሉትን ለአገሩ መንግሥት እንዲያስተላልፍ ይጠበቅበታል:: በቢሮው ውስጥ ተቀምጦ የሚሠራው ሥራ ውጤቱ ውስን ነው:: ወታደር ካልበላ አይዋጋም እንደሚባለው ሁሉ አንድ ዲፕሎማት በተመደበበት አገር የሚገኙትን የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ዲፕሎማቶች ላንቃቸውን በመጠጥ ሲያርስና ሆዳቸውን ሲሞላው በጭንቅላቶቻቸው ውስጥ የያዟቸው ፋይሎች ይከፈታሉ፤ አንደበታቸውም ይሰላል:: ኤምባሲ ከፍቶ የግብዣ በጀት መዘጋት ማለት ለሾፌር ቆንጆ አውቶሞቢል አስረክቦ ነዳጅ እንደመከልከል ዓይነት ነው::

ኦታዋ በሐምሌ መጀመሪያ ላይ ገብቼ የዘውድ ሥርዓት ግርሰሳ መታሰቢያ መስከረም ሁለትን ለማክበር በነሐሴ ዝግጅት ጀመርን:: ግብዣው የሚደረገው ብሔራዊውን በዓል ለማክበር ብቻ ሳይሆን በየቦታው ለተጋበዝንበት በምላሹ ወይም በተራችን ማኅበር የምናወጣበት ዕለትም አድርገን ስላየነው ዝግጁቱን በጽሞና ተያይዘነው ነበር:: ገንዘብ ስለሌለ የግብዣ ፕሮግራማችሁን ሰርዙ የሚል መመሪያ ከአዲስ አበባ መጣና የምንገባበት ጠፋብን:: ያዘጋጀናቸው የጥሪ ወረቀቶች ተሸርክተው ተጣሉ:: የሰውን በልተን ጠጥተን የኛ ተራ ሲደርስ እንዴት እፍርታም ሆነን እንገኛለን? ብለን በጣም ተሸማቀቅን:: የግብዣ ጥሪ ሲደርሰን ቁስላችን እየተነካብን መታመም ሆነ:: በግብዣ ላይ ለመገኘት መድፈር አቃተን:: ተገኝተንም ከሆነ ሰው ሁሉ እየተጠቃቀሰ እነዚያ እፍርታሞች መጡ የሚለን ስለሚመስለን ድንጉጦች ሆንን:: የአገራችንን ክብር ከፍ የምናደርግ ዲፕሎማቶች ሳንሆን ከረሃብ አገር የመጣን አገር አዋራጅ ቀላዋጮች ተደረግን አልን:: ጉዳዩ ወይም ችግሩ በስፋት ሲታይ አገራችንን ከድህነት የምናላቅቃት መቼ ይሆን? ብለን በጽሞና እንድናስባት ተጨማሪ ምክንያት አገኘን:: ለራሱ ክብር ያለው ሕዝብ ውርደትን ወደ ክብር የመለወጥ ችሎታ

ስላለው መጪውን ዓመታት በተስፋ እንጠባበቃለን ብለን እራሳችንን አታለልን።

ከብዙ ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያድለው የመንገደኞች ቦርሳ ነበር። መልኩ አረንጓዴ ሲሆን በብጫ ይሁን በቀይ ቀለም Ethiopian የሚል ጽሑፍ ነበረበት። ኢትዮጵያዊ መንገደኛ ቦርሳውን በትከሻው አንጠልጥሎ መዞር ይወድ ስለነበር "ኢትዮጵያዊ ነኝ፣ ዕዩኝ" ለማለት አደባባይ የወጣ ያስመስልበት ነበር። ይኩራራ የነበረው በባዶ ነው? ወይስ በተጨባጭ? የሚለውን ወደጎን እንተወው። ትልቁ የ1965 ድርቅ ይፋ ከሆነ በኋላ ቦርሲት ወደ ኋላ ቅሪ ትባላለች፤ ቀስ በቀስም ጥፊ ተባለች። በኢትዮጵያዊነታችን ስለምናፍር ማንነታችን እንዲታወቅብን አንፈልግም እንደማለት ነበር። በተመሳሳይ፣ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ለተጋበዝነው መልሰን መጋበዝ ሲያቅተን ከኔ ቢጤዎች አገር የመጣን የኔ ቢጤዎች እንጂ ዲፕሎማቶች አይደለንም ብለን እራሳችንን በልባችን ሳንክድ አልቀረንም። የአቤ ጉበኛው አልወለድም ፍጡር መፈጠሬ ለፍዳና ስቃይ ከሆነ ማሕፀን ውስጥ ልቅር እንዳለው ሁሉ እኛም ካናዳ የተመደብን የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እጃችን አጥሮ አገር ከምናሰድብ አገር ውስጥ እጅና እግራችንን ሰብስበን ብንቀመጥ ይሻል ነበር ብያለሁ።

ለብሔራዊ በዓል ብቻ ሳይሆን ለሌላም ዓይነት መስተንግዶ ለኤምባሲው የተመደበለት የመስተንግዶ በጀት ስላልነበረው ዲፕሎማቶቹ የምንኖረው ድምፅ አጥፍተንና ተደብቀን ነበር ለማለት ይቻላል።

በየዓመቱ መንግሥት በሚያደርገው የበጀት ረቂቅ ውይይት ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በጀት አንሶናልና ይጨመርልን እያሉ ሲወተውቱ መስማት የተለመደ ነበር። ዲፕሎማቶች ውጭ ሄደው ኑሯቸውን ያደላደሉ አንሷቸው ደመወዝና አላዋንስ እንዲጨመርላቸውና የሥራ ማስኬጃ ገንዘብ ከፍ እንዲደረግላቸው ደፍረው ጠየቁ እየተባሉ ውስጥ ውስጡን ይብጠለጠሉ ነበር። በልክስክስ ወይም ሕገወጥ ድርጊት ውስጥ

የተሰማሩትን አንዳንዶቹን ትተን የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች የተደላደለ ኑሮ ይኖራሉ የሚለው እምነት ከእውነት የራቀ ስለመሆኑ ምስክር ነኝ፡፡

ብሔራዊ ዕቅድ ሲወጠን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችና ኮሚሽኖች የገንዘብ ጥያቄዎቻቸውን ያቀርቡ የነበረው ለተግባራዊነታቸው በአጫቸው ፕሮጀክቶች አስደግፈው ሲሆን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ግን ከሥራ ጠባዩ የተነሳ ዝርዝር የሥራ እቅድ እንዲያቀርብ አይጠበቅበትም ነበር፡፡ ጎሹ ወልዴ የተጠቀሰው ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ኃላፊ ሆኖ የጠየቀው ገንዘብ ባለመመደቡ ሲበሳጭ እናያለን፡፡ የቡና እረፍት ሲደረግ፣ ሌሎቹ እንደሚያደርጉት አንተም ይህን አደርጋለሁ፣ ያንን እፈጥራለሁ፣ እንዲሁም አለም ለኢትዮጵያ የሚሰግድበትን ትልም አውጥቻለሁና ለተግባራዊነቱ ይህን ያህል ገንዘብ ይመደብልኝ ብለህ አቀራረብህን ብታስተካክል ይሻልሃል እንለዋለን፡፡ ሥራችሁ ጭብጥነት የለውም ለማለት እንደፈለግንም ገብቶታል፡፡ የመለሰልንም፣ እውነታችሁን ነው፤ ብጠየቅ ኖሮ ወዳጅ የሚበራከትበትን፣ እንዲሁም የጠላት ቁጥር የሚመናመንበትን እቅድ አቀርብ ነበር በማለት ነው፡፡ ጎሹ ይህን የተናገረው ኢትዮጵያ በሶቪየቶች ጉያ ተወሽቃ ምዕራቡ ዓለምን ለምኔ ባለችበት ወቅት ስለነበር እንደ ጎሹ ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ምን ማድረግ እንዳለበት እንደሚያውቅ ሊነግረን ፍልጎ ነው፡፡ ገባን፤ ተግባባን፡፡ ጎሹም ብዙ ሳይቆይ የተቀመጠበትን ወንበር የፈለጉት እነአሻጥሬና እነጎንትሌ ተቀባብለው አዳከሙኝ ብሎ አገሩን ጥሎላቸው ኮበለለ፡፡

ብዙ ኤምባሲዎችን ፈልፍሎ ሁሉንም ከማስራብ አንዳንዶቹን ዘግቶ የተቀሩትን ተንከባክቦ መያዝ ሳይሻል አይቀርም የምንል ጥቂት አልነበርንም፡፡

ከካናዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባለሥልጣኖች ጋር አልፎ አልፎ ውይይት እናካሄድ ነበር፡፡ የመንግሥቱ መንግሥት ሊወድቅ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ ከአፍሪቃ ጉዳይ ኃላፊያቸው ጋር ሁለት ጊዜ ተነጋግረናል፡፡ ኢትዮጵያን አስመልክቶ ካናዳ የምትከተለው ፖሊሲ ከአሜሪካኖቹ ጋር

ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሁለቱ አገሮች የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች በየጊዜው እየተገናኙ ውይይት እንደሚያካሄዱ ነግረውኛል። ይህን የነገሩኝ ሳልጠይቃቸው ነበር።

በመጀመሪያው ስብሰባ የሰነዘሩት ሐሳብ፣ የአሰብ ወደብ ወደ ኢትዮጵያ ቀርቶ ኤርትራ እንድትገነጠል መፍቀድ የሚል ነበር። የመገንጠል ጥያቄ ቦታ እንደሌለው፣ አገሪቱን ለማስገንጠል ማንም ሥልጣን ወይም መብት እንደሌለው፣ የሚሻለው ለሁሉም ተስማሚ የሆነ የፖለቲካ መፍትሔ በመፈለጉ ላይ ማተኮር እንደሆነ ያለንን አቋም ገልጬላቸው ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ።

በሁለተኛው ስብሰባ የመፍትሔ ሐሳብ ነው ተብሎ የቀረበው፣ የኢትዮጵያ ችግር መንግሥቱ ኃይለማርያም ስለሆነ ሥልጣኑን ለቆ ቢሄድ ኢትዮጵያን የገጠሟት የፖለቲካም ሆነ አንድነትዋን የማስጠበቅ ችግሮች ይከስማሉ የሚል ነበር። ይህን ስሰማ በአንድ በኩል በጣም ደስ አለኝ በሌላ በኩል ጥርጣሬ አደረብኝ። ችግሩ መንግሥቱ ነው ብለው ካመኑ፣ መንግሥቱ ደግሞ ለማሳመን እንደሞከረው እሱ የቆመው ብቻ ሳይሆን የተፈጠረው የኢትዮጵያን አንድነት ለማረጋገጥ ነው ስለሚል ሥልጣን ልቀቅ ቢሉት እንትን አለቀ ቢሉ እንትን ቀለለ እንዲሉ ከመተባበር ወደኋላ አይልም ብዬ ገመትኩ። በሌላ በኩል ግን ካናዳውያንም ሆኑ አሜሪካኖች እርግጠኛው ፍላጎታቸው በየግንባሩ የተሰማራውን ሰራዊት ያለመሪ አስቀርተው ትጥቁን ለማስፈታት ሲ አይ ኤ የጠነሰሰው ደባ ሳይሆን አይቀርም ብዬም ተጠራጠርኩ።

በሰጧቸው መልስ፣ "ሐሳቡ በጣም ጥሩ ነው፤ የአንድ ሰው መገለል ችግሩን የሚፈታው ከሆነ አስፈላጊው ሁሉ መደረግ ይኖርበታል፤ እኔ የኢትዮጵያ አምባሳደር ብቻ ሳልሆን አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊም ነኝ፤ ነገ አዲስ አበባ ሄጄ መንግሥቱን "ኢትዮጵያን የገጠማት አንድነትዋን የማስከበር ችግር ሊፈታ ነው፤ የሚጠይቀው ያንተ ከሥልጣን መነሳት ብቻ

ነው ብዬ ልነግረው ዝግጁ ነኝ፤ ግን አንድ ነገር ልጠይቃችሁ፣ መንግሥቱ ሥልጣኑን ለቆ ከሄደ በኋላ እናንተና በጠቅላላው የምዕራቡ ዓለም የኢትዮጵያን አንድነት እንደሚያስከብር ማረጋገጫ ለመስጠት ዝግጁ ነው?" አልኳቸው። የማነጋግራት የአፍሪቃ ጉዳይ ኃላፊያቸው ሴት ናት። የምጸት ሳቅ ሳቀችና በወንበርዋ ላይ ወደኋላ ተለጥጣ፣ ያልከውን ዋስትና ማንም ሊሰጥ አይችልም አለች። ለእቅጭ ጥያቄ እቅጭ መልስ። በልቤ ነጭ ሁሉ አፍረቃዊን ለማታለል ከመሞከር መቼም አይተኛም፣ የየዋሁና ደጉ አፍሪቃ ሕዝብ አምላክ ይፋረዳችሁ ብዬ አዝኜ ወደ ቢሮዬ ተመለስኩ።

ወያኔ አዲስ አበባ ከመግባቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ አገራችን ስላለችበት ሁኔታና ወደፊት ስለሚጠብቃት እድል የካናዳ የዜና ማሰራጫ ድርጅት ቃለመጠይቅ ሊያደርግልኝ ፈልጎ ቀጠሮ እንይዛለን። ቃለመጠይቁ የሚደረግበት ቀን ከመድረሱ በፊት ወያኔ አዲስ አበባ ይገባል። የዜናው ድርጅት ይደውልልኝና የቴክኒክ ችግር ስለገጠመን ለአንተ ቃለመጠይቁን ላለማድረግ ወስነናል ብለው አስታወቁኝ። እኔ የወደቀ መንግሥት ተጠሪ ስለሆንኩ ምክንያት ፈልገው ከሰልፍ አስወጡኝ እንጂ ፕሮግራሙ አልቀረም። ኢትዮጵያን ስለሚጠብቃት የወደፊት እድል ኤክስፐርት ሆኖ የቀረበው ደርግ ሲመሠረት የመርማሪ ኮሚሽን ዋና ጸሓፊ የነበረውና በኋላ ከድቶ የተገንጣዮች ጠበቃና ቃልአቀባይ የነበረው በረከት ሀብተስላሴ ነበር። መንግሥቱ አገር ጥሎ መሄዱ ምን የሚያስከትል ይመስልሃል? ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ ሲመልስ፣ በአበሻ ባሕል አንድ ሰራዊት መሪው ከተመታበት ወይም ጦር ሜዳ ጥሎ ከሸሸ ሰራዊቱ ተፈታ ማለት ስለሆነ የኢትዮጵያ ሰራዊት ሳይዋጋ መሣሪያውን ጥሎ ይበተናል አለ።

ካናዳና አሜሪካ ኢትዮጵያን አስመልክቶ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያቸውን እንደሚያስተባብሩና መንግሥቱ ኃይለማርያም ጥሎ እንዲሄድ ሁለቱም ስለመፈለጋቸው ተናግሬአለሁ። በረከት ያለውን ስሰማ የኢትዮጵያን እድል የወሰኑት ሁለቱ መንግሥታት ብቻቸውን ሳይሆኑ ከኢሳያስና ከመለስ ጋርም እየተመካከሩ እንደነበረ ለመገመት ልዩ እውቀት አያሻውም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ሰዎችን ቀድሞም አያምንም፣ ወደፊትም ማመን የለበትም:: የአገራችን ችግሮች አብዛኞቹ ምንጫቸው ከውጭ ነው:: የውስጥ ችግሮቻችንን ተወያይተን እንዳንፈታ ችግሩን የሚያውሰበስቡትና የሚያባብሱት የውጭ ኃይሎች ናቸው:: ይህን የሚያደርጉት ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን ደባ ደርሶበት እውነተኛ ጠላቶቹን ማሳፈር እስካልቻለ ድረስ ፍዳውን ሲያይ መኖሩ የማይቀር ነው::

ወያኔ በግንቦት አዲስ አበባ ገብቶ ሰኔ 3 በተጻፈ ደብዳቤ ከሰኔ 1 ጀምሮ የሥራ ዘመንህ ያበቃ ስለሆነ ሥራህን ለጉዳይ ፈጻሚው አስረክበህ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ እንድትመለስ የሚል ትእዛዝ ደረሰኝ:: በእጄ የነበሩትን መዛግብትና ገንዘብ አረካክቤ፣ ይህን ለማድረጌ ከጉዳይ ፈጻሚው ደረሰኝ ተረክቤ ኤምባሲውን ለቅቄ እንድወጣ በተባልኩበት ቀን ጥዬ ወጣሁ:: አብዛኛዎቹ የኤምባሲ ሠራተኞችም ተመሳሳይ እርምጃ ወሰዱ:: ከቤተሰቤ ጋር በዕለቱ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሄደን ወደ አገራችን መመለስ እንደማንፈልግ ገልጸን ካናዳ ውስጥ ለመኖር እንዲፈቀድልን ጠየቅን:: ፓስፖርቶቻችን ላይ “ተሰርዟል” የሚል ማኅተም አትመው ወደ ኢሚግሬሽን ቢሮ ላኩን::

የኢሚግሬሽን ቢሮ ለምን ወደ አገሬ ለመመለስ እንደማልፈልግ በጽሑፍ እንድገልጽ ጠየቀኝ:: ለዚህ የተሰጠኝ ጊዜ ከሃያ ደቂቃ የማይበልጥ ነበር:: ከሰጠኋቸው ምክንያቶች መካከል፣ የኢ ሰ ፓ ማእከላዊ ኮሚቴ አባልና በሚኒስትር ደረጃ የመንግሥት ባለሥልጣን ስለነበርኩ ወያኔ በሰጠው መግለጫ መሠረት የሕዝብ ጠላት ነህ ብሎ ሊያስረኝ እንደሚፈልግ፣ በአንድ ወቅት ወያኔ ከመሸገበት ባስተላለፈው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከደርግ ቀጥሎ ቀንደኛው ጠላታችን የጉራጌ ብሔረሰብ ነው በማለቱና እኔም የዚህ ብሔረሰብ አባል በመሆኔ፣ እኔ በኢትዮጵያ አንድነት እንዲሁም ሕዝብ በጎሳ ወይም በሃይማኖት ሳይከፋፈል አብሮ የሚኖርበት ዘዴ ወይም ስልት ይፈለግ በሚለው የማምን ሲሆን የወያኔ መንግሥት ግን ሕዝብን በብሔር

ለመሸንሸንና ብሎም አገርን ለመበታተን የተዘጋጀ ስለሆነ ሊተናኮለኝ ይችላል የሚል ነበር፡፡

የኢሚግሬሽን ቢሮ የካናዳን ጥገኝነት እንደጠየቅን የሚገልጽ ወረቀት ሰጥቶ አሰናበተን፡፡ የስደተኛነት ማመልከቻችን ከስድስት ወር ጥበቃ በኋላ ተቀባይነት አገኘ፡፡ ወድያው በካናዳ ቋሚ ነዋሪ ለመሆን አመለከትን፡፡ ፈቃዱ ከአንድ ዓመት በኋላ ተሰጠን፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# የስደት ኑሮ

የቤተሰባችን ቁጥር ሰባት ነው:: ኤምባሲውን ስንለቅ ግሩም 14፣ ኅሊና 13፣ ኖላዊ 11፣ ቅድስት 10፣ ዮሐንስ 6 አመታቸው ነበር:: ኤምባሲውን ጥለን ስንወጣ መግቢያችን የት እንደሚሆን አናውቅም:: ይሰጠኝ የነበረው ወርኃዊ ደመወዝ የቤት ወጪ ለመሸፈን እንኳ የማይበቃ ስለነበር ከአዲስ አበባ ስንወጣ ብሔራዊ ባንክ በነበረው ደንብ መሠረት ፈቅዶልኝ የመነዘርኩትን 4000 ዶላር በማሟያነት እየተጠቀምኩበት የተረፈኝ ርዝራዥ ነበር:: መኪናም ሆነ የቤት እቃ የለንም:: የነበረን ንብረት ልብሳችን ብቻ ነበር ለማለት ይቻላል:: ዕፀገነት ጠንካራ ሰው በመሆኗና ልጆቼ ደግሞ ያዩትን ሁሉ አውርዱልን የሚሉ ዓይነቶች ስላልሆኑ በዚህ ተጽናናሁ::

እድሜ ለወዳጅና ዘመድ ብዙ ሰው ደረሰልን:: እዚያው ኦታዋ የተዋወቅናቸው አቶ ጌታቸው አየለና ባለቤቱ ወይዘሮ ብስኩት አስጠጉን:: ሦስት መኝታ ክፍል ባለው ቤታቸው ውስጥ ከአዲስ አበባ በሾፌርነትና በሠራተኛነት ከኛ ጋር አብረው መጥተው የነበሩትን ጨምሮ ዐሥራ አንድ ሆነን ሰፈርንበት:: ወዳጄ አቶ አበበ እንግዳሰውም በምክርና በሐሳብ ረዳኝ::

ከኦታዋ ውጭ መጀመሪያ ከደረሱልን መካከል ወዳጄ አቶ ዮሴፍ አሰፋና ባለቤቱ ወይዘሮ ጆቫና ፓውሎ ይገኙበት ነበር:: ዮሴፍ ከቶሮንቶ ድረስ መጥቶ ጠይቆን ተመለሰ::

እነጌታቸው ዘንድ እያለን መንግሥት ቀለብ እንዲሰፍርልንና ቤት ተከራይተን አዲሱን ኑሯችንን እንድንያያዘው እንዲረዳን ጠየቅን:: ድሆች

መሆናችን ከተረጋገጠ በኋላ ተፈቀደልን፡፡ ተፈላጊውን ፎርማሊቲ ለማሟላት በጎአድራጎት ቢሮ ድረስ መሄድ ነበረብኝ፡፡ እዚያ የሚታየው ሰው ዓይነቱ ብዙ ነው፤ ከየአገሩ ግፈኛ ያባረረው ስደተኛ፣ ሥራ አጥ፣ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ቤት ኪራይ መክፈል ያቃተው ወይም ልጆቹን መመገብ የተሳነው አባወራ፣ በዕፅ የደነዘዘ፣ በመጠጥ የተለከፈ፣ የሥራ ሐሞቱ የፈሰሰ፣ ወንጀለኛ በመሆኑ ቀጣሪ ያጣ፣ ወዘተ፡፡ ቀና ብዬ ሰው ለማየት አፈርኩ፡፡ ሠርቶና ተምሮ ላፈር ተብሎ በቁሜ ሙሾ ሲደረደርልኝ የሰማሁ መሰለኝ፡፡ ኀፍረትና ብስጭት እየተፈራረቁ ስላጠቁኝ ያንን ቢሮ የረገጥኩበት ቀን ከመዝገብ ምነው በተፋቀ ብዬ ተራግሜአለሁ፡፡ ቢሆንም፣ ለዚህ የተዳረግነው በሠራሁት ጥፋት እንዳልሆነ ስለማውቅ ከቁጥጥሬ ውጭ የሆነውን ምንም ላደርገው አልችልም ብዬ እራሴን ለማጽናናትና ቤተሰቤን ለማረጋጋት ሞከርኩ፡፡

እነጌታቸው ዘንድ አንድ ወር ተኩል ከተቀመጥን በኋላ አንድ ቤት ለመከራየት ፈልገን ሥራ ወይም ወርኃዊ ገቢ ስላልነበረኝ ባለቤቱ አላከራይም አለን፡፡ ጌታቸው ኃላፊ ሆኖ በውሉ ላይ ፈረመልን፡፡ መንግሥት በዳረጎት ከሚሰጠን ገንዘብ ውስጥ የሚበልጠው እጅ የሚውለው ለቤቱ ኪራይ ክፍያ ነበር፡፡

የተከራየነው ቤት የልብስ ማጠቢያ ማሺን አልነበረውም፡፡ አውቶሞቢል እንዳልነበረን ጠቅሻለሁ፡፡ ገንዘብ ጎራሽ የልብስ ማጠቢያ ማሺን ይገኝ የነበረው ከቤታችን በእግር የሃያ ደቂቃ መንገድ ላይ ነበር፡፡ ዕፀገነት የሚታጠቡ ልብሶቻችንን በጆርባዋ ተሸክማ አጥባ ትመልሳለች፡፡ እስከዛሬ የሚገርመኝ ሰፈራችን ግርጌ ያለውን ዳገት በዚያ የነሐሴ ሙቀት እንዴት አድርጋ እንደወጣችው ነው፡፡ ያንን ክምር በጆርባዋ ተሸክማ ስትነጉድ የፈረንጅ ውላጅ እየተጠቃቀሰ ይመለከታት ነበር፡፡ ዕፀገነት የአምባሳደር ሚስት እንደነበረችና ከወራት በፊት በአገሩ ጠቅላይ አገረገዥና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጋብዛ የክብር ስፍራ የነበራት ሴት እንደነበረች ተጠቃቃሾቹ ቢያወቁ ኖሮ ምን ይሉ እንደነበር አናውቅም፡፡ እኛም ብንሆን ከዚያም በፊት

ሆነ ከዚያን በኋላ ትልቅ የልብስ ክምር በጀርባው ተሸክሞ በመንገድ የሚሄድ ሰው ዐይተን አናውቅም፡፡ አዲስ አበባም ቢሆን አንድ ሰው የልብስ ክምር በጀርባው ተሸክሞ ወንዝ ሲወርድ ከጋሼ ኬርጋ በኋላ ሌላ ሰው ማየቴን አላስታውስም፡፡

ዕፀገነት በዚህና በሌላም መንገድ ተሸክማ ቤተሰቡን ዳር ያደረሰች ሴት ናት፡፡ ስለልጅነቷ እንደምትነግረኝ ከሆነ አጥር ስትዘል፣ ኳስ ስትረግጥ፣ ከወንዶች ጋር ስትደባደብና እንጀራ ስትጋግር እግሯን እሳት ቢለበልባት ምጣድ ሰብራ ሮጣ ያመለጠች ችግር ወይም መከራ አጠገቧ ሳይደርስ ተቀማጥላ ያደገች፣ ዛፍ ላይ መውጣት የምትወድ ነበረች፡፡ ታዲያ ያቺ "ወንዲሎ" ዛሬ እንዲህ የቤቱ ምሰሶ ትሆናለች ብሎ በቅርብም ሆነ በሩቅ የሚያውቃት አይገምትም ነበር፡፡ ነገሩ ሳይደግስ አይጣላም ሆነና ለእኔና ለልጆቼ እሷን ጣለልን፡፡

ውለታቸውን እግዚአብሔር ይክፈላቸውና አቶ ጌታቸው ጀምበሬና ወይዘሮ አስቴር አድማሴም የልብስ ማጠቢያና ማድረቂያ ማሺኖች ገዙልንና ዕፀን ከጀርባ ሸክማና ረጅም የእግር ጉዞ ብቻ ሳይሆን ከፈረንጅ የጎሪጥ ዕይታም ገላገሏት፡፡

እኔና ዕፀገነት የተገናኘነው እንደዚህ ነው፡፡ የፍቅር አምላክ አፍሮዳይት ወደ አማልክቶች ንጉሥ ወደ ዜውስ ዘንድ ትሄድና ታደሰና ዕፀገነት እንዲገናኙ ስለምፈልግ እባክህን ዘዴ ፍጠር ብላ አልቅሳ ትማጸነዋለች፡፡ እሺ ይልና እቅዱን ይነግራታል፡፡ የኢትዮጵያን ንጉሥ ከቦታው አስነሳውና አገሩን ወታደሮች እንዲያስተዳድሩት አደርጋለሁ፤ ንጉሡን አቅፎ ደግፎ ያኖረው ሥርዓት እንዲፈራርስ አደርግና ሕዝቡ ስለተደረገው ለውጥ መረዳት እንዲችል፣ ከማይምነት እንዲላቀቅና እውቀት እንዲገበይ አደርጋለሁ፤ ለዚህ ፕሮግራም መሳካት ተማሪዎችን በአራቱም ማእዘን እንዲሰራጩ አደርጋለሁ፤ ተማሪዋ የቀኛዝማች ወልዴ አሳመረችን ወደአላማጣ እልካታለሁ፣ እዚያ ከደረሰች በኋላ ጤንነቷ ለጊዜው እንዲታወክ

አደርጋለሁ፤ እጮኛዋ ሄዶ እንዲያመጣትና ራስ ደስታ ሆስፒታል እንድትተኛ አደርጋለሁ፤ የእጮኛዋ ጓደኛ፣ ታደሰ፣ ሊጠይቃት ሲመጣ ከምታስታምማት ታናሽ እህቷ ጋር እንዲገናኙ አደርጋለሁ ብሎ ለአፍሮዳይት ሲዘረዝርላት “ጌታዬ፣ ለአንተ ምን ይሳንሃል?” ብላ እጅ ነስታ ወጣች።

አሳመረች በዘመቻ ጣቢያ ሆና መታመሟን እጮኛዋ ስሜ ሲሰማ ሄዶ ሊያመጣት ቁርጥ ውሳኔ ያደርጋል። ለመነሳት አንድ ቀን ሲቀረው ለአባቷ ለቀኛዝማችና ለእናቷ ለእማማ ሙሉነሽ ለመንገር ቤታቸው ድረስ፣ አማኑኤል መሳለሚያ፣ ሰፈር ሰላም፣ ይሄዳል። ስሜ ያሰበውን ወይም እቅዱን ተናግሮ ከመጨረሱ እማማ ሙሉነሽ “ስምዬ፣ እሺ፣ መሄዱንስ ሂድ እንበል፤ ለመሆኑ እዚያ ስትደርስ የት ነው የምታድረው?” ብለው ይጠይቁታል።

“እማማ፣ ምንም ችግር የለም፤ ሆቴል አለ እኮ።” የእማማን ጥያቄ ውስጠ ምስጢር ስሜ አልተረዳውም።

“አይ፣ መንገዱም ሰላም አይደለም አሉ፤ ሆቴልም ማግኘት ያስቸግራል አሉ፤ የለም፣ ግድየለም አትሂድ”

“እማማ፣ ምንም ችግር የለም፤ ሆቴል የሚጠፋ አይመስለኝም፤ ቢጠፋም መኪና ውስጥ መተኛት ይቻላል”

“እኔ ደስ አላለኝም፤ ባትሄድ ይሻላል፤ እሺ ስትመለሱ የት ነው የምታድሩት? በአንድ ቀን አዲስ አበባ መድረስ አይቻልም”

“እማማ፣ ምንም ችግር የለም፤ ሆቴል በየደረሱበት ሁሉ ይገኛል እኮ፤ በተለይ ደሴ የምናድር ከሆነ”

“ይኸው፣ ይኸው፣ የፈራሁት፣ የለም ስመዬ፣ ግድየለም፣ ባትሄድ ይሻላል”

የዜውስን ትልም ሰው መለወጥ ስለማይችል ስሜም ሄደ፣ አሳመረችም መጣች፣ ዕፀገነትና ታደሰም ተገናኙ፡፡ ገና ሲያያት በውበቷ፣ በፈገግታዋና በጨዋታዋ ተማረከ፣ እንደፈለግሽ አድርጊኝ ብሎ ወድያው እጁን ሰጣት፣ ቀጥሎም ልቡንና ሁለመናውን አስረከባት፡፡

አሳመረችንና ስሜን በተመለከተ የእማማ ስጋት በከንቱ ነበር፣ በሰርጋቸው ማግስት የምስራች አብሳሪዎች ብር አምባር ሰበረልዎ፣ ጀግናው ልጅዎ እያሉ የልጃቸውን ታማኝነት አረጋገጡላቸው፣ እሳቸውም ልጆቼ ተባረኩ ብለው መረቋቸው፡፡

እኔና ዕፀገነትም ለቁም ነገር እንደምንፈላለግ ገሀድ የወጣው የሰርጋቸው ዕለት በጥር 1968 ነበር፡፡ የኛ የጋብቻ ሥነሥርዓት የተፈጸመው በህዳር 4 ቀን 1970፣ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ደጃፍ ቆሞ አራት ዓመት ሙሉ ስወጣና ስገባ ይመለከተኝና ይጠብቀኝ በነበረው በስደተኛው መድኃኔ ዓለም ቤተክርስትያን ውስጥ ነበር፡፡ ቤተክርስትያኑ ለተፈሪ መኮንን ተማሪዎች የማጥኛና ፈጣሪን የማመስገኛ ስፍራ ብቻ ሳይሆን ከእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ሴቶች ተማሪዎች ጋር ማዶ ለማዶ እየተያየን የፍቅር ድብብቆሽ የምንጫወትበትና ፍቅርን በሐሳባችን የምናፍተለትልበት ስፍራም ጭምር ነበር፡፡ ስደተኛው መድኃኔ ዓለምን መምረጤ የድብብቆሹና የወዲያ ወዲህ የማያው ዘመን ማክተሙን ለሚመለከተው ሁሉ ለማብሰርና መድኀንዬ ጸሎቴን ሰምቶ ዕፀገነትን ስለሰጠኝ ምስጋና ለማቅረብም ነበር፡፡ ስደተኛው መድኃኔ ዓለም ሙሽሮቹን ወደቤቱ የጠራን እኛም በተራችን እንደምንሰደድ አስቀድሞ አውቆ ላገራችሁ ያብቃችሁ ብሎ ሊመርቀን ፈልጎም ይሆናል፣ ማን ያውቃል? ለሱ ለማያልቅበት ምንስ ይሳነዋል?

እላይ እንደገለጽኩት ሁለት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆች ወልደናል፡፡ ግሩምንም ከልጆቻችን ለይተን አናየውም፡፡ ስለሕፃንነታቸው ዘመን ስለእያንዳንዱ ያለን ትዝታ የተለያየ ነው፡፡ የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ነው

እንዲሉ ጠባያቸው የተለያየ ስለሆነ እያንዳንዳቸውን እንደጠባያቸው መያዝ እንደሚገባን የተረዳነው ገና ከማለዳው ነው።

ግሩም በሕፃንነቱ የሚታወቀው በሩጫው ነበር። ላይ ታች እንደመሮጥ ያህል የሚያስደስተው ነገር የነበረ አይመስልም። በነጋ በጠባ ለአጭር ርቀት ውድድር የሚለማመድ ይመስል ነበር። ጥርሱን ይለቅማል እያልን ዘወትር እንሰጋ ነበር። የፈራነው አልቀረም አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ጥርሱ ተሸርፎ መጣ። ምን ሆነህ ነው? ተብሎ ቢጠየቅ ስሮጥ ወድቄ ነው አለ። ጥርሱ የተሸረፈው ወድቆ ሳይሆን በእርግጫ ጨዋታ መሆኑን እዚህ ካናዳ ከመጣን በኋላ ነገረኝ። ግሩም ለቀኛዝማች ቤተሰብ የመጀመርያው የልጅ ልጅ ስለሆነ ቀኞ ስሙ ወግደረስ እንዲባል ፈልገው ነበር። በኔ በኩል ደግሞ የተወለደው ብሔራዊ ባንክ አዲሱን ገንዘብ ባወጣበት በጥቅምት 5፣ 1969 ስለነበር ብሩ እንበለው ብዬ ነበር። ሁለቱም ተቀባይነት ሳያገኙ ቢቀሩም ቀኛዝማች ግን በስያሜአቸው ጸኑ።

ኅሊና ደግሞ ቤታችን የመጣ ወዳጅና ዘመድ ሁሉ በደባልነት ተመዝግቦ ከኛ ጋር እንዲቆይ የምትጋብዝ ይመስልባት ነበር፤ ሰው ሲሸኝ ስታይ ታዝን ነበር። አሁንም ቢሆን በጣም ሩህሩህና ሰፍሳፋ ነች። ይህች ዓለም፣ በተለይም ሰሜን አሜሪካ፣ ለእርሷ ዓይነቱ ሰዎች ብዙም ስለማታመች ከዕፀገነት ጋር ስንጨዋወት አምላክ ይጠብቃት እንባባላለን። የእቃ ገጣጣሚነትዋንና ጠጋኝነትዋን፣ በደፈናው እጀ ወርቅነትዋን የእንጀራ እናቴ እልፍነሽ እዚህ ኦታዋ መጥታ በነበረበት ወቅት ዕይታ፣ "አ አ ይቺ ልጅ ባል እንዳታጣ እፈራለሁ!" ብላለች። ለምን እንዲህ አልሽ ብትባል ማን ያበሻ ወንድ ነው እያወቀ የምትበልጠውን ሚስት የሚያገባ አለች። የዘመኑ ወንድ ስንፍናን ሙያው አድርጎ ስለያዘው እንኳን የተሰበረ ሊጠግን ያዘነበለም ስለማያቀና እንዲያውም ተፈላጊነትዋ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፤ ምስክራችን ኖላዊና ግሩም ናቸው ብለን መልሰንላታል።

ኖላዊ በሕፃንነቱ የሚታወቀው በእልኸኛነቱና በአልቃሻነቱ ነበር፤ ሃያ አራት ሰዓት የሚያለቅስበት ጊዜ ነበር፣ ትላለች እናቱ። በምላሹ ወንድ ልጅ መያዝ ወይም ማሳደግ አቅቶሽ ነው እያልኩ እቀልድባት ነበር። የመጀመሪያው ወንድ ልጄ ልቅሶ ለኔ የሙዚቃ ድምፅ ነው እያልኩም አናድዳት ነበር። ቢጨንቃት ሐኪም ቤት ድረስ ይዛው ሄዳለች። ሐኪሙ እናንት የቢሮ ሠራተኛ እናቶች ከሥራ መልስ የልጅ ልቅሶ መስማት ስለማትፈልጉ ነው እንጂ ልጁ ምንም አልሆነም፤ ይልቅስ ይህን ጤነኛ ልጅ እዚህ ድረስ ይዘሽ መምጣትሽ ለሌላ በሽታ ማጋለጥ ስለሆነ ጥፋት ነው ብሎ ገስጾ መልሷታል። በአሁኑ ወቅት ኖላዊ እንደ አያቱ እንደ ገጎ ሰራጋ፣ እንደ አጎቱ ዶክተር ብርሃኔና ልጁ ሚካኤል የረጋ ነው። ከጠባዩ ሸጋነት የተነሳ ለጓደኛነት የሚፈልገው ብዙ ነው። በትምህርት ቤትና በስፖርት ሜዳ በጠባይ ተሸላሚ ነበር። ሰውን ተናግሮ ማስቀየም አያውቅበትም፤ ስለሰው መጥፎ ነገር አያወራም፤ ሰውን ማማት አይወድም። አቶ ሁሉን በሆዱ ነው።

ሦስተኛዋ ልጃችን በሕፃንነቷ በጣም የረጋች ስለነበረች ቅድስት የሚለውን ስም አወጣሁላት። እያደገች ስትሄድ ግን ሐሳቧንና ስሜቷን ለመግለጽና መብቷን ለማስከበር ወደኋላ የማትል ሆና ተገኘች። አልፎ አልፎ ያባትና ልጅ ጥል ስንጣላ ያወጣሁልሽን ስም መልሺ እላታለሁ። ስታንጎራጉር ድምፏ ማራኪነት አለው። ዕፀገነትም እንደዚሁ። ለምን የእናትና ልጅ የሙዚቃ ባንድ አትመሰርቱም? እላቸዋለሁ። ከእናቷ ጋር የሚመሳሰሉበት ሌላ ነጥብ በቤት ንጽሕናና በቤት እቃ አቀማመጥ ረገድ አጥፊ ሲያገኙ ሳያወላውሉ ጦርነት ለመክፈት የተዘጋጁ መሆናቸው ነው። እናቲቱ ቅድስት ባትኖርልኝ ኖሮ እሞት ነበር ስትል በይ እንደሱ እያልሽ በቁጥጥርሽ ሥር አድርገሽ በዝብዢት እላታለሁ።

የመጨረሻው ልጃችን ዮሐንስ በሕፃንነቱ ዘመን "ልገልበጥላችሁ?" ወይም "ልገለባበጥላችሁ" ማለት ይወድ ነበር። አንድ እንግዳ ቤታችን ሲመጣ ብዙ ልጆች እንደሚያደርጉት መሸሽግ ወይም መሽኮርመም ሳይሆን ትርኢት

ለማሳየት ዝግጁ መሆኑን በፈቃደኛነት ቀርቦ ያውጅ ነበር። እዚህ ካናዳ ከመጣን በኋላ የጠየቃቸውን አንዳንድ ነገሮች እሺ ብለን ስናሟላለት ወንድሞቹና እህቶቹ ይበላሻል የሚል ስጋት ነበራቸው። አሁን ግን በዲሲፕሊን ረገድ ከሁሉም ቢሻል እንጂ አያንስም። ወላጆቹ የፈለግሁትን ካሟሉልኝ እኔም በበኩሌ እነሱ ከኔ የሚፈልጉትን ማሟላት አለብኝ የሚል እምነት ያደረበት ይመስለኛል። በጣም ንቁና ቀልጣፋ ስለሆነ ቤቱ ውስጥ የሱን እርዳታ የማይፈልግ የለም። ሁሉን አውቃለሁ የሚል በሽታ እንዳይጸናወትህ ተጠንቀቅ እያልኩ እመክረዋለሁ። በዚህም ረገድ አላሳፈረኝም።

ወደ ስደት ኑሯችን ስመለስ፣ ወደ ተከራየነው ቤት እንደገባን የዕፀገነት ታናሽ ወንድም ክፍለማርያም ከፍሎሪዳ መጥቶ ጠይቆን ተመለሰ። አውቶሞቢልም ገዛልን። ምስኪንነታችን ያልተዋጠለት አንዳንድ ታዛቢ ተሽከርካሪውን የገዙት በቀበሩት ገንዘብ መሆን አለበት አለ። በወቅቱ ዚምባብዌ ይኖሩ የነበሩት ታላቅ ወንድሜ ብርሃኔና ባለቤቱ ገነትም ጠይቀውን ተመልሰዋል። በችግር ጊዜአችን ከደረሱልን ሌሎች ወዳጆቻችንና የቤተሰብ አባላት መካከል ስሜና አሳመረች፣ ጌቱና አምባሽ ወርቅ፣ ኢየሱስ ወርቅ ዛፉ፣ ክፍሌ ሽንኮሩና አስቴር፣ ግርማ ታደሰ፣ ከበደ አድነውና ዮዲት፣ መርስኤ እጅጉና ትርሲት ጋሜ፣ ግርማ ኃይለልዑልና ዘነበወርቅ፣ ወልደየሱስ ገብረማርያምና ማናለብሽ ይገኙበታል።

ኤምባሲውን ለቅቀን ስንወጣ የነበረኝ ግምት ሥራ ለማግኘት ረጅም ጊዜ አይፈጅብኝም የሚል ነበር። የሥራ ማመልከቻ በየቦታው አስገባሁ፣ ነገር ግን ለኢንተርቪው የሚጠራኝ ድርጅት ጠፋ። ከኤምባሲው ሳልወጣ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ በካናዳ ቴሌቪዥን ጣቢያ ለካናዳ ሕዝብ መልዕክት ሲያስተላልፍ መንግሥቱን በሥልጣን ያቆየው አንድም በድርቅ ሳቢያ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው እርዳታ ነው ብሎ ተናግሮ ስለነበር ተቃውሞዬን በመግለጽ ለቴሌቪዥኑ ጣቢያ፣ ለአዘጋጆቹና ለተባባሪዎቻቸው ደብዳቤ አሰራጭቼ ነበር። የደብዳቤው መንፈስ ለፖለቲካ ተብሎ ለተራበ ሕዝብ

ምግብና መድኃኒት እንዳይደርስ መንገድ መዝጋት ኢሰብኣዊ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነበር፡፡ የቴሌቪዥኑ ድርጅት የደብዳቤዬን ግልባጭ ለዳዊት ይልክና መልስ ስጥበት ይለዋል፡፡ ዳዊት በቀጥታ ለኔ ብቻ በእጁ በጻፈው ደብዳቤ "አምባሳደርነቱም ይቀርና ሥራ አጥተህ ትንከራተታለህ" ብሎ ዝቶብኝ ነበር፡፡ ዳዊት መልኩ ብቻ ሳይሆን ምላሱም ጥቁር ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት የልጅነት ጓደኛዬ ኪዳኔ ወልዴ መልኩ ከዳዊትም የጠቆረ ነው፡፡ "ያልኩት ለመፈጸሙ ምስክሬ ይኸው ጥቁሩ ምላሴ" እያለ እየጎለጎለ ያሳየን ነበር፡፡ ዳዊት እንደተነበየው የሥራው ነገር በእርግጥም የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ፡፡ ያለሁበትን ሁኔታ ከሰማ ይሄኔ ጮቤ እየረገጠ እልል ይላል ብያለሁ፡፡

ዳዊት በደብዳቤው ሌላም ነገር ብሎኛል፡፡ እሱና የሱ ተባባሪዎች የደርግን መንግሥት ገልብጠው ሥልጣን ሲይዙ እንደሚፋረዱኝ ዝቶብኛል፡፡ የዳዊት ተባባሪዎች ተገንጣይና አስገንጣይ እንደነበሩ በሐምሌ 1983 በታተመው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ አማካይነት ገሀድ ወጥቷል፡፡ በበኩሌ ፍርዱን ለኢትዮጵያ ሕዝብና አምላክ ትቼዋለሁ፡፡

ደኅና ትምህርትና የሥራ ልምድ ያለውን ሰው ሥራ የሚያስይዙ ድርጅቶች አሉ ተባለና አንዱ ዘንድ ተጠጋሁ፡፡ የድርጅቱ ኃላፊ ሴት ናት፡፡ ለአንተ በጣም ጥሩ ሥራ ለማግኘት ከአንድ ሳምንት በላይ አይፈጅብኝም፤ በእንዲህ ቀን ደውል ብላ አሰናበተችኝ፡፡ በተባለው ቀን ብደውል የለችም ተባልኩ፤ ደጋግሜም ብደውልም ሴትዮዋን በጭራሽ ማግኘት አቃተኝ፡፡ ብዙ ጊዜ ደውዬ ሳሰለቻቸው ጊዜ ብቅ በል አለችኝና ሄድኩ፡፡

"ስማ ሰውዬው፣ በአንተ ጉዳይ ተጨማሪ ጊዜ ማጥፋት አልፈልግም፤ ቀጣሪዎች ስሙን አታንሺብን ብለውኛል" አለችኝ፡፡

"ይህን ያህል ማን አውቆኝ? ምን ቢፈጠር ነው?" ብዬ ጠየቅኋት፡፡

"ከመንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር በመሥራትህ"

“እኔ መንግሥቱ በሚመራው መንግሥት ውስጥ ልሥራ እንጂ በግሌ የሠራሁት ወንጀል የለም፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያሳዝን ድርጊት አልፈጸምኩም፤ በሥልጣን አልባለግሁም፤ እናንተ አንድ ሰው ጥፋተኛ ነው ተብሎ እስካልተፈረደበት ድረስ ንጹሕ ነው ተብሎ ይታመናል በምትሉ ሰዎች ፊት እንዴት እንደወንጀለኛ ተደርጌ እታያለሁ?”

“እንጃልህ፣ የኔ ችግር አይደለም” ብላ አሰናበተችኝ::

የተጠቀመችበት ቋንቋ ደም የሚያቀዘቅዝ ነበር:: በእንግሊዝኛ There is a strong undercurrent running against you in this town ነበር ያለችኝ:: ትርጉሙ ባጭሩ ሊያስጠጋህ ወይም ሊቀርብህ የሚፈልግ የለምና አገሩን ለቅቅህ ብትጠፋ ይሻልሃል እንደማለት ነበር:: ዐይን ያልከፈቱ ሕፃናት ከአገራቸው አውጥቼ እዚህ በሰው አገር ጉዴ ሊፈላ ነው ብዬ ከፍተኛ ስጋት አደረብኝ:: ምንም ምርጫ ስለሌለኝ አገሬ እስክመለስ ያባቴ እንትን ያድርገኝ እንዲሉ የመጣው ቢመጣም እዚሁ ኦታዋ ለመከርቸም ቆረጥኩ:: ሰባት ሆኜ ከቤቴ የወጣሁ የነጣሁ ደሃ ምንስ ምርጫ ነበረኝ?

ያስጠጋኝ መስሎ የገፋችኝን ካናዳ ትቼ ውጭ ውጭ ለማየት ተገደድኩ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ላስተማረኝና ዋሺንግተን ከተማ ለሚገኝ ለመምህሬ ለቮን ፒሽክ ያለሁበትን ሁኔታ ገልጬ ሥራ በማስያዝ ይረዳኝ እንደሆነ ጠየቅሁት:: ካናዳ ውስጥ አንድ ወደሚያውቀው ባለሥልጣን ዘንድ ላከኝ:: ሰውዬው ወደሌላ መራኝ:: እንዲህ እየተቀባበሉኝ በመጨረሻ አንድ የተወሰነ ፕሮጄክት እንዳስተባብርለት ኤኮኖሊንክስ የሚባል የጥናት ድርጅት በአጭር ጊዜ ኮንትራት ቀጠረኝ:: የድርጅቱ ባለቤት ፕሮፌሰር ኪት ሄይ ይባላል:: ሥራው የተገኘው ኤምባሲውን ለቅቄ በወጣሁ በሦስተኛው ዓመት ነበር:: ኤምባሲውን ለቅቀን ከወጣነው ውስጥ ሹሜ ይገኝበት ነበር:: ታደሰ ሥራ ጀመረ ተብሎ ሲነገረው ሳያስበው ዕንባው ዱብ ዱብ እንዳለ ያዩ ሰዎች ነገሩን:: ሰውን ችግር ካልደረሰበት እርግጠኛ ወዳጁን እንደማያውቅ መመስከር ቻልን:: የኛ ናቸው ከምንላቸው ሰዎች አንዳንዶቹ ድራሻቸው

ጠፋ። ይደርሱልናል ብለን ያላሰብናቸው ሰዎች እርዳታቸውን ጭነው ከቸች አሉልን። ሻምበል አለማየሁ ኃይሌ ሲገደል ስለጊዜያዊና ዘላቂ ወዳጅ ደኅና ትምህርት አግኝቼ ስለነበር ሰዎች ሸሹኝ ብዬ ብዙም አልተበሳጨሁም። እውነቱን ለመናገር ይህን ያህልም ሰው ሸሽን የሚያሰኝ ሁኔታ አልነበረም። በተቃራኒው የደረሰልን ሰው ብዙ ስለነበር ወደፊት የሚገጥመንን በተስፋ ለመጋተር ረዳን።

ለድርጅቱ ሦስት ወር ያህል ሰርቼ መጠነኛ ገንዘብ አገኘሁ። ያገኘሁትን ገንዘብ መጠን በየወሩ የዳረጎት ቼክ ለሚልክልኝ ድርጅት አስታወቅሁ። የእርዳታው ቼክ ተቋረጠ። እንደገና ወደ ድርጅቱ ዳረጎት እንዳልመለስ የሥራ ፍለጋውን አጥብቄ ተያያዝኩት። በኤኮኖሚንክስ አማካይነት ወደ አሜሪካ፣ ዛሚቢያና ጋያና፣ ደቡብ አሜሪካ ደርሼ ተመልሻለሁ።

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት በአሜሪካ ውስጥ ባንክ ለማቋቋም ያስብና የማኅበሩ ኃላፊዎች አቶ ፋሲልና አቶ ቸሩ ጥናት እንዳደርግላቸው ጠየቁኝ። ስለጉዳዩ ለመወያየት አትላንታ፣ ጆርጂያ፣ ድረስ ሄጄ ከማኅበሩ አመራር አባላት ጋር ተገናኘሁ። ዋሺንግተን ከተማ አጠገብ በሚገኘው በስፕሪንግፊልድ፣ ቨርጂኒያ፣ በጓደኞቼ በሳሙኤል በቀለና በየሺሐረግ ቤት ተቀምጬ ጥናቱን በአርባ ቀን አጠናቅቄ አስረከብኩ። ጥናቱን በሲልቨር ስፕሪንግ፣ ሜሪላንድ፣ ያቀረብኩ ዕለት ከተገኙት መካከል አቶ ምናሴ ለማና አቶ ደበበ ሀብተዮሐንስ ነበሩ። የአቶ ደበበ ግርፍ መሆኔንና አቶ ምናሴ ባደላደሉት ቤት ገብቼ መውጣቴን በኩራት ተናገርኩ።

የካናዳ የግልም ሆነ መንግሥታዊ ድርጅቶች በራቸውን በተለይ ከአውሮፓ ውጭ ለመጣ ባለሙያ ክፍት ለማድረግ ፈቃደኛነት ይጎድላቸዋል። ውድድርና አዳዲስ ሐሳብ ይፈራሉ ይባላል። ድርጅቶቹ የሚጠቀሙበት ሽፋን ግን ከውጭ የሚመጡት የሥራ አመልካቾች በካናዳ ውስጥ በቂ የሥራ ልምድ ስላላካበቱ ነው የሚል ነው። አመልካቾች በሙያቸው የመሥራት ዕድል እየተነፈጋቸው በካናዳ ውስጥ የሥራ ልምድ እንዴት

ማካበት ይችላሉ? ሱሪን በአንገት ማውለቅ ማለት ይህ ነው! ከፍተኛ እውቀት ያላቸው ስደተኞች እጅና እግራቸውን አጣጥፈው በየቤታቸው ተቀምጠዋል ወይም ከፍተኛ ሙያ በማይጠይቅ የጉልበት ሥራ ላይ ተሰማርተዋል:: ይህ በተለይ ከአፍሪቃ ተሰደን በመጣነው ላይ ጎልቶ ይታያል:: ብዙ ነጮች ጥቁሮች ከነሱ ጋር እኩል ተሰልፈው የሚጠበቅባቸውን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አይመስላቸውም:: በካናዳ ውስጥ ስላለው የነጭና የጥቁር ግንኙነት ያለኝ አስተያየት በግጥም ነጭና ጥቁር በሚል ርእስ 511 ላይ ሰፍሯል::

# ኬፕ ታውን፣ ደቡብ አፍሪካ

እላይ እንደገለጽኩት ካናዳ ለድርጎ ሰፈራ እንጂ ለሥራ እንዳልፈለገኝ ስረዳ በሌሎች አገሮች ውስጥ የሚሠሩ የማውቃቸውን ሰዎች ሳፈላልግ ሚስተር ኖምቬቴን በስልክ አገኘሁትና አነጋገርኩት:: ሚስተር ባክስ ኖምቬቴ የደቡባዊና ምስራቃዊ አፍሪቃ ንግድ ቀጠና ድርጅት ፒ ቲ ኤ ዋና ጸሓፊ በነበረበት ወቅት ባንክና ውጭ ንግድ ሆኜ በሥራ እንገናኝ ነበር:: ችግር ላይ መሆኔን ሲሰማ "እኔ ዘንድ ወደ ኬፕ ታውን ብትመጣ ለአንተ የሚሆን ሥራ ይኖራል" አለኝ:: እንዳጋጣሚ ሆኖ እሱ የሚመራውን የጥናት ድርጅት ብቃት ያላቸውን ሰዎች አሰልፈህ ሥራውን ካልመራህ በቀር እርዳታ እናቋርጥብሃለን ብለው አስፈራርተውት ስለነበር እኔ ስደውልለት በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ መግደል መሆኑን ተረድቶ ደስ ሳይሰኝ የቀረ አይመስለኝም::

እአአ በማርች 1996 ኬፕ ታውን ገባሁ:: እንደሚታወሰው በእነኔልሰን ማንዴላ ትግል የፖለቲካ ሥልጣን ከዘረኞች ነጮች ወደ ጥቁር አፍሪቃውያን የተሸጋገረው እአአ በ1994 ነበር:: የደቡብ አፍሪቃ ነጮች ሥልጣን ከእጃቸው እንዳይወጣ ለምን እንደፈለጉ ለመረዳት ኬፕ ታውንና አካባቢውን ተዘዋውሮ ማየት ይበቃል:: አገሩን ለፈረንጂ ምድረገነት ለጥቁር ግን ሲኦል አድርገውታል:: ጥቁሮችን ዐያቸው የነበረው የከተማው

ማዘጋጃ ቤት በየቦታው ያስቀመጣቸውን የቁሻሻ መጣያ በርሜሎችን ሆድ እቃ ሲመረምሩ፣ ጠዋት ባቡር አምጥቶ ሲያፈሳቸውና ማታ ማታ ግር እያሉ ወደባቡር ጣቢያ ሲሮጡ፣ ውራጅ ተራ ሲርመሰመሱ፣ እንዲሁም ከተማው አጠገብ በሚገኘው የካርቶንና ፕላስቲክ ቤቶች መንደር ውስጥ ሲዳክሩ ነበር፡፡ የኬፕ ታውን ከተማን የሚቆጣጠሩትና የሚገለገሉበት ፈረንጆችና በመጠኑ ክልሶች ናቸው፡፡ የከተማው ንጽሕና፣ ዘመናዊነትና የባንክ፣ ቴሌፎንና ተመሳሳይ አገልግሎት ደረጃው ሰሜን አሜሪካ ከማውቀው አያንስም፡፡ በአንዳንድ መስክ የሚሻልም ይመስላል፡፡

ጥቂት ቀናት ሆቴል ውስጥ ከቆየሁ በኋላ የሚከራይ አፓርተማ ፍለጋ ተሰማራሁ፡፡ ደቡብ አፍሪቃ ውስጥ ነጭ በሚኖርበት አካባቢ ጥቁር እንዳይኖር በሕግ የተከለከለ እንደነበረ የማያውቅ ያለ አይመስለኝም፡፡ ጥቁሮች የፖለቲካ ሥልጣን ከተረከቡ በኋላ ሕጉ ቢሻሻልም የደቡብ አፍሪቃ ጥቁሮች ነጮች አካባቢ ለመኖር በተለይ የኤኮኖሚ አቅማቸው አይፈቅድላቸውም፡፡ ነጮቹ ጥቁርን ስለሚጸየፉ አቅም ያገኙት ጥቁሮችም ቢሆኑ በአጠገባቸው እንዲኖሩ አይፈልጉም፡፡ ችግሩ ሥር የሰደደ ነው፡፡ ነጭ የጥቁር የበላይ ነው ብለው ነጩን አሳምነውታል፡፡ አንዳንድ ጥቁሮችም የእምነቱ ተካፋይ የሆኑ ይመስላል፡፡ የአፓርታይድ ሥርዓት ካደረሳቸው በደሎች ዋነኛው የጥቁሩን ሥነልቦና መስለቡ ነው፡፡ ስለሆነም ጥቁሩ እውነተኛ ሥልጣን በእጁ እስኪያስገባ በጣም ረጅም ጊዜ ሳይፈጅ የሚቀር አይመስለኝም፡፡

ኮለምቢያ ዩኒቨርስቲ ሳለሁ ሞሰስና ፒተር የሚባሉ ጥቁር ደቡብ አፍሪቃውያን የክፍል ጓደኞቼ ነበሩ፡፡ የደቡብ አፍሪቃን ድንበር በሕገወጥ መንገድ አሳብረው በመውጣት ነበር አሜሪካ መድረስ የቻሉት፡፡ በትምህርታቸው ደከም ያሉ ስለነበሩ አልፎ አልፎ እረዳቸው ነበር፡፡ ስለደቡብ አፍሪቃ ጥቁሮች ለማወቅ የነበረኝን ጉጉት ለማርካት ብዙ ጥያቄዎችን አቀርብላቸው ነበር፡፡ ይበልጥ ቅርበት የነበረኝ ከሞሰስ ጋር ስለነበር ስለባሕላዊ ሙዚቃቸው፣ ምግቦቻቸው፣ መጠጦቻቸውና ባጠቃላይ

ስለአኗኗራቸው በየጊዜው እጠይቀዋለሁ:: ስለአገራችን በዝርዝር እንዲያውቅ አደርጋለሁ:: ታዲያ ጥያቄዎቼን መስማት አይወድም ነበር፤ ቢችል አርእስቱን እንድንለውጥ ይገፋፋኛል ወይም የተድበሰበሰ መልስ ይሰጠኛል ወይም ጥቁሮቹም እንደነጮቹ የሠለጠኑና ዘመናዊነትን ያቀፉ አድርጎ ይነግረኛል:: ሐቁን እንደማይነግረኝ ይታወቀኛል፤ ለጥያቄዎቼ የተብራራ መልስ ለምን እንደማይሰጠኝ ለመረዳት ሳልችል እቀራለሁ:: ጥያቄዎቼን ማዥጎድጎዴን እንደማላቆም ሲያውቅ አንድ ቀን እንዲህ አለኝ "ስማ ታደሰ፣ አንድ ያልተረዳኸው ነገር አለ፤ የደቡብ አፍሪቃ ዘረኞች እኮ እኛነታችንና የኛ ነው የምንለውን ነገር ሁሉ አሳፋሪና ወራዳ እንደሆነ አድርገው አእምሮአችንን በውሸት ስለጠቀጠቁት አፋችንን ሞልተንና ኮርተን ስለባሕላችን መናገር ይተናነቀናል" ያለኝ በአእምሮዬ ተቀርጾ ቀርቷል::

የሚከራይ አፓርተማ ለማግኘት የቻልኩት ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ነበር:: ጥቁር በመሆኔ ምክንያት እየፈለጉ እንድሄድላቸው ያደርጉ ነበር:: ጥቁር ቆሻሻ ነው ብለው ስለሚያምኑ የኪራይን ቤት በንጽሕና ስለመጠበቅ ደጋግመው ያነሳሉ::

እዚያው የተዋወቅሁት ፀሐይ ንጋቱ የሚባል ኢትዮጵያዊ ወዳጄ የሴት ጓደኛው የሞዛምቢክ ተወላጅ ነበረች:: በነዋሪነት ጆሃንስበርግ ከተማ የገባችው እኔ ኬፕ ታውን ከመግባቴ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎ ነበር:: ከተማው ውስጥ የኪራይ አፓርተማ ትፈልግና የሚያከራያት ታጣለች:: ማስታወቂያ ጋዜጣ ላይ ዐይታ ለመከራየት ስትሄድ አሁን ተከራየ እያሉ ይመልሷታል:: ተስፋ ቆርጣ ሳለ አንዲት የፖርቱጊዝ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነች ሴት ቤት ፈላጊዋም ፖርቱጊዝ እንደምትናገር ስታውቅ አጠገቧ የነበረውን ባዶ አፓርተማ በስሟ ትከራይና ታስገባታለች:: ፎቁ (በእንግሊዝኛው floor) ላይ የነበሩት ነዋሪዎች በሙሉ እንዴት ጥቁር ሰው አጠገባችን ሊኖር መጣ ብለው ከፍተኛ ተቃውሞ ያስነሳሉ:: ነጯ ፖርቱጊዝ እስኪ የምታደርጉትን አያለሁ ብላ ሽንጧን ገትራ ተከራከረች:: አንድ ወይም

ሁለት ነዋሪዎች ሲቀሩ የተቀሩት ፎቁን ጥለው እንደሄዱ የፀሐይ ጓደኛ ነገረችን፡፡

ፀሐይ ኬፕ ታውን ከተማ ውስጥ መኖሪያ አፓርታማ ይገዛና በጣም ያስውበዋል፡፡ እሱ በነበረበት ፎቅ ላይ የነበሩት ነዋሪዎች የሚያደርገውን ዝም ብለው ይመለከታሉ፡፡ የነሱን የሚያስንቅ አንድ ጥቁር መኖሪያውን ሲያደራጅ ሲያዩ ዐይናቸው ይቀላል፡፡ የእድሳቱና የማስዋቡ ሥራ መጠናቀቁን እንዳወቁ አፓርተማህ ፊለፊት ያስቀባኸው ቀለም ሌሎቻችን ስላልተስማማንበት ድንጋዩን አንስተህ ቀድሞ እንደነበረው እንድትመልስ እንጠይቃለን ብለው ቀንድ አስበቅለውታል፡፡ ገንዘቤን ኢትዮጵያ ይገኔ ገብቼ በሥራ ላይ ላውለው አስቤ ትብብር ብጠይቅ የቢሮክራሲው ውጣውረድ ናላዬን ስላዞረውና ገንዘቤም ስለባከነ ጥዬላቸው ወጣሁ፣ እዚህ ደግሞ ነጩ የጥቁርን ዐይን ዐልይ ብሏል፣ ታድያ የት እንድረስ? እያለ አምርሮ ይናገር ነበር፡፡

ከመሥሪያ ቤት እስከ መኖሪያዬ ድረስ ርቀቱ በእግር የሠላሳ አምስት ደቂቃ መንገድ ነው፡፡ ዝናብ ካልጣለ በቀር የምመላለሰው በእግር በፓርላማው አጠገብ ነበር፡፡ የነጭ ዘር ከጥቁር ይበልጣል፣ ነጭና ጥቁር አንድ አካባቢ መኖር የለባቸውም፣ ነጭና ጥቁር አንድ ላይ መማር የለባቸውም፣ ምርጥ መሬት በነጮች እጅ መግባት አለበት፣ ጥቁር መማር ያለበት የነጭን ትእዛዝ ለመቀበል የሚያስችለውን ያህል ብቻ ነው፤ ወዘተ የሚሉት ርኩስ ሕግጋት የተደነገጉት በዚሁ አፍጥጦ በሚያየኝና አፍጥጬ በማየው ግዙፍ ሕንጻ ውስጥ ነበረ፡፡ የጥቁር ዘር ሁሉ ይህን ሕንጻ መጥቶ ማየት አለበት እል ነበር፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሆኜ እንግሊዛዊው የእንግሊዝኛ አስተማሪ፣ ሞስባክ፣ በፈለጋችሁት አርእስት ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርቡ ይለንና እኔ ያቀረብኩት ጥናት “ትምህርት በአፓርታይድ ሥርዓት” የሚል ነበር፡፡ የክፍል ጓደኞቼን ጥናታዊ ጽሑፎችን ሲያርም የእኔን ግን

ሳያርም እንዳለ ነበር የመለሰልኝ፡፡ ነገሩ አፍንጫ ሲመታ ዐይን ያለቅሳል መሆኑ ገባኝና የወረወረልኝን የማይገባኝን ዝቅተኛ ማርክ ተቀብዬ፣ ንዴቴን ውጬ ያለፍኩት ጉዳይ ነበር፡፡ ይህ የሆነው ደቡብ አፍሪቃ ከመሄዴ ልክ ከሠላሳ ዓመት በፊት ነበር፡፡

ኬፕ ታውን ውስጥ የሚኖሩ ከአገራችን የፈለሱ ጥቂት ስደተኞች ነበሩ፡፡ ሁለቱ በምመላለስበት የእግር ጎዳና፣ ለንግድ በተፈቀደ ስፍራ፣ የአገራችንን የባሕል እቃዎች ቸርቻሪዎች ነበሩ፡፡ ብዙ ጊዜ እንገናኝ ነበር፡፡ የስደተኞቹ አላማ ደቡብ አፍሪቃን መቆያ አድርጎ ወደ አውሮፓ፣ አሜሪካ ወይም አውስትራሊያ ለመሸጋገር ነበር፡፡

ወደ ደቡብ አፍሪቃ ከመምጣቴ ከጥቂት ወራት በፊት ለሥራ ጉዳይ ሉሳካ፣ ዛምቢያ፣ ሄጄ በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያውያን ወኅኒ ቤት ውስጥ አሉ ሲባል ሰምቼ ልጠይቃቸው ሄድኩ፡፡ ቁጥራቸው አምስት ያህል ነበር፡፡ ወህኒ ቤቱ የሰው ማስፈሪያ ሳይሆን የአውሬ ጉሮኖ ይመስል ነበርና በጣም አዘንኩላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ወጣት በያለበት ተበትኖ ሲንከራተትና ሲያንቆራጥጡት ማየት የማይሽር ጠባሳ አእምሮ ውስጥ የሚተው ጉዳይ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከየት ነው የመጣችሁት? ምን አጥፍታችሁ ነው እዚህ ያስገቧችሁ? ብዬ ጠየቅኋቸው፡፡ "ድንበር እያሳበርን ወደ ናሚቢያና ደቡብ አፍሪቃ ልንገባስንል ተያዝን፤ የአገራችን ሁኔታ ምኑም ስላላማረን ዕድላችንን ለመሞከር የወጣን ነን፤ ሌላ የሚቀበላችሁ አገር ካላገኛችሁ ወደ አገራችሁ ትጋዛላችሁ ብለውናል፤ ብዙዎቻችን ለመመለስ በፍጹም ፈቃደኛ አይደለንም፤ መመለስ የሚፈልጉትን በተመለከተ የዛምቢያ መንግሥት የበጀት እጥረት ስላለበት ለአየር መጓጓዣ የሚከፈል ገንዘብ እስኪሰበሰብ ድረስ እዚሁ እንድንማቅቅ ተፈርዶብናል" ብለው ነገሩኝ፡፡

በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ አበሻ የሌለበት አገር አይገኝም ይባላል፡፡ እኔም እንደተባለው ሳይሆን አይቀርም ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህን አስመልክቶ መስኮብ ውስጥ የተማረ አንድ ወዳጄ የሚከተለውን ነገረኝ፡፡ አንድ ጊዜ

ኦስተንዴ፣ ቤልጅግ፣ ሄዶ ሳለ ባቡር ጣቢያ ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ የሚመስል ሰው ያያል፤ ማንነቱን ለማወቅ ይፈልግና ይጠጋዋል፡፡ ኢትዮጵያዊን ለመለየት ብዙም ከባድ አይደለም፤ አንድ ሰው ማድረግ ያለበት አንገቱን ትንሽ ጎንበስ ማድረግ ብቻ ነው፤ ሰውዬው አጸፋውን ከመለሰ ማንነቱን ነገረ ማለት ነው፡፡ አንገት ተቀለባብሰው ከተዋወቁ በኋላ፣

“ወንድሜ፣ እዚህ ነው የምትኖረው?” ብሎ ይጠይቃል፣ ወዳጄ፤

“አይ አይደለም፣ የምንኖርበትን አገር ስሙን ብነግርህም የምታውቀው አይመስለኝም” ይለዋል፡፡ ወዳጄ የዓለምን ካርታ ጠጥቼዋለሁ የሚል ዓይነት ነበርና እንዴት ተደፈርኩ? የሚል ስሜት ያድርበታል፡፡

የዓለም ካርታን አስመልክቶ “አቶ ምንተስኖት ነኝና ይልቅስ ንገረኝ” ሲለው

“ቶንጋ” ይለዋል፡፡

“ምን አልክ?”

“አላልኩህም፣ አታውቀውም”

ወዳጄም ቶንጋ የት እንደሚገኝ ከተረዳ በኋላ “ለመሆኑ እዚያ የዓለም መጨረሻ ድረስ ምን ልታደርግ ሄድክ?” ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ የቶንጋ ንጉሥን ልጅ ሆላንድ ውስጥ ይተዋወቅና ፍቅርን ርቀት አያግደውም እያለ እየዘፈነ መክነፉን ገለጸለት፡፡ ሰውዬው ወይም ዝርያው በቶንጋ አልጋ ከወረሰ በእስር ቤት ከመማቀቅ ወይም እንደኔ ዓይነቱ ሳይፈልጉት በሰው አገር ሙጭጭ ብሎ ከመጎለት የአገር ልጅ ወደነገሠበት መሄድ ሳይሻል አይቀርምና ወደ ውድ እናት አገራችን እስክንመለስ ድረስ እንደወጣን ውጭ የቀረን ኢትዮጵያውያን ቶንጋን በልባችን እንያዝ፡፡ የቶንጋ ሰዎች መደበኛ ምግባቸው የአሳማ ሥጋ ስለሆነ ወደ ቶንጋ መፍለስ የሚፈልግ የኦርቶዶክስ ክርስትያንና የእስላም ሰራዊት ሥነልቦናዊ ዝግጅት ያድርግ፤

የእስራኤል ልጆች የኢያሪኮ ከተማን ለመውረር ሲተምሙ ጥም አሸንፎት ውሃ በሁለት እጁ ሲጠጣ የተገኘ ወታደር ወደኋላ እንደመለሱት ሁሉ የአሳማ ሥጋ ሃራም ወይም እርም ነው፣ አልበላውም የምትል ኢትዮጵያዊ በየቤትህ አርፈህ እንድትቀመጥ።

እነኃይሌ ገብረሥላሴና ደራርቱ ቱሉ ኬፕ ታውን አጠገብ በሚገኘው የዩኒቨርስቲ ከተማ በሆነው በስቴልንቦሽ በዓለም አገር አቋራጭ ሩጫ እአአ በሜይ 1996 የተወዳደሩ ዕለት ኬፕ ታውን ውስጥ የሚገኙት ስደተኞች አትሌቶቻችንን ሲያበረታቱ ውለዋል። እዚያ የነበረው ተመልካች በአድናቆት ሲመለከት የዋለው ሯጮቹን ብቻ ሳይሆን በቁጥር ጥቂት ቢሆኑም በድጋፋቸው ጥንካሬ ግን እዚያ ከነበረው ሁሉ ይበልጡ የነበሩትንና አረንጓዴ ብጫ ቀዩ ባንዲራችን የሚያውለበልቡትን ኢትዮጵያውያንንም ነበር። "በነጻነታችን ኮርተን የኖርን፣ ቅስማችን ያልተሰበረ ጥቁሮች አርማችንን ተሸክመን ለዘረኞች ቅዱስ፣ ለጥቁሮች ግን ርኩስ ወደሆነው፣ ለአፓርታይድ ሥርዓት ጠበቃና ጋሻ ጃግሬ ወደ ነበረው ወደ ስቴልንቦሽ ዩኒቨርስቲ ሜዳ መጥተናል፤ የኢትዮጵያ ምርጥ አትሌቶችም በዘረኞች ቤተመቅደስ ውስጥ የድል አቧራ እንደዕጣን አጭሰው በጥቁር ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ላይ የተሠራውን ግፍና በደል ለመበቀልና የአሸናፊነት አርማ ከፍ አድርገው ለማውለብለብ ተዘጋጅተዋልና ዘረኛ ጉድህ ፈላ" እያሉ የሚዘምሩ ይመስል ነበር።

ከውድድሩ በፊት አትሌቶቻችንን የመተዋወቅ ዕድል አግኝቼ ነበር። በተለይ ኃይሌና ደራርቱ ከአእምሮዬ አይጠፉም። ኃይሌ በራሱ ላይ በጣም የሚተማመንና ጭንቀት ሲያልፍ የማይነካው ሰው እንደሆነ ተመለከትኩ። ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት የምታሸንፍ ይመስልሃል? ብዬ ጠይቄው ነበር። ምንም ሳይወላውል "አላሸንፍም" ብሎኛል። አንድ ተወዳዳሪ እንዲህ በግልጽ ሲናገር ሰምቼ አላውቅም ነበርና ለምን እንዲህ አልክ? ብዬ ጠየቅሁት። "እንደምታየው እኔ አጭር ነኝ፤ ሜዳው ወጣገባነት አለው፤ እንዲህ ዓይነቱ የውድድር ስፍራ የሚቀናው ረጅም ቅልጥም ላለው ተወዳዳሪ ነው፤ እኔ

የምሮጠው ለልምዱ ስል ነው» ብሎኝ ነበር፡፡ በውድድሩ በእርግጥም ቅልጥማሙ የኬንያው ፖል ቴርጋት ሲያሸንፍ ኃይሌ ሦስተኛ የወጣ ይመስለኛል፡፡

በቀኑ የነበረው አስገራሚ ትዕይንት ደራርቱን የሚመለከት ነበር፡፡ እንደተለመደው እውነተኛው የሴቶች ውድድር በእኛና በኬንያ አትሌቶች መካከል የተደረገው ነው፡፡ የሁሉም ተመልካች ዐይን ሚከተለው እነሱን ነበር፡፡ ደቡብ አፍሪቃውያኖች ተስፋ የጣሉባት አንዲት ነጭ ነበረቻቸው፡፡ ጥቂት ዙሮች ከተሮጠ በኋላ ኬንያኖቹ ደራርቱን መሀል አስገብተው መንገድ ይዘጉባታል፡፡ ጥቂት ቆይቶም ከኋላ የምትከተላት ኬንያዊት ቁርጭምጭሚቷ ላይ ትረግጣታለች፡፡ ደራርቱ ትወድቃለች፤ ጫማዋም ይወልቃል፡፡ ተነስታ ጫማዋን ፍለጋ ወደኋላ ስትሄድ ከኋላ ተንደርድረው የሚመጡት ሊረጋግጧት ሲሉ እንደምንም መከላከል ቻለች፡፡ የቅርብ ተወዳዳሪዎቿ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎቹም ጥለዋት ያመልጣሉ፡፡ የተመልካቹ ትኩረት ከሯጮቹ ወደ ደራርቱ ዞረ፡፡ እንደኔው በተመልካቹ አእምሮ ይጉላላ የነበረው ደራርቱ የሴት እንባዋን ረጭታ፣ የአርሲዋ እመቤት የኬንያኖችን ድራሽ እንድታጠፋ ተማጽና ወደመልበሻ ክፍል ማምራቷ አይቀርም የሚል ነበር፡፡ ቀጥሎ የታየው ተአምር ግን የሚታመን አልነበረም፡፡ ጫማዋን በፍጥነት አጥልቃ እንደንፋስ መንጎድ ጀመረች፡፡ በጣም ረጅም ርቀት ጥላዋት ቢሄዱም ተስፋ ሳትቆርጥ ሩጫውን ቀጠለች፡፡ መጨረሻ ሆና የነበረችው ደራርቱ አራተኛ ወይም አምስተኛ ለመውጣት በመቻሏ ተመልካቹ ሁሉ በጣም ተደነቀ፡፡ መድረሻው መስመር ላይ ለጥቂት ቀድማ የገባችው የስታድዮሙ ሕዝብ ተነስቶ ሲያበረታታት የነበረችውን ያቺን ነጭ ደቡብ አፍሪቃዊትን ነበርና የኢትዮጵያ አምላክ «ወድቃ በተነሳቸው ደራርቱ ይገባሃለሁ ቅድሚያ ለደራርቱ» እንዳለና እንዳስቀደማት መሰከርን፡፡ ኬንያኖቹን በተመለከተ ደግሞ ጌጤ ዋሚ ውድድሩን ስላሸነፈች ኢትዮጵያ ያላት ኃይለኛ ጠባቂ አምላክ ብቻ ሳይሆን ተበቃይ ልጆችም እንደሆነ ዓለም መሰከረ፡፡

ውድድሩ ተጠናቆ ከየአገሩ የመጡት አትሌቶች ወደየተመደቡላቸው አውቶቡሶች ሲሰማሩ ደራርቱ እንኳን ልትራመድ መቆምም ስለተሳናት ወንዶቹ የትግል ጓዶቿ አውቶቡስ ውስጥ ተሸክመው አስገቧት፡፡ ለካስ ከወደቀችበት እንደዚያ አስፈንጥሮ ያስሮጣት እልህና ወኔ ነበር እንጂ እንደቁስሏማ ቢሆን ኖሮ መነሳት የነበረባት በወሳንሳ ነበር፡፡

አትሌቶቻችን ካረፉበት ሆቴል እስከ መወዳደሪያው ስፍራ አብሬ ሄጄ ስለነበር የተመለስኩትም አብሬ ነው፡፡ ደራርቱ ላይ በደረሰው አደጋ ሁሉም አዝኖ የተለመደው የአበሻ ከንፈር መጠጣ ጆሮዬን ሊያደነቁረው ነው ብዬ ስጠብቅ ምንም ነገር ያልተፈጠረ ይመስል ጨዋታውና ቀልዱ ደራ፡፡ የትዕይንቱ ኮከብ ተዋናይና መሪ እራሷ ደራርቱ ሆና ቁጭ አለች፡፡ ሴቶቹ አትሌቶች ግማሾቹ በስተራስጌ ተቀሩት በስተግርጌ ሆነው እራስዋንና ጉንጯን ይደባብሳሉ፣ ቁስሏን ያሻሻሉ፣ ወንዶቹ ደግሞ የኋላ ደጀን ሆነው ይመለከታሉ፡፡ በጨዋታ ጣልቃ እያስገቡ የሚወያዩት ወደፊት ስለሚጠብቋቸው ውድድሮች እንጂ በደራርቱ ላይ ስለደረሰው ጊዜያዊ ችግር አልነበረም፡፡ ይህም ሲባል በአፋቸው ሳይሆን በድርጊት ትኩረታቸው ሙሉ በሙሉ ደራርቱ ላይ ነበር፡፡ አንድ የእርግማን፣ የስድብ ወይም የቁጣ ቋንቋ አልሰማሁም፡፡ ኬንያኖቹን ሲወቅሱ አልሰማሁም፡፡ የአትሌቶቻችንን የማሸነፍ ምስጢር ደረስኩበት፡፡ ያ የታወቅንበት ለራስ የማዘን በሽታ ከአገር ከወጣሁ በኋላ በአዋጅ ታገደ እንዴ? ብዬ እራሴን ጠየቅሁ፡፡ በአየር ጠባይና ምግብ ማመካኘት እንዲሁም የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ብሎ ማሳበብ ቀረ ማለት ነዋ አልኩ፡፡ ጽኑ አላማ ላለው ሰው ለራስ እንደማዘንና ለሽንፈት ሰንካላ ምክንያት እንደመስጠት መጥፎ ነገር የለም፤ ያሽመደምዳል፡፡ አንድ ሰው ችግር ሲደርስበት ፕሮብሌም ለመፍታትና የሕይወትን ፈተና ለማለፍ ዕድል እንደተሰጠው አድርጎ ከቆጠረው ችግርን እንዳመጣጡ ተቀበሎ ማስተናገድ ስለሚችል የተለመው ዓላማ ለመሳካት ያለው ዕድል ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶቻችን በጎ መንፈስ ተላብሰው ወደፊት ስለሚጠብቃቸው ትግል ሲወያዩ ስሰማ በጣም ደስ አለኝ፡፡ ይህ አመለካከት በሁሉም

ኢትዮጵያዊ አእምሮ ውስጥ ሰርጾ ገብቶ ከሆነ የአገራችን የወደፊት ዕድል አስተማማኝ መሠረት ተጥሎለታል ብዬ ተከራራሁ::

የኢትዮጵያ ልጆች በአንድ ጀምበር በደልንና ዘረኝነትን ድል መትተው ወደ አገራቸው ተመለሱ:: ደቡብ አፍሪቃን ለቅቄ ወደ ካናዳ ከተመለስኩ በኋላ ኃይሌ ገብረስላሴ “ይቻላል” የሚለውን መፈክር ሁሉም እንዲያነግበው ግራና ቀኝ አደለው መባሉን ስሰማ “ገና ምን ዐይተን፣ ሎጋው፣ ያብባል ገና” ብዬ ከሩቁ አጅቤአለሁ::

ሰኞ ጠዋት ቢሮ ስገባ ደቡብ አፍሪቃውያኑ በአድናቆት ሲያወሩ የነበረው የደራርቱን ጀብድ ነበር:: ፕሮግራሙ በቴሌቪዥን መተላለፉንና በመላው ደቡብ አፍሪቃ መታየቱን ተረዳሁ::

ወደ ደቡብ አፍሪቃ ስለወሰደኝ ተልእኮ ስንመለስ፣ በደቡብ አፍሪቃ ላይ ተጥሎ የነበረው የኤኮኖሚ ማእቀብ በመነሳቱ ዋናው ተጠቃሚዎች ተጨቋኞቹ ጥቁሮቹ ሳይሆኑ ጨቋኞቹ ነጮች እንደሆኑ ወለል ብሎ ታየኝ:: በማእቀብ ምክንያት ከውጭው ዓለም ጋር የነበራቸው ግንኙነት ውስን ሆኖባቸው የነበሩት ነጮች በመላው ዓለም ተሰራጭተው የመሥራት፣ የመነገድና ኢንቬስት የማድረግ ዕድላቸው እንደሰፋላቸው ተመለከትኩ:: ጥቁሩን ከተዘፈቀበት አዘቅት ውስጥ ለማንሳት የሥልጠና፣ የሥራና የትምህርት ዕድል እንዲሁም የጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ተጨማሪ ታክስ ይጣል ቢባል ነጮቹ ሞተን እንገኛለን ይሉ እንደነበር ተመለከትኩ:: በጥቁሮች ላይ የተፈጸመው በደልና ግፍ የዘረኞችን ኅሊና እንደማይኮሰኩሰው አየሁ:: ተምረናልና ሥልጣን ይገባናል የሚሉትን ጥቁሮች አስጠግቶ የምቾት ኑሮን እንዲለምዱና ለሕዝባቸው ሳይሆን ለቀላቢያቸው ጥብቅና እንዲቆሙ ለማድረግ ነጮቹ ሲረባረቡ ዐየሁ:: ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም ቆመናል በሚሉት ላይ የስም ማጥፋት ዘመቻ እንደሚካሄድባቸው ተረዳሁ:: ወሳኝ የሆኑትን የኤኮኖሚው ላእላይ መዋቅሮችን ግን በምንም አይነት ከቁጥጥራቸው ሥር እንዲወጡ ነጮቹ እንደማይፈልጉ ማንም የሚገነዘበው ጉዳይ ነበር:: ባጭሩ፣ የነጻነቱ ትግል

ነጻ ያወጣው ጥቁሮቹን ሳይሆን ነጮቹን እንደሆነ በዐይኔ አይቼ ለመመስከር ዕድል አገኘሁ፡፡

በጥናቱ ማእከል ውስጥ ከተሰጡኝ የሥራ ድርሻዎች አንዱ ድርጅቱ ገንዘብ ከፍሎ የሚያስጠናቸውን ጥናቶች መገምገም ነበር፡፡ የጥናቶቹ ዓላማ ጥቁሩ የኑሮው ደረጃ ከፍ እንዲልና ሥልጣን በእጁ ማስገባት እንዲችል ብቃቱ ከፍ እንዲል በየመስኩ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ለማፋጠን መንግሥትንና ሌሎችንም ለማሳሰብ ነበር፡፡ ጥናቶቹ አብዛኛዎቹ የሚካሄዱት በደቡብ አፍሪቃውያን ፕሮፌሰሮች ነበር፡፡ ሆኖም አብዛኛዎቹ ነጮች በመሆናቸው የሚቀርቡት ጥናቶች ጥቁሮች ያሉበትን አሳፋሪ ሁኔታ ለመለወጥ እንዲቻል ደፋር ወይም ስርነቀል እርምጃ እንዲወሰድ የሚገፋፉ ሳይሆኑ ያለው ሁኔታ Status quo ተጠብቆ እንዲቆይ በተዘዋዋሪ የሚያሳስቡ ነበሩ፡፡ የጥቁሮችን ሁኔታ ለማሻሻል ሲባል የመንግሥት ወጪ ከሚጠበቀው በላይ ቢንር ወይም የነጮች ድርጅቶች ጥቁር ሠራተኞችን በብዛት እንዲቀጥሩ ወይም እንዲያሠለጥኑ ተጽእኖ ቢደረግባቸው ወይም የገቢ ታክስ ቢጨመር ኢንቬስተሮች ይሸሻሉና ጥንቃቄ ይደረግ እያሉ በጥናቶቹ አማካይነት ያሳስቡ ነበር፡፡ የነጻነት ትግል የተካሄደው ጥቁሮች በአገራቸው የበላይነት እንዲኖራቸው ስለሆነ ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ መንግሥት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ አለበት የሚለውን አስተሳሰብ ፕሮፌሰሮቹ በተዘዋዋሪ ለማክሸፍ ይጥሩ ነበር ለማለት ይቻላል፡፡ ዘረኛው የደቡብ አፍሪቃ መንግሥት ላወጣቸው ኢሰብአዊ ሕግጋት ርዕዮተዓለማዊ መሠረት ያደላደሉት ወይም ያስጨበጡት የአገሩ ዘረኛ ፕሮፌሰሮች መሆናቸው ሲታወስ ከነጭ ፕሮፌሰሮች ብዕር ወይም ልሳን የጥቁሮች ትንሣኤ ይሰበካል ብሎ ማመን ዘበት ነው፡፡

ሚስተር ኖምቬቴ አንድ ቀን ቢሮው ድረስ ይጠራኝና "እገሌ የሚባለው የስቴልምቦሽ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰር ያደረገውን ጥናት አስመልክቶ በጽሑፍ የሰጠኸውን አስተያየት ለፕሮፌሰሩ አሳይቼው ነበር፤ ታደሰ ተስፈንጣሪ ነው አለኝ ብሎ ነገረኝ፡፡ በተጨማሪም ሚስተር ኖምቬቴ "ከውጭ የማገኘው

እርዳታ ስለመነመነ ፊቴን ወደ አገር ውስጥ ድርጅቶች ለማዞር ተገድጃለሁ" ማለት ከጀመረ ውሎ አድሮ ነበር። ይህ ማለት ከነጮች ጋር እርቀ አውርዶ እሱ የሚመራው ድርጅት የነጮችን ጥቅምና የበላይነት በማይጻረር መልኩ መምራት እንደሚጠበቅበት ተገንዝቦ ነበር ማለት ነው። ስለሆነም፣ ሽንጥን ገትሮና አፍ ሞልቶ "የቆምኩት የጥቁሮችን መብት ለማስከበር ነው" የሚለው መፈክር አትራፊ ሆኖ ስላልተገኘ ወደጎን ተደረገ።

የተዳከመው የድርጅቱ ሥራ የሚያንሰራራበትን መንገድ በመፈለጉ ላይ የበኩሌን አስተዋፅኦ ማድረግ አለብኝ በሚል እምነት ተገፋፍቼ ማእከሉ የተሻሻለ የጥናት ዕቅዶች ማጎደር አጠናቅሮ ለዓለም አቀፍና ለአህጉራዊ እርዳታ ሰጭ ድርቶች እንዲያሰራጭ ሐሳብ አቀረብኩ፤ በዚህ ረገድ ከኔ የሚጠበቅ ነገር ካለ ለመተባበር ዝግጁ መሆኔን ገለጽኩ። ይህ የሆነው የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ ለመገምገም በተደረገ ስብሰባ ላይ ነበር። ድርጅቱ በቋፍ ላይ መሆኑ አጠያያቂ አልነበረም። "ስማ፣ ታደሰ" አለኝ ሚስተር ኖምቬቴ፣ "እሱን የራስህ የሆነ ድርጅት ስታቋቁም ትደርስበታለህ" አለና ለማገልገል በተሟሟቀው ስሜቴ ላይ ውሃ ቸለሰበት። ሦስት ሳምንት ያህል ቆይቶ አንድ ቀን ቢሮዬ ብቅ አለና "ያኔ ያቀረብከውን ሐሳብ በሐሳቤ ሳወጣውና ሳወርደው ሰነበትኩ፤ ያልከው ትክክል መሆኑን አሁን ደርሼበታለሁ፤ ለምን አሁን አንድ ነገር አናደርግም?» አለኝ። በማናለብኝነት ያፈሰሰውን ሐሞቴን አፍሼ የማነሳበት ጥበብ እንዳልታደልኩ ለመረዳት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም።

ስድስት ወር ከሠራሁ በኋላ ሚስተር ኖምቬቴ "የውጭ እርዳታ ስለተቋረጠብኝ ላቆይህ አልችልም" ስላለኝ በመስከረም 1989 ወይም እአአ በሴፕቴምበር 1996 ወደ ኦታዋ ተመለስኩ። ወቅታዊው ትግሌ ዘረኞች ለቀበሩት መርዝ መድኃኒት መፈለግ መሆኑ ቀርቶ ከኑሮ ባላንጣዎች፣ ከእነቤት ኪራይ ክፍያና ፈጣሪ የከፈታቸውን ሰባት ጉሮሮዎች ከመሙላት ጋር ሆነ።

እአአ በጃንዋሪ 1997 የዓለም አቀፍ ገንዘብ ድርጅት IMF ለዐሥራ ስምንት ቀን ሥራ ወደ ጋቦሮኔ፣ ቦትስዋና ላከኝ:: የሄድኩት ከIMF ቡድን ጋር ተለጥፌ ነበር:: የቡድኑ መሪ ፒዬሮ ኡጎሊኒ ይባላል::

በጋቦሮኔ ከተማ የሚኖሩ ጥቂት ኢትዮጵያውያንን አገኘሁ:: በአገሩ የUSAID ተጠሪ ዜግነቱ አሜሪካዊ በትውልድ ግን ኢትዮጵያዊ ነበር:: የኢትዮጵያ ፓስፖርት የያዙት ደግሞ በዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰርነት፣ በመንግሥት አማካሪነትና በኮንሰልታንትነት የሚሠሩ ነበሩ:: በሥራቸው ደስተኞች ቢሆኑም የአገሬው ሰዎች ለአስተዋፅኦዎቻቸው ተገቢውን ዋጋ የማይሰጡ ስለሚመስላቸው ቅሬታ እንደነበራቸው ተገነዘብኩ::

ቦትስዋና አልማዝ በብዛት እያመረተች ስለምትሸጥ በአፍሪቃ ደረጃ ሀብታም ናት:: በቦትስዋና ሰዎች አመለካከት ሌላ አፍሪቃዊ ወደ አገራቸው የሚመጣው ለሀብት ሽሚያ ስለሆነ ባዳን ፊት የመንሳት አዝማሚያ አለ:: ይህ ዝንባሌ ብዙ አገር ውስጥ ያለ ነው:: ሊብያኖች የውጭ አገርን ሰው፣ በተለይም ጥቁር አፍሪቃዊን የሚያንቋሽሹትና የጎሪጥ የሚያዩት አንድም ከቤንዚን ሽያጭ የተገኘውን ገንዘባቸው ሊቀራመት እንደመጣ አድርገው ስለሚያዩት ነው:: ሌላው ቀርቶ ናይሮቢ ውስጥ ለኢትዮጵያውያን የሚሠሩ አንዳንድ የቤት ሠራተኞች ከአሠሪዎቻቸው ጋር ሲጣሉ "እናንተ ኢትዮጵያውያን፣ የማናውቃችሁ ሆነን ነው እንዲህ የምትንቀባረሩብን?! ከአገራችሁ ችግር ያባረራችሁ መናጢ ድሆች እዚህ መጥታችሁ አለፈላችሁ" እንደሚሉ ከአንዴም ሁለቴ ተነግሮኛል::

በጋቦሮኔ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን እነአቶ ከበደ አሊና ባለቤቱ፣ አቶ ኃይሉ አለማየሁ፣ ዶክተር ብርሃኑ አበጋዝ፣ ኢትዮአሜሪካኑ ጭምር፣ እየተቀባበሉ አስተናገዱኝ:: ከብቸኝነት ጋር ሳልተዋወቅ ወደ "አገሬ" ተመለስኩ::

ከቦትስዋና እንደተመለስን ፒዬሮ አማካሪ ቀጥሮ ወደ ሳሞአ መላክ ለሚፈልግ ለአንድ የIMF ባለሥልጣን እኔ ለሥራው እንደምመጥን ያለውን አስተያየት ይነግረዋል። ሰውዬው በስልክ ቃለመጠይቅ ካደረገልኝ በኋላ እንደሚቀጥረኝ ነገረኝ። ቅጥሩ እውን የሚሆነው ግን የሳሞአ ባለሥልጣኖች ከተስማሙ ብቻ ነው። ቶንጋ ኢትዮጵያዊው ልዑል አጠገብ ለመሄድ ዕድል ገጥሞኝ ነበር ማለት ነው። የሳሞአ መንግሥት አዎንታዊ መልስ ሳይሰጥ ይዘገያል። በተደጋጋሚ ማስታወሻ ቢላክለትም ባለሥልጣኖቹ ገና አልወሰንም እያሉ ጉዳዩን አስተኙት። በመጨረሻ ቁርጡን ካልነገራችሁን እርዳታውን እንደሌለ ቁጠሩት ሲባሉ "ስሙን የላካችሁልን አማካሪ እኛ የምንጠይቀውን የብቃት መለኪያ የሚያሟላ ስላልሆነ አንቀበለውም፤ ሌላ የሚያሟላ ላኩልን" ብለው መለሱ። እናንተ የምትፈልጉት አማካሪ ምን ምን አሟልቶ የተገኘ መሆን አለበት? ተብለው ቢጠየቁ መልስ አልነበራቸውም። የምትፈልጉትን ካላወቃችሁ የእርዳታ ጥያቄያችሁ ውድቅ ተደርጓል ተብለው ተነገራቸው። ዋሺንግተን ወርጄ ሳለ በስልክ ቃለመጠይቅ ያደረገልኝን ባለሥልጣን "ለመሆኑ እኔን አንቀበልም ያሉበት እርግጠኛው ምክንያት ምን ይመስልሃል?" ብዬ ጠየቅሁት። "እንዲህ ዓይነቱን ምስጢር ለውጭ ሰው መንገር ክልክል ነው፤ ነገር ግን አንተን በተመለከተ የወሰዱት አቋም እኛንም በጣም ስላስቆጣን ሳልደብቅ ልንገርህ፤ ሊቀበሉህ ያልፈለጉት ከአፍሪቃ የመጣህ ጥቁር ስለሆንክ ነው" ብሎ ፍርጥርጥ አድርጎ ነገረኝ።

ከቦትስዋና መልስ አንድ ዓመት ሙሉ ሥራ ብፈልግም እስኪ ብቅ በልና ኢንተርቪው እናድርግህ የሚለኝ ካናዳዊ ድርጅት አሁንም ጠፋ። የኑሮ ችግርም እየጠና ሄደ። ይህም ሲባል ልጆቼ በትምህርታቸው ወደኋላ እንዳይቀሩ ማበረታታቱን ቀጠልን። ተመልሼ በዳረጎት ሰጭዎች እጅ ብወድቅ እዚያው ተቀርቅሬ እቀራለሁ የሚል ከፍተኛ ፍራቻ ስላደረብኝ እየተራብንም ቢሆን ጊዜውን ለመግፋት ወሰንን። ገንዘብም ከሰው ተበደርን። አመለካከታችንን በትክክል ያልተረዱልን አንዳንድ ሰዎች "ተቸግረውም ከሆነ ጥፋቱ የራሳቸው ነው፤ መንግሥት ቀለብ

ሊሰፍርላቸው፣ የቤት ኪራይ ሊከፍልላቸው ሲችል ኮርተው እምቢ ብለዋል» ይሉን እንደነበር ሰማን። የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚያስችለኝ እውቀትና የሥራ ችሎታ እያለኝ በዚህ ለጋ ዕድሜዬ እጅ አልሰጥም ማለቴ እውነት ነው። የተሻለ ነገር መመኘት ኀጢአት አይደለም፤ ሁሉም የሚጥረውና የሚግረው የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው፤ ይህ ባይሆንማ ኑሮ ሰው ሁሉ ከመሬት ባልተነሳም ነበር።

በችግር ላይ ችግር እንዲሉ የዕፀገነት ታላቅ እህት፣ የልብ ጓደኛ፣ መካሪና፣ አማካሪ፤ የጓደኛዬ የስሜ ባለቤት፣ የምናሳድገው ልጃችን የግሩም እናትና ለኔ ደግሞ ጠባቂ እህቴ በመስከረም 1990 አረፈችና ሁሉም ነገር ዙሪያው ገደል ሆነብን። አሳመረች ለእኔና ለዕፀገነት ስንቸገር የምትደርስልን፣ ስንከፋ አይዟችሁ የምትለን፣ ስንኮራረፍ የምታስታርቀን ታላቅ እህታችን ነበረች። ቀደም ብሎም የቅርብ ጓደኞችንና ሚዜያችን አስፋው አገኘሁ እንደዚሁ ተለይቶን ስለነበር ከሩቁም ቢሆን አይዟችሁ የሚል ዘመድና ወዳጅ ሲመናመንና ባለንበት ባዕድ አገር ሥራው ሲጠፋ ተስፋችን ጨልሞ ታየን። ቢሆንም ተስፋ ሳንቆርጥ ጥረታችንን እጥፍ ድርብ ማድረግ እንዳለብን ተስማማን።

አሳመረች ከማረፏ ቀደም ብሎ ዋሺንግተን ወርጄ ሥራ ለማፈላለግ ቀጠሮዎች ይዤ ነበርና ዕፀገነትን ሐዘንዋን ሳታበርድ ትቻት ተነስቼ ወረድኩ። ካነጋገርኳቸው መካከል፣ የዓለም ባንክ ኃላፊዎች እንደሚቀጥሩኝ ፍንጭ ሰጡኝ፤ ኦታዋ ተመልሼ ጥሪያቸውን እንድጠባበቅ፣ ለፎርማል ኢንተርቪው እንደምጠራና የአየር መጓጓዣ ቲኬት እንደሚላክልኝ ተነገረኝ። ጥሪው ከዛሬ ነገ ይመጣል እያልኩ ሰነበትኩ። ጥሪው የዘገየው የዓለም ባንክ ቢሮክራሲ የተንዛዛ በመሆኑና የፈረንጆች የገናና የአዲሱ ዓመት በዓል በመቃረባቸው በእንጥልጥል የቆዩ ጉዳዮችን ወደሚቀጥለው ዓመት የመግፋት አዝማሚያ ያይል ስለነበር ነው። ከዋሺንግተን በተመለስኩ በሦስተኛው ወር፣ ማለትም በጥር 1990፣ እአአ በጃንዋሪ 1998፣ ከ IMF ይደወልና ለአምስት ሳምንት ሥራ ሞንሮቪያ፣ ላይቤርያ፣ ለመሄድ ፈቃደኛ

እንደሆንኩ እጠየቃለሁ፡፡ ጠያቂዬ ፒዬሮ ነበር፡፡ ከመቅጽበት "በደስታ" ብዬ መለስኩለት፡፡

# ላይቤርያ

እአአ በ1978 የተደረገው የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ጉባኤ የተካሄደው በላይቤርያ፣ ሞንሮቪያ ከተማ ነበር፡፡ የላይቤርያ መንግሥት ጉባኤው የተዋጣለት ነበር እንዲባልለትና ዝናን ለማትረፍ ፈልጎ ሁለት ትላልቅ ሆቴሎች፤ የመሪዎች መኖሪያ ሰፈር፣ መንገድና ትልቅ የጉባኤ አዳራሽ አሠራ፡፡ ወጪው የተሸፈነው ከውጭ በተገኘ ብድር ጭምር ነበር፡፡

በላይቤርያ የሕዝቡ መደበኛ ምግብ ሩዝ ነው፡፡ ምርቱ በአገር ውስጥ የሚመረት ሳይሆን በውጭ ምንዛሪ የሚገዛ ነው፡፡ ዋጋውን ከሕዝቡ የመግዛት አቅም ጋር ለማመጣጠን መንግሥት ድጎማ ያደርጋል፡፡ የመሪዎቹ ጉባኤ የመንግሥትን ካዝና ያራቁትና በጀት ለማስተካከል ሲል መንግሥት የሩዝ ዋጋ ድጎማ ይቀንሳል፡፡ ሕዝቡ ቅሬታውን ይገልጻል፤ ሰላማዊ ሰልፍ ይደረጋል፡፡ ወታደሩ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ነኝ ብሎ ይነሳል፡፡ የዐሥር አለቃ ሳሙኤል ዶ የቶልበርትን መንግሥት ይገለብጥና በሥልጣን ኮርቻ ይፈናጠጣል፡፡ ቶልበርትና ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸው ይረሸናሉ፡፡ ዶና ጭፍሮቹ ባለማወቅ ወይም የግል ጥቅምን በማስቀደም የነበረውን ሥርዓት ያፈራርሳሉ ወይም ያሽመደምዳሉ፡፡ ብዙ ሰው፣ በተለይም የተማረውና ባለሙያው፣ አገር ለቆ አሜሪካ ይገባል፡፡ የኤኮኖሚው ቀውስ ይባባሳል፤ ማጠፊያው ያጥራል፡፡

ላይቤርያ በብዙ መንገድ ለአሜሪካኖች ጠቃሚ አገር ነበረች፡፡ የስለላ ማእከል ናት፤ የአሜሪካ ፕሮፓጋንዳ አስተላላፊ ናት፤ የተወርዋሪ ግብረኃይል ማስፈሪያ ናት፤ የጦር መርከብ ማስጠጊያ ናት፤ ኮምዩኒዝምን ለመቋቋም በሚደረገው ትግል ደጀን ናት፡፡ ስለሆነም በትረ ሥልጣን ማንም ይጨብጥ ማን የአሜሪካ ጥቅም እስከተጠበቀ ድረስ አሜሪካኖች በሥልጣን

ላይ ካለው መንግሥት ጋር ይተባበራሉ፣ ከዚህም አልፎ መንግሥቱ እንዳይዳከምና ሥልጣኑን ተቀናቃኝ እንዳይነጥቀው ባላቸው መሣሪያ ሁሉ ድጋፍ ይሰጣሉ። ዶ ቶልበርትንና ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን አጨድክ ተብሎ አውላላ ሜዳ ላይ አልተጣለም፤ በሁለቱ አገሮች መካከል የነበረው የዲፕሎማቲክ ግንኙነት አልተቋረጠም። እንዲያውም አሜሪካኖች ለላይቤርያ የሚያደርጉትን እርዳታ ጨመሩ። የበጀት ጉድለት ማሟያ ከIMF ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በብድር መልክ እንዲያገኙ አሜሪካኖች ረድተዋቸዋል። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ዋናው ታሳቢ ከአሜሪካ ጋር ግንኙነት ያለው መንግሥት ለአሜሪካኖች ጠቃሚ ነው? ወይስ አይደለም? ነው እንጂ ስለዴሞክራሲ፣ ሰብኣዊ መብት፣ ጂኒጃንካ የሚለፈፈው የአስመሳዮች ቲያትር ነው። ላይቤርያ ጥሩ ማስረጃ ናት። እዚህ ነጥብ ላይ እንደገና እንመለስበታለን።

ላይቤርያን የቆረቆሩት አሜሪካኖች ናቸው። ከ175 ዓመት በፊት የአሜሪካ መንግሥት በባርነት ይተዳደሩ የነበሩ ጥቂት ጥቁሮችን በመርከብ ጭኖ አምጥቶ አሁን ሞንሮቪያ በተከተመችበት የባሕር ዳርቻ ያራገፋቸዋል። በካርታ ላይ ላይቤርያ የሚባል አገር ይስልና ለአውሮጳ መንግሥታት ያሳውቃል። እነፈረንሳይና እንግሊዝ አካባቢውን ሲቀራመቱት ላይቤርያን አልነኳትም።

ከአሜሪካ ወደ አፍሪቃ የተመለሱት ጥቁሮች እነማን ናቸው? ለሚለው መልሱ በውል አይታወቅም። አንዱ መላምት እንደሚለው ከሆነ በስንፍናቸውና በወንጀለኛነታቸው ተለይተው የታወቁትን አስቸጋሪ ባሮች የአሜሪካ መንግሥት በግዛቱ ውስጥ ከያሉበት ሰብስቦ በመርከብ ጭኖ ወደ አፍሪቃ ወስዶ እንዳራገፋቸው ነው። ሌላው መላምት የሚለው ደግሞ የጊዜው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ሞንሮ ከአንዲት ጥቁር ይወልዱና፣ ድርጊታቸው እንዳይታወቅባቸው ክልሶቹን ልጆቻቸው ከአጠገባቸው ለማባረር ስልት ሲያውጠነጥኑ ባሮችን ወደ አፍሪቃ መመለስ የሚለው ሐሳብ እንደመጣላቸው ነው።

ከአሜሪካ የተመለሱት ጥቁሮች ዐይን ካልከፈተው ያገሬው ሰው ጋር ሲነጻጸሩ የተሻለ ንቃት ወይም ጮሌነት ስለነበራቸው ከነጮች ስለባርያ አገዛዝ የተማሩትን ሳይውል ሳያድር በተግባር አዋሉት። ከአሜሪካ ላይቤርያ ወደተባለው አገር የተመሱት ጥቁሮች ቁጥራቸው ከጠቅላላው (የላይቤርያ) ሕዝብ ከአምስት በመቶ ባይበልጥም ልዩ ልዩ ስልት በመጠቀም የዋሁን ነባር አፍሪቃዊ በገዛ አገሩ ባሪያ አድርገው ባናቱ ላይ ተፈናጥጠው ተቀመጡበት። ተባብሮ እንዳያስወግዳቸው በከፋፍለህ ግዛው ስልት በመጠቀም ለመቶ ዓመት ያህል ረግጠው ገዙት። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ በጄኔቫ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ ሲቋቋም ባርነትን ካገራችሁ ካላስወገዳችሁ በቀር የማኅበሩ አባል መሆን አትችሉም ስለተባሉ ለይስሙላ እሺ ቢሉም ከውጭ የመጡት የበላይ፣ ያገሬው ሰው የእነሱ አገልጋይ ሆኖ ቀረ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ያገሬው ሰው በሞንሮቪያ ከተማ መሬት እንዳይገዛ ክልክል ነበር። ያገሬው ልጆች በዩኒቨርስቲ ገብተው መማር አይችሉም ነበር።

ላይቤርያ እንደገባሁ አትኩሮቴን ከሳቡት ነገሮች መካከል አንዱ በአለቃና በበታች ሠራተኛ መካከል የነበረው ግንኙነት ነበር። ለእያንዳንዱ ባለሥልጣን ከመኪና ሲወርድ በር የሚከፍቱለት፣ ቦርሳውን ተቀብለው የሚያንጠለጥሉለት፣ ከፊት ፊት እየተራመዱ ሰውን ገለል የሚያደርጉለት፣ መቀመጫ ወንበሩን የሚያመቻቹለት፣ በቢሮው ዙሪያ ተኮልኩለው "ትልቅነቱን" የሚያስመሰክሩለት፤ ደወል ሲደውል ከመቅጽበት አቤት ጌታዬ ብለው ከቸች የሚሉለት፣ ሻይ ወይም ቡና አፍልተው የሚያቀርቡለት በአጠቃላይ ሽር ጉድ የሚሉለት ጥቂት ሠራተኞች ይመደቡለታል። ቢሮው በራፍ ተቀምጦ ደኅንነቱን የሚጠብቅ የክብር ዘበኛ በተጨማሪ ይመደብለታል። የክብር ዘቡ ደረጃው ከሽርጉድ ባዮቹ ከፍ ያለ ነው። እነሱን የሚቆጣጠራቸውና የሚያንቀራጥጣቸው እሱ ነው፤ ወለም ዘለም ያሉ እንደሆነ ወዮላቸው። ለበታች ሠራተኞች የሚከፈላቸው ደመወዝ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ምሳቸውን ሳይበሉ ይውላሉ፤ እርጥባን የሚጥልላቸው ካለ እጅ እጁን ያያሉ። አለቅዬው ግን በመሥሪያ ቤት

ሒሳብ ምርጥ ምግብ ተገዝቶ ይመጣለትና በር ዘግቶ ያጋብሳል። የበታች ሠራተኞች አብዛኞቹ የአገሬው ሰዎች ናቸው። አለቆች ደግሞ አብዛኛዎቹ ከባርነት የተመለሱት ጥቁሮች ዝርያ ናቸው። አሁን በቢሮ አካባቢ የተመለከትኩትና የገለጽኩት ግንኙነት ቀደም ብሎ የነበረው የባሪያና ጌታ ግንኙነት ርዝራዡ ነው።

የ0ሥር አለቃ ዶ መንግሥት ገልብጦ ሥልጣን ለመያዝ ያነሳሳው አንድም የተዋረዱትን የአገሩን ሰዎች ተገቢ ስፍራቸውን ለማስያዝ ነበር። ላይቤርያ ማለት ሞንሮቪያ ብቻ እንዳልሆነች በሚገባ ተገንዝቦ ልማት በገጠር እንዲስፋፋና የትምህርት ዕድል እንዲዳረስ ጥረት አድርጓል። ጥረቱን ተራማጅ ምሁራን ሲደግፉለት ሥልጣን ተቀማን ያሉት አኩርፈው አገር ጥለው ወደ አሜሪካ ኮበለሉ። ውሎ ሲያድር ዶና ጭፍሮቹ በሥልጣን ባለጉ፣ ኤኮኖሚው ተንኮታኮተ፣ አገሪቱ ከውጪው ዓለም ጋር የተፈራረመቻቸውን ልዩ ልዩ ግዴታዎች፣ በተለይም የገንዘብ ክፍያን የሚመለከቱትን፣ መወጣት አቃታት።

ዶ ፕሬዚዳንት ሆኖ የመንግሥት እቃ ግዢ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ቻርለስ ቴለር ነበር። ቻርለስ ዝርያው ከአሜሪካ ከተመለሱት ባሮች ነው። ላልተገዛ እቃ የሐሰት ደረሰኝ በማቅረብ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ይሰርቃል። ወንጀሉን የሒሳብ መርማሪ ይደርስበታል። ሊታሰር ሲፈለግ አምልጦ አሜሪካ ይገባል። በማኩረፍ ወይም ሕይወታቸውን ለማዳን ቀደም ብለው አሜሪካ የገቡት ላይቤርያኖች እንኳን ደኅና መጣህ ብለው ይቀበሉታል። የዶ መንግሥት ሌባውን ያዙልኝ ብሎ የአሜሪካን መንግሥትን ይጠይቃል። ይኖርበት የነበረው የማሳሹሴትስ ግዛት ባለሥልጣኖች ቻርለስን ይዘው ያስሩታል። ወኅኒ ሰብሮ ይወጣል። እንዴት መውጣት እንደቻለ በውል ባይታወቅም ሁለት መላምቶች ግን ይነገራሉ። የመጀመሪያው የሚለው አሜሪካኖች ዶ የሚመራውን መንግሥት ለማስወገድ ስለፈለጉ ቻርለስ ቴለር የፈለጉትን እንዲፈጽምላቸው እንደለቀቁት ነው። ሁለተኛው መላምት ከዚህ የበለጠ ተአማኒነት ያለው

ይመስላል:: ቻርለስ ዶን ለመገልበጥና ሥልጣን ለመያዝ ችሎታው አለው ብለው ያመኑ በአሜሪካ የሚኖሩ ላይቤርያኖች፣ በተለይ ከባርነት የተመለሱት ዝርያዎች፣ ከእስር ቤት አስመለጡት:: ይህን ያደረጉት ወደቀድሞ ቦታቸው የሚመልሳቸው ተቆርቋሪ ወይም የኛ ነው የሚሉት ሰው ያገኙ መስሏቸው ነው::

ቻርለስ በቀጥታ ወደሊብያ ይሄዳል:: ወታደራዊ ልምምድ ያደርጋል:: ሊብያ አፍሪቃን ለማስለም አስፈላጊውን ሁሉ ለማድረግ ከተዘጋጁት የእስልምና ተከታይ አገሮች እንዷ ስለመሆኗ መጠራጠር አይቻልም:: ሊብያኖች ላይቤርያ ገብተው የተቆናጠጡት በዘመነ ዶ ነበር:: ፕሬዚዳንት ሬጋን ፕሬዚዳንት ቀጣፊን ሊገድለው ፈልጎ ትሪፖሊን ካስደበደበ ጀምሮ ሊብያኖች አሜሪካኖችን ለመበቀል ከወሰዷቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ አሜሪካኖች የኛ ነው ወደሚሉት አካባቢ እየሄዱ በልዩ ልዩ ዘዴ ማሸበር፣ ቢቻልም ማስለቀቅ እንደ ዓይነተኛ ዘዴ ይዘውት ነበር ይባላል:: ቻርለስ ወደ ሊብያ የሄደው አሜሪካኖች የኛ ነው ከሚሉት ከላይቤርያ ሊብያኖች አሜሪካኖችን ለማባረር ካላቸው ፍላጎት ጋር የተገናኘ ነው ይባላል:: ቻርለስ የውንብድና ሥልጠናውን እንዳጠናቀቀ ሊብያኖች መሣሪያና ገንዘብ አስታቅፈው ወደ አገርህ ሂድና የምታደርገውን አድርግ ይሉታል::

"ነጻ አውጪው" ቻርለስ ቴለር በምሥራቅ በኩል አሳብሮ እአአ በ1989 ላይቤርያ ተመልሶ ይገባና በመንግሥት ላይ ጦርነት ያውጃል:: የከፋ የእርስበርስ ጦርነት ለሰባት ዓመታት ይካሄዳል:: ዶ ጆሮው ተቆርጦ ይረሸናል:: (ዶ ከኢትዮጵያዊት ቁባቱ ልጅ ስለወለደ በላይቤርያም፣ እንደቶንጋ፣ የአልጋ ተቀናቃኝ መሆናችን እንዳይዘነጋ::) እአአ በ1997 "ነጻ ምርጫ" ይደረግና ቻርለስ ቴለር ሕዝብ ከሰጠው ድምጽ 87% አገኘ ተባለና ሥልጣን ይይዛል:: ቻርለስ በጦርነት ያንኮታኮተውን አገር መልሶ ለመገንባት የውጭ እርዳታ ይጠይቃል:: ጥያቄ ከቀረበላቸው መካከል IMF አንዱ ነበር:: ፒዬሮ ለአምስት ሳምንት ሥራ ወደ ላይቤርያ ትሄድ እንደሆነ ብሎ የጠየቀኝ የረጂዎችን የግንባታ ግንባር እንዳጠናክር ነበር::

ሞንሮቪያ እንደገባሁ ሰው ስለ ቴለር ሲያጉረመርም ሰማሁና የውስጥ ሕመማቸው ምን እንደሆነ ለማውጣጣት ፈልጌ ለአንድ የባንክ ኦፊሰር፣ ቻርለስ ቴለር በጣም የምትወዱት መሪያችሁ ቢሆን ነው በጣም በከፍተኛ ድምፅ የመረጣችሁት እለዋለሁ። ቱግ ይላል። ሰውዬው ከአገሬው ሰዎች አንዱ ነው፤ ማለትም ትውልዱ የአሜሪካ ባርነት የለበትም። ነገሩን አልደረስክበትም ይልና ቻርለስ በከፍተኛ ድምፅ እንዴት እንዳሸነፈ እንደሚከተለው አስረዳኝ። ባላገሩ ማለትም ከሞንሮቪያ ውጭ ያሉትን አካባቢዎች የቻርለስ "ነጻ አውጪው" ጦር ወይም ወንበዴ ይቆጣጠር ስለነበር የፖለቲካ ተወዳዳሪዎቹ፣ እነኤለን ሰርሊፍ፣ እሱ በሚቆጣጠረው አካባቢ ሄደው ለምን መመረጥ እንደሚፈለጉ ለሕዝብ ገለጻ እንዳያደርጉ አገዳቸው። ደፍረን እንመጣለን ካላችሁም ለደኅንነታችሁ ኃላፊነቱን አልወስድም ይላቸዋል። እናት የወለደችው እስቲ ግዛቴ ይገባና፣ ደፋር ከተገኘም የቀባጭነት ሂሳብ በነፍስ አስከፍለዋለሁ ማለቱ ነበር። ሞንሮቪያ ውስጥም የቻርለስ ሰዎች እየተዘዋወሩ ሕዝቡን፣ ቻርለስን ወይም ሌላ ዙር ጦርነት፣ ከሁለቱ አንዱን ምረጥ ይሉታል። ሕዝቡ በእርስበርሱ ጦርነት ከመጠን በላይ ተሰቃይቶና ደህይቶ ስለነበር ጦርነት እንደገና ከሚመጣ ቻርለስ ቴለር ረግጦ ይግዛን ብሎ በራሱ ላይ ለመፍረድ ተገደደ። በተጨማሪ፣ ቻርለስ ቴለር ገና ተማሪ ሳለ የአገሩ ፕሬዚዳንት ለመሆን የጋለ ምኞት እንደነበረው ብዙ ላይቤርያኖች፣ በተለይም በዩኒቨርስቲ አብረውት የተማሩ ሰዎች ያውቁ ስለነበር ፍላጎቱን እናሟላና እንገላገለው ያሉ ይመስል ነበር።"

ገና ከኦታዋ ከመነሳቴ ፒዬሮ በአንድ ጉዳይ ላይ በሚገባ እንዳስብበት መክሮኝ ነበር። የአጭሩ ጊዜ ሥራ እንደተጠናቀቀ የረጅም ጊዜ ሥራ እዚያው ላይቤርያ የማግኘት ዕድል እንዳለኝ ጠቁሞ ምስጢሩ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር መተባበርና እሱ የሚለኝን ማሟላት መሆኑን ነግሮኝ ነበር። እርዳታውን በላይቤርያ ስም IMFን የጠየቀው የገንዘብ ሚኒስትሩ ሳሊቢ መሆኑንና በላይቤርያ ውስጥ የእንጀራ ገመዴን የመቀጠል ወይም የመበጠስ ኃይል ያለው ሰው እንደሆነ ነግሮኛል።

ወደ ላይቤርያ የሄድኩት ፕሬዚዳንት ቻርለስ ቴለር ላቋቋመው ባንኪንግ ኮሚሽን በአማካሪነት እንዳገለግል ነበር። የላይቤርያ ባንኪንግ ሲስተም ፈራርሶ እንዳልነበር ሆኖ ድራሹ ሊጠፋ በቋፍ ላይ ነበር። ዶ ሥልጣን እንደያዘ አካባቢው የነበሩ ባለሥልጣኖች ለዝርፍያና ስርቆት እንዲያመቻቸው ሲሉ ለብዙ ዓመታት የተካበቱትን መልካም የአሠራር ዘዴዎች ወደ ጎን አደረጓቸው። የደረጃ የአሠራር ሥርዓትና አስተማማኝ ሲስተም ተሻረና ግለሰቦች በመሰላቸው መንገድ ወይም በፍርደ ገምድልነት የሚሠሩበት ሁኔታ ተፈጠረ። ዓለም እየተራቀቀና በሳይንሳዊ አሠራር መንገዱንና ተስፋውን እያበራ ሲራመድ እነሱ ጭልጥ ብለው ከአዘቅት ሰጠሙ። ፕሮፌሽናሊዝም ገደል ገባ። የሁሉ ነገር ደረጃው ዝቅ እያለ ሄደ። ተቆርቋሪ አገር ወዳድ አልፎ አልፎ ሥልጣን ላይ ከወጣ ሰልፍ አበላሽ እየተባለ ወደ ውጭ ተጣለ። አንድ ጊዜ አንድ ሚኒስትር ከውጭ አገር የሥራ ጉብኝት ሲመለስ ያልተጠቀመበትን ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ ቢያደርግ ኮምዩኒስት መጣብን ተብሎ ከሥራው ተባርሯል። ባለሥልጣን ወደውጭ ሲሄድ ይዞት የሚሄደው ገንዘብ በአገሪቱ አቅም አኳያ ሲታይ እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ የሁሉም ባለሥልጣን ምኞት ለጥቃቅኑ ጉዳይ ሁሉ ወደ ውጭ መሮጥ ነው። አንዳንድ ባለሥልጣኖች ከአገር ውስጥ ይበልጥ በውጭ አገር የሚያሳልፉት ጊዜ ይበልጣል። የመንግሥት ካዝና በተለያየ መንገድ ስለሚዘረፍ የመንግሥት በጀት ከቁጥጥር ውጭ ሆነና በቴለር ዘመን የአገሩ ፕሬዚዳንት እያንዳንዱን ክፍያ የሚያጸድቅበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ባንኮች የሚያሰባስቡት ተቀማጭ ገንዘብ ለመንግሥት በብድር መልክ እየተሰጠ የበጀት ማሟያ ሆነ። የአገሪቱ ውስን የውጭ ምንዛሪ በባንክ ባለሥልጣኖች አቀነባባሪነት በግለሰቦች ኪስ ውስጥ እንዲገባ ተደረገ፣ የባንኩ ካዝና ተራገፈ። አገሪቱን የገጠማት የፖለቲካ ቀውስ መልክ ለማስያዝ በተለያየ ጊዜ ጥምር መንግሥት ተቋቁሟል እየተባለ ፓርቲዎች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን እንደቅርጫ ሥጋ እየተከፋፈሉ ማለብ ተያያዙት። ባንኮችን የሚቆጣጠር ጠፍቶ ሕዝቡ በባንኮች ያስቀመጠው

ገንዘብ ባከነ። ባንኮች የሰበሰቡትን ተቀማጭ ገንዘብ የባንኮቹ ባለቤቶችና የቦርድ አባላት በብድር መልክ ተከፋፈሉት። ላይቤርያኖች ብድር መውሰድ እንጂ መመለስ ብዙም ስለማይቀናቸው ያልተመለሰ ብድር ቁልሉ ከባንኮች የመሸከም አቅም በላይ ሆነ። ቻርለስ ቴለር የሞንሮቪያ ከተማን ለመያዝ በኤፕሪል 6፣ 1996 የቀሰቀሰው ከፍተኛ ውጊያ ለከተማው መዘረፍ ምክንያት ሆነ። በዕለቱ የደረሰውን ጥፋት ሕዝቡ አሁንም ሲያስታውሰው ይበረግጋል። የኤፕሪልን ወር ለመጥራት ይሳቀቃል። በዚያ ቀውጢ ዕለት ባንኮች ካዝናዎቻቸው ተራቆቱ፣ አንዳንዶቹ በእሳት ጋዩ። ዘረፋው ባስከተለው መዘዝ አብዛኞዎቹ ባንኮች ተዘጉ፤ በባንክ ገንዘብ ካስቀመጠው ሕዝብ አመዛኙ ሙልጭ ወጣ።

የአገሩ ማእከላዊ ባንክ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመው ሊዘጋ ተቃርቦ ነበር። በዱቤ ለገዛው እቃና አገልግሎት ክፍያ መፈጸም ስላቃተው የመጸዳጃ ቤት ወረቀት የሚሸጥ ሱቅ ሳይቀር ለማእከላዊው ባንክ በጥሬ ገንዘብ ካልሆነ በቀር በዱቤ አልሸጥም አለ። መንግሥት ከፍተኛ የሆነ የበጀት እጥረት ስላጋጠመው ከባንኩ  የወሰደውን ከፍተኛ መጠን ያለው ብድር መክፈል ተሳነው። በተዋረድ ባንኩ ከዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የወሰደውን ብድር ዋናውንም ሆነ ወለዱን መክፈል ሳይችል ይቀራል። ማእከላዊው ባንክ ሥራውን ከነጭራሹ አቆመ እንዳይባል መንግሥት መጠነኛ ገንዘብ በድጎማ መልክ ሊሰጠው ተገደደ።

የባንክ ዘርፍ ቀውስ ውስጥ ሲዘፈቅ ለኤኮኖሚው መዳከም ተጨማሪ ምክንያት ሆነ። የምርት ዕድገት አዘቀዘቀ፤ የሕዝቡ የመግዛት አቅም ተዳከመ፤ የአዳዲስ ኢንቬስትመንት ምንጭ ደረቀ።

በሞንሮቪያ ከተማ የቧንቧ ውሃ የለም፤ ኮረንቲ የለም፤ የከተማ አውቶቡስ የለም፣ ትልቁ የመንግሥት ሆስፒታል ሥራውን ከሞላ ጎደል አቁሞ ነበር። አብዛኛው ሰው በሻማና በኩራዝ ነው የሚጠቀመው። ልጆች ሲቧርቁ፣ ሲጫወቱ ስለማይታይ ይህ ክስተት ከሰዉ ተፈጥሮ ነው? ብዬ እራሴን

መጠየቁ አልቀረም:: ውሎ አድሮ የተገነዘብኩት የጦርነቱ ውርጅብኝ የሕፃናቱን አእምሮ ሳይቀር እንደበከለውና ልጅነታቸውን እንደበላው ነው::

ለማጠቃለል፣ እአአ ከ1989 እስከ 1996 በላይቤርያ ላይ የወረደው መዐት አይጣል ነው:: ከሚሠራ ነገር የማይሠራው በጣም ይበልጣል:: ሰው እንደሚሞት ሁሉ አገርም ሊሞት እንደሚችል ላይቤርያን ሄዶ ማየት ነው:: የግል ጥቅምን ለማካበት ወይም በቂም በቀል ወይም በማናህሎኝነት ተነሳስቶ የሚደረግ የእርስበርስ ጦርነት ሁሉም ተሸናፊ ወይም ከሳሪ የሚሆንበት የአጥፍተህ ጥፋ ከንቱ የሞኞች ትግል ሊሆን እንደሚችል ላይቤርያን ሄዶ ማየት ብቻ ነው::

ቻርለስ ቴለር ባንክ ካልሠራ ኤኮኖሚው ሊያንሰራራ እንደማይችል ተገንዝቤአለሁ ብሎ የአገሩን የባንክ ኢንዱስትሪ ስለገጠመው ችግር በስፋትና በጥልቀት ዳስሶ ኢንዱስትሪው እንዲያንሠራራ ምን መደረግ እንዳለበትና በተለይ ጠንካራ ማእከላዊ ባንክ ለመገንባት መወሰድ ያለባቸውን ዝርዝር እርምጃዎች ያካተተ ዘገባ የሚያቀርብለት የባንኪንግ ኮሚሽን አቋቋመ::

በኮሚሽኑ አማካሪነቴ የኔ ኃላፊነት ኮሚሽኑ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች መስመር እንዳይስት ከዳር ቆሞ መጠበቅ፣ የኮሚሽኑ አባላት ባንክን የሚመለከቱ ቴክኒክ ነክ ጥያቄዎችን ሲያነሱ መልስ መስጠት፣ መገምገም ያለባቸው ነጥቦች ወይም መዳሰስ ያለባቸው ችግሮች በኮሚሽኑ የሥራ ፕሮግራም ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፣ ኮሚሽኑ በተሳሳተ ወይም በተዛባ መረጃ ወይም ፍቱንነት በሌለው ፅንሰ ሐሳብ ላይ ተመርኩዞ ወደ ተሳሳተ ድምደማ እንዳያመራ መጠበቅ፣ ኮሚሽኑ የሚያደርጋቸው ትንታኔዎችና የሚደርስባቸው መደምደሚያዎች በቅጡ ተሰባስበው ለፕሬዚዳንቱ በሚቀርበው ዘገባ ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ ነበር::

ሞንሮቪያ ደርሼ ከኮሚሽኑ ጊዜያዊ ሊቀመንበር ጋር ከተዋወቅሁ በኋላ (ሊቀመንበሩ ደቡብ አፍሪቃ ሄዶ ነበር) ገንዘብ ሚኒስቴሩን፣ ሳሊቢን፣ ለመተዋወቅ ወደ ቢሮው ሄድኩ:: ተጨባብጠን እያለ እጄን ሳይለቅ ፍሪሜስን (freemason) ወይም የሜሶኒክ ሎጅ (Masonic lodge) አባል እንደሆንኩ ጠየቀኝ:: እኔ ስለተጠቀሰው ድርጅት መጀመሪያ የሰማሁት ከሃያ አመታት በፊት በጣሊያን አገር ባለሥልጣኖች ሜሶኒኮኖች ሆነው ስለተገኙ ወደ ወኅኒ ተጋዙ የሚል ዜና ሲነገር ነበር:: ድርጅቱን የወንጀለኞች መሰብሰቢያ ጎሬ አድርጌ እወስደው ነበርና የሚኒስትሩ ጥያቄ አስደነገጠኝ:: ለጥያቄው መሠረቱ ምን እንደሆነ ብጠይቀው የእጅ አጨባበጤ ፈርጠም ያለ ሆኖ ስላገኘው መሆኑን ነገረኝ:: ግምቱ የተሳሳተ መሆኑን ሲያውቅ ቅር እንደተሰኘ ከፊቱ አነበብኩ::

የፍሪሜስን ድርጅት የተመሠረተው ከ600 አመታት በፊት በእንግሊዝ አገር በሥራ ፈላጊ ግንበኞች ሲሆን ባለንበት ዘመን ድርጅቱ የሚያቅፋቸው አባላት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው በንግድ አስተዳደር ሙያ የተሰለፉ ፕሮፌሽናሎችን ነው ይባላል:: የፍሪሜስኖች ዓላማ፣ አደረጃጀትና አሠራር ምስጢር በመሆኑ በውል ባይታወቅም አባላቱ በግልም ሆነ በወል ጥቃት እንዳይደርስባቸው ወይም ጥቅም እንዳይቀርባቸው እርስበርስ የሚረዳዱበት ተቋም ነው:: የእከከኝ ልከክህ ማኅበር ስለሆነ ማኅበሩን ተጠግቶ በወንጀል ተግባር ውስጥ ለመሰማራት የሚያመች ድርጅት ይመስላል:: ለዚህም ይሆናል በጣልያን አገር የሜሶኒክ ሎጅ እንደ ወንጀል ድርጅት የሚታየው:: ላይቤርያ ውስጥ ግን የድርጅቱ አባል መሆን ያኮራል:: በላይቤርያ የድርጅቱ እንቅስቃሴ ጤናማ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል:: በአንድ ወቅት ጤናማ የሚመስል ድርጊት በሌላ ወቅት ወንጀል ሆኖ ሊታይ ይችላል፤ በግልባጩ ደግሞ በአንድ ወቅት እንደወንጀል የተወሰደ ድርጊት በሌላ ጊዜ ግን ጤናማ ሆኖ ሊታይ ይችላል:: ወሳኙ ጊዜ ነው:: ሆኖም፣ በሕዝብ ላይ ማሴር፣ ሕዝብን መከፋፈል፣ የሕዝብን መብትና አለኝታ ገፎ ለግል ጥቅም ማዋል፣ በጓደኝነት ወይም በማኅበር አባልነት ዜጎችን ማበላለጥ በማናቸውም ዘመን ቢሆን ወንጀል ነው::

ፍሪሜስን መሆን አለመሆኔን ሚኒስትሩ ለምን ለማወቅ እንደፈለገ ግልጽ የሆነልኝ ከእኔ የሚጠብቀው አንድ ነገር እንዳለ በማያሻማ ቋንቋ ሲነግረኝ ነበር። "ለአገሪቱ የሚያስፈልጋት ምን ዓይነት ገንዘብ ነው?" ለሚለው ጥያቄ መልሱ የአሜሪካን ዶላር ነው። ይህን ቦታ እንድይዝ የተደረገው የአሜሪካ ዶላር ቀድሞ እንደነበረው የላይቤርያ ዋናው የመገበያያ ገንዘብ አደርጋለሁ ብዬ ቃል ስለገባሁ ስለሆነ ከዚህ ውጭ የሚሆን ነገር የለም፤ ከፕሬዚዳንቱም ጋር ተመካክረን መፍትሔው ይኸው ነው ብለን ስለተማመንን አንተ ሌላ ሐሳብ አምጥተህ ነገሩን እንድታሳክርብን ወይም እንድታውሰበስብብን አይፈለግምና ተጠንቀቅ" ብሎ ሸኘኝ። ፍሪሜስን ነኝ ብለው ኖሮ በማኅበራችን ስም እንድትተባበረኝ ተማጽኜሃለሁ ሊለኝ ኖሯል።

የኮሚሽኑ ሊቀመንበር የቴለር የቅርብ ሰውና ጓደኛው ነበር። ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር ግን ሆድና ጀርባ ናቸው። ኮሚሽነሮቹ በቁጥር ዐሥር ሲሆኑ በአገሩ ውስጥ አሉ የሚባሉ የባንክና ፋይናንስ ሰዎች ናቸው። ሁለቱ የማእከላዊ ባንክ አዛዥ የነበሩ ናቸው። በተለይ አንደኛው ባንኩን አስበዝብዞ ገደል የከተተው እሱ ነው ተብሎ በቴለር ሰዎች ይታመናል። በኮሚሽኑ ውስጥ ገብቶ እንዲሠራ የተፈለገው በኅሊና በትር ለማሰቃየት ብቻ ሳይሆን ሌባን መያዝ በሌባ ነው የሚለውን ፈሊጥ በመከተል ጭምር ነበር ተብሏል። በተጨማሪ፣ ቴለርን ተቃዋሚዎቹ እንዲቋቋሙት፣ ቢሆንላቸውም እንዲያሸንፉት የባንክን ካዝና ክፍት ያደረገላቸው ስለሆነ እንፋረደዋለን የተባለ ሰው ነው። ወያኔ ታደሰን በተመሳሳይ ምክንያት እንፋረደዋለን አለ የተባለው ዓይነት መሆኑ ነው። ሌላው የቀድሞ የባንክ አዛዥ ደግሞ በፖለቲካ አቋሙ የቴለር ወገን ስለነበር፣ ሁሉ ነገር የተበላሸው እሱ ከ17 ዓመት በፊት በዶ መንግሥት ባንኩን ጥሎ እንዲሄድ በመደረጉ ስለሆነ ቦታው እንደገና ይሰጠኛል ብሎ የቋመጠ ሰው ነበር። የኮሚሽኑ ምክትል ሊቀመንበርም ነው። ከ25 ዓመት በፊት ጀምሮ እንተዋወቃለን። ከሊቀመንበሩ ጋር እሳትና ጭድ ናቸው።

ኮሚሽኑ አማካሪ ያስፈልገኛል ብሎ የIMFን እርዳታ የጠየቀው ሊቀመንበሩ ደቡብ አፍሪቃ እያለ ነበር:: የእርዳታው ጥያቄ በላይቤርያ ስም ያስተላለፈው የገንዘብ ሚኒስትሩ ስለነበር ሚኒስትሩና ሊቀመንበሩ ባላቸው የፖለቲካ ወይም የእኔእበልጥ እኔእበልጥ ትግል ሊቀመንበሩ እኔን የባላጋራው ደጋፊ አድርጎ ወሰደኝ:: ከሌላ ባላጋራው፣ ከኮሚሽኑ ምክትል ሊቀመንበር፣ ጋር ደግሞ ቀደም ብሎ እንደምንተዋወቅ ሲደርስበት ስለኔ ያለው አመለካከት በይበልጥ የከፋ ሆነ::

የኮሚሽኑ አባላት ስለሚነጋገሩባቸው ጉዳዮችና ስለሥራ ፕሮግራማቸው ስረዳ አስደንጋጭ ሆኖ አገኘሁት:: አንድ ሕመምተኛ የሚፈወስበትን መንገድ እንደመፈለግ ዙርያውን ከቦ እግዚኦ እንደሚል የአስታማሚ ስብስብ ይመስሉ ነበር:: ኮሚሽኑ በያዘው መንገድ ቢቀጥል አያያዛቸው ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ መሆኑን ተገነዘብኩ:: የላይቤርያን የባንክ ኢንዱስትሪ ስለገጠመው ችግር ከአታዋ ከመነሳቴ በፊትም አንዳንድ ሰነዶች አገላብጬ ስለነበር ኮሚሽኑ ሊዳስሳቸው የሚገባ ብዙ ጉዳዮች እንዳልታሰበባቸው ተመለከትኩ::

በላይቤርያ ሁኔታ የአገሪቱ የመገበያያ ገንዘብ የላይቤርያ ዶላር ይሁን? ወይስ አሜሪካ ዶላር? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ለሌሎቹ የመነጋገሪያ ርእሶች ወሳኝነት ወይም መሠረታዊነት ስላለው ጥያቄው በምንም ዓይነት ሊታለፍ የማይችል ጉዳይ ሆኖ አገኘሁት:: አንድ ማእከላዊ ባንክ የሚቋቋምበት ዋና ምክንያት የዋጋ ግሽበትን ለመግታት ወይም የገንዘብ እጥረት አጋጥሞ የኤኮኖሚ እንቅስቃሴን መዳሸቅ ለመከላከል የገንዘብ ስርጭትን ወይም የወለድ መጠንን እንዲቆጣጠር ስለሆነ ዋናውን የመገበያያ ገንዘብ የሚያወጣውና የሚቆጣጠረው ሌላ አገር እስከሆነ ድረስ ወደ ተጠቃሚው አገር የሚያቋቁመው ማእከላዊ ባንክ ውጤታማነቱ መለስተኛ ወይም ውስን ይሆናል:: በተዋረድ፣ እንደዚህ ዓይነቱ አገር የሚያወጣቸው ባንክ ነክ ሕግጋትና ደንቦች ይህን ሐቅ የሚያንጸባርቁ መሆን ይኖርባቸዋል:: ስለዚህ የአገሪቱ ዋና የመገበያያ ገንዘብ የላይቤርያ

ዶላር ወይስ የአሜሪካ ዶላር ይሁን? የሚለው ጥያቄ ሚኒስትሩ እንዳለው ያለቀለት ጉዳይ ሳይሆን እንዲያውም የኮሚሽኑ ዋና የመነጋገሪያ ርእስ ሊሆን እንደሚገባው ተገነዘብኩ።

የኮሚሽኑን ተልእኮ የተሳካ ለማድረግ መዳሰስ ያለባቸውን ጉዳዮች በዝርዝር አቅርቤ ሥራው መቼ ሊጠናቀቅ እንደሚገባው የሥራ ፕሮግራም አወጣሁላቸው። ሚኒስትሩ ስለመገበያያው ገንዘብ የነገረኝን ለኮሚሽኑ አባላት ነግሬ ከሱ ጋር እንዲወያዩበት ሐሳብ አቀረብኩላቸው። የኮሚሽኑ አባላት በሰጡኝ መልስ ጉዳዩ መሠረታዊ ስለሆነ በኮሚሽኑ መመርመር ያለበት መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ጉዳዩ በኮሚሽኑ እንዳይታይ የሚፈለግ ከሆነም ኮሚሽኑን ካቋቋመው ከአገሩ ፕሬዚዳንት መመርያ በቀጥታ ካልመጣለት በቀር ሚኒስትሩ ተናገረ የተባለውን አላውቅም የሚል አቋም ወሰደ። ኮሚሽኑ የቀረበውን የመነጋገሪያ ዝርዝር የሥራ ፕሮግራም ተስማምቶ አጸደቀው።

በኮሚሽኑ ውስጥ የሚባለውንና የሚተነፈሰውን ሁሉ ለገንዘብ ሚኒስትሩ እየወሰደ የሚተፋለት ኮሚሽነር አለ። ሚኒስትሩ ኮትኩቶ ያሳደገው ሰው ነው። ስለአገሪቱ ዋና የመገበያያ ገንዘብ ኮሚሽኑ ሊነጋገርበት እንደተስማማ ሚኒስትሩ ሲሰማ በጣም ይናደዳል። ለታደሰ መመሪያ ሰጥቼው እንዴት ደፍሮ ጉድ ያደርገኛል? ብሎ ጥርስ ነከሰብኝ። እውነቱን ለመናገር ላይቤርያ በገባሁ ማግስት ሚኒስትሩ እኔ እንዳልኩህ ካልሆነ በቀር ወዮልህ ብሎ ያስፈራራኝ ዐሥራ ሰባት ዓመታት በደርግ መንግሥት ውስጥ ስሠራ ጎሊናዬን ሽጬ ነጬን ጥቁር፣ ጥቁሩን ነጭ ነው ያላልኩት ሰውዬ ዛሬ እዚህ ደርሼ ፈተና ሊደቀንብኝ ነው ብዬ ማዘኔ አልቀረም። ፒዬር ሚኒስትሩ ያለህን ከፈጸምክ ኮንትራትህ ሊራዘም ይችላል ያለኝ ከአእምሮዬ አልጠፋም። በሌላ በኩል አጨቃጫቂው ጉዳይ መሠረታዊነት ያለው ስለሆነ በቀላሉ ማለፍ እንደማይቻል ተገንዝቤአለሁ። የእንጀራ ገመዴ ተበጥሶ ወደ ኦታዋ ብመለስ ቤተሰቤን የማስተዳድርበት እጅ እንደሚያጥረኝ ተገንዝቤአለሁ። ሁሉንም ካገናዘብኩ በኋላ፣ የስራጋ አምላክ አንተ

ታውቃለህ፣ ለእውነት ተገዝቼ በመሸበት ልደር፣ ልጆቼን የአባቴ አምላክ ጠብቅ ብዬ ተልእኮዬን በልበሙሉነት ተያያዝኩት:: የእውነት አምላክ እዚህ ድረስ አድርሶኛል፣ ማምሻው ላይ መንገድ ላይ ጥሎኝ አይሄድም ብዬ ተማመንኩበት::

በወጣው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የኮሚሽኑ ሥራ ከሦስት ወር በፊት እንደማይጠናቀቅ ሲታወቅ ፒዬሮ ከዋሺንግተን ስልክ ደውሎ ሚኒስትሩ የአገልግሎት ጊዜህ እንዲራዘም ይጠይቀን፣ አዎንታዊ መልስ ወድያው እንሰጣለን ብሎ ነገረኝ:: ለኮሚሽኑ ሊቀመንበር ይህንኑ ነገርኩት:: ላይቤርያ ከIMF ጋር ያላት ግንኙነት በገንዘብ ሚኒስትሩ በኩል ስለሆነ ኮሚሽኑ ለሚኒስትሩ የጻፈውን ደብዳቤ ይዤ ቢሮው ድረስ ሄድኩ:: ሚኒስትሩ ሥራ በዝቶበታል ተብሎ እንግዳ ማረፊያ ውስጥ ከሁለት ሰዓት በላይ አስጠበቀኝ:: ስንገናኝ "ለአንተ እንዴት የሥራ እድሳት ማስታወሻ ልልክ እችላለሁ? የምልህን የማትሰማ ከጠላቶቼ ጋር ያበርክ ሰው ነህ!" ይለኛል::

ላይቤርያ በደረስኩ በአምስተኛው ሳምንት ዕፀገነት ከኦታዋ ትደውልና የዓለም ባንክ ሰዎች በእግር በፈረስ እንደሚፈልጉኝ ትነግረኛለች:: ይህን መልዕክት ከማግኘቴ በፊት የኮሚሽኑን ሥራ ለማጠናቀቅና ከዚያም በኋላ የቅጥር ኮንትራቴ ተራዝሞ የማእከላዊ ባንክ አማካሪ እንድሆን IMF እንዲጠየቅ መወሰኑን ነግረውኝ ስምምነቴን ገልጬ ነበር:: ፒዬሮም ይህን አስቀድሞም ጠቁሞኝ ስለነበር የቀረው ወረቀት መለዋወጥ ብቻ ነው በሚል እምነት ዓለም ባንክ ሌላ ሰው እንዲፈልግ መልዕክት አስተላለፍኩ:: ነገሩ ላለው ይጨመራል ሆነና ከሌላ ድርጅትም የሦስት ወር ሥራ እንደሚጠብቀኝ ማረጋገጫ ደርሶኝ ነበር:: ለዚህኛው ግን መልስ ገና አልሰጠሁም ነበርና ሚኒስትሩ እድሳቱን አይሆንም ካለ ለጊዜውም ቢሆን መግደርደሪያ አለኝ ብዬ ተጽናናሁ::

ሚኒስትሩ የእድሳቱን ማስታወሻ ለIMF ለመላክ ፈቃደኛ አለመሆኑን ለኮሚሽኑ አባላት ነግሬ፣ ሌላ ሥራ የሚጠብቀኝ መሆኑን ገልጬ ለመሄድ

መዘጋጀቴን እነግራቸዋለሁ:: ይደናገጣሉ:: ታደሰ ከሄደ የኮሚሽኑ ሥራ ዳር ሊደርስ እንደማይችል ሊቀመንበሩና ጥቂት የኮሚሽኑ አባላት ለሚኒስትሩ ይንገሩት ተብሎ ተወሰነ:: አሁንም አይሆንም ካለ ፕሬዚዳንቱ እንዲያውቁት ተደርጎ ለሚኒስትሩ መመሪያ እንዲደርሰው ይደረግ ተባብለው ተስማሙ:: ሚኒስትሩ ሳይወድ የእድሳቱን ደብዳቤ ለመላክ ተገደደ::

የላይቤርያ ዋናው ብሔራዊ ገንዘብ የላይቤርያ ዶላር ወይስ የአሜሪካ ዶላር? በሚለው ጥያቄ ላይ ኮሚሽኑ ሰፊ ውይይትና ክርክር ካካሄደ በኋላ የላይቤርያ ዶላር እንዲሆን ወሰነ:: እኔም የመከርኳቸው ይህንኑ ነበር:: ታደሰ በላይቤርያ ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ገብቷል ብሎ ሚኒስትሩ በIMF ላይ ከሰሰኝ:: በበኩሌ የሰጠሁት መልስ እንደሚከተለው ነበር:: መጀመሪያ፣ ተጠሪነቴ ለኮሚሽኑ እንጂ ለሚኒስትሩ አይደለም፤ ሁለተኛ፣ እኔ የፖለቲካ ሰው ሳልሆን የቴክኒክ አማካሪ ስለሆንኩኝ መፍትሔ ሐሳቦችን በተመለከተ ያለብኝ ኃላፊነት ያሉትን አማራጮች በመዘርዘር የእያንዳንዱን ጥቅምና ጉዳት አንጠርጥሬ ለኮሚሽኑ አባላት ማሳወቅ ሲሆን የትኛው አማራጭ ይሻላል ብሎ የመወሰን ሥልጣን የኮሚሽኑና የላይቤርያ መንግሥት ነው፤ ሦስተኛ፣ ጉዳዩን አስመልክቶ የማውቀውን ወይም አንድና አንድ ሁለት ብዬ የምደርስበትን መደምደሚያ አትናገር ማለቱ አግባብ አይደለም ብዬ ተከራከርኩ::

ስለብሔራዊ ገንዘብ የገንዘብ ሚኒስትሩ የወሰደውን አቋም የIMF ሰዎች እንዲደግፉለት ተማጽኖ እሺ ብለውት ስለነበር ከዋሺንግተን የመጣ አንድ የIMF ቡድን እኛ የላክንህ ሰው ሆነህ እንዴት እኛ የወሰድነውን አቋም አትደግፍም? ብለው በመገረም ጭምር ነዘነዙኝ:: ለዚህም የሰጠሁት መልስ፣ ላይቤርያኖች የራሳቸው የሆነ ገንዘብ እንዲኖራቸው ቢደረግ በቅጡ ሊያስተዳድሩትና ሊቆጣጠሩት ስለማይቻሉ ሌላ አገር ባወጣው ገንዘብ ይጠቀሙ ማለት ነጻ ነን ለሚሉ ላይቤርያኖች ክብረነክ መሆኑን ጠቅሼ የሚሻለው በገንዘብ አስተዳደርና ቁጥጥር አካባቢ ያሉትን ባለሙያዎቻቸው ብቃት ከፍ በማድረጉ ላይ ማተኮር ነው ስል ያለኝን ሐሳብ በግልጽ

አሳወቅኋቸው፡፡ ለዚህ በቂ መልስ ስላልነበራቸው የቡድኑ መሪ “ላይቤርያ የራስዋን ገንዘብ ማስተዳደር አትችልም ካልን መጀመሪያውኑ ለምን አማካሪ ላክን? ታደሰ የተናገረው እውነት ነው” ብሎ አጽድቆ ወደ ዋሺንግተን ተመለሱ፡፡

ስለላይቤርያ ገንዘብ አንባቢ ሊያውቀው የሚገባ አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ቴለር በሥልጣን ላይ ሲወጣ የላይቤርያ ሕጋዊ ገንዘብ የአሜሪካ ዶላር ነበር፡፡ ቅንስናሽ ገንዘብ ወይም ሳንቲሞች ግን ላይቤርያ ያወጣቻቸው ናቸው፡፡ የአሜሪካ ዶላር ሕጋዊ ገንዘብ ነው ይባል እንጂ ከአሜሪካ ጋር የተደረገ ምንም ዓይነት ስምምነት ወይም ውል የለም፡፡ የአሜሪካ ማእከላዊ ባንክ የተቀዳደዱ ወይም ያረጁ ባንክኖቶችን ከላይቤርያ ማእከላዊ ባንክ ተቀብሎ በምትኩ አዳዲስ ኖቶችን የመስጠት ግዴታ የለበትም፡፡

ላይቤርያ ሰላም በነበረችበት ዘመን ሞንሮቪያ የምዕራብ አፍሪቃ ነዋሪዎች ለሽመታና ፈንጠዝያ የሚጎርፉባት ከተማ ነበረች፡፡ የከተማዋ ማራኪነት አንድም ዶላር በቀላሉ የሚገኝባት ስፍራ ስለነበረች ነው፡፡ የገንዘብ ሚኒስትሩ የተሾመው የታሪክን ሂደት በማቆም ዛሬን ወደ ትናንት እለውጣለሁ ብሎ ቃል ስለገባ ነበር፡፡

የቶልበርት መንግሥት ወድቆ ዶ ሥልጣን ከወሰደና በተለይም ቴለር የቀሰቀሰው የእርስበርስ ጦርነት ከተፋፋመ በኋላ ብዙ ላይቤርያኖች ዶላራቸውን ሰብስበው ወደ አሜሪካ እግሬ አውጭኝ አሉ፡፡ የሚወጣ እንጂ የሚገባ የአሜሪካ ዶላር እየመነመነ ስለሄደ የባንኮች ካዝና ተሟጠጠ፡፡ በሕዝብ እጅ ይዘዋወር የነበረው የአሜሪካ ዶላር እጅግ በመቀነሱ የመገበያያ ገንዘብ እጥረት አጋጠመ፤ ኤኮኖሚው ተቃወሰ፡፡ ማእከላዊው ባንክ ባለአምስት ዶላር የላይቤርያ ባንኮኖት ወይም የወረቀት ገንዘብ ለመጀመሪያ ጊዜ አሳትሞ አሰራጨ፡፡ ቀደም ብሎም በሕግ አንድ የላይቤርያ ዶላር ከአንድ የአሜሪካ ዶላር ጋር ዋጋው እኩል ነው ተብሎ ነበር፡፡ ነገር ግን በኤኮኖሚው ውስጥ የተሰራጨው የላይቤርያ ዶላር ብዛት እየጨመረ ሲሄድ በሌላ በኩል የአሜሪካ ዶላር መጠኑ እየቀነሰ ሲመጣ የላይቤርያ

ዶላር የምንዛሪው ዋጋ አሽቆልቁሎ እኔ ላይቤርያ ስደርስ የአንድ የላይቤርያ ዶላር ዋጋ ወደ ሁለት የአሜሪካ ሳንቲም ገደማ ወርዶ ነበር፡፡

የላይቤርያ ዶላር ዋጋ ማሽቆልቆል ለአንዳንድ ወስላታ የማእከላዊው ባንክ ባለሥልጣኖችና ወዳጆቻቸው ከፍተኛ የብዝበዛ በር ከፈተላቸው፡፡ በሕግ የሁለቱ ገንዘቦች ምንዛሪ እኩል ነው ስለተባለ አንድ መቶ የላይቤርያ ዶላር ይዞ ለመጣ ሰው አንድ መቶ የአሜሪካን ዶላር ይሰጠዋል፡፡ በጥቁር ገበያ መቶው የአሜሪካን ዶላር ወደ 4000 የላይቤርያ ዶላር ይለወጣል፡፡ አራት ሺው (4000) የላይቤርያ ዶላር ለባንክ ቢቀርብ 4000 የአሜሪካ ዶላር ያስገኛል ማለት ነው፡፡ ሕግን ተገን አድርገው በዚህ በለየለት የቅጥፈት ዘዴ በባንክ ውስጥ የነበረውን የአሜሪካ ዶላር አንድ ሳይቀር ተቀራመቱት፡፡ መንግሥትና ባንኮች የማእከላዊው ባንክ ባለሥልጣኖችን ቀበኛነት ስላወቁ ገንዘባቸውን በባንኩ ውስጥ ለማስቀመጥ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ፡፡ ቀደም ብሎ እንደጠቀስኩት የመንግሥት ድጎማ ባይኖር ኖሮ ባንኩ መዘጋቱ የማይቀር ነበር፡፡

የቴለር መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ የባንኩ ምክትል አዛዥ ጸሓፊ ስለደመወዝ ማነስና ስለኑሮ ውድነት አንስታ ካጉረመረመች በኋላ "መቼም ያለፈው ወርቃማ ዘመን ተመልሶ አይመጣም" ትለዋለች፣ አለቃዋም "እንዴት እንዲህ ትያለሽ? ያለፈው ጊዜ እኮ ለላይቤርያኖች የመከራ ዘመን ነበር፤ ደጉ ዘመን እፊታችን ነው ያለው" ይላታል፡፡

"ይህን ካዝና ታያለህ?" ብላ ትጠይቀዋለች፡፡

"አዎን ለመሆኑ ለምንድነው እዚህ የተቀመጠው?" ብሎ ጥያቄዋን በጥያቄ ይመልሳል፡፡

"ከአንተ በፊት የነበረው ሰውዬ ከባለጉዳይ፣ በተለይም የላይቤርያ ዶላር ወደ አሜሪካን ዶላር እንዲለወጥላቸው ከሚጠይቁ ሰዎች፣ የምሰበስብለትን የወሮታ ገንዘብ የሚያከማችበት ነበር" ብላ ሳትፈራ በግልጽ ነገረችው፡፡

አንተና መሰሎችህ ሰነፎች ናችሁ ማለቷ ነበር:: አዲሱ አለቃዋ ቢፈልግም በአሠራሩ መጠቀም አይችልም፣ ምክንያቱም ባንኩ የአሜሪካ ዶላር የለውምና:: የጸሐፊዋ አባባል በአገር ጥቅም አኳያ ሲታይ፣ ባልዋን "በደጃችን ያለውን ሞፈር ለምን ፈልጠን አናነደውም?" እንዳለችው ሞኝ ሴት መሆኑ ነው:: በላይቤርያ አንድ ሰው 'ትልቅነቱ' የሚለካው በሐቀኛነቱ ወይም በፍትሐዊ አስተዳደሩ ሳይሆን በዚህም በዚያም ብሎ፣ ነጥቆም፣ ቀምቶም፣ አወናብዶም ቢሆን ሀብት አከማችቶ ሰው ያለኔ ማን አለ? ብሎ ደረቱን በማሳበጥ ነው::

ፕሬዚዳንት ቴለር የኮሚሽኑን ዘገባ በረቂቅነቱ ጭምር ከዳር እስከዳር አንብቦት ስለነበር በጣም ከመደሰቱ የተነሳ እንዲህ ዓይነቱን ዘገባ የምረከበው በታላቅ ሥነሥርዓት ነው ይልና የፓርላማ አባላት፣ ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮችና የሃይማኖት መሪዎች ባሉበት የማስረከቡ ሥነሥርዓት በድምቀት ተከናወነ:: ፕሬዚዳንቱ ባደረገው ንግግር እንዲህ ዓይነት ጥራት ያለው መፍትሔ አዘል ዘገባ እንድናዘጋጅ የረዳን ኢትዮጵያዊው ወንድማችን ስለሆነ በዘገባው ውስጥ ለተካተቱት የውሳኔ ሐሳቦች በተግባር መተርጎም የሱ እዚህ መቆየት አስፈላጊ ስለሆነ የጀመረውን ሥራ ሳይጨርስ ካገር እንዳይወጣ የመውጫ ቪዛ እንዳይሰጠው መመሪያ አስተላልፌአለሁ ብሎ ሰዉን አሣቀው::

ኮንትራቴ ታድሶ የማእከላዊው ባንክ አማካሪ እንድሆን የIMF ስምምነት እንደሚጠየቅ ተነገረኝ:: ሥራውን ከመጀመሬ በፊት ቤተሰቤን ለመጠየቅ ወደ ኦታዋ እሄዳለሁና ከመነሳቴ በፊት ጥያቄው ለIMF ይተላለፍልኝ ብዬ ጠየቅሁ:: ምንም ችግር የለም፤ የገንዘብ ሚኒስትሩ የእርዳታውን ጥያቄ እንዲያስተላልፍ ተጽፎለታል ተብሎ ተነገረኝ፤ የደብዳቤውም ግልባጭ ተሰጠኝ:: ወደ ኦታዋ ለመነሳት ጥቂት ቀናት ሲቀሩኝ ሚኒስትሩ ጥያቄውን ሳያስተላልፍ ወደ አቢጃን ለእረፍት እንደሄደ ደረስኩበት:: ምን ይሻላል? ብዬ ብጠይቅ መልስ የሚሰጠኝ አጣሁ:: ደግነቱ ከዋሺንግተን ተደውሎ አንድ የIMF ቡድን ሊያነጋግርህ ስለሚመጣ ጉዞህን በአንድ ሳምንት

አራዝመው የሚል መልዕክት ደረሰኝ፡፡ ቡድኑ እላይ የገለጽኩት ለላይቤርያ ስለሚያስፈልጋት የገንዘብ ዓይነት ሊያነጋግረኝ የተላከው ነው፡፡

ሚኒስትሩ አቢጃን የሄደው ወደ ላይቤርያ መመለሴን ለማጨናገፍ አስቦ እንደሆነ ግምት ወስጃለሁ፡፡ የሄድኩ መስሎት ቢመለስ እዚያው አገኘኝ፡፡ ቢሮው ድረስ ሄጄ የእርዳታውን ጥያቄ ፈርሞ እንዲልከው አሳሰብኩት፡፡ ደብዳቤው እስኪዘጋጅ እንግዳ ማረፊያው ተቀምጠህ ጠብቅ አለኝ፡፡ ቢሮው ከሰዓት በኋላ በዘጠኝ ሰዓት የተገኘሁ የደብዳቤው ግልባጭ በእጄ የገባው ከምሽቱ በሁለት ሰዓት ነበር፡፡ የልጆቼ አምላክ እባክህን ትዕግስቱን ስጠኝ ብዬ የፈጸመብኝን በደል በጸጋ ተቀበልኩ፡፡

ከኮሚሽኑ ባለሥልጣኖች ጋር ያደረግሁት ስምምነት ወደ ኦታዋ እአአ በሜይ 1998 አጋማሽ ሄጄ በወሩ መጨረሻ ወደ ሞንሮቪያ ተመልሼ በጁን ወር መግቢያ ላይ አዲሱን ሥራዬን እንደምጀምር ነበር፡፡ ሞንሮቪያ ሦስት ወር ተኩል ቆይቼ ኦታዋ ስመለስ ዕፀገነት ቤቱን ቀጥ አድርጋ በመያዟና፣ ልጆቻችን መስመር ሳይስቱ በትምህርታቸው በርትተው በማግኘቴ የቤተሰቡ የወደፊት ዕድል ብሩህ ሆኖ ታየኝ፡፡ እኔ ብልጡ በዓለም የታወቀውን የኦታዋን ከባድ ክረምት በሙቀት ቦታ አሳልፌ ተመለስኩ ብዬ አስቀናኋቸው፡፡ ከሞንሮቪያ ሙቀት ኃይለኛነትና ከማያቋርጠው የወባ ቢምቢ ፉጨት የተነሳ ያለእንቅልፍ ሲገላበጡ እንደሚታደርና ፈጣሪ እባክህን ቅዝቃዜ አምጣ ተብሎ እንደሚለመን ግን አልነገርኳቸውም፡፡ ክፍለማርያም ገዝቶልን የነበረው ሼቭሮሌት ስቴሽን ዋገን፣ የቤት ስሙ ቢግ ዳዲ፣ የአገልግሎት ዘመኑን ጨርሶ ስለነበር ሌላ ሻል ያለ አውቶሞቢል ገዛንና ባለውለታችን ቢግ ዳዲን እያዘንን ወደ ኦታዋ ከተማ ሶማሌ ተራ ላክነው፡፡ ከአገራችን በወጣን በስምንተኛው ዓመት መኪናን ያህል ነገር መግዛት በመቻላችን አንኳን ለዚህ ያበቃን ተባብለን ፈጣሪያችንን አመሰገንን፡፡

ወደ ላይቤርያ ተመልሼ ለመግባት እንድችል የላይቤርያ መንግሥት ፈቃድ ወደዚያ በሚልከኝ በIMF በኩል እንደገና መጠየቅ ነበረበትና ተጠየቀ፡፡ እኔን

በተመለከተ ለላይቤርያ የይለፍ መሥሪያ ቤት ጥያቄው የሚቀርበው በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል ስለሆነ አሁንም ተመልሼ በሚኒስትሩ እጅ ውስጥ ወደቅሁ:: የሚፈለገውን የይለፍ ፎርማሊቲ ሚኒስትሩ እንዲያስጨርስ IMF ደጋግሞ መልዕክት ቢያስተላልፍለትም ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ ፋይሉን አስተኛው:: ከሁለት ወር የሚበልጥ ጊዜ ከባከነ በኋላ ሚኒስትሩ በግፊት ኃይል የሚጠበቅበትን ፈጸመና በመስከረም አጋማሽ ወደ ሞንሮቪያ ለመመለስ ቻልኩ::

መንግሥት የኮሚሽኑን ምክር ተቀብሎ ኮሚሽኑ ያቀረባቸውንና መንግሥት ያጸደቃቸውን የውሳኔ ሐሳቦች ወደ ተግባር የሚተረጉም ጽሕፈት ቤት ወይም ሰክሬታሪያት አቋቋመ:: የኮሚሽኑ ሊቀመንበር የነበረው የፕሬዚዳንቱ የቅርብ ወዳጅ ኤማኑኤል ሻው በጽሕፈት ቤቱ የበላይ ኃላፊነት ተመደበ:: ጽሕፈት ቤቱ ከተያያዛቸው ዋና ዋና ተግባሮች መካከል ማእከላዊውን ባንክ ማጠናከር ስለነበር ባንኩ ከሞላ ጎደል በጽሕፈት ቤቱ ሥር ሆኖ ነበር ለማለት ይቻላል:: የጽሕፈት ቤቱ ተግባር የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የባንኩን የሥራ መመሪያዎችንና የመተዳደሪያ ደንቦች ማሻሻል፣ የባንኩን ቦርድ አባላትንና አዛዥ መርጦ ማሾም፣ ባንኮችን በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የባንክ ሕግጋትን አሻሽሎ ማርቀቅና በፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት በኩል ለፓርላማ ማቅረብ፣ የተዘጉት ባንኮች የሚከፈቱበትን መንገድ ማመቻቸት ወይም ሒሳባቸው ተጣርቶ አስቀማጩ ገንዘቡን እንዲያገኝ ማድረግ፣ ብቸኛውን ባለአምስት የላይቤርያ ዶላር ባንክኖትን አስወግዶ በምትኩ ልዩ ልዩ ዋጋ ያላቸው ባንክኖቶች ማሰራጨት ይገኙበት ነበር:: እኔ ለስሙ የማእከላዊው ባንክ አማካሪ ልሁን እንጂ በቅርብ የምሠራው ከጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች ጋር ስለነበር ከባንኩ አዛዥ ጋር ግንኙነት ነበረኝ ለማለት አያስደፍርም::

የተሻሻሉት የባንክ ሕጎች ለፓርላማ ከመቅረባቸው በፊት የሚመለከታቸው ሚኒስትሮች በተገኙበት ዋናው የላይቤርያ ገንዘብ ከላይቤርያ ዶላርና ከአሜሪካ ዶላር የትኛው ይሁን? የሚለው ጥያቄ ለውይይት ቀረበ:: ጉዳዩ

እንደገና እንዲነሳ የፈለገው ወገን ላይቤርያ ያለ አሜሪካ ድጋፍና ጠባቂነት ምንም ዓይነት እርምጃ ልታደርግ አትችልምና ላይቤርያ አሁንም የአሜሪካ ዕዳ ወይም ሸክም መሆንዋን ለማመልከት በአሜሪካ ዶላር መጠቀም መቀጠል አለብን ብሎ ተነሳ። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት በኮሚሽኑ ደረጃ ስምምነት የተደረሰው የአገሪቱ ዋና ገንዘብ የላይቤርያ ዶላር ነው ይባል እንጂ በዓለም ተቀባይነት ያለው ማንኛውም የውጭ አገር ገንዘብ፣ በተለይም የአሜሪካ ዶላር፣ ላይቤርያ ውስጥ ያለገደብ በነጻ ሊዘዋወር ይችላል፣ ባንኮችም በተቀማጭነት ሊቀበሉት ይችላሉ ተብሎ ነበር። ነጥቡ በሚመለከተው የባንክ ሕግ ውስጥ እንዲንጸባረቅ ተደርጓል። የአሜሪካ ዶላር አፍቃሪዎች የሚሉት አሜሪካ ዶላር የበላይነት ኖሮት የላይቤርያ ዶላር በጥገኝነት ወይም በሁለተኛ ደረጃ እንዲወሰድ ነበር።

ጉዳዩ ኤኮኖሚክስን፣ ፋይናንስን ወይም ባንኪንግን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን አንድ ነጻ ነኝ የሚል አገር ነጻነቱን ለማረጋገጥ እስከየት ድረስ መሄድ ይኖርበታል? የሚለውን የሚጨምር ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ አንባቢ ሊያውቀው የሚገባ ጉዳይ አለ። ከአሜሪካ የተመለሱት ባሮች ዝርያዎች፣ ሁሉም ባይሆኑ ቅሉ፣ አብዛኛዎቹ በልባቸው እራሳቸውን እንደ አሜሪካውያን እንጂ እንደ አፍሪቃውያን አይቆጥሩም። አያቶቻቸውና ቅድመአያቶቻቸው የነጭ አሜሪካኖች ባሮች ሳሉ የዜግነት መብት ያልነበራቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደ እቃ ወይም ሸቀጥ ተቆጥረው ይሸጡ፣ ይለወጡና በስጦታ መልክ ይበረከቱ እንደነበር ማስታወሱ የአሜሪካዊነት ስሜታቸውን አያቀዘቅዘውም። አሜሪካ የልጆቻቸው ማስተማሪያ፣ የእረፍት ማእከልና የንብረት ማከማቻ ቤታቸው ነው። ሞንሮቪያ ውስጥ የሚታየው አብዛኛው ማኅበራዊ ሥነሥርዓትና ባሕል ከአሜሪካ ጥቁሮች የተወረሰ ነው። የሚለብሱት የሚቀምሱት የሌላቸውና የሰውን እጅ የሚያዩት ሰዎች እሁድ ወደ ቤተክርስትያን ሲሄዱ፣ ወይም በሰርግና ሐዘን ላይ ሲገኙ የሚለብሱት ልብስና የሚዋቡበት ጌጣጌጥ ልክ አሜሪካ ውስጥ እንደሚታየው ነው። የሚጠቀሙበት አንዳንድ የሥነጽሑፍ፣ የቢሮና የሕግ ቋንቋ በጣም አሮጌ ከመሆኑ የተነሳ ከሙቶ

ዓመት በፊት የአሜሪካ ሰዎች እንዴት ይጽፉ እንደነበር ለማወቅ ላይቤርያን መጎብኘት ነው፡፡

ሞንሮቪያ አትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ የተመሠረተች ከተማ ናት፡፡ አንድ ሰው ውሃው ዳርቻ ቆሞ በሐሳቡ ባሕሩን አቋርጦ እስከመጨረሻው ቢጓዝ የሚደርሰው አሜሪካ ነው፡፡ "ወደፊት፣ ይልይለት" ለሚል ላልደላው አፍሪቃዊ ጎስቋላ አፍሪቃን በሐሳቡ እንደ ሸክም በመቁጠር ጥሏት መሰደድ ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ አሜሪካኖች ጥቁሩን ባርያ ላይቤርያ አምጥተው ያራግፉት እንጂ ባሮቹ መጀመሪያ ከየት አካባቢ ተፈንግለው እንደተሸጡ ስለማያውቁ አንድ ከባርነት ለተመለሰ አፍሪቃዊ የቀድሞ አባቶቹ እትብት የተቀበረበትን፣ ልጅ ወልዶና አሳድጎ ከዚያም ሲያረጅ የተቀበረበትን ቦታ ስለማያውቀው ላይቤርያ ለሱ ምኑም አይደለችም፤ ማንነቱን ስለማያውቅ ውስጠ ቀፎነት ይሰማዋል፡፡ ላይቤርያን የኔ ነሽ የሚላት የሚፈልገውን ሁሉ እስካቀረበችለት ድረስ ብቻ ነው፡፡ መጥፎ ቀን ሲመጣ ጥሏት ይሮጣል፡፡ ለዚህም ነው አንድ ነገር ኩሽ ባለ ቁጥር የተመላሾች ባሮች ዝርያዎች ሻንጣቸውን አንጠልጥለው በአያቶቻቸውና ቅድመአያቶቻቸው አሳዳሪዎች ጉያ ስር ለመሸጎጥ የሚጣደፉት፡፡ በሌላ አገላለጽ ላይቤርያ ለተመላሾቹ ባሮች መጠቀሚያ ስፍራ እንጂ ቀድሜ ልደፋልሽ የሚሏት አገር አይደለችም፡፡

ነገሩ ሲጠቃለል፣ አብዛኛዎቹን ባሮች በተመለከተ ከአሜሪካ ወደ አፍሪቃ የተመለሰው ሥጋቸው እጅ መንፈሳቸውና ልባቸው አልነበረም፡፡ ከዚህም አልፎ ዐይናችንን የከፈትነው ከሌሎች ጥቁር አፍሪቃውያን ቀድሞ ስለሆነ ከሌላው አፍሪቃዊ የተለየን ወይም የተሻልን ነን ብለው እራሳቸውን ይኮፍሳሉ፤ ሳያውቁት እራሳቸውን ይጠላሉ፣ ያጥላላሉ፣ በዳያቸውን ያመልካሉ፣ ማረኝ ይላሉ፡፡ በሌላ ሕዝብ የተገዛ አንድ ሕዝብ መከራው እዚህ ላይ ነው፤ ሥነልቦናው ስልብ ነው፡፡ ከአሜሪካ የተመለሱት ባሮች አሜሪካውያን ነንና ይህንን ስሜታችንን የሚቀንስ ወይም የሚያደበዝዝ ማንኛውንም ክስተት እንዋጋለን ብለው ሻንጣቸውን ገትረው ይሟገታሉ፡፡

የላይቤርያ ዶላር ወይስ የአሜሪካ ዶላር? ሚለው ክርክር ወይም ንትርክ የአገሬው ተወላጆች ከመጤ ጥቁር ባሮች ጋር የሚያደርጉት ክርክር ብቻ ሳይሆን የላይቤርያ ገዢው መደብ ከራሱ ጋር በማካሄድ ላይ ያለው የሥነልቦና ጦርነት ነጸብራቅም ነበር፡፡

ፕሬዚዳንቱ በሚሰበስበው በሚኒስትሮቹ ስብሰባ ላይ እንድገኝ ጥሪ በጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በኤማኑኤል ሻው በኩል ደረሰኝ፡፡ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ጋር ለግጭት የዳረገኝ ጉዳይ እንደገና መቀስቀሱን አስተዋልኩና አዘንኩ፡፡ በአማካሪነቴ ማለት ያለብኝን ሁሉ ስለተናገርኩና ነጥቦቹ በዘገባው ውስጥ ስለተካተቱ በስብሰባው ላይ የኔ መኖር አስፈላጊ አይደለም አልኩት፡፡ በተጨማሪ የሰጠሁት ምክንያት፣ ጉዳዩን ሊመረምሩ የተዘጋጁት በፕሬዚዳንቱ መሪነት የፖለቲካ ሰዎች ስለሆኑና እኔ የፖለቲካ አማካሪ ስላልሆንኩ መገኘቴ ትክክል አይሆንም፤ ቀደም ብሎም ገንዘብ ሚኒስትሩ በIMF ላይ ሲከሰኝ ታደሰ በላይቤርያ ፖለቲካ ውስጥ ጣልቃ ገባ ብሎ ስለሆነ ታሪክ እራሱን እንዳይደግምና ቀጥሮ የላከኝ ድርጅትም የእንጀራ ገመዴን እንዳይበጥስ እፈራለሁ አልኩት፡፡ ከፕሬዚዳነቱ ጋር ተመካክሬ እነግርሃለሁ አለኝና ጉዳዩ በቀጠሮ አደረ፡፡ በማግስቱ፣ ፕሬዚዳንቱ መገኘትህ አስፈላጊ ነው ብለዋል፤ የመጣኸው ልታማክረን ስለሆነ ለምንጠይቅህ ጥያቄ መልስ መስጠት ምንም የሚያስፈራህ ነገር የለምና እንድትገኝ ብለዋል ብሎ ነገረኝ፡፡ ነገሩ እዚህ ከደረሰ አልገኝም የምልበት መንገድ እንደሌለ ግልጽ ነው፡፡

በስብሰባው ላይ ፕሬዚዳንቱ ስለላይቤርያ ሕጋዊ ወይም ኦፊሴል ገንዘብ ከቀረቡት ሁለት አማራጮች የትኛው እንደሚሻል አማካሪዎቹ ያለንን አስተያየት ጠየቁ፡፡ ከኔ ሌላ ሶስት የIMF አማካሪዎች አሉ፡፡ ሦስቱም በተለያየ መስክ የተመደቡ ሲሆን እኔ ግን ሁለገብ አማካሪ ወይም ጄኔራል አድቫይዘር ነኝ፡፡ ወዳጄ አቶ በቀለ ታምራት የሒሳብ አያያዝ አማካሪ ነበር፡፡ በስብሰባው ላይ መናገር ስላልፈለግሁ ድምጽ አጥፍቼ ተቀመጥኩ፡፡ ፕሬዚዳንቱ መናገር እንዳልፈለግሁ ሲያይ "ምንም የሚያስፈራህ ነገር

የለም፣ ማንም ሐሳብህን ሰጠህ ብሎ ሊቃወምህ ወይም ሊጎዳህ አይችልምና ተናገር" ብሎ አደፋፈረኝ። ስለሁለቱ አማራጮች ያለኝን አስተያየት ለኮሚሽኑም ያስጨበጥኩትን ደገምኩት። አገሪቱ የላይቤርያ ዶላርን ቀዳሚ ገንዘብዋ እንድታደርግና የገንዘብ አስተዳደርና የባንክ ቁጥጥር ስልትዋን እንድታሻሽል ወይም እንድታጠናክር መከርኩ። አብዛኛዎቹ ሚኒስትሮች የላይቤርያ ዶላርን ሲደግፉ ጥቂቶቹ የአሜሪካን ዶላር ይሁን አሉ።

እንደፈራሁት የገንዘብ ሚኒስትሩ IMF ደወለና ታደሰ በማያገባው ነገር ገብቶ በላይቤርያኖች የፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ ተዘፍቋል ብሎ እንደገና ከሰሰኝ። ሚኒስትሩን ያስቆጣው ሌላም ነገር ነበር፣ ባንኩ ከገንዘብ ሚኒስቴር ቁጥጥር ነጻ ካልሆነ የአገሪቱ የገንዘብ አስተዳደርና ቁጥጥር ንቅዘት ሊፈወስ እንደማይችል ኮሚሽኑን ማስገንዘቤንና ይህ አቋም በተረቀቀው አዲሱ የባንክ አዋጅ ውስጥ እንዲካተት ማስደረጌን ስላልወደደው ነበር። ሚኒስትሩ ሁሉን አውቃለሁ፣ ሁሉንም በጉያዬ ሥር አድርጌትና ልቆጣጠረው የሚል በሽታ የተጸናወተው ሰው ስለነበር 'ትልቅነቱን' ለመቀነስ የመጣሁ ሰው አድርጎ ዐይቶኛል። አሁን ምንም ምርጫ ስለሌለኝና የልጆቼ ጉሮሮ እንዳይዘጋ መዋጋት ስላለብኝ ሰውዬው አሁንም ከራሴ እንዳልወረደና እንዳልተኛልኝ ስረዳ ለባንኮች ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ለሻው የፈራሁት መድረሱን ነገርኩት። እሱም ወዲያው ሄዶ ሚኒስትሩ አሁንም እየተፈታተነኝ ስለመሆኑ ለፕሬዚዳንቱ ተናገረ። ፕሬዚዳንቱ እኔንና ሌሎቹን አማካሪዎች በመያዝ የተጀመረው የባንክ ዘርፍን የማደራጀትና የማጠናከር ሥራ ዳር ለማድረስ ቆርጠው መነሳታቸውን እንዳውቅ መልዕክት በሻው በኩል ደረሰኝ። በተጨማሪ፣ ቀጥሮ የላከኝ ድርጅት ቢያሰናብተኝ የላይቤርያ መንግሥት በገዛ ገንዘቡ በአማካሪነት ሊቀጥረኝ እንደተዘጋጀና ሥራዬን ተረጋግቼ እንድሠራ ተነገረኝ። ሚኒስትሩን በተመለከተ መንግሥት አስፈላጊውን እንደሚያደርግ ሻው ቱስ አለልኝ።

ከአፕሪል 6፣ 1996 ዘረፋ በፊት በአገሩ ዐሥራ ሁለት ወይም ዐሥራ ሦስት ባንኮች ነበሩ። ሁሉም ሞንሮቪያ ውስጥ፣ ከሞላ ጎደል አንድ አካባቢ፣

የተከማቹ ናቸው፡፡ ለማመን አዳጋች ቢሆንም ከሞንሮቪያ ውጭ አንድም የባንክ ቅርንጫፍ የለም፡፡ በግርግሩ ሳቢያ ሳይዘጉ የተረፉት ባንኮች ሦስት ብቻ ነበሩ፡፡ ሁለቱ ባለቤትነታቸው የውጭ አገር ሰዎች ሲሆን ሦስተኛው በአገሬው ሰዎችና በሌባኒዞች ኅብረት የተቋቋመ ነበር፡፡ ስሙ ሉቢ ይባላል፡፡ የውጭዎቹ ባንኮች ትናንሹ አስቀማጭ፣ ማለትም አብዛኛው ላይቤርያዊ፣ እንዳይጠጋቸው በልዩ ልዩ ዘዴ ይጠቀሙ ስለነበር ሉቢ የሰፊው ሕዝብ ባንክ ነበር፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን የአገሩ ፕሬዚዳንት ቻርለስ ቴለር በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ ሉቢ ችግር ላይ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ጋዜጠኞች ይሰማሉ፡፡ ለሕዝብ ያሰማሉ፡፡ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ገንዘባቸውን ያወጣሉ ወይም ማስቀመጥ ያቆማሉ፡፡ ሌላውም አስቀማጭ ገንዘቡን ማውጣት ይጀምራል፡፡ በእርግጥም ሉቢ ችግር ላይ ወደቀ፡፡

በላይቤርያ ውስጥ በቋፍ ላይ ያልነበረ ባንክ አልነበረም፡፡ እላይ እንደገለጽኩት ብዙ የላይቤርያ ተበዳሪ ብድር መውሰድ እንጂ መመለስ ሞት ይመስለዋል፡፡ የባንክ ኃላፊዎች በባለአክስዮኖች የተሰጣቸውን አደራና በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ማክበር ነውር ሳይመስላቸው አይቀርም፡፡ ማእከላዊው ባንክ ባንኮቹን በቅጡ መቆጣጠር አልቻለም፡፡ ይህ አንድ ላይ ሲዳመር ያስከተለው ውጤት የባንኩ ዘርፍ በጣም መዳከም ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ የኤፕሪል 6 ግርግር ወይም ዘረፋ ኢንዱስትሪውን እንዲለይለት አደረገ፡፡ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ከቆዩት መካከል አንዱ ሉቢ ነበር፡፡

አንድ ባንክ ችግር ውስጥ ገብቷል ብሎ መናገር፣ ያውም በአገር መሪ፣ ባንኩ ሊዘጋ ነውና ገንዘብ ያስቀመጥክ ተሽቀዳድመህ አውጣ እንደማለት ነው፡፡ ፕሬዚዳንቱ ለምንድነው የሉቢን እድሜ የሚቀጭ ንግግር ያደረገው? እኔ እንደተመለከትኩት የፖለቲካ ጨዋታ ያለበት ጉዳይ ነበር፡፡

አዲስ አበባ ባንክ ውስጥ እአአ በ1970 ወይም 1971 የብድር ክፍል ኃላፊ በነበርኩበት ወቅት ብድር መስጠት ያዝ እናደርጋለን:: አንድ የብድር አመልካች ይመጣና እኔ የታወቅሁ ደንበኛችሁ ነኝ፤ ገንዘቡን በእስቸኳይ እፈልገዋለሁና ስጡኝ ብሎ ወጥሮ ይይዘኛል:: የገንዘብ እጥረት ስላለብን ሰሞኑን ተመለስ እለዋለሁ:: አመልካቹ በቀጥታ ወደ ባንኩ ሦስተኛ ሰው ወደ አቶ ገብረመድህን ሽንቁጤ ዘንድ ይሄድና ባንኩን በእርግጥ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞታል እንዴ? ብሎ ይጠይቀዋል:: ዜናውን ከየት እንደሰማው ሲጠየቅ ታደሰ እንደነገረው ይገልጻል:: እውነት አይደለም፤ የጠየቅኸውን ብድር አሁን ውሰድ ተብሎ ይሰጠዋል:: ሰውዬው ከተሰናበተ በኋላ አቶ ገብረመድህን ቢሮው ድረስ ያስጠራኝና “ስማ ታደሰ፣ ባንክ ገንዘብ አጥሮታል ወይም ችግር ውስጥ ገብቷል ብሎ መናገር በራስ ላይ የሞት ፍርድ እንደመፍረድ ነው፤ ያደረግኸው ስሕተት ትምህርት ይሁንህና ባንክ የገንዘብ እጥረት ገጥሞታል ብለህ መቼም ቢሆን እንዳትናገር” ብሎ የማልረሳውን ትምህርት አስተምሮኛል:: ዋናው አለቃችን አቶ ደበበ ሰምተው ቢሆን ኖሮ ምን ያደርጉኝ እንደነበር አላውቅም::

ሉቢን ገጠመው ስለተባለው ችግር ለመወያየት ስብሰባ ይጠራል:: ጠሪውና ሰብሳቢው የባንኮች ማደራጃ ቢሮ ኃላፊ ሻው ነበር:: ሻው የወሰደው አቋም የሕዝብ ገንዘብ እንዳይባክን አዲሱ የባንክ አዋጅ በደነገገው መሠረት ሉቢን የማእከላዊው ባንክ የሚሾመው ሰው እንዲቆጣጠረው ማድረግ ያስፈልጋል የሚል ነበር:: ባንኩ ከቁጥጥር ነጻ ለመሆን ከፈለገ ግን የባንኩ ቦርድ አባላት ከባንኩ የወሰዷቸውን ብድሮች እንዲመልሱ፣ ውዝፍ ብድሮች እንዲሰበሰቡ፣ የባንኩ ባለቤቶች ተጨማሪ ካፒታል እንዲያዋጡ፣ የባንኩ ፕሬዚዳንት እንዲባረር ያስፈልጋል ይላቸዋል::

ሉቢ ችግር ውስጥ የገባው አንድም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ማእከላዊው ባንክ ውስጥ ስላስቀመጠና ገንዘቡን መንግሥት በብድር መልክ ወስዶ ስለበላው ነው:: መንግሥት የወሰደውን ገንዘብ ቢመልስ ኖሮ የሉቢ

የገንዘብ እጥረት ችግር ከመቅጽበት ይቃለል ነበር:: ስለዚህ በመሠረቱ የሉቢ ችግር እራሱ መንግሥት የፈጠረው ነው::

የሉቢ ባንክ ፕሬዚዳንት ሚስተር ዲቫይን ላይቤርያ ውስጥ አሉ ከሚባሉት የባንክ ሰዎች አንዱ ነው:: ላይቤርያ ውስጥ ሁሉም ነገር በአንጻራዊ መልኩ ሲታይ አንዱ ከአንዱ ይሻላል ማለት ነው እንጂ ሚስተር ዲቫይንም ቢሆን የባንኩን ካዝና እንደራሱ ጓዳ ያየበት ጊዜ አይጠፋም፤ ለግል ድርጅቶቹ ብድር ሰጥቷል፤ ለጉዞ እየተባለ የውሎ አበሉን በደንብ ጨልፏል:: ቢሆንም ከብዙዎቹ ካየኋቸው የባንክ ሰዎች ቢሻል እንጂ የከፋ እንዳልሆነ ተመልክቻለሁ::

በስብሰባው ላይ ሻው ስላቀረበው ሐሳብ ምን አስተያየት እንዳለኝ ይጠይቀኛል:: እንደሻው አስተሳሰብ ታደሰን ገንዘብ ሚኒስትሩ ሲፈታተነው ሻው ጋሻና ከለላ የሆነለት ሰው ስለሆነና IMF ቢያባርረው የላይቤርያ መንግሥት እንዲቀጥረው ጥርጊያ ጎዳና ያበጀለት ሰው ስለሆነ የሻውን አቋም ከመደገፍ ወደኋላ አይልም የሚል ሳይሆን አይቀርም:: የሰጠሁት መልስ ግን እንዲህ የሚል ነበር:: በእርግጥ ውዝፍ ብድሮችን መሰብሰብ ያስፈልጋል፤ ባንኩም ቁጥጥሩን ማጠናከር ይኖርበታል:: የላይቤርያ ሕዝብ የቀረው ሉቢ ብቻ ነው፤ ላይቤርያኖች የሚያካሂዱት ባንክ ሉቢን ብቻ ነው፤ እውነቱን ለመናገር ሉቢን ችግር ውስጥ የከተተው እራሱ መንግሥት ነው፤ የመንግሥት አትኩሮት መሆን ያለበት ሉቢን እንዴት በቁጥጥራችን ሥር እናድርገው ሳይሆን ሉቢ ተጠናክሮ ሥራውን መሥራት የሚችልበትን መንገድ መፈለግ ላይ ነው፤ መንግሥት ሉቢን ለመንከባከብና ከችግር እንዲወጣ ለማድረግ ልዩ ኃላፊነት ያለበት ይመስለኛል ብዬ ተናገርኩ::

የባንኩ አዋጅ እንደጸደቀ አንድ ቀን ሻው የአዋጁን ቅጂ በቀኝ እጁ ጭምድድ አድርጎ ጨብጦ ወደኔ እያውለበለበው "ታደሰ፣ ይሄ ላንተ የባንክ አዋጅ ነው፤ ለኛ ግን ስንት የምንፈልገውን ሰው ማጥመጃ መረባችን እንደሆነ አታውቅም" ብሎ እየፈነደቀ ነግሮኛል:: የሉቢው ሚስተር ዲቫይንና

ኮሚሽኑ ውስጥ ከነበሩት የቀድሞ የባንክ አዛዦች አንዱ ሚስተር ቪንተን ቴለር ሥልጣን ላይ ለመውጣት ሲዋጋ ሙከራውን ለማክሸፍ በሥልጣን ላይ የነበረውን መንግሥት ረድተዋል የሚል ቂም ተይዞባቸው ስለነበር ብድር በምድር እንዲሉ እነቴለር የጠላቶቻቸውን ወዳጆች ለመምታት እየተዘጋጁ ነበር ማለት ነው፡፡ በተለይ ሉቢን ለመጣልና ሚስተር ዲቫይንን ለመዘረር የተደረገው ሙከራ፤ ጠንካራ የባንክ አዋጅ ያስፈልገናል ሲሉ ለካስ በአእምሯቸው የነበረው በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፎች ለመግደል ነበር፡፡

ሻው የጠበቀውን ያህል ሐሳቡን እንዳልደገፍኩለት ሲያውቅና የመንግሥትን ኃላፊነት አበክሬ ሳነሳ መልስ ባይሰጥም በጣም እንደተናደደ ከፊቱ ማንበብ ይቻል ነበር፡፡ ስብሰባው ሲበተን ሚስተር ዲቫይንና የሉቢ ባንክ ቦርድ ሊቀመንበር ቀርበው እናመሰግናለን አሉኝ፡፡ ሻው ይህንንም ዐይቶ ከሆነ የበለጠ እንደሚናደድ አንድና ሁለት የለውም፡፡

ከሻው ጋር የነበረኝ ግንኙነት ከዚያን ቀን ጀምሮ ተቋረጠ ለማለት ይቻላል፡፡ የማደራጃ ጽሕፈት ቤቱ የሥራ ፕሮግራም ምን እንደሆነ ስለማውቅና እኔው አርቅቄ ያስጸደቅሁት ስለሆነ በፕሮግራሙ መሠረት በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ያለኝን አስተያየት መስጠት ቀጠልኩ፡፡ ቢሆንም ፊት ለፊት ተገናኝቶ እንደሚደረግ ውይይት ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡

ቴለር የገንዘብ ሚኒስትሩን ከቦታው አነሳና የባንኩ አዛዥ አድርጎ ሾመው፡፡ ይሄ የሆነው እኔ ላይቤርያ በተመለስኩ አንድ ዓመት ሊሞላኝ አካባቢ ነው፡፡ ክስተቱን በእኔ ቦታ ሆኖ ለሚያየው ሰው አነጣጣሪ የእንጀራ ገመድ በጣሽ እንደተላከብኝ ነው፡፡ ቴለርና ሻው "ሰይ ብንል ብናከረባብት" ብለው ሚኒስትሩንና እኔን አንድ ላይ ለመቅጣት የወሰዱት እርምጃ ሳይሆን አይቀርም አልኩኝ፡፡ እነዚህ ሰዎች በሥራ እያመካኙ ሰውን ለማጥፋት የተነሱ ሳይሆን አይቀርም አልኩኝ፡፡ እኔንም ከሚኒስትሩ፣ ከዲቫይንና ከቪንተን ለይተው አላዩኝም ማለት ነው አልኩኝ፡፡ ሥልጣን ፈላጊዎች

በቅድሚያ የሚታያቸው ሥልጣናቸውን ተጠቅመው ሕዝብን በሚገባ ማስተዳደርና ኑሮውን ተረጋግቶ እንዲያሸንፍ መርዳት ሳይሆን የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን ማጥፋት ነው አልኩኝ፡፡ ለዚህ ነው የአፍሪቃ ችግር ሥር እየሰደደ የሚሄደው አልኩኝ፡፡ በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ የጠቀስኩትን ሚስተር ማክናማራን ካገኘሁት አፍሪቃን ጠፍሮ የያዘውን አባዜ ደርሼበታለሁ ብዬ እነግረዋለሁ አልኩኝ፡፡

ከሻው ጋር ስምም በነበርንበት ወቅት ገንዘብ ሚኒስትሩን አስመልክቶ “ማእከላዊው ባንክ ከገንዘብ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ውጭ መሆን አለበት የሚለውን ነጥብ እንዲህ አክርሮ የሚቃወመው እሱ እራሱን የባንኩ አዛዥ አድርገን ብንሾመው አቋሙ ምን ይሆን?” ብሎ ተንከትክቶ የሣቀው ትዝ አለኝ፡፡ አባባሉ ተስፋዬ ዲንቃን አስታወሰኝ፡፡ ተስፋዬ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር በነበረበት ወቅት ካፒታል ቻርጅ የሚባለው ነገር በፍጹም ለገንዘብ ሚኒስቴር መከፈል የሌለበት ነው እያለ ይሟገት እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን፡፡ እሱ የጦርነቱ ፊታውራሪ ሆኖ እነባንክም ሰልፋችን ከሱ ጋር ነበር፡፡ ተስፋዬ የገንዘብ ሚኒስትር ይሾምና የትግል ጓዶቹ፣ ተስፍሽ፣ ቶሎ በላ፣ ምን ትጠብቃለህ? መሣሪያው በእጅህ ገብቷል ብንለው፣ ቀልዳችሁን አቁሙ የገንዘብ እጥረት ስላጋጠመን ሌላ ተለዋጭ የገንዘብ ምንጭ እስካላገኘሁ ድረስ ክፍያው እንዲቀር ማድረግ አልችልም ብሎናል፡፡

ሻው ያኮረፈኝ የቴለር መንግሥት የሚፈልጋቸውን ሰዎች እማስያዙ ላይ ስላልተባበርኩት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ወቀሳ ኢትዮጵያም ውስጥ እያለሁ ያለፍኩበት ስለነበር ምንም አልገረመኝም፡፡ አንድ ቀን ገሰሰ ወልደኪዳን፣ የደርጉ የኤኮኖሚ ጉዳይ ኃላፊ ወይም ምክትል ሳለ፣ ይጠራኝና ቢሮው ድረስ እሄዳለሁ፡፡ እዚያ አንድ ፊቱን የማውቀው ሰው አገኛለሁ፤ ስሙን እረስቼዋለሁ፤ ቀኛዝማች ነው፤ በትውልድ የትግራይ ወይም የኤርትራ ክፍለሀገር ተወላጅ ነው፤ በትራንስፖርት ሥራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡ ገሰሰ ሰውዬውን ለምን እንደጠራው በውል ትዝ ባይለኝም

ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ትዝ የሚለኝ ሰውዬውን ለአብዮቱ ጭዳነት አስቦት ኖሮ እኔን አቋሙን እንድደግፍለት ወይም እንዳጠናክርለት አስቦ ነበር የጠራኝ፡፡ የገሰሰን አቋም ትክክል ሆኖ ስላላገኘሁት ለቀኛዝማቹ ሽንጤን ገትሬ ተከራከርኩለት፡፡ ለከሳሽ ምስክርነት የተጠራሁት ሰውዬ የተከሳሽ ጠበቃ ሆኜ ቁጭ አልኩ፡፡ ገሰሰ እንደተናደደብኝ አወቅሁ፡፡ የእውነት አምላክ ከሚቀየመኝ ገራሙ ገሰሰ ቢቀየመኝ ይሻለኛል አልኩ፡፡ ቀኛዝማቹ የወዳጄና ጎረቤቴ የመብራቴ መንግሥቱ ወዳጅ ኖሮ አልፎ አልፎ እንገናኝ ነበር፡፡ ነፍሴን ያዳንከው ሰውዬ ይለኝ ነበር፡፡

ሌላ ጊዜ ደግሞ የደርግ ጽሕፈት ቤትን ተገንና ደጀን አድርጎ በጣም ብዙ ሰው ስለማስጨረሱ የሚነገርለት ሻለቃ ብርሃኑ ከበደ የአዲስ አበባ ባንኩን የቁጥጥር ክፍል ኃላፊ ይስሐቅን ወስዶ በቁጥጥሩ ሥር ያውለዋል፡፡ ይስሐቅ የኤርትራ ክፍለሀገር ተወላጅ ነው፡፡ የባንክ ኃላፊዎች ደውለው መወሰዱን ይነግሩኛል፡፡ በዚያን ዘመን ከብርሃኑ የበለጠ የሚፈራ ሰው አልነበረም፡፡ ገንዘብ ያላቸውን ሰዎች አውጥቶ እየደፋ ገንዘባቸውን የዘረፈና ያስዘረፈ ሰው ነው፡፡ ሰዉ ሰው በላው ጭራቅ ይለዋል፡፡ እኔ ዐይቼው አላውቅም፡፡ ስልክ ደወልኩለትና ለይስሐቅ መታሰር ምክንያት ነው ስለተባለው ጥፋት እንደሚከተለው አስረዳሁት፡፡ ይስሐቅ በግሉ ምንም ያጠፋው ነገር የለም፣ አጠፋ የተባለው ጥፋት የባንክን መመሪያ ተከትሎ የወሰደው እርምጃ ነው፣ የባንኩን ህልውና ለመጠበቅ የወሰደው እርምጃም ነው፣ ሰውዬው የሚጠበቅበትን ነው የፈጸመው፣ መታሰር ካለ መታሰር ያለብን መመሪያውን ያወጣነውና የምናስፈጽመው የባንክ ኃላፊዎች ነን፣ በተሰጠው መመሪያ መሠረት የባንኩን ጥቅም ያስጠበቀውን ሰውዬ ማሰር ትክክል ስላልሆነ እንድትለቅልን፣ አይሆንም ካልክ ለእነመንግሥቱ ለመንገር እንገደዳለን አልኩት፡፡ በስልክ ከሃያ ደቂቃ በላይ ከተጨቃጨቅን በኋላ ጉዳዩን እንደገና አጣራለሁ አለኝ፡፡ በማግስቱ ፈትቶ ለቀቀው፡፡

አዲሱ የባንክ አዛዥ ሳሊቢ፣ የቀድሞው ገንዘብ ሚኒስትር፣ ወደ ባንክ ለመምጣት የጎሊና ዝግጅት ሲያደርግ ቆይቶ አዲሱን ቢሮ ለመረከብ ጥቂት ቀናት ሲቀሩት ሦስቱን የባንኩ አማካሪዎች ቤቱ ድረስ ይጠራና ታደሰ ባንኩን ለቆ ሄዷል ወይስ አሁንም አለ? ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ አለመሄዴን ይገልጹለታል፡፡ የተረዳሁት ሹመቱን ሲቀበል ታደሰን አልፈለገውምና አባርሩልኝ እንዳላቸው ነው፡፡ በምላሹ የቅጥር ኮንትራቱ የሚያልቀው ባንኩ ገብተህ ሥራ ከጀመርክ በኋላ ስለሚሆን አንተ የፈለግከውን አድርገው ያሉት ይመስለኛል፡፡

ከሳሊቢ በፊት የነበረው የባንኩ አዛዥ ለአዲሱ የገንዘብ ሚኒስትር የቅጥር ኮንትራቴን እድሳት ጥያቄ ለIMF እንዲያስተላልፍ ጠይቆት በጥያቄው መሠረት ተፈጽሞ ነበር፡፡ ሳሊቢ ከሚኒስትርነቱ ከተነሳ በኋላ በመንግሥት ወጪ ለእረፍትና ቤተሰቡን ለመጠየቅ ዋሺንግተን ሄዶ በነበረበት ወቅት IMF ደርሶ የቅጥር ኮንትራቴ እንዲታደስ እንደማይፈልግ ነግሯቸው ተመለሰ፡፡

የIMF ባለሥልጣኖችን ደጋግሜ ብጠይቅም ስለኮንትራቴ መታደስ የሚነግረኝ ሰው ጠፋ፡፡ የሚጠብቁት አዲሱ የባንኩ አዛዥ ሥራውን እስኪረከብ ድረስ መሆኑ ግልጽ ነበር፡፡ እቃዬን ለቀርቃቢ ዐሳይቼ የአውሮፕላን ቦታ ከያዝኩ በኋላ የመጓጓዣውን ቲኬት እንዲልኩልኝ ለIMF መልዕክት አስተላለፍኩ፡፡ የመጣልኝ መልስ ኮንትራቴ እንደማይታደስ የሚያረጋግጥና ወደመጣህበት ወደ ኦታዋ እንድትመለስ የሚል ነበር፡፡

አንድ እሁድ ቀን የሳሊቢ ረዳት መኖርያዬ ድረስ ይመጣና አማካሪዎች ሳሊቢ ቤት ድረስ እንድትመጡ ስለተባለ እንድትገኝ ይለኛል፡፡ አይ ተሳስተህ መሆን አለበት፤ ሌሎቹን አማካሪዎች መሆን አለበት፤ እኔ እዚህ ውስጥ ልኖርበት አልችልም፤ እንደምታየው እቃዬን ለመቀርቀብ በዝግጅት ላይ ያለሁ ሰው ነኝ፤ ኮንትራቴ እንደተሰረዘ ከIMF ማረጋገጫ ደርሶኛል እለዋለሁ፡፡ የለም፣ ግደየለህም፣ አንተንም ጥራው ብሎኛል ይለኛል፡፡

አሁንም አላመንኩትም:: በሌላ በኩል ረዳቱ ኮጀሎ በጣም ንቁና ቀልጣፋ ስለሆነ ጉዳይ ፈጻሚያችን እሱ ነው:: ይህም ሆኖ መጠራቴን ብጠራጠርም ከኔ አይቅር በሚል ከሌሎቹ አማካሪዎች ጋር ተያይዘን ወደ ሳሊቢ ቤት ሄድን:: አማካሪዎቹ እኔም መጠራቴን ሲያዩ ግር ተሰኙ::

ሳሊቢ እኔንም እንደሌሎቹ ጨብጦ ተቀመጥ አለኝ:: ስለባንኩ አደረጃጀትና ሌሎችም ጉዳዮች ውይይት ከፈተ:: ኮጀሎ ተሳስቶ ሳይሆን አይቀርም የሚለው ጥርጣሬዬ አሁንም እንዳለ ነው:: እንደ ሳሊቢም ሆኜ ሳስብ፣ አንዴ ቤቴ ድረስ ከመጣ እንዴት አገልለዋለሁ? ብሎ ያስተናገደኝ መሰለኝ:: ጥርጣሬዬ ቦታ እንደሌለው የተረዳሁት በውይይቱ መጨረሻ ነበር:: ኮንትራቴ እንዲታደስ ለIMF በማግስቱ ጥያቄ እንደሚተላለፍ ነገረኝ:: የIMF ባለሥልጣን ኮንትራትህ አይታደስም ብሎ በጻፈበት እጁ መልሶ ታድሶልሃል ብሎ እንዲጽፍ ሲገደድ ምናልባት በድርጅቱ ታሪክ የመጀመሪያው ሳይሆን አይቀርም::

ኮንትራቴ እንዲታደስ ሳሊቢ ለምንና እንዴት እንደወሰነ በውል የማውቀው ነገር የለም:: ግምት ግን አለኝ:: ኮንትራቴ እንዲታደስ ሳሊቢ አለመፈለጉን ባንኩ ውስጥ የነበሩ የሥራ ኃላፊዎችና አንዳንድ ሠራተኞች ጭምር ሰምተው ነበር:: የኮሚሽኑ አባላትም እንደዚሁ:: ሌላው ቀርቶ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሳይቀሩ የባንክን ዘርፍ ችግሮች ለመፍታት መንግሥት ያስጠናው ጥናትና የወሰናቸው ውሳኔዎች ግሩም ናቸው ተብሏል:: ፕሬዚዳንት ቴለር ታደሰን እንፈልገዋለን ብሎ በአገሩ ባለሥልጣኖች ፊት ተናግሯል::

አንድ ቀን ከባንኩ ሦስተኛ ሰው ከፔትሪ ጋር ጎን ለጎን ቁጭ ብለን ሥራችንን ስንሠራ ድምጹን ዝቅ አድርጎ ለራሱ የሚናገር አስመስሎ «የዚህ አለም ነገር ይገርማል፣ በአዲሱ የባንክ አስተዳደር ዘመን መጨረሻ መሄድ ያለበት ሰው መጀመሪያ እንዲሄድ እየተደረገ ነው» አለ:: የላይቤርያን ማእከላዊ ባንክ እንደገና ለማደራጀትና አጠናክሮ ለማቋቋም፣ የፈራረሰውን

የባንክ ኢንዱስትሪ መልሶ ለመገንባት እልህ አስጨራሽ ሥራ ለመሆኑ አንድና ሁለት የለውም። የኮሚሽኑ አማካሪ ሆኜ ዘርፉን ስለገጠሙት ችግሮች ጥልቅ ግንዛቤ አግኝቻለሁ፣ በተግባር እንዲተረጎሙ የቀረቡት የማሻሻያና የማጠናከሪያ ሃሳቦች ብዙዎቹን ያፈለቅሁትና አሰባስቤ በዘገባ መልክ እንዲቀረጹና እንዲካተቱ ያደረግሁት እኔ ነኝ፣ አዋጆቹ ሲረቀቁ አማካሪና አስተባባሪ ሆኜ የሠራሁት እኔ ነኝ፣ ከአንቀጾቹ ጀርባ ያለውን አስተሳሰብ በደንብ የማውቀው እኔ ነኝ፣ ባንኩ ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ሊከተለው የሚገባውን የድርጊት ፕሮግራም ያረቀቅሁት እኔ ነኝ። ስለዚህ ሥራው ገና ከመጀመሩ እኔ ተነስቼ ብሄድ ተልእኮው ሊሳካለት እንደማይችል ውስጠ አዋቂዎች ለአዲሱ አዛዥ ለሳሊቢ የነገሩት ወይም ያስጠነቀቁት ይመስለኛል።

ከሳሊቢ ጋር ስንሠራ እኔ ከሥራ ውጭ ሌላ የማየው ነገር እንደሌለ ተመለከተ። ለፖለቲካ ጨዋታም ምንም ዓይነት ዝንባሌ እንደሌለኝ ተረዳ። እሱም ሆነ ሌላ ማንም በተፅእኖ ኃይል ማድረግ የሌለብኝን እንደማያስደርገኝ፣ መምከር የሌለብኝን እንደማልመክር፣ ስሕተት ዐይቼ እንደማላልፍ፣ የሸፍጥ ተባባሪ እንደማልሆን ካየ በኋላ ለኔ የነበረው ከበሬታ ከፍ ያለ ይመስለኛል። ያልሆነ ነገር እኔ ዘንድ ይዞ መጥቶ እሰየው እንደማልለው ስለሚያውቅ ሌላ ተባባሪ ፍለጋ ይሄዳል። አጓጉል ሥራ ሲሠሩ ታደሰ እንዳይሰማ ይላል።

ሚኒስትር በነበረበት ወቅት ባንኩ እንዴት ከሚኒስትሩ ቁጥጥር ነጻ ይሆናል? ያለው ሰውዬ ግንባር ቀደም የባንክ ነጻነት ተዋጊ ሆኖ ቁጭ አለ። ከIMF ጋር ላሉት ግንኙነቶች በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል መሆኑ ቀርቶ ከባንኩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ተመሠረተ። ለአማካሪዎች የኮንትራት እድሳት የሚጠየቀው በገንዘብ ሚኒስትሩ መሆኑ ቀርቶ በቀጥታ በባንኩ አዛዥ ሆነ። ሚኒስትር ሆኖ የመንግሥት ገንዘብ ማእከላዊው ባንክ ውስጥ መቀመጥ የለበትም ብሎ የነበረው ሰውዬ እንደምንም ተጣብሶ በሙሉም ባይሆን የመንግሥት ገንዘብ ወደ ባንኩ እንዲመለስ አደረገ። ሌላም ሌላ።

ፔትሪ እንዳመለከተው ሌሎቹ አማካሪዎች ከእኔ ቀደም ብለው ወደየመጡበት ሲመለሱ በመጨረሻ የተሰናበትኩት እኔ ነኝ። የላይቤርያ ጸጥታ ሁኔታ አስጊ ስለሆነ አገሩን ለቅቀህ መውጣት አለብህ ብሎ IMF ባያዘኝ ኖሮ ሳሊቢ ኮንትራቴ እንደገና እንዲራዘም ለመጠየቅ ተዘጋጅቶ ነበር። ላይቤርያን ሦስት ዓመት ካገለገልኩ በኋላ እአአ በጁን 2001 ወደ ኦታዋ ተመለስኩ። ለስንብት ግብዣ ከተደረገልኝ ሆቴል እስከ መኖሪያዬ ድረስ በራሱ መኪና ነድቶ የወሰደኝ ማንነቴን ከማወቁ በፊት አጥብቆ የተዋጋኝ፣ ማንነቴን ሲያውቅ ግን ከፍ አድርጎ ያስቀመጠኝ ሳሊቢ ነበር።

ላይቤርያ በነበርኩበት ወቅት አየር ለመቀበል ከምንሄድባቸው ስፍራዎች አንዱ በከተማው በስተምሥራቅ በባሕር ዳርቻ የሚገኝ አንድ የመዝናኛ ስፍራ አለ። የሚያንቧርቅ ሙዚቃ ሁሌ ይሰማል። "ዲያሎ" የሚለው ሙዚቃ በአእምሮዬ ተቀርጾ ቀርቷል። ዲያሎ በኒውዮርክ ፖሊሶች በአርባ አንድ ጥይቶች ተደብድቦ የተገደለው የጊኒ ተወላጅ ነው። ምስኪኑን ደርሶ ሊያድነው የሞከረ ሰው አልነበረም። የመከላከያ መሣሪያ አልያዘም። ዘረኞች ዒላማ አድርገው ተኩስ ተለማመዱበት። እንዲህ ዓይነቱን ታሪክ ስሰማ አንኳን የግፈኛውን የራሴንም መፈጠር እስከመጥላት እደርሳለሁ። እንዲህ ዓይነቱ ወንጀል በኅሊናዬ ላይ የሚተወው ጠባሳ ምን ጊዜም አይፋቅም። እግዚአብሔርን እንዲህ ዓይነቶቹን ከይሲዎች ለምን ፈጠርክ? ብዬ አማርረዋለሁ።

ዲያሎ ወደ አሜሪካ የሄደው ሕይወቱ የሚለመልም መስሎት ነበር። ያተረፈው ግን ምኞቱና ተስፋው ከዕድሜው ጋር አብሮ መቀጨት ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ወጣቱ አሜሪካ ገነት እየመሰለው አገሩን ጥሎ ሲኀርፍ ይታያል። ከአገር ውጭ አገር እንደሌለ የሚረዳው ውሎ ሲያድር ነው። ባለቤት በመሆንና እንግዳ በመሆን መካከል ልዩነት አለ። በራስ አገር ንጹሕ አየር ተንፍሶ፣ እንደ ጥጃ ቧርቆ፣ ከጠፋም አሹቅ በልቶ እንደማደግና እንደማርጀት የመሰለ ነገር እንደሌለ የሚያወቀው በእንግድነት ውጭ አገር ተሸማቅቆ የሚኖር ሰው ብቻ ነው።

በዲያሎ ላይ ስለተፈጸመው ግፍና አገርን ጥሎ ስለመኮብለል ያለኝን አስተያየት በግጥም በመጽሐፉ መጨረሻ አስቀምጬዋለሁ። የተገጠመው በየካቲት 1992 በሞንሮቪያ ከተማ ነው።

# መደምደሚያ

ታደሰ ማነው? ለሚለው ጥያቄ መልሱን ለማስጨበጥ የወጣሁበትንና የወረድኩበትን የሕይወት ጎዳና ለአንባቢ አሳይቻለሁ፤ ገጎ ስራጋና አባባ አሶሬ በልጅነት አእምሮዬ ውስጥ ጽፈው ያስቀሩትን ገልጩ አስነብቤአለሁ:: አባቴ ለሰው በጎ እንጂ ክፉ የማይመኙ፣ በደልና ግፍ የሚያንገሽግሻቸው፣ ሰውን በሰውነቱ እንጂ በሀብቱ ወይም በሹመቱ የማያበላልጡ፣ ማንነታቸውን በሀብት ብዛት ወይም ማነስ የማይለኩ፣ ከሰውና ከፈጣሪያቸው ጋር ስምም ሁነው ያመጣውን ሁሉ በጸጋ እየተቀበሉ የኖሩ ሰው ናቸው:: አባባ አሶሬ ደግሞ ሳላውቅ ፍርድ አዛብቼ ከሆነ እግዚአብሔር ይከፋብኛል ብለው ከመፍራት የተነሳ የተጣላን ካስታረቁ በኋላ ለደስደስ የሚቀርብ ምግብም ሆነ መጠጥ ካለ በአፋቸው እንዲገባ ፈጽሞ የማይፈቅዱ ሰው ነበሩ:: ሥነልቦናዬን ቀርጸው ማንነቴን የወሰኑት ሁለቱና እነሱን የመሳሰሉ ሰዎች ናቸው::

ኢትዮጵያችንም ሆነች ዓለም ለሰው ልጅ የተሻለ ስፍራ የሚሆኑት እንደ አሳዳጊዎቼ የመሳሰሉ ሰዎች ሲበራከቱና ደቀመዛሙርቶች ሲያፈሩ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ::

ትምህርት ያለ ግብረገብ ብቻውን አደገኛ መሣሪያ ሲሆን ዐይቻለሁ፤ ብልጣብልጦችና የሥልጣን ጥመኞች በማደንዘዣነት ወይም በማስፈራሪያነት ሲጠቀሙበት ተመልክቻለሁ:: ተባባሪያቸው ላለመሆን ያደረግሁት ትግል ያሰብኩትን ያህል ባይሆንም ውጤታማ በመሆኑ ደስ ይለኛል::

ደካማ ሰው ዘለዓለም ይኖር እየመሰለው በአንድ አፍታ ፈርሶ ለሚቀረው ሥጋውና ብን ብላ ለምትጠፋው ሕይወቱ እያደላ ከመቃብር በላይ

በሚውለው ስሙ ላይ ሲፈርድ ከማየት የበለጠ አሳዛኝ ነገር የለም፡፡ ግፈኞችን፣ ተፅቢተኞችን፣ ፍርድ የሚያዛቡትን፣ ደሃ የሚያስለቅሱትን፣ አንዱን ቀብረው ሌላውን የሚያነግሡትን መምከርና መመለስ ይገባል፣ ሲያስፈልግም ባመቸው መንገድ ሁሉ መዋጋት ያስፈልጋል፡፡

ታደሰን ከውስጥ ሆኖ ይገፋው የነበረው ኃይል ምን እንደነበረ አንባቢ አሁን እንደተረዳልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በኢትዮጵያ ሰላም ሰፍኖ ሕዝቡ የኑሮ ደረጃውን ለማሻሻል ያለውን ፍላጎት እውን ለማድረግ እንዲችል ቁልፍ በሆኑ ልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ከተሰየሙት ዜጎች ብዙ ይጠበቃል፤ ሕዝብ ለልማት እንዲነሳሳና እንዲሰለፍ የሚያንቀሳቅሱትና የሚመሩ እነሱ ናቸውና፡፡ ሕዝብ መሪውን ካመነ መፈንቀል የማይችለው ድንጋይ እንደሌለ ጽኑ እምነት አድሮብኛል፡፡ ምስጢሩ ያለው የሕዝብን አመኔታ ከማግኘቱ ላይ ነው፡፡

በአመራር ላይ የተቀመጠ አንድ ኀላፊ ከዚህ በታች የሰፈሩትን መርሆች የሥራ መመሪያው አድርጎ ቢቀበላቸውና ለተግባራዊነታቸው ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርግ ፍቅርና መተሳሰብ ይደረጃሉ፤ ተመሪ በመሪው ላይ ያለው እምነት ያድጋል፤ የእድገትና የብልጽግና በር ይከፈታል፤ ብሎም ሰላም ይሰፍናል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ፡፡ ሆኖም፣ የሰው ልጅ ከሌላው ልምድ ለመማር ያለው ፍላጎት ወይም ዝንባሌ ዝቅተኛ ስለሆነ ብዙ መጠበቅ ባይቻልም ተስፋ ሳንቆርጥ ዴሞክራሲያዊ አሠራሮችን ከማራመድና ከማስፈን ጎን ለጎን የመሪዎቻችንን ባሕርይ ለመግራት ወይም ለማረቅ ትግላችን መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ኃላፊነት የተሰጠህ አንተ ሕዝብን እንድታገለግል እንጂ ሕዝብ አንተን እንዲያገለግል እንዳልሆነ ዘወትር አስታውስ፤

ሥልጣንን ሕዝብን ለማገልገያ ሳይሆን ለራሳቸው መገልገያ ለማድረግ ከሚፈልጉ ራቅ፤

ሥልጣንህን የሕዝብ አጀንዳ ማራመጃ እንጂ የግል ፍላጎትህን ማስፈጸሚያ ወይም ድክመትህን ማንጸባረቂያ መሣሪያ አድርገህ አትጠቀምበት፤

በአንተና በሥርህ በተመደቡ ሠራተኞች መካከል ምንም ዓይነት መሠረታዊ ልዩነት እንደሌለ እመን፤

የሠራተኛን ክብር በፍጹም አትንካ፤ ያለበለዚያ ወቅት ጠብቆ ወይም አድብቶ ያዋርድሃል፤

ሠራተኛን በማስፈራራት ሳይሆን በፍቅር ኃይል ለመያዝ ሞክር፤ ይህም ሲባል ጠንክረህ መገኘት ሲኖርብህ አትልፈስፈስ፤

በኃላፊነትህ ሥር የተመደቡትን ሳታበላልጥ በእኩልነት ተመልከታቸው፤

አታዳላ፤

የበታቾችህን በጽሞና አድምጣቸው፤

ፍትህ አታዛባ፤

በኃላፊነት የተመደብከው ሁሉንም ነገር ታውቃለህ ተብሎ ሳይሆን በሥርህ የተመደቡትን አዋቂዎች ጥረት እንድታስተባብር መሆኑን አትዘንጋ፤

አባት በልጆቹ ላይ ክፉ እንደማያስብ ሁሉ በሥርህ ከተመደቡ ሠራተኞች ጋር እልህ አትጋባ፤

ከሥርህ የተመደበውን ሠራተኛ አበረታታው እንጂ በራሱ ላይ እምነት እንዲያጣ አታድርገው፤ ቀልቡን አትግፈፈው፤

አሉባልታ የሚያመላልሱትን አታቅርባቸው፤

በሥራህ እንጂ በሰዎች አትመካ፤

ለእውነትና ለተበደለ ጥብቅና ቆመህ በመሸበት እደር፤

ዕድልና ሰው ከጊዜ ጋር ተለዋዋጭ መሆናቸው አትርሳ፤

ስሕተትህን በጸጋ ተቀበል፤

የማታውቀውን አውቃለሁ ብለህ ከመቅረብ የማታውቀውን አላውቅምና አስተምሩኝ ብለህ ብትቀርብ የሰዎችን ከበሬታ እንደምታተርፍ አትጠራጠር፤

ምስጉን ሥራ፣ መልካም አርአያነትና ትክክለኛ ዳኝነት የደስታ ምንጭ መሆናቸውን አትርሳ፤

ሰዎች ያላግባብ ቢበድሉህ ወይም ቢያንገላቱህ የእነሱን ኀሊናቢስነት እንጂ ያንተን ማንነት ስለማያንጸባርቅ አትበሳጭ፤ ሞራልህን አታስነካ፤

ከሸፍጠኞች፤ ከግፈኞች፣ ከጨቋኞች፣ ከቀማኞችና ፍርድን ከሚያጓድሉ ጋር አትግጠም፤

ተቻችሎ መኖር ድክመት አይምሰልህ፤ ይህም ሲባል እያወቅህ ሐቅን አታዛንፍ፤

ሐሳብህን የሚቃወም ሰው ሲያጋጥምህ ከእኔ የተለየ ሐሳብ ያለው ሰው ተገኘ ብለህ አስብ እንጂ ጠላት ተነሳብኝ ብለህ ሥጋት አይግባህ፤ ይልቅስ

የሐሳብ ልዩነት ባይኖር ኖሮ የሰው ልጅ ከነበረበት ፈቀቅ አይልም ነበር ብለህ አስብ፤

ሁሉንም እንደኔ በደላው ወይም ማንም በእኔ ላይ የደረሰው ስቃይ ባልደረሰበት ብለህ ተመኝ፤

ሁሉም ነገር ያልፍና ስምህና ሥራህ ብቻ ለዘለዓለም እንደሚቀሩ አትርሳ፤ ስለሆነም ለፈራሹ ሥጋህ መጠን አልፈህ አታድላ::

# ግጥሞች

በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ ትረካዎች በተመለከተ በልቤ ውስጥ የሚጉላላውን ጥልቅ ስሜት ከስድ ንባብ ይልቅ በግጥም ማንጸባረቅ እንደሚሻል ተረድቻለሁ፡፡ መደበኛ የግጥም ሕግጋትን ብሰባብራቸውም የተጠቀሰውን አጻጻፍ ዘይቤ በመጠቀም ውስጥ ውስጤን የሚነዝረኝን ትኩሳት ለአንባቢ ማሳየት እችላለሁ የሚል እምነት አለኝ፡፡

# ገሀነም ወይስ ገነት?

ገና በጨቅላነቴ

ባከተመ ማግስት ወተት መጋቴ

በሕይወት እያለች ያቤሸወት እናቴ

ዶቃና ማተብ ባንገቴ

ቅቤ ባናቴ

በቁንጮዬ ማማር አይ ኩራቴ፤

ጀምሬ እንደእንቦሳ መቧረቅ

በጎርፍ መንቦጫረቅ

ሽኮኮ በነበረበት ወቅት ትልቁ ብርቅ

ጥብቆ ጥለቅ አልጠልቅ

ተያይዘን ትንቅንቅ

ክፉና ደግ ሳላውቅ

ከብት ሳር እንዲበላ

ወረድን ቆላ

መጠሪያ ስሙ አጋላ::

ታላቁ ደንባርጋ

አትንኩኝ ባዩ የስራጋ

ተጣልቶ ከልጅ ከጎረቤት

አየሁ ወንድማማቾች ሲደበድቡት በኅብረት

ቆጥረውት እንደጠላት

ባለመረዳት እንዳላቸው ሁሉም የተወራረሰ ሕይወት::

ቀኑ ትዝ ይለኛል እንደዛሬ

ጠራራ ፀሐይ እንዲሁም የሳለሞ[3] በሬ፡፡

ደንቡ በመካከል

ግራና ቀኝ ሲከላከል

አረፈ ዱላ በጭንቅላቱ

ግንባሩ ተበርግዶ ደሙ ፈሰሰ ባናቱ፤

ደንቡ እልኸኛ

ለጥቃት የማይተኛ

ዘለለ ሊያሸብር

ወራባ[4] የማንገፍር

የዞጋራ[5] ጥፍር

አጥቂውን ሊዘርር፡፡

---

[3] ባካባቢው የነበረ ሀብታም ገበሬ

[4] በጉራጌኛ ጎበዝ

[5] በጉራጌኛ ነብር

ገጠማቸው ደም ተላብሶ

እሳት ጎርሶ

አጥር ምሶ::

የወንድማማቾቹ መተጋገዝ ቀረ በአእምሮዬ ተቀርጾ

ጎሊናዬ በበደልና በአድላዊነት ላይ አምጾ::

ዘመናት አልፈው ዘመን ተተክቶ

ዘሩ የተበላሸ ፍጡር በዝቶ

በመርዘኛ በሽታ ተወግቶ

በሞራል ድርቅ መሬት ነቅቶ

የአገሬ ሰው ደህይቶ

አየሁት ተስፋው ተንኮታኩቶ::

ጥንብ አንሳዎች አንዣበቡ

ተጠራርተው ተሰባሰቡ

በአድማ ተረባረቡ

ደካማውን ዘንጥለው ሊመገቡ

የአዞ እንባ ሊያነቡ

ከዚያም እርኩስ ገድላቸውን ሊናበቡ።

ሙታን ተነሱ ከመቃብራቸው

ርኩቻው እንቅልፍ ነስቷቸው

ዘር መጥፋቱ የሞት ሞት መሆኑ ታውቋቸው።

እንክርዳዱን ለመንቀል ተማማሉ

ማ ማንን ወለደ? ቢሉ

የፍጡራን አመጣጥ ቢያሰሉ

ተከሰተላቸው የኃይል ልጅ መሆኑን ኃይል

በቀል መውለዱን በቀል

ተረግዞ በበደል

የተጸነሰ በፍረደ ገምድል::

ያገሬ ሰው ኖረ ሳይታደል

የቆመበትን መሬት ሲነድል

ሲግተለተል ወደ ገደል::

ሳይንስ ያልተማረ ከትውልድ ትውልድ

ያልተገነዘበ ኃይል ኃይልን እንደሚወልድ

መቆሚያ ሳይኖረው የሚዥጎደጎድ

እያንቧረቀ እንደነጎድጓድ

እንደሚጠራርግ ያገኘውን ሁሉ በመንገድ::

ነገሩ የተበላሸው ልጆች ሆነን

ትርጉሙ ሳይገባን

ጨዋታ ሲያምረን

የቡድንና የቡድን አባቶች ተባብለን

ቄጠማና አበባ እያለ ቦምብና መትረየስ መርጠን

ጎራ ለይተን

በአደገኛ የ«አዋቂዎች» ጨዋታ ተማርከንና ተዋድቀን

አሸናፊ በተሸናፊ ሲሳለቅ ረክተን

ሳናጤን ተሸናፊ አሸናፊን ለመጣል እንደሚጠብቅ ጊዜን።

የመጠፋፋት ትልም

የማያከትም

የዘለዓለም

ይሄ ነው ገሀነም።

ከይሲ የጥፋት እሳት ሲለኩስ

የመበላላት ድግስ ሲደግስ

ያስከሬን ጉድጓድ ሲምስ

መደመርና ማባዛት እያለ መቀነስና ማጣፋትን ሲያወድስ

ሕዝብ መግቢያ ጠፍቶት ሲታመስ

እንዲሁም፣ ዳኝነት ለወገናዊነት ካሻጠረ

በሌላው ፊቱን ካዞረ

ሐቅን እንዳያይ ከታወረ

በኀጠኞች ከታጠረ

በእርኩስ ዓላማ ከነፈረ

የመሪ አእምሮ በትዕቢት ከተወጠረ

በመናኛ ድርጊት  ከከሰረ

ፖለቲከኛ በከፋፋይነት ንግድ ከከበረ

ንብረት ጠባቂ ባላደራ ከቀማኛ ጋር ካሴረ

ፍትሕን ለማንገሥ

ክብርን ለማስመለስ

ጥላቻን ነቅሎ ፍቅርን ለማላበስ

ሁሉም እንዲባባል አንቺ ትብሽ አንተ ትብስ

ብሎም ኢትዮጵያዊነት እንዲታደስ

የረከሰውን ለመቀደስ

ይገባዋል ያገር ወዳድ ልብ ሊሸፍት

የደም ስሩ ሊነረት

ኅሊናው ሊያቃትት

ምሁር በፍትሕ አምላክ እያለ ሊወተውት

የአሻፈረኝ ሠራዊት ሊበራከት

ጀግና ሊያውጅ ክተት::

በፖለቲካ ሊቃውንት ጥንትም እንደተገለጸው

የሚገባውን ነው ሕዝብ የሚዋጀው

ገሀነም ወይ ገነት ታስቦ በከፈለው

መሥዋዕትነት በማይቀረው::

# የኢትዮጵያ አብዮት

በልጆችዋ ጡጫ እንዲሁም እርግጫ የቆሳሰለችው፣ የተንገላታችው

ገበናዋ ታይቶ ዓለምም ጉድ ብሎ እርቃን የቀረችው

ደረትዋን ዳሌዋን እምብርትዋን ሁሉንም ምኑን ምናምኑን

ላስራ ሦስት ወራት በፀደይ በበጋ በበልግም በክረምት ገልባ የሰጠችው

ፈጣሪ ፍረደው የወላዲት መካን ሆኜላችኋለሁ

የገበና ሽፋኝ አልተፈጠረም ወይ፣ እናንተ ኀፍረተቢስ

እናት ኀፍረተቢስ እያደረጋችሁ ብላ የጮኸችው

ጠብቃ ብታጣ ኮረምቱ ሶሬሳ ወዳቂ እሚያነሳ

ሁሉን እርግፍ አርጋ ሞት አይሉት ሰመመን ባፍጢሟ ተደፍታ

ተከናነበችው፡፡

እናቴን የማላውቅ ኢትዮጵያ እምዬ

አይዞሽ ደረስኩልሽ ልጥል ነቃቅዬ

እሾህ ጋሬጣሽን ላነደው አምክዬ

ብበላም እንቆቆ ያለምባንክን ንቂ

የንዋይ አምሮቴን ካእምሮዬ አውልቂ

ክብሬ ደስታዬ በኢትዮጵያ እናቴ መሆኑን አውቂ

ተጋሁኝ ለሥራ ባጨሩ ታጥቂ።

የድህነት አምባ የደዌ ሙዝየም

የደንቆሮ አምባ ማእከል የመሃይም

አምታች ቃልቻ የሰፈረባት

ቀርቦለት ቆንጆ የሚደፍርባት

ከሌለው ተነጥቆ የሚበላበት

ሱሪ በአንገት የሚወልቅባት

አወናባጅ ሐቀኛን የረገጠባት

መብት እጅ በጅ ተቸርችሮባት

አቆርቋዥ የሰፈነባት

ግንድ ከቅርንጫፍ የተንሰራፋባት

የደለበባት ደም መጣጭ በዋግምት

ኢትዮጵያችን ናት የፈረደባት

ዋይታዋ የሆነ የቁራ ጩኸት

ሐቀኛ ልጅዋ እስኪደርስላት።

ጎሊናው ተደፍኖ ማሰብ የተሳነው

አካሉን አቁስሎ ይህ መብል ነው ያለው

እንደዳይነሶር ለሆዱ አደር ለተራበው

እራሱን በልቶ እንደወደመው

አጥፍቶ ሲጠፋ ማየት የተሳነው

ተነሳ ጎበዝ በጊዜ እናንበርክከው

አካላቱን ዳሰን ይወገድ የተበላሸው

አለ አብዮተኛ ወደፊት ያማተረው።

ደም መጣጩ ሁሉ አፈ ልክስክሶ

በቀላማጅነት ሆድን ያሻከረ ስብእና አራክሶ

ብዙውን ብሔር በስም ማጥፋት ዘመቻ ጥላሸት አቶ አልብሶ

የቂም በቀል ትውልድ በብዛት ጠንስሶ

አስክሮ ሊጨርስ አናክሶ አናክሶ

ሞራለ ስንኩል ተሸፋፋኝ ሽፋፋኝ አቶ አለባብሶ

የሕይወት መሠረት መጣርን መጋርን መሥራትን አራክሶ

ዘርፎአደርነትን አስመሳይነትን ክቦ ክቦ አንግሦ

ይህ ሁሉ በሽታ ይነቀል ከሥሩ ይጣል ተገርስሶ

ያቀፈው ሥርዓት በስብሶአልና ይመንገል በግፊ በኃይል ተደርምሶ

የቅጥፈት ማጎደር፣ ማንአህሎኝነት ሁሉም ተደምስሶ።

ይደልብ ሀብታችን ይድላው ሕይወታችን ይስፈን ሰላማችን

የእድገት አቅጣጫ ባዲስ ተቀይሶ

ብሎ ተነሳ አብዮተኛ

ኢትዮጵያ ከወደቀችበት ሳትነሳ ተማምሎ ላይተኛ።

ኢትዮጵያዊነት የማፈርያ ሳይሆን መፈሪያ መጠሪያ መታወቂያ አርማ

ሁሉም የሚሰለፍ በሽሚያ ሊያነግበው

ለጥፎ በግንባር በጆርባ በደረት ዓለም እንዲያየው

አብስሮ መሆኑን የሰው መጀመሪያ

ነበረ ምኞቱ ያገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንቅልፍ ለምኔ ያለው፡፡

የግራ የቀኙን ቃኝቼ ዐይቼ

ተነሳሁ ለማብሰር ለውድ ወገኖቼ

ለዘመኔ ትውልድ ለትግል ጓዶቼ

ቅብብሎሽ ዱላ ይዘው ለሚሮጡት

የነገን ምንነት ወሳኞች ለሆኑት

አንድም በሠሩት አለዚያም ባልሠሩት

መፍጠር እንደሚቻል አዲስ ኢትዮጵያ

ለልጆችዋ ሁሉ እኩል መናኸርያ፡፡

እንደዚህም አልኩት አማኙን ወገኔ

ያመነ በታምር በጽድቅ በኩነኔ

የእግዚአብሔር ምርጥ ናት ኢትዮጵያ እናታችን

አይደለም መውደቅዋ ለመሰባበር ወይ ለመበታተን

ነው እኮ ባምላክ ፈቃድ ለመጠገን ለመነሳት

የክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት የሚበሰርባት

የሚነፋባት ባራቱም ማእዘን መለከት

ጻድቃን ከኀጥአን ሲለዩ ተብላ ምድረገነት

አውሬና ሰው ከመላእክት ጋር የሚፈነጩባት

ሳይታወቃቸው ቀን ከሌሊት

ላያዩ ግፍ ጭቆና ዋይታ ለቅሶ ሐዘን

ሳይውል የረሃብ መድኃኒት ለማስተንፈሻ ቁንጣን

ሰው ለሰው የደስታ ምንጭ እንደሚሆን

መድኃኒቱ እንጂ እንደማይሆንበት ባላንጣ ሰቀቀን።

ገነት ከደጅህ ቀርባለች ስለተባለ

ልቤ በምኞት ነሆለለ

ሽፈተ ተነሳ ኮበለለ

የነፍስ አድን መሣሪያ በሐሳብ ወለወለ

በምድረሲኦል ገንቢና ጠባቂ ላይ አቀባበለ፡፡

ተነሳሁ አዲስ ወኔ ተላብሼ

አንቺን ይድላሽ እንጂ ደሜንም አፍስሼ አጥንቴን ከስክሼ

እጠራርጋለሁ ግሳንግሱን ሁሉ በእንባ ማድረቂያሽ አፍሼ

እጥለዋለሁ እንዳያንሰራራ በጸረሕይወት ኬሚካል ለውሼ

አራቱ ማእዘናትን ከዳር እስከዳር ዳር አስሼ፡፡

ይሻላል ፈውስ መሻት ታማለች እማዬ

ተነስ ወንድምዬ ተነሽ አበባዬ

ብለን ተባብለን በልጅነት መንፈስ ሁሉን ነገር ጥዬ

የሕይወቴን እትብት ከተጨቆነ ጋር በገሀድ ቀጥዬ

ፍቱን መድኃኒቴን አእምሮዬን ስዬ፣

ለመሆን አንደበተ ርቱዕ ጥብቅና ለመቆም ባደባባይ ውዬ

ሐሳቤን ለመግለጽ ማንጎሌን አሹዬ፣

ጎበዝ ተበራታ ያ የጠበቅኸው ቀን ይኸው ነግቶልሃል

ያዘው ሳያመልጥህ ክንድ ይፈርጥም ብዬ

ወደኋላ ሳልል ይኸው ዘመትኩበት በኋላ ቀርነት በሁለመናዬ::

እውቀት፣ ትምህርት፣ ማሰብ፣ መመራመር፣ መጭመቅ ጭንቅላትን

የሚሆኑ መስሎኝ ፍቱን መድኃኒት ለያዘን አባዜ

ለሚሉት በሽታ ወገኔ ዘመዴ ማለት ልጄ የወንዜ

ቦይ ቀደን ለማገናኘት ዶርዜ ከመንዜ

ለማፍሰስ ኢትዮጵያዊነት ያለገደብ ከኦሞ እስከ ተከዜ

ነበረ ምኞቴ ሽቅብ ለመውጣት ቁልቁል ለመውረድ ያለሐሳብ ምንም ጊዜ::

ሕይወትህ በሕይወቴ መሆኑን

በሚገባ ጠንቅቀን አውቀን

ይህ የኔ ያ ያንተ ተባብለን ላንከፋፈል

በተቃራኒው አንተ ትብስ አንቺ ትብሽ ልንባባል

ይበልጥ ግን ይበልጥ የቸገረው ሊብስ

ልንባባል ያንተ ሕይወት ሲኮስስ

ምን ዋጋ አለው የኔ ብቻውን ቢንከላወስ

ካልሆነ በቀር ለማኝ ለመሆን ረሃብን ለማስታገስ

ብሎም ክብርን በትብያ ለማርመስመስ

ላይቻል ቆሞ መሄድ የተነሳ ካቅም ማነስ

ሊኮን የባላንጣ ሲሳይ ለባለደንደስ

መከፋፈል ነፋስ ለመስገባት ቤት ለማፈራረስ

መሠረት ለመሸርሸር ብሎም የቆሙበትን መሬት ንዶ ለማረስ

ለራስ ላይኮን ጠላት አስገብቶ ለማውረስ

አክሊል አውርዶ ጠላት እራስ ላይ ደፍቶ ለማንገሥ

ኋላም ተቀምጠው የሰቀሉትን ቆሞ ለማውረድ አቅም ሊያንስ

እጣችን ሊሆን የሚያዝ የሚጨበጥ ጠፍቶ ልንባክን መላ ጠፍቶን ልንርመሰመስ

ባልሞት ባይ ተጋዳይነት ልንንከላወስ

አየር ለመቧጠጥ አፈር ለመማስ

እራስን ለማመቻቸት ለቀላል ጉርስ

በዚህ ዓይነት ሁላችንም አንድ ባንድ ልንዋጥ ልንደመሰስ

ኢትዮጵያዊነት ሊዘቅጥ ወደ ምድረ ከርስ

ፈጣሪ ይህን መዐት ዕያየህ እስከ መቼ ትታገስ?

እባክህን በምታውቀው ረቂቅ ጥበብህ የጎበጠውን አቅና

መንገድ የሳተውን መልስ

ማስመስከር እንዲቻል ኢትዮጵያችን እጆቿን ወደ እግዚአብሔር

መዘርጋትዋ እንዳልሆነ ዋጋቢስ

ቀን ሊወጣ መስሎኝ

አዲስ ዘመን ልናይ እየነጋ መስሎኝ

መስሎኝ፣ ወታደር ከሲቪል የሚተባበሩ

ሕዝብን በሰላም በርጋታ በፍቅር የሚያስተዳድሩ

በጭቆና ላይ በጋራ አሲረው በጋራ አብረው በጋራ ሚዘምቱ

ጠላት ወዳጅ ሆኖ የግራ የቀኙን ትጥቅ የሚያስፈቱ

አድናቂያቸው በዝቶ ሽማግሌ አሮጊት እንዲሁም ወጣቱ

ሁሉም ደስ ብሎት ኢትዮጵያ ተብላ ምድረገነቲቱ

የሚፈስብሽ ማርና ወተቱ

የኛይት ወርቂቱ

በሦስቱ ቀለማት ያሸበረቅሺቱ

ባራቱም ማእዘናት ባርባራቱ ታቦት ታጥረሽ ያለሺቱ

እማማ ኢትዮጵያ የጥንቱ የጠዋቱ

የድንቅነሽ እናት የሰው ዘር ምንጪቱ

የሸራቢን ደባ ያፈራረስሺቱ

በራጉኤል ደጃፍ ክርስቲያን ከእስላም ያስተባበርሺቱ

የቱን ላውራ የቱን ትቼ ኧረ ምኑን ስንቱ?

እንዲያው ዝም ይሻላል ቃል አይጥፋ ከንቱ::

አወይ ደመፍል መሆን ነዳጅ ባገር ፍቅር

ቆም ብሎ ማሰብ ግራ ቀኝ ማማተር

በውል አድብቦ አማራጭ መመርመር

ተብሎ ነበረ ጊዜ ማባከን ነው ተቆጥሮ እንደነውር::

ሥራው የነበረ መመራመር

የዓለም ሕዝቦችን ልምድ በውል መቀመር

ጥቅምና ጉዳት ማንጠርጠር

አንጓሎ ጎጂን ከጠቃሚ ማበጠር

ጠብቆ ሚዛን ቀኝን ከግራ ማሰባጠር

የሀብት ክምችትና ሰላም እንዲዳብር

ብሩህ የሥራ እድል እንዲፈጥር

ነበር የመማሩ ዓላማ ግራ ባይጋባ ኖሮ ምሁር።

ከሰሜን ከደቡብ ከምዕራብ ከምሥራቅ ተጠራራ

ተካተተ ባብዮት ጎራ

ሊፈታ ያለማደጋችንን ምስጢር

መሆኑን ሰው ሰራሽ ወይስ ተፈጥሮአዊ ቅምር

ተይዘን እግር ተወርች ተደርገን ጥፍር

ለምን እንደተሸከምን የድህነት ቀምበር።

ምሁር ተብዬው ግራ ቢገባው

ኢትዮጵያን የተበተባት እንቆቅልሽ መፍታት ቢሳነው

የእናቱ ችግር የእግር እሳት ሆኖ ቢለበልበው

ቀኝ አውለኝ ብሎ በሚያማትብ አማኝ አገር

መልሱ ግራ ነው ብሎ አምበልብሎ አማኙን ግራ አጋብቶት አረፈው::

ነገሩ የቸገረው እርጉዝ ያገባል ሆነና

በክፋት ሳይሆን በቀና

የወደቀችውን እናታችን አንገት ለማድረግ ቀና

ወዳጅ ደስ እንዲለው ጠላት ተቃጥሎ እንዲቀና

ነበረ ምኞቱ የወጣቱ ለእናቱ ለመጓዝ ለመገስገስ

ቀኝ ይሁን ግራ ያዋጣል ብሎ ምሁር በቀየሰለት ጎዳና::

ኢትዮጵያዊ የማይደፈር የማይገሰሰው

በወግ አጥባቂነቱ የታወቀው

በታምር አማኝነቱ የተደነቀው

ከያዘ የማይለቅ የማይፍረከረከው

ከአይሁድ በላይ አይሁድ የሆነው

በግሪጎርያን ዘመን አቆጣጠር ዓለም በተቀበለው

ሪቪዥኒዝም ነው ብሎ የተሣለቀው

ያነገበ ታምርንና ታማኝነትን እንደ መለያው

ለችግርህ ነው ቢሉት ግራ መንጎድ መፍትሄው

በማለዳ ተነሳ ብሎ እግዚኦ ስምንተኛው ሺህ ታምረኛው::

ተባለ መራመድ ሲቻል የምን መጎተት

በደረት መሳብ ለተባይ በረከት

ፈቀቅ ላይባል ለማድቀቅ አጥንት

በሕልም እሩጫ ለመንገታገት

በትቢያ ኖሮ ትቢያ ለማሸተት

ተባለ እንዲህ ከመኖር ይሻላል መሞት::

ወጣ አዲስ ደንብ ያሰላለፍ

ተራማጅ በግራ ረድፍ

አድኅሪ በቀኝ ክንፍ

የተፈረጀ ለፖለቲካ ሰይፍ።

የግራ ጉዞ ውጤት ሆኖ ቀረ የሕልም እንጀራ

ያስከተለ ከፍተኛ የሕይወት ኪሳራ

አንድ ትውልድ የነጠፈበት የቀረ ሳይጎመራ።

የግራ ሥርዓት ሆኖ ተገኘ አክሳሪ

አድራጊ ተመራማሪን በቁም ቀባሪ

ታታሪን ተብትቦ አሳሪ

ሳይንስ ተማሪን አደናጋሪ

ያሰኘ አርቲስትን አብዮት ቦርቧሪ

አገር ወዳድን መሀል ሰፋሪ

ተቃዋሚን አክራሪ ተስፈንጣሪ

ገንጣይ ካስገንጣይ አስተባባሪ

በጥቅሉ ሥርዓቱ ሆነ ለኅብረተሰብ መውደቂያ ጉድጓድ ቆፋሪ

ሕዝብ አማተበ ብሎ እግዚኦ ምን ትጠብቃለህ ፈጣሪ

ተሸጋገርን እኮ ከጉልት ሥርዓት ጭቆናና ግፍ ወደ ሆነበት ሐሳብ ተቆጣጣሪ፡፡

አማኙም አለ ያመጣው ይህን ሁሉ መዐት

ነው እኮ ባባቶቻችን ሃይማኖት አለመጽናት

እግዚአብሔርን ትቶ እምነትን በሰው ልጅ መመሥረት

ተነሳ እስላም ከክርስትያን አርማውን አንግቦ ባንድነት፡፡

አማኝ ተሟጠጠ እምነቱ በሰው ሥራ

ቆረጠ ላያዳምጥ ፖለቲከኛ ቢጣራ፡፡

አለ አማኝ በግሌ ብራወጥ ምን ዋጋ አለኝ?

ነገ የዘመኑ ጉልበተኛ ተነስቶ ሊያሯሩጠኝ

እንዳሰኘው ላይ ታች ግራ ቀኝ

የላቤን ዋጋ ሊቀማኝ

የበይ ተመልካች ሊያደርገኝ

ቤተሰቤን ሊበትንብኝ፡፡

ከዚህ ሁሉ ጣጣ ፈንጣጣ

ዘለዓለም ውሃ ወቀጣ

የሕልም ፍሰት የማይታይ የማይጠጣ

ሆኖ ቢቀር ዘወትር ገባሪ ለዘመኑ ባላንጣ

ሕዝብ ሽፈተ በልቡ ተከተተ ለደፈጣ

ማንም ላይነቀንቀው የፈለገውን ይዞ ቢመጣ

ስለሆነም የፖለቲካ ሥራ በኢትዮጵያ ውሃ ጠጣ፡፡

ሲቪል ከወታደር አስተሳሰቡ ለየቅሉ

ብዬ ጠየቅሁ እንዴት አንድ ላይ ሊሠሩ ይችላሉ?

ሲቪል የሕዝብን አመኔታ የሚዋጀው ባንጎሉና በማንጎሉ

ጠየቅሁ እንዴት ወታደርና ሲቪል አንድ ላይ ይሰለፋሉ?

አንዱ ግራ ሲል ሌላው ቀኝ አግብቶ ሰልፍ ሲበላሽ ሊጣሉ

ብዬ ጠየቅሁ አይደለም ወይ የሚታገሉ?

ቢቀመጡ የሚሻል ሁሉም በየጠበሉ

አይደሉም እንጴ አልኩኝ አልፎ አልፎ የሚበላሉ?

ምንም እንኳን አሁን በየወንዙ ቢማማሉ

ወታደር ይለው አይደለም እንጴ ለሲቪሉ

ይህ ሸንካፋ ቀጥ ብሎ መሄድ የሚሳነው ሽምልምሉ

አመራር ሲሰጡት የሚቀናው ሁሉንም ላጥናው ባይ ላመሉ

ዞሮ ዞሮ ላይቀር ለባለሥልጣን ማጎብደዱ የጓዳ አርበኛ ፍልፈሉ

በበኩሉስ ሲቪል ይተርብ የለም ወይ ወታደርን እያለ እነአቶ ተጋደሉ?

የሚቀናው መገንባት ሳይሆን ማፈራረስ ማቃጠሉ

የሚሾመው የሚሸለመው በታዛዥነቱ በኃይሉ

በእሺታ የተገራው አእምሮው ለምን? በሚል ፈሊጥ ባለመወልወሉ

የተመቻቸ ላምባገነን አገዛዝ ጸረ ዴሞክራሲ እንዲሉ

ጠየቅሁ እንዴት ሲቪልና ወታደር አብረው ለመሥራት እንደተዋዋሉ?

ለወታደር ተፈጥሮ የለገሰውን አንገት ለማየት አዙሮ

በቅጣትና ልምምድ ኃይል ባንድ አቅጣጫ ቀስሮ

የግል አመለካከቱን በአእምሮው አሳቻ ስፍራዎች ቀብሮ

በፖለቲካ ጨዋታ ወይም አጫዋችነት ሳይገባ እንዲኖር ታፍሮ ተከብሮ

ነበረ ሥልጠናው አቤት ጌታዬ እያለ ለመኖር ድንበር አስከብሮ::

ዐይነ ኅሊናውን እንደጋሪ ፈረስ ሸብቦ አስሮ

አዙሮ ማየት ድክመት ነው ብሎ አዋጅ አስነግሮ

ሁሉም ወደፊት ብሎ አምኖ ተማምኖ

ነዳው ሲቪልን ከጀርባው መሣርያ ደግኖ::

ታድያ እንዴት ሊሆን ይችላል ወታደር ያገር አስተዳዳሪ?

አይደለም ወይ አልኩኝ አዲሱ ተልእኮው ከሥልጠናው ጋር ተጻራሪ?

ለሥነልቦናው ችግር ፈጣሪ

ብሎም በሆነው ባልሆነው ተሸባሪ እንዲሁም አሸባሪ::

ጥያቄ መጠየቅ፣ ጥናት ማካሄድ፣ ነገር ማብላላት፣ ግራ ቀኙን

ማየት፣ ማሰላሰሉ

ነገር ጭብጡ እስኪገኝና እምብርቱ እስኪያዝ አገላብጦ ማንከባለሉ

ስለሆነ ሲቪል ጥርስ ነቅሎ የሠለጠነበት መለያ ባሕሉ

አልኩኝ ያስፈርጅ አይደል እንዴ ከሚያወላውሉ?

ሕይወት አደጋ ላይ አውጥተው የጣሉ

በወታደር ሰፈር በኃይል በሚምሉ

የሲቪልን ድክመት በሚያብጠለጥሉ።

ና ግድየለም ግባ ተጫወት

ባዲሱ አስተሳሰብ ደም ማፍሰስ ወንጀል ነው፣ አታስብ ታድዬ

በሕዝብ ስለማመን፣ ሲቪልን መከተል ካንተው ነን ተብዬ፣

ከደርግ አባላት ጋር ዐሥራ ሰባት ዓመት ተንኳተትኩ በተስፋ እራሴን ደልዬ።

ጥጥና ሸማኔ መስሎኝ የማፈራ

እምዬ ኢትዮጵያን ከወገብዋ በታች እንዲሁም ከበላይ ጸጉር አጎፍራ

ዓለም የሚመኛት ውቢትዋ ሙሽራ

እኔስ መስሎኝ ነበር ዘላለም የምትኖር ታፍራና ተከብራ፡፡

ያገሬን ሰው ላሰኝ ረሃብ ድንቁርና ሂድልኝ ከጎኔ

ለማስዋብ ለማስጌጥ ኢትዮጵያ እናቴን ባገሬ ሽማኔ

ነበረ ምኞቴ በሕልሜም በውኔ

ብዙ ሥራ እያለ እንቅልፍስ ለምኔ?

ብዬ የተነሳሁ ግራ ቀኝ ሳልል ለድሃው ወገኔ

የክፉ ዘመን ውልድ እንዲህ መባከኔ

የሚያጠያይቅ እንዳለ እርግማኔ

የተፈረደብን በምድር ኩነኔ

ከልጅነት ሕልሜ ምነው መባነኔ

እንዳይሆን ሆነና ሁሉም ፈረሰና ተሰድጄ አረፍኩት ወይ እኔ ወይ እኔ!

አሁንስ ምን ይሉኝ ለፈሰሰ ውሃ እንዲህ መብከንከኔ?

አሁንም ያቅራራል የዘመኑ ጉልበተኛ አማጭ

ከብዙኀን ቀምቶ ወገኑን አብላጭ

ከፍ አድርጎ ራስጌ አስቀማጭ

ሌላውን ወደታች ረጋጭ

ድህነት ዘሪ ረሃብ አጫጅ

የረሃብተኛን አጥንት ጋጭ

እንደጣረሞት ደም መጣጭ

ደንደሳም ልብ አሳባጭ

የሕዝብ ተስፋ አጫጭ

መሳይ የልብ ትርታ አድማጭ

ወንድም ከወንድም አጋጭ

ጎበዝ ነኝ ባይ አካል ገዝግዞ ቆራጭ

አላታሚ ቁራጩን ከዋናው አካል

ተልታይ ሥጋ እንዲያመረቅዝ ቁስል

አፍዪ እንደችግኝ የማይነጥፍ በቀል

በሽታ አስተላላፊ የማይሽር ከዳር እስከዳር

መሬት ቀማኛ ሊገነባ ቤተመንግሥት

ኑሮ ሊደላደል ሊተክል ሐውልት

ደሳሳ ጎጆ እፍራሽ

ደሃ አስለቃሽ

ሰውን እንደጥራጊ ደጅ አፍሳሽ

ከሃዲ የናት ጡት ነካሽ

የውድ እናቱን ታሪክ አርካሽ

አጥላልቶ የሚሰጥ ለጠላት ተንኳሽ

ላሰፈሰፈ ለውድቀትዋ አናፋሽ

በቁም ቀባሪ በር ዘግቶ አሳጥቶ ትንፋሽ

ደቁሶ እንዲያሻት ዙርያዋን የከበባት ጠላት

እንስትፋንስዋ እስኪቋረጥ ተዳርጋ ለቁም ሞት።

ያላወቅህ መሆኑን የኢትዮጵያ አምላክ ኃይለኛ

እረፍት የማያውቅ ሃያ አራት ሰዓት የማይተኛ

ሽረኛ ጠላቶችዋን የሚያደርቅ እንደመጋኛ

አይዞሽ ኑሪልን እናታችን ዘለዓለም ለኛ።

ከፋፋይ የዘራው በሽታ

ተዘንግቶ መሆኑን የሚያዳርስ ሁሉም ቦታ

በግፍ የወረወሩት ጦር ተመልሶ እራስን እንደሚመታ

እንደሚፈጸም በጠዋቱ ሳይቆይ እስከማታ

ይኸው ዐየነው ሲወድቅ ትግራይ

ባሞካሻቸው ልጆቹ እጅ በእነተጋዳይ

ሲከቱት ለሌሎች በቆፈሩት ጉድጓድ

ዘንግተው መሆኑን የኢትዮጵያ አምላክ መሐሪ ብቻ ሳይሆን

ሲያስፈልግም አድራጊ ዶጋመድ::

እስካሁን የተገኘው ውጤት

በሰው ልጅ አመራር ያሚጠጠ እምነት

ኢትዮጵያዊን ያደረገ ለፈጣሪው እንዲገዛ ብሎ ሰጥ ለጥ

ማንንም ፖለቲከኛ ሳያዳምጥ

በትግል ወላፈን ተጠምዶ ከመርመጥመጥ

ላይ ታች ግራ ቀኝ ከመራወጥ

ከዚህ ሁሉ ይሻላል ታግሶ አርፎ መቀመጥ

ሁሉንም እንዲያበጀው ትቶ ለፈጣሪ እንዲፈልግ ፈሊጥ

እንዲሁም አለ እኔ ምስኪኑ ምን አለኝ አቅም?

የማይበጀኝ መሆኑን አይቸዋለሁ ሁሉንም

ብሎ ወሰነ ለመከናነብ ፍዳ ላለማየት

ዓለምን ረስቶ በዓለም ተረስቶ እንደገና ለማንቀላፋት

ለመተኛት ሌላ ሺህ አመት

ይመስል የሚጠብቀው ሲነቃ

የተሻለ ዓለም የሚያመረቃ

ሊል እንደ ግርማ ታደሰ ይሄ ነው፤ አለቀ፤ በቃ።

አይ ተስፈኛ መሆን ተላላ

ሳይለፉ ሳይላላጡ ሊለበስ ሊበላ

ኢትዮጵያዊ አትዘናጋ ጊዜ አታጥፋ

መታገል እጣህ መሆኑን እወቅ አታንቀላፋ

የልጅ ልጆችህን ዕድል አውጥተህ አትድፋ፡፡

ታውቃለህ ዛሬ ያልተከሉት ነገ እንደማይበቅል

ተነሳ፣ አረምን በጊዜው ጎልጉል፣

ያስቸገረውን በደቦ ንቀል፡፡

# ባለጸጋን መለማመጥ

የኤኮኖሚስት ጠቃሚነቱ ሲከስም

ሲመክን የጠነሰሰው ትልም

ቋንቋው ዘቅጦ በ“ግፊት አድርጉ!” ተከፍቶ በዚሁ ሲደመደም

በራዥ ከላሽ እየተባለ ተቀርቋሪ ከአክራሪዎች ጋር ሲላተም

አዋቂ ምሁሩ አፉ በአይዲኦሎጂ ተሸብቦ ሲለጎም

የተስፋ ጭላንጭል ሲጨልም

የውጭ ምንዛሪ እጥረት ሁሉንም ሲፋለም

የተለመደ ነበር ባለሥልጣን የበታቹን ማንቆራጠጥ

ሱሪውን በአንገቱ ሲያወልቅ ጠልፎ መዘርጠጥ

ኤክሰፐርቶችን ማሯሯጥ

የሚወጣቸው ነገር ቢኖር ደጋግሞ መናጥ

የውጭ ምንዛሪ ጠያቂን መገላመጥ

ፍላጎቱን በፍረደ ገምድልነት መቆራረጥ

ሲመሽ የሕልም እንጀራ ማላመጥ

ሲነጋ እንደተለመደው ዐይን ፍጥጥ

እያንከባለሉት ማጉረጥረጥ፣ ተነስቶ መንቆራጠጥ

የመሬቱን መቧጠጥ፣ ወደ ሰማይ ማንጋጠጥ

ላይና ታች ማዘጥዘጥ

የደብረባንክ ቅሪቶችን ማሟጠጥ

ትርፍራፊዎችን መልቀም፣ የሒሳብ ምንችቶችን በማገላበጥ

ነፍስና ሥጋ እስኪላቀቅ ውሃ መውቀጥ

እጅና እግር እስኪላላጥ

እራስን ደንቅሮ በማጥ

ሲጠፋ ዘዴ ምንም ፍሬ የሚሰጥ

ነበር ሥራችን መጓዝ ለልመና ቦርሳ ይዞ መሮጥ

ጠባይ አሳምሮ ባለጸጎችን ለመለማመጥ::

የሊብያ መንግሥት ተስማማ ሊሰጥ ብድር

ከተከናወነ በኋላ የባንኮች ድርድር::

ወደትሪፖሊ ተጀመረ ጉዞ

የልመና ኮረጆ ተይዞ::

ሮም አየር ማረፊያ መንገደኞች ተሰበሰቡ

ሊብያኖች ተጠየቁ ቀድመው አውሮፕላኑ ውስጥ እንዲገቡ::

የመቀመጫ ቁጥር ስላልተሰጠው ተሳፋሪው

ነገሩ ሆነብኝ የተለየ ከማውቀው

ከአየር መንገዶች አሠራር ከተለመደው::

ትዝ አለኝ የአገራችን የመስተንግዶ ሥርዓት

እንግዳ እንደንጉሥ የሚከበርበት

እግሩ ታጥቦ፣ ተስሞ፣ የሚታጀል በቅባት

ቀርቦለት ምርጥ ቁርበት

እሱ በመደብ ባለቤት በመሬት::

እንዲሁም ትዝ አለኝ ትልቁ እስክንድር

ስላደረገው የሊብያ ጉዞ በእግር

ስለፋርስ ዘመቻው አማልክትን ለመጠየቅ ምክር

አይቀናህም ቢሉት ዘመቻው ሊቀር::

ሊብያኖቹ አውሮፕላኑ ውስጥ ቀድመው የገቡት

ድርጊታቸው መሰለን ያክብሮት

ታስቦ የእንግዶቻቸው ምቾት

ምርጥምርጡን መቀመጫ ለኛ ያስቀሩት::

መሰለኝ ስንገባ እንዳንገፋ

መስተንግዶ ሊዛቅልን ባካፋ::

ታየኝ ስጓዝ ወደ አማልክቶች አገር በብሩኮች ታጅቤ

ልመለስ አገሬ ዶላር ዝቁ እንደልቤ

እፎይ ልል የባንክን ካዝና አደልቤ

ወይስ እያየሁ ነው የሕልም ቅቤ?

አልቀረም በመጠኑም ቢሆን ማሰቤ::

ይህን ሳወጣ ሳወርድ በየፈርጁ

ተመለሰ አስተናጋጁ

አጨበጨበ በጁ::

ቁጣ በተመላ አንደበት

አዘዘን እንድንሳፈር በቅጽበት፡፡

ተሳፋሪው እንደበግ ታጎረ

ይከብዳል ለማለት ተሳፈረ፡፡

ተመለከትን ሊብያኖች ምርጥ ምርጡን መቀመጫ ይዘው

ሊብያዊ ያልሆነውን ሁሉ የነሱ አጃቢ አስመስለው፡፡

ሌላው መቀመጫ ፈልጎ እንዲቀመጥ ታዘዘ

ሁሉም ግራና ቀኝ መቃኘት ተያያዘ፡፡

ትሪፖሊ እንደምንም ተደረሰ

በጎ አመለካከቴ ሁሉ ተወሰወሰ፡፡

ከጉምሩክ ክልል ለመውጣት

ብሎም ወደ ከተማ ለመግባት

የሚሞላው ፎርም ስለተጻፈ በዐረብኛ

ቋንቋውን የማይችል ተሳፋሪ ተጨነቀ ክፉኛ፡፡

ከየት ይምጣ ተርጓሚ ፈቃደኛ?

ሆቴሌ ገብቼ ክፍሌ ከመድረሴ

በስልክ ተማጸንኳቸው ለስላሳ መጠጥ እንዲያመጡልኝ በነፍሴ

በውሃ ጥም ስለደረቀ ምላሴ።

መጠበቁ ቢበዛብኝ

ጥሙን መቋቋም ቢያቅተኝ

መልሼ ደወልኩ እንዲረዱኝ።

ትዕዛዜን የተቀበለው ሠራተኛ

ምንድነው የሚያስቸኩልህ? ብሎ አሳረፈኛ!

አስመስሎ ውሃ ጥም በእሹሩሩ የሚተኛ።

ከሰውዬው ጋር ስጨቃጨቅ

አምባሳደራችን አሉ ብቅ።

ጠየቁኝ ምን እንደሆነ ችግሩ

ሳስረዳቸው፣ አሉኝ ተወው ለኔ ነገሩ

በዐረብኛ ለረጅም ጊዜ አወሩ

ተሳሳቁ፣ የቆጡን የባጡን ቀባጠሩ።

የአምባሳደሩ ዋና ትኩረት

የሆቴሉን ሠራተኛ እሹሩሩ ማለት

ሌክቸር ሰጡኝ ስለሊብያዊ ኩሩነት

ለባዕድ ማሳየት እንደሚፈልግ የበላይነት፡፡

ኦቾጉድ! አልኩኝ በልቤ

በዘይት ልቡ ያበጠ ሕዝብ ዘይቤ፡፡

በማግስቱ ጠዋት ሄድኩ ባንኩ ድረስ

ተልዕኮዬን ከግቡ ለማድረስ፡፡

ተነገረኝ ዋናው ኃላፊ እንደሌሉ

እንደሚቻል ከምክትላቸው ጋር መዋዋሉ፡፡

ተወለካክፎ እንዲቀር ነገሩ

ከካዝና እንዳይወጣ ዶላሩ

ገባኝ ዘዴ እንዳቀነባበሩ

እሰማ ነበርና ሲያወሩ

በኃዳፊ ለጋስነት ድብን ብለው እንደሚያሩ፡፡

እሺ ብዬ ሄድኩ ምክትሉ ቢሮ

በር አንኳኩቼ ከመግባቴ ጠየቀኝ እንዳለን ቀጠሮ

ፊልጎ እንዲፈጠር አምባጓሮ፡፡

አለኝ፣ አልደረሰኽም እንዴ መልዕክት?

ለድርድር እንዳላደረግን ዝግጅት?

ድርድሩ ተጀመረ እንደምንም

እንደነሱ ያለ አስቸጋሪ ተደራዳሪ ዐይቼ አላውቅም፡፡

ዋናው ጉዳይ ተጠናቀቀ

ድርድሩ በሦስት ቀን አለቀ፡፡

ነገሩ ተሳካ ብዬ ስደሰት

በመጨረሻው ደቂቃ  ውሃ ቸለሱበት፡፡

ውሉ በዐረብኛና በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ

አረብኛው የበላይነት ይኖረዋል አለ አፉን ሞልቶ

ሌሎች የተፈራረሙትን ማየት ትችላለህ አለኝ ተዝናንቶ

የመጣሁት የውጫሌ ውል ከተቀደደበት አገር መሆኑን ዘንግቶ፡፡

ባገላብጠው ብሠራው

ምንም ቅም ስላላለው

የችግሩን ይዘት መንግሥት እንዲያውቀው

መልዕክት አስተላለፍኩ አዲስ አበባ ለሚመለከተው።

አስተያየት ላክሁ በዝርዝሩ

መልክ እንዲይዝ ድርድሩ

ከፍተኛ የሊብያ ባለሥልጣኖችን እንዲያነጋግሩ

የሁለቱን ቋንቋዎች እኩልነት እንዲያከብሩ

እንዲጠየቁ ከመስመር የወጣውን ተደራዳሪ እንዲገሩ።

መልስ እስኪመጣ ድረስ

ሥራዬ የነበረ በየቀኑ ኤምባሲያችን መመላለስ

ከሠራተኞቹ መካከል

ትሪፖሊ ከመጣ ሳምንት የሚያክል

ዐየሁ አብጦ ግንባሩ

ማወቅ ፈለግሁ ምን እንደሆነ ነገሩ

ከካይሮ ወደ ትሪፖሊ ሲመጣ

ጠፍቶበት ኖሮ ሻንጣ

ልብስ የሚቀይረው ቢያጣ

ኤርፖርት ተመላለሰ ለማጠያየቅ

የእቃው ዱካ ሳይጠፋ ሳይርቅ::

ምንድነው ደጋግመህ የምትጠይቀን?

እኛ ያንተ ሻንጣ ሌባ ነን?

በሀብት እንደሆነ የታወቅን

ብለው ደበደቡት እንግዳውን

ግንኙነት እንዲያሻሽል የተላከውን::

ሌላም ሌላም ነገሩኝ

የሰማሁት ሁሉ ዘገነነኝ::

መቼ ያልቃል የሊብያኖች ግፍ ተነግሮ

ዲፕሎማት ይኖራል አቀርቅሮ

በያቅጣጫው ባይነቁራኛ ተወጥሮ

እንደሌባ ተቆጥሮ::

ድንገት ቢያሰማ የመኪና ጥሩምባ

የት አባቱ ሊገባ

ይዳረጋል ለስድብና ድብደባ::

ሰማሁ ሌላም ሌላ

በስብእናቸው ላይ የሚያጠላ

በአእምሮዬ ውስጥ ተተክሎ የሚጉላላ::

ነገሩኝ እንደሆነ የጥቁር ደም ደመከልብ

ገዳይ ከተያዘ ማለት ያለበት አገኘሁት መሪያችንን ሲሳደብ::

ከብዙ ጉትጎታ በኂላ የመጣው መልስ

ነበር የሞቱት አባቶቻችንን የሚቀሰቅስ

ተግባራዊ ቢሆን ከትውልድ ትውልድ የሚያስወቅስ::

ታዲያ ምን ያደርጋል እምቢ ካሉ

በዚህ መናኘ ምክኒያት ገንዘቡን እንዳይከለክሉ

እንዳሉት ይሁንላቸው ቶሎ ይፈረም ውሉ

አሉኝና ቁጭ አሉ::

ትዝ አለኝ ባለሥልጣኖቻችን ሲሉት የሰማሁትን

ታንክና ዶላር ለማግኘት የሚጠይቁን

ከሆነ በወረቀት ላይ ፊርማ ማስቀመጥ

እንድናግበሰብስ የተገኘውን ያህል ሸቀጥ

የሚያቅማማ ካለ ስብእናው ይቀጥቀጥ

አሳቢነቱ በርዕዮተዓለም ዋግምት ይመጠጥ

ሐሳባዊ ብለነው ይንቀጥቀጥ

ላቷ እንደተቆረጠ በግ ይደንግጥ

ቀኝ መንገደኛ ብለነው ሽንቱ ያምልጥ

ከራሱ ጋር በሚያደረገው ትግል ኅሊናው ይላላጥ

ጠልቶ የተፋውን መልሶ ይዋጥ

አድኑኝ ብሎ ባለሥልጣኖችን ይለማመጥ

በጉያችን ሥር ይርመጥመጥ

ከተቻለም ያስመስክር ከጳጳሱ ቄሱ እንደሚበልጥ

ወደ መጨረሻው አዘቅት በመስመጥ

ለሥርዓቱ ተገዢነቱን ለማረጋገጥ

ሲያስፈልግ እንጋልበው ሽምጥ

ብለንበት ቁጢጥ።

የዐረብኛን የበላይነት ላለመቀበል ወስኜ

ድጋፍ ባለማግኘቴ በግኜ

ከባልደረባዬ ጋር አመራን ወደ ሆቴል

ሒሳብ ከፍለን፣ ለመሄድ፣ ለመገላገል

አገሬ ስመለስ ፍርድ ለመቀበል።

ሒሳብ ሠራተኛውን ብንጠይቅ የክፍያውን መጠን

የሊብያው ባንክ ልጠየቅበት እንዳለ ተረዳን።

ተደራዳሪው በማናለብኝነት ያሳረረውን ቆሽት

እንዲሁም ያጨማለቀውን የድርድር ሥርዓት

በስጦታ በማሸት በማሿሸት

ፈለገ ሊያነጻ የሞራሉን እድፈት

ካሳ ሊከፍል ለአደራደሩ ግድፈት።

ምንም እንኳ ከደሃ አገር ብንመጣ

ባለመታደል ምንም ካጣ ከነጣ

አላወቀም ኩራት ከቤታችን ተሟጦ እንዳልወጣ።

የገንዘብ ኮሮጆውን ሽምቀቆ ዕያየሁት እያጠበቀ

የበላይ ትእዛዝ መኖሩን እያወቀ

አንገላቶ ሞራሌን እያላሸቀ

የረሃብተኛ ጉሮሮ እያነቀ

በድንፋታ እየተመጻደቀ

ወደታች ሊያየኝ እየፈለገ እያዘቀዘቀ

ባገኝ አላገኝ ሰመመን ኅሊናዬን እያሳቀቀ

በፍርፋሪ ሊደልለኝ መሞከሩ ቆራጥነቴን አጠበቀ

የበላይነቱን ላለመቀበል ሕዋሳቴ ሁሉ ተጠነቀቀ።

ከሆቴሉ ጋር እከፍል አትከፍል ጦፈ ክርክር

ሠራተኞቹ ተንሾኳሹኩ አደረጉ ምክክር

ግራ ተጋባን አልገባንም የግርግሩ ምስጢር።

ማምረራችንን ሲያውቁ

ከፍለን ከነሱ መላቀቁ

ሠራተኛው ተቀበለን ሒሳብ እያየን የጎሪጥ

ከቆየ በኋላ ሲያሰላስል ሲንቆራጠጥ።

ወደ አየር ማረፊያ በጉዞ ላይ ሳለን

የትራፊክ ፖሊስ ተከታትሎ አስቆመን።

አሁን ደግሞ ምን መጣ?

አያልቅ የነዚህ ሰዎች ጣጣ

ብለን ከመኪናው ብንወጣ

አንደኛው ኑሮ የባንኩ ሠራተኛ

እንዲጠራን የተላከ መልዕክተኛ

ነገረን ውሉን ለመፈራረም እንደተዘጋጁ

ካሁን በኋላ ምንም ጊዜ ሳይፈጁ::

ያሰብነው በመሳካቱ ልቤ ረካ

ወስጠ ጎሊናዬ በደስታ አስካካ

ገጽታዬም ከመቅጽበት ፈካ::

ተመልሰን ባንክ አዳራሽ እንደደረስን

ተደራዳሪው ደስ እንዳለው ነገረን

ሐሳባችንን ቀይረን

ስለተቀበልን ሐሳቡን::

አውሮፕላን አስመልጠው

ቢሮ ዘግተው አንገላትተው

ሊያሹኝ እንድሆን የፍላጎታቸው ተገዥ

ሞራለቢስ በደመነፍስ ተጓዥ

ሊያደርጉኝ አርማቸውን ያዥ

ትንሽነታቸውን ዐየሁ ግራና ቀኝ ሲያዥ::

ከንዴት ብዛት መተንፈስ ጀመርኩ ቁና ቁና

ታየኝ ነገሩ እንደማይቃና

እንዳለበት እርግምና

ነገሩ የተበላሸው ካችአምና

መስማማትን ረግጠን ስለትግል ስናጠና

ተጠፋፍተን እራሳችንን ለመዳረግ ለልመና::

ምን ነበረበት የድህነት ጉንተላ

አደባባይ ሳይወጣ ባውላላ

በጉያችን ተደብቆ እዚያው ቢብላላ?

መድኃኒት እስኪገኝለት ባገር

የማያዳግም የሚያሽር

ምን ይሉታል ድህነትን እንደታቦት ተሸክሞ መዞር?

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ መጨመር

ሥጋ አኮስሶ ኅሊናን መደመር

ለደንቆሮ መሃይም መገበር

ሀብት ለነፋው ውጥርጥር

የታደለ ከምድረ ከርስ እንዲዝቅ ዶላር

ሳይወጣ ሳይወርድ ሳይጥር ሳይግር፡፡

ድንገት ትዝ አለኝ

ሰውዬው ቀደም ብሎ በነገር የሸነቆረኝ

እስካሁን ውጋት ሁኖ የሚያመኝ፡፡

ድርድሩ እኮ የሚደረገው

እኩልነት ባላቸው ሁለት ነጻ ወገኖች ነው ብለው

አለኝ ይሻላል ቢቆም ቀልድህ

ካልገባህ ግልጽ ላድርግልህ

እውቀት የሌለው ያለው የጻፈውን ዳዊት እንደሚደግም

እንዲሁም አለኝ፣ ካልፈለገ አላልኩም ነጻነት የለውም

ባዶ ቤቱ ገብቶ ለመፈርገም

ጉዞ ሊጀምር እንደሚችል ማዝገም፡፡

ያለው በሌለው ሲያላግጥ

አብነት አለው በእርግጥ

ደሃ ቢተጋ በማንም እንደማይበለጥ

ለመዳን ከመለማመጥ

ከተንፏቃቂነት ለማምለጥ

ላለመታየት የጎሪጥ

በዐይን ግርፋት ላለመላላጥ

ትቢያ ላይ ላለመንከባለል የሀብታም ፍርፋሪ ለመዋጥ

ያስፈልጋል ሥራን ማወደስ

የሥራ ጀግኖችን ሕዝቡ እንዲያመልካቸው መቀስቀስ

ሥማቸውን መዘከር በቤተመቅደስ

ማሳወቅ እንደታደሉ መንግሥተሰማያትን ለመውረስ

ከመካከላቸው መርጦ ማንገሥ

እንዲሆኑ ለሠርቶ አደሩ ሞገስ

በአንጻሩ አፍራሾችን መመለስ

ቅሬታን በቅጡ አስተናግዶ ማስተንፈስ

ፈንድቶ ቤት እንዳይደረመስ

ሕዝብን በዋይታ እንዳያተራምስ

የተገነባው እንዳይፈርስ

ጥርጣሬና አለመተማመን እንዳይነግስ

ሠራተኛ እጁን እንዳይንተራስ

የዕውቀት ጮራ ጠፍቶ አገር ጨለማ እንዳይለብስ

ሕዝብ ተያይዞ ወደ መቀመቅ እንዳይገሰግስ::

አልኩኝ ምን ዓይነት ትውልድ ነው የተረገመ

በሙሉ ኃይል ከራሱ ጋር የተላተመ

የነገ ተስፋውን አፈር ያቃመ

ሞፈር አሰቅሎ ጎበዙን ጠመንዣ ያሸከመ

ለሞት ተጠራርቶ በሕይወት ላይ ያደመ::

ፖለቲከኛ በባዕድ ርእዮተዓለም ተነክሮ

ለነያላን ቼስ ተጫዋቾች ገብሮ

የሥራ ፈጣሪን ቅስም ሰብሮ

ለምን? ያለውን በወኀኒ አጉሮ

የረገበውን ሁሉ አክርሮ

ከመስማማት መታገል ተከብሮ

ሰነፍ በትጉህ ላይ አብሮ

መሃይም ምሁራንን አስተምሮ

ተወረወረ የልማት ተስፋ ተሽቀንጥሮ

ሕዝቡን ለማኖር አይኖሩት ኑሮ

ድህነት በጉሮሮው ውስጥ ተሰንቅሮ፡፡

ይህን ሳሰላስል ፈዝዤ

በቀሳፊ ንዴት ተይዤ

"ሰውዬው የምጠብቀው አንተን ነው

ትፈርም እንደሆነ በቶሎ ልወቀው"

አለና ውሉን ከማኅደሩ አወጣው፡፡

እንደምንም የትዕግሥትን አምላክ ተማጽኜ

እራሴን ለመቆጣጠር ወስኜ

ነገርኩት ከመንገድ የተመለስኩ መሆኑን በሱ ጥያቄ መሠረት

ውሉ ሳይፈረም ቢቀር እሱ እንደሚጠየቅበት

አስገንዝቤ አመራሁ ወደበሩ

አልኩት መሆኑ ፍጻሜው፣ መጨረሻው፣ የድርድሩ።

ሰውዬው ማምረሬን ሲያውቅ

ፈርቶም ይሆናል እንደሚጠየቅ

ጋበዘኝ እንድቀመጥ

ፊርማችንን እንድናስቀምጥ

ገልጾ ውሉ እንደተስተካከለ በኔ ሐሳብ መሠረት በግልጥ።

የእንግሊዝኛው ተፈርሞ ወደኔ ተላለፈ

በተጣላንበት አንቀጽ ዐይኔ አረፈ።

ቢነሳ ክርክር ውሉን በሚመለከት

በግልጽ ተቀምጧል ዐረብኛው እንደሚኖረው የበላይነት

ማመን አልቻልኩም እንዲህ ዓይነት ቅጥፈት

ተወዳዳሪ የሌለው ቅሌት

የሰከረ በበታችነት ስሜት

አንቀጹ መስሎት የበሽታው መድኃኒት

በማናቸውም ዘዴ ያለበት መገኘት

ለትልቅነታቸው ሊያቀርቡት በማስረጃነት

ተበዳሪዎችን ሊያሳንሱበት

የተለከፉ በለየለት እብደት

የሚመጣ ከመዋኘት በነዳጅ ዘይት፡፡

ስለዋና ሲነሳ አንድ ነገር ትዝ አለኝ

እስካሁን የሚሰቀጥጠኝ፡፡

የመንግሥታት ልዑካን በተሰበሰቡበት

ድሃ፣ ሀብታም፣ ኃያል፣ ደካማ፣ ሁሉም ዓይነት

አንድ የዘይት አምራች አገር ሚኒስትር

ለጉባኤው ባደረገው ንግግር

ዘረዘረና አገሩ ስላደረገው እርዳታ

በመደምደሚያው ላይ እንደሚከተለው አስገነዘበ በእርጋታ

ገልጾ አገሩን የጎበኘውን መሪ ብዛት

ብሎ አሳረገ በድፍረት በማናለብኝነት

ሳይሸሽግ ምን ያህል እንደተጠየፈ ድህነት

አለ መሪዎቹ የተግተለተሉት እንዳልነበረ በቤንዚን ለመዋኘት፡፡

የውሉን የመጨረሻ ገጽ ሰርዤ

ደልዤ ደላልዤ

ሊብያ ያመጣኝን አምላክ አውግዤ

ቃል ሳልተነፍስ ተነሳሁ ቦርሳዬን ይዤ፡፡

ቆራጥነቴን እንዳየ - - -

ተደራዳሪው ትክክለኛውን ቅጂ ከመሳቢያ አውጥቶ

በጥሞና ወደኔ ተጠግቶ

በሽሙጥ ፈገግታ አፉን ከፍቶ

አለኝ፣ አንተ የማትቻል ነህ ከቶ፡፡

ያስተላለፈውን ፈርሞ

ካረጋገጥኩ በኋላ አሁንም እንዳልተጻፈ ተጣሞ

መስማማቴን አበሰርኩ

ታወቀኝ ድል እንዳደረግኩ

የሰውዬውን ትንሽነት አስመሰከርኩ

ሞራለቢሱን አንበረከክኩ

ስብእናውን አኮሰስኩ

ድሃም የበላይ ሊሆን እንደሚችል አስተማርኩ

በደስታ ተውጬ አየር ማረፊያ ከነፍኩ

ያገሬን ዘፈን እየዘፈንኩ

አምላክ መልሶ ሊብያን እንዳያስረግጠኝ ተማጸንኩ፡፡

ያገሬ ሰው ቢሆንም ብርቱ

ጠንካራ በእምነቱ

እራሱ ለራሱ ስለሆነ ጠላቱ

አልኩኝ መቼ ነው የሚወርድለት ምህረቱ?

ከስቃይ የሚድንበት ሰዓቱ?

ብልጽግና የሚገባ ከቤቱ?

ወደሌላ አገር መሄድ ስለነበረብኝ

ሒሳብ ባልደረባዬ እንዲያወራርድልኝ

ሮም ስንደርስ ላስረክበው አወጣሁ ደረሰኝ።

አገላብጬ ባየው

ዐይኔ ማመን አቃተው።

ገንዘብ ተቀባዩ ገንዘቡን ባንካቸው የሚከፍለው መስሎት

ተማምኖ ሳናጣራ እንደምንፈርምለት

ሌላ ያዘዘውን በኛ ሒሳብ ጨምሮበት

ነበር ያዘጋጀው ዘዴ የስርቆት።

የምንከፍል እራሳችን ብንሆን

ገምቷል እንደምንመረምር ሒሳቡን

ገንዘቡን ሳንከፍል አስቀድመን።

ሳይሆን ቀረ ተታለልን

ሒሳቡን ሳንመረምር መክፈላችን

ሠራተኛውን አምነን

ከነሱ ለመላቀቅ ቸኩለን

አልን የታዘዘ ነው ካምላካችን፡፡

ላለው ይጨመርለታል

ከሌላው ይወሰድበታል

እንደተጻፈው በወንጌል

የተጠቀምንበት የምጸት ቃል

እራሳችንን ለማታለል፡፡

# ነጭና ጥቁር

የግጥሙን መንፈስ ለማስጨበጥ ካናዳውን ጥቁሮችንና ነጭ ያልሆነውን ሁሉ ቪዚብል ወይም ጎልቶ የሚታይ ይሉናል:: ለአባባል ያህል እናያችኋለን ይበሉ እንጂ ምርጫቸው ግን ሳንታይ በየቤታችን ተሸጉጠን ብንቀመጥላቸው ነው:: በተለይ ጥቁሮች ወደካናዳ እንዳይገቡ እንደሚከላከሉ በደንብ ይታወቃል:: ግጥሙ የተገጠመው በየካቲት 1985 ነው::

ሳለሁ ባገሬ እሰማ ነበር

ካናዳውያን ሰውን እንደማይከፋፍሉ በዘር

የሁሉም መብት እኩል እንደሚከበር

ማንነቱን ለማረጋገጥ ለማንም ክፍት እንደሆነ ማናቸውም በር

ሥራ መሆኑን የሰው ምስክር::

እዚህም ከመጣሁ ካናዳ ተባለች ከአገሮች ሁሉ ምርጥ

የምታመች ለኑሮ ያለስጋት ለመቀመጥ

ተገላግሎ ከአምባገነን ቆመጥ

ርቆ ከግፈኛ ረመጥ፡፡

ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች በያመቱ

ጥቁር፣ ብጫ፣ ነጭ፣ በያይነቱ

ካናዳ ይገባሉ ኑሮአቸውን ሊመሠርቱ

ከየአህጉራቱ፣ ከአምስቱ፡፡

ከዕለታት አንድ ቀን ሆስፒታል ሄጄ

ለመጠየቅ የታመመ ወዳጄ

አጣሁት ወጥቼ ወርጄ፡፡

ነርስ እንድትረዳኝ ጠየቅኋት

የነገርኳት ስም መያዝ ቢሳናት

እንዲሆናት ምልክት

ጥቁር መሆኑን ጠቆምኳት፡፡

ጥቁር የሚለው ቃል ከኔ አፍ በመውጣቱ

ማመን አቃታት በውነቱ፡፡

ነገረችኝ የጸዳ መሆኑን ሆስፒታሉ

ከዘረኛነትና ከመሳሰሉ፡፡

አሳወቀችኝ መዝገብ እንደማይያዝ በዘር

የሁሉንም እኩልነት ለማክበር፡፡

የነርሷ መልስ አስገረመኝ

ነገሩ በጣም ከነከነኝ፡፡

ቀላሉን ነገር ማክበዷ

ምነው የሌለውን ፈጥራ መረበድበዷ?

ተረዳሁ ሁኔታዋ እንዳልሆነ ጤናማ

በድንገት እንደነካሁ ነርቭ ደካማ፡፡

ፊዚክስ ተምረው ስለቀለማት ጠንቅቀው ያወቁ

የተፈጥሮን ምስጢር እያየናቸው ሲፈለቅቁ

ወደ ጠፈር የመጠቁ

ስለማይታየው ሳይቀር የእውቀት ጮራ የፈነጠቁ

እሳተገሞራ ጉያ ውስጥ መንኮራኩር እየለቀቁ

አልኩኝ ምን ያህል ቢራቀቁ ነው ቢያውቁ

ዐይኔን ግንባር ያሉት ግዙፉን ጥቁር ላለማወቁ?

ነገሩ ነው አስገራሚ

ግራ የሚያጋባ ለሰሚ::

ጥቁሩን በኦፊሴል «የሚታየው» እያሉት

አስበው ነጩ እንዲጠብቀው ባይን ቁርኝት

እንዳይተቃቀፉ በስሕተት

እንዳይወራረስ የሁለቱ ሕይወት

ለምንድነው ጥቁሩን ጥቁር ለማለት የፈሩት?

ብሎም ኅልውናውን የሚፍቁት?

እሱነቱን በመካድ እሱነቱን የሚያስክዱት?

ለማያውቀውማ የሚመስለው ለሱ ታስቦለት

ሊፍቁለት ጥቁርነት

አጋንንትነት ባርያነት

የበታችነት::

ነጮች ናቸው ሰይጣንን ጥቁር አድርገው የሳሉት

ፊቱን ያከሰሉት

ወንጌል አስረክበው ጥቁሩን አገሩን የቀሙት

ባርያ ነጋዴና ኮሎኒያሊስት ሆነው የዘመቱበት

የሱን ቤት አፍርሰው የራሳቸውን ለመገንባት፡፡

ታዲያ ጥቁር ሲባል

የሚታያቸው የፈጸሙት ኢሰብአዊ በደል፡፡

መጥፎ በሽታ አደገኛ ልክፍት

ይባላል ጥቁርን መግፋት

ገፍቶ ቢመጣ መትፋት

ቢበላ ማስተፋት

እንዳይኖር እንዳይሽር ማኖር በትሩፋት

አስሮ ማስቀመጥ እንዳያዩት

ማሠልጠን ባጫዋችነት

ነጭን ለማዝናናት

አላብሶ ገጽታ የውሸት

ዶላር ጐዝጉዞ ማስተኛት

የጥቁርን ጥበብ ፈላጊነት ለማኮላሸት

እንዲረጋገጥ ዘመናዊ ባርነት፡፡

ስለሆነም፣ በሽታው አይደለም ሥነሕይወታዊ

የሚመደብ ነው ከሥነልቦናዊ፡፡

ስሙ ይባላል መካድ፣ ትልቅ ሕመም

መፈወስ ያለበት ዘመን ሳይጨልም

አበው ያሉት እንዲፈጸም

ለተደበቀ በሽታ መድኃኒቱ አይገኝም፡፡

# ዲ ያ ሎ

ዲያሎ[6]፣ ደሌ[7] ዲያሎ

ዲያሎ፣ ጭሎ[8] ዲያሎ

እንቡጥ ጮርቃው ሎጋው መለሎ

ቀጠፈህ አይደል ዘረኛ በማናለብኝነት ሕግን ተጠልሎ?

ተጠየቅ ዲያሎ

የዋሁ ጅሎ

ማነው የወሰደህ አታሎ?

አንቀልቅሎ

በወዳጅ ተመስሎ

---

[6] በኒውዮርክ ፖሊሶች በ41 ጥይት የተረሸነ የጊኒ ዜጋ

[7] ልጅ፣ የቁልምጫ አጠራር፣ ጉራጌኛ

[8] ልጅ፣ በጉራጌኛ

ምኞትህን አገንፍሎ

ስሜታዊነትህን አቀጣጥሎ

በውሸት ወሬ ደልሎ

ከእናትህ ጉያ ነጥሎ

ከተከበርክበት ቀዬ ፈንቅሎ

ተነገረህ ወይ ዲያሎ፣ ስለጉዳዩ ስታወጋ

እንደምትሆን በዘረኞች አገር

ርብራብ፣ አራተኛ ዜጋ

እንደሆነ ያጥንትህ ፍላጭ የወኅኒ እጉር መውጫው የተዘጋ

ነጻ ተብዬው ወገንህን እንዳሰማሩት ለነጭ አሽከርነት፣ ቁሻሻ ጠረጋ

እንደተሸረበበት ደባ በዕፅ ደንዝዞ፣ እንዳይተጋ

ዋይ ዋይ እንደሚል፣ ውሎ ካደረ ስምሪቱ፣ ማንነቱን ፍለጋ

ወንድሜ ዲያሎ፣ ዳግም ስትመጣ

አደብን ግዛና በአገርህ እርጋ

ሰውነትህ ታውቆ፣ ባንደኛነት ዜጋ

ምናለበት ብትቆረጥም ጥሬ፣ ካልተገኘም ቀጋ

ዲያሎ፣ ሄድክ አሉ ወርቅ ልታፍስ

የነጻነት አየር ልትተነፍስ

በሰው በላው አገር ያምሮትህን

ሀምበርገር፣ ቺዝበርገር ልታጋብስ

ዶላር በቁና ልታፍስ

የድህነትን አድማስ ልትምስ

የሥልጣኔ ካባ ልትለብስ

ከዚያም፣ ወደአገርህ ልትመለስ

ያየኸውን በምድረ ጊኒ ልትነሰንስ

ልብህ ውልቅ እስኪል አጥንትህ እስኪከሰከስ

ያለገደብ ከአድማስ አድማስ

ሰላም ብልጽግና ለሁሉም እንዲዳረስ

ስብዕናን ልታጎለምስ

ለራስህም ጎጆ ልትቀልስ፡፡

አይ ሞኞ፣ ቀረህ ተደፍተህ እንደወጣህ

ክንድህን ሳትንተራስ

አንገትህ ብሎ ቀልበስ

ውሃ ውሃ ብትል ጠብ ላይልህ የሚላስ የሚቀመስ

የቁም ልቅሶ ሳይለቀስ

ገድልህ ሳይወደስ

ሶምሶማ ሳይሰግር የኮረምቱ[9] ፈረስ

አርባህ ሳይደገስ

ምሳ ስታስብ ዘረኛ አደረገህ ቁርስ

የእምባ ጠባቂ አምላክ እባክህን ባርክ የዲያሎን ነፍስ

የግፈኛውን፣ የዘረኛውን፣ አውግዝ፣ ውገር፣ አኮስስ

---

[9] በጉራጌኛ ጎበዝ

ሞጅረው በገሀነም፣ ዕጣው ይሁን የዲያቢሎስ

በቂም በቀል ሳይሆን በዚህኛው ዓለም ፍትህ እንዲነግስ

ምድረ ገነት እንዲቀየስ።

ዲያሎ፣ አንተማ ነበረ ሐሳብህ

ተመልሰህ ወደ ውድ አገርህ

ወዳጅ ከያቅጣጫው ልታሰባስብ

ከሰሜን ከምሥራቅ ከምዕራብ ከደቡብ

አንተን በፍቅር ጨዋታ ሊያጅብ

ሎጋው ሽቦ ብሎ ተሸክሞ ለጫጉላ ቤት ሊያስረክብ

ብር አንባር ሰበርልሽ ለማብሰር ሊጠባበቅ ተጠልሎ በስብሳብ

አጭልጎ ሊያይ ትግል በመደብ

ፍቅረኛህን ክንድ ስታንተራስ

ሁለንተናዋን ስትዳስስ

ክብረንጽህና ስትገስ

አንጀት ስታርስ

ሁለት አንድ መሆኑን ስታረጋገጥ ባዲስ ማቴማቲክስ

ልትባባሉ አንች ትብሽ አንተ ትብስ

ሳትጎርስ ልታጎርስ

ሲወስዳት እንቅልፍ

ትንፋሽዋን ልታነፈንፍ

ፈርተህ በዚያው እንዳትቀር

ሁለንተናህን አስገዝተህ ለፍቅር::

መሆኑን ተረድተህ የሕይወት ምስጢሩ

መቻል ከራስ አልፎ ለሌላ መኖሩ::

ዲያሎ ተመኝተህ ነበር ወልደህ ልትልስ፣

ልታበረክት ምሁር የሳይንስ

አፍሪቃን የሚያገሰግስ

ልትድር፣ ልትደግስ

የልጅ ልጆችህን ልታሰኝ ደስ

በቤትህ ፍጡር ልታርመሰምስ

ዘርህ ፈልቶ ልትንፈላሰስ

ብሞት አይቆጨኝም እስክትል ድረስ

ባዛውንቶች መሀል አዋቂ ኅምቱ ተብለህ

ጋቢ ወይ ቡልኮ ተከናንበህ በኩርሲ ልትኮፈስ

የተራብ ልታከሰክስ

የታረዘ ልታለብስ

ልታተጋ ገበሬ እንዲያርስ

ልታበረታታ ነጋዴ ያለሐሳብ ቆላ ደጋ እንዳሻው እንዲመላለስ

በሐቀኝነትህ ልትወደስ

በዳይ ለተበዳይ ልታስክስ

ግፍ እንዳይነግስ

ደሃ እንዳያለቅስ

ደባ እንዲኮስስ

እውነት እንዲጎለምስ

መሬት የተሸከመችውን ተቆጥታ እንዳታተራምስ

አርገፍግፋ ደጅ እንዳታፈስ

እንዲያውም ባርካ እንድትቀድስ

አቅፋ እንድታጎለምስ

ፍጥረትም ፈጣሪን እንዲያወድስ፡፡

ዲያሎ፣ በመጨረሻም ልትመለስ

እናት አፍሪቃ ከርስ

ሆነህ የነገው ትውልድ ማዳበርያ ቁስ

ሰብና ስብዕና እንዲለመልም፣ እንዳይገረሰስ

የጄኖም ፕሮጀክት ዳር ሳይደርስ

ሳይፈታ የአፈጣጠር ምስጢር

ሳይረጋገጥ አፍሪቃዊ መሆኑ እናት ዘር፡፡

ዲያሎ፣ አይ ተላሴ

ተስፈኛ ባተሌ

ምነው በነገሩህ መመደብክን

በዘረኞች ጎራ አልባሌነትክን።

አደረጉህ አይደል አሻሻጭ የቸርቻሪ

መጠለያ የለሽ ተንከራታች አዝዋሪ

ባላፊ አግዳሚ ዐይነ ግርፋት ተወጋሪ

የሐሩር ቁር መስካሪ

ከጅ ወዳፍ ኗሪ

ፖሊስ ሲመጣብህ ደንባሪ፣ ተሰዋሪ

እንደ ፈጥኖ ደራሽ ተወርዋሪ

ቤተክርስትያን እንደገባች ውሻ ተባራሪ

ተሽለኩላኪ፣ ተቀያያሪ

ብትያዝ ቀባጣሪ

ዲያሎ፣ ኑሮህ ነበር የብጣሪ ብጣሪ

ምን ነበር በክንፉ ወደ አገርህ ቢመልስህ ፈጣሪ

በናት አገርህ ብትበላስ አሹቅ ፍርፋሪ?

ዲያሎ፣ ክደው አስካዱህ መኖርክን

እስክትፈራ ጥላህን።

ዘረኛ ወጣ ዘሩን ሊያጸዳ

ባዳኝ ውሻ እየተረዳ

ገባ ከተደበቅህበት ጓዳ

ዐይንህ ፈጠጠ ሊፈነዳ

የሌለህ ማምለጫ ቀዳዳ

አርከፈከፉብህ የጥይት ናዳ

ቆራርጠው ጣሉህ አስደግፈው ግድግዳ

በጠራራ ፀሐይ ባውላላ በሜዳ።

የግፋቸው ብዛት

በቁም በጣጠሱህ አደረጉህ ወንፊት።

የፈለጉት ከሆነ ማጥልያ

የህሊና ማንጓለያ

የላሸቀውን መለያያ

የጠነባውን መጣያ

ለመድፋት እማቃጠያ

ነው የምንለው ዲያሎ ሆነ ጧፍ

ዘረኝነትን አቅልጦ እሚያንጠፈጥፍ

የተሰዋ ለጥቁሮች እልፍ አዕላፍ

ዝናው የሚናኝ ካጽናፍ አጽናፍ

ቅዱስነቱ በእምቢልታ የሚለፈፍ

ገድሉ በወርቅ ቀለም የሚጻፍ፡፡

ስማኝ ያህጉሬ ሰው

ጉድጓድህ የተማሰው

አፍዝ አደንግዝ ዐይነ ጥላ

በጭንቅላትህ ተደንቅሮ እየተጉላላ

ስተህ መሆንህን እራስህ ለራስህ አባ መላ

መድኃኒት ትፈልጋለህ ታገኘው ይመስል በነጭ ኬላ

እንዳትቀርበው የታጠረ በሾህ አሜኬላ

ዐይንህ እያየ ዲያሎ ተቀርጥፎ ሲበላ

የስጋህ ቅዳጅ የደምህ ቅጅ ያጥንትህ ፍላጭ በጥይት ሲቆላ

ያህጉሬ ሰው አይ ተላላ

የቀረህ ባውላላ

አላወቅህ እንደተከበብክ በጥንብ አንሳ በተኩላ

ልትጣል፣ ልትዘነጠል፣ ልትበላ።

ስማኝ የአፍሪቃ ሶሬሳ

የሞትክ እሬሳ

ምን ትጠብቃለህ? ይብቃ ተነሳ

ክንድህን አንሳ

አግሳ እንዳንበሳ

ዘረኝነትን ተዋጋው ነግ በኔ መሆኑን አትርሳ

ምንድነው መልስህ ግዙፉ ዘረኛ ዘርማንዘርክን በታትኖ ሲበሳሳ

ሲዳረግ ላበሳ

ረቂቁ ሰርጎገብ በደም ዘልቆ በቁም ሲያሳሳ

የሚያጋድም ባልጋ ጠፍሮ እንደንስሳ

እስከሕይወት ፍጻሜ አበሳ ባበሳ

ታይቶ የማይታወቅ የወጣት ትውልድ ግርሰሳ

ባፍሪቃ ላይ የወረደው መዐት አይነሳ አይነሳ።

ያህጉሬ ሰው፣ ምን ትጠብቃለህ ፈዛዜ

የቆምክበት መሬት ሲነጥፍ ያለጊዜ

አርሰህ እንዳትበላ ቅጠል እንዳትለቅም ለያዘህ አባዜ

ዋ! ወድቀህ እንዳትቀር ሳትታደል ለኑዛዜ።

አትርሳ፣ የሕይወት ምስጢሩ

ተፈጥሮ እውስጥህ ለጥፎ ማኖሩ

ዘዴው የጣራ ግድግዳ ወለል ማገር አሠራሩ

አሽክሞሃል በትከሻህ ኮምፒዩተር

ከተሚላ ሶፍትዌር

ኑሮህን አሸንፈህ እንድትኖር፡፡

ታዲያ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ እያለ ለምንድነው ማማረሩ?

የባዕድ እጅ ማየት፣ ጦስ መዞሩ

ወደ ሩቅ ማማተሩ

መሄድ፣ መንጎድ፣ መዳረግ

እናት ዘርን እንደእንክርዳድ ለቆጠሩ?

አፍሪቃውያን ተነሱ፣ ለስራ ተባበሩ

ማንነታችሁን አስመስክሩ

ህልውናችሁን አብስሩ

ጨቋኝን ውገሩ

በበዝባዥ ጉሮሮ አጥንት ሰንቅሩ

ከፋፋይ መንጥሩ

ልጆቻችሁን አስተምሩ

ባንድነት ገመድ ተሳሰሩ

ከዚያም ጉሮ ወሸባዬ አዝምሩ

የዲያሎን ደም ለመበቀል ይሄ ነው ምስጢሩ፡፡

ያለበለዝያ፣ ይሆናል የንጹህ ደም ጩኸት፣ የዘላለም ጸጸት

የሚያንገበግብ ረመጥ የእግር እሳት

የሚያባንን ሌሊት

ህሊና የሚያስት

ጽዋው የሚያንኳኳ የሁሉንም ቤት

ይህን ሰምቶ ተከናንቦ ለተኛ ወዮውለት

አይቀርለትም የሞት ሞት፡፡

ጊዜ ያነሳቸው ዘረኞች

ቢሆኑም የዋናው ዘር ፍልፍሎች

ናቸው የናት ጡት ነካሾች

ይማሩ ይሆናል እውነቱ ሲገለጥ

ያፍሪቃዊ ማንነት ሲረጋገጥ፡፡

ጆሮ ዳባ ልበስ ካሉ

ዘር ለማመንመን በየወንዙ ከተማማሉ

ሊያስወግዱ ከውስጣቸው ዋና ዘር እንዲሁም ድቅሉን ሊያገሉ

በጽዳት ዘመቻ ለያንጓልሉ

ሳያስተውሉት የቆሙበትን መሠረት ነድለው ሊጥሉ

የሰው ልጅ ወዮወለት ጠፍተው ያጠፋሉ።

ተማምነው በባዮኤንጂንየሪንግ በተፈጠረው በዚህ ሰሞን

ሊፈታተኑ ተፈጥሮን

በሚሊዮን ዓመታት ያቀናበረውን

ሊተኩ ፈጣሪን

ዐይናቸው ሲቅበዘበዙ

ሲቀበጣጥሩ ብዙ ብዙ

የሕይወትን ሰበዝ ሊመዙ

እኔ አላማረኝም ይሄ ያጥፍተህ ጥፉ መዘዙ።

የዚህ ዓለም ነገር ተለዋዋጭ

ዘዋሪ ፍርቱና ስትል ረጭ

ኋላ የነበረው ፊት፣ ፊት የነበረው ኋላ

ቁጭ፣ ዐይን ቁልጭ፣ ቁልጭልጭ፡፡

ዘመኑ ሲመጣ

ቀን ሲወጣ

ፈውስ ያገኝና ያፍሪቃውያን ጣጣ ፈንጣጣ

ዘረኛ ይላል ማሩኝ

የሰረቫይቫል ምስጢሩን አስተምሩኝ

ይመሰከራል፣ ምንም ቢበድላት፣ እናት በልጅዋ

መሆን እንደማትችል ጨካኝ፡፡

ያኔ ለሚቀሰቅሰኝ

ወሮታውን እከፍላለሁኝ፡፡

አድርሻዬ፣ ነጭ አምባ

ውሎዬ ከነጫጭባ

አገሬ በድል እስክገባ

የደስታ እንባ ሳነባ

ትውልድ ሳተባ፡፡